[illegible] ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

# መጻሕፍተ ብሉያት

፩ቱ

<u>እሉ እሙንቱ</u>

ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት)

ኦሪት ዘፀአት

❖

አንድምታ ትርጓሜ

አሳታሚ፡- ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

ማውጫ


| | | ገፅ |
|---|---|---|
| 1ኛ | ኦሪት ዘልደት (ዘፍጥረት) | 1-330 |
| 2ኛ | ኦሪት ዘፀአት | 1-252 |


# ኦሪት ዘልደት (ዘፍጥረት)

## መቅድም ፤

ኦሪት ዘልደት ማለት ዜና ዘፍጥ
ረት ማለት ነው፤ የጥጦስን፣
የሐሳዊ መሚሕን፣ የምጽአትን፣
የመንግሥተ ሰማያትን ነገር ትና
ገራለችና ፤ አንድም ቃለ እግዚ
አብሔር ማለት ነው ፣ ከመገዘ
በሎሙ፣ ከመገዘ በሎሙ እያለ
ሠርቷታልና፣ አንድም ወወረደ
ኤር ቅዱስ እንዲል፣ ቃል ቅዱስ
ሲል ነው፣

አንድም ብርሃን ዘተፈነወ ማለት
ነው፤ ኤርምያስ ማለት ብርሃን
ማለት እንደሆነ ፤ አንድም
መጽሔት ማለት ነው፤ መጽ
ሔት (መስተዋት) የዓይንን
ጉድፍ፣ የጥርስን እድፍ ለይቶ
እንዲያሳይ ኦሪትም ጽድቅንና
ኃጢአትን ቄጥራ ቄጥራ ለይታ
ትናገራለችና ፤ አንድም ስምዕ
ማለት ነው፤ ስማዕ እስራኤል
አሐዱ ውእቱ እግዚአብሔር
አምላክከ ብላ አምልኮቱን ትመ
ሰክራለችና (ዘዳ.፮፡፬)፤ አንድም
ሕግ ሥርዓት ማለት ነው ፣
ሕግ ሠርታ ሕገ ይኩንክሙ፣
ሥርዓት ሠርታ ሥርዓተ ይኩ
ንክሙ ትላለችና ፣ ይህችንም
ኦሪት በተራራ ይመስላታል ፣
ከተራራ ላይ የወጣ ሰው አቈል
ቍሎ በተመለከተ ጊዜ የወጣ
ውን የወረደውን ፣ ያለፈውን
ያገደመውን ያያል፤ ኦሪትንም
የተማረ ሰው ዓለም ከተፈጠረ
ጀምሮ እስከ ምጽአት የሚሆነ
ውን ያውቃልና ፣

ጥንተ ነገሩስ እንደምን ነው
ቢሉ፣ ጌታ እስራኤልን ከግብጽ
ካወጣቸው በኋላ ሙሴን ጠርቶ
ሕግ እሠራላችኋለሁና ወደ ደብረ
ሲና ውጣ አለው፣ እሱም ሕዝ
ቡን ለአሮንና ለሖር አስጠብቆ
(ኢትትዋከቱ) ግር ግር አትበሉ፤
ነገርም ያለበት ሰው ቢኖር እነ
ዚህ ይስሟችሁ፤ ካስተማርኋችሁ
ትምህርት፣ ከሠራሁላችሁ ሥር
ዓት አትውጡ ብሎ ኢያሱን
አስከትሎ ወደ ደብረ ሲና
ወጣ፤ ኢያሱን ከእግረ ደብር
ትቶ እሱ ከርእሰ ደብር ወጥ
ቷል፣ ሰባት የብርሃን መጋረጃ
ተጋርዶ ነበር፣ ስድስቱን ገብቶ
ከሰባተኛው ሲደርስ ቆመ፣ ስድ
ስቱን ቀን በስድስቱ ዕለታት
የተፈጠሩ ሃያ ሁለቱን ሥነ
ፍጥረት በልቡናው ሲሥልበት
ሰንብቷል፤ ሠላሳ አራቱን ቀን
ወነበቦ ወነበቦ ያለውን ቃል
ሲነግረው ሰንብቷል፤ አርባ ቀን
ይሆናል፣ ሙሴም ይህን ዓርባ
ውን ቀን ጾሟል፣ ጾመ ሙሴ
፵ዓ መዓልተ ወ፵ዓ ሌሊተ እን
ዲል፣ ኢያሱ አርባ ቀን ሙሉ
ምን ሲመገብ ሰንብቷል? ቢሉ


www.ethiopianorthodox.org

ሙሴን ያጸና መንፈስ ቅዱስ አጽንቶት አርባውን ቀን ጾሟል፡ ወኢያስተ በሲና ጾመ እንዲል፣ ይህንንም በደብረ ሲና የነገረ ውን ጻፈው ብሎት አምስት ክፍል አድርጎ ጽፎታል፡ እሊ ህም አሪት ዘልደት ፣ አሪት ዘፀአት፣ አሪት ዘሌዋውያን፣ አሪት ዘኍልቍ፣ አሪት ዘዳግም ናቸው፣ አምስት አድርጎ መጻፉ ስለምን ነው ቢሉ ፣ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከአምስተኛ ባሕርየ ነፍስ የተፈጠረ ሰው እንዲያመሰግንበት እንዲጠበቅ በት ባወቀ ገንዘብ ፤ አንድም አምስቱ ሕዋሳተ አፍአ፣ አም ስቱ ሕዋሳተ ውስጥ እንዲያመሰ ግኑበት እንዲጠበቁበት ባወቀ ገንዘብ ፤ አንድም ኋላ ጌታ ሰው ሆኖ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር የሚያስተምር ነውና የዚያ ምሳሌ ነው፤ አሪት ዘዳግ ምስ ለአበው የነገረውን ለው ሉድ ለመንገር መልሶ አንብቦ ታል እንጂ አንድ ነው ብሎ አራት ክፍል አድርጎ ጽፎ ታል፣ ስለምን ቢሉ በአራቱ ማዕዝን ያለ ሰው በአራቱ ማዕዝን ምሉዕ የሆነ ጌታን እንዲያመሰግንበት ባወቀ ገን ዘብ ፤ አንድም ሐዋርያት ከነቢያት ያላገኙትን አምሳል መርገፍ አያደርጉም፤ ወንጌል

አራት ክፍል ሆና የምትጻፍ ናትና፣ ለወንጌል አምሳል መር ገፍ ልትሆን፡ ይህስ አይደለም ሐዋርያት በሲኖዶስ፣ ሠለስቱ ምእት በፍትሐ ነገሥት አም ስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ብለው ቈጥረዋል ብሎ ባለፈው ማጽ ናት ነው፣ አሪት ዘኢያሱን፡ አሪት ዘመሳፍንትን፣ አሪት ዘሩትን፣ በየዘመናቸው የነበሩ ነቢያት ካህናት ጽፈውታል፣ ስምንት ይሆናል ፤ ስምንት መሆኑም፣ የስምንቱ ብሔረ አሪት ምግብና ሲፈጸም አማ ናዊት ሕገ ወንጌል እንድት ሠራ ለማጠየቅ ነው ፤ በዚህም በአሪት ዘጠኝ ነገሮች አሉበት፣ ሕግ፣ ስምዕ፣ ትእዛዝ፡ አኰቴተ እግዚአብሔር፡ ነገራተ እግዚአብሔር፣ ተግሣጽ፣ ምዕ ዳን፣ ጥበብ ሥጋዊ፤ ጥበብ መን ፈሳዊ ነው፣ ሕግ መላው ነው፤ ስምዕ፣ ስማዕ እስራኤል ፩ዱ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ ያለው ነው ፤ ትእዛዝ ይኸን ሥሩ፣ ይኸን አትሥሩ የሚለው ነው፣ አኰቴተ እግዚአብሔር የሚለው እለ ሙሴ እለ ዲቦራ እንዳመሰገኑት ምስጋና ያለ ነው፣ ነገራተ እግዚአብሔር የሚለው ወነበቦ ወነበቦ ያለው ነው፣ ተግ ሣጽ፣ ላለፈው እንዲህ ለምን አደረግህ? ብሎ መቅጣት ነው፣



ምዕዳን ለሚመጣው እንዲህ አታድርግ ብሎ መምከር ነው፣ ጥበብ ሥጋዊ፣ እረሱ፣ ቆፍሩ፣ ጻፉ፣ ደጕሱ፣ ቤት ሥሩ፣ አጥር እጠሩ ትላለችና ይህን የመሰለ ሁሉ ነው ፣ ጥበብ መንፈሳዊ፣ በሃይማኖት ጸንታችሁ ጹሙ ጸልዩ ፣ ምግ ባር ትሩፋት ሥሩ ትላለችና፡ ሕግ ስምዕ ያለውን አንድ ወገን አድርጎ ዘጠነኛ ጸሎት ነው፣ ጸሎትስ ጥበብ መንፈሳዊ ካለው ይገባል ብሎ ዘጠነኛ ትንቢት ነው፡ ነቢየ ያነሥእ ለክሙ እግዚአብሔር ዘከማየ ወሎቱ ስምዕዎ፣ (ዘዳ.፲፰:፲፩) ወትከውን ሕይወትከ ስቅልተ ቅድመ አዕይንቲከ ወኢትትአ መና ለሕይወትከ ብላ ተናግራ ለችና ፣ (ዘዳ. ፳፰:፷፮) ፡

ይህም ተጽፎ ሲነበብ፣ ሲተረ ጐም ከነቢያት እስከ ሐዋርያት ደርሷል ፣ ሐዋርያትም ለቀሌ ምንጦስ ሰማንያ አንድ መጽ ሐፍ ቈጥረው ሲሰጡት ከብ ሉያት ስምንት በሐውርተ አሪት ብለው ቈጥረው ሰጥተውታል፣

ስምንቱስ በሐውርተ አሪት ማን ማን ናቸው ቢሉ፤ አሪት ዘል ደት፤ አሪት ዘፀአት፣ አሪት ዘሌዋውያን፤ አሪት ዘኍልቍ፣ አሪት ዘዳግም፣ አሪት ዘኢያሱ፣ አሪት ዘመሳፍንት፣ አሪት ዘሩት ናቸው ፣

አሪት ዘልደት አለ፤ ዜና ዘፍጥ ረት ሲል ነው፣ መኑ ይወልዶ ለሕንባባተ ነጠብጣብ ወሶበ ተወለድኩ ነሣእኩ ነፍሰ ከመ ኵሉ እንዲል ኢዮ. ፴፬፣፳፰፡ ጥበ. ፯፣፫ ፡

ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት ቈጥራ ቈጥራ ትናገራለችና፡ አንድም ዘልደት እንዳለ ይሆ ናል፣ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዳዊት ድረስ እገሌ እገሌን ወለደ እያለች ልደተ አበውን ትናገ ራለችና ፣

ይኸውም ለከንቱ አልተጻፈም፣ እኛ ልንመከርበት ልንገሠጽበት ነው እንጂ፣ ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጽ ዚአነ ተጽሕፈ ከመ በትዕግሥትነ ወበተወክሎተ መጻ ሕፍት ንርከብ ተስፋነ እንዲል፣ ሮሜ. ፲፭:፬ ፤

እስከዚህ አርእስት ነው፣ ሠለ ስቱ ምእት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት እንደሰጡ፤ ይህንንም አርእስት ሰጥተዋል፣ እሱ ግን፣ ነገሩን፣ በቀዳሚ ገብረ እግዚ አብሔር ሰማየ ወምድረ ብሎ ያመጣዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፩

፩፡ በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ፤

በቀዳማዊ ቃሉ፣ በቀዳማዊ ሥልጣኑ ፤ አንድም በቀዳማዊ ልጁ በመጀመሪያ መፍጠሩ ፤ አንድም በመጀመሪያ ዕለት በመጀመሪያ ሰዓት ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፣ የፈጠረበትም ወንጌላዊው ዮሐንስ፣ ወርኁ መጋቢት ፣ ቀኍጥሩ ፳፱ ፣ ዕለቱ ዕለተ እሑድ፣ ሰዓቱ መጀመሪያ ነው ፤ (ሐተታ) እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጥር አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው ፤ ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፍለው፣ እንደዛሬ ሁሉ በአንድነት፣ በሦስትነት ሲሠለስ፣ ሲቀደስ ይኖር ነበር፤ ፍጥረት ሳይኖር ማን ያመሰግነው ነበር ? ቢሉ፣ ምስጋና የባሕርዩ ስለሆነ ፤ አንድም ምስጉን ባሕርዩ በቅድምና ስለነበረ፣ እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተጸርዐ አላ ምሉእ ውእቱ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል፤ ቅዳ.ዘ፫፻ት ፩፣፴፫_፴፬፣ ከዚህ በኋላ፣ ክብሩ በባሕርዩ ብቻ እንደቀረ ዓውቆ ይኸን ዓለም ልፍጠር ብሎ አሰበ ፣ አስቦም አልቀረ፣ ሰውንና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ፣ የቀሩትን ፍጥረታት ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጠረ፤ ይኸንንም ስለ አምስት ነገር ፈጥሮታል፣ ከሀሊነቱን፣ ባዕልነቱን፣ ርኅብነቱን፣ ዘኢይትረከብነቱን፣ ራትዕነቱን ለመግለጥ ፣ ከሀሊነቱ ይህን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ አምጥቶ መፍጠሩ ፣ ኋላም እምኀበ ቦ ኀበ አልቦ ማሳለፉ ፣ ባዕልነቱ ዛሬ ባለጸጋ ብዙ ሰው ጠርቶ ሲያበላ ሲያጠጣ፣ ጠጅ ላለው ጠጅ፣ ሥጋ ላለው ሥጋ የሰጠ እንደሆነ ባለጸግነቱ ይታወቃል፣ ጌታም ግዙፋን ፍጥረት አራዊትን፣ እንስሳትን፣ ሰውን ፈጥሮ ግዙፍ ምግብ ዘርእን፣ ተክልን፣ መመገቡ ፣ ረቂቃን ፍጥረታት መላእክትን ነፍሳትን ፈጥሮ መንፈሳዊ ምግብ ቅዳሴን መመገቡ፤ ባዕልነቱን ይገልጣል፣ ርኅብነቱ በሥነ ፍጥረት ይመረመራል፣ ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐወቅ በፍጥረቱ እንዲል፤ (ሮሜ.፩:፳) ዘኢይትረከብነቱ፣ ባሕርዩ አይመረመርምና፣ ራትዕነቱ ዲያብሎስ ቢክድ በንስሐ እንዳይመለስ ዓውቆ ቦታውን ለአዳም ሰጥቶበታል፣ አዳም ቢበድል በንስሐ እንዲመለስ ዓውቆ



ቦታውን መላእክትን አስጠብቆለታል ፣ ወአዘዞሙ ለኪሩቤል ወለሱራፌል ዘውስተ እደዊሆሙ ሰይፈ እሳት እንተ ትትመየየጥ ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ ዕፀ ሕይወት ብሎ እንዲያመጣው (ዘፍ.፫:፳፬) ፣ ይህ ራትዕነቱን ይገልጣል፣ በዚህም ቀን ሰባቱን ፍጥረታት ፈጥሮአል ፤ ወገብረ ፯ተ ዘመደ እንዲል (ኩፋሌ.፪:፰)፣ ሰባቱስ ፍጥረታት ማን ማን ናቸው ቢሉ፣ ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃ፣ መሬት፣ ጽልመት፣ መላእክት፣ ብሩህ ሰማይ ናቸው፣ እንዲህ ከሆነ የሰማይንና የምድርን ተፈጥሮ ብቻ ተናግሮ የቀረውን ስለምን ያልተናገረ ቢሉ፣ በሰማይና በምድር ያሉ ከሆነ ብሎ፤ አንድም ሰሎሞን እሳተ ኀዩል፣ ነፋስ ኀዩል፣ አው ማየ ኀዩል፣ ይላል፣ እነዚህ ኃያላን ናቸው ፣ አንሥቷቸው ቢሆን መናፍቃን እነዚህ ኃይል ሁነው ፈጠሩ ባሉት ነበርና ከመናፍቃን ምክንያት ለማጥፋት፤ አንድም ሁሉንም አሁን ወደፊት ያመጣቸዋል፣ የጨለማን ተፈጥሮ ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ ብሎ፤ የነፋስን ተፈጥሮ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ ብሎ ፣ የመላእክትን ተፈጥሮ ወአዘዞሙ ለኪሩቤል ወለሱራፌል ብሎ ያመጣዋል፣ (ም. ፫:፳፬) ፤

በዚህም ሰዓት አራቱን ባሕርያት፣ ነፋስን፣ እሳትን፤ ውሀን፤ መሬትን፤ ፈጥሮአል፣ ስለምን ከፍ ብሎ ፰:፲ ዝቅ ብሎ ፪ት፣ ፫ት ያልፈጠረ አራት አድርጎ የፈጠረ ቢሉ፤ በኔም በባሕርዩ አራት ነገር አለ ሲል፣ ይኸውም ኃያልነት፣ ፈታሒነት፣ መንጽሒነት፣ ባዕልነት ነው፣ እሳት ኃያል ነው፣ ባሕር ገደል ካልከለከለው ሁሉን ያቃጥላል፤ ጌታም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ቢያጠፋ ይቻለዋልና ኃያል ነኝ ሲል እሳትን ፈጠረ፣ እግዚአብሔር ኃያል ወመስተ ዓግሥ እንዲል፣ (መዝ.፯:፲፩)፣ ነፋስ ፍሬውን ከገለባ፣ ገለባውን ከፍሬ ይለያል ፣ ጌታም ጻድቃንን ከኃጥአን፤ ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያልና ፈታሒ ነኝ ሲል ነፋስን ፈጠረ፣ ውሀ መንጽሒ ነው ሁሉን ያነጻል፤ ጌታም መንጽሔ ሥጋ ወነፍስ ነውና መንጽሒ ነኝ ሲል ውሀን ፈጠረ፣ መሬት ባዕል ነው፣ ብዕል ሁሉ ይገኝበታል፤ ወበረከተ ምድር እንተ ባቲ ኮሉ ብሎ እንዲያመጣው፣ ጌታም ሁሉ የተገኘ ከሱ ነውና ባዕል ነኝ ሲል መሬትን ፈጠረ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ምድርሰ ሀለወት ዕሩቃ ፣

ምድርኒ ሲል ነው፡ ምድርም ከአዝርዕት ከአትክልት ከሰው ባዶዋን ነበረች፣ አንድም እምትካት ይላል፣ ከጥንት ጀምሮ፡ አንድም ከንቱታ ብድውታ ይላል፣ ከአዝርእት ከአትክልት ከንቱ ሆና ምድረ በዳ ነበረች፡ አንድም ሀለወት ወኢሀለወት ይላል፣ ሀለወት በልበ እግዚአብሔር ፡ ወኢሀለወት በተፈጥሮ በመታየት አልነበረችም ፡ አንድም ሀለወት ወኢታስተርኢ ይላል ፣ ሀለወት በተፈጥሮ ፣ ወኢታስተርኢ በውሀ ተሸፍና አትታይም ነበር ፡

ወኢኮነት ድሉተ ፣

በአዝርእት በአትክልት አልተዘጋጀችም ነበር ፡

ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ ፣

የጨለማን ተፈጥሮ አመጣ ፡ ጨለማው በውሀው ላይ ሰፍሮ ነበር ፡

ወመንፈስ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ ፣

የነፋስን ተፈጥሮ አመጣ ይጼልል በሚለው፣ ይነፍሕ ይላል፣ አንድ ነው ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውሀው ላይ ይሰፍፍ ነበር፣ (ሐተታ) መንፈስ እግዚአብሔር ያለውንም ፣ መሻፍቃን የሚባል ሊቅ ለማየት ሕይወት የሚሆናቸው ፣ ማየትን የሚያጠራቸው ነፋስ ነው ብሎ ተርጉሞታል፡ ትርጓሜ ኦሪትም በጥምቀት የሚሰጥ የሀብተ መንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው ብሎአል፡ ሳዊሮስም ከእመቤታችን ደመ ድንግልናን የከፈለ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው ብሏል ፣ (ሃይ:አ: ሳዊ:ዘአንጾኪያ፣ ክፍል ፱) ፡

፫፡ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ወኮነ ብርሃን ፣

እግዚአብሔር ብርሃን ይፈጠር አለ ፡ ብርሃንም ተፈጠረ ፡

፬፡ ወርእዮ እግዚአብሔር ለብርሃን ከመ ሠናይ ውእቱ ፣

እግዚአብሔር ብርሃንን የበቃ ፍጥረት እንደሆነ ዓውቆ ፈጠረ፡ ከመ ሠናይ ባለው ከመ ጠብ ይላል፡ ከመ ሠናይ ማለት ነው፡ ጠቢት ማለት ሠናይ ማለት እንደሆነ ፣

ወፈለጠ እግዚአብሔር ማዕከለ ብርሃን ወማዕከለ ጽልመት ፣

እግዚአብሔር በብርሃንና በጨለማ መካከል ድንበር ለየ ፣ (ታሪክ) ለይኩን ብርሃን ያለበት ምክንያት ምንድን ነው? ቢሉ፡ ጌታ መላእክትን ሕያዋን፣ ለባውያን፣ ነባብያን አድርጎ ፈጥሮአቸው ነበርና ምንት ንሕነ እም አይቴ መጻእነ ወመኑ ፈጠረነ



ወሚመ በበርእስነኑ ተፈጠርነ ተባባሉ ፣ ዲያብሎስን ከሁሉ በላይ አድርጎ ፈጥሮት ነበርና ከወደላይ እኔ ፈጠርሁ የሚል ድምጽ አጣ፡ ከወደታችም እንዲህ ሲሉ ሰማ፣ እኔ ፈጠርኹ ልበል ብሎ አሰበ ፣ አስቦም አልቀረ አነ ፈጣሬሆሙ ለእሉ ፍጡራን አለ፣ ያንጊዜ የእሱ ወገኖች ከሦስት ተከፍለዋል፣ የተጠራጠሩ አሉ፣ አዎን ፈጠርከን ያሉ አሉ ፣ ምን አንተ ትፈጥረን እኛ ፈጠርንኽ እንጂ ያሉም አሉ ፣ የተጠራጠሩት በአየር ቀርተዋል፣ አዎን ፈጠርከን ያሉት ወደዚህ ዓለም ወርደዋል ፣ ምን አንተ ትፈጥረን እኛ ፈጠርንህ እንጂ ያሉት አብረው ወርደዋል፣ ያንጊዜ በመላእክት ሽብር ጸናባቸው፣ ወአህድአሙ መልአከ ሰላም በቃሉ እንዲል፣ ቅዱስ ገብርኤል ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ ብሎ አጽንቷቸዋል፣ ዛሬ ድል የተነሣን ጦር በጎ አርበኛ ባለህ ጽና ብሎ እንዲያጸናው፣ ለብሥራትም ያበቃው ይህ ነው ፡ ወበእንተዝ ደለዎ ከመ ይጹር ዜናሃ ለማርያም እንዲል ፡

ከዚህ በኋላ ጨርሰው ሳይክዱ ለይኩን ብርሃን ብሎ ብርሃኑን ፈጠረላቸው ፣ ይህ ዕውቀት ሆኖላቸው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አመስግነዋል፡ (ሐተታ) ስለምን ሰባቱን በአርምሞ ብርሃንን በነቢብ ፈጠረ ቢሉ፣ በአርምሞም በነቢብም መፍጠር ይቻለኛል ሲል መናፍቃን በአርምሞ እንጂ በነቢብ ፡ በነቢብ እንጂ በአርምሞ መፍጠር አይቻለውም ባሉ ነበርና ምክንያት ለማጥፋት ፡ አንድም ቀድሞ ሰማዕያን መላእክት አልነበሩምና ሰባቱን በአርምሞ ፈጠረ፣ አሁን ግን ሰማዕያን መላእክት አሉና ብርሃንን በነቢብ ፈጠረ ፣ ይህም ቢሆን የልቡና ነቢብ ነው ፡ ወዘይነብብ ጽድቀ በልቡ እንዲል፣ መዝ.፲፬:፪ ፣ ያውስ ቢሆን በፊት ጨለማን ፈጥሮ ኋላ ብርሃንን ስለምን ፈጠረ ቢሉ ፡ በፊት ብርሃንን ፈጥሮ በኋላ ጨለማን ቢፈጥር ሠናይ አምላክ ፣ ብርሃንን ቢፈጥር እኩይ አምላክ ጨለማን ፈጠረ ባሉ ነበርና ፣ ከመናፍቃን ምክንያት ለማጥፋት፣ ይኸማ በፊት ብርሃንን ፈጥሮ በኋላ ጨለማን ቢፈጥር ሠናይ አምላክ፣ ብርሃንን ቢፈጥር እኩይ አምላክ ጨለማን ፈጠረ ቢሉ ይሆን የለምን ብሎ፣ የሚያልፈውን በፊት የሚያልፈውን በኋላ መፍ

www.ethiopianorthodox.org

ጠር፤ ክፉዉን በፊት በጎውን በኋላ ማምጣት ለጌታ ልማዱ ነው፣ በፊት የሚያልፈውን ይህን ዓለም አወርሶ፣ በኋላ የማያልፈውን መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርሰን፤ በፊት የምታልፍ ኦሪትን ሠርቶ በኋላ የማታልፈውን ወንጌልን እንደሠራልን፣ በፊት መከራውን አምጥቶ በኋላ ጸጋውን ክብሩን እንዲሰጠን፣ እንደዚህም በፊት ጨለማን ፈጥሮ በኋላ ብርሃንን ፈጠረ ፤

ሌሎች ሰዎች ግን ይህንን ይዘው በዚህ ቀን ስምንት ፍጥረታትን ፈጠረ ይላሉ፤ ነገር ግን በኩፋሌ ወገብረ እግዚአብሔር ሰብዓተ ዘመደ ይላልና በዚህ ይረታሉ፤ ይህም ብርሃኑ ከሰባቱ ልዩ አይደለም፣ የተዳፈነን እሳት በጭድ በገለባ እንዲገልጡ በእሳት ባሕርይ ተሠውሮ የነበረውን መግለጥ ነው፣ ይህንስ ዓለም በምን ቋንቋ ፈጥሮታል ቢሉ በሶርያ ቋንቋ ፈጥሮታል ፣ በሶርያ ቋንቋ እግዚአብሔር ማለት ሀያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት የፈጠረ አምላክ ማለት ነው ፤ አንድም በዕብራይስጥ ቋንቋ ፈጥሮታል ፤ ይኸም ሊታወቅ አብርሃምን ወተናገሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም በልሳነ ፍጥረቱ ይለዋል ፤

፭፤ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለብርሃን መዓልተ ፣

እግዚአብሔር ብርሃንን መዓልት አለው፣ ሥራሕ ማለት ነው፣ ሰው ሲጥር ሲግር የሚውልበት ስለሆነ ፤

ወለጽልመት ሌሊተ ፣

ጨለማውንም ሌሊት አለው፣ ሰው ቀን ሲጥር ሲግር ውሎ የሚያርፍበት ስለሆነ ፤

ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፣

ጨለማ ሁኖ አድሮ ነጋ ፤

ወኮነ መዓልተ ፣

ብርሃንም ሆነ ፣ ያንጊዜ ኑሮ አይደለም በዛሬው ስለታወቀ ነው እንጂ ፤ አንድም ነቢዩ ሙሴ ባወቀ ተናግሮታል ፤

ወኮነ አሐደ ዕለተ ፣

ሌሊትና መዓልት አንድ ዕለት ሆነ፣ ዕለት ብሂል ዘያስተዛውጎሙ ለመዓልት ወለሌሊት እንዲል፣ (የሐ፡አፈ፡ወ፡ተግሣጽ)፤

፮፤ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ ፣

እሑድ ማታ ለሰኞ አጥቢያ እግዚአብሔር በውሀ መካከል ጠፈር ይፈጠር አለ ፣

ከመ ይፍልጥ ማዕከለ ማይ ወማይ፣

በውቅያኖስና በሐኖስ መካከል ሆኖ ደንበር ይለይ ዘንድ ፤



ወኮነ ከማሁ ፣

እንዳለውም ሆነ ፣ ማለት ተፈጠረ ፤ (ሐተታ) ጠፈር ማለት ኃይል ጽንዕ ማለት ነው፣ ለሐኖስ ኃይል ጽንዕ ነውና ፤ አንድም ቤት ማለት ነው ፤ በውስጡ ሰው አራዊት እንስሳት ይኖሩበታልና፤

፯፤ ወገብረ እግዚአብሔር ጠፈረ ወፈለጠ ማዕከለ ማይ ዘታሕተ ጠፈር ወማዕከለ ማይ ዘመልዕልተ ጠፈር፣

ወኮነ ከማሁ ያለውን ወገብረ እግዚአብሔር ብሎ አመጣው፣ በሐኖስና በውቅያኖስ መካከል ድንበር ለየ፣ ይኸንንም ወረሰዮ በአምሳለ ቀቀብ ይላል፤ በዚህ ሌሊት ውቅያኖስና ሐኖስ እንደ አሮት ፣ ጠፈር እንደ ሰይፍ ሆነው ተገኝተዋል ፤

፰፤ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለውእቱ ጠፈር ሰማየ ፣

እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ አለው ፣ ሥዕለ ማይ ማለት ነው፣ ይኸማ ሰባቱን ሰማያት ሰማይ ይላቸዋል፣ ሥዕለ ማይ ማለት ነውን ? ብሎ ልዑል ማለት ነው ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ፣

የበቃ ፍጥረት እንደሆነ አውቆ ፈጠረው ፤

ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፣

ጨለማ ሆነ አድሮ ነጋ ፤

ወኮነ ክልኤተ ዕለተ ፣

ሁለት ዕለት ሆነ፤ ዕለት ሁለት ፍጥረት ስምንት ሆነ፤ (ሐተታ) ጠፈርንም ወረሰዮ በአምሳለ አዝረቅ ይላል፤ በሰማያዊ ቀለም አምሳል ፈጥሮታል፤ እጅግም ቢበራ ዓይን ይበዘብዝ ነበርና፤ እጅግም ጨለማ ቢሆን ለዓይን ይከብድ ነበርና፤ ይህንንም የዓይን ማረፊያ ሊሆን ፈጥሮታል፤ ጠፈር ባይኖር የሰው የእንስሳ የአራዊት ዓይን ሁሉ ማረፊያ አጥቶ ወልቆ ወልቆ በወደቀ ነበርና ፤

፱፤ ወይቤ እግዚአብሔር ለይትጋባእ ማይ ዘመትሕተ ሰማይ ውስተ አሐዱ መካን ወያስተርኢ የብስ ፣

ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥቢያ ከጠፈር በታች በዚህ ዓለም ያለ ውሀ በአንድ ቦታ ተወስኖ የብሱ ይገለጥ አለ፤

ወኮነ ከማሁ ፣

እንዳዘዘው ሆነ ማለት፣ ተገለጠ፤ አንድም የብሰ ይላል ፣ የብስ ሆኖ ተገለጠ ፤

ወተጋብአ ማይ ውስተ ምዕላዲሁ ወአስተርአየ የብስ ፣

ውሀው በሚወሰንበት ቦታ ተወሰነ ፣ የብሱም ተገለጠ፤ የብሰ ቢል የብስ ሆኖ ተገለጠ ፤ (ሐተታ) ከዚህ እስከ ብሩህ ሰማይ ደርሶ የነበረውን ውሀ

www.ethiopianorthodox.org

ከሦስት ክፍሎ ሚሰውን አርግቶ ጠፈር አድርጎታል፤ ሚሰውም ከጠፈር በላይ ያለው ብጽብጽ ውሀ ነው፤ ስሙን ሐኖስ ብሎ ታል፤ ሚሰውን ይህንን ዓለም ከሰባት ክፍሎ ሰባተኛውን ዕጣ አጕድጕዶ በዚያ ወስኖታል፤ ስሙን ውቅያኖስ ብሎታል፤

፲፡ ወሰመዮ እግዚአብሔር ለየብስ ምድረ ፤

እግዚአብሔር የብሱን ምድር አለው፤ ማኅደር ማለት ነው፤

ወለምዕላዲሁ ለማይ ሰመዮ ባሕረ፤

ውሀው የተወሰነበትንም ቦታ ባሕር አለው፤ ጕድጓድ ማለት ነው ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ፤

እግዚአብሔር ማዘጋጀቱን የበቃ እንደሆነ አውቆ አዘጋጀ ፤

፲፩፡ ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቊል ምድር ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ወበበአርአያሁ ፤

ከዚህም ምድርን ለምለም ገብት መስላ ቢያያት፤ አንድም ዘጠኝ ወር በጋ ገበሬ ሲያንቀረቅባት እንደ ባጀች እርሻ ሆና ቢያያት፤ ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥቢያ እግዚአብሔር በየመልኩ፤ በየወገኑ፤ በየዘሩ የሚዘራውን ዘር ተክል ምድር ታስገኝ አለ ፤

ወዕፀ ዘይፈሪ ፤

የሚያፈራውን ዘር ተክል ታስገኝ አለ ፤

ወይገብር ፍሬሁ ዘእምውስቴቱ ዘርእ ዘይወፅእ ፤ ወዘይከውን በበዘመዱ ዲበ ምድር ፤

ዘእምኔሁ ሲል ነው፤ ይገብርና ዘይወፅእ አንድ ወገን ፤ ዘሩ ከሱ የሚገኘውን ፍሬ የሚያፈራውን ዘር ተክል ታስገኝ አለ፤ ጤፍ ዘርቶ ጤፍ፤ ስንዴ ዘርቶ ስንዴ ማለት ነው፤ ዘእምውስቴቱ ቢል ከውስጡ ዘሩ የሚገኝ እንደ ዱባ፤ እንደ ቅል ያለውን፤ ዘእምታሕቱ ቢል እንደ ሽንኩርት ፤ እንደ ድንች ያለውን፤ ዘእምገቦሁ ቢል እንደ ባቄላ፤ እንደ ባርማሽላ (በቆሎ) ያለውን፤ ዘእምላዕሉ ቢል እንደ ገብስ ፤ እንደ ማሽላ ያለውን ታስገኝ አለ ፤

ወኮነ ከማሁ ፤

እንዳለው ሆነ ማለት አስገኘች፤

፲፪፡ ወአውፅአት ምድር ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ወበበአርአያሁ ፤

ወኮነ ከማሁ ያለውን አውፅአት ምድር ብሎ አመጣው፤ ምድርም በየመልኩ በየወገኑ በየዘሩ የሚዘራውን ዘር ተክል አስገኘች ፤



፲፫፡ ወዕፀ ዘይፈሪ ወዘይገብር ፍሬሁ ዘእምውስቴቱ ዘርእ ዘይወፅእ በበዘመዱ መልዕልተ ምድር ፤

አውፅአት ምድር መልዕልተ ምድር ብለህ ግጠም፤ ምድር ዘሩ ከሱ የሚገኘውን ፍሬ የሚያፈራውን ዘር ተክል በየወገኑ በዚህ ዓለም አስገኘች ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ፤

እግዚአብሔርም የበቃ ፍጥረት እንደሆነ አውቆ ፈጠረ፤ (ታሪክ) በዚህ ዕለት ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥቢያ አራት ፍጥረታትን ፈጥሮአል፤ ወገብረ እግዚአብሔር አርባዕተ ዘመደ እንዲል፤ ኩፋሌ ምዕ. ፫:፩ ምን ምን ፈጥሮአል ቢሉ በጥፍር የሚላጡ እነሎሚን እነትርንጎን እነ ሙዝን አንድ ወገን አድርጎ ፤ በማጭድ የሚታጨዱትን አዝርእት አትክልት አንድ ወገን አድርጎ ፤ በምሳር የሚቈረጡትን እነዋንዛን እነዝግባን አንድ ወገን አድርጎ ፤ አራተኛ ዕፀወ ገነትን ይላሉ ፤ ዕፀወ ገነትን ስለምን አራተኛ አድርጎ ቈጠራቸው ቢሉ ብርሃን አይለያቸውምና፤ መዓዛቸውም ከሩቅ ይሸታልና፤ ለቅመዋቸው ሲመለሱ ፍሬ ተክተው ይገኛሉና፤ የእነዚህም መገኛቸው ከምድር ስለሆነ ተፈጥሮአቸው ከአራቱ ባሕርያት ነው ፤ ይህም በዚህ ይታወቃል፤ ከነፋስ እንደ ፈጠራቸው ይታወቅ ዘንድ በነፋስ ያብባሉ ያፈራሉ፤ እስመ ነፋስ ያገዝፎ ለፍሬ እንዲል ፤ ወኃይለ በቀላትስ በሁከተ ነፋስ ይነውኅ ወይማስን እንዲል ፤ (መቅ. ወንጌል) ፤ ከእሳትም እንደ ፈጠራቸው ይታወቅ ዘንድ እንደ እስታ፤ እንደ ዶግ ያለውን ሲሰብቁት እሳት ይወጣዋል፤ ከውሀውም እንደ ፈጠራቸው ይታወቅ ዘንድ እንደ ወርካ እንደ ቀልቋል እንደ ቅንጭብ ያለውን ሲወጉት ደም ይወጣዋል፤ ከምድርም እንደ ፈጠራቸው ይታወቅ ዘንድ ቈርጠው ቢጥሏቸው ፈርሰው በስብሰው አፈር ይሆናሉ ፤ ለእነዚህም ሁለት ሁለት ባሕርይ አላቸው፤ መሬት ርጡብ ነው ይቡስ ነው፤ ውሀ ቈሪር ነው ርጡብ ነው፤ እሳት ውዑይ ነው ይቡስ ነው፤ ነፋስ ውዑይ ነው ቈሪር ነው፤ እለዚህም መስተፃርራን ናቸው፤ በመካከላቸው አንድ አንድ አስታራቂ አኑሮአል ፤ መሬትና ነፋስ መስተፃርራን ናቸው፤ ውሀ በመካከላቸው ሆኖ ያስታርቃል፤ በርጡብነቱ ከመሬት፤ በቈሪርነቱ ከነፋስ ሆኖ ያስታርቃቸዋል፤ እሳትና ውሀ መስተፃርራን ናቸው፤ ነፋስ በመካከላቸው ሆኖ ያስታርቃቸዋል፤ በቈሪ

www.ethiopianorthodox.org

ርነቱ ከውሀ፣ በውዑይነቱ ከእሳት ሆኖ ያስታርቃቸዋል ፣ እነዚህም አራቱ ባሕርያት አንዱን ዘመን ከአራት አድርገው ተካፍለው ይመግቡታል፣ ከመጋቢት ፳፯ እስከ ሰኔ ፳፭ የመሬት ባሕርይ ይመግባል፤ ወርኃ መሬት ነው፣ ዘመኑም ጸደይ ይባላል ፣ ይህም በዚህ ይታወቃል፣ መሬት ቢቈፍሩ፣ ደንጊያ ቢፈነቅሉ ቡቃያ ያስገኛል፣ ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ የውሀ ባሕርይ ይመግባል፤ ወርኃ ማይ ነው፤ ዘመኑም ክረምት ይባላል፣ ይህም በዚህ ይታወቃል ፣ ዝናማት ይበዛሉ ፣ አንቅዕት ይነቃሉ፣ አዝርእት አትክልት ይበቅላሉ፤

ከመስከረም ፳፮ እስከ ታኅሣሥ ፳፭ የነፋስ ባሕርይ ይመግባል፤ ይህንንም ወርኃ መፀው ይለዋል፤ በዚህ ይታወቃል ፤ አዝርእት አትክልት ያብባሉ ያፈራሉ ፣ እስመ ነፋስ ያገዝፎ ለፍሬ ወኃይለ በቀኁላትሰ በሁከተ ነፋስ ይነውኅ ወይማስን እንዲል ፣

ከታኅሣሥ ፳፮ እስከ መጋቢት ፳፭ የእሳት ባሕርይ ይመግባል፤ ወርኀ እሳት ነው ዘመኑም ሐጋይ ይባላል ፤ ይህም በዚህ ይታወቃል፤ አዝርእት አትክልት ይደርቃሉ፣ ዋዕየ ፀሐይ ይጸናል፤

እለዚህም አራቱ ባሕርያት በዚህ ዓለም ምሉአን ናቸው፤ ከዚህም በታች አሉ፣ እለዚህም ሁለቱ ክቡዳን፤ ሁለቱ ቀሊላን ናቸው፤ ክቡዳኑ መሬት፣ ውሀ፤ ቀሊላኑ እሳት፣ ነፋስ፣ ናቸው፤ ክቡዳኑ መሬት፣ ውሀ፣ ወደታች እንውረድ ሲሉ፤ ቀሊላኑ እሳት፣ ነፋስ፣ ይሸከሟቸዋል፤ ቀሊላኑ እሳት፣ ነፋስ፣ ወደላይ እንውጣ ሲሉ፣ ክቡዳኑ መሬት፣ ውሀ፣ ያስቀርዋቸዋል ፤

እነዚህንስ እንደምን አድርጎ አኑሮአቸዋል ቢሉ፣ ከዚህ ዓለም እስከ ጠፈር ፤ ከጠፈር እስከ ምድር ፣ እያራራቀ አኑሮአቸዋል፤ እንደዚህስ ባይሆን ነፋሱ እሳቱን አነሣሥቶት ፣ እሳቱ ውሀውን አንፍሮት ፤ ውሀው መሬቱን አግሎት፣ አትክልት አዝርእት አርረው ተንተክትከው በቀሩ ነበር፤ እንስሳት፣ አራዊት ሰዎች በውሀ ጥም አርረው ከስለው ባለቁ ነበር፤ አንድም እንደ እንጀራ አነባብሮ በከሃሊነቱ አስማምቶ አኑሮአቸዋል፤

የክረምት ውሀ ይሞቃል፣ የበጋ ውሀ ይቀዘቅዛል፣ ስለምን ነው ቢሉ ክረምት ሲመጣ በጋ ሲወጣ ዋዕይ ወደ ውስጥ ገብቶ ይመግባል፤ ክረምት ሲወጣ በጋ ሲመጣ ቍር ወደ ውስጥ ገብቶ



ይመግባል፤ ስለዚህ ነው፣ እነዚህንም ሰብል ዛሬ ለመሰብሰብ እንዲመቹ አድርጓቸዋል፤ እኩሌታውን ደረቅ ፤ እኩሌታውን ኅመር ፤ እኩሌታውን ዝርዝር ፤ እኩሌታውን ቡቃያ አድርጎታል፤

ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፣

ጨለማ ሁኖ አድሮ ነጋ ፤

ወኮነ ሠለስተ ዕለተ ፣

ሦስት ቀን ሆነ፤ (ሐተታ) ዕለት ሦስት፤ ፍጥረት ዐሥራ ሁለት ሆነ ፤

## ገባኤ

፲፬፤ ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩኑ ብርሃናት ውስተ ጠፈረ ሰማይ ፣

ጠፈርና ሰማይ አንድ ወገን ማክሰኞ ማታ ለረቡዕ አጥቢያ እግዚአብሔር በሰማይ፣ ፀሐይ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ይፈጠሩ አለ፤ አንድም ሰማይ በሚባል ጠፈር፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ ከዋክብት ይፈጠሩ አለ ፤

ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር ፣

በዚህ ዓለም ያበሩ ዘንድ ፤

ወይፍልጡ ማዕከለ መዓልት ወማዕከለ ሌሊት ፣

በመዓልትና በሌሊት መካከል ድንበር ሁነው ይለዩ ዘንድ ፤

ወይኩኑ ለትእምርታት ፣

ለመዓልትና ለሌሊት መለያ ምልክት ይሆኑ ዘንድ፤ አንድም ለሰው ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ፤ (ሐተታ) ፀሐይ መውጣቱ የመወለዳችን፤ በጠፈር ማብራቱ በዚህ ዓለም የመኖራችን፤ መግባቱ፣ የመሞታችን፤ ተመልሶ መውጣቱ የመነሣታችን ምሳሌ ነውና፤

ወለአዝማናት ፣

አራት ክፍለ ዘመን ብሎ ለመቍጠር ፤

ወለመዋዕላት ፣

ሰባት ቀን ብሎ ለመቍጠር፤

ወለዓመታት ፣

ሦስት መቶ ስድሳ አምስቱን ቀን ዓመት ብሎ ለመቍጠር ምልክት ይሆኑ ዘንድ ፀሐይንና ጨረቃን፣ ከዋክብትን ፈጠረ፤

፲፭፤ ወይኩኑ ለአብርሆ በጠፈረ ሰማይ ከመ ያብርሁ ዲበ ምድር ፣

ሰማይ በሚባል ጠፈር ሁነው በዚህ ዓለም ያበሩ ዘንድ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት ይፈጠሩ አለ፤

ወኮነ ከማሁ ፣

እንዳለው ሆነ ማለት፤ ተፈጠሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኮነ አርባዕተ ዕለተ ፤

አራት ቀን ሆነ፤ (ሐተታ) ዕለት
አራት ፤ ፍጥረት ዐሥራ አም
ስት ሆነ ፤

፳፤ ወይቤ እግዚአብሔር ለታውዕእ
ማይ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይ
ወት ፤

ረቡዕ ማታ ለኃሙስ አጥቢያ፤
ደመ ነፍስ የሌላት ባሕር በደመ
ነፍስ ሕያዋን የሆኑ ፍጥረታ
ትን ታስገኝ አለ፤

ወአዕዋፈ ዘይሠርሩ መልዕልተ ምድር
ወመትሕተ ሰማይ ፤

ከጠፈር በታች ከምድር በላይ
የሚበሩ አዕዋፍንም ታስገኝ አለ፤

ወኮነ ከማሁ ፤

ይገኙ እንዳለ ተገኙ ፤

፳፩፤ ወገብረ እግዚአብሔር አናብ
ርተ ዐበይተ ፤

እግዚአብሔር ታላላቅ ፍጥረ
ታት የሚሆኑ ብሔሞትንና ሌዋ
ታንን ፈጠረ፤

ወኵሎ ነፍሰ ሕይወት ዘይትሐወስ
ዘአውዕአ ማይ በበዘመዱ፤

በየወገኑ ባሕር ያስገኛቻቸውን፤
በልባቸው የሚሳቡትን፤ በደመ
ነፍስ ሕያዋን የሚሆኑትን ፍጥ
ረታት ፈጠረ፤ (ሐተታ) ብሔ
ሞትና ሌዋታን ተፈጥሮአቸው
ከእንስሳ ወገን ነበረ፤ ዐበይት
ስለሆኑ ለይቶ አመጣቸው ፤

ወኵሎ አዕዋፈ ዘይሠርሩ በበዘመ
ዱሙ ፤

በየወገናቸው የሚበሩ አዕዋፍ
ንም ሁሉ ፈጠረ ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ፤

የበቁ ፍጥረታት እንደሆኑ አውቆ
ፈጠረ ፤

፳፪፤ ወባረኮሙ እግዚአብሔር ወይቤ፤
ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለም
ድር ፤

አዘዞሙ ሲል ነው፤ ብዙ፤ የብዙ
ብዙም ሁኑ፤ ባሕርንም ምሉዋት
ብሎ አዘዛቸው ፤

ወአዕዋፍኒ ይብዝኁ ውስተ ምድር፤

አዕዋፍንም፤ በዚህ ዓለም ይበዙ
ዘንድ አዘዛቸው ፤

(ታሪክ) በዚህ ቀን ሦስት ፍጥረ
ታት ፈጥሮአል፤ በልባቸው የሚ
ሳቡ፤ በእግራቸው የሚሽከረ
ከሩ፤ በክንፋቸው የሚበሩ ተሐ
ዋስያንን ሁሉ ከባሕር ፈጠረ፤
እነዚህም መገኛታቸው ምንም
ከባሕር ቢሆን፤ ተፈጥሮዋቸው
ከአራት ባሕርያት ነው፤ ከእነዚ
ህም ከባሕር ተገኝተው በዚያው
ጸንተው የቀሩ አሉ ፤ አንድ
ጊዜ ወደ የብስ ፤ አንድ ጊዜ
ወደ ባሕር የሚሉ አሉ፤ በረው
በረው የሔዱ አሉ፤

ይኸውም ምሳሌ ነው ፤ ባሕር
የጥምቀት ፤ በባሕሩ ጸንተው



የቀሩቱ፤ በክርስትናቸው ጸን
ተው የሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ
ነው ፡

በረው በረው የሔዱት፤ ወደ
ክህደት፤ ወደ ኃጢአት የሔዱ
ሰዎች ምሳሌ ነው፤ አንድ ጊዜ
ወደየብስ ፤ አንድ ጊዜ ወደ
ባሕር የሚመላለሱ፤ አንድ ጊዜ
ወደ ሃይማኖት ወደ ጽድቅ፤
አንድ ጊዜ ወደ ክሕደት ወደ
ኃጢአት፤ የሚመላለሱ ሰዎች
አምሳል ነው ፤

ይህስ አይደለም ፤ ወባረኮሙ
ለክልኤሆሙ በአሐቲ በረከት
ይላል ብሎ ሁሉም የበጎ ነው፤
ባሕር የዚህ ዓለም ፤ በባሕር
ጸንተው የቀሩት በሚስታቸው
ቈርበው፤ ጸድቀው፤ ዐሥራቱን
በኵራቱን አውጥተው የሚኖሩ
የሰብአ ዓለም ምሳሌ ነው፤ በረው
በረው የሂዱት፤ ኀድግዎ ወመ
ንንዎ ለዝ ዓለም ብለው የሚ
ሂዱ የመናንያን ምሳሌ ናቸው፤
አንድ ጊዜ ወደየብስ ፤ አንድ
ጊዜ ወደ ባሕር የሚሉት፤ ተድላ
ዓለም ሲጸናባቸው ወደ ዕፀበ
ገዳም፤ ዕፀበ ገዳም ሲጸናባቸው፤
ወደ ተድላ ዓለም የሚሉ ሰዎች
ምሳሌ ነው፤ ደመ ነፍስ ከሌላት
ባሕር በደመ ነፍስ ሕያዋን የሚ
ሆኑ ፍጥረታት እንደ ተገኙ ፤
ለምእመናን ምክንያተ ሕይወት

የሚሆን ጌታ፤ ፍትወት እንስ
ሳዊት ከሌለባት ከእመቤታችን
ለመገኘቱ ምሳሌ ነው፤

፳፫፤ ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፤

ጨለማ ሁኖ አድሮ ነጋ ፤

ወኮነ ኃምስተ ዕለተ ፤

አምስት ቀን ሆነ፤ (ሐተታ) ዕለት
አምስት፤ ፍጥረት ዐሥራ ስም
ንት ሆነ፤

፳፬፤ ወይቤ እግዚአብሔር ለታውዕእ
ምድር ዘመደ እንስሳ ወዘይትሐወስ፤

ኃሙስ ማታ ለዓርብ አጥቢያ
እግዚአብሔር የእንስሳ ወገን
የሆኑትንና በልባቸው የሚሳቡ፤
በእግራቸው የሚሽከረከሩ፤ ፍጥ
ረታትን ሁሉ ምድር ታስገኝ
አለ ፤

ወአራዊተ ምድር ዘበበዘመዱ ፤

በዚህ ዓለም የሚኖሩ አራዊት
ንም ታስገኝ አለ፤ ሱቱኤል ዕዝራ
ወአዕዋፈ ዘይሠርሩ ብሎ ጨም
ሮበታል፤ በክንፋቸው የሚበሩ
ፍጥረታትንም ፈጠረ፤

ወኮነ ከማሁ ፤

እንዳለው ሆነ ማለት አስገኘች፤

፳፭፤ ወገብረ እግዚአብሔር እንስሳ
በበዘመዱ ፤

እግዚአብሔር እንስሳትን በየወ
ገናቸው ፈጠረ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኵሎ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር በበዘመዱ ፤

በልባቸው የሚሳቡትን፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩትንም ሁሉ በየወገናቸው ፈጠረ ፤

ወአራዊተ ምድር በበዘመዱ ፤

የምድር አራዊትንም በየወገናቸው ፈጠረ ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ፤

የበቁ ፍጥረታት እንደ ሆኑ አውቆ ፈጠረ፤ (ታሪክ) በዚህም ቀን ሦስት ፍጥረታት ፈጥሮ አል ፤ ወገብረ እግዚአብሔር ሠለስተ ዘመደ እንዲል፤ በልባቸው የሚሳቡ ተንቀሳቃሾችን አንድ ወገን፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ አራዊትን እንስሳትን አንድ ወገን፣ በክንፋቸው የሚበሩ አንሥርትን አዕዋፍን አንድ ወገን አድርጎ ቈጥሮ ሦስት ፍጥረታት ፈጥሮአል፤ እነዚህም መገኛታቸው ከየብስ ስለሆነ ተፈጥሮአቸው ከአራቱ ባሕርያት ነው፤

ፍጥረት ሀያ አንድ ሆነ ፤

፳፮፤ ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ፤

እግዚአብሔር ዓርብ በነግህ በእኛ አምሳል፣ በእኛ አርአያ ሰውን እንፍጠር አለ፤ (ሐተታ) ንግበር ማለት የአንድነት፤ በአርአያነ ማለት የሦስትነት፤ አንድም ንግበር ማለት የሦስትነት፤ በአርአያነ ማለት የአንድነት ነው ፤ አንድም ንግበር ያለው ያንድነት የሦስትነት ይሆናል ፤ ንግበር ብሎ ማብዛቱ የሦስትነት፣ እንደ አንድ ቃል ሆኖ፣ ንግበር ማለት የአንድነት ነው፤ እየራሳቸው ቃል ልብ ፣ እስትንፋስ ቢኖራቸው እኔ ላድርግ ፣ አንተ አድርግ እሱ ያድርግ ባሉ ነበርና፤ ኢይቤ እግበር አነ፤ ወአንተ ግበር፤ ወይግበር ዝኩ አላ ይቤ እግዚአብሔር ንግበር እንዲል ፤ ይቤ የአንድነት ፣ ንግበር የሦስትነት በአርአያነ ያለውም የአንድነት የሦስትነት ይሆናል ፤ በሦስቱ አርአያ አንድ ሰው መገኘት፣ የአንድነት ፣ በአርአያነ ብሎ መዘርዘሩ የሦስትነት ነው ፤ ሥላሴን በምን እንመስላቸዋለን ቢሉ፣ ሥላሴ ለባውያን፣ ነባብያን ፣ ሕያዋን ናቸው ፤ እኛም በነፍስ ለባውያን ፣ ነባብያን ፣ ሕያዋን ነንና ፤ አንድም ለሰው ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ፣ እንዳለው፣ ሥላሴም በልብ፣ በቃል፣ በእስትንፋስ ይመሰላሉና ፤

አንድም ለሰው ፍጹም መልክ እንዳለው ለሥላሴም ፍጹም መልክ አላቸውና ፤



ነአምን ከመቦ ለእግዚአብሔር መልክዓት ጽዱቃት ዓይን ፣ ወእዝን፣ አእዳው፣ ወአእጋር፣ ወእለ ተርፉ እምኔሆን አባላት፣ እንዲል፣ (ሃይ አበው የአትናቴዎስ ድርሳን)፣ አንድም በአርአያነ ወበአምሳሊነ ከመ ይኩን ይላል ፣ ሥላሴ በባሕርይ የሚገዙትን እኛ በጸጋ እንገዛለንና ፤

ከመ ይኩንን ዓሣተ ባሕር፣ ወአራዊተ ምድር ወአዕዋፈ ሰማይ፣

አራዊትን፣ አዕዋፍን፣ ዓሣትን፣ ይገዛ ዘንድ፣ አዳምን እንፍጠር አለ፤

ወእንስሳሂ ወኵሎ ምድረ ፣

እንስሳትንና ዓለሙን ሁሉ ይገዛ ዘንድ ፤

ወኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ፣

በምድር የሚመላለሰውን ሁሉ ይገዛ ዘንድ አዳምን እንፍጠር አለ፤

፳፯፤ ወገብሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ እመሕያው በአምሳለ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር አዳምን በራሱ አምሳል ፈጠረው ፤ (ሐተታ) ስለምን አዳምን በነግህ፣ የቀሩትን በሠርክ ፈጠረ ቢሉ፤ የሠርክ ተከታይ ጨለማ ነው፣ እነዚያን አላዋቆች ናቸው ሲል፤ የነግህ ተከታይ ብርሃን ነው፣ እሱን አዋቂ ነው ሲል ነው ፤ ይህስ ይሁን እነዚያን በፊት ፈጥሮ እሱን በኋላ መፍጠሩ ስለምን ነው ? ቢሉ ፣ በሰው ልማድ ዛሬ ባለጸጋ በፊት ምግቡን አዘጋጅቶ ኋላ ሰውን እንዲጠራ ፤ ጌታም በፊት ምግቡን ፈጥሮ በኋላ እሱን ፈጠረ፤ ያውስ ቢሆን እሱን ቀንቶ (ቀና ብሎ) እንዲሄድ ፣ እነዚያን ተጐንብሰው እንዲሄዱ አድርጎ ስለ ምን ፈጠራቸው ቢሉ ፣ የገዥና የተገዥ ምልክት ነው፤ አንድም ለነዚያ ተስፋ ትንሣኤ የላቸውም ፣ ለእሱ ግን ተስፋ ትንሣኤ አለው ሲል ነው ፤

፳፰፤ ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ ፣

ወንድ ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ (ሐተታ) በዚህስ ጊዜ ሔዋን ገና አልተፈጠረችም በኋላ ከታወቀ ብሎ፤ አንድም በእሱ ባሕርይ አለችና እንዲህ አለ ፤

ወባረከሙ ወይቤሎሙ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር ወቅንይዋ፣

ብዙ፣ የብዙ ብዙ ሁኑ፣ ምድርንም ምሉዋት፣ ግዙዋት ብሎ ባረካቸው ፤

ወኰንንዎሙ ለዓሣተ ባሕር ወለአራዊተ ምድር ፣

ዓሣትን የምድርንም አራዊት ግዟቸው ብሎ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለአዕዋፈ ሰማይኒ ወለኵሉ እንስሳ፣ ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር፣

የሰማይ አዕዋፍንና እንስሳትን ሁሉ፣ በዚህም ዓለም የሚመላ ለሰውን ሁሉ ግዙአቸው ብሎ ባረካቸው ፤

፳፱፡ ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ ወሀብኩክሙ ኵሎ ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ ወይበቍል በበዘርኡ ትገዝር እዎ ዲበ ኵሉ ምድር ፣

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ በየወገኑ፣ በየዘሩ የሚዘራውን፣ የሚበቅለውን ዘር ተክል ሁሉ በዚህ ዓለም ትዘሩት ዘንድ እነሆ ሰጠሁአችሁ፤ አንድም ሰጥቼአ ችኋለሁና (ዝርእዎ) ዝሩት፤

ወኵሎ ዕፀ ዘሀሎ ውስቴቱ ዘርኡ ዘይዘራእ በበፍሬሁ ፣

ዘሩ በውስጡ ያለውን፣ ፍሬው የሚዘራውን ተክል ሁሉ ሰጠሁ አችሁ፤ በዕንጨትነት የሚዘራ ተክል አለና ፤

ለክሙ ይኩንክሙ መብልዐ ፣

ለእናንተ ምግብ ይሁናችሁ ፤ (ለክሙ ውእቱ መብልዕም ይላል) ፤

ወለኵሉ አራዊተ ምድር ወለኵሉ አዕዋፈ ሰማይ ፣

ለአራዊትም፣ ለአዕዋፍም፣ ምግብ ይሆን ዘንድ ሰጠሁአችሁ ፤

ወለኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ፣

በደመ ነፍስ ሕያው ሆኖ በምድር ለሚገር ሁሉ ምግብ ሊሆን ዘሩን ተክሉን ሰጠሁአችሁ ፤

ወኵሉ ሐመልማለ ሣዕር ይኩንክሙ መብልዐ ፣

ዘሩ፣ ተክሉ ሁሉ ምግብ ይሁ ናችሁ አለ፤

ወኮነ ከማሁ ፣

እንዳለውም ሆነ ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ኵሎ ዘገብረ ከመ ጥቀ ሠናይ ፣

እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥ ረት ሁሉ እጅግ ያማረ፣ ፈጽሞ የበቃ ፍጥረት እንደሆነ አውቆ ፈጠረ፤ (ሐተታ) እስካሁን ወር እየ እግዚአብሔር ከመ ሠናይ ሲል መጥቶ አሁን ከአዳም ላይ ሲደርስ ጥቀ ሠናይ አለ፤ የሰው ተፈጥሮ ከሁሉ እንዲበልጥ ለማጠየቅ ፤ ሰሎሞን የሥነ ፍጥረትን ነገር ሲናገር መጥቶ፣ ወፍሥሐየኒ ጥቀ በዕጓለ እመ ሕያው እንዳለ፤

ወኮነ ሌሊተ ወጸብሐ ፣

ጨለማ ሆኖ አድሮ፣ ነጋ ፤

ወኮነ ስድስተ ዕለተ ፣

ስድስት ዕለት ሆነ፤ (ሐተታ) ዕለት ስድስት፣ ፍጥረት ሃያ ሁለት ሆነ ።



# ምዕራፍ ፪

፩፡ ወተፈጸመ ሰማይ ወምድር ወኵሉ ዓለሞሙ ፣

የሰማይና የምድር የሠራዊቶቻ ቸውም ተፈጥሮ ሁሉ ተፈጸመ፤ (ሐተታ) የሰማይ ሠራዊት ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት፣ የምድር ሠራዊት፣ ዕፀው፣ አእባን፣ እን ስሳት፣ አራዊት ደቂቀ አዳም ናቸው ፤

፪፡ ወፈጸመ እግዚአብሔር ግብሮ ዘገብረ ፣

እግዚአብሔር የጀመረውን ፍጥ ረት ሁሉ ፈጥሮ ፈጸመ፤ ማለት ሰማይን ከነግሡ፣ ምድርን ከነ ልብሱ፣ ፈጥሮ ጨረሰ፤ (ሐተታ) እስካሁን ባዕድ ከባዕድ ፍጥረት ሲፈጥር ሰንብቶ ነበር ፤ እንግ ዲህ ወዲህ ግን፣ ግብር እምግ ብር ቢራባ እንጂ፣ ሌላ ባዕድ ፍጥረት አይፈጥርምና እንዲህ አለ፤

ወአዕረፈ እግዚአብሔር በሳብዕት ዕለት እምኵሉ ግብሩ ፣

እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ሥራ ከመሥራት ዐረፈ፤ ዐረፈ ማለቱም በጌታ ድካም ኑሮበት አይደለም ፣ መፍጠርን ተወ ሲል ነው፤

፫፡ ወባረካ እግዚአብሔር ለዕለት ሳብዕት ወቀደሳ ፣

እግዚአብሔር ሰባተኛዪቱን ቀን ከስድስቱ ዕለታት ለይቶ አከ በራት ፤

እስመ ባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ ዘአኀዘ ይግበር ፣

ይሠራ ዘንድ ከጀመረው ሥራ ሁሉ ዐርፎባታልና ፤ (ሐተታ) መናፍቃን፣ ፍጥረትስ ነበረው ዕለት አለቀበት እንጂ እንዳይሉ አንድ ቀን አተረፈ ፤ ዕለትስ ነበረው ፍጥረት አለቀበት እንጂ እንዳይሉ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ አለ ፤

## ጉባኤ

፬፡ ዝንቱ ፍጥረተ ሰማይ ወምድር አመ ኮነት ዕለት እንተ ባቲ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ፣

ሰማይንና ምድርን የፈጠረባት ዕለተ እሑድ በተገኘች ጊዜ የተ ደረገ የሰማይና የምድር ተፈ ጥሮ ይህ ነው ፤

፭፡ ወኵሉ ሐመልማለ ሐቅል እም ቅድመ ይኩን በምድር ወኵሉ ሐመ ልማለ ምድር እምቅድመ ይብቊል፣

ይኩንና ይብቀል አንድ ወገን፣ በምድር ላይ ዕፀውና አዝርእት፣ አትክልት ሳይፈጠሩ፣ ሰማይ ንና ምድርን የፈጠረባት ዕለተ እሑድ በተገኘች ጊዜ የተገኘ

www.ethiopianorthodox.org

የሰማይና የምድር ተፈጥሮ ይህ ነው ፡ እንድም ይህ የሰማይና የምድር ተፈጥሮ ፤ ሰማይንና ምድርን የፈጠረባት ዕለተ እሑድ በተገኘች ጊዜ የተገኘ ነው፤ ኢ.የገዘነመ ማንሻ ፡ እን ድም በዚህ ዓለም ዕፀውና አዝ ርእት አትክልት ሳይፈጠሩ፤

ወእምቅድመ ይትፈጠር አዳም ፣

አዳምም ሳይፈጠር ፤

ኢ.የገዘነመ እግዚአብሔር ዲበ ምድር፣

ጌታ በምድር ላይ ዝናም አላዘ ነመም ፤

ወአልቦ ሰብእ ዘይትጌበራ ለምድር፣

ከዚህ አስቀድሞ ምድርን የሚ ያርሳት የሚቈፍራት አልነበ ረም፤

፮፡ አላ ነቅዐ ማይ የዐርግ እምድር ወይሡቅያ ለየብስ ፣

የመስኖ ውሀ ውስጥ ለውስጥ ምድርን ያጠጣት ነበር እንጂ፣ ዝናም አላዘነመም ነበር፤

፯፤ ወገብሮ እግዚአብሔር ለሰብእ እመሬተ ምድር ፣

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር፣ መሬትን ነሥቶ ፈጠረው ፤ (ሐተታ) መፈጠሩንማ ምነው ከዚህ ቀድሞ ተናግሮት አልነበ ረምን ቢሉ፣ ተፈጥሮውን ተና ግሮ መገኛውን አልተናገረም ነበርና እመሬተ ምድር አለ፤ ከመሬትም ማለቱ በመክብቡ ለመናገር ነው እንጂ፣ ተፈጥሮ ውስ ከአራቱ ባሕርያት ነው፤ አንድም ወነፍሐ በገጹ ለማለት ደገመው፤

ወነፍሐ በገጹ መንፈሰ ሕይወት ፣

ሕይወት የምትሆነው ነፍስን አሳደረበት፤ አንድም የጸጋ ሕይ ወት የሚሆነው መንፈስ ቅዱስን አሳደረበት ፤

ወኮነ እጓለ እመሕያው በመንፈሰ ሕይወት ፣

አዳም ሕይወት በምትሆን ነፍስ ሕያው ባለ አእምሮ ሆነ ፤ (ሐተታ) ነፍሐ በገጹ ማለቱ፣ አሁን ዛሬ ሰው ጐተራውን በፊት ሠርቶ በኋላ እህል እንዲያኖር በት፣ በፊት ሥጋን ፈጥሮ ኋላ ነፍስን አምጥቶ አሳደረበት ማለት አይደለም ፤ ሥጋን ከአራቱ ባሕርያት፣ ነፍስንም እምኀበ አልቦ አምጥቶ ሲፈጥር ሲያዋ ሕድ አንድ ጊዜ ነው፤ የነፍስና የሥጋ ተዋሕዶ በተዓቅቦ ነውና ነፍሐ በገጹ አለ እንጂ፤ አንድም አዳም በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ሕያው ሆነ ፤ (ሐተታ) ከዚህ ለአዳም ልጅነትን ዕለቱን እንደ ሰጠው አድርጎ ተናግሮታል ፤ አክሲማሮስ ግን አዳምን በአርባ ቀን በልጅነት አክብሮ ብርሃንን

የግል ቤተ መጻሕፍት



አልብሶ ብርሃንን አጐናጽፎ መላ እክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ገነት እንዳገቡት ይናገራል፤

፰፡ ወተከለ እግዚአብሔር አምላክ ውስተ ኤዶም ገነተ መንገለ ጽባሕ፣

እግዚአብሔር በምሥራቅ በኩል ባለች ኤዶም በምትባል ስፍራ ገነትን (ተክልን) አዘጋጀ፤ ውስተ ገነተ አዳም ይላል ፣ ለአዳም ተብላ በተፈጠረች በገነት ተክ ልን አዘጋጀ፤ አንድም ኤዶም ገነት አንድ ወገን፣ በምቹ ቦታ በገነት ተክልን ተከለ አለ፣ እን ዲገኝ አደረገ፤ (ሐተታ) አዝር እት አትክልት የተገኙትማ ማክ ሰኞ አይደለምን ቢሉ ፣ ዕፀወ ገነት ከዚህ ዓለም ዕፀው ልዩ ስለሆኑ እንዲህ አለ እንጂ የተ ገኙትስ በዕለተ ሠሉስ ነው ፤ አንድም ወሤሞ ለማለት ደግ ሞታል ፤

ወሤሞ ህየ ለእጓለ እመሕያው ዘገ ብሮ ፣

የፈጠረውን አዳምንም በገነት አኖረው ፤

፱፤ ወአብቈለ ዓዲ እግዚአብሔር እምድር ኵሎ ዕፀወ ዘሠናይ ለበሊዕ ወሠናይ ለርእይ ፣

ዳግመኛም እግዚአብሔር ሊያ ዩት ሊበሉት ደስ የሚያሰኘውን ተክል እንዲበቅል አደረገ ፤ (ሐተታ) መብቀላቸውንማ በማ ክሰኞ ሥነ ፍጥረት ተናግሮት የለምን ቢሉ፣ ዘሠናይ ለበሊዕ ለማለት ደግሞታል፤ አንድም ወዕፀ ሕይወትኒ ለማለት አመ ጣው ፤

ወዕፀ ሕይወትኒ ተከለ ማእከለ ገነት፣

ዕፀ ሕይወትንም በገነት መካከል እንዲገኝ አደረገ ፤

ወዕፀኒ ዘያርኢ ወያሌቡ ሠናየ ወእ ኩየ ፣

ቢበሉት ክፉውን፣ ባይበሉት በጐ ውን የሚያሳውቅ ዕፀ በለስንም እንዲገኝ አደረገ፤ አንድም ቢበ ሉት ቅሉ በጎውን የሚያሳውቅ ዕፀ በለስን አስገኘ ፤ አዳምና ሔዋን ከገነት ከወጡ በኋላ የፊት ክብራቸውን የኋላ ተዋ ርዶቸአውን አይተው ይህንን ዕፀ በለስ ባንበላ እንዴት ባለ አንዋዋር እንኖር ነበረ? ብለ ዋልና፤ (ሐተታ) ዕፀ ሕይወትስ ዕፀ በለስስ የተገኙት በዕለተ ሠሉስ አይደለምን አሁን እንደ ተገኙ አድርጎ ስለምን ተናገራ ቸው ቢሉ፣ መገኘታቸውስ በዕ ለተ ሠሉስ ነው፤ ነገር ግን አሁን ለአዳም ይህን ብላ፣ ይህን አት ብላ ብሎ ሥርዓት የሚሠራለት ነውና ይህን ሲያይ መልሶ ተና ግሮታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

(ታሪክ) ለአዳም ሦስት ዕፀዋት ተሰጥተውት ነበር ፤ አንዱን ሊጠብቀው ፣ አንዱን ሊመገበው፣ አንዱን ሺሕ ዓመት ኑሮ ሊታደስበት፣ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በበላ ጊዜ የሚታደስበት ዕፅ ተነሥቶታል ፤ በሚታደስበት በዕፀ ሕይወትም ፈንታ፣ ዛሬ ሥጋው፣ ደሙ ገብቶልናል፤ ሥጋውን ፣ ደሙን ተቀብለን፣ በልጅነት ታድሰን መንግሥተ ሰማያት የምንገባ ሁነናል ፤

፲፡ ወፈለግ ይወፅእ እምትድሚሁ ከመ ይስቅዩ ለገነት ፣

እምኔሁ ሲል ነው፣ ገነትን ያጠጣት ዘንድ ውሀ ከዕፀ ሕይወት ሥር ይፈልቃል ፤

ወእምህየ ይትፈለጥ ለአርባዕቱ መዓዝነ ዓለም ፣

ከዚህም ነቅቶ አራቱን መዓዝነ ዓለም ዞሮ ለማጠጣት ከአራት ይከፈላል ፤

፲፩፡ ስሙ ለአሐዱ ፈለግ ኤፌሶን፣

ያንዱ ወንዝ ስሙ ኤፌሶን ይባላል፤

ወውእቱ ዘየዓውድ ውስተ ኵሉ ምድረ ኤውላጦን ፣

ይኸውም ወንዝ ኤውላጦን የተባለውን ምድር ሁሉ እየዞረ የሚያጠጣ ነው ፤ ኤውላጦን የተባለውም ምድረ ጽርዕ ነው፤

ወህየ ሀሎ ወርቅ ፣

ከዚያ ወርቅ ይገኝበታል ፤

፲፪፡ ወወርቃ ለይእቲ ምድር ሠናይ፣

ጽሩይ ሲል ነው፤ ወርቁም እጅግ የጠራ ያማረ ነው ፤

ወህየ ሀሎ ዕንቍ ዘያሐቱ፣ ወዕንቍ ሐመልሚል ፣

ከዚያም የሚያበራ ዕንቍ፣ ቅጥልጣልም ዕንቍ አለ፤

፲፫፡ ወስሙ ለካልእ ፈለግ ግዮን ፣

የሁለተኛው ወንዝ ስሙ ግዮን ይባላል ፤

ወውእቱ ዘየዐውድ ውስተ ኵሉ ምድረ ኢትዮጵያ ፣

ይኸውም ወንዝ የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ እየዞረ የሚያጠጣ ነው፤ ይኸውም ዓባይ ነው፤

፲፬፡ ወፈለግ ሣልስ ጤግሮስ ፣

ሦስተኛውም ወንዝ ጤግሮስ ይባላል ፤

ውእቱ ዘየዐውድ ላዕለ ፋርስ ፣

ይኸውም ወንዝ የፋርስን አገር ዞሮ የሚያጠጣ ነው ፤

ወፈለግ ራብዕ ውእቱ ኤፍራጥስ፣

አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው ፤ ይኸውም ህንድን ዞሮ የሚያጠጣ ነው፤ በዚህ አላቀናውም፤ በመጽሐፈ ቅዳሴ አቅንቶታል ፤ ቦ ዘይወፅእ እምሥ



ራቅ፣ ወየሐውር ለምዕራብ ከመ ይስቂ ዘህየ ፤ ወቦ ዘይወፅእ እምዕራብ ፤

ወየሐውር ለምሥራቅ ከመ ይስቂ ዘህየ ፤ ወቦ ዘይነቅዕ እምደቡብ ወይሰወጥ ለሰሜን ከመ ይስቂ ዘህየ፤ ወቦ ዘይፈልፍል እምሰሜን ወይሰወጥ ለደቡብ ከመ ይስቂ ዘህየ እንዳለ፣ (ቅዳሴ አትናቴዎስ ፣ ምዕ. ፪ ቁ. ፲፯-፲፱) ፣

ይኸውም ምሳሌ ነው፤ አራቱ አፍላጋት የአራቱ ወንጌላትና የአራቱ ወንጌላውያን፣ ከአንድ ዕፀ ሕይወት ሥር ነቅተው ይህን ዓለም ዞረው በዚህ ዓለም ያሉ አገርእትን፣ አትክልትን እንዳያጠጡ፤ አራቱ ወንጌላውያንም ይህን ዓለም ዞረው በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናንን የማስተማራቸው ምሳሌ ነው ፤ ወንጌላቱ ቢሉ በአራቱ መዓዝነ ዓለም ለመነገራቸው ምሳሌ ነው፤ ካንድ ከዕፀ ሕይወት ሥር መንቃታቸው፣ ወንጌላውያኑ፣ ከጌታ ለመማራቸው፤ ወንጌላቱ ከጌታ ለመገኘታቸው ምሳሌ ነው ፤ ወርቃኒ ሠናይ ያለው የምእመናን፤ ዕንቍ ዘያሐቱ የጴጥሮስ፤ ዕንቍ ሐመልሚል የጌታ ምሳሌ ነው፤ ሐመልሚል አለው አምላክ ወሰብእ ነውና ፤

፲፭፡ ወነሥኦ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው ዘገብሮ፣ ወሤሞ ውስተ ገነት ፣

እግዚአብሔር የፈጠረውን አዳምን ወስዶ በገነት አኖረው ፤

ከመ ይትገበራ ወይዕቀባ ፣

ያሰናዳት ይጠብቃት ዘንድ ፤ (ሐተታ) ይትገበራ ማለቱ፣ በገነት እርሻ ቁፋሮ ኖሮ አይደለም ፣ የወደቀውን ማንሣት ፣ የበሰለውን መልቀም ነው፤ ይዕቀባ ማለቱስ ከምን ይጠብቃታል ቢሉ ፣ ከአዕዋፍ ፤ ምነው የገነት ፍሬ ቈርጠው በልተውት ወዲያው ተክቶ ይገኝ የለምን ቢሉ፣ ንዋየ እግዚአብሔር በከንቱ አይበላሽምና ኢትክዐው ንዋየከ በከንቱ፣ እንዲል፤ (ሲራክ ፳:፭)፤ አንድም የገሥና የተገዥ ምልክት እንዲሆን፤ ሀኬት እንዳይሰለጥንበት ዐቂበ ሕግንም ሲያስተምረው ነው ፤ (ሐተታ) ወሤሞ ውስተ ገነት አለ ፣ አዳምን በፈጠረው በአርባ ቀን፣ ሔዋንን በፈጠራት በሰማንያ ቀን በልጅነት አክብሮ ወደ ገነት አግብቶአቸዋል ፤ የኋላ ሰዎች ይህንን ይዘው ሥርዓት ሠርተዋል ፤ ወንድ የወለደች እንደሆነ በአርባ ቀን ፤ ሴት የወለደች እንደሆነ በሰማንያ ቀን ፣ እጉለ ርግብ ዘውግ

www.ethiopianorthodox.org

ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ይገቡ ነበር ፡ ዛሬም እኛ ወንድ ቢሆን በአርባ ቀን፣ ሴት ብትሆን በሰማንያ ቀን ከቤተ ክርስቲያን ሄደን ተጠምቀን ስም ተሰይመን፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብለን የምንመጣ ሆነናል፡

፲፮፡ ወአዘዞ እግዚአብሔር ለአዳም ወይቤሎ እምኵሉ ዕፀ ዘሀሎ ውስተ ገነት ብላዕ ፣

እግዚአብሔር አዳምን በገነት ካለው ዕፅ ሁሉ የተገኘውን ብላ ብሎ አዘዘው ፡

፲፯፡ ወእምዕፀ ዘየአኢ ወየሌቡ ሠናየ ወእኩየ ኢትብላእ እምኔሁ፣

እምና እም አንድ ወገን፣ በጎውን ክፉውን ከሚያሳውቅ ከዕፀ በለስ ግን አትብላ አለው ፡ (ሐተታ) ስለምን ቢሉ፣ የገዥና የተገዥ ምልክት ሊሆን፡ አንድም ጾምን ሲያስተምረው ነው፡ ምሥጢሩ ግን አምላክነቴን አትሻ ሲለው ነው፡ አንድም ሥጋዬን ደሜን በማይገባ አትቀበሉ ሲል ነው ፡

እስመ በዕለተ ትበልዕ እምኔሁ ሞተ ትመውት ፣

ከዚያ ዕፅ በምትበላበት ቀን የሞት ሞትን ትሞታለህና አትብላ አለው ፡

፲፰፡ ወይቤ እግዚአብሔር ኢኮነ ሠናየ ለእጓለ እመሕያው ይንበር ባሕቲቱ ፣

እግዚአብሔርም አዳም ብቻውን መኖር አይገባውም አለ ፡

አሳ ንግበር ቢጸ ዘይረድኦ ፣

ዘትረድኦ ሲል ነው ፡ የምትረዳው ባልንጀራን እንፍጠርለት እንጂ ፡ ቢጽ በተፈጥሮ ነው ፡ አንድም ዘይረድኦ እንዳለ ይሆናል ፡ በእሱ ባሕርይ አለችና (ሐተታ) በምን ትረዳዋለች ቢሉ፣ በወሊደ ውሉድ፣ በአቅልሎ ክበደ ዋዕይ ፡ አንድም በሥራ ፣ እሱ የአፍአውን ፣ እስዋ የውሥጡን በመሥራት ትረዳዋለችና ፡ አንድም ብቻ ከመኖር ትረዳዋለች ፡ ብቻ መኖር ጽኑዕ ገድል ነውና ፡ ይህንንም ንግበር ቢጸ ያለውን የሚቀድመው አለ የተሳለፈ ነው፡ አሁን ወደፊት፣ ወለአዳምሰ ኢተረክበ ረድኤቱ ዘከማሁ ብሎ እንዲያመጣው ፡

፲፱፡ ወገብረ እግዚአብሔር ዓዲ አራዊተ ገዳም እምድር፣ ወኵሎ አዕዋፈ ሰማይ ወአምጽኦሙ ኀበ አዳም ፣

እግዚአብሔርም ዳግመኛ የዱር አራዊትን ፣ የሰማይ አዕዋፍን ከምድር ፈጥሮ ወደ አዳም አመጣቸው፡ (ሐተታ) ምነው ተፈጥሮአቸውንማ ካሁን በፊት ተና



ግሮት አልነበረምን ቢሉ ወአምጽኦሙ ለማለት ደግሞታል ፡

ከመ ይርአይ ወምንተ ይሰምዮሙ፣

አይቶ ስም ያወጣላቸው ዘንድ፡ (ሐተታ) ስለምን ወደሱ አመጣቸው ቢሉ ፡ የገዥና የተገዥ ምልክት ሊሆን፡ ተገዥ ይመጣል እንጂ ገዥ አይሄድምና፡ አንድም አሁን ስም አወጣላቸው የሚል ነውና ፡

ወኵሎ ዘሰመዮሙ አዳም ለለነፍሰ ሕይወት ውእቱ ይኩን ስሞሙ፣

በደማዊት ነፍስ ሕያዋን ለሆኑት ሁሉ፡ አዳም ያወጣላቸው ስም፣ ይጠሩበት ዘንድ ነው፡

፳፡ ወሰመዮሙ አዳም ለኵሉ በበአስማቲሆሙ ለእንስሳ ወለኵሉ አዕዋፈ ሰማይ ወለኵሉ አራዊተ ገዳም፣

ለእንስሳት፣ ለአዕዋፍ፣ ለአራዊትም ሁሉ አዳም ስም አወጣላቸው ፡ ላም ፣ በሬ ፣ ዋኖስ፣ ርግብ፣ ዝሆን፣ አንበሳ እያለ፡

ወለአዳምሰ ኢተረክበ ረድኤቱ ዘከማሁ፣

ለአዳም ግን፣ እንደሱ ያለ ረዳት አጋዥ አልተገኘለትም (አላገኘም) ነበር፡ (ታሪክ) ጌታ ዓርብ በነግህ አዳምን ፈጥሮ ፡ ቅዳሜ መፍጠሩን ተወ፡ እሑድ እንስሳትን፣ አራዊትን አመጣለት፣ ስም አወጣላቸው፡ ሰኞ ማክሰኞ አዕዋፍን አመጣለት፣ ስም አወጣላቸው፡ ረቡዕ፣ በየብስ የተፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት ስም አወጣላቸው፡ ኃሙስ፣ በባሕር የተፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት፣ ስም አወጣላቸው፡ ተባዕትና እንስት ሁነው አይቶ፣ ከኔ በቀር ብቻውን የተፈጠረ የለም ብሎ አዘነ፡ በዚህ ጊዜ ጌታ፡ ኢኮነ ሠናየ ለእጓለ እመሕያው ይንበር ባሕቲቱ ብሎ ንግበር ቢጸ ዘይረድኦ አለ፡

፳፩፡ ወአምጽአ እግዚአብሔር ድቃሰ ላዕለ አዳም ወኖመ፣

እግዚአብሔር በአዳም እንቅልፍን አመጣበት ተኛ ፡

ወነሥአ እግዚአብሔር አሐተ እም ዓጽመ ገቦሁ ወመልአ ሥጋ መካና፣

ከአዳም ጐድን አንድ አጥንትን ነሥቶ የነሣበትን የአዳምን ጐድን ሥጋ መላት፡ (አንድም) ከአዳም የነሣትን ዓጥንት፣ ሥጋ መላት ፡

፳፪፡ ወነደቃ እግዚአብሔር ለይእቲ ዓጽመ ገቦ እንተ ነሥአ እምአዳም፣

እግዚአብሔር ከአዳም የነሣትን ያችን ዓጥንት ቀረጻት፣ ዓይን፣ ጆሮ፣ አፍ፣ አፍንጫ፣ እጅ፣ እግር፣ አወጣላት፡

ወረሰያ ብእሲተ፣

የሴት አካል ያላት አድርጎ ፈጠራት፡ አንድም ሥትፍት፣ ብርሀት አደረጋት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአምጽአ ኀበ አዳም ፤

መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች የምታምር አድርጎ ወደ አዳም አመጣት፤ (ሐተታ) አዳም ተኝቶ ሳለ ሔዋንን ስለምን ፈጠራት? ቢሉ፣ ተዋሕዶአቸው በመኝታ ነውና፤ አንድም ማእከለ ነቂሕ ወነዊም ሆኖ ሳለ ፈጥሮአታል፤ ስለምን ነው ቢሉ የጌታ ሥራው ሁሉ አማናዊ ነው እንጂ ምትሐት አይደለም፤ ነቅቶ ሳለ ቢፈጥራት ባመመው ነበርና ፤ ተኝቶም ሳለ ቢፈጥራት ይህች እንግዳ ፍጥረት ምንድርናት ብሎ ባዕድ ባደረጋት ነበርና ፤ ይህስ አይደለም ፤ ነቅቶ ሳለ ቢፈጥራት እንዳያመው ማድረግ፣ ተኝቶም ሳለ ቢፈጥራት ባዕድ እንዳያደርጋት ማድረግ ለጌታ ይቻለዋል ብሎ ፤ የአዳምን ነቢይነት ለመግለጽ ዛቲ ዓጽም እምዓጽምየ የሚል ነውና፤ አንድም ለምሳሌ አዳም ማእከለ ነቂሕ ወነዊም ሁኖ ቀዳሚት ሔዋንን እንዳስገኘ፣ ጌታም በሰውነቱ መዋቲ በመለኮቱ ሕያው ሁኖ ዳግሚት ሔዋን ጥምቀትን ለማስገኘቱ ምሳሌ ነው ፤

የፈጠራትስ ከቀኝ ጎኑ ነውን ወይስ ከግራ ጎኑ ቢሉ፤ ከግራ ጎኑ ነው፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ ግራ ደም ይበዛበታል፤ ሴቶችም ደም ይበዛባቸዋል፤ ግራ ደካማ ነው፤ ሴቶችም ደካሞች ናቸውና ፤ አንድም ከቀኝ ጎድኑ ነው ፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ ፤ ቀኝ ብርቱ ነው፤ ሴቶችም ለተራድኦ ብርቱዎች ናቸውና፤ ቀኝ ፈጣን ነው፣ ሴቶችም ለተራድኦ ፈጣኖች ናቸውና ፤ አንድም ለምሳሌ አዳም ከቀኝ ጎኑ ቀዳሚት ሔዋንን እንዳስገኘ፤ ጌታም ከቀኝ ጎኑ ዳግሚት ሔዋን ጥምቀትን አስገኝቷልና፤ ያውስ ቢሆን ከፍ ብሎ ከግንባሩ ዝቅ ብሎ ከእግሩ ያልፈጠራት ከጎኑ የፈጠራት ስለምን ነው? ቢሉ፤ ከግንባሩ ፈጥሮአት ቢሆን፣ ሴቶች ፈጽመው በኰሩ ነበርና ፤ ዝቅ ብሎ ከእግሩም ፈጥሮአት ቢሆን ፣ ፈጽመው በተናቁ ነበርና ፤ ከቤተሰብ በላይ፣ ከባልዋ በታች ሁና ትኑር ሲል ከመካከል ጐድኑ ፈጠራት፤ አንድም ጐድን በልብስ፣ በድግ ይሠወራል ፣ ሴትም ለባልዋ ሥውር ገንዘቡ ናትና፤ ወፍጥረታሂ ኢያዔውቀክሙኑ እንዲል (፩ቆሮ.ም. ፲፩ቁ. ፲፬-፲፭) ፤

፳፫፤ ወይቤ አዳም ሶቤሃ ዛቲ ዓጽም እምዓጽምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ ፣

አዳም ያንጊዜ ይህች ዓጥንት ያጥንቴ ፍላጭ ፣ ይህች ሥጋ



የሥጋዬ ቊራጭ ናትና ሚስት ትሁነኝ አለ ፤

እስመ እምታ ወፅአት ይእቲ ፣

ባል ከምሆናት ከእኔ ተገኝታለችና ሚስት ትሁነኝ አለ ፤ አንድም ከእኔ ከባልዋ ተገኝታለችና ሚስት ትሁነኝ አለ አዳም፣ ይላል ነቢዩ ሙሴ ፤

፳፬፤ ወበእንተዝ የኀድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይተልዋ ለብእሲቱ፣

ስለዚህም ነገር (ሔዋን ከአዳም ጐን ስለተገኘች) ወንድ አባት እናቱን ትቶ ሚስቱን ተከትሎ ይሄዳል አለ፣ ቈላ ብትወርድ ቈላ፣ ደጋ ብትወጣ ደጋ ይሔዳል ፤

ወይከውኑ ክልኤሆሙ አሐደ ሥጋ፣

ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ አለ፤ አንድ ክብር በመውረስ፣ አንድ ልብስ በመልበስ ነው፤ አንድም ወበእንተዝ ብለህ መልስ፤ ፈቃደ ሥጋ በሚነሣበት ጊዜ የኀድግ እሞ፣ ወይእቲኒ ተኀድግ አባሃ፤ ወንድ ልጅ ከእናቴ ሳድርገው አይልም፤ ሴት ልጅም ከአባቴ ሳድርገው አትልምና፣ (ወይተልዋ) ይትላጸቃ ሲል ነው፤ ወይታለዋ አባግዐ ቀርሜሎስ እንዲል ፤

በግብር ከእስዋ ጋራ አንድ ይሆናል፤ (ወይከውኑ) ሁለቱ አንድ አካል ይሆናሉ አለ በግብር፤ (ሐተታ) ወንድ ቢወለድ የእንተ ነው፣ ሴት ብትወለድ የእንቺ ናት አይባባሉምና ፤ አንድም የሁለቱን መልክ ይዞው ይወለዳሉና፤ አንድም ሁለት ሁነው አንድ ልጅ ያስገኛሉና ፤ አንድም ከእናት ደም፣ ከአባት ዘር ተከፍሎ አንድ ሰው ሁኖ ይወለዳልና ፤

## ገባኤ

፳፭፤ ወሀለዉ አዳም (ወሔዋን) ወብእሲቱ ዕራቃኒሆሙ ወኢይትኃፈሩ፣

አዳምና ሔዋን ከዚህ ዓለም ልብስ ዕራቁታቸውን ሳሉ አይተፋፈሩም ነበር፤ (ሐተታ) ብርሃን ለብሰው ነበርና ፤ ብርሃን ይገልጻል እንጂ ይሠውራልን? ቢሉ፣ እሱ ሠውር ካለው ይሠውራልና፤ አንድም እንደ ሕፃን አይተፋፈሩም ነበር ፤ አንድም ወሀለዉ ብለህ መልስ፤ አዳምና ሔዋን ከልብሰ ኃጢአት፣ ዕራቁታቸውን ነበሩ:: (ወኢይትኀፈሩ) ሰባቱንም ዓመት፣ ኃፍረተ ነፍስ አልነበራቸውም ::

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፫

፩፥ ወአርዌ ምድርሰ ይጠብብ እምኵሉ አራዊተ ገዳም ዘገብረ እግዚአብሔር ፣

እባብ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከዱር አራዊት ሁሉ ይልቅ ይተነኰል ነበር፤ አንድም አብነት ይልሕም እከየ ይላል በቀሌምጦንስ ፤ በክፋት ከሁሉ ይከፋ ይጸና ነበርና፤ (ታሪክ) ይህ አርዌ ምድር ጥንቱን ሲፈጠር በአምሳለ እጓለ ገመል ይላል፣ የግመል ወሳብሬ አህሎ ተፈጥሮ ነበር፤ ኋላ ሐኑር በእንግድዓከ ወመሬተ ብላዕ ባለው ጊዜ አራት እግሩ ተስቦ ወደ ሆዱ ገብቶአል፤ ለምድር ቀርቦ በልቡ የሚሄድ ስለሆነ አርዌ ምድር ተብሎአል፤ ይህስ ከምን ይገኛል ቢሉ ከቀሌምንጦስ ይገኛል፤ አንድም ምድር ያለው አዳምን ነው፣ ዘምድረ ለብሰ እንዲል (መጽ: ኪዳን)

ምድራዊ አዳምን ስላሳተ አርዌ ምድር ተብሎአል ፤ አንድም ዲያብሎስ ከሁሉ በክፋት ይጸና ነበር ፤

ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት፣

ዲያብሎስ ሔዋንን እንዲህ አላት ፤

ምንትኑ ዘይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኵሉ ዕፅ ዘውስተ ገነት፣

እግዚአብሔር በገነት ካለው ዕፅ ሁሉ አትብሉ ያላችሁ ስለምን ነው? አላት፤ (ሐተታ) ዕፀ በለስ ብዬ ለይቼ የነገርሁዋት እንደ ሆነ፣ ክፋቴን፤ ተንኰሌን ታውቅብኛለች ብሎ አልብሶ (ሠውሮ) ተናገረ፤ ዓመፃ ወዕአት እመዛግብቲሃ ፣ ወአቡሃ ለሐሰት የሚያሰኘው ይህ ነው ፣ (ሂኖክ ፲፱:፫፤ ዮሐ. ፰:፵፬) ፤

፪፥ ወትቤሎ ብእሲት ለአርዌ ምድር እምዕፅሰ ዘይፈሪ ዘሀሎ ማዕከለ ገነት ንበልዕ፣

ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለቺው፤ በገነት ካለውስ ዕፅ ሁሉ እንበላለን ፤

፫፥ ወባሕቱ እምፍሬ ዕፅ ዘሀሎ ማዕከለ ገነት ይቤለነ እግዚአብሔር ከመ ኢንብላዕ እምኔሁ ፣

አዘዘነ ሲል ነው፤ ነገር ግን በገነት ካለው ዕፀ በለስ እንዳንበላ አዝዞናል ፤

ወከመ ኢንግሥሦ ፣

እንኳን ልንበላው እንዳንነካው አዝዞናል ፤

ከመ ኢንሙት ይቤ፣

ይኸውም ነፍሳን ተመቅኝቶን አይደለም ፣ እንዳንሞት ብሎ ነው ፤



፬፥ ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት አኮ ሞተ ዘትመውቱ፣

ዲያብሎስ ሔዋንን እንዲህ አላት ፣ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎስ አይደለም ፤

፭፥ አላ እስመ የአምር እግዚአብሔር ከመ አመ ዕለተ ትበልዑ እምኔሁ ይትፈታሕ አዕይንቲክሙ ፣

ከዚህ ዕፀ በለስ በበላችሁ ጊዜ ዓይነ ልቡናችሁ እንዲገለጽ ያውቃልና ፤

ወትከውኑ ከመ እግዚአብሔር፣

እንደ እሱ የባሕርይ አምላክ እንድትሆኑ ያውቃልና፤

ወተአምሩ ሠናየ ወእኩየ፣

ክፋውን መልካሙን እንድታውቁ ያውቃልና ስለዚህ ነው እንጂ፣ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎስ አይደለም አላት፤ (ሐተታ) ጣዖት መስበክ ጀመረ፤ ከአዳምና ከሔዋን የሚወለዱ ዜውስ አርጤምስ የሚመለኩ ናቸውና ፤

(ታሪክ) ይኽንንስ ሁሉ ከወዴት አግኝቶ ነግሮአታል ? ቢሉ ፤ አዳምና ሔዋን ሰባት ዓመት በገነት ሲኖሩ ሰይጣን በምን ምክንያት ላስታቸው ? እያለ ምክንያት አጥቶ ሲጠባበቃቸው ይኖር ነበር፤ እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ፣ ስም ለመሰየም ወደ አዳም ሲመጡ በጉዳና አገኛቸው፤ እስከ ሰባት ዓመትስ ስም ሳይሰየሙ አይቀሩም ብሎ ለደጅ ጥናት ለተልእኮ ይመጡ ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን፣ ለደጅ ጥናት ለተልእኮ መጥተው ሲመለሱ በጉዳና አገኛቸው ፤ ወደ እሪያ ቢቀርብ፣ አፍርሆ ወአደንገዖ ይላል፣ አስፈራው አሳስቀረበውም፤ ፈቀቅ ብሎ ቁሞ ፣ አይቴ ሖርክሙ ውሉደ መሬት ወዴት ሄዳችሁ ነበር አላቸው ፤ ከጌታችን ከንጉሥ ከኵሉ ከአዳም ዘንድ ደጅ ልንጠና አሉት፤ ምንተ ይቤለክሙ አዳም፤ አዳም ምን አላችሁ ? ምን ነገራችሁ ? አላቸው፤ ያለንም የለ አሉት፤ እንዲያውሳ ጥቂት ምን ነገራችሁ ? አላቸው ፤ ከኛ አንዳችን አርደህ ብላ፤ አልበህ ጠጣ ብንለው፣ እኔስ እንበለ አሐቲ ዕፅ ከአንዲት ዕፅ በቀር የከለከለኝ የለም ፤ ሁሉን ግዛ ንዳ፣ ሁሉን ብላ ጠጣ ብሎ ሰጥቶኛል፤ ይኽችንም የከለከለኝ ነፍጎኝ ተመቅኝቶኝ አይደለም፣ ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ እንዳልሞት ነው እንጂ አለን አሉት ፤ ያን ጊዜ ምንኛ ከአፋፍ ላይ ቁሞልኛል ? ከአፋፍ ላይ የቆመን ሰው ገፍቶ መጣል ያቅታልን ብሎ እንዲያስተው ዓወቀ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሲያስታቸውስ በምን አድሮ አስቶአቸዋል ? ቢሉ ፤ ለአዳም ተድላ ደስታ ሊሆን መልኩ ያማረ መዓዛው የሠመረ እባብ ተፈጥሮ በገነት ይኖር ነበር ፤ በእሱ አድሮ አስቶአቸዋል ፤ ይህስ አይደለም ፤ በገነት ከአዳምና ከሔዋን በቀር ሌላ ፍጥረት አልነበረም ብሎ መልክዋ ያማረ፣ መዓዛዋ የሠመረ እባብ፣ የግመል ወሳብሬ ያህል ሁና ተፈጥራ ነበር ፤ በእስዋ አድሮ አስቶአቸዋል፤

ይኸስ እንደምን ነው ቢሉ፤ ስም ለመሰየም ስትመጣ ከጐዳና አገኛት፤ እስከ ሰባት ዓመትስ ስም ሳትሰየም አትቀርም ብሎ ለደጅ ጥናት፣ ለተልእኮ ስትመጣ በመንገድ ተገናኙ፣ ወዴት ትሂጃለሽ ? አላት ፤ ከጌታዬ ከንጉሡ ኰሉ ከአዳም ዘንድ አለችው ፤ መልካም ነዋ አብረን እየተጫዋወትን እንሂድ አላት፤ ነገሩስ ደግ ነበር፣ ምን ይሆናላ የእኔ መልክ ያማረ፣ መዓዛዬ የሠመረ ነው፣ ያንተ መልክህ የከፋ መዓዛህ የከረፋ ነው ፣ እንደምን ይሆናል ? አለችው ፤ እንግዲያው መልካሙ የት ላይ ነዋ ፤ ያንቺ መልክ የኔን ክፉ መልክ ያስወድደዋል፣ ያንቺ መዓዛ የኔን ክርፋት ይለውጠዋል ያስመስግነዋል ብሎ በከንቱ ውዳሴ ልብዋን ደቃት (ጠለፋት) ፤ በከንቱ ውዳሴ የማይነደፍ የለምና እርስዋም በከንቱ ውዳሴ ተነደፈች፤ ተከታትለው ሲሄዱ የዚህች የገነት ጐዳናዋ አቀበትዋ አይመችም ጐጻጉጽ ነውና በዚህ ጐዳና እንወቅበት አላት፤ ምን እናድርግ አለችው፤ ፊት አንቺን ልዘልሽ ፣ ኋላ እኔን ታዝሊኛለሽ አላት ፤ አዝሏት ሄዶ እኩሌታ ጐዳና ሲደርሱ፣ ፍዳ ያርኩኪ ፀሩኒ ፣ እንዳዘልኩሽ እዘሊኝ አላት፣ አዘለችው፤ ቅቤ ከጋለ ደንጊያ ላይ ሲያኖሩት ቀልጦ እንዲሠርፅ፣ በእስዋ ሥጋው ሆኖ ሄደ ፤ ከአዳም ዘንድ ሲደርስ በሐከ ኦ አዳም ንጉሠ ሰማይ ወምድር፣ የሰማይና የምድር ጌታ አዳም እንዴት አደርክ ? እንደምን ውለህ አድረኻል ? አለው ፤ አዳምም ፍልጥ አርዌ ምድር፤ ንጉሠ ምድር ነኝ እንጂ፤ ንጉሠ ሰማይ ነኝን አለው ፤ አንድም መላእክት ጊዜያት (አቀጣሮ) አስተምረውት ነበርና ያን እስኪጨርስ ዝም አለው ፤ አንድም የወንድ ልጅ አእምሮው ህዱእ ነውና ዝም አለው ፣ ነገሩን አልተቀበለውም ፤

ነገሩን እንዳልተቀበለውና ደስ እንዳላሰኘውም አይቶ ወደ ሔዋን



ቢሄድ፣ እርስዋንም ሥራ ፊትታ እግርዋን ዘርግታ፣ እጅዋን በጭንዋ ላይ አፋትላ (አነባብራ) አገኛት ፤ በሐኪ ኦ ሔዋን ንግሥተ ሰማይ ወምድር አላት ፤ ሴቶች ውዳሴ ከንቱ ይወዳሉና ይህን ቢላት ደስ አላት ፤ ነገሩን እንደተቀበለችው አይቶ ፣ ምን ምን ብሉ ብሎአችሁአል ? አላት ፤ እርስዋም ከአንዲት ዕፅ በቀር ሁሉንም ብሉ ብሎናል ፤ ያቺንም የከለከለን ነፍጎን ተመቅኝቶን አይደለም፣ የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎ ነው እንጂ አለቻው፤ እርሱም የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎስ አይደለም፣ አምላክ ትሆናላችሁ ብሎ ነው እንጂ ብሎአታል ፤ እርስዋም መልስ ሳላት መልስ እንደሌላት ሆናለች፤ ይህን ዕፀ በለስ ብትበሉ የባሕርይ አምላክ ትሆናላችሁ ቢላት፣ በቅጠል የባሕርይ አምላክ መሆን የሚገኝ ከሆነማ፣ አንተ በልተኸው የባሕርይ አምላክ አትሆንምን? ብትለው መልስ ነበርና፤ ቢጠላችሁ እንጂ ነው ቢላት፣ ከጠላን ፍጠረን ሳንለው ለምን ፈጠረን ? ብትለው መልስ ነበረ ፤ ቢመቀኛችሁ እንጂ ቢላት ፣ ከተመቀኘንማ ሁሉን ብሉ ሁሉን ግዙ መቼ ይለን ነበር? ብትለው መልስ ነበርና መልስ ሳላት መልስ እንደሌላት ሆነች፤ ይህንንስ በምን ቋንቋ ነገሮአታል ቢሉ ዓለም በተፈጠረበት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነግሮአታል፤ ከዚያ አስቀድሞ በአንድ ቋንቋ ይናገሩ ነበርና ፤ ወይትናገሩ አሐደ ከንፈረ ፣ እንዲል ፤ አንድም የሁሉም ቋንቋ ተገልጾላቸው ያውቁ ነበር፤ ዘአዕዋፍ ድምፀ ፣ ወዘአራዊት ንቃወ፤ በመንፈስ ቅዱስ ያዕቆብ ለበወ ፤ እንዲል ፤

፮፤ ወሶበ ርእየት ብእሲት ከመ ሠናይ ዕፁ ለበሊዕ ወሠናይ ውእቱ ለአዕይንት ወለርእይ፣ ወሠናየ ያጤይቅ፣

ሔዋንም፣ ዕንጨቱ ሊበሉት የሚያስጐመጅ፣ አይተውትም ለዓይን ደስ የሚያሰኝ፣ በጎውንም ነገር የሚያሳውቅ እንደሆነ ባየች ጊዜ ፤

ነሥአት እምኔሁ ወበልዐት፤ ወወሀበቶ ለብእሲሃ፣ ምስሌሃ ወበልዑ ፣

ለአዳም ሰጠችው ፣ አብረውም በሉ፤ (ሐተታ) ሲበሉትስ እንደ ምን አድርገው በልተውታል? ቢሉ፤ ጥንቱንም ከፍጡር ከአዳም በታች አድርጎ ፈጥሮሻል፣ አሁንም ከእርሱ በላይ እንድትሆኚ፣ አስቀድመሽ አንቺ ብዪ፤ ከዚህ በኋላ ለርሱ ስጭው ብሎአታል ፤ አንድም የእርስዋ

www.ethiopianorthodox.org

ጸጋ ሲገፈፍ አይቶ እርሱ ያመ ልጠኛል ብሎ ሔዋን ያምላክ ነት ሥራ እንዲህ አይደለምና በቀኝ እጅሽ ለርሱ ሰጥተሽ በግራ እጅሽ አንቺ ይዘሽ ተያ ይታችሁ አንድ ጊዜ ብሉት ብሎአታል ፤

፯፤ ወተፈትሐ አዕይንቲሆሙ ፣

ዓይነ ልቡናቸው ተገለጠ ፤

ወአእመሩ ከመ ዕራቃኒሆሙ እሙ ንቱ፣

ዕራቁታቸውንም እንደሆኑ አወቁ ፤ ዲያብሎስ የበጎ አስመ ስሎ ነግሮአቸው ነበር፣ የክፉ ሆኖባቸዋል ፤

ወኃፍኑ ወሰፈዩ ቈጽለ በለስ ፣

አፍረው የበለስ ቅጠል ሰፍተው ለበሱ ፤

ወገብሩ ሎሙ መዋርዕተ፣

ድኮ ጉለኛ ማገጠቆ አድርገው ዕርቃናቸውን ሠወሩ ፤

፰፤ ወሰምዑ ቃለ እግዚአብሔር እንዘ ያንሶሱ ፍና ሠርክ ውስተ ገነት፣

በሠርክ ጊዜ ጌታ በገነት ውስጥ ድምፀ ሰኰና ብእሲ እያሰማ ወደነርሱ ሲመጣ በሰሙ ጊዜ፤

ወተኃብኡ አዳም ወብእሲቱ እምቅ ድመ እግዚአብሔር ማዕከለ ዕፀዊሃ ለገነት ፣

ከእግዚአብሔር ፊት በገነት እንጨት መካከል ተሠወሩ ፤

(ሐተታ) ስለምን ቃል እያሰማ መጣ ቢሉ ፣ እንዳይደነግጡ እንዳይፈሩ ብሎ ነው ፤ እነሆ አሁን ዛሬ ሰው ባለቤትም ሆነ ጐረቤት ከውጭ ሲመጣ ከቤት ያለ ሰው ዕራቁቱን ቢሆን ጉዳይም ቢያደርግ ፣ እንዳያ ፍር እንዳይደነግጥ ቃል እንዲ ያሰማ ፤ አንድም ሁለተኛ ከመ በደል ለማዳን ፤ ኃጢአት ሠር ተው ዝም ብሎአቸው ቢሆን አላወቀብንም ብለው ሁለተኛ በበደሉ ነበርና ፤ አንድም ፈጽሞ እንዳልተጣላቸው ሲያጠይቅ ነው፤ በሠርክም መሆኑ ሰኰና ብእሲም ማሰማቱ አምስት ሺሕ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ፣ ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ አድንሃለሁ ሲል ነው ፤

፱፤ ወጸውዖ እግዚአብሔር ለአዳም ወይቤሎ አይቴ ሀሎከ አዳም ፣

እግዚአብሔርም አዳምን ጠርቶ አዳም ወዴት አለህ ? አለው ፤ (ሐተታ) ያለበትን የማያውቅ ሆኖ አይደለም ፣ ሊያናግረው ቢሻ እንዲህ አለ እንጂ፤ አን ድም በኋላ ዘመን አላዋቂ ሥጋን ተዋሕጄ አድንሃለሁ ሲል ነው፤ ይህንንም አይቴ ቀበርክምዎ ለአልዓዛር ካለው ጋራ አንድ ነው ብሎ ቅዱስ ቄርሎስ አስ



ማምቶታል ፤ ሃይ. አበ. ቄር ድርሳን ፤ አንድም እንደምን ባለ አንዋዋር አለህ ? በክብርን ነው ወይስ በኃሣር ነህ? አለው፤ አንድም ያን የፈለግኸውንስ አምላክነት ተከፍክፈኸው አረ ፍኽ ? ሲለው ነው ፤

፲፤ ወይቤ አዳም ቃለከ ሰማዕኩ እንዘ ታንሶሱ ውስተ ገነት ወፈራህኩ እስመ ዕራቅየ አነ ወተኀባእኩ ፣

አዳምም ወደኔ ስትመጣ በገ ነት ውስጥ ቃልኽን በሰማሁ ጊዜ እኔ ዕራቁቴን ስለሆንኹ ፈርቼ ተሠወርኹ አለ፤

፲፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር መኑ አይድዐከ ከመ ዕራቅከ አንተ፣

እግዚአብሔርም ራቁትህን መሆንህን ማን ነገረህ ? የነገረህ ማነው ? አለው ፤ አንድም ዕራ ቁትህን የምትሆንበትን ዕፀ በለስ ብላ ብሎ ማን ነገረህ ? ማን ብላ አለህ ?

እምዕፀ ዘአዘዝኩከ ከመ ኢትብላዕ እምኔሁ የጊ በላዕከ ፣

አትብላ ያልኹኽን ዕፀ በለስ ምንአልባት በልተህ ይሆን ?

፲፪፤ ወይቤ አዳም ብእሲት እንተ ወሀብከኒ ምስሌየ ትንበር ይእቲ ወሀበተኒ ወበላዕኩ ፣

አዳምም ካንተ ጋራ ትኑር ብለህ የሰጠኸኝ ሔዋን አታላ ሰጠችኝ በላሁ አለ ፤

፲፫፤ ወይቤላ እግዚአብሔር ለብእ ሲት ለምንት ገበርኪ ዘንተ፣

እግዚአብሔርም ሔዋንን እን ደዚህ ያለውን ነገር ለምን አደረግሽ ? አላት ፤

ወትቤ ብእሲት፣ አርዌ ምድር አስ ፈጠተኒ ወበላዕኩ፣

ሔዋንም አርዌ ምድር (እባብ) አታለለችኝ በላሁ አለች፤

፲፬፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር፣

እግዚአብሔርም አርዌ ምድርን እንዲህ አለው፤ ምክንያተ ስሕ ተት የሆነ እሱ ነውና መርገምን በእሱ ይጀምራል ፤

እስመ ገበርከ ለዝንቱ ርጉመ ኩን እምኵሉ እንስሳ ወእምኵሉ አራዊተ ምድር ፣

ይህን ሥራ ስለ ሠራኸው በዚህ ዓለም ካሉ ከአራዊት፣ ከእንስ ሳት ሁሉ ተለይተህ ርጉም ሁን፤

ወበእንግድዓከ ሑር፣

በልብህ ተስበህ ሂድ አለው ፤ (ሐተታ) እንዲህ ባለው ጊዜ እግሩ ተሰብስቦ ተጠቅልሎ ከሆዱ ገብቶ በመሬት እየተሳበ የሚ ሄድ ስለሆነ አርዌ ምድር ተብ ሎአል ፤

ወመሬተ ብላዕ ኵሎ መዋዕለ ሕይ ወትከ ፣

ባለ ዘመንህም ሁሉ ምግብህ መሬት ይሁን አለው፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

ኵሎ መዋዕለ ሕይወትከ አስተ ፃርር ብለህ ወደ ታች ግጠም፤

፲፭፣ አስተፃርር ማዕከሌከ ወማዕከለ ብእሲት፣

ባለ ዘመንህ ሁሉ በአንተና በሔ ዋን መካከል ፤

ማዕከለ ዘርእከ ወማዕከለ ዘርኣ፣

በሔዋን ልጆችና በአንተ ወገኖች መካከል ፀብን አጸናለሁ፤

ወውእቱ ይዕቀብ ርእሰከ፣

እርሱ ጠብቆ ራስ ራስህን ይቀ ጥቅጥ፤

ወአንተ ዕቀብ ሰኰናሁ ፣

አንተም ጠብቀህ እግሩን ንደ ፈው ብሎ ረገመው፤ (ሐተታ) ይህም ሊታወቅ፤ እባብ ራሱን ካልመቱት አይሞትም ፤

፲፮፣ ወለብእሲትኒ ይቤላ እግዚአብ ሔር አብዝኆ አበዝኆ ለኃዘንኪ ወለ ሥቃይኪ ፣

ሔዋንንም እግዚአብሔር እን ዲህ አላት፤ ኃዘንሽን፣ ፃዕርሽን አበዛዋለሁ ፤

ወበፃዕር ለዲ ኵሎ መዋዕለ ሕይወ ትኪ ፣

በምትወልጂበት ጊዜ ሁሉ በፃር በጋር ውለጂ ፤

ወወሊደኪ ይኩን ምግባእኪ ኀበ ምትኪ ፣

በፃር በጋር ከወለድሽም በኋላ፣ መመለሻሽ ወደ ባልሽ ይሁን፤

ወውእቱ ይቀንይኪ ፣

ከመ ትኩኒ እግዝእቶ ብሎዋት ነበርና ገዥሽም ይሁን፤ አንድም ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር ብለህ መልስ፤ ጌታ ዲያ ብሎስን እንዲህ አለው፤ ይህን ነገር ስለአደረግኸው ከሕዝቡ ከአሕዛቡ ተለይተህ ርጉም ሁን፣ የክሕደት ነቅዑ እርሱ ነውና መርገምን በርሱ ይጀምራል፤ ዓመፃ ወዕአት እመዛግብቲሃ እን ዲል ሄኖክ ፤ ባለ በዘመንህ ሁሉ ተዋርደህ ኑር፣ ወብላዕ መሬተ፤ ኀሡር ጒስቋላ ሁን፤ አስተፃርር ባንተና በመምህራን መካከል ፤ በወገኖ ችህና በደቀ መዛሙርቶቻቸ ውም መካከል ፀብ ክርክርን አመጣለሁ፤ እነዚያም ጠብቀው በመስቀል ራስ ራስህን ይቀጥቅ ጡህ አለ ድል ይነሡህ ፤ አን ተም ሰኰና ሕሊናቸውን ለማ ሳት ጠብቃቸው ፤ (ወለብእሲ ትኒ ይቤላ) ጌታ መምህራንን ጥራችሁ ግራችሁ ምግባር ትሩ ፋት ሥሩ አላቸው ፣ ምግባር ትሩፋትም ከሠራችሁ በኋላ ጸጋውን ክብሩን ለማግኘት መመለሳችሁ ወደ እኔ ይሁን ፤ ዋጋችሁንም የምሰጣችሁ እኔ ነኝ ፤ አንድም ምእመናንን ጥራችሁ ግራችሁ ምግባር ትሩ ፋት ሠርታችሁ ጸጋ ለማግኘት



መመለሳችሁ ወደ እኔ ይሁን፤ ዋጋችሁንም የምሰጣችሁ እኔ ነኝ አላቸው ፤

፲፯፡ ወለአዳምኒ ይቤሎ እግዚአብ ሔር ፣

አዳምንም እግዚአብሔር እን ዲህ አለው ፤

እስመ ሰማዕከ ቃለ ብእሲትከ ወበ ላዕከ እምውእቱ ዕፅ ባሕቲቱ ዘአዘ ዝኩከ ከመ ኢትብላዕ፣

ከዚያ ዕንጨት ብቻ እንዳትበላ፤ አትብላ ብዬ ካዘዝኩኽ ዕንጨት የሚስትህን ቃል ሰምተህ በል ተሃልና ፤

ርግምተ ትኩን ምድር በተግባርከ፣

ምድር በሥራህ የተረገመች ትሁን፤ አንድም በዘር በሩካቤ የተወለዱ ልጆችህ የተረገሙ ይሁኑ ፤

ወበፃዕር ብላዕ ኵሎ መዋዕለ ሕይ ወትከ፣

ባለ በዘመንህ ሁሉ ጥረህ ግረህ ብላ ፤ አንድም ምግባር ትሩ ፋት ሠርተህ ጸጋ ክብር ተቀ በል ፤

፲፰፡ አሥዋከ ወአሜከላ ይብቍልከ፣

እሾህ አሜከላ ይብቀልብህ ፤ (ሐተታ) እንዲህ ባለው ጊዜ በምድር የበቀሉ ዕፀዋት እሾ ኹን የሚኰሰኵሰውንም ነገር ሁሉ አስገኝተዋል፤ ሦክ ወአሜ ከላ ባለው ተርቢሎስ ይላል ፣ ሦክ ወአሜከላ ማለት ነው ፤ አንድም በሆድ ውስጥ ያሉ ተሐዋስያን ናቸው ፤

ውብላዕ ሣዕረ ገዳም ፣

አርሰህ ቈፍረህ እህል ተመገብ፤ አንድም መክረህ አስተምረህ ዋጋህን ጸጋ ክብር አግኝ፤ ይደ ልዎ ዐስቡ ለዘይትቀነይ እንዲል (ማቴ.፲:፲) ፤

፲፱፡ ወበሐፈ ገጽከ ብላዕ ኅብስተከ እስከ ትገብእ ውስተ መሬት እንተ እምኔሃ ወፃእከ ፣

ወደተገኘኸባት መሬት እስክት መለስ ድረስ፣ ጥረህ ግረህ ደክ መህ ብላ፤ አንድም ንስሐ ገብ ተህ ምግባር ትሩፋት ሠርተህ ሥጋውን ደሙን ተቀበል፣ ኅብ ስተከ ማለቱ የሚሰጥ በኅብስ ትነት ነውና ፤

እስመ መሬት አንተ ወውስተ መሬት ትገብእ ፣

ጥንቱን ከመሬት ተገኝተሃልና እስከ ትገብእ ይለዋል፤ አንድም ከመሬት ተገኝተሃልና ወደ መሬ ትነትህ ትመለሳለህ ፤

፳፡ ወሰመየ አዳም ስማ ለብእሲቱ ሔዋን ፣

አዳምም የሚስቱን ስም ሔዋን ብሎ ጠራት ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ይእቲ እሞሙ ለሕያዋን ፤

የሕያዋን እናት ናትና፤ ይህስ
አይደለም አትብዩ ያላትን ዕፀ
በለስ በልታ እመ ምውታን ተብ
ላለች ብሎ እመቤታችን በን
ጽሕና በድንግልና ጸንታ ተጠ
ርታበታለችና ፤ እሞሙ ለኩ
ሎሙ ሕያዋን እንዲላት፤ (ውዳሴ
ማርያም ዘሠሉስ) ፤ አንድም
የሕያዋን የጌታና የእመቤታ
ችን መገኛ ሁናለችና እርስ
ዋም ቅሉ ተጠርታበታለች ፤

፳፩፤ ወገብረ እግዚአብሔር ለአዳም
ወለብእሲቱ አእዳለ ዘማእስ ወአልበ
ሰሙ፤

ዘውእቱ ማእስ ሲል ነው ፤
እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋ
ንን ቍርበት አለበሳቸው ፤
(ሐተታ) ከወዴት አምጥቶ አለ
በሳቸው ? ቢሉ ፤ አንበሳ የሰበረ
ውን፤ ነምር የጫረውን አምጥቶ
አልብሶአቸዋል ፤ ወይትናገሩ
አሐደ ከንፈረ፤ እንዲል፤ ...ከሰ
ባት ዓመት አስቀድሞስ በአራ
ዊትና በእንስሳት መካከል ጠብ
የለም ብሎ እንስሳትን ያስገኘ
ጌታ ይህን ማስገኘት ይሳነዋ
ልን ? እምነበ አልቦ አምጥቶ
አልብሶአቸዋል ፤ አንድም ቅር
ፍተ ዕፅ ነው ፤ የፋርስ ነገሥ
ታት ቀለም እያገቡ በወርቅ
በብር እያስጌጡ ይለብሱት
ነበር ፤ አንድም አእዳለ ልብስ
ዘማእስ ሲል ነው፤ የአካላቸው
ልብስ የሚሆን ቍርበትን አለ
በሳቸው ፤

፳፪፤ ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ
አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ
ያእምር ሠናየ ወእኩየ ፤

እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፤
አዳም መልካሙንና ክፉውን
ለይቶ ያውቅ ዘንድ ከእኛ እንደ
አንዱ ሆነ አለ ፤ በፍና ተሣ
ልቆ ፤

ወይእዜኒ ዮጊ ያሌዕል እዴሁ ወይነ
ሥእ እምዕፀ ሕይወት ወይበልዕ ወየ
ሐዩ ለዓለም፤

ወይም እኮ ዛሬም እጁን ከፍ
ከፍ አድርጎ ከዕፀ ሕይወት በልቶ
በሕይወት ይኖር ይሆናል አለ፤
ወአውፅኦ ማንሻ፤ አንድም ወይቤ
እግዚአብሔር ብለህ መልስ ፤
አዳም መልካሙን ክፉውን ያውቅ
ዘንድ ከኛ እንዳንዱ ሆነ፤ አሁ
ንም አዳም እጁን ከፍ ከፍ አድ
ርጎ ከዕፀ ሕይወት አምጥቶ በልቶ
ለዘለዓለም በሕይወት ይኖር
ይሆናል ብሎ፤ አውፅኦ ብለህ
እሥር፤ አንድም አዳም ሥጋ
የባሕርይ ዕውቀትን ያውቅ
ዘንድ፤ ከእኛ አንዱን ወልድን
ኾነ፤ በመልዕልተ መስቀል እጁን
ዘርግቶ ተሰቅሎ፤ መከራ መስ
ቀልን ተቀብሎ የሐዩ በትን
ሣኤ፤ (ያሐዩ) ምእመናንን በዘ



ላለም ሕይወት ያኖራል፤ አን
ድም አዳም ምእመን ከእኛ
ተወልዶ (ኮነ ከመ አሐዱ) በል
ጅነት ለኛ አካል ብልት ሆነ፤
(ወይእዜኒ)፤ አሁንም እደ ልቡ
ናውን ከፍ አድርጎ ንስሐ ገብቶ፤
ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ለዘ
ላለሙ ሕያው ሆኖ ይኖራል፤

፳፫፤ ወአውፅኦ እግዚአብሔር ለአ
ዳም እምገነተ ተድላ ፤

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር
አዳምን ተድላ ደስታ ካለበት
ከገነት አወጣው ፤

ከመ ይትገበሩ ለምድር እንተ እም
ኔሃ ወፅአ፤

የተገኘባትን መሬት ያርሳት
ይቈፍራት ዘንድ፤

ወአኅደሮ ቅድመ ገነተ ትፍሥሕት፤

ተድላ ደስታ ባለባት በገነት
አንጻር ባለ በደብር ቅዱስ፤ አኖ
ረው፤ (ሐተታ) ስለምን ቢሉ ገነ
ትን እያየ ኀዘን እንዲጸናበት
ብሎ፤ አንድም ተስፋ እንዳይቈ
ርጥ፤ የቀደመ ክብሩን የኋላ
ተዋርዶውን አይቶ ንስሐ እንዲ
ገባ፤

፳፬፤ ወአዘዞሙ ለኪሩቤል ወለሱራ
ፌል ዘውስተ እደዊሆሙ ሰይፈ እሳት
እንተ ትትመየየጥ ከመ ይዕቀቡ
ፍኖተ ዕፀ ሕይወት፤

የመላእክትን ተፈጥሮ አመጣ፤
ቦግ ቦግ የምትል፤ አንድም እንደ
በለው ሰይፍ እጥፍ ዘርጋ የም
ትል የእሳት ሰይፍ በእጃቸው
የተያዙት ኪሩቤልንና ሱራፌልን
ዕፀ ሕይወት ያለባትን የገነትን
ጐዳና ይጠብቁ ዘንድ አዘዛቸው፤
ፍኖተ ዕፀ ሕይወት ባለው ፍኖተ
ገነት ይላል፤ ሰይፈ እሳት ባለ
ውም ፤ ሐፀ እሳት ፤ ኲናተ
እሳት ይላል አብነት ፤ በቁሙ
ሐፀ እሳት ኲናተ እሳት ነው፤
አንድም ሥልጣናቸው ነው ፤

ስለምን መላእክትን አስጠበቀ
በት ቢሉ ፤ ይህም ኀዘን ይጽና
በት ብሎ ነው፤ ፈጽሞ ቢጣላኝ
ነው እንጂ መላእክትን ያስጠ
ብቅብኝ ነበርን ብሎ እንዲ
ያዝን ፤ አንድም ተስፋ እንዳ
ይቈርጥ ፤ ፈጽሞ ቢጣላኝማ
ለሌላ ይሰጥብኝ አልነበረምን?
መቼ መላእክትን ያስጠብቅ
ልኝ ነበረ ? ብሎ ንስሐ እንዲ
ገባ ፤ (ሐተታ) የመላእክት
ተፈጥሮ ከምን ነው ? ቢሉ
ከነፋስ ከእሳት ነው ፤

ወሶበ አንተ ኢየእኩትከ ለዘፈጠ
ረከ እምነበልባለ እሳት ወእምነፋስ
ፈጠረ ህየንቴከ ሰብአ ዘማሬ እማይ
ወእመሬት እንዲል ፤ (መቃ.
ሣልስ ፪:፲-፲፩ ፤ ፫:፯-፲) ፤

ከዕለተ እሑድስ አስቀድሞ ግብር
እምግብር የተፈጠረ የለም ብሎ
እንደ ነፋስ፤ እንደ እሳት የሚ
ራቀቁ የሚፋጠኑ ስለሆነ እን

www.ethiopianorthodox.org

ዲህ አለ እንጂ፣ ተፈጥሮአቸ ውስ እምኀበ አልቦ ነው ፤ አንድም ነፋስ ፣ እሳት ፈጻም ያነ ፈቃድ ናቸው ፤ በነፋስ ጥቅመ ሰናያርን ገልብጦ ጥሎ በታል፤ በእሳት ሰዶም ገሞራን አጥፍቶበታል፤ እንደዚህም ሁሉ መላእክት በየጊዜው ፈቃዱን ይፈጽማሉና እንዲህ አለ ።

## ምዕራፍ ፬

### ገባኤ

፩፤ ወአእመራ አዳም ለሔዋን ብእሲቱ ፣

አዳም ሚስቱን ሔዋንን በግብር አወቃት፤ (ሐተታ) ይህም እንዲያው አይደለም ፤ አዳም ንስሐ ገብቶ መቶ ዘመን አለቀሰ ፤ በኃሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እም ወለተ ወለትከ ብሎ ተስፋውን ነገረው ፤ ይኸማ ያለ ሩካቤ ይሆናልን ? ብሎ በግብር አወቃት ፤ አንድም መልአኩ ነግሮታል ፤

ወፀንሰት ወወለደቶ ለቃየል ፣

እርስዋም ፀንሳ ቃየልን ወለደች፤

ወትቤ አጥረይኑ ብእሴ ዘእግዚአብሔር ፣

ከእግዚአብሔር ዘንድ ወንድ ልጅ አገኘን ስትል ቃየል አለቺው፤ (ሐተታ) ቃየል ማለት ጥሪት ማለት ነው፣ ላባት ለናቱ ጥሪት ሆኖ ተሰጥቶአልና፤ አንድም ክፍለት ተጋብአ ማለት ነው ፣ ሲወለድ ከአባት ዘር ከእናት ደም ተከፍሎ ነውና፤ አንድም በኵረ ቀታልያን ማለት ነው ፤

፪፤ ወደገመት ወወለደቶ ለአቤል እኁሁ ፣

ዳግመኛም ወንድሙን አቤልን ወለደች፤ አቤል ማለት በግዕ፣ ደመና ማለት ነው፤ አንድም በኵረ ምውታን ማለት ነው፤

ወኮነ አቤል ኖላዌ አባግዕ ፣

አቤል በግ ጠባቂ ሆነ፤ አሁን ጠጕሩ ያላረረውን፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን፣ ቀንዱ ያልከረከረውን፣ የሰባውን ሠዋ የሚለው ነውና እንደ አርእስት አነሣው፤

ወቃየልሰ ኮነ መስተገብረ ምድር ፣

ቃየል ግን ምድርን የሚያርስ የሚቈፍር ገበሬ ኾነ ፤ አሁን አባር የመታውን ያልተለቀመውን ሠዋ የሚለው ነውና እንደ አርእስት አነሣው ፤ (ሐተታ) ያንጊዜ እርሻ ቁፋሮ ኑሮ አይደለም፣ ለታብቀኍል ባለው የተገኘውን ዘር፣ ተክል የሚያርም፣ የሚኰተኵት ስለሆነ ኮነ መስተገብረ ምድር ብሎታል ፤



፫፤ ወኮነ እምድኅረ ብዙኅ መዋዕል፣

ከብዙ ቀን በኋላ እንዲህ ኾነ፤

አምጽአ ቃየል እምፍሬ ምድር መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ፣

ቃየል ምንጊዜስ እግዚአብሔር ይበላው ይመስል ብሎ ዓባር የመታውን ያልተለቀመውን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አቀረበ፤

፬፤ ወአቤልሂ አምጽአ መሥዋዕተ እምበኵረ አባግዒሁ ወእምስቡሐኒሆሙ ፣

አቤል ግን እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነው ፤ ንጹሕ ነገርን ይወዳል ብሎ፣ ቀንዱ ያልከረከረውን፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን፣ ጠጕሩ ያላረረውን፣ ዓመት የሆነውን በግ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ፤

አቤልሰ አሥረፀ (አብቈለ) ጽድቀ እምነፍሱ እንዲል ፣

ወነጸረ እግዚአብሔር ላዕለ አቤል ወላዕለ መሥዋዕቱ ፣

እግዚአብሔርም አቤልን በዓይነ ምሕረት አየው ፤ መሥዋዕቱንም ወዶ ተቀበለለት ፤

፭፤ ላዕለ ቃየልሰ ወላዕለ መሥዋዕቱ ኢነጸረ ፣

ቃየልን ግን፣ በዓይነ ምሕረት አላየውም፤ መሥዋዕቱንም ወዶ አልተቀበለለትም፤

ወአኅዘኖ ለቃየል ጥቀ ፣

መሥዋዕቱ ሳያርግለት መቅረቱም ቃየልን እጅግ አሳዘነው፤

ወወድቀ ገጹ ፣

ልቡ አዝኖ ፊቱ ጠቈረ፤ ኢይደቅ ልቡ ለእግዚእየ እንዲል፤ (፩ኛ.ሳሙ. ፣ ፲፫-፴፪) ፤ አንድም ወወድቀ በገጹ ይላል፣ አንገቱን ደፋ አዘነ ተቈረቈረ፤

፮፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለቃየል ለምንት ተነዝን ፣

ጌታ ቃየልን እንዲህ አለው፤ ለምን ታዝናለህ ፤

ወለምንት ወድቀ ገጽከ ፣

ልቡናህስ ለምን አዘኖአል ? ወደቀ በገጽከ ይላል ፣ አንገትህንስ ለምን ደፍተሃል ?

፯፤ አኮ በጽድቅ ዘአምጻእከ ሊተ ፣

መሥዋዕቱን፣ በሚገባ የሠዋህልኝ አይደለም ፤

ወርቱዕሰ በጽድቅ ታምጽእ ሊተ ፣

የሚገባውስ በእውነት ልትሠዋልኝ ነበር ፤

አበስከ እንከ አርምም ፣

በደልህ፣ እንግዴህ ወዲህ ዝም በል ፤

ውነቤከ ምግባዒሁ ለእኁከ ፣

ወንድምህ ከሕይወት ወደ ሞት መመለሱ በአንተ ነው፤ አንድም

www.ethiopianorthodox.org

በሞት ወደ መቃብር መመለሱ በአንተ ነው፤ አንድም ውነቤከ ምብጸሒሁ ለእኑከ ይላል፤ ወንድምህ ለሞት የሚደርስበት ደንጊያ በአንተ እጅ ተይዟል ፤

ወአንተ ትኴንኖ፣

ትቀትሎ ሲል ነው፣ ወንድምህን አንተ ትገድለዋለህ፤

ወይቤሎ ቃየል ለአቤል እኁሁ፣ ነዓ ንሑር ሐቅለ ፣

ቃየልም፣ ወንድሙን አቤልን፤ እህሉን ተክሉን ጉብኝተን እሸቱን እንኩቶውን በልተን ውሃ ጠጥተን እንምጣ ና ወደ ዱር እንሒድ አለው ፤

፰፤ ወኮነ እንዘ ሀለዉ ገዳመ ተንሥአ ቃየል ላዕለ አቤል እኁሁ ወቀተሎ፣

በዱር ሳሉ ቃየል በጠላትነት ተነሥቶ ወንድሙን አቤልን ገደለው፤ (ታሪክ) ይህስ እንደ ምን ነው ቢሉ፤ ሔዋን መንታ መንታ እያደረገች ወልዳለች፤ የወለደቺውም ፲፭ት ጊዜ ነው ቢሉ ሠላሳ ይሆናሉ፤ ፴ ጊዜ ነው ቢሉ ስድሳ ይሆናሉ፤ ቃየልና ሉድ ፤ አቤልና አቅሌማ፣ መንትያዎች ናቸው ፤ አካለ መጠን ባደረሱ ጊዜ አዳም ሔዋንን ጠርቶ፤ አ ሔዋን ወርዘዉ ደቂቅኪ፤ ልጆችሽ አደጉ እናጋባቸው አላት፤ እርስዋም ይሁን እሺ አለችው፤ አዳምም፣ እኅትና ወንድም አይጋቡ የምትል ሕግ እንድትሠራ በሕገ ልቡና ተገልጾለት ያራራቅሁ መስሎት የቃየልን መንትያ ለአቤል ፤ የአቤልን መንትያ ለቃየል ትሁን አለ ፤ ቃየልም የኔን መልካም ለሌላ፤ የሌላውን ክፉ ለኔ እንደምን ይሆናል? ብሎ አዘነ ፤ ሉድ ወትመስል ሔዋንሃ እማ ይላል ፤ መልክ ከደም ግባት አስተካክላ የያዘች ናት፤ አቅሌማ ዓይነ መፍጠምጫ ጠጉረ ላሁጫ ናት፤ አዳምም ይህን ሰምቶ መሥዋዕት ሠዉና መሥዋዕቱን የተቀበለለት ሉድን ያግባ አለ፤ አቤል እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነው፣ ንጹሕ ነገርን ይወዳል ብሎ፣ ጠጉሩ ያላረረውን፣ ዓመት የሆነውን የሰባውን ሠዋ ፤ መሥዋዕቱን ተቀበለለት፤ ቃየል ግን፣ እግዚአብሔር ይበላው ይመስል ብሎ ዓባር የመታውን፣ ያልተለቀመውን መሥዋዕቱን ሠዋ፣ ሳይቀበልለት ቀረ ፤ እያዘነ ሲሄድ ሰይጣን ከመንገድ ቈይቶ፣ አ አዛል ብእሲ ምንት ያቴክዘከ አለው ፤ እኔ ያላዘንሁ ማን ይዘን ፤ አባቴ ቢያደላ በእኔ ፤ እግዚአብሔር ቢያደላ በእኔ አለው ፤ ወንድምህን አትገድለውምን ሁለቱስ ለማን ይሆ



ናሉ አለው ፤ ለካ እንዲህ ያለም ነገር አለ ? ብሎ ከዚህ አብነት ነሥቶ ገድሎታል ፤ አንድም አንዱ ሰይጣን በሰው አምሳል፣ አንዱ ሰይጣን በቀኊራ አምሳል ሁነው ያያቸዋል፤ በሰው አምሳል የሆነው ሰይጣን ደንጊያ ወርውሮ በቀኊራ አምሳል የሆነውን ሰይጣን ሲገድለው ያየል፤ ከዚህ አስቀድሞ ሞት ይወራ (ተጠርቶ) ነበር እንጂ ንዋየ ሞት (የሞት መሣሪያ) አልታወቀም ነበርና፣ ለካ እንዲህ ያለም ነገር አለ ? ብሎ ከዚህ አብነት ነሥቶ ገድሎታል፤ አንድም እሸቱን እንኩቶውን እንብላ ብሎ ወደ ዱር ይዞት ሂደ ፤ ከበሉም በኋላ ውሀ ለመጠጣት አብረው ወደ ወንዝ ወረዱ ፤ እንዳይጠረጥር ብሎ ቃየል አስቀድሞ ጠጥቶ አቤልን ጠጣ አለው ፤ ተጐንብሶ እጠጣለሁ ሲል በድንጋይ ፈጥፍጦ ገድሎታል ፤

፱፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለቃየል አይቴ ውእቱ አቤል እኁከ ፣

እግዚአብሔር ቃየልን ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? አለው፤

ወይቤሎ ቃየል ኢየአምር ቦኑ አነ ዐቃቢሁ ለአቤል እኁየ ፣

እኔ ምን አውቃለሁ በውኑ የአቤል ጠባቂው እኔ ነኝን? አለው፤

፲፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለምንት ገበርከ ቃየል ፣

እግዚአብሔርም ቃየልን ጠባቂው ካልሆንህ ለምን ገደልከው አለው ፤

ቃለ ደሙ ለአቤል እኁከ በጽሐ ኀቤየ እምድር ፣

ጽራኃ ደሙ ሲል ነው፣ የደሙ ጩኸት እነሆ ከምድር ወደ እኔ ደረሰ ፤ አንድም በቀለ ደሙ ሲል ነው፤ የደሙ በቀል ወደኔ ደረሰ ፤ አንድም ጽራኃ ነፍሱ ሲል ነው ፤ በማደሪያዋ ጠርቶ፣ እስመ ነፍስ ተኃድር በደም፣ እንዲል፤ ጩኸቱ እስከ ዐሥር ትውልድ ደረሰ፣ ሄኖክ እንዳየው ፤

(ታሪክ) እንደምን ነው? ቢሉ፣ መላእክት ለሄኖክ መዓርገ ነፍሳትን እያዞሩ ሲያሳዩት የአቤል ነፍስ ከዚያ ሁሉ ተለይታ ቃየል እኁየ ቀተለኒ እያለች ስትንጸረጸር ሰማት፤

ዘ ይእቲ ዘመኑ ነፍስ ? ብሎ ጠየቀ፤ ዘአቤል ዘቀተሎ ቃየል እኁሁ ኪያሁ ትስኪ እስከ አመ ይትኀጐሉ ዘርኡ እምገጸ ምድር ፤ ከዚህ ዓለም በማየ አይኅ ልጆቹ እስኪጠፉ ድረስ እሱን ትካሰሣለች ብለው ነግረውታል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወይእዜኒ ርግምተ ትኩን ምድር እንተ አብቀወት አፉሃ ከመ ትስተይ ደሞ ለእኁከ እምእዴከ ፨

አሁንም በአንተ እጅ የፈሰሰ የወንድምህን ደም የጠጣች ምድር የዘሩባትን አታብቅል፣ የተከሉባትን አታጽድቅ አለ ፡፡

፲፪፡ እስመ ትትጌበራ አንተ ፨

አንተ ታርሳታለህ ትቈፍራታለህና ፡፡

ወኢትወስክ ከመ ተሀብከ ኃይለ ፨

ፍሬውን ትሰጥህ ዘንድ የዘራህ ባትን አታብቅል፤ የተከልክባትን አታጽድቅ፤ (ሐተታ) ይኸውም አልቀረ፣ ዛሬም የሰው ደም የፈሰሰበት መሬት፣ ዘር ተክል አያበቅልም ፡፡

ርዑደ ወድንጉጸ ኩን ላዕለ ምድር፣

በዚህ ዓለም ብርር፣ ብርር እያልህ ኑር አለው፤ (ሐተታ) ይኸውም አልቀረ ፣ ዛሬም ነፍስ የገደለ ሰው ብርር ፣ ብርር ሲል ይኖራል ፡፡

፲፫፡ ወይቤሎ ቃየል ለእግዚአብሔር፣

ቃየልም እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፡፡

ተዓቢኑ ኃጢአትየ ዘእምትትኃደግ ሊተ ፨

ኃጢአቴ ከትሠረይልኝ ይልቅ፣ እየበዛች እየጸናች ትሂዳለችን? አለ ፤ (ሐተታ) ይኸውም ትዕቢት ነው፣ ንስሐ ሳይገባ እንዲህ ማለት፤

፲፬፡ ናሁ ታወፅአኒ እምድር ፨

እነሆ ከደብር ቅዱስ ታወጣኛለህ ፡፡

ወእምቅድመ ገጽከ እትኀባዕኑ ፨

ከባለሟልነትህም ትለየኛለህ ? እትኀባዕኑ ማንኛ፤ አንድም ከደብር ቅዱስ እነሆ ታወጣኛለህ? (ወእምቅድመ ገጽከ እትኀባዕኑ) ከዚያስ ብሄድ ከአንተ እሠወራለሁን ?

ወእከውን ርዑደ ወድንጉጸ በዲበ ምድር ፨

በዚህ ዓለም ብርር፣ ብርር ስል እኖራለሁ ፡፡

ወኵሉ ዘረከበኒ ይቀትለኒ ፨

ያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል አለ፤ (ሐተታ) ለእርሱ ስለመሰለው እንዲህ አለ፤

፲፭፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር አኮ ከማሁ ፨

እግዚአብሔርም ቃየልን ያገኘህስ ሁሉ የሚገድልህ አይደለም አለው ፡፡

ኵሉ ዘቀተሎ ለቃየል ሰብዓተ በቀለ ይቀውም ፨

ቃየልን የገደለ ሰው ሁሉ ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያለ



ፍጹም ፍዳን ይቀበላል፤ አንድም አሳ በሳብዕ ትውልድ እትቤቀለከ ይላል፣ አብነት፤ በሰባተኛው ትውልድ በላሜህ ተበቅዬ አጠፋሃለሁ እንጂ ያገኝህ ሁሉ የሚገድልህ አይደለም አለው ፡፡ (ሐተታ) ይኸውም የጌታ መዓቱ ነው እንጂ ምሕረቱ አይደለም፤ ወዲያው የሞተ እንደሆነ ፍዳው ይቀልለታል ፡፡ እስከ ሰባት ትውልድ የቈየ እንደሆነ ግን በኃጢአት ላይ ኃጢአት እየጨመረ፣ በፍዳ ላይ ፍዳ ይጨምርበታልና ፡፡

ወገብረ እግዚአብሔር ለቃየል ተአምረ ከመ ኢይቅትሎ ኵሉ ዘረከቦ፣

ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው እግዚአብሔር ለቃየል አዋጅ ነገረለት ፡፡ አንድም ምልክት አደረገለት፣ ዕንጨቱ ሣሩ ሁሉ ደም ሆኖ ታይቶታል ፡፡

፲፮፡ ወወፅአ ቃየል እምቅድመ ገጸ እግዚአብሔር ፨

ቃየልም ከደብር ቅዱስ ወጥቶ ከባለሟልነት ተለይቶ ፡፡

ወኃደረ ውስተ ምድረ ፋዩድ ዘአንጻረ ኤዶም ፨

በገነት አንጻር ባለ ፋዩድ በሚባል ቦታ ኖረ፤ (ሐተታ) ምድረ ፋዩድ ማለት፣ ምድረ ፍርሃት ወድንጋፄ፣ ምድረ ኃሣር ወመርገም ማለት ነው ፡፡

፲፯፡ ወአእመራ ቃየል ለብእሲቱ ፨

ቃየልም ሚስቱን በግብር ባወቃት ጊዜ ፡፡

ወፀንሰት ወወለደቶ ለሄኖህ ፨

ፀንሳ ሄኖህን ወለደች ፡፡

ወሐነፀ ሀገረ ፨

አገር አቀና ፡፡

ወሰመያ ለይእቲ ሀገር በስመ ወልዱ ሄኖህ ፨

ያችንም አገር በልጁ ስም ሄኖህ ብሎ ጠራት ፡፡

፲፰፡ ወወለዶ ሄኖህ ለጋይዳድ ፨

ሄኖህም ጋይዳድን ወለደ ፡፡

ወጋይዳድ ወለዶ ለሚኤል ፨

ጋይዳድም ሚኤልን ወለደ ፡፡

ወሚኤል ወለዶ ለማቱሳላ ፨

ሚኤልም ማቱሳላን ወለደ ፡፡

ወማቱሳላ ወለዶ ለላሜህ ፨

ማቱሳላም ላሜህን ወለደ፤ በሳብዕ ትውልድ እትቤቀለከ ያለው ሰባተኛው ትውልድ ይህ ነው፤

፲፱፡ ወነሥአ ላሜህ ለርእሱ ክልኤተ አንስትያ ፨

ላሜህም ለራሱ ሁለት ሚስቶችን አገባ፤

ስማ ለአሐቲ ሐዳ፣ ወስማ ለካልእታ ሴላ ፨

ያንዲቱ ስምዋ ሐዳ፤ የሁለተኛይቱም ስምዋ ሴላ ይባላል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፡ ወወለደቶ ሐዳ ለዮሴድ ፤

ሐዳ ዮሴድን ወለደችው ፤

ወውእቱ ኮነ አቡሆሙ ለእለ ዮነድሩ ውስተ አዕፃዳተ ኖሎተ እንስሳ ፤

እርሱም ዘለሳ ዘልሰው፣ ከብት አርብተው የሚኖሩ የዘላኖች አባት ነው ፤

፳፩፡ ወስመ እኁሁ ኢዮቤል ፤

የወንድሙም ስም ኢዮቤል ይባላል ፤

ወውእቱ አርአየ ማኅሌተ ወመሰንቆ፣

እርሱም መሰንቆ መምታትን ዘፈን መዝፈንን አስተማረ ፤

፳፪፡ ወሴላሂ ወለደቶ ለቶቤል ፤

ሴላም ቶቤልን ወለደችው ፤

ወውእቱ ኮነ ኃሐቤ ብርት ወሐፂን ፤

ቶቤልም ብረትንና ናስን የሚሠራ ሆነ ፤

ወእኅቱ ሎቱ ኖሂም ስማ ፤

እኅቱም ኖሂም ትባላለች (ሐተታ) ለሴቶች ጥበብን ሁሉ ያስተማረች ይህች ናት ፤

፳፫፡ ወይቤሎን ላሜህ ለአንስቲያሁ ሐዳ ወሴላ ፤

ላሜህም ሚስቶቹን፣ ሐዳ፣ ሴላ፣ ብሎ ጠራቸው፤ አንድም ሚስቶቹን ሐዳን ሴላን እንዲህ አላቸው ፤

ስምዓኒ ቃልየ አንስትያየ ወአጽምዓኒ ነገርየ ፤

ሚስቶቼ ቃሌን ስሙ ነገሬንም አድምጡ ፤

እስመ ብእሴ ቀተልኩ በቍስልየ፣

አቍሲልየ ሲል ነው፤ መትቼ ቃየልን ገድያለሁና ፤

ወወሬዛ በፀልዕየ ፤

አጽሊእየ ሲል ነው፤ መሪዬንም መትቼ ገድያለሁና ነገሬን ስሙኝ አላቸው፤ አንድም በዑረትየ ሲል ነው፤ በዕውርነቴ ቃየልን፣ መሪዬንም መትቼ ገድያለሁና ነገሬን ስሙኝ አለ፤ (ታሪክ) ይህስ እንደምን ነው ቢሉ፤ ቃየልን ኩን ርዑደ ወድንጉፀ ብሎት ነበርና ሰው ሲያይ ከዱር ይገባ ነበር፤ ላሜህ እየተመራ ሲሄድ መሪውን አንተ ከዱር የሚንኰሻኰሽ ምንድር ነው? ድንጋይ ስጠኝ አለው፤ አንሥቶ ሰጠው ፤ ቢወረውር መታው ፤ ገድየዋለሁ መሰለኝ እጄን ሞቆኛልና እስቲ ሂደህ እየው አለው፤ ቢሄድ ሲንፈራፈር ወድቆ አገኘው፤ ተመልሶ መጥቶ የዓለሙን ሁሉ አባት ቃየልን ገድለኸዋል ብሎ ነገረው፤ አዬ ብሎ ደረቱን ደቅቶ አለቅሳለሁ ሲል መሪውን ደግሞ ገድሎታልና እንዲህ አለ ፤



፳፬፡ እስመ ስብዓ እትቤቀል በቃየል ፤

ስብዓት በቀለ ያቀውም ያለውን ይዘረዝራል፡ አቤልን የገደለ፡ ቃየልን የገደለውን ሰው ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያልኹ እበቀለዋለሁ ብሎአልና ፤

ወበላሜህሰ ስብዐ ለለሰብዑ ፤

የገዳይ ገዳይ እኔን የገደለን ሰው ሥላሴ ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያሉ እንዴት ይበቀሉት ይሆን ? ላሜህ ራሱን ያስጠብቃል፤ አንድም አንድ ቃየልን የገደለን ሰው ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያልኹ እበቀለዋለሁ ብለዋልና ድርብ ገዳይ እኔን የገደለን ሰው ሥላሴ ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያሉ እንዴት ይበቀሉት ይሆን? አሁንም ራሱን ያስጠብቃል፤ አንድም አውቆ የገደለ ቃየልን የገደለን ሰው ፍጹም በቀል እበቀለዋለሁ ብሎአልና ሳላውቅ የገደልሁ እኔን የገደለ ሰውን ሥላሴ ሰባቱን አንድ፣ ሰባቱን አንድ እያሉ እንዴት ይበቀሉት ይሆን ? አሁንም ራሱን ያስጠብቃል ፤ አንድም በምክንያት የገደለ ቃየልን ፍጹም በቀል እበቀለዋለሁ ብሎአልና ያለምክንያት የገደልኹ እኔን ሥላሴ እንዴት ይበቀሉኝ ይሆን? አሁን ተዘክሮ ነው፤ አንድም ወንድሙን የገደለ ቃየልን ፍጹም በቀል እበቀለዋለሁ ብሎአልና፣ አባቴን የገደልኹ እኔን ሥላሴ ፍጹም በቀል እንዴት ይበቀሉኝ ይሆን ? አንድም አንድ የገደለ ቃየልን ፍጹም በቀል እበቀለዋለሁ ብሎአልና ሁለት የገደልሁ እኔን ፍጹም በቀል እንዴት ይበቀሉኝ ይሆን ?

፳፭፡ ወአእመራ አዳም ካዕበ ለብእሲቱ ፤

ዳግመኛም አዳም ሚስቱን በግብር አወቃት ፤ (ሐተታ) እንዲያው ያወቃት አይደለም፣ አዳምና ሔዋን በአቤል ሞት አራት ሱባዔ ሲያለቅሱ ኑረዋል፤ ይህም ሃያ ስምንት ዘመን ይሆናል ፤ ከዚያ በኋላ መልአኩ አቤል ወልድከ ተሳለመ ዕፀዊሃ ለገነት ብሎ ነግሮታል፣ ከዚህ በኋላ በግብር አወቃት ፤

ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ፤

ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

ወሰመየቶ ስሞ ሴት ፤

ስሙንም ሴት አለችው፣ ምትክ ማለት ነው ፤

እንዘ ትብል አንሥአ ሊተ እግዚአብሔር እግዚእየ ዘርአ ካልአ ህየንተ አቤል ዘቀተሎ ቃየል ፤

ጌታዬ እግዚአብሔር ቃየል ስለገደለው ስለ አቤል ፈንታ

www.ethiopianorthodox.org

ሌላ ልጅ ምትክ ሰጠኝ ስትል፣ ምትክ አለችው ፤

፳፮፡ ወሴትሂ ወለደ ወልደ ፣

ሴትም ወንድ ልጅን ወለደ ፤

ወሰመዮ ስሞ ሄኖስ ፣

ስሙንም ሄኖስ አለው ፤ ሄኖስ ማለት መዓዛ ፣ ጣዕም ፣ መሠረት ኑዛዜ ማለት ነው ፤

ወውእቱ ዘአኀዘ ከመ ይጸውዕ ስመ እግዚአብሔር ፣

ይኸውም ሄኖስ ስመ እግዚአብሔርን መጥራት የጀመረ ነው፤ አንድም ዘተአመነ ይጸውዕ ይላል አብነት፤ የእግዚአብሔርን ስም ይጠራ ዘንድ የታመነ ነው (ታሪክ)፤ ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ፣ ከአቤል ጀምሮ እስከ ሄኖስ ድረስ፣ ደመ አቤል ያጥፉን እያሉ ሲምሉ ኖሩ ፤ ኋላ ግን፣ ሄኖስ ተመራምሮ መማል በእግዚአብሔር ስም ነው እንጂ በዕሩቅ ብእሲ ደም ነውን ? ብሎ ስመ እግዚአብሔር እየጠራ ይምል ጀመር፤ ይህን ጊዜ ጌታ ሃያ ሁለቱን አሌፋት በጸፍጸፈ ሰማይ ጽፎ አሳይቶታል፤ ከዚያ በኋላ ስመ እግዚአብሔርን እየጠሩ የሚምሉ ሁነዋል፤ ሀያ ሁለት መሆኑም የሀያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ምሳሌ ነው፤ ኋላም እስራኤል፣ ግናያቱን አድርሰው

ጸሎታቸውን በዚህ ያሥሩ ነበር፣ ዛሬ እኛ ጸሎታችንን በአቡነ ዘበሰማያት እንድናሥር ።

## ምዕራፍ ፭

### ጉባኤ

፩፡ ዝመጽሐፍ ዘፍጥረተ እጓለ እመ ሕያው ፣

የሰውን ተፈጥሮ (ትውልድ) የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፤ አንድም ይህ መጽሐፍ የሰውን ተፈጥሮ (ትውልድ) ይናገራል፤

ወበዕለተ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም በአምሳለ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔር አዳምን ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብሎ በፈጠረው ጊዜ፤

፪፡ ገብሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ፣

አንድ ወንድ ፣ አንዲት ሴት (ወንድና ሴት) አድርጎ ፈጠራቸው ፤

ወባረኮሙ ፣

አብዝኑኖሙ ሲል ነው ፤ አበዛቸው ፤

ወሰመየ ስሞ አዳም በዕለተ እንተ ባቲ ገብሮሙ ፣

በተፈጠሩባት ቀን ስሙን አዳም አለው፣ ምን ያምር ማለት ነው፣ አንድም አዳም ማለት ምጥን ፍጥረት ማለት ነው ፤ እንደ



ድንክ አያጥር ፤ እንደ ረዓይት አይረዝም፣ መካከለኛ አድርጎ ፈጥሮታልና ፤ አንድም እመሬት ሥጋው ማለት ነው ፤ አንድም እምድር ዘተሠገወ ማለት ነው ፤

፫፡ ወሐይወ አዳም ክልኤተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፣

አዳም ሁለት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ዘከመ ራእዩ ወዘከመ አምሳሊሁ ፣

በግብር በመልክ የሚመስለውን ልጅ ወለደ ፤

ወሰመዮ ስሞ ሴት ፣

ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው ፤ ምትክ ማለት ነው ፤

፬፡ ወኮነ መዋዕሊሁ ለአዳም ዘሐይወ እምድኅረ ወለዶ ለሴት ፯ተ ምእተ ክረምተ ፣

አዳም ሴትን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፭፡ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለአዳም፣ ተስዐተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ወሞተ፣

የአዳም መላ ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሆነ ከዚያም በኋላ ሞተ፤ (ሐተታ) የአዳም መላ ዘመኑ

ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ነው፤ ሺሕ ሊሞላው ሰባ ዘመን ሲቀረውሙቶአል ፤

ወአኀፀፀ ሰብዓ ክረምተ እንዲል ኩፋሌ ፯:፫ ፣

ዕፀ በለስን ባይበላ ሺሕ ዘመን ሲመላው ዕፀ ሕይወትን በሉቶ ታድሶ መንግሥተ ሰማያት ይገባ ነበር ፤

፮፡ ወሐይወ ሴት ፪ተ፻ተወ፭ተ ዓመተ ፣

ሴትም ሁለት መቶ አምስት ዓመት ኖረ ፤

ወወለዶ ለሄኖስ ፣

ሄኖስን ወለደ፤ ሄኖስ ማለት፣ ጣዕም፣ ኑዛዜ፣ መሠረት፣ መዓዛ ማለት ነው ፤

፯፡ ወሐይወ ሴት እምድኅረ ወለዶ ለሄኖስ ሰብዐተ ምእተ ወሰብዐተ ዓመተ ፣

ሴትም ሄኖስን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ከሰባት ዓመት ኖረ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፰፡ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሴት ተስዐተ ምእተ ዐሠርተ ወክልኤተ ዓመተ ወሞተ ፣

የሴትም መላው ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ዐሥራ ሁለት ሆነ፤ ከዚያም

www.ethiopianorthodox.org

በኋላ ሞተ፤ ቃየልን በክፋት፤ አቤልን በሞት፣ ከቀኀጥር አወጣ፤

፱፤ ወሐይወ ሄኖስ ፺ተ ወተስዓ ዓመተ ፣

ሄኖስም መቶ ዘጠና ዓመት ኖረ፤

ወወለዶ ለቃይናን ፣

ቃይናንንም ወለደ ፤ ቃይናን ማለት፣ ጥሪት ተጋብኦ ማለት ነው፤

፲፤ ወሐይወ ሄኖስ እምድኅረ ወለዶ ለቃይናን ሰብዓተ ምእተ ዐሠርተ ወኃምስተ ዓመተ ፣

ሄኖስም ቃይናንን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ኖረ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፲፩፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሄኖስ ዘሐይወ ተስዓተ ምእተ ወኃምስተ ዓመተ ወሞተ ፣

የሄኖስም መላ ዘመኑ ዘጠኝ መቶ አምስት ዓመት ሆነ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፪፤ ወሐይወ ቃይናን ምእተ ወሰብዓ ዓመተ፣ ወወለዶ ለመላልኤል ፣

ቃይናንም መቶ ሰባ ዘመን ኖሮ መላልኤልን ወለደ፤ መላልኤል ማለት ስብሐተ እግዚአብሔር ማለት ነው፤ አንድም መልአከ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

፲፫፤ ወሐይወ ቃይናን እምድኅረ ወለዶ ለመላልኤል ሰብዓተ ምእተ ወ፵ዓ ዓመተ ፣

ቃይናንም መላልኤልን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ አርባ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፲፬፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለቃይናን ተስዓተ ምእተ ወዓሠርተ ዓመተ፤ ወሞተ ፣

የቃይናን መላ ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ዐሥር ዓመት ኾነ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ፤

፲፭፤ ወሐይወ መላልኤል ምእተ ወስሳ ወኃምስተ ዓመተ፤ ወወለዶ ለያሬድ፣

መላልኤልም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖሮ ከዚያ በኋላ ያሬድን ወለደ፤ ያሬድ ማለት ርደት ማለት ነው ፣ በርሱ ዘመን ደቂቀ ሴት ከደብር ቅዱስ ወርደዋልና ፤

፲፮፤ ወሐይወ መላልኤል እምድኅረ ወለዶ ለያሬድ ሰብዓተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፣

መላልኤልም ያሬድን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤



፲፯፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለመላልኤል ሰመንተ ምእተ ተስዓ ወኃምስተ ዓመተ ወሞተ ፣

የመላልኤልም መላው ዘመኑ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሆነ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፰፤ ወሐይወ ያሬድ ምእተ ወስሳ ወክልኤተ ዓመተ፤ ወወለዶ ለሄኖክ፣

ያሬድም መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት ኖሮ ሄኖክን ወለደ ፤ ሄኖክ ማለት ተሐደሰ ማለት ነው ፤ ይህስ ብልየት ነበረበት ማለት ይሆናል ብሎ ሐዲስ ተሐድሶ ማለት ነው ፤ አዳም አትብላ ያለውን ዕፀ በለስ በልቶ ብልየትን ቢያመጣ እሱም በጾም በትኅርምት ኑሮ ተሐድሶን አም ጥቶአልና፤ ይህም ሄኖክ ከእግረ ገነት ስድስት ዓመት ተሠውሮ ኑሮ በሰባተኛው ዘመን መላእ ክት ወደ ገነት አውጥተውታል፤ ኋላ በልጅነት ታድሰን መንግ ሥተ ሰማያት የመግባታችን ምሳሌ ነው ፤

፲፱፤ ወሐይወ ያሬድ እምድኅረ ወለዶ ለሄኖክ ሰመንተ ምእተ ዓመተ ፣

ያሬድም ሄኖክን ከወለደ በኋላ፣ ስምንት መቶ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ፤

፳፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለያሬድ ተስዓተ ምእተ ስሳ ወ፪ተ ዓመተ ወሞተ ፣

የያሬድም መላ ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሁለት ሆነ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ፤

፳፩፤ ወሐይወ ሄኖክ ምእተ ስሳ ወኃምስተ ዓመተ፣ ወወለዶ ለማቱሳላ፣

ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖሮ ማቱሳላን ወለደ፤ ማቱሳላ ማለት ሞት ተፈናዊ ማለት ነው፤ እስመ በመዋዕሊሁ ተፈነወ ሞት እንዲል ፤

፳፪፤ ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር ፣

ሄኖክም እግዚአብሔርን በሃይማኖት ጸንቶ፣ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ ደስ አሰኘው ፤

ወሐይወ ሄኖክ እምድኅረ ወለዶ ለማቱሳላ ክልኤተ ምእተ ዓመተ ፣

ሄኖክም ማቱሳላን ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፳፫፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለሄኖክ ሠለስተ ምእተ ስሳ ወኃምስተ ዓመተ፣

የሄኖክም መላ ዘመኑ ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ዘመን ሆነ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር ፤

ሄኖክም እግዚአብሔርን በሃይማኖት ጸንቶ፣ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ ደስ አሰኘው፤ ተናግሮት አልነበረምን ? ለምን ደገመው ቢሉ ኢተረክበ ለማለት ፤

ወኢተረክበ እስመ እግዚአብሔር ነበአ ፤

ለሞት አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ከረአይት ከእጃቸው፣ ከግብራቸው፣ ከፍዳቸው ሠውሮታልና ፤ አንድም በዚህ ዓለም አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ሠውሮታልና ፤

፳፭፤ ወሐይወ ማቱሳላ ምእተ ሰማንያ ወሰብዓተ ዓመተ፣ ወወለዶ ለላሜህ ፤

ማቱሳላም መቶ ሰማንያ ሰባት ዘመን ኖሮ ላሜህን ወለደ ፤ ላሜህ ማለት ለምንት ሊተ ዕረፍት ማለት ነው ፤

፳፮፤ ወሐይወ ማቱሳላ እምድኅረ ወለዶ ለላሜህ ስብዓተ ምእተ ሰማንያ ወክልኤተ ዓመተ ፤

ማቱሳላም ላሜህን ከወለደ በኋላ ሰባት መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመት ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤

፳፯፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለማቱሳላ ተስዓተ ምእተ ስሳ ወተስዓተ ዓመተ ወሞተ ፤

የማቱሳላ መላው ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዘመን ሆነ፤ ከዚያ በኋላ ሞተ ፤

፳፰፤ ወሐይወ ላሜህ ምእተ ሰማንያ ወክልኤተ ዓመተ፣ ወወለደ ወልደ፣

ላሜህም መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመት ኖሮ ወንድ ልጅን ወለደ፤

፳፱፤ ወሰመዮ ስሞ ኖኅ ፤

ስሙንም ኖኅ አለው፤ ኖኅ ማለት ዕረፍት ትፍሥሕት ተረፍ ማለት ነው ፤

ወይቤ ዝንቱ ሀለዎ ያዕርፈኒ እምቅኔየ ፤

ከመገዛቴ ያሳርፈኝ ዘንድ አለው ሲል ዕረፍት አለው ፤

ወእምኀዘን ዘእምእዴየ ፤

በእጄ ሠርቼ፣ በቃሌ ተናግሬ በሠራሁት ኃጢአቴ ከመጣብኝ ኃዘን ደስ ያሰኘኛል ሲል ትፍሥሕት አለ ፤

ወእምድር እንተ ረገማ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር የረገማት ምድር ስትጠፋ እርሱ ይቀራል ሲል ተረፍ አለው ፤



፴፤ ወሐይወ ላሜህ እምድኅረ ወለዶ ለኖኅ ኃምስተ ምእተ ስሳ ወኃምስተ ዓመተ፣

ላሜህም፤ ኖኅን ከወለደ በኋላ አምስት መቶ ስድሳ አምስት ዘመን ኖረ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ፤

፴፩፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለላሜህ ስብዓተ ምእተ አርብዓ ወሰብዓተ ዓመተ፤ ወሞተ፣

የላሜህ መላው ዘመኑ ሰባት መቶ አርባ ሰባት ዘመን ሆነ ከዚያም በኋላ ሞተ፤

፴፪፤ ወኮኖ ለኖኅ ኃምስተ ምእተ ዓመተ፣

ኖኅ አምስት መቶ ዘመን ኖረ፤

ወወለደ ኖኅ ሠለስተ ደቂቀ፤ ሴም፣ ካም፣ ወያፌት፣

ሴምሃ፣ ካምሃ፣ ያፌትሃ ሲል ነው፤ ሦስት ልጆችን ሴምን፣ ካምን፣ ያፌትን ወለደ፤ አንድም ሦስቱን ልጆች ወለደ፣ እኒህም ሴም፣ ካም፣ ያፌት ናቸው፤ (ሐተታ) ሴም ማለት ሠናይ ቡሩክ ፍጹም ማለት ነው፤ ካም ማለት ጸሊም ርጉም ማለት ነው፤ ያፌት ማለት ቀይሕ ማለት ነው፣ የቀዩዮች የሮማውያን አባት ነውና፤ አንድም ርኁብ ማለት ነው፤ ለያርኅብ ደወሎ ለያፌት ብሎ እንዲያ መጣው ::

## ምዕራፍ ፮

### ገባኤ

፩፡ ወኮነ ሶበ አኀዙ ይብዝኁ ደቂቀ ሰብእ ዲበ ምድር ፤

የአዳም ልጆች በምድር ላይ ይበዙ ዘንድ በጀመሩ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፤

ወተወልዳ ሎሙ አዋልድ ላህያት፣

ልሁያት ሲል ነው፤ ኮነ ያለውን ተወልዳ ብሎ አመጣው፤ መልክ ከደም ግባት አስተባብረው የያዙ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤ (ሐተታ) ቃየል አቤልን ከገደለ በኋላ ሉድንና አቅሌማን አግብቶ ከሁለቱም ወልዶአል ፤ ከሉድ የተወለዱ እንደ እናታቸው መልከ መልካሞች ሁነዋል፤ እስመ እምብእሲት ላህዩት ተወልዳ ሎሙ አዋልድ ላህያት እንዲል፤ ከአቅሌማ የተወለዱ ግን እንደ እናታቸው መልከ ክፉ ሁነዋል ፤

፪፤ ወሶበ ርእዩ ደቂቀ እግዚአብሔር ከመ ሠናያት እማንቱ አዋልደ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ፤

የእግዚአብሔር ልጆች የሚሆኑት ደቂቀ ሴት ደቂቀ ቃየልን መልከ መልካሞች እንደሆኑ ባዩ ጊዜ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ነሥኡ ሎሙ አንስትያ እምኵሉ ኃረዩ ፤

እንዱም አንዱ የወደዱዋትን የመረጡዋትን አንድ አንድ አገቡ ፣ በአንዲት ሚስት ጸኑ ማለት አይደለም ፣ የጊዜውን መናገር ነው፤ (ታሪክ) ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ፤ እሊህ ደቂቀ ሴት ፣ ከሴት ርቀን ንጽሕ ጠብቀን በደብር ቅዱስ እንደ መላእክት ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያልን ፈጣሪያችንን እያመሰገንን እንኖራለን ብለው ተሳሉ ፤ ለጊዜው ከሴት ራቁ ንጽሕ ጠበቁ፤ የመላእክት ትሩፋት፤ የአጋንንት ኃጢአት ተገለጠላቸው ፤ እንደ መላእክት ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ በደብር ቅዱስ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑ ኖሩ፤ ከዕለታትም አንድ ቀን ደቂቀ ቃየል፣ ወንዶችም ሴቶችም በወገባቸው የወገብ ድባ እያሠሩ ሐፍረታቸውን አውጥተው እንደ ባዝራ፣ እንደ አለሌ ሲንጣጣጡ አይተው በሐፀ ዝሙት ተነደፉ፤ ንዑ ንረድ ወንንሣእ አሐተ አሐተ እምአዋልደ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው እለ ርኢነ ወእለ ኃረይነ ብለው ወርደው ቀርተዋል፤ አንድም ለሌላ ሥራ ከወረዱ ዘንድ በዚያው ተሳስበው ቀርተዋል፤ ዛሬ ለመፍቅደ ደብር ከገዳም የወጣ መነኮሴ፣ በዓለም ተሳስቦ እንዲቀር ፣ በቀድሞ ግብራቸው መላእክት ብሎዋቸዋል፤

፫፡ ወይቤ እግዚአብሔር ኢይኑብር መንፈስየ ላዕለ ዕጓለ እመሕያው ለዓለም ፤

እግዚአብሔርም ደቂቀ ሴት እንዲህ ከሆኑ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለሙ አይደርባቸው አያድርባቸውም አለ፤ አንድም ረድኤቴ ለዘለዓለሙ አያድርባቸውም አይደርባቸው አለ ፤

እስመ እሙንቱ ዘሥጋ ፣

ሥጋውያን ደማውያን ናቸውና፣ ይህስ አያስፈርድባቸውም ብሎ ሥጋዊ ደማዊ ሥራ ይሠራሉና፤

ወይኩን መዋዕሊሆሙ ምእተ ወዕሥራ ዓመተ ፣

ዘመናቸውም መቶ ሃያ ዘመን ይሁን አለ ፤ አንድም ማየ አይኅ የሚወርድበት መቶ ሀያ ዘመን ይሁን አለ ፤ (ታሪክ) ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ፤ ለአዳም ሺህ ዘመን ተሰጥቶት ነበር ፣ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስን በበላ ጊዜ ሰባ ዘመን ተከፍሎበታል ፤

ወአሕፀፀ ሰብዓ ክራማተ እንዳለ ፣ ከዚያ በኋላ ዘመን እየተከፈለ መጥቷል ፤ ጌታ ለኖኅ በመቶ ሃያ ዘመን ማየ አይኅን አመጣለሁ ብሎ ነገረው ፤ እኒህ



ደቂቀ ቃየልና ደቂቀ ሴት ፣ ጌታ ለኖኅ ሲነግረው ሰምተው፤ መቶውን ዘመን እንደፈቀድን ሆነን ሀያው ዘመን ሲደርስ (ሲቀር) ንስሐ እንገባለን ብለው ጸንተው ኃጢአት ሠርተዋል፤ ጌታም አውቆባቸው ፤ መቶው ዘመን ተፈጽሞ ሀያውም ዘመን ሳይደርስ፤ በመካከሉ ማየ አይኅ አጥፍቶአቸዋል፤ ኖኅስ እንደምን ሆኖ ድኗል ቢሉ መላእክት ቀላል ቀላሉን እንጨት ከገነት አምጥተው ሰጡት ፤ መርከብ ሠርቶ ከዚያ ገብቶ ድኗል፣ አንድም ወእምቅድመ ምእት ዓመት ቆሙ ዕፀዊሃ ለገነት ይላል ብሎ ከመቶ ዘመን አስቀድሞ ፤ መላእክት ተክሉን ከገነት አምጥተው ሰጡት ፣ እርሱ ተክሎ አድርሶ ኋላ ያንን እየቈረጠ መርከብ ሠርቶ ከዚያ ገብቶ ድኗል ፤

፬፡ ወሀለዉ እለ ያርብሕ በእማንቱ መዋዕል ውስተ ምድር ፣

በዚያም ወራት በዚህ ዓለም ቁመታቸው ሺህ ሁለት ሺህ ክንድ የሆነ አርበኞች ነበሩ ፤

ወእምድኅሬሁኒ ሶበ ቦኡ ደቂቀ እግዚአብሔር ኀበ አዋልደ ሰብእ ወወለዱ ሎሙ ፣

ደቂቀ ሴትም አዋልደ ቃየልን ባገቡ ጊዜ ልጆች ወለዱላቸው፤

ወእሙንቱኒ ኮኑ እለ ያርብሕ ፣

እነዚህም አርበኞች ሆኑ ፤

እለ እምፍጥረተ ዓለም ዕደው እለ አስመዩ ስሞሙ ፣

ከተወለዱ ጀምሮ ስማቸውን ያስጠሩ አርበኞች ሆኑ ፤

፭፡ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ በዝኃ እከዮሙ ለዕጓለ እመሕያው ላዕለ ምድር ፣

እግዚአብሔርም በዚህ ዓለም የደቂቀ ሴት ኃጢአታቸው እንደ በዛ ባየ ጊዜ ፤

ወበኵሉ ጊዜ ውስተ እኪት ፣

ሁልጊዜ በኃጢአት እንደ ጸኑ ባየ ጊዜ ፤

ወኵሉ ሕሊናሆሙ ውስተ እከይ እምንእሶሙ በኵሉ መዋዕሊሆሙ፣

ከሕፃንነታቸው፤ አንድም ከጥቂትነታቸው ጀምሮ ባለ ዘመናቸው ሁሉ ፤ አሳባቸው ወደ ኃጢአት እንደሆነ ባየ ጊዜ ፤

፮፡ ወነስሐ እግዚአብሔር እስመ ገብሮ ለዕጓለ እመሕያው ላዕለ ምድር፣

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ሰውን ስለፈጠረው ተጸጸተ ፤ (ሐተታ) እንዲህ ስላለ ግን ሰው ሳያውቅ ሥራውን ሠርቶ እንዲጸጸት ተጸጸተ ማለት አይደለም፤ ለበጎ ነገር አብነት ይሆናል ብዬ ብፈጥረው ለክፉ ነገር አብነት ሆነ አለ፤ ሲል ነው፤ ወሐለየ

www.ethiopianorthodox.org

ማንሻ፡ አንድም አዝኗልና ሐለየ ወይቤ ይሏል ፡

፯፡ ወሐለየ ወይቤ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔርም አሰበ እንዲህም አለ፡

እደመስሶ ለዕጓለ እመሕያው ዘገበርክዎ እምላዕለ ምድር ፤

የፈጠርኹትን ሰውን ከዚህ ዓለም አጠፋዋለሁ ፡

እምሰብእ እስከ እንስሳ ፤

ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ፡

ወአራዊት ወአዕዋፈ ሰማይ ወዘይት ሐወስ ፤

አራዊትን፣ አዕዋፍን በዚህ ዓለም የሚንቀሳቀሱ ጥቃቅኑን ፍጥረታት ሁሉ አጠፋለሁ አለ ፡

እስመ ነሳሕኩ ዘገበርክዎ ፤

ስለ ፈጠርኹት፣ ለምን ፈጠርኹት ብዬ አዝኛለሁና፡ (ሐተታ) ስለምን በእንስሳት ፈረደባቸው ሕጉን ያፈረሰ ሰው አይደለምን? ቢሉ፣ የነዚህ ጥፋት የሰው ጉዳት ነውና፡ አንድም የሰው ምግባሩ፡ ትሩፋቱ ሁሉን እንዲጠቅም፣ ኃጢአቱም ሁሉን ይጎዳልና ፤ ሰዎችን ለማጥፋት የታዘዘው መዓትና መቅሠፍት ለነዚያም ተርፎአቸዋል ፡

፰፡ ወኖኅሰ ረከበ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር ፤

ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን መወደድን አገኘ፡

፱፡ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለኖኅ፤

የኖኅ ልደቱ ደግነቱ እንዲህ ነው ፡

ብእሲ ጻድቅ ውእቱ ወፍጹም ፤

ደግ ሰው ነበር፡ ፍጹም ሰውም ነበር፡ (ሐተታ) ጻድቅ በምግባር በትሩፋት፣ ፍጹም በሃይማኖት ነው ፡

ወእምልደቱ አሥመሮ ለእግዚአብሔር ፤

ከተወለደ ጀምሮ እግዚአብሔርን አገለገለው፡ (ሐተታ) ወዲያው እንደ ተወለደ ቅዱስ ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ ብሎ አመስግኗልና እንዲህ አለ፡

፲፡ ወወለደ ኖኅ ሠለስተ ደቂቀ ሴም፣ ካም፣ ወያፌት ፤

ኖኅም ሦስት ልጆችን ወለደ፣ እሊህም ሴም፣ ካም፣ ያፌት ናቸው ፤ (ሐተታ) ስለምን ደገመው ተናግሮት አልነበረምን? ቢሉ፣ መጽሐፍ አንድ ነገር ቢቀረው መድገም ልማዱ ነውና፣ እነዚያ በኃጢአታቸው ጠፉ ፤ እነዚህ በደግነታቸው ዳኑ ለማለት ደገመው ፡



፲፩፡ ወማሰነት ምድር በቅድመ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ባወቀው ነገር ምድር ጠፉች ተበላሸች ፡

ወመልአት ዓመፃ ፤

ኃጢአትንም ተመላች፡ አንድም ኃጢአት በምድር በዛች፣ ሰፈነች ፤ ትርፍርፍ አለች ፡

፲፪፡ ወርእየ እግዚአብሔር ለምድር ከመ ማሰነት ፤

እግዚአብሔርም ምድር እንደ ተበላሸች ባየ ጊዜ ፡

ወከመ አማሰኑ ፍኖቶሙ በዲበ ምድር ኵሉ ዘሥጋ ፤

ሥጋውያን ደማውያን ሁሉም በዚህ ዓለም የማይገባ ሥራ እንደሠሩ ባያቸው ጊዜ ፡

፲፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ ፤

ፈጣሪው እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፡

ጊዜሁ ለዕጓለ እመሕያው በጽሐ ቅድሜየ ፤

በእኔ ትእዛዝ ሰው የሚጠፋበት ጊዜው ደረሰ አለው ፡

እስመ መልአት ዓመፃ በዲበ ምድር እምኔሆሙ ፤

ከእነሱ የተነሣ ኃጢአት በዚህ ዓለም መልታለችና ፡

ወናሁ አነ እደመስሶሙ እምድር ፤

እነሆ እኔ ከዚህ ዓለም አጠፋቸዋለሁና ፡ በጽሐ ደረሰ አለው ፡ ግበር ማንሻ ፡ አንድም አጠፋቸዋለሁና ፡

፲፬፡ ግበር ለከ ታቦተ እንተ ዕፅ ርብዕት ፤

አራት ማዕዘን አድርገህ መርከብ ሥራ አለው ፡

ወትቀብአ እንተ ውስጣ ወእንተ አፍአሃ በፒሳ ፤

ቅብአ ሲል ነው ፡ በውስጥም በውጪም ሰም አዶሮ ማር ሙጫ ቅባት አለው ፡

፲፭፡ ወከመዝ ትገብራ ፤

ግበራ ሲል ነው፣ እንዲህ አድርገህ ሥራት ፡

ሠለስተ ምእተ በእመት ኑኃ፣ ወኃምሳ በእመት ርኅባ፣ ወሠላሳ በእመት ቆማ ፤

አቆልቋይዋን (አግዳሚ ርዝመትዋን) ሦስት መቶ ክንድ ፤ ወርድዋን አምሳ ክንድ፣ ወደ ላይ ቁመትዋን ሠላሳ ክንድ አድርገህ ሥራ አለው ፤ ቆማ ባለው ሠራ ይላል ቆማ ማለት ነው ፡

፲፮፡ ወመስኮተ ግበር ለይእቲ ታቦት፣

ለዚያችም መርከብ ብርሃን የሚገባበት መስኮት አብጅላት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሶበ በጽሒት ለተፈጽሞ አሐቲ እመት እንዘ ትተርፍ ግበር ሀየ ኖኅታ ውስተ ገቦሃ ፤

ልትፈጸም አንዲት ክንድ ስትቀር ፤ በጐንዋ በኩል ደጃፍ አውጣላት፤

ወግበር ላቲ መዓርጋተ ተጽራሐ ፤

የአዳራሽነትዋን እርከን ማለት መውጫ መውረጃ አብጅላት፤

ወተሥላሰ ግበር፤

ሦስት ክፍል አድርገህ ሥራት አለው፤ (ሐተታ) በቁመት ከፍሏ ታል ያሉ እንደሆነ ፤ በፊት ዐሥር ክንድ ሠርቶ መረባ ጥሏል ፤ እንዲህ እያደረገ ወደ ላይ ሦስት ክፍል ሠርቷል ፤ እንዲህ አድርጎ ሠርቶ የማይ በሉትን ከታች ፤ የሚበሉትን ከመካከል አኑሮአቸዋል፤ እርሱ ከልጆቹ ጋራ ከላይ ሆኖአል ፤ በአቆልቋዩ (በአግዳሚ ርዝመቱ) ነው የከፈላት ያሉ እንደሆነ፤ መቶ ክንድ ሰፍሮ መከታ ሠርቷል ፤ እንዲህ እያደረገ መቶ መቶውን ክንድ ከፍሎታል ፤ እንዲህም አድርጎ ሠርቶ ፤ የሚበሉትን በቀኝ ፤ የማይበሉትን በግራ አኑሮቸአዋል ፤ እርሱ ከልጆቹ ጋራ በመካከል ሆኖአል ፤

፲፯፤ ወናሁ አነ አመጽእ ማየ አይኅ በዲበ ምድር፤

እነሆ እኔ በምድር ላይ የጥፋት ውሃን አመጣለሁ ፤

ወእደመስስ ኵሎ ዘሥጋ ዘቦ መንፈስ ሕይወት ዘሀሎ ላዕለ ምድር ወመትሕተ ሰማይ ፤

ከጠፈር በታች ከምድር በላይ ያለውን በደማዊት ነፍስና በነባቢት ነፍስ ሕያው የሆነውን ሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ አጠፋለሁ ፤

ወይመውት ኵሉ ዘሥጋ ፤

ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ ይጠፋል፤

፲፰፤ ወአቀውም ኪዳንየ ምስሌከ ፤

አንተን እንዳላጠፋህ ቃል ኪዳኔን ካንተ ጋራ አጸናለሁ ፤

፲፱፤ ወትበውእ አንተ ውስተ ታቦት፤

ባእ ሲል ነው፤ አንተ ወደ መርከቡ ግባ ፤

ወብእሲትከ ወደቂቅከ ወአንስትያ ደቂቅከ ምስሌከ ፤

ሚስትህም ልጆችህም የልጆችህም ሚስቶች ካንተ ጋራ ወደ መርከቡ ይግቡ ፤

፳፤ ወእምኵሉ እንስሳ ወአዕዋፍ፤ ወዘይትሐወስ፤ ወአራዊት ወእምኵሉ ዘሥጋ ታበውእ ምስሌከ ተባዕተ ወአንስተ ፤

ከእንስሳ ወገን ከአዕዋፍም ወገን የሆነውን ከጥቃቅኑም ከታላላቁም አራዊት ወገን የሆነውን፤ ከሥጋዊ ከደማዊ ወገን የሆነውንም ሁሉ፤ ተባትና እንስት እያደረግህ ይዘህ ግባ፤

፳፩፤ ወንሣእ ለከ እምኵሉ መባልዕት ዘይሴሰዩ ፤

ምግብ ከሚሆነው ሁሉ እነዚያ የሚመገቡትን ይዘህ ግባ፤ አንድም ዘትሴሰይ ይላል አንተ የምትመገበውን ይዘህ ግባ አለው፤ ለሁለቱም ያመጣል ፤

ወአስተጋብእ ኀቤከ ፤

ምግቡን ሰብስበህ ይዘህ ግባ፤

ወይከውነከ መብልዐ ለከ ፤

ላንተ ምግብ ይሆንህ ዘንድ ፤ ዘትሴሰይ ላለው ይሰጧል ፤

ወለኵሎሙ አራዊት ወእንስሳ ፤

ለአራዊትና ለእንስሳት ሁሉ ምግብ ይሆናቸው ዘንድ ዘይሴሰዩ ላለው ስጥ ፤

፳፪፤ ወገብረ ኖኅ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር አምላክ ፤

ኖኅም ገዥ ፈጣሪ የሚሆን እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ።



## ምዕራፍ ፯

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ፤

እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው ፤

ባእ አንተ ወኵሉ ቤትከ ውስተ ታቦት ፤

አንተ ከወገኖችህ ጋራ ወደ መርከብ ግባ ፤

እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ በዛቲ ትውልድ ፤

እምዛቲ ትውልድ ሲል ነው፤ ከዚህች ትውልድ ደግ ሰው አንተን አግኝቻለሁና ፤

፪፤ ወእምእንስሳ ዘንጹሕ አብእ ምስሌከ ሰብዓተ፤ ሰብዓተ ተባዕተ ወአንስተ ፤

ከሚበሉትም እንስሳት፤ ተባትና እንስት ሰባት ፤ ሰባት እያደረግህ ይዘህ ግባ ፤

ወእምእንስሳ ዘኢኮነ ንጹሐ ክልኤተ፤ ክልኤተ ተባዕተ ወአንስተ ፤

ከማይበሉትም ተባትና እንስት ሁለት ፤ ሁለት እያደረግህ ይዘህ ግባ ፤

፫፤ ወእምአዕዋፈ ሰማይ ዘንጹሕ ሰብዓተ ፤ ሰብዓተ ፤

ከሚበሉት አዕዋፍም እንስትና ተባት ሰባት፤ ሰባት እያደረግህ ይዘህ ግባ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምአዕዋፈ ሰማይ ዘኢኮነ ንጹሐ፣ ክልኤተ ፣ ክልኤተ ተባዕተ ወአንስተ ፣

ከማይበሉትም አዕዋፍ ተባትና እንስት ሁለት ፣ ሁለት እያደረግህ ይዘህ ግባ ፤

ዘትሴሰይ ፣

ላንተ ምግብ ከሚሆኑ ሰባት ፣ ሰባት ይዘህ ግባ አለው፣ ሁለቱ ለዘር፣ አምስቱ ለምግብ ለመሥዋዕት እንዲሆኑ ፤

ወዘይከውን ዘርአ በዲበ ምድር ፣

ለዘር እንጂ ፣ ምግብ ከማይሆነው ፣ ሁለት ሁለት አግባ አለው ፤

፬፡ እስመ እስከ ሰብዑ መዋዕል አመጽእ ዝናመ ዲበ ምድር ፣

እስከ ሰባት ቀን ድረስ በምድር ላይ የጥፋት ውሃን አመጣለሁና ፤

፵ዓ መዓልተ ወ፵ዓ ሌሊተ ፣

አርባ ቀን በመዓልትም በሌሊትም የጥፋት ውሀን አመጣለሁና ፤

ወእደመስስ ኵሎ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ፣

በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ጥቃቅኑን ፍጥረት ሁሉ አጠፋለሁና፣ ባእ አንተ ወኵሉ ቤትከ ብለህ እሠር ፤

፭፡ ወገብረ ኖኅ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር አምላኩ ፣

ኖኅ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ፤ (ሐተታ) ስለምን ከሚበሉቱ ሰባት፣ ሰባት አግባ አለው ቢሉ ለምግብ ፣ ለመሥዋዕት፣ ለዘር ይሆናልና፤ ከማይበሉትም ሁለት ፣ ሁለት አግባ አለው ለዘር ብቻ ነውና ፤

፮፡ ወአሚሁ ኮኖ ለኖኅ ስድስቱ ምእተ ዓመት ፣

ያን ጊዜ ኖኅ ከመርከብ እስኪገባ ድረስ ስድስት መቶ (ዘመን) ዓመት ሆኖት ነበር ፤

ወመጽአ ማየ አይኅ ላዕለ ኵሉ ምድር ፣

በምድር ላይ ሁሉ የጥፋት ውሀ ታዞዞ መጣ ፤

፯፡ ወቦአ ኖኅ ወብእሲቱ ወደቂቁ ወአንስትያ ደቂቁ ምስሌሁ ውስተ ታቦት በእንተ ማየ አይኅ ፣

ኖኅም ማየ አይኅ የሚመጣ ስለሆነ ሚስቱን ልጆቹንም ከነ ሚስቶቻቸው ይዞ ወደ መርከብ ገባ ፤

፰፡ ወእምአዕዋፍ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ ፣

ከአዕዋፍም ከሚበሉትና ከማይበሉት ወገን ፤

ወእምእንስሳ ዘንጹሕ ወዘኢኮነ ንጹሐ፣

ከእንስሳትም ከሚበሉትና ከማይበሉት ወገን ፤



ወእምኵሉ ዘይትሐወስ ፣

በዚህ ዓለም ከሚንቀሳቀስ ከጥቃቅኑ ፍጥረት ወገን ሁሉ ፤

፱፡ ቦኡ ኀበ ኖኅ ውስተ ታቦት ተባዕት ወአንስት ፣

ተባትና እንስት እየሆኑ ኖኅ ወዳለበት ወደ መርከብ ገቡ ፤

በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኖኅ ፣

እግዚአብሔር ኖኅን ከማይበሉት ሁለት ሁለት፤ ከሚበሉት ሰባት ሰባት ፤ ይዘህ ግባ እንዳለው ፤

፲፡ ወኮነ እምድኅረ ሰቡዕ መዋዕል፣

ከሰባት ቀን በኋላም እንዲህ ሆነ፤ ኮነ ያለውን ያምጣው ፤

ወመጽአ ማየ አይኅ በዲበ ምድር፣

በምድር ላይ ማየ አይኅ ታዞዞ፤ ኮነ ያለው ይህ ነው፤ (ሐተታ) ስለምን ሰባት ቀን ሰነበተ ቢሉ ታግሦ ታግሦ ካልተመለሱ መከራን እንዲያመጣ ለማጠየቅ ፤ (አንድም) ፈጥኖ ባያጠፋን ንስሐ ገብተን እንመለስ ነበር ባሉ ነበርና፤ ምክንያት ለማጥፋት፤

፲፩፡ አመ ኮነ ስድስቱ ምእተ ዓመተ ሕይወቱ ለኖኅ ፣

የኖኅ ዕድሜው ስድስት መቶ ዘመን በሆነ ጊዜ ፤

በካልእ ወርኅ ፣

በሁለተኛው ወር በግንቦት ፤ (ሐተታ) ዘመን የሚለወጥ በሚያዝያ ነውና ግንቦትን ካልእ አለው ፤

አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጽልመት ፣

ጨረቃ ጠፍ ሁና አድራ፣ ሠርቅ ባደረገች በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ፤ በፀሐይ በዐሥራ ሰባተኛው ቀን ፤

፲፪፡ ወበይእቲ ዕለት ተሠጥቁ ኵሉ ቀላያት፣

በዚያች ቀን ከምድር በታች ያሉ ውሆች ሁሉ በሰባ ዓይን መሬቱን ቀደው ወደ ላይ ፈሉ ፤

ወተርኅወ አሥራብ ሰማይ ፣

ከጠፈር በላይ ያለ ሐኖስም ፣ በሰባት መሽረብ ተከፍቶ ወረደ፤

ወኮነ ዝናም ዲበ ምድር ፵ዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ፣

ዓርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ማየ አይኅ ዘነመ፤

፲፫፡ ወበይእቲ ዕለት ቦአ ኖኅ ወሴም፣ ወካም ወያፌት ደቂቁ፤ ወብእሲቱ፣ ወአንስትያ ደቂቁ ውስተ ታቦት ፣

በዚያችም ቀን ኖኅ፣ ልጆቹም ሴም፣ ካም፣ ያፌት ሚስቱና የልጆቹም ሚስቶች ወደ መርከብ ገቡ ፤ (ሐተታ) ከላይ ቦአ ኖኅ ወብእሲቱ ካለ በኋላ፣ ወእምድኅረ ሰቡዕ መዋዕል መጽአ ማየ አይኅ አለ፤ ከዚህ በይእቲ ዕለት ተሰጥቁ ኵሉ ቀላያት ወተርኅወ አሥራብ ሰማይ ብሎ፣

www.ethiopianorthodox.org

በይእቲ ዕለት ቦአ ኖኅ ወደቂቁ አለ፤ እንደምን ነው ቢሉ፤ ኖኅ ከነልጆቹ ወደ መርከብ የገበበትና ማየ አይኅ የዘነመበት ዕለቱ አንድ ነውና በይእቲ ዕለት አለ እንጂ፣ ማየ አይኅ የወረደውስ ከመርከብ በገቡ በስምንተኛው ቀን ነው፤ ይኸውም ወእምድኅረ ሰቡዕ መዋዕል በማለቱ ይታወቃል ፤

፲፬፡ ወአራዊትኒ በበዘመዶሙ ፤ ወኵሉ እንስሳ በበዘመዶሙ፣ ወዘይትሐወስ ወአዕዋፍ በበዘመዶሙ ፣

አራዊቱ በየወገናቸው፣ እንስሳትም በየወገናቸው፣ የሚንቀሳቀሰው ጥቃቅኑ ፍጥረትና አዕዋፍ ሁሉ በየወገናቸው ፤

፲፭፡ ወእምነ ኵሉ ዘሥጋ ቦአ ውስተ ታቦት ኀበ ኖኅ፤ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኖኅ ፣

ከሥጋዊ ከደማዊ ወገን የሚሆኑት ሁሉ እግዚአብሔር ኖኅን እንዳዘዘው፣ ኖኅ ወዳለበት ወደ መርከቡ ባንድነት ገቡ፤ (ሐተታ) እንደምን ሆነው ይገቡለታል ቢሉ ፤ መጥቅዕ በመታ ጊዜ ተሰብስበው ገብተውለታል፤ አንድም መልአኩ በነፋስ አውታር እየያዘ ያገባለታል ፤

አንድም በፈቃደ እግዚአብሔር ተሰብስበው ገብተውለታል ፤

፲፮፡ ወዐፀዋ እግዚአብሔር ለታቦት እምአፍአ ፣

እግዚአብሔር የመርከቢቱን መስኮት በውጪ በኩል ዘጋት ፤ (ሐተታ) የብርሃን መግቢያ መስኮት ትቶ ነበር፤ መልአኩ ሱርያል፣ በዚያ ውሀ እንዳይገባበት ብሎ በክንፉ ጋርዶለታልና እንዲህ አለ ፤

፲፯፡ ወኮነ አይኅ በዲበ ምድር ፵ዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ፣

በምድርም ላይ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ማየ አይኅ ዘነመ፤

ወመልአ ማይ ወአልዐላ ለታቦት ፣

ውሀውም መልቶ መርከቢቱን አንሳፈፋት፤

ወተለዐለት እምድር ፣

ከምድር ለቀቀች፤

፲፰፡ ወጸንዐ ማይ ጥቀ በላዕለ ምድር፣

ውሀውም በምድር ላይ እጅግ በዛ በረታ፤

ወጸለለት ይእቲ ታቦት ላዕለ ማይ፣

መርከቢቱ በውሀው ላይ ዋኘች ተንኳፈፈች፤

፲፱፡ ወፈድፋደ በዝኃ ጥቀ ማይ ዲበ ምድር ፣

ውሀው እጅግ በዝቶ ወደላይ ወጣ ፤



ወከደነ ኵሎ አድባረ ነዋኃተ ዘመትሕተ ሰማይ ፣

ከሰማይ በታች ያሉ ረጃጅሞቹን ተራራዎችንም ሁሉ አጠለቃቸው፤ ስለርዝመታቸው ዘመትሕተ ሰማይ ብሎአቸዋል ፤

፳፡ ዐሠርተ ወኃምስተ እመተ ተለዐለ መልዕልቶሙ ማይ ፣

ውሀውም ከተራሮቹ በላይ ዐሥራ አምስት ክንድ ወጣ፤ (ሐተታ) በምን ታውቋል ቢሉ ፣ ነቢዩ ባወቀ ተናግሮታል፤ አንድም ኖኅ በጸጋ ሰፍሮታል፤ አንድም አራራተ ነበረት ታቦት እንዲል ፤ መርከቢቱ ከተራራው ላይ ባረፈች ጊዜ ውሀው የነበረበት ቢሰፈር ዐሥራ አምስት ክንድ ሁኖአል፤ አንድም ገነት ከአራራት በላይ ዐሥራ አምስት ክንድ ትበልጣለች፣ ውሀው በከንፈረ ገነት ደርሶአል ፣ መርከቢቱ ሠላሳ ክንድ ናት፤ እኩሌታዋን አጥልቆአት እኩሌታዋ ቀርቶአል ፤

፳፩፡ ወሞተ ኵሉ ዘሥጋ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር ወኵሉ ዕጓለ እመሕያው ፣

በምድር ላይ የሚንቀሳቀስና ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ ሰውም ሁሉ ጠፉ ፤

፳፪፡ ወኵሉ ዘመንፈስ ፣ ወኵሉ ዘሀሎ ላዕለ የብስ ሞተ ፣

በየብስ ያለው በደመ ነፍስ ሕያው የሚሆነው ሁሉ አለቀ፤

፳፫፡ ወተደምሰሰ ኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ገጸ ለምድር፤ እምዕጓለ እመሕያው እስከ እንስሳ ወአዕዋፈ ሰማይ፣

በዚህም ዓለም የሚንቀሳቀሰው ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ እስከ አዕዋፍ ድረስ ፈጽሞ ጠፉ፤

ወተርፈ ኖኅ ባሕቲቱ ወእለ ቦአ ምስሌሁ ውስተ ታቦት ፣

ኖኅ ከእርሱም ጋራ ወደ መርከብ የገቡት ብቻ ቀሩ፤

፳፬፡ ወተለዐለ ማይ መልዕልተ ምድር ምእተ ወኃምሳ ዕለተ ፣

ውሀውም በምድር ላይ መቶ አምሳ ቀን ሙሉ መልቶ ኖረ ፤ (ሐተታ) አርባውን ቀን ሳያቋርጥ ዘንሞአል ፤ መቶ ዐሥር ቀን ሳይጨምርም ሳይጐድልም ስንብቶአል፣ መቶ አምሳ ቀን ያለውም ይህ ነው።

## ምዕራፍ ፰

፩፡ ወተዘከሮ እግዚአብሔር ለኖኅ፣

እግዚአብሔር ኖኅን በረድኤት አሰበው ፣ (ሐተታ) አሁን ውሃውን የሚያደርቅ ውዑይ ነፋስ አመጣ ፤ የሚል ነውና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለኲሉ አራዊት ወለኲሉ እንስሳ፤ ወለኲሉ ዘሀሎ ምስሌሁ ውስተ ታቦት ።

አራዊትንም እንስሳትንም ሁሉ ከእርሱ ጋራ በመርከብ ያሉትንም ሁሉ በረድኤት አሰባቸው፤

ወአምጽአ እግዚአብሔር ነፋሰ ላዕለ ምድር ።

እግዚአብሔርም ውሀውን የሚያደርቅ ነፋስ እንዲነፍስ አደረገ ፤

ወነትገ ማይ ።

ውሀውም ጐደለ ፤

፪፤ ወተከሥቱ አንቅዕተ ቀላይ ።

የውሀው ምንጮች ሁሉ ተከፈቱ ፤ (ሐተታ) የወጣበትን ትቶ በሌላ በኩል ሰዶታልና፤ አንድም የውሀ ምንጮች ሁሉ ተደፈኑ አለ። ወደላይ መፍላቱ ቀረ፤

ወአስረበ ሰማይኒ ተዐጽወ ወቆመ ዝናም እምሰማይ ።

በጠፈር ያለ ሰባቱ መሸረብ ተዘግቶ ዝናም መዝነሙ ቀረ ፤

፫፤ ወአኅዘ ይኅልቅ ማይ ወይሐውር እምድር ።

ውሀው ከምድር እየጐደለ ይሔድ ጀመረ ፤

ወእምድኅረ ምእት ወኃምሳ ዕለት ሐፀ ማይ ።

ከመቶ አምሳ ቀን በኋላ ውሀው እያደር ይጐድል ጀመር ፤

፬፤ ወነበረት ይእቲ ታቦት በሳብዕ ወርኅ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጽልመት ላዕለ አድባረ ዓራራት ።

በሰባተኛው ወር በጥቅምት ፤ ጨረቃ ጠፍ አድራ ሠርቅ ባደረገች በዐሥራ ሁለተኛው ቀን መርከቢቱ በዓራራት ላይ አረፈች ፤

፭፤ ወማይሰ የሐፅፅ ወይነትግ እስከ ዐሥር ወርኅ ።

ውሀው ግን እስከ ዐሥረኛው ወር እስከ ጥር ድረስ እየጐደለ እየደረቀ ይሄድ ነበር ፤

ወአመ ኮነ ዐሠርቱ ወአሐዱ አውራኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኅ አስተርአዩ አርእስቲሆሙ ለአድባር ።

በዐሥራ አንደኛው ወር በየካቲት መባቻ የተራሮቹ ራሶች ተገለጡ ታዩ ፤

፮፤ ወኮነ እምድኅረ አርብዓ ዕለት አርኃወ ኖኅ ኆኅተ መስኮታ ለታቦት እንተ ገብረ ።

ከአርባው ቀን በኋላም የተዘጋውን የመርከቢቱን መስኮት ኖኅ ከፈተ፤ አርባ ቀን ያለው ከየካቲት ሠላሳ ከመጋቢት ዐሥር ጨምሮ ነው ፤

፯፤ ወፈነዎ ለቋዕ ከመ ይርአይ እመ ነትገ ማይ እምገጸ ምድር ።

ውሀው ከምድር ላይ ጐድሎ እንደሆነ ያይ ዘንድ ኖኅ ቍራውን ላከው ፤



፰፤ ወሖረ ወኢገብአ እስከ አመ ኀልቀ ማይ እምገጸ ምድር ።

ሄዶም ውሀው ከምድር ጨርሶ እስኪጐድል አልተመለሰም ፤ (ሐተታ) ከዚያ በኋላ ተመለሰ ማለት አይደለም፣ ፍጻሜ የሌለው እስከ ነው፤ ኢወለደት ሜልኮል እስከ አመ ሞተት እንዲል፤ በማየ አይኅ ያለቀ የእንስሳት፣ የአራዊት ውዳቂ አይታጣምና በዚያ ምክንያት ቀርቷል ፤

፱፤ ወፈነዋ ለርግብ እምድኅሬሁ ከመ ትርአይ እመ ነትገ ማይ እምገጸ ምድር ።

ከእርሱም በኋላ ውሀው ጐድሎ እንደሆነ ታይ ዘንድ ርግብን ላካት ፤

ወኢረከበት ኀበ ታዕርፍ እገሪሃ ወገብአት ኀቤሁ ውስተ ታቦት ።

እግርዋን የምታሳርፍበት አጥታ ኖኅ ወዳለበት መርከብ ተመለሰች ፤

እስመ ማይ ሀሎ ውስተ ኲሉ ገጸ ምድር ።

ውሀው በምድር ላይ ሁሉ መልቶ ነበርና፤

ወሰፍሐ እዴሁ ወነሥአ ውስተ ታቦት ኀቤሁ ።

እጁን ዘርግቶ ወደ መርከቡ አገባት ፤

፲፤ ወተዐገሣ ሰቡዐ መዋዕለ፤ ካዕበ ፈነዋ ለርግብ ውስተ ምድር ከመ ትርአይ ።

ሰባት ቀን ታግሦ ውሀው ደርቆ እንደሆነ ታይ ዘንድ ሁለተኛ ጊዜ ርግብን ላካት ፤

፲፩፤ ወገብአት ኀቤሁ ርግብ ፍና ሠርክ ወባቲ ውስተ አፉሃ ቈጽለ ዘይት ።

ርግብም በአፍዋ የዘይት ቅጠል ይዛ ማታ ጊዜ ወደ ኖኅ ተመልሳ መጣች፤ (ሐተታ) ውሃው ደረቀ የምስራች ስትል ነው ፤

ወአእመረ ኖኅ ከመ ነትገ ማይ እምድር ።

ኖኅም ውሀው እንደጐደለ አወቀ፤

፲፪፤ ወተዐገሠ ሰቡዐ መዋዕለ ካዕበ ፈነዋ ለርግብ ።

ሰባት ቀን ታግሦ ዳግመኛ ርግብን ላካት፤

ወኢደገመት ገቢአ ኀቤሁ ።

ዳግመኛም ወደርሱ አልተመለሰችም፤ (ሐተታ) ኤርምያስ፣ አግብአት ሥልሰ ቃላ ለኖኅ ይላል፤ ከዚህ ኢደገመት አለ፣ አይጣላምን ቢሉ አይጣላም ፣ ሁሉም አንድ ነው፤ በፊት ላካት እግርዋን የምታሳርፍበት አጥታ ተመልሳ መጥታለች፤ ሁለተኛ ላካት የዘይት ቅጠል ይዛ መጣች፤

www.ethiopianorthodox.org

ሦስተኛ ላካት፣ ውሀው ከደረቀ እንግዲህ ወዲህ እናንተ ወደኔ ትመጣላችሁ እንጂ፣ እኔ ወደ እናንተ እመጣለሁን ስትል ቀር ታለችና፤ ይህ መቅረትዋ፣ የውሀውን መድረቅ የሚያስረዳ ስለ ሆነ ኤርምያስ መቅረትዋን ስለ መምጣት ቈጥሮላት፤ አግብአት ሥልሰ ቃላ አለ፤ ከዚህ ሦስተኛ አለመመለስዋን ሲያይ ኢደገመት አለ ፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ርግብ፣ የመንፈስ ቅዱስ፤ ቋዕ (ቁራ) ፣ የሰይጣን ፣ ርግብ ውሀው ደረቀ የምስራች ስትል የዘይት ቅጠል ይዛ ታይታለች፤ መንፈስ ቅዱስም ፍዳ መርገም ጠፋ ሲል በርግብ አምሳል ታይቶአልና፣ ቋዕ (ቁራ) የሰይጣን ምሳሌ፣ ቁራ በዋለበት እንደቀረ፤ የኖኅንም ፈቃድ እንዳልፈጸመ፤ ሰይጣንም የጌታን ፈቃድ አይ ፈጽምምና ፤ አንድም ርግብ የወንጌል፣ ቋዕ የኦሪት ምሳሌ ነው፤ አንድም ርግብ የእመቤታችን ምሳሌ ናት ፤ ርግብ ሐፀ ማየ አይኅ፣ ስትል ቈጽለ ዘይት ይዛ እንደ ታየች ፣ እመቤታችንም ሐፀ ማየ መርገም ስትል ጌታን ፀንሳ ተገኝታለችና ፤ አንድም ወደገመት ይላል አብነት ፤

፲፫፡ ወአመ ኮነ ስድስቱ ምእቱ ወአሐደ ዓመተ ሕይወቱ ለኖኅ አመ ርእሰ ሠርቀ ወርኀ ቀዳማይ ኀልቀ ማይ እምድር ፣

የኖኅም ዘመኑ ስድስት መቶ አንድ ዓመት በሆነ ጊዜ በመጀመሪያው ወር በሚያዝያ መባቻ ውሀው ከምድር ፈጽሞ ደረቀ፤

ወከሡተ ኖኅ ጠፈረ ለታቦት እንተ ገብረ ፣

ኖኅም የብርሃን መግቢያ ልት ሆን የሠራትን የመርከብዋን መስኮት ከፈተ፤

ወርእየ ከመ ኀልቀ ማይ እምገጸ ምድር ፣

ውሀው፣ ከምድር ላይ ፈጽሞ እንደ ደረቀ አየ ፤

፲፬፡ ወበካልእ አመ ዐሡሩ ወሰኑዩ ለጽልመት የብሰት ምድር ፣

በሁለተኛውም ወር ግንቦት በባተ ጨረቃ ጠፍ አድራ ሠርቅ ባደረገች፤ አንድም ብርሃንዋን ባጣች፤ ሕፀፅ ባደረገች በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ምድር ፈጽማ ደረቀች፣ በዓመቱ ማለት ነው ፤

፲፭፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ፣

እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው ፤

፲፮፡ ፃእ እምነ ታቦት አንተ ወብእሲትከ ወደቂቅከ ወአንስትያ ደቂቅከ፣

እግዚአብሔርም ኖኅን አንተ፣ ሚስትህን፣ ልጆችህን፣ የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ አለው ፤

፲፯፡ ወኵሎ ዘሀሎ ምስሌከ ፣

ካንተ ጋራ ያለውም ሁሉ ይውጣ አለው ፤

ወኵሎ ዘሥጋ እምአዕዋፍ እስከ እንስሳ፣ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር አውፅእ ምስሌከ ፣

ይፃእ ሲል ነው ፤ ከአዕዋፍ ጀምሮ እስከ እንስሳ ያለውም ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውም ጥቃቅኑ ፍጥረት ሁሉ ካንተ ጋራ ይውጣ አለው ፤

ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር፣

ብዙ፣ የብዙ ብዙ ሁኑ፣ ምድርንም ምሉአት አለው ፤

፲፰፡ ወወፅአ ኖኅ ወብእሲቱ ወደቂቁ ወአንስትያ ደቂቁ ምስሌሁ ፣

ኖኅም ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ የልጆቹንም ሚስቶች ይዞ ከመርከብ ወጣ፤

፲፱፡ ወኵሎ አራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፍ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር በበዘመዱ ወፅኡ እምታቦት ፣

አራዊትና እንስሳት አዕዋፍም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታትም ሁሉ በየወገናቸው ከመርከብ ወጡ ፤ (ሐተታ) ከሚበሉት አምስት ፤ ከማይበሉት አምስት አስቀርቶ ሰዶአቸዋል፤ ከሚበሉት ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ ፣ ንህብ ናቸው ፤ ከማይበሉቱ ፈረስ ፣ በቅሎ ፣ አህያ፣ ውሻ፣ ድመት ናቸው፤ ይህም ምሳሌ ነው፤ መርከብ የሥልጣነ እግዚአብሔር፣ ኖኅ ከነልጆቹ የጻድቃነ ብሊት ፣ በውስጥ ያሉትን ማየ አይኅ አላገኛቸውም ፤ ጻድቃነ ብሊትንም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሥቃየ ገሃነም አላገኛቸውም ፣ ምግባራቸው እንደ ድንኳን እንደ አጎበር ሁኖላቸው በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀው ይኖሩ ነበር እንጂ ፤ ነፍሶሙስ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ሥቃየ ገሃነም እንዲል ፤ ጥበ. ፫:፩፤ ከመርከብ በአፍአ ያሉቱ የኃጥአነ ብሊት ፤ በአፍአ ያሉትን ማየ አይኅ አጥፍቶአቸዋል፤ ኃጥአነ ብሊትንም ሥቃየ ገሃነም አግኝቶአቸዋል፤ አንድም መርከብ የእመቤታችን፣ ኖኅ የጌታ፣ በቀኝ በግራ ያሉቱ በእመቤታችን ቃል ኪዳን ያመኑ የሕዝቡ የአሕዛቡ ምሳሌ፤ አንድም መርከብ የመስቀል፣ ኖኅ የጌታ ፣ በቀኝ በግራ ያሉቱ የፈያታዊ ዘየማንና የፈያታዊ ዘፀጋም ምሳሌ ናቸው ፤ አንድም መርከብ የጥምቀት፣ ኖኅ ከነልጆቹ የጥሙቃን ፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ ጥምቀት በሦስቱ



www.ethiopianorthodox.org

ሥላሴ ስም ነውና ፤ አንድም መርከብ የቤተ ክርስቲያን ፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ ቤተ ክርስቲያንም ሦስት ክፍል ናትና ፣ ኖኅ ከነልጆቹ የምእመናን ምሳሌ ፤ አንድም መርከብ የትንሣኤ፣ ኖኅ ከነልጆቹ የሙታን ፣ ሦስት ክፍል መሆንዋ የትንሣኤያችን ፣ በኵር ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል፣ እኛም በሦስተኛው ንፍሐተ ቀርን እንነሣለንና ፤ እስመ ውእቱ ቀሠፈነ ወይፈውሰነ ወውእቱ አቍሰለነ ወይሔርየነ ወያሐይወነ በሰኑይ መዋዕል፣ ወአመ ሣልስት ዕለት ንትነሣእ ወነሐዩ በቅድሚሁ እንዲል፤ ሆሴ: ፮:፪ ፤

፳፤ ወነደቀ ኖኅ ምሥዋዐ ለእግዚአብሔር ፣

ኖኅ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚሠዋበትን ሠራ ፤

ወነሥአ እምእንስሳ ወእምኵሉ ዘንጹሕ ወአዕረገ ቍርባነ ዲበ ምሥዋዕ ፣

መሥዋዕት ከሚሆነው ሁሉ ከእንስሳ ወገን አምጥቶ በመሠዊያው ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤

፳፩፤ ወአጼነወ እግዚአብሔር መዓዛ ሠናየ ፣

ጌታም ያማረ የተወደደ መሥዋዕት በጎ መዓዛ አድርጎ ተቀበለለት ፤

ወይቤ እግዚአብሔር ሐለይኩ ከመ ኢይድግም ረጊሞታ ለምድር በእንተ ምግባሩ ለዕጓለ እመሕያው፣

እግዚአብሔር ሰው ኃጢአትን ስለ ሠራ ሁለተኛ ምድርን እንዳላጠፋት አላጠፋትም ብዬ ተናገርኹ አለ ፤

እስመ ሥዑም ውስተ ልቦሙ ለዕጓለ እመሕያው እከይ በኵሉ ጊዜ እምንእሰሙ ፣

ንቡር ድልው ሲል ነው፤ ከሕፃንነታቸው (ከጥቂትነታቸው) ጀምሮ ሁልጊዜ በሰው ልቡና ኃጢአት ሰፍኖ ይኖራልና ፣ ምንም ቢኖር ሁለተኛ አላጠፋትም ብዬ ተናገርኹ አለ ፤

ወኢይደግም እንከ አማስኖቶ ለኵሉ ዘሥጋ ዘሕያው ፣

በደመ ነፍስ ሕያው ሁኖ የሚኖረውን ሁሉ እንግዲህ ወዲህ አላጠፋም፤

፳፪፤ በከመ ገበርኩ ኵሎ መዋዕሊሃ ለምድር ፣

ምድር ጸንታ የምትኖርበትን ዘመን ሁሉ እንደ ፈጠርኹ ፤

ዘርእ ወማዕረር፤ ቍር ወሐፍ፣ ሐጋይ ወክረምት፤ መዓልት ወሌሊት ኢይትነደግ ፣

ዘርና መከር፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት ፣ መዓልትና ሌሊት መፈራረቅ አይቀርም አይቅር ፡፡



## ምዕራፍ ፱

፩፤ ወባረኮሙ እግዚአብሔር ለኖኅ ወለደቂቁ ፣

እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን አከበራቸው ፣ አበዛቸው አዘዛቸው ፤

ወይቤሎሙ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር ወኰንንዋ ፣

ብዙ፣ የብዙ ብዙ ሁኑ፣ ምድርንም ምሉአት፣ ግዙአት፣ ብሎ አዘዛቸው ፤

፪፤ ወይፍርሁክሙ ወይርዐዱ እምኔክሙ ኵሉ አራዊተ ገዳም ወአዕዋፈ ሰማይ ፣

የዱር አራዊት፣ እንስሳት፣ የሰማይም አዕዋፍ ሁሉ እናንተን ይፍሩዋችሁ ፣ ይንቀጥቀጡላችሁ ፤ (ሐተታ) ይኸውም አልቀረ ፣ ዛሬ አራዊት ሰው ያዩ እንደሆነ የሚሸሹ ይህ ቃል ኪዳን ይዟቸው ነውና ፤

ወእንስሳ ወዘይትሐወስ ዲበ ምድር ወዓሣተ ባሕር ወሀብኩክሙ ውስተ እደዊክሙ ይኩንክሙ ለክሙ ፣

እንስሳትን በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውንም ፍጥረት በባሕር ያሉ ዓሣትንም ምግብ ይሁኑአችሁ ብዬ በእጃችሁ የተያዙ አድርጌ ሰጥኋችሁ ፤

፫፤ ወኵሉ ዘይትሐወስ ዘሕያው ለክሙ ይኩንክሙ መብልዐ ፣ ከመ ሐመልማለ ሣዕር ወሀብኩክሙ ኵሎ፣

እህሉን፣ ተክሉን፣ ምግብ አድርጌ እንደ ሰጠኋችሁ፣ በደመ ነፍስ ሕያው የሆነውን፤ ተንቀሳቃሹንም ሁሉ ምግብ ይሁናችሁ ብዬ ሰጠሁአችሁ ፤

፬፤ ወባሕቱ ኵሎ ሥጋ ዘቦ ደም ኢትብልዑ ፣

ነገር ግን ደም ያለበትን ሥጋ ሁሉ አትብሉ ፤

እስመ ደም ነፍስክሙ ውእቱ ፣

ደም ነፍሳችሁ ነውና፤ (ሐተታ) የበሉት የጠጡት ደም ይሆናል፣ በዚያው ላይ ነፍስ ታድራለችና ነፍስክሙ አለ ፤ እስመ ነፍስ ተኃድር በደም እንዲል (ዘሌ. ፲፯:፲፬)፤ አንድም ነፍስ በባሕርይዋ መብላት የለባትም ብሎ የአሕዛብ ሥራ ነውና ደምን አትብሉ አለ ፤ ደሙን አርግተው ቈልተው ይበሉታልና ፤

፭፤ ወእትኃሠሥ እምእደ አራዊት፣

እንግዲህ ወዲህስ አራዊት ሰውን በግፍ ቢገድሉ ከአራዊት ደሙን እመራመራለሁ ፤

ወእምኵሉ እደ ሰብእ ፣

ሰውም አራዊትን በግፍ ቢገድል ደማቸውን ከሰው እመራመራለሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምእደ ብእሲ ዘእኁሁ እትኃሠሥ ነፍሰ ኵሉ ዕጓለ እመሕያው ።

ወንድም ወንድሙን በማይገባ ቢገድል፣ ደሙን ከገዳዩ እመ ራመራለሁ ፤

፮፡ ወዘከዐወ ደመ ሰብእ ህየንተ ደመ ዝኩቱ ይትከዐው ደሙ ።

የሰውን ደም በማይገባ ያፈሰሰ ደሙ ይፈስሳል ይፍሰስ ፤

እስመ በአምሳለ እግዚአብሔር ገበር ክዎ ለሰብእ ።

ሰውን በእኔ አምሳል ፈጥሬዋ ለሁና ፤ ሐተታ እንዳለፈው (ም. ፩:፳፯) ፤

፯፡ ወአንትሙሰ ብዝኑ ወተባዝኑ ወምልዕዋ ለምድር ።

እናንተ ግን ብዙ፣ የብዙ ብዙ ሁኑ ፣ ምድርንም ምሉዋት ፤

፰፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ወለደቂቁ ምስሌሁ እንዘ ይብል ።

እግዚአብሔርም ኖኅን ከልጆቹ ጋራ እንዲህ አለው ፤

፱፡ ናሁ አቀውም ኪዳንየ ምስሌክሙ በዲበ ምድር ።

መሐላዬን በምድር ላይ ለናንተ እነሆ አጸናለሁ ፤

ወምስለ ዘርእክሙ እምድኅሬክሙ፣

ከእናንተ በኋላ ለሚነሡ ለልጆ ቻችሁም መሐላዬን አጸናለሁ፤

፲፡ ወለኵሉ ነፍስ ሕያው እንተ ምስሌክሙ አዕዋፍ ወእንስሳ ወአራ ዊተ ምድር ዘወዕኡ እምታቦት ።

ከናንተ ጋራ ከመርከብ ለወጡ በደመ ነፍስ ሕያዋን ለሆኑ፣ ለአዕዋፍ ለእንስሳም ለአራዊትም መሐላዬን አጸናለሁ ፤

፲፩፡ አቀውም ኪዳንየ ምስሌክሙ ወኢይመውት ኵሉ ዘሥጋ በማየ አይኅ ።

እንግዲህ ወዲህ በየኃጢአቱ አጠፋዋለሁ እንጂ ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ አንድነት በማየ አይኅ እንዳይጠፉ ከእናንተ ጋራ እንደ እናንተ መሐላዬን አጸናለሁ ፤

ወኢየመጽእ እንከ ማየ አይኅ ለአማ ስኖ ኵሉ ምድር ።

ምድርንም ሁሉ ለማጥፋት ዳግ መኛ ማየ አይኅን አላመጣም ፤

## ገባኤ

፲፪፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ፣

እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው ፤

ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ኪዳንየ ዘእ ሁበክሙ አነ ።

እኔ የምሰጣችሁ የመሐላዬ ምል ክት ይህ ነው፤

ማዕከሌየ ወማዕከሌክሙ ።

በኔና በናንተ መካከል ምልክት ሊሆን ጸንቶ የሚኖረው፤



ወማዕከለ ኵሉ ነፍስ ሕይወት እንተ ሀለወት ምስሌክሙ ለትውልድ ዘለ ዓለም ።

በደመ ነፍስ ሕያዋን በሚሆኑ፣ ለልጅ ልጅ ዘመን ከእናንተ ጋራ በሚኖሩ ፍጥረታትም መካ ከል የምሰጣችሁ ምልክት ይህ ነው፤ አንድም ምልክት ሊሆን፤

፲፫፡ እሠይም ቀስትየ በውስተ ደመና ።

የዕርቅ ምልክት የምትሆን ቀስ ቴን (ብርሃኔን) በደመና ላይ ሥዬ አሳያለሁ ፤

ወትከውን ተአምረ ለኪዳንየ ማዕ ከሌየ ወማዕከሌክሙ ፣ ወማዕከለ ምድር ።

በእኔና በእናንተ በምድርም መካከል ምልክት ትሆናለች ፤

፲፬፡ ወትከውን ሶበ አጸለምን ደመና ላዕለ ምድር ታስተርኢ ቀስትየ በላ ዕለ ደመና ።

ትከውንና ታስተርኢ አንድ ወገን ፤ ደመናን በምድር ላይ ባዞርኹ ጊዜ፣ ቀስቴ በደመናው ላይ ተሥላ ትታያለች ፤

፲፭፡ ወእዜክር እንከ ኪዳንየ ዘሀሎ ማዕከሌየ ወማዕከሌክሙ ።

እንግዲህም በእናንተና በእኔ መካከል ያለውን ቃል ኪዳን አስቤ ፤

ወማዕከለ ኵሉ ነፍስ ሕይወት ፣ ወበኵሉ ዘሥጋ ።

በደመ ነፍስ ሕያው በሚሆንና በሥጋዊ በደማዊ መካከል ሁሉ ቃል ኪዳኔን አስቤ ፤

ኢየመጽእ ማየ አይኅ ከመ አደ ምስሶ ለኵሉ ዘሥጋ ።

ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ አጠፋ ዘንድ ማየ አይኅን አላመጣም፤

፲፮፡ ወትወዕእ ቀስትየ በደመና ወእ ሬእያ ከመ እዜክር ኪዳንየ ዘለዓለም ዘማዕከሌየ ወማዕከለ ኵሉ ዘሥጋ ዘቦ መንፈስ ሕይወት ዘሀሎ መልዕ ልተ ምድር ።

በምድር ላይ ባለ በደመ ነፍስ ሕያው ሆኖ በሚኖር በሥጋዊ በደማዊ ሁሉና በእናንተ መካ ከል የሚሆን መሐላዬን አስብ ዘንድ፣ የዕርቅ ምልክት የምት ሆን ቀስቴን በደመና ተሥላ አያታለሁ ፤

፲፯፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኖኅ፣

እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው ፤

ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ኪዳንየ ዘአቀውም ማዕከሌየ ወማዕከሌክሙ፣

በኔና በናንተ መካከል ለዘላለሙ የማጸናው የቃል ኪዳኔ ምል ክት ይህ ነው፤ (ሐተታ) ይህን ንስ ቀስተ ደመና እንደምን አድርጎ አሳይቶታል ቢሉ፣ በቀ

www.ethiopianorthodox.org

ስተኛ ልማድ አሳይቶታል ፣ ቀስተኛ የሚነድፍ የሆነ እንደ ሆነ፣ አውታሩን ወደርሱ፣ ደጋኑን ወደ ጠላቱ ያደርገዋል ፤ የማይነድፍ የሆነ እንደሆነ ፣ ደጋኑን ወደርሱ ፣ አውታሩን ወደ ጠላቱ ያደርገዋል፤ ጌታም አላጠፋችሁም ሲል፣ ደጋኑን ወደርሱ አውታሩን ወደ ኖኅ አድርጎ አሳይቶታል፤ እንዲህ አድርጎ ያሳየው ስለምን ነው? ቢሉ፤ ይህ ቀስተ ደመና ኅባባ ነው ኅብሩም ብዙ ነው፣ ሰው በብዙ ወገን ቢበድለኝ በየኃጢአቱ አጠፋዋለሁ እንጂ፣ ባንጹ ኃጢአት ሁሉን አላጠፋም ሲል ነው፤ አንድም ይህ ቀስተ ደመና ኅብሩ አራት ነው፤ ቀይ፣ ነጭ፣ ጥቁር ፣ ቢጫ ስለምን ነው እንዲህ አድርጎ ያሳየው? ቢሉ፣ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰው ቢበድለኝ ፣ አራቱን ባሕርያት ተዋሕጄ አድነዋለሁ ሲል ነው ፤ ይህም ምሳሌ ነው ፤ ቀዩ የእሳት ባሕርይ፣ ነጩ የውሀ ባሕርይ ፣ ጥቁሩ የነፋስ ባሕርይ ፣ እስመ ነፋስ ጸሊም በአርአያሁ እንዲል ፤ ብጫው የመሬት ባሕርይ ነው ፤ አንድም ጐልቶ የሚታየው እሳትና ውሀ የመሰለው ነው፤ ስለምን ነው እንዲህ አድርጎ ያሳየው ቢሉ፣ ከዚህ አስቀድሞ ሰውን በንፍር ውሀ እንዳጠፋሁ እንግዲህ ወዲህ ሰውን በንፍር ውሀ አላጠፋውም ሲል ነው ፤ ይህም ምሳሌ ነው ፤ እሳት የመንፈስ ቅዱስ ፣ ውሀ የጥምቀት ፣ ጥቁሩ የደሙ፣ ብጫው፣ የሥጋው ፣ ደመና የእመቤታችን ምሳሌ፣ በጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ በሥጋዬ፣ በደሜ አድንነለሁ ሲል ነው ፤

ይህም ቀስተ ደመና ዛሬ መታየቱ ለከንቱ አይደለም፤ የእናንተ ኃጢአት የሰብአ ትካትን ኃጢአት አከለ፤ እኔ ግን እንዳላጠፋችሁ በኖኅ መሐላ ጸንቻለሁ ሲል እንዲህ አድርጎ ያሳያል ፣ ደመና ኖኅ የደኅንነት ምልክት እንደሆነች ፣ እመቤታችንም የድኅነት ምልክት ናትና ፤

፲፰፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቁ ለኖኅ እለ ወፅኡ እምውስተ ታቦት፣ ሴም፣ ወካም፣ ወያፌት ፣

ከመርከብ የወጡት የኖኅ ልጆች እሊህ ናቸው ሴም ፣ ካም ፣ ያፌት ናቸው ፤

ወካምሰ አቡሁ ውእቱ ለከነዓን ፣

ካም የከነዓን አባት ነው፤ (ሐተታ) ስለምን ለይቶ ወካምሰ ብሎ አነሣው ቢሉ አሁን ወደ ፊት ከነዓን አይቶ ለካም ነገረው፤ ካም በአባቱ ሳቀበት የሚል ነውና፣ እንደ አርእስት አነሣው፤

፲፱፤ ወእሉ ሠለስቱ ደቂቁ ለኖኅ እለ ተዘርኡ ውስተ ኵሉ ምድር ፣

በዓለም ሁሉ የሰው ዘር የሆኑ የኖኅ ሦስት ልጆች እነዚህ ናቸው ፤ አንድም እለ ተዘርወ ይላል፣ በዓለም ሁሉ የተበተኑ እኒህ ናቸው ፤

፳፤ ወእምድኅረ አይኅ አኀዘ ኖኅ ይትገበራ ለምድር ፣

ከማየ አይኅ በኋላ ኖኅ ምድርን ያርማት ይኰተኵታት ጀመር፤

ወተከለ ዐፀደ ወይን ፣

የወይን ሐረግ ተከለ፤

፳፩፤ ወሰትየ እምኔሁ ወሰክረ ወተዐርቀ በውስተ ቤቱ ፣

ከወይኑም ጠጥቶ ሰክሮ በቤቱ ውስጥ ዕርቃኑን ጣለ፤ (ሐተታ) አሁን ወይን ተከለ አለ፣ ወዲያውም ከዚያው ከተተከለው ወይን ጠጥቶ ሰከረ አለ ፤ እንደምን ነው ከወዴት አግኝቶ ጠጣ ቢሉ ከማየ አይኅ የተረፈውን አቀናንቶ አፍርቶለት ጠጥቷል፤ ከማየ አይኅስ የተረፈ የለም ብሎ እንደ ፌሾ ያለ ፈጥኖ የሚደርስ ወይን አለ ፣ ያንን ተክሎ አፍርቶለት ጠጥቶአል፤ አንድም በተአምራት ዕለቱን ደርሶለት ጠጥቶአል ፤ አንድም በሚገባ የተተከለ ነው ፤ ወይን በተተከለ በሦስት ዓመቱ ያፈራል ፤ የመጀመሪያውን አዕዋፍ ይበሉታል፤ የአራተኛው ዓመት ለቤተ እግዚአብሔር ይሆናል፤ የአምስተኛው ዓመት ለባለቤቱ ይሆናል ፣ ያንን ጠጥቶ ሰከረ ፤

፳፪፤ ወርእየ ካም አቡሁ ለከነዓን ፣ ዕርቃነ አቡሁ ሰሐቀ ወወፅአ ወነገሮሙ ለክልኤሆሙ አኃዊሁ በአፍአ፣

የከነዓን አባት ካም፣ አባቱ ዕርቃኑን እንደ ጣለ አይቶ ዘበተበት፤ ወጥቶም በአፍአ (በውጭ) ሳሉ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው ፤

፳፫፤ ወነሥኡ ሴም ወያፌት ልብሰ ወወደዩ ክልኤሆሙ ዲበ ዘባናቲሆሙ ወሖሩ ድኅሬተ ወከደኑ ዕርቃነ አቡሆሙ ፣

ሴምና ያፌትም ያንዳቸውን ልብስ ለብሰው ያንዳቸውንም ልብስ በስተኋላቸው ጋርደው፣ የሚወጡ መስለው ፊታቸውን ወደ ውጭ መልሰው የኋሊት ገብተው አባታቸውን ያንዳቸውን ልብስ አለበሱት ፤

ወገጾሙ ድኅሬሆሙ አግብኡ ወኢርእዩ ዕርቃነ አቡሆሙ ፣

ፊታቸውንም ወደ አባታቸው ቢመልሱ የአባታቸውን ዕርቃን አላዩም ፤ አንድም ፊታቸውን ወደ ውጪ መልሰው ወጡ ፣



www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወሶበ ጽሕወ ኖኅ እምስካረ ወይኑ ፤

ኖኅም ከወይኑ ስካር በነቃ ጊዜ፤

አእመረ ኵሉ ዘገብረ ቦቱ ወልዱ ዘይንእስ ፤

ዘይንእሶ ለሴም ነው ፤ ከሴም ቀጥሎ ካም ፤ ከካም ቀጥሎ ያፌት፤ ይወለዳሉና፤ ከስካሩ በነቃ ጊዜ ከሴም የሚያንስ ልጁ ካም ያደረገበትን ሁሉ አወቀ፤ አንድም የወይን ስካር ፈጽሞ አእምሮን አያሳጣምና ታናሹ ልጁ ከነዓን ያደረገውን አወቀ፤ ማለት ከነዓን አይቶ ለካም እንደ ነገረው፤ ካም እንደ ዘበተበት፤ ያፌትና ሴም ልብሳቸውን እንዳ ለበሱት አወቀ፤ አንድም ባወቀ ጊዜ ፤

፳፭፤ ወይቤ፤ ኖኅ ርጉመ ለይኩን፤ ከነዓን ገብረ ወነባሬ ይኩን ለአኃዊሁ፤

ከነዓን ርጉም ይሁን፤ ለወንድሞቹም ቤተሰብ ተገዥ ይሁን አለ ፤ (ሐተታ) የሳቀበት ካም አይደለምን? ስለምን ከነዓንን ረገመው ቢሉ አይቶ ለካም የነገረው ከነዓን ነውና፤ አንድም የልጅ ጉዳት ለአባቱ ነውና፤ አን ድም ወባረኮሙ ብሎ ነበርና፤ እግዚአብሔር የመረቀውን መር ገም አይገባም ሲል ነው ፤

ይህም ምሳሌ ነው፤ ኖኅ የጌታ፤ ኖኅ በወይን ስክሮ ራቁቱን እን ደሆነ ጌታም በፍቅረ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ተስቦ ራቁቱን ተሰቅሎአልና፤ ካም የጸሐፍት የፈሪሳውያን ምሳሌ፤ ካም አይቶ እንደ ዘበተበት፤ ጸሐፍት ፈሪሳ ውያንም በጌታ ዘብተውበታ ልና፤ ሴምና ያፌት የዐሐይና የጨረቃ ምሳሌ፤ ሴምና ያፌት ልብሳቸውን ተገፈው እንዳለበ ሱት፤ ዐሐይና ጨረቃም ብር ሃናቸውን ተገፈው የጌታን ዕር ቃን ሠውረዋልና፤ አንድም የዮ ሴፍና የኒቆዲሞስ ምሳሌ ናቸው፤ እነዚያ ልብሳቸውን እንዳለበ ሱት ዮሴፍና ኒቆዲሞስም በድ ርብ በፍታ ገንዘው ቀብረውታ ልና ፤

፳፮፤ ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለሴም ፤

የሴም ፈጣሪው እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ፤

ወይኩን ከነዓን ገብሮ ፤

ከነዓንም የሴም ተገዥ ይሁን አለ ፤

፳፯፤ ወያርኅብ እግዚአብሔር ብሔሮ ለያፌት ፤

ለያፌትም ግዛቱን እግዚአብሔር ያስፋለት አለ ፤ (ሐተታ) ይኸ ውም ይታወቅ ዘንድ የልጆቹ ከተማ (ሀገር) ሰማንያ ቀን ያስ ገዛል ፤



ወይኅድር ውስተ ቤቱ ለሴም ፤

እግዚአብሔር በሴም፣ በወገኖቹ ይደር፤ አንድም ጌታ ከነገደ ሴም ከተወለደች ከእመቤታ ችን ከነፍስዋ ነፍስ፣ ከሥጋዋ ሥጋ ነሥቶ በማኅጸንዋ አድሮ ሰው ይሁን፤

ወይኩን ከነዓን ገብሮ ፤

ከነዓንም የሴም ተገዥ ይሁን፤

፳፰፤ ወሐይወ ኖኅ እምድኅረ አይኅ ሠለስተ ምእተ ወሃምሳ ዓመተ ፤

ኖኅም ከማየ አይኅ በኋላ ሦስት መቶ አምሳ ዘመን ኖረ፤

፳፱፤ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለኖኅ ተስዓተ ምእተ ወሃምሳ ዓመተ ወሞተ፤ የኖኅ መላ ዘመኑ ዘጠኝ መቶ አምሳ ዘመን ሆነ ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ::

## ምዕራፍ ፲

፩፤ ወከመዝ ውእቱ ልደቶሙ ለደ ቂቀ ኖኅ፣ ሴም፣ ወካም፣ ወያፌት፣

የኖኅ ልጆች፣ የሴም፣ የካምና የያፌት፣ ትውልዳቸው እንዲህ ነው ፤

ወተወልዱ ሎሙ ደቂቅ እምድኅረ አይኅ ፤

ከማየ አይኅ በኋላ ልጆች ተወ ለዱላቸው ፤

፪፤ ወደቂቀ ያፌት፣ ጋሜር፤ ወያኅግ ወማዴ፣ ወይህያን፣ ወቶቤል፣ ወሞ ሳህ፣ ወቴርሳ ፤

የያፌትም ልጆች ፣ ጋሜር ፣ ያኅግ፣ ማዴ፣ ይህያን፣ ቶቤል፣ ሞሳህ፣ ቴርሳ ናቸው፤ (ሐተታ) ያኅግ የጎግ ማጎግ አባት ነው፤ ማዴ የሚዶናውያን አባት ነው፤ ይህያንም የዮናናውያን አባት ነው ፤ ዮናናውያንም የተባሉ ጽርአውያን ናቸው፤ ቶቤልም የብርቱኳል፣ የመቄዶናውያን አባት ነው፣ ሞሳህ የዮሳክኒን፣ የቱርክም አባት ነው ፤ ቴርሳ ዕንቁ ማለት ነው፣ ይኸውም በደሴት የሚኖሩ የነጋድያን አባት ነው ፤

፫፤ ወደቂቀ ጋሜር አስባንሶ ወኤራ ፌት ወቴርጋሞ ፤

የጋሜርም ልጆች ፤ አስባንሶ ኤራፌት ቴርጋሞ ናቸው ፤

፬፤ ወደቂቀ ይህያን፣ ኤልሳ፣ ወኤው ትራስስ፣ ወቁጥኤ፣ ወሮድኢ ፤

የይህያንም ልጆች ኤልሳ ፤ ኤውትራስስ፣ ቁጥኤ፣ ሮድኢ ናቸው ፤

፭፤ ወእምነ እሉ ተፈልጡ ደሰያቲ ሆሙ ለአሕዛብ ፤

ከእነዚህም የተወለዱ አሕዛብ የሚኖሩበት አገራቸው ተለየ፤

www.ethiopianorthodox.org

በበምድሮሙ ለለአሐዱ ፩፩ በበነገሮሙ ፤ ወበበነገዶሙ ወበበሕዘቢሆሙ ፤

አንዱም አንዱ በየወገናቸው በየነገዳቸው በየቋንቋቸው የሚኖሩበት አገር ሁሉ ተለየ ፡፡

፮፡ ወደቂቀ ካም ኩሳ ፤ ወምስጥ ያርም፤ ወፉጥ፤ ወከነዓን ፤

የካምም ልጆች ኩሳ ፤ ምስጥ ያርም፤ ፉጥ፤ ከነዓን፤ ናቸው፤ (ሐተታ) ኩሳ (ኩሽ) የኢትዮጵያ አባት ነው፡ ምስጥ ያርም የም ሥራውያን አባት ነው፤ ፉጥ የልዳ አባት ነው ፤ ከነዓንም የዐሥሩ አንዱ ነገደ ከነዓን አባት ነው ፡ ዐሥሩ አንዱን ነገደ ከነዓን ወደፊት ያመጣቸዋል ፡

፯፡ ወደቂቀ ኩሳ ሶባ ወኤውላጥ ወሶቤቅታ ወራጌም ወሰብቃታ ፤

የኩሳ ልጆችም ሶባ፤ ኤውላጥ፤ ሶቤቅታ ፤ ራጌም ፤ ሰብቃታ ናቸው ፡

ወደቂቀ ራጌም ሶባ ወዮዳድን ፤

የራጌምም ልጆች ሶባና ዮዳድን ናቸው ፡

፰፡ ወኩሳ ወለዶ ለናምሩድ ፤

ኩሳም ናምሩድን ወለደ፡ ናምሩድ ማለት አዳኝ ማለት ነው፡ አንድም አርበኛ ማለት ነው ፡

ወውእቱ ዘኮነ ያርብሐ ነዓዌ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ይኸውም ናምሩድ እግዚአብሔር በሚያውቀው ነገር ዓርበኛ ሆነ ፤ ቅድመ እግዚአብሔር አለ፤ እግዚአብሔርን ልውጋ ያለ ይህ ናምሩድ ነውና ፡

፱፡ ወበእንተ ዝንቱ ይቤሉ ከመ ናምሩድ ያርብሐ ዘኮነ ነዓዌ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

ስለዚህም ነገር ሰዎች እንደ ናምሩድ እግዚአብሔርን አድናለሁ ያለ ዓርበኛ የለም አሉ ፡

፲፡ ወኮነ ቅድመ ጥንተ መንግሥቱ በባቢሎን ፤

አስቀድሞ የመንግሥቱ መጀመሪያ በባቢሎን ሆነ ፡

ይህ ናምሩድ ከኃይለኛነቱ የተነሣ ዘውድ ሠውሮ አሠርቶ ከሰማይ ወረደልኝ ብሎ በባቢሎን ነግሦአል ፡

ወኤሬ ወአርከድ ወካሌድን በምድረ ሰናዖር ፤

ኤሬ፤ አርከድ፤ ካሌድን፤ በሰናዖር የሚኖሩ የኩሳ ልጆች ናቸው፡ አሁን በሰናዖር ግንብ ሠሩ የሚል ነውና እንደ አርእስት አነሣቸው ፡



፲፩፡ ወእምይእቲ ምድር ወፅአ አሦር፤

ከዚህችም ከሰናዖር አሦር የሚባል ዓርበኛ ተነሣ፤ ይህ አሦር የጨኪ ረዳት ቦለድ ነው ፡

፲፪፡ ወነደቃ ለነነዌ ወለሮቢት ሀገር ዐባይ ፤

እርሱም እኒህን ሁለቱን አገሮች ነነዌንና ሮቢትን ቀጸራቸው፡

፲፫፡ ወምሥጥ ያርም ወለዶሙ ለለደልኪም ወለሰሚጡዓም፡ ወለሩቤኤል ወለንፍቤኤም ወለጴዮርስናአም ፤ ወለኮስሮኖዓም ፤

ምስጥ ያርም የሚባለውም ለደልኪምን፤ ሰሚጡዓምን፤ ሩቤኤልን፤ ንፍቤኤምን፤ ጴዮርስናአምን፤ ኮስሮኖዓምን ወለደ ፡

፲፬፡ ወእምኔሁ ወፅኡ ፍልስጥኤም ወቅፍርኖኤም ፤

ከእርሱም ፍልስጥኤምና ቅፍርኖኤም ተወለዱ፡ እነዚህም አራቱ ነገደ ፍልስጥኤም ናቸው፡

፲፭፡ ወከነዓን ወለዶ ለሲዶን በኵሩ ወለኬጤዎን ፤

ከነዓንም የበኸር ልጁን ሲዶንን፤ ኬጤዎንንም ወለደ፡

፲፮፡ ወለኢያቡሴዎን ወለአሞሬዎን ወለጌርጌሴዎን ፤

ኢያቡሴዎንን ፤ አሞሬዎንን ፤ ጌርጌሴዎንን ፡

፲፯፡ ወለኤዌዎን፤ ወለፌርዜዎን፤ ወለሲዎን ፤

ኤዌዎንን ፤ ፌርዜዎንን ፤ ሴዎንን፡

፲፰፡ ወለኤራዴዎን፤ ወለስማንኤር፤ ወለአማቲ ፤

ኤራዴዎንን፤ ስማንኤርን፤ አማቲን ወለደ፡ (ሐተታ) እነዚህም ዐሥሩ አንድ ናቸው ፡ ሰባቱን ኢያሱ አጥፍቶአቸዋል፤ አራቱ በዱር በገደል እየሆኑ እስራኤልን ሲያስቸግሩ ኑረዋል ፡

ወእምድኅረ ዝንቱ ተዘርው ነገደ ከነዓን ፤

ከዚህም በኋላ ዐሥሩ አንዱ ነገደ ከነዓን በሀገሩ ሁሉ ተበተኑ ፡

፲፱፡ ወኮነ ደወሎሙ ለከነዓን እምሲዶን እስከ ጌራራ ወጋዛ ፤

የእነዚህም ሀገራቸው ከሲዶን ጀምሮ እስከ ጌራራ እስከ ጋዛ ድረስ ነው፡

ወይበጽሕ ፤ እስከ ሰዶም ወገሞራ ፤ ወሲዳማ ፤ ወሲባዮ እስከ ሴላ ፤

እስከ ሰዶም፤ እስከ ገሞራ፤ እስከ ሲዳማ፤ እስከ ሲባዮ፤ እስከ ሴላ ይደርሳል ፡

፳፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቁ ለካም፤ በበነገዶሙ ወበበነገሮሙ ወበበብሔሮሙ፤ ወበበአሕዛቢሆሙ ፤

በየወገናቸው ፤ በየቋንቋቸው ፤ በየሀገራቸው ፤ የሚኖሩ የካም ልጆች እነዚህ ናቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወለሴምኒ ተወልዱ ሎቱ ደቂቅ፣

ለሴምም ልጆች ተወለዱለት ፤ (ሐተታ) ስለምን ሴምን ወደ ኋላ አመጣው ቢሉ፣ መጽሐፍ፣ ትቶት የሚሔደውን በፊት ፤ ይዞት የሚሔደውን በኋላ ማምጣት ልማዱ ነው ፣ በደቂቀ ነቢያት በፊት የአሕዛብን፣ ኋላ የእስራኤልን ፣ በኩፋሌ በፊት የኤሳውን ኋላ የያዕቆብን እን ዳመጣ፣ ከዚህም ይዞት የሚሄ ደው የሴምን ነውና በኋላ አመ ጣው ፤

ወውእቱ አቡሆሙ ለኵሉ ደቂቀ ኤቦር ፣

እርሱም ለኤቦር ልጆች ሁሉ አባታቸው ነው ፤

እኁሁ ለያፌት ዘየዐቢ ፣

የያፌት የትልቅ ወንድሙ ልጅ የሚሆን ብሎ ለኤቦር ቀጸለ ፤

፳፪፡ ወደቂቀ ሴም፣ ኤላም፣ ወአሦር፣ ወአርፋክስድ፣ ወሉድ፣ ወአራም ፣

የሴምም ልጆች ፣ ኤላም ፣ አሦር ፣ አርፋክስድ ፣ ሉድ ፣ አራም ናቸው ፤

፳፫፡ ወደቂቀ አራም፣ ዑሳሕ፣ ወዮ ምኤል፣ ወያቴር፣ ወሞሳሕ ፣

የአራምም ልጆች፣ ዑሳሕ፣ ዮም ኤል፣ ያቴር፣ ሞሳሕ ናቸው፤

፳፬፡ ወአርፋክስድ ወለዶ ለቃይንም፣

አርፋክስድም፣ ቃይንምን ወለደ፤ (ሐተታ) አርፋክስድ ማለት ፈውስ ከለዳውያን ማለት ነው፤ ቃይንም ማለት ጥሪት ማለት ነው ፤

ወቃይንም ወለዶ ለሳላ ፣

ቃይንም ሳላን ወለደ ፤ ሳላ ማለት ተፈናዊ ማለት ነው ፤ እስመ ይቤ ተፈነውኩ እንዲል፤

ወሳላ ወለዶ ለኤቦር ፣

ሳላም ኤቦርን ወለደ ፤ ኤቦር ማለት ዐዳዊ ፈለግ ማለት ነው፣

፳፭፡ ወለኤቦር ተወልዱ ሎቱ ክል ኤቱ ደቂቅ ፣

ለኤቦርም ሁለት ልጆች ተወለ ዱለት ፤

ስሙ ለአሐዱ ፋሌቅ ፣

ያንዱ ስሙ ፋሌቅ ይባላል ፤ ፋሌቅ ማለት ክፍለት ማለት ነው ፤

እስመ በመዋዕሊሁ ተከፍለት ምድር፣

በእርሱ ዘመን ምድር ተከፍላ ለችና ፤

ወስመ እኁሁ ዮቃጢን ፣

የወንድሙም ስም ዮቃጢን ይባ ላል ፤



፳፮፡ ወዮቃጢን ወለዶሙ ለኤልሞ ዳድ ወለሰሌፋ ወለሴራሴርሞት ወለ ሲራሐ ፣

ዮቃጢንም የወለዳቸው እነዚህ ናቸው ፤ ኤልሞዳድ ፣ ሰሌፋ ፣ ሴራሴርሞት፣ ሲራሐ ናቸው፤

፳፯፡ ወለሐደራ፣ ወለአዜላ፣ ወለዴ ቄላ ፣

ሐደራ፤ አዜላ፣ ዴቄላ ፤

፳፰፡ ወለኡባላ፣ ወለአቤሚሌክ፣ ወለ ሴጌሆ ፣

ኡባላ፣ አቤሚሌክ ሴጌሆ ናቸው፤

፳፱፡ ወለሑፍር ወለሔዊ ወለኢዮቦር፣

ሑፍር፣ ሔዊ፣ ኢዮቦር፣ እነዚ ህን ሁሉ ወለደ ፤

ወእሉ ኵሎሙ ደቂቁ ለዮቃጢን፣

እነዚህም ሁሉ የዮቃጢን ልጆች ናቸው ፤

፴፡ ወኮነ ምንባራቲሆሙ እምነ ማሴ እስከ ሳፌራ ፣

እነዚህም የሚኖሩበት ሀገራ ቸው፣ ከማሴ ጀምሮ እስከ ሳፌራ ድረስ ሆነ ፤

ወይበጽሕ ደብረ ሠረቃዌ ፣

በምሥራቅ እስካለው ተራራ ይደርሳል ፤

፴፩፡ እሉ እሙንቱ ደቂቁ ለሴም በበነገዶሙ ወበበነገሮሙ፣ ወበበብሔ ሮሙ ወበበሕዘቢሆሙ ፣

በየነገዳቸው፣ በየቋንቋቸው፣ በየ ሀገራቸው፣ በየወገናቸው፣ የሚ ኖሩ የሴም ልጆች እሊህ ናቸው፤

፴፪፡ ወእሉ ደቂቀ ነገደ ኖኅ በበዘ መዶሙ ፣

በየወገናቸው የሚጠሩ የኖኅ ልጆች እሊህ ናቸው ፤

ወእምነ እሉ ትውልድ ተዘርዉ አሕ ዛብ ውስተ ገጸ ምድር እምድኅረ አይኅ ፣

ከማየ አይኅ በኋላም ከነዚህ የተ ወለዱ አሕዛብ በአራቱም ማዕ ዘን ሁሉ ተበተኑ ።

## ምዕራፍ ፲ወ፩

፩፡ ወአሐዱ ነገሩ ለኵሉ ዓለም ወአሐዱ ቃሉ ፣

አሐዱና አሐዱ አንድ ወገን፤ ከዚያ አስቀድሞ ሰው ሁሉ በአ ንድ ቋንቋ ይናገር ነበር ፤

### ጉባኤ

፪፡ ወኮነ እምድኅረ ተንሥኡ እምጽ ባሕ ረከቡ ገዳመ፣ በምድረ ሰናዖር ወነደሩ ህየ ፣

ከዚህም በኋላ፣ ከምሥራቅ ተነ ሥተው በሂዱ ጊዜ ሰናዖር በሚ ባል አገር ምድረ በዳ አግኝተው በዚያ ኖሩ ፤

፫፡ ወተበሀሉ አሐዱ ምስለ ካልኡ፣

አንዱ ካንዱ ጋራ እንዲህ ተባ ባሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ንዑ ንጥፋሕ ግንፋለ ወናብስሎ በእሳት ፤

ኑ ፣ ጡብ እየጣልን በእሳት እንተኩሰው ተባባሉ ፡

ወኮኖሙ ግንፋሎሙ ዕብነ ፣

ጡቡ እንደ ደንጊያ ጸናላቸው ፡

ወፒሳ ዕቡሮሙ ፣

የሠሩትም ኖራ እንደ ሰም፣ እንደ ሙጫ፣ እንደ አዱሮ ማር ሆኖላቸው ፡

፬፡ ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ ንዑ ንንድቅ ሀገረ ፣

እርስ በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፡ ኑ፣ አገር እናቅና ፡

ወማኅፈደ ዘይበጽሕ ርእሱ እስከ ሰማይ ፣

ርዝመቱም እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፡

ወንግበር ለነ ስመ እንበለ ንዘረው ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ፣

በአራቱ ማዕዘን ሁሉ ሳንበተን፣ ግንብ ሠርተን ስማችንን እናስጠራ አሉ ፡

፭፡ ወወረደ እግዚአብሔር ውስተ ሀገሮሙ ፣

ጌታም ተንኰላቸውን አውቆባቸው፣ በእግር ያይደለ፣ በግብር ወዳለበት አገር መጣባቸው ፡

ከመ ይርአይ ውእተ ማኅፈደ ዘነደቁ ዕጓለ እመሕያው ፣

ሰብአ ሰናዖር የሠሩትን ግንብ ገልብጦ ይጥልባቸው ዘንድ ፡

፮፡ ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ አሐዱ ዘመድ ውእቱ ኵሉ ወአሐዱ ነገሩ፡ ወከመዝ አኀዙ ይግበሩ ፣

እግዚአብሔርም እንዲህ ያለ ሥራ ይሠሩ ዘንድ የጀመሩ በአንድ ቋንቋ ቢናገሩ፣ አንድ ወገን ቢሆኑ አይደለምን? አለ፡

ወኢየኀድግ ይእዜ ገቢረ ዘሐለዩ በልቦሙ ፣

አሁንም በልባቸው አስበው የጀመሩትን ሥራ አይተዉትም ብሎ ፡

፯፡ ንዑ ንረድ ወንዝርዎ ለነገሮሙ ከመ ኢይሳምዑ ነገሮሙ አሐዱ ምስለ ካልኡ ፣

ሥላሴም ያንዱን ቋንቋ አንዱ እንዳይሰማው ወርደን ቋንቋቸውን እንለያየው አሉ ፡

፰፡ ወዘረወ እግዚአብሔር ነገሮሙ፣

እግዚአብሔርም በቋንቋ ለያያቸው ፡

ወዘረዎሙ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር፣

እነሱንም በዓለሙ ሁሉ በተናቸው ፡

ወኀደጉ እንከ ነዲቆታ ለይእቲ ሀገር ወለውእቱ ማኅፈድ ፣

ሀገሩን ማቅናት ግንቡን መሥራት ተዉ፡ (ታሪክ) ይህስ እን



ደምን ነው? ቢሉ፣ ከነገደ ካም የተወለደ ናምሩድ የሚባል ሰው ነበር፣ ልብሰ መንግሥት አሠርቶ ሉል ከሰማይ ወረደልኝ ብሎ ነግሦአል፡ እርሱን ይዘው አባቶቻችንን እንደ ማየ አይኅ ያጠፋቸው፣ የሚጠጉበት ግንብ ባይሠሩ ነው፡ ማየ አይኅ በወረደ ጊዜ እንዳያጠፋን የምንጠጋበት ግንብ እንሥራ ብለው ሥራ ጀመሩ፡ አንድም ይህ ሁሉ እንደ የሚጫወትብን በላይ ሁኖ ነው፣ እርሱን ገድለነው እንረፍ ብለው ወደ ምዕራብ ሀገር ሲሄዱ ሰናዖር ከምትባል ቦታ ደረሱ፣ ይህች ሰናዖር ሰፊ ሜዳ ናት፡ ከዚያ ላይ ግንብ ይሠሩ ጀመር ፡ የጡቡንም መጠን እንዲህ አድርገውታል፡ አቈልቋዩን (አግዳሚ ርዝመቱን) ዐሥር ክንድ ግዘፉን ፣ ቁመቱን ሦስት ክንድ አድርገውታል፡ ግንቡ የተመሠረተበትንም የቦታውን ስፋት ስድሳ ግመል ከነሳቢው ከነመሳቢያው አተርትሮ የሚያስቆም የፈረስ አፍታ የሚያደክም፣ የወንድና የሴት መልክ የሚለይበት፣ ጉልማሳ ክቡድ ሸክም ተሸክሞ የሚያሳርፍበት፣ ያን አንዱን አንድ እያሉ ዐሥራ ሦስት ምዕራፍ አድርገው መሥርተውታል ፡ ወሐነፅዎ ለጥቅመ ሰናዖር

፵ወ፫፻፲ ዓመተ እንዲል ፡ ኩፋሌ፣ ም. ፲ ቁ. ፲፱ ፡ አርባ ሦስት ዓመት ሠርተውታል ወደ ላይ ቁመቱ አምስት ሺሕ አራት መቶ ሠላሳ ሦስት ክንድ ከሁለት ስንዝር ነበር ፣ በፀሐይ እያበሰሉ ይበሉ ጀመር፡ ከዚህ በኋላ ፍላፃቸውን ወደላይ ቢወረውሩት በአየር ላይ ያሉ አጋንንት በምትሐት ደም እየቀቡ ይሰዱላቸው ጀመር ፡ አሁን ገና ባለቤቱን ወጋነው፣ አሁን አጋፋሪውን ወጋነው ፣ ቀኝ አዝማቹን ፣ ግራ አዝማቹን ወጋ ነው ይባባሉ ጀመር ፡ ሥላሴ ፍጥረቱ ሁሉ በከንቱ ቢጐዳ አይወዱምና ሰባ ሁለት ቋንቋ አመጡባቸው ፡ አንዱ እሳት አምጣ ሲለው ውሀ ያመጣል ፡ አንዱ ውሀ ሲለው ደንጊያ ፣ ደንጊያ ሲለው ጭቃ ፣ ጭቃ ሲለው ዕንጨት ያመጣ ጀመር፡ እንዲህ አድርገው በቋንቋ ለያይዋቸው ፣ የማይሆንላቸው ሆነ ፣ ትተውት ወረዱ ፡ ግንቡንም ጣዖት አድርገው እንዳያመልኩት ሥላሴ ጽኑ ነፋስ አስነሥተው በትነውታል፡ ባቢሎን ተብሎአል ፡ አንድም እነርሱ በቋንቋ በነገር ስለ ተለያዩ ፣ በቦታ ስለተበተኑበት ባቢሎን ተብሎአል ፣ ባቢሎን ማለት ዝርው ማለት ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይህን ጊዜ ቋንቋ ከሦስት ተከ
ፍሏል ፤ ሠላሳ ሁለቱ በነገደ
ካም፣ ሃያ አምስቱ በነገደ ያፌት፣
ዐሥራ አምስቱ በነገደ ሴም
ቀርቷል ፤

፱፡ ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስማ
ባቢሎን ፤

ስለዚህም ሀገሪቱ ባቢሎን ተብላ ተጠራች፤ ዝሩት ማለት ነው፤

እስመ በህየ ዘረዎሙ እግዚአብሔር ለነገረ ኵሉ በሐውርት ፤

እግዚአብሔር በዚያ የሰውን ሁሉ ቋንቋ ለይቶበታልና ፤

ወእምህየ ዘረዎሙ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር፤

ከዚያም ቦታ እግዚአብሔር አሕዛብን በዓለም ሁሉ በትኖበታልና ፤

፲፡ ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለሴም ፤

የሴም ልደቱ እንዲህ ነው ፤

ምእት ዓመት ሎቱ እምአመ ተወልደ አመ ይወልዶ ለአርፋክስድ በካልእ ዓም እምድኅረ አይኅ ፤

ማየ አይኅ በሆነ በሁለተኛው ዓመት አርፋክስድን በወለደው ጊዜ መቶ ዘመን ሆኖት ነበር፤

፲፩፡ ወሐይወ ሴም፣ እምድኅረ ወለዶ ለአርፋክስድ ኃምስተ ምእተ ዓመተ፣

ሴም አርፋክስድን ከወለደ በኋላ አምስት መቶ ዘመን ኖረ ፤

ከዚህ ቀድሞ አበው በድንግልና የኖሩትን ፤ ከወለዱም በኋላ ፣ የኖሩትን ደምሮ ይናገር ነበር፤ ከዚህ ግን፣ በድንግልና የኖሩትን ዘመን ለብቻ፤ ከወለዱ በኋላ የኖሩትን ዘመን ለብቻ አድርጎ ይጽፋል እንጂ ደምሮ አይጽፍም ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ፣ ወሞተ፣

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፣ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፪፡ ወሐይወ አርፋክስድ ምእተ ወሠላሳ ወኃምስተ ዓመተ ፤

አርፋክስድ በድንግልና መቶ ሠላሳ አምስት ዘመን ኖረ ፤

ወወለዶ ለቃይንም ፤

ቃይንምንም ወለደ ፤

፲፫፡ ወሐይወ አርፋክስድ እምድኅረ ወለዶ ለቃይንም አርባዕተ ምእተ ወአርብዓ ዓመተ ፤

አርፋክስድ፣ ቃይንምን ከወለደ በኋላ አራት መቶ አርባ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

ወሐይወ ቃይንም ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፤ ወወለዶ ለሳላ ፤

ቃይንም በድንግልና መቶ ከሠላሳ ዘመን ኖሮ ሳላን ወለደ ፤



ወሐይወ ቃይንም እምድኅረ ወለዶ ለሳላ አርባዕተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ፣

ቃይንም ሳላን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ፣ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፬፡ ወሐይወ ሳላ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ወወለዶ ለኤቦር ፤

ሳላ በድንግልና መቶ ሠላሳ ዘመን ኖሮ ኤቦርን ወለደ ፤

፲፭፡ ወሐይወ ሳላ እምድኅረ ወለዶ ለኤቦር አርባዕተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፤

ሳላ ኤቦርን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፣ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፮፡ ወሐይወ ኤቦር ምእተ ወሠላሳ ወአርባዕተ ዓመተ ወወለዶ ለፋሌቅ ፤

ኤቦር በድንግልና መቶ ሠላሳ አራት ዘመን ኖሮ ፋሌቅን ወለደ ፤

፲፯፡ ወሐይወ ኤቦር እምድኅረ ወለዶ ለፋሌቅ አርባዕተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፤

ኤቦር ፋሌቅን ከወለደ በኋላ፣ አራት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፲፰፡ ወሐይወ ፋሌቅ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ፣ ወወለዶ ለራግው ፤

ፋሌቅም በድንግልና መቶ ሠላሳ ዓመት ኖሮ ራግውን ወለደ ፤

ራግው ማለት እኩይ ጽኑዕ ማለት ነው፤ በዘመኑ የሠሩት ግንብ ፈርሶባቸው በቋንቋም ተለያይተው ሥራ ትተዋልና፤

፲፱፡ ወሐይወ ፋሌቅ፣ እምድኅረ ወለዶ ለራግው ክልኤተ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ፤

ፋሌቅ ራግውን ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ሠላሳ ዘመን ኖረ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፳፡ ወሐይወ ራግው ምእተ ወሠላሳ ወክልኤተ ዓመተ ወወለዶ ለሴሩህ፣

ራግውም በድንግልና መቶ ሠላሳ ሁለት ዘመን ኖሮ ሴሩህን ወለደ ፤ (ሐተታ) ሴሩህ ማለት ምዩጥ ማለት ነው፤ ሴሩክ ያለ እንደሆነ ዐላዊ ማለት ነው፤ ልጆቹ የሰው ገንዘብ ሲቀሙ ይኖራሉና፤ አንድም ሀላዊ ማለት ነው፤ ልጁ የልጅ ልጁ የሚኖር ስለሆነ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወሐይወ ራግው እምድኅረ ወለዶ ለሴሩህ ክልኤተ ምእተ ወሰብዓተ ዓመተ ፤

ራግው ሴሩህን ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ሰባት ዓመት ኖረ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፳፪፡ ወሐይወ ሴሩህ ምእተ ወሠላሳ ዓመተ ወወለዶ ለናኮር ፤

ሴሩህም በድንግልና መቶ ሠላሳ ዓመት ኖሮ ናኮርን ወለደ ፤ ናኮር ማለት ነግድ ወፈላሲ ማለት ነው ፤

፳፫፡ ወሐይወ ሴሩህ እምድኅረ ወለዶ ለናኮር ክልኤተ ምእተ ዓመተ ፤

ሴሩህ ናኮርን ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፳፬፡ ወሐይወ ናኮር ምእተ ወተስዓተ ዓመተ ወወለዶ ለታራ ፤

ናኮርም በድንግልና መቶ ዘጠኝ ዘመን ኖሮ ታራን ወለደ፤ ታራ ማለት ያፍ ዕኑስ ማለት ነው፤ እስመ በመዋዕሊሁ ያስተጼንስ ዖሙ ቋዓት ወአዕዋፍ እንዲል፤ ኩፋሌ ፲:፳፱ ፤

፳፭፡ ወሐይወ ናኮር እምድኅረ ወለዶ ለታራ ምእተ ወዕሥራ ወተስዓተ ዓመተ ፤

ናኮር ታራን ከወለደ በኋላ መቶ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ኖረ ፤

ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ወሞተ ፤

ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወለደ ፤ ከዚያም በኋላ ሞተ ፤

፳፮፡ ወሐይወ ታራ ምእተ ዓመተ ወወለዶሙ ለአብራም ወለናኮር ወለአራን ፤

ታራ መቶ ዘመን ኖሮ አብራምን፤ ናኮርን፤ አራንን ወለደ፤ አብራም ማለት አበ ውሁዳን ማለት ነው ፤

፳፯፡ ወአራን ወለዶ ለሎጥ ፤

አራንም ሎጥን ወለደ ፤

፳፰፡ ወሞተ አራን በቅድመ ታራ አቡሁ በምድር እንተ በውስቴታ ተወልደ በምድረ ከላውዴዎን ፤

አራን በከላውዴዎን ውስጥ ባለች ኡር በምትባል ሥፍራ በተወለደባት አገር ከአባቱ አስቀድሞ ሞተ ፤

ታሪክ ፤ ወሞተ አራን በቅድመ ታራ አቡሁ ያለው እንደምን ነው ቢሉ? ሴሩህ ናኮርን፤ ናኮር ታራን፤ ታራ አብርሃምን ይወልዳል ፤ ይህ ሴሩህ ፤ ብኑ የሚባል ልጅ ነበረው፤ እንዘ በቆሁ



ተመስጠ ሕፃኑ ይላል፤ በሕፃን ነት ተቀሠፈበት፤ ይወደው ነበርና እንቅበረው ቢሉ ከመውደዱ የተነሣ አላስቀብርም አለ፤ ሲወጣ ሲገባ ልጄ ብኑ፤ ልጄ ብኑ እያለ ኀዘን ጸናበት፤ የሀገሩ ሰዎች ወጥቶ በሔደበት ያንን ልጅ ቀብረው እንጨት ጠርበው ፤ ጆሮ ፤ አፍንጫ ፤ ዓይን ፤ እጅ ፤ እግር ቀርጸው ቀለም ቀብተው፤ ቀሚስ አጥልቀው፤ በኋላው አቁመው ልጅህ ተነሣልህ አሉት ፤ ልጄ ብኑ ነህን አለው፤ በዚያ በዕንጨት ያደረ ሰይጣን፤ እ፤ አለ፤ አም ላክ ካልሆነ ተነሥቶ ተነጋገረውን ? ብለው የሚያመልኩበት ሆኗል ፤ ከሴሩህ እስከ ናኮር ፤ ከናኮር እስከ ታራ ፤ ከታራ እስከ አብርሃም ደረሰ፤ የሀገሩ ሰዎች ሁሉ እንጨት ጠርበው፤ ደንጊያ አለዝበው ያመልኩ ጀመር ፤

አብርሃምም አባቱ ታራን ምንት ተድላ ወረድኤት ለነ አባ፤ አባቴ ከዚህ ከጣዖቱ የምናገኘው ረብሕ ጥቅም ምንድን ነው? አለው፤ ወአአምር ወልድየ አነ ፤ ልጄ እኔም እንዳይረባን እንዳይጠቅመን አውቃለሁ፤ የዚህ አገር ሰዎች በፍቅረ ጣዖት ተናደዋልና እንዳያጠፉን፤ እንደ ወንዘሁ ይሻገሩ፤ እንደ ሀገሩ ይኖሩ ብዬ ነው እንጂ አለው፤ ይህም ታራ ከዕለታት በአንዱ ቀን ዕንጨት ጠርቦ ደንጊያ አለዝቦ አብርሃ ምን ሒድ ሽጠህ ና አለው፤ ይዞ ሲሔድ አፍ ሳለው የማይናገር፤ እጅ እግር ሳለው የማይዳስስ የማይሔድ ምንድን ነው? አለ፤ ከገበያውም ገብቶ አፍ ሳለው የማይናገር፤ እጅ ሳለው የማይ ዳስስ፤ እግር ሳለው የማይሄድ ጣዖት ግዙ አላቸው ፤ ባለቤት ያቀለለውን ገንዘብ ባለዕዳ አይ ቀበለውም እንዲሉ፤ እርሱ እን ዲህ እያለ ምን ሊረባን ብለው አንገዛም አሉ ፤ አንድም ረክሶ በት ይዞት ሲመለስ ፤ ርቦኛል አብላኝ ፤ ጠምቶኛል አጠጣኝ ቢለው ዝም አለው ፤ እንዲያ ውም የደከመው ሰው ቢያጫ ውቱት ግዳጅ ይፈጽምለታልና አጫውተኝ አለው ፤ ዝም አለው ፤ እንዲያው ዕንጨቱን ተሸክሜያለሁ ? ይህስ ፍጡር ነው እንጂ ፈጣሪዬ አይደለም፤ ፈጣሪዬ ሌላ ነው ብሎ አውርዶ በድንጋይ ቀጥቅጦ ጥሎ ስነ ፍጥረትን ይመለከት (ይመረምር) ጀመር፤ ተራራውን ከፍ ብሎ ቢያየው አምላክስ ይህ ነው ብሏል፤ ይህንንም አንዱ ተራራ አንዱን ሲበልጠው አይቶ፤ በፈጣሪ መብለጥ መበላለጥ የለበትም፤ ይህም አምላክ አይደለም

www.ethiopianorthodox.org

ብሎ ፡ ነፋስ ባሕር ሲገሥጽ ፣ ዛፍ ሲያናውጥ አይቶ አምላክስ ይህ ነው ብሏል ፡

ነፋስንም፣ ተራራ ሲገታው መገጊያ ሲመልሰው አይቶ ፈጣሪንስ የሚገታው የለም፣ ይህም አምላክ አይደለም ብሎ፤ የባሕሩን፣ ማዕበሉን፣ ሞገዱን አይቶ፣ አምላክስ ይህ ነው ብሏል፤ ባሕርም ሲመላ ሲጐድል አይቶ በፈጣሪስ ሕፀፅ የለበትም ፣ ይህም አምላክ አይደለም ብሎ እሳት፣ ደረቁን ከርጥቡ ለይቶ ሲበላ ፣ ቋያውን ሲያቃጥል አይቶ አምላክስ ይህ ነው ብሏል ፡

እርሱንም ውሃ ሲያጠፋው መንገድ ሲከለክለው አይቶ፣ ይህም አደለም ብሎ ፀሐይ በዓለሙ መልቶ ሲያበራ አይቶ አምላክስ ይህ ነው ብሏል፤ እርሱም በምሥራቅ ወጥቶ በምዕራብ ሲገባ አይቶ በፈጣሪስ መውጣት መግባት የለበትም፣ ቀን ቢመግበን ሌሊት ማን ይመግበናል ለዚህም ፈጣሪ አለው ብሎ፣ አምላከ ፀሐይ ተናበበኒ አለ፣ ወተናገሮ በልሳነ ፍጥረቱ እንዲል ፤

መልአኩ እነዚህ ሁሉ ፍጡራን ናቸው፣ የፈጠራቸው አለ ብሎ ነግሮታል፤ ከዚህ በኋላ አንድነቱን፣ ሦስትነቱን ገልጦለታል፣ ያን ጊዜ ቤተ ጣዖቱን አቃጠለው፣ ወንድሙ አራን ጣዖቱን አወጣለሁ ብሎ ገብቶ ተቃጥሎ ሰማዕተ ጣዖት ሆኖ ሙቷል ፡

፳፱፡ ወነሥኡ አብራም ወናኮር አንስትያ ሎሙ ፣

አብራምና ናኮር ሚስት አገቡ፤

ወስማ ለብእሲተ አብራም ሶራ ፣

የአብራም ሚስት ሶራ ትባላለች፤ እመ ወሁዳን ማለት ነው፤

ወለብእሲተ ናኮር ሚልካ ወለተ አራን ፣

የአራን ልጅ የምትሆን የናኮርም ሚስት ስሟ ሚልካ ይባላል ፤

አቡሃ ለሚልካ ወአቡሃ ለዮስካ ፣

የሚልካና የዮስካ አባት ብሎ ለአራን ቀጸለ፤ ዮስካ ያላት፣ ሶራ ናት፤ እድምተ ስም ሠናይተ ላህይ ማለት ነው፤ አንድም እማ ለሚልካ ወለተ አራን፣ የሚልካ እናቷ፤ የአራን ልጅ ናት፤ ወአቡሃ ዮስካ፣ አባቷም ዮስካ ነው፤ አንድም እማ ለሚልካ ወለተ አራን አበዮስካ ፤ የአራን ልጅ የሚልካ እናቷ አበዮስካ ናት ፤



## ጉባኤ

፴፡ ወሶራሰ መካን ይእቲ ወአልባቲ ውሉድ ፣

ሶራ ግን መካን ነበረችና ልጅ አልነበራትም፤

፴፩፡ ወነሥኦሙ ታራ ለአብራም ወልዱ ወለሎጥ ወልደ አራን እኁሁ ለአብራም፤ ወለሶራ መርዓቱ፣ ብእሲተ አብራም ፣

ታራ ልጁን አብራምንና የአብራም ወንድም የሚሆን የአራን ልጅ ሎጥን፤ የልጁ የአብራም ሚስት ሶራንም ይዞ ተነሣ፤

ወአውፅኦሙ እምድረ ከላውዴዎን ከመ ይሑሩ ምድረ ከነዓን ፣

ወደ ከነዓን ይሄዱ ዘንድ ከከላውዴዎን አወጣቸው፤

ወሶበ በጽሑ ካራን ኀደሩ ህየ ፣

ካራን በደረሱ ጊዜ ከዚያ ኖሩ፤

፴፪፡ ወኮነ ኵሉ መዋዕሊሁ ለታራ ክልኤተ ምእተ ወኃምስተ ዓመተ፣

የታራ መላ ዘመኑ፣ ሁለት መቶ አምስት ዓመት ሆነ፤

ወሞተ ታራ በምድረ ካራን ፣

ታራም ካራን በሚባል አገር ሞተ::

## ምዕራፍ ፲ወ፪

፩፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም ፣

እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው ፡

ፃእ እምድርከ ወእምአዝማዲከ ወእም ቤተ አቡከ ፣

ከአባትህ ወገን፣ ከዘመዶችህ ተለይተህ ከአገርህ ውጣ ፡

ወሑር ውስተ ምድር እንተ አርእየከ አነ ፣

እኔ ወደማሳይህ ወደ ከነዓንም ሂድ ፡

፪፡ ወእሬስየከ ሕዝበ ዐቢየ ወእባርከከ ፣

ብዙ ወገን አደርግሃለሁ፤ አከብርሃለሁ ፡

ወአዐቢ ስመከ ፣

ስምህንም አከብረዋለሁ አገነዋለሁ አለ ፣ አበ ብዙኃን እንድትባል አደርግሃለሁ ፡

ወትከውን ቡሩከ ፣

ክቡር ትሆናለህ ፡

፫፡ ወእባርኮሙ ለእለ ይባርኩከ፤ ወእረግሞሙ ለእለ ይረግሙከ ፣

የሚመርቁህን እመርቃቸዋለሁ፤ የሚረግሙህንም ሰዎች አጠፋቸዋለሁ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይትባረኩ ብከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ፤

አሕዛብም ሁሉ ባንተ ይመረረ ቃሉ፤ አብርሃምን ያከበረ ያክብርህ እያሉ ፤

፬፡ ወሖረ አብራም በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ፤

አብራምም እግዚአብሔር እንዳ ዘዘው ወደ ከነዓን ሔደ ፤

ወሖረ ሎጥሂ ምስሌሁ ፤

ሎጥም ከእርሱ ጋራ ሔደ ፤

ወአመ ወፅአ አብራም እምካራን ሰብዓ ወኀምስቱ ክረምቱ ሎቱ ፤

አብራምም ከካራን ወደ ከነዓን በወጣ ጊዜ ሰባ አምስት ዓመት ሆኖት ነበር፡ (ሐተታ) ከዚህ አሪት ታራ አብርሃምን በመቶ ዘመኑ ወለደው አለች፡ ታራንም በሁለት መቶ አምስት ዘመኑ ሞተ ትላለች ፡ አብርሃምም ከካራን በወጣ ጊዜ ሰባ አምስት ዘመን ሆኖት ነበር ትላለች፡ ዘፍ.፲፩:፳፯-፴፪፡ ፲፪:፬ ፤

ከዚያ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት፡ ወእምዝ መዊቶ አቡሁ አፍለሶ ውስተ ዛ ሀገር ኀበ ሀለውክሙ አንትሙ ይእዜ ትነብሩ ይላል፡ የሐዋር. ሥራ ፯:፬ ፡ እንደም ነው ቢሉ፤ ታራ በመቶ ዘመኑ አብርሃምን ወልዶታል፡ በዚያው በተወለደበት በከላውዴዎን ስድሳ አንድ ዘመን አብረው ኑረዋል፤ ከዚያ በኋላ ፃእ እምድርከ ወተ ፈለጥ እምአዝማዲከ ብሎት፤ ከከላውዴዎን ወደ ካራን ወጣ፤ በካራን ዐሥራ አራት ዘመን ይኖራሉ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ፃእ እምድርከ አለው፤ ከካራን ወደ ከነዓን ይወጣል፤ በከነዓን ሠላሳ ዘመን ይኖራል ፤ ከዚህ በኋላ ለአብርሃም መቶ አምስት፤ ለታራ ሁለት መቶ አምስት ዘመን ሲሆነው አባትህ ሞተ ብለው ለአብርሃም ነገሩት ፤ ከከነዓን ወደ ካራን መጥቶ አባቱን ቀብሮ ተቀምጦ ሳለ፤ ፃእ እምድርከ ወተፈለጥ እምአዝማዲከ ብሎት ወደ ከነዓን ሔዷልና ሉቃስ ወእምዝ መዊቶ አቡሁ አፍለሶ ያለው ስለዚህ ነው ፤

፭፡ ወነሥአ አብራም ለሶራ ብእሲቱ ወለሎጥሂ ወልደ እኁሁ ፤

አብራምም ሚስቱን ሶራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን ይዟቸው ወጣ ፤

ወኵሎ ንዋዮሙ ዘአጥረዩ በካራን፤ ወወፅኡ ወሖሩ ወበጽሑ ምድረ ከነዓን ፤

በካራን የሰበሰቡትን (ያፈሩትን) ገንዘብ ሁሉ ይዘው ከካራን ወጥተው ሔደው ከነዓን ደረሱ፤



፮፡ ወየዳ አብራም ለይእቲ ምድር እስከ ሴኬም ኀበ ዕፅ ነዋህ ፤

አብራም ከነዓንን፤ ረጅም ዛፍ እስካለባት እስከ ሴኬም ድረስ ዞሮ አያት፤ አንድም ተመራት፤

ወሰብአ ከነዓንሰ ሀለዉ ይእቲ አሚረ ውስተ ይእቲ ምድር ፤

የከነዓን ሰዎች ግን ያንጊዜ በከነዓን ነበሩ፤ (ሐተታ) አብራም፤ እኒህ ሁሉ ሳሉ እንደምን ያወርሰኛል ብሎ አልተጠራጠረም ለማለት ሰብአ ከነዓንን አነሣ፤

፯፡ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብራም ፤

እግዚአብሔርም ለአብራም ታየው ተነጋገረው ፤

ወይቤሎ ለዘርእከ እሁባ ለዛቲ ምድር፤

ከነዓንን ለልጆችህ አወርሳቸዋለሁ ብሎ ነገረው ፤

ወነደቀ አብራም በሀየ ምሥዋዓ ለእግዚአብሔር ዘአስተርአዮ ፤

አብራምም ለታየው ለተነጋገረው ለእግዚአብሔር ምሥዋዕ (ጸፈጸፈ) ሠራ ፤

፰፡ ወግዕዘ እምሀየ መንገለ ሠርቅ ውስተ ምድረ ቤቴል ፤

ከዚያም ተነሥቶ በምሥራቅ በኩል ወዳለቺው ቤቴል ተጓዘ፤ ቤቴል ማለት ቤተ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

ወተከለ ሐይመቶ ውስተ ቤቴል አንጻረ ባሕር ዘመንገለ ጋይ ወኃደረ ሀየ ፤

ድንኳኑንም በጋይ በኩል ባለች በቤቴል ምዕራብ ተክሎ ሰፈረ፤

ወነደቀ ሀየ ምሥዋዓ ለእግዚአብሔር፤

በዚያም ለእግዚአብሔር ምሥዋዕ ጸፈጸፈ ማለት ሠራ ፤

ወጸውዓ ስመ እግዚአብሔር ፤

ቃለ እግዚአብሔርን ጠየቀ ፤ የእግዚአብሔርንም ስም አመሰገነ ብትልም ይሆናል ፤

፱፡ ወተንሥአ ወሖረ ወግዕዘ አብራም ውስተ አዜብ ፤

አብራምም፤ ከቤቴል ተነሥቶ ወደ አዜብ ተጓዘ ፤

ከመ ይኅድር ሀየ ፤

በአዜብ ይኖር ዘንድ ፤

፲፡ ወሰበ ጸንዐ ረሀብ፤ ውስተ ብሔር ወረደ አብራም ውስተ ግብጽ ፤

በከነዓንም ረሀብ በጸና ጊዜ አብራም ወደ ግብጽ ተሰደደ ፤

ከመ ይኅድር ሀየ ፤

በግብጽ ይኖር ዘንድ ፤

እስመ ጸንዐ ረሀብ ውስተ ብሔር ፤

በከነዓን ረሀብ ጸንቶ ነበርና ፤

፲፩፡ ወኮነ ሶበ ቀርበ አብራም ከመ ይባእ ውስተ ግብጽ ፤

አብራም ወደ ግብጽ ሊገባ በቀረበም ጊዜ እንዲህ ሆነ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤላ አብራም ለሶራ ብእሲቱ ፣

ኮነ ያለውን ይቤላ ብሎ አመ ጣው፣ ሚስቱ ሶራን እንዲህ አላት፡

አአምር ከመ ብእሲት ላሀዪተ ገጽ አንቲ ፣

አንቺ መልክ ከደም ግባት አስ ተባብረሽ የያዝሽ እንደ ሆንሽ አውቃለሁ ፡

፲፪፡ ወእምከመ ርእዩኪ ሰብአ ግብፅ ይብሉ ብእሲቱ ይእቲ ወይቀትሉኒ ወኪያኪሰ ያሐይዉኪ ፣

የግብጽ ሰዎች ያዩሽ እንደሆነ፣ ሚስቱ ናት ብለው ይገድሉኛል፣ አንቺን ግን ያድኑሻል (ይተዉ ሻል) ፡

፲፫፡ ወበሊዮሙ እንከ እኅቱ አነ ፣

ምኑ ነሽ ? ቢሉሽ እኅቱ ነኝ በዪ ፣ እኔም እኅቴ ናት እላቸ ዋለሁ አላት ፡

ከመ ያሠንዩ ሊተ በእንቲአኪ ፣

ባንቺ ምክንያት ለኔ በጎ ነገርን ያደርጉልኝ ዘንድ ፡

ወትሕየው ነፍስየ በእብሬትኪ ፣

ባንቺ ዘመናይነት፣ ባንቺ እመ ቤትነት ሰውነቴ ትዳን ፡

፲፬፡ ወኮነ ሶበ በጽሐ አብራም ውስተ ግብጽ ፣

አብራምም ግብጽ በደረሰ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፡

ወርእይዋ ለብእሲቱ ሰብአ ግብጽ ከመ ሠናይት ጥቀ ፣

ኮነ ያለውን ርእይዋ ብሎ አመ ጣው፣ የግብጽ ሰዎችም መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች እንደሆነች ባዩ ጊዜ ፡

፲፭፡ ወርእይዋ መላእክተ ፈርዖን ፣

የፈርዖንም ሹማምንት ባዩዋት ጊዜ ፡

ወሰድዋ ኀበ ፈርዖን ፣

ይህቺስ ለንጉሥ ትገባለች ብለው ወደ ፈርዖን ወሰዱዋት ፡

ወአብእዋ ውስተ ቤቱ ፣

ወደ እልፍኙ አገቡዋት ፡

፲፮፡ ወአሠነዩ ለአብራም በእንቲአሃ፣

በእርስዋም ምክንያት ለአብራም በጎ ነገር አደረጉለት ፡

ወአጥረየ አግብርተ ወአዕማተ ወአባ ግዓ ወአልሕምተ ፣

ወንድ ባርያን፣ ሴት ባርያን፣ በጉን፣ ላሙን ገዛ ፡

ወአግማለ፣ ወአብቅለ፣ ወአዕዱገ ፣

ግመሉን፣ በቅሎውን፣ አህያውን ገዛ ፡

፲፯፡ ወሣቀዮ እግዚአብሔር ለፈርዖን ዐቢየ ሥቃየ ወእኩየ ለቤቱሂ ወለቤ ቱሂ ፣

እግዚአብሔር በፈርዖን ጽኑ ደዌ አመጣበት፡ ደዌውስ ምን



ድን ነው ቢሉ ፡ ብልቱ መጠ ጊያ (ትራስ) ያህል ሆኖ አብጦ አል ፡ ወለቤቱ ፣ በወገኖቹም ጽኑ ደዌ አመጣባቸው ፡

በእንተ ሶራ ብእሲቱ ለአብራም ፣

የአብራም ሚስት ሶራን ስለወ ሰደ ፡ ወቀሠፎ ውስተ ነፍስቱ ብሎ ፣ ኋላ በአቤሜሌክ ያመ ጣዋል፡ የጉልማሳ ሚስት ወስ ደሃልና እሷን ካልመለስኽ አት ድንም አለው ፡

፲፰፡ ወጸውዖ ፈርዖን ለአብራም ወይ ቤሎ ፣

ፈርዖንም አብራምን ጠርቶ እንዲህ አለው ፡

ምንትኑ ዝ ዘገበርከ ላዕሌየ ዘኢነገ ከኒ ከመ ብእሲትከ ይእቲ ፣

ሚስትህ እንደ ሆነች ያልነገ ኸኝ ይህ በኔ ያደረግኸው ነገር ምንድር ነው ?

፲፱፡ ለምንት ትቤለኒ እኅትየ ይእቲ፣

እኅቴ ናት ለምን አልኸኝ ?

ወነሣእክዋ ትኩነኒ ብእሲተ ፣

እኔስ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ለምን ወሰድኋት ?

ወይእዜኒ ነያ ብእሲትከ ንሥአ ወሑር ፣

አሁንም ሚስትህ ያቻትልህ ይዘህ ሂድ አለው ፡

፳፡ ወአዘዘ ፈርዖን ያስተፋንውዎ ዕደው ለአብራም ወለብእሲቱ ወለ ኵሉ ንዋዮሙ ፣

ፈርዖንም አብራምን ሚስቱን፣ ገንዘቡን ሁሉ ይዘው ይሸኙት ዘንድ አዘዘ ።

## ምዕራፍ ፲ወ፫

፩፡ ወዐርገ አብራም እምግብጽ ውእቱ ወብእሲቱ ወኵሉ ንዋዩ ፣

አብራም ከግብጽ ወጣ ፡ እሱ ሚስቱን ገንዘቡንም ሁሉ ይዞ ወጣ፡

ወሎጥሂ ምስሌሁ ውስተ አዜብ ፣

ሎጥም ከአብራም ጋራ ወደ አዜብ ወጣ ፡

፪፡ ወአብራምሰ ብዕለ ጥቀ በእንስሳ ወበወርቅ ወበብሩር ፣

አብራምም በከብት፣ በወርቅ፣ በብር፣ እጅግ ከበረ፡

፫፡ ወገብአ እምኀበ መጽአ እምአዜብ ውስተ ቤቴል፣ ውስተ መካን ኀበ ሀሎ ቀዲሙ ፣

ከግብጽ ከመጣላት ከአዜብ ቀድሞ ወደነበረባት ወደ ቤቴል ተመለሰ፡ አንድም ከግብጽ ወደ ርስዋ ከመጣላት ከአዜብ፡ ቀድሞ ወደነበረባት ወደ ቤቴል ተመ ለሰ ፡ አንድም ከቤቴል ወደ ርስዋ ከሔደላት፣ ከአዜብ ከመ ጣላት ከግብጽ ቀድሞ ወደ ነበ ረባት ወደ ቤቴል ተመለሰ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስመ በህየ ዐፀዱ በማዕከለ ቤቴል ወበማዕከለ ጋይ ፤

ድንኳኑ በቤቴልና በጋይ መካከል ተተክሎ ነበርና፤

፬፡ ውስተ መካን ኀበ ገብረ ምሥዋዓ ህየ ቀዲሙ ፤

ቀድሞ ምሥዋዕ በሠራባት ቦታ ባለ በጋይና በቤቴል ድንኳኑ ተተክሎ ነበርና፤

ወጸውአ አብራም ስመ እግዚአብሔር በህየ ፤

ስመ እግዚአብሔርን በጠራበት፤ አንድም ስመ እግዚአብሔርን ጠራ ፤

፭፡ ወሎጥኒ ዘሖረ ምስለ አብራም አጥረየ አባግዓ ወአልሕምተ ወእንስሳ ፤

ወአብራምስ ብዕለ ጥቀ ብሎ ነበርና፤ ከአብራም ጋራ የሔደ ሎጥም በጎችን፣ ላሞችን፣ ፈረስ፣ በቅሎን ገዛ ፤

፮፡ ወኢአከሎሙ ምድር ከመ ይኅድሩ ኅቡረ ፤

ኢአከለቶሙ ሲል ነው፤ ምድር ከነዓን፤ አብራምና ሎጥ አብረው ይኖሩባት ዘንድ አልበቃቻቸውም ፤

፯፡ ወኮነ ጋዕዝ ማዕከለ ኖሎት ዘሎጥ ወዘአብራም ፤

በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል በሣርና በውሀ ምክንያት ጸብ ክርክር ሆነ ፤

ወሀለዉ ይእተ አሚረ ሰብአ ከነዓን ወፌሬዜዎን ኅዱራን ውስተ ይእቲ ምድር ፤

ያንጊዜም የከነዓንና የፌርዜዎን ሰዎች ያችን አገር በዝተው ወርሰዋት ነበር፤ ከነዓን የጠበበቻቸው አብራምና ሎጥ ብቻ ይዘዋት አይደለም፣ ሰብአ ከነዓን በዝተው ወርሰዋት ነው ለማለት ፤

፰፡ ወይቤሎ አብራም ለሎጥ ፤

አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው ፤

ኢይኩን ጋዕዝ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ፡ ማዕከለ ኖሎትየ ወማዕከለ ኖሎትከ፣

በእኔና በአንተ ፤ በእኔ እረኞችና በአንተ እረኞች መካከል ጸብ ክርክር አይሁን ፤

እስመ አኃው ንሕነ ፤

እኛ ወንድማማች ነንና ፤

፱፡ ወናሁ ኵላ ምድር ቅድሜከ ይእቲ ፤

እነሆ አገሩ ሁሉ በፊትህ ነው ፤

ተሌለይ እምኔየ ፤

ከእኔ ተለይተህ ሒድ ፤

እመ የማነ አነ ወአንተ ፀጋመ ፤

እኔ ወደ ቀኝ ብሔድ፣ አንተ ወደ ግራ ትሔዳለህ ፤



ወእመ አኮ አንተ የማነ ወአነ ጺጋም፣

ይህም ባይሆን አንተ ወደ ቀኝ ብትሔድ እኔ ወደ ግራ እሔዳለሁ ፤

፲፡ ወአልዐለ ሎጥ አዕይንቲሁ፣ ወርእየ ኵሎ አሕቃላቲሁ ለዮርዳኖስ፣

ሎጥም አንገቱን አቅንቶ የዮርዳኖስን አውራጃ ሁሉ ተመለከተ ፤

ወርውይ ውእቱ ኵሉ ምድሩ ፤

ከመ ርውይ ሲል ነው፤ ሀገሩ ሁሉ ለምለም እንደሆነ አየ ፤

ዘእንበለ ይገፍትዖን እግዚአብሔር ለሰዶም ወለገሞራ ፤ ከመ ገነተ እግዚአብሔር ውእቱ ፤

እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ሳያጠፋቸው፣ እንደ ፈጠራት እንደ ገነት ነበሩና፣ ገነት ደስ እንድታሰኝ ደስ ያሰኙ ነበርና፤ አንድም፤ ገነት ልምላሜ እንዳ ይታጣባት ልምላሜ አይታጣባቸውም ነበርና፤

ወከመ ምድረ ግብጽ ፤

ምድረ ግብጽም ደስ እንድታሰኝ ደስ የሚያሰኙ ነበርና፤ አንድም ምድረ ግብጽ ልምላሜ እንዳይታጣባት ልምላሜ አይታጣባቸውም ነበርና፤

፲፩፡ ወኀረየ ሎቱ ሎጥ ኵሎ አሕቃላተ ዮርዳኖስ ፤

ሎጥ የዮርዳኖስን አውራጃ ሁሉ መረጠ ፤

ወግዕዘ ሎጥ እመንገለ ሠርቅ፣ ወተሌለዩ አሐዱ እምካልኡ ፤

ሎጥም በምሥራቅ በኩል ወዳለች ወደ ሰዶም ተጓዘ፤ አንዱ ከአንዱ ተለያዩ ፤ አብራም ከሎጥ ፤ ሎጥ ከአብራም ተለያዩ ፤

፲፪፡ አብራም ኃደረ ምድረ ከነዓን፣

አብራም በከነዓን ቀረ፤ (ሐተታ) ስለምን አብራምን ከዚያ እንዲቀር አደረገ ቢሉ፣ ተስፋውን የነገረው ለአብራም ነውና ፤ አንድም ወርሰዋት የሚኖሩ የአብራም ልጆች ናቸውና ስለ ዚህ ከዚያው እንዲቀር አደረገው ፤

ወሎጥኒ ኃደረ ውስተ አድያም ፤

ሎጥም የሰዶምና የገሞራ መወሳሰኛ በሚሆን ቦታ አደረ ፤

ወግዕዘ ውስተ ሰዶም ፤

ከዚያም ተነሥቶ ወደ ሰዶም ተጓዘ ፤

ጉባዔ

፲፫፡ ወሰብአ ሰዶምሰ እኩያን ፤

የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎች ነበሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኃጥኣን ጥቀ በቅድመ እግዚአብ ሔር ፤

በእግዚአብሔር ፊት ክፉዎች ነበሩ፤ ዘር ይቀበሉ ዘር ያቀብሉ ነበርና ፤

፲፬፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብ ራም እምድኅረ ተሌለየ እምኔሁ ሎጥ፤

ሎጥ ከእርሱ ከተለየ በኋላ፤ እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው ፤

ነጽር በአዕይንቲከ ወርኢ እምዝንቱ መካን ኀበ ሀለውከ ለመንገለ መስዕ ወአዜብ ወሠርቅ ወባሕር ፤

ከዚህ ካለህበት ቦታ ጀምሮ አንገትህን አቅንተህ አራቱንም መዓዝን ተመልከት ፤

፲፭፡ እስመ ኵሎ ለንታሃ ለዛቲ ምድር አንተ ትሬኢ ለከ እሁባ ፤

ይህችን የምታያትን ምድር ሁሉ (ከነዓንን) ላንተ እሰጥሃለሁና፤

ወለዘርእከ እስከ ለዓለም ፤

ከአንተም በኋላ ለልጆችህም እስከ ዘለዓለሙ አወርስሃለሁና፤

፲፮፡ ወእሬስዮ ለዘርእከ ከመ ኆፃ ባሕር ፤

ልጅህን፤ የልጅ ልጅህን እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ ፤

እመቦ ዘይክል ኈልቈቶ ለኆፃ ባሕር ይኄልቆ ለዘርእከሂ ፤

የባሕር አሸዋን መቍጠር የሚ ቻለው ሰው ቢኖር፤ ልጅህን፤ የልጅ ልጅህንም ይቍጠረው፤ ያም አይቆጠር ይህም አይቆ ጠር፤ (ሐተታ) በምን ምክንያት እንዲህ አለው ቢሉ ፤ ቀድሞ ከዘመዶቹ ሁሉ ተለየሁ፤ ደግሞ ዛሬ ከአንድ ወንድሜ ልለይ ? ብሎ አዝኗል ፤ በዚህ ምክን ያት እሬስዮ ብሎታል ፤

፲፯፡ ተንሥእ ወዑዳ ለምድር ውስተ ኑኃ ወርኅባ እስመ ለከ እሁባ ፤

ለአንተ እሰጥሃለሁና የከነዓንን ወርዷን ቁመቷን፤ ምሥራቋን ምዕራቧን ዙረኽ እያት አለው፤ (ሌላ ሐተታ) ቅርብ ቅርቡን በእግረ ሥጋ ፤ ያስረግጠዋል ፤ ሩቅ ሩቁን በዓይነ ሥጋ ያሳየ ዋል፤ ብሔረ ከነዓንስ ሰፊ ናት አትፈጸምም ብሎ ቅርብ ቅር ቡን በእግረ ሥጋ ያስረግጠዋል፤ በዓይነ ሥጋ ያሳየዋል ፤ ሩቅ ሩቁን በእግረ ሕሊና ያስረግጠ ዋል በዓይነ ሕሊና ያሳየዋል ፤

፲፰፡ ወግዕዘ አብራም ኀበ ዕፅ እንተ ውስተ ኬብሮን ፤

አብራምም በኬብሮን ወዳለው ዛፍ ተጓዘ ፤

ወነደቀ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚአብ ሔር ፤

በዚያም ለእግዚአብሔር የሚ ሠዋበትን ምሥዋዕ (ጸፈጸፈ) ሠራ ።



## ምዕራፍ ፲ወ፬

፩፡ ወኮነ በመዋዕለ አሜሬሮን ንጉሠ ሰናዖር ወአርዮ ንጉሠ ሴላስድ፡ ወኮ ሎዶጎሞር ንጉሠ ኤሎም ወቴሮጋ ንጉሠ አሕዛብ ፤

በሰናዖር ንጉሥ በአሜሬሮን በሴ ላስድ ንጉሥ በያርዮ በኤሎም ንጉሥ በኮሎዶጎሞር በአሕ ዛብ ንጉሥ በቴሮጋ ዘመን እን ዲህ ሆነ፤ (ሐተታ) አሁን ይህን ንጉሠ አሕዛብ ማለቱ፤ የቀሩት ነገሥት አሕዛብ ያይደሉ ሁነው አይደለም ፤ ቴሮጋንን ለይቶ ንጉሠ አሕዛብ ያለው ፤ ስመ ነገድ ነው ፤

፪፡ ወጸብዕዎሙ ለባላቅ ንጉሠ ሰዶም፤ ወለባሮስ ንጉሠ ገሞራ፤ ወለሰናዖር ንጉሠ ሰዶም ፤ ወለሴሜድር ንጉሠ ሲባዮ ወንጉሠ ባላ እንተ ይእቲ ሴጎር፤

ኮነ ያለውን ጸብዕዎሙ ብሎ አመጣው፤ የሰዶም ንጉሥ ባላ ቅንና የገሞራ ንጉሥ ባሮስን ፤ የሰዶም ንጉሥ ሰናዖርንና የሲ ባዮ ንጉሥ ሴሜድርን ፤ ሴጎር የምትባል የባላ ንጉሥንም ድል አደረጋቸው፤ ሴጎር ማለት ምስ ጋረ እግር ማለት ነው፤ ዘአእረፈ ባቲ ሎጥ ይላታል ፤

፫፡ ወእሉ ኵሎሙ ተጋብኡ ውስተ ቈላተ ኤሌቄን ፤

እነዚህም ሁሉ፤ ኤሌቄን በሚ ባል ቦታ ተሰበሰቡ ፤

እንተ ይእቲ ባሕረ ኤሎን፤

ይህችውም የጨው ባሕር ናት፤

፬፡ ወተቀንዩ ዐሠርተ ወክልኤተ ዓመተ፤ ለኮሎዶጎሞር፤ ወለነገሥት እለ ምስሌሁ ፤

ለኮሎዶጎሞርና ከእርሱም ጋራ ላሉ ነገሥታት ዐሥራ ሁለት ዓመት ተገዙ ፤

ወአመ ኮነ ዐሠርተ ወሠለስተ ዓመተ አጽረሩ ፤

ዐሥራ ሦስት ዓመት በሆነም ጊዜ በሰማይ የለ ዱር፤ በሰዶም የለ ግብር ብለው ግብር ነሡ፤ (ግብር አቀለጡ) ፤

፭፡ ወመጽአ ኮሎዶጎሞር ወነገሥት እለ ምስሌሁ ፤

ኮሎዶጎሞርና ከእርሱም ጋራ ያሉ ነገሥታት መጡ ፤

ወቀተልዎሙ ለእለ ያርብሕኒ በአስ ጣሮስ ወበቀራንዮን ፤

አርበኞቹንም አስጣሮስ ቀራን ዮን በሚባሉ ሥፍራዎች ላይ ወጓቸው ፤

ወለሕዝብኒ ጽኑዓን ምስሌሆሙ ፤

የማይደክሙ ኃያላኑንም እንደ አርበኞቹ (ከአርበኞቹ ጋራ) አጠ ፉዋቸው ፤

ወለአሚዎስ ወለሀገረ ሴዊ ፤

አሚዎስንም ወጉት፤ የሴዊ አገ ርንም አጠፉት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወለኬሬዎስ እለ አድባረ ሴይር፣ እስከ አድባረ ጠራሚዎስ ወፋራን እንተ ውስተ ሐቅል ፤

በምድረበዳ እስካለች እስከ ፋራንና እስከ ጠራሚስ ተራሮች ድረስ በሴይር ተራሮች ያሉ፣ የኬሬዎስንም አርበኞች ሁሉ አጠፉዋቸው ፤

፰፡ ወተጋቢኦሙ መጽኡ እንተ አዘቅተ ተስናን ፤

ተሰብስበውም ፀብ ክርክር ወደ ሚደረግባት ጉድጓድ መጡ ፤

እንተ ይእቲ ቃዴስ ፤

ይህችውም ቃዴስ ናት ፤

ወቀተልዎሙ ለመላእክተ አማሌቅ ለኵሎሙ ፤

የአማሌቅን አለቆች ሁሉ አጠፉዋቸው ፤

ወለአምዮስ ፤

ንጉሡ አምዮስንም ገደሉት፤

ወለእለ ይነብሩ ውስተ አስቃና ፤

በአስቃና የሚኖሩትንም ሁሉ አጠፉዋቸው ፤

፱፡ ወወፅኡ ንጉሠ ሰዶም ወንጉሠ ገሞራ፣ ወንጉሠ አዳማ፣ ወንጉሠ ሲባዮን፣ ወንጉሠ ባላ፣ እንተ ይእቲ ሴጎር ፤

የሰዶም ንጉሥና የገሞራ ንጉሥ፣ የአዳማ ንጉሥና የሲባዮን ንጉሥ፣ ሴጎር የምትባል የባላ ንጉሥም እነዚህ ሁሉ ወጥተው ፤

፱፡ ወተአኀዙ በቈላተ ኤሌቄን ምስለ ኮሎዶጎሞር ንጉሠ ኤሎም ወቴሮጋ፣ ንጉሠ አሕዛብ ወአሚሬሮን፣ ንጉሠ ሰናያር ወያርዮ ንጉሠ ሴላስድ ፤

ከኤሌም ንጉሥ ከኮሎዶጎሞር ፤ ከአሕዛብ ንጉሥ ከቴሮጋ ፤ ከሰናያር ንጉሥ ከአሚሬሮን ፤ ከሴላስድ ንጉሥ ከያርዮ ጋራ ኤሌቄን በሚባል ቦታ ይዋጉ ጀመር ፤

እሉ አርባዕቱ ነገሥት ምስለ እልክቱ ኃምስቱ ነገሥት ፤

እሊህ አራቱ ነገሥታት ከአምስቱ ነገሥታት ጋራ ይዋጉ ጀመር ፤

፲፡ ወውእቱስ ቈላተ ኤሌቄን ምሉዕ አዘቅተ ኰለንታሁ ፤

ይህም የተዋጉበት ኤሌቄን ፈጽሞ ረግረግ የተመላ ነው ፤ አሁን ከረግረጉ ገብተው አለቁ የሚል ነውና እንደ አርእስት አነሣው ፤

ወተሰብሩ ንጉሠ ሰዶም ወንጉሠ ገሞራ ፤

የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ድል ሆኑ ፤

ወቀተልዎሙ በህየ ፤

በዚያም ገደልዋቸው ፤

ወእለሰ ተሰብሩ ጐዩ ውስተ አድባር ፤

ድል የተነሱት ግን ሸሽተው ወደ ተራራ ወጡ ፤



፲፩፡ ወነሥኡ ኵሎ አፍራሰ ሰዶም ወገሞራ፣ ወኵሎ ስንቆሙ ወሐሩ፣

የሰዶምንና የገሞራን ፈረሶች ስንቃቸውንም ሁሉ ማርከው ሔዱ ፤

፲፪፡ ወነሥእዎ ለሎጥሂ ወልደ እኁሁ ለአብራም ፤

የአብራም የወንድም ልጅ ሎጥ ንም ማረኩት፤

ወንዋያቲሁኒ አእተዉ ፤

ገንዘቡንም ዘርፈው ወደ አገራቸው አገቡ፤

ወውእቱ ይነብር በሰዶም ፤

እርሱ በሰዶም ይኖር ነበርና፤

፲፫፡ ወበጽሐ እለ አምሰጡ ወዜነውዎ ለአብራም ፤

ከሰልፍ አምልጠው የሔዱ ሰዎች ከአብራም ዘንድ ደረሱ፤ ወንድምህ ሎጥ ተማረከ ብለው ለአብራም ነገሩት፤

እንዘ ሀለዉ ኀበ ኀበ ዕፅ ምስለ አምሮስ እኁሁ ለኤስኬል ወለአውናን ፤

የኤስኬልና የአውናን ወንድም ከሚሆን ከአምሮስ ጋራ በዛፍ ሥር በአንድነት ተቀምጠው ሳሉ ነገሩት፤ አንድም እኁሁ ለኤስኬል ብለህ ወለአውናን ዜነውዎ በል፤ ለአውናንም ሎጥ ተማረከ ብለው ነገሩት፤ አንድም እንዘ ሀለወ ምስለ አምሮስ ወምስለ አውናን በል፤ አብራም ከአምሮስና ከአውናን ጋራ ሳለ፣ ወንድምህ ሎጥ ተማረከ ብለው ነገሩት፤

እለ ቅሩባን እሙንቱ ለአብራም ፤

የአብራም ዘመዶቹ የሚሆኑ ብሎ ለኤስኬልና ለአውናን ቀጸለ ፤

፲፬፡ ወሶበ ሰምዐ አብራም ከመ ተፄወወ ሎጥ ወልደ እኁሁ ፤

አብራም የወንድሙ ልጅ ሎጥ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ ፤

ኈለቆሙ ለእሊአሁ ወለኵሎሙ ሰብአ ቤቱ ፤

ወገኖቹንና ቤተሰቡን ሁሉ ቈጠረ፤

ወኮኑ ሠለስተ ምእተ ዐሠርተ ወሰመንተ ፤

ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሆኑ ፤

ወዴገኖሙ ወተለዎሙ እስከ ዳን ፤

እስከ ዳን ዕፃ ድረስ ተከተላቸው፤ አንድም እስከ ጽንፍ ሲል ነው፣ እስከ ዳርቻ ተከተላቸው ፤

፲፭፡ ወበጽሖሙ ሌሊተ ምስለ ደቁ ወቀተሎሙ ወዴገኖሙ እስከ ኮቤር እንተ ፀጋመ ደማስቆ ፤

አብራም ከአሽከሮቹ ጋር በሌሊት ገስግሶ ፣ በደማስቆ ግራ

www.ethiopianorthodox.org

እስካለችው እስከ ኮቤር ድረስ ተከትሎ ደርሶ አጠፋቸው፤

፲፮፤ ወንሥአሙ አብቅሊሆሙ፣

በቅሎቻቸውንም ማረከ፤

ወነሥአ ለሎጥሂ ወልደ እኁሁ፣

የወንድሙን ልጅ ሎጥንም ይዞ ተመለሰ፤

ወንዋዮሙሂ፣ ወአንስቲኒ፣ ወሕዝበኒ አእተወ ፣

ገንዘቡንም ሴቶችንም ቤተሰቡንም ሁሉ ይዞ ገባ ፤

፲፯፤ ወወፅአ ንጉሠ ሰዶም ወተቀበሎ እምድኅረ ገብአ እም ነበ ቀተሎ ለኮሎዶጎሞር ወለነገሥት እለ ምስሌሁ በቈላተ ሴዋ ፣

አብራም፣ ኮሎዶጎሞርንና ከእርሱ ጋራ የነበሩ ነገሥታትንም በቈላተ ሴዋ ድል ነስቶ ሲመለስ የሰዶም ንጉሥ ወጥቶ ተቀበለው ፤

ወውእቱ ገዳም ዘመንግሥቱ ውእቱ፣

ይኸውም አብራም ድል የነሳበት ቦታ ኮሎዶጎሞር በሚገዛው አገር ያለ ምድረ በዳ ነው፤ አብራም ጥቂት ሁኖ ብዙውን ከሚገዛው አገር ሔዶ ድል ነሳው ለማለት፣ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለመናገር እንዲህ አለ፤ (ሐተታ) ይህም ምሳሌ ነው፣ አብራም የጌታ፣ ሎጥ የሃይማኖት፣ ፫፻፲፰ቱ ሰዎች፣ የ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት፤ ፭ቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር፣ የመናፍቃን፣ አምስቱ ነገሥተ ሰዶም የምእመናን ምሳሌ ፣ አብራም ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሰው ይዞ አሕዛብን ድል ነስቶ ሎጥን እንደ መለሰ ፣ ጌታም በሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት አድሮ መናፍቃንን ድል ነሥቶ ሃይማኖትን የመመለሱ ምሳሌ ነው ፤

፲፰፤ ወመልከ ጼዴቅ አውፅአ ኅብስተ ወወይነ ፣

መልከ ጼዴቅም ኅብስተ አኰቴት ፣ ጽዋዓ በረከትን ይዞ ተቀብሎታል ፤

ወካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል ውእቱ፣

የልዑል የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚሆን ፤

ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ ፣

ይኸውም የኢየሩሳሌም ንጉሥ ነው ፣ ንጉሠ ሰላምም ይላል ፣ ደቂቅየ ተፋቀሩ የምትል ወንጌልን የሚያስተምር የክርስቶስ ምሳሌ ነውና ፤

፲፱፤ ወባረኮ ለአብራም ፣

መልከ ጼዴቅ አብራምን መረቀው ፤



ወይቤሎ ቡሩኩ አብራም ለእግዚአብሔር ልዑል ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ ፣

አብራም ሆይ፣ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የእግዚአብሔር ክቡር ፍጥረቱ አንተ ነህ አለው፤

፳፤ ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል ዘአግብኦሙ ለጸላእትከ ውስተ እዴከ፣

ጠላቶችህንም በእጅህ የጣለልህ እግዚአብሔር፣ ክቡር ምስጉን ነው አለው፤

ወወሀቦ ዐሥራተ እድ እምኵሉ ፣

አብራም ለመልከ ጼዴቅ ከገንዘቡ ሁሉ ከዐሥር አንድ ሰጠው፤ (ሐተታ) ምን ገንዘብ አለውና ይሰጠዋል? ቢሉ ከያዘው ከስንቁ ሰጥቶታል፤ አንድም እምኵሉ ዔዋሁ ይላል፤ ከነገሥተ ሰዶም ገንዘብ ያይደለ፣ ከነኮሎዶጎሞር ማርኮ ካመጣው ገንዘብ ከዐሥር አንድ አውጥቶ ሰጠው፤ (ታሪክ) አብራም አራቱን ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ወግቶ ሲመለስ ፣ በዘመኑ የተደረገ ተአምራት ትዝ ቢለው ፤ አንድም የችኮላ አነጋገር፣ በመዋዕልየኑ ትፌኑ ወልደከ ወሚመ ታርእየኒ ኪያሃ ዕለተ አለ ፤ ጌታም አኮ ዘአርእየከ ኪያሃ አላ አምሳሊሃ ዕድዎ ለዮርዳኖስ ወትረክቦ ለመልከ ጼዴቅ አለው፤ መልከ ጼዴቅም ኅብስተ በረከት፣ ጽዋዓ አኰቴት ይዞ ተቀበለው ፤

ይኸውም ምሳሌ ነው፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት፣ አብራም የጥሙቃን፣ መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት ፤ ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኰቴት የሥጋው የደሙ ምሳሌ ፣ መልከ ጼዴቅ ከአብራም ፣ ከአሥር አንድ እንደ ተቀበለ ፣ ጌታም ከምእመናን ዐሥራት ጾምን ዐሥራት ጸሎትን የመቀበሉ ምሳሌ ነው ፤

፳፩፤ ወይቤሎ ንጉሠ ሰዶም ለአብራም ፣

የሰዶም ንጉሥ አብራምን እንዲህ አለው ፤

ሀበኒ ሰብአ ፣

ሰዎቹን ስጠኝ አለው፤ ያለ ሰው አገር አይቀናምና ፤

ወጥሪተሰ ንሣእ ለከ ፣

ገንዘቡ ግን ላንተ ይሁንህ አለው፤

፳፪፤ ወይቤሎ አብራም ለንጉሠ ሰዶም፣

አብራም የሰዶምን ንጉሥ እንዲህ አለው ፤

አሌዕል እዴየ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ፣

ሰማይንና ምድርን ወደፈጠረ ወደ እግዚአብሔር እጄን ከፍ ከፍ አድርጌ እናገራለሁ ፤

፳፫፡ ከመ ኢይንሥእ ኢፈትለ ወኢ ቶታነ አሣእን እምንዋይከ ፣

ካንተ ገንዘብ፣ የልብስ መስፊያ ክር፣ የጫማ ማዘቢያ ጠፍር፣ እንዳልወስድ፣ እጄን ከፍ ከፍ አድርጌ እምላለሁ ፤

ከመ ኢትበል አነ አብዐልክዎ ለአ ብራም ፣

አብራምን እኔ አከበርሁት እን ዳትል ፤

፳፬፡ ዘእንበለ ዘበልዑ ሰብእየ እክለ፣

ሰዎቹ ከበሉት እህል በቀር ገን ዘብህ ይመለስልህ አለው ፤

ዳዕሙ ዕደው እለ ሖሩ ምስሌየ፣ ኤስ ኬል ወመምሬ እሙንቱ ይንሥኡ ክፍሎሙ ፣

ነገር ግን ከእኔ ጋራ የዘመቱት ኤስኬልና መምሬ በጨኸት የመጡ ናቸውና አዘዙብን እን ዳይሉ ፈንታቸውን ይውሰዱ አለው ።

## ምዕራፍ ፲ወ፭

### ግባኤ

፩፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም በራእይ፣

ሀበኒ ሰብአ ወጥሪተሰ ኅደጉ ለከ ብሎ ነበርና፣ ሰዎቹን ካሰናበተ በኋላ፤ አንድም ነገሥተ ኮሎዶ ጎሞርን ድል ነሥቶ ከተመለሰ

በኋላ ቃለ እግዚአብሔር በራ እይ ወደ አብራም መጣ ተነገረ፤

ወይቤሎ ኢትፍራህ አብራም ፣

ጌታም አብራምን እንዲህ አለው፤ ድል እሆናለሁ ብለህ አትፍራ፤ አንድም ገንዘብ አጣለሁ ብለህ አትፍራ ፤

አነ አጸንዐከ ፣

እኔ አጸናሃለሁ ማለት፣ ሁሉን ድል እንድትነሣ አደርግሃለሁ፤

ወአዐብየከ ፣

ባለ ጸጋ አደርግሃለሁ፤

ወአስብከኒ ብዙኅ ውእቱ ጥቀ በኀ ቤየ ፣

ከእኔም የምታገኘው ገንዘብ ብዙ ነው አለው፤

፪፡ ወይቤሎ አብራም ምንት ውእቱ እግዚኦ ዘትሁበኒ ፣

ምንት ይበቊዐኒ ሲል ነው ፤ አብራምም አቤቱ ጌታዬ ብት ሰጠኝስ ምን ይረባኛል ምን ይጠ ቅመኛል ? ሰው ገንዘብ መፈ ለጉ ለልጁ አልነበረምን፣ ልጅ የለኝ አለው ፤

ወናሁ እመውት እንዘ አልብየ ውሉድ ፣

እነሆ ልጅ ሳልወልድ እሞታ ለሁ ፤



ወናሁ ወልደ ማሴቅ ዘደማስቆ ዘይ ብልዎ ኢየውብር፣ ዘእምወልደ ዘመ ድየ ውእቱ ይወርሰኒ ፣

ከዘመዴ ወገን የተወለደ፣ የደ ማስቆ ሰው የሚሆን የማሴቅ ልጅ ኢየውብር የሚባለው እርሱ ይወርሰኛል ፤ ልጅ ከሌ ለኝ ገንዘብስ ብትሰጠኝ ምን ይሆነኛል ? አለው ፤

፫፡ ወይቤ አብራም እስመ ሊተ ኢወ ሁብከኒ ዘርአ ወልደ ዘመድየ ይወር ሰኒ ፣

አብራምም ልጅ አልሰጠኸኝ ምና ከዘመዴ የተወለደ ኢያው ብር ቢወርሰኝ ምን ይጠቅመ ኛል ? አለ ፤

፬፡ ወበጊዜሃ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም ፣

ያን ጊዜ ከአብራም ዘንድ ቃለ እግዚአብሔር መጣ ተነገረ ፤

ወይቤሎ እንዘ ይብል ውእቱሰ ኢይ ወርሰከ አላ ካልእ ዘይወፅእ እምሐ ቌከ፣ ውእቱ ይወርሰከ ፣

ከአብራክህ የተወለደ ልጅህ ይወርስሃል እንጂ፣ ኢየውብር አይወርስህም ብሎ ነገረው ፤

፭፡ ወአውፅኦ አፍአ ፣

ይህን ከነገረው በኋላ ወደ ውጭ አውጥቶ ፤

ወይቤሎ ነጽር ውስተ ሰማይ ላዕለ፣

አንገትህን ቀና አድርገህ ወደ ሰማይ ተመልከት አለው ፤

ውኁልቆሙ ለከዋክብት ለእመ ትክል ኈልቆቶሙ ፣

መቊጠሩን ከቻልኽ ከዋክብትን ቊጠር አለው፣ «ኢይክል ኈል ቆቶሙ» ያለበት ነው ፤ እኔስ መቁጠር አይቻለኝም ብሏል ፤

ወይቤሎ ከማሁ ውእቱ ዘርእከ ፣

እንግዲያስ ልጆችህም እንደዚህ ይበዛሉ አለው ፤

፮፡ ወአምኖ አብራም ለእግዚአብሔር፣

አብራምም ልጆችህ ይበዙልሃል ቢለው፣ ሳይጠራጠር እግዚአ ብሔርን አመነው ፤

ወተኈለቈ ሎቱ ጽድቀ ፣

ይኸውም ማመኑ ጽድቅ ሆኖ ተነገረለት ፤ በእንተ ጽድቅ ይላል፣ ስለ ጽድቅ ሆኖ ተቈ ጠረለት ፤

ይኸም ምሳሌ ነው፣ እስራኤል ልጆቹን በከዋክብት፣ አሕዛብ ልጆቹን በአሸዋ መስሎ አሳይ ቶታል፤ (አንድም) በባሕርይም (በሥጋም) በሃይማኖትም የሚ ወልዳቸውን ጻድቃን ልጆቹን በከዋክብት፣ በባሕርይ (በሥጋ) እንጂ ፤ በሃይማኖት የማይወል ዳቸውን ኃጥአን ልጆቹን በአሸዋ መስሎ አሳይቶታል፤

፯፡ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብ ሔር አምላክከ ዘአውፃእኩከ እምድረ

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፤ ከመ ኢይነሥእ ኢፈትለ ወኢ ቶታነ አሣእን እምንዋይከ ፤

ካንተ ገንዘብ፣ የልብስ መስፊያ ክር፣ የጫማ ማዘቢያ ጠፍር፣ እንዳልወስድ፣ እጄን ከፍ ከፍ አድርጌ እምላለሁ ፤

ከመ ኢትበል አነ አብዐልክዎ ለአ ብራም ፤

አብራምን እኔ አከበርሁት እን ዳትል ፤

፳፬፤ ዘእንበለ ዘበልዑ ሰብእየ እክለ፣

ሰዎቼ ከበሉት እህል በቀር ገን ዘብህ ይመለስልህ አለው ፤

ዳዕሙ ዕደው እለ ሖሩ ምስሌየ፣ ኤስ ኬል ወመምሬ እሙንቱ ይንሥኡ ክፍሎሙ ፤

ነገር ግን ከእኔ ጋራ የዘመቱት ኤስኬልና መምሬ በፎጬኸት የመጡ ናቸውና አዘዙብን እን ዳይሉ ፈንታቸውን ይውሰዱ አለው ::

## ምዕራፍ ፲ወ፭

### ገባኤ

፩፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም በራእይ፣

ሀበኒ ሰብአ ወጥሪተሰ ኅደገ ለከ ብሎ ነበርና፣ ሰዎቹን ካሰናበተ በኋላ፤ አንድም ነገሥተ ኮሎዶ ጎሞርን ድል ነሥቶ ከተመለሰ በኋላ ቃለ እግዚአብሔር በራ እይ ወደ አብራም መጣ ተነገረ፤

ወይቤሎ ኢትፍራህ አብራም ፤

ጌታም አብራምን እንዲህ አለው፤ ድል እሆናለሁ ብለህ አትፍራ፤ አንድም ገንዘብ አጣለሁ ብለህ አትፍራ ፤

አነ አጸንዐከ ፤

እኔ አጸናሃለሁ ማለት፣ ሁሉን ድል እንድትነሣ አደርግሃለሁ፤

ወአዐብየከ ፤

ባለ ጸጋ አደርግሃለሁ፤

ወአስብከኒ ብዙኅ ውእቱ ጥቀ በኀ ቤየ ፤

ከእኔም የምታገኘው ገንዘብ ብዙ ነው አለው፤

፪፤ ወይቤሎ አብራም ምንት ውእቱ እግዚአ ዘትሁበኒ ፤

ምንት ይበቍዐኒ ሲል ነው ፤ አብራምም አቤቱ ጌታዬ ብት ሰጠኝስ ምን ይረባኛል ምን ይጠ ቅመኛል ? ሰው ገንዘብ መፈ ለገ ለልጁ አልነበረምን፣ ልጅ የለኝ አለው ፤

ወናሁ እመውት እንዘ አልብየ ውሉድ ፤

እነሆ ልጅ ሳልወልድ እሞታ ለሁ ፤



ወናሁ ወልደ ማሴቅ ዘደማስቆ ዘይ ብልዎ ኢየውብር፣ ዘእምወልደ ዘመ ድየ ውእቱ ይወርሰኒ ፤

ከዘመዴ ወገን የተወለደ፣ የደ ማስቆ ሰው የሚሆን የማሴቅ ልጅ ኢየውብር የሚባለው እርሱ ይወርሰኛል ፤ ልጅ ከሌ ለኝ ገንዘብስ ብትሰጠኝ ምን ይሆነኛል ? አለው ፤

፫፤ ወይቤ አብራም እስመ ሊተ ኢወ ሀብከኒ ዘርአ ወልደ ዘመድየ ይወር ሰኒ ፤

አብራምም ልጅ አልሰጠኸኝ ምና ከዘመዴ የተወለደ ኢያው ብር ቢወርሰኝ ምን ይጠቅመ ኛል ? አለ ፤

፬፤ ወበጊዜሃ ኮነ ቃለ እግዚአብሔር ኀበ አብራም ፤

ያን ጊዜ ከአብራም ዘንድ ቃለ እግዚአብሔር መጣ ተነገረ ፤

ወይቤሎ እንዘ ይብል ውእቱሰ ኢይ ወርሰከ አላ ካልእ ዘይወፅእ እምሐ ቋከ፣ ውእቱ ይወርሰከ ፤

ከአብራክህ የተወለደ ልጅህ ይወርስሃል እንጂ፣ ኢያውብር አይወርስህም ብሎ ነገረው ፤

፭፤ ወአውፅአ አፍአ ፤

ይህን ከነገረው በኋላ ወደ ውጭ አውጥቶ ፤

ወይቤሎ ነጽር ውስተ ሰማይ ሳዕለ፣

አንገትህን ቀና አድርገህ ወደ ሰማይ ተመልከት አለው ፤

ውኑልቆሙ ለከዋክብት ለእመ ትክል ኈልቆቶሙ ፤

መቍጠሩን ከቻልኽ ከዋክብትን ቍጠር አለው፣ «ኢይክል ኈል ቆቶሙ» ያለበት ነው ፤ እኔስ መቁጠር አይቻለኝም ብሏል ፤

ወይቤሎ ከማሁ ውእቱ ዘርእከ ፤

እንግዲያስ ልጆችህም እንደዚህ ይበዛሉ አለው ፤

፮፤ ወአምና አብራም ለእግዚአብሔር፣

አብራምም ልጆችህ ይበዙልሃል ቢለው፣ ሳይጠራጠር እግዚአ ብሔርን አመነው ፤

ወተኈለቈ ሎቱ ጽድቀ ፤

ይኸውም ማመኑ ጽድቅ ሆኖ ተነገረለት ፤ በእንተ ጽድቅ ይላል፣ ስለ ጽድቅ ሆኖ ተቈ ጠረለት ፤

ይኸም ምሳሌ ነው፣ እስራኤል ልጆቹን በከዋክብት፣ አሕዛብ ልጆቹን በአሸዋ መስሎ አሳይ ቶታል፤ (አንድም) በባሕርይም (በሥጋም) በሃይማኖትም የሚ ወልዳቸውን ጻድቃን ልጆቹን በከዋክብት፣ በባሕርይ (በሥጋ) እንጂ ፤ በሃይማኖት የማይወል ዳቸውን ኃጥአን ልጆቹን በአሸዋ መስሎ አሳይቶታል፤

፯፤ ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብ ሔር አምላክከ ዘአውፃእኩከ እምድረ

www.ethiopianorthodox.org

ከላውዴዎን ከመ አሀብከሃ ለዛቲ ምድር ትትዋረሳ ፤

እግዚአብሔርም ልትወርሳት ከነዓንን እሰጥህ ዘንድ ከከላውዴዎን ያወጣሁህ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው ፤

፰፡ ወይቤሎ እግዚኦ በምንት አአምር ከመ እወርሳ ፤

አቤቱ ጌታዬ ከነዓንን እንድ ወርሳት በምን አውቃለሁ ? አለው፤ (ሐተታ) እንዲያወርሰ ውማ ነግሮት የለምን ? ቢሉ የምወርስበትን ጊዜውን በምን አውቀዋለሁ ሲል ነው ፤

፱፡ ወይቤሎ ንሣእ ሊተ ላሕመ ዘሠለ ስቱ ዓመቱ ወጠሌ ዘሠለስቱ ዓመቱ፤ ወበግዐ፣ ዘሠለስቱ ዓመቱ ፤ ወማዕ ነቀ ፣ ወንሣእ ዘንተ ኵሎ፣

ንሣእና ንሣእ አንድ ወገን፤ ሦስት ዓመት የሆነውን ላም ፣ ሦስት ዓመት የሆነውን ፍየል፣ ሦስት ዓመት የሆነውን በግ፤ ዋኖስን ርግቡን፣ ይህን ሁሉ ይዘህ አምጣልኝ አለው ፤

ወምትሮሙ እማዕከሎሙ ፣

ላሙን፣ ፍየሉን፣ በጉን፣ ከሁለት ከሁለት ለያቸው አለው ፤

ወለአዕዋፍሰ ኢትምትሮን ፣

ርግብንና ዋኖስን ግን ገዝግዘህ ተዋቸው እንጂ አትቈረጣቸው አለው ፤

፲፡ ወነሥአ ሎቱ ከማሁ ዘንተ ኵሎ ወመተሮሙ እማዕከሎሙ ፣

ጌታ እንደነገረው ይህንን ሁሉ አምጥቶ ከሁለት ከሁለት ለያቸው፤

ወአንበረ ዘተመትረ በአንፃረ ቢጹ፣

ከሁለት ከሁለት የለየውንም የላሙን በላም፣ የፍየሉን በፍየል፣ የበጉን በበግ አንፃር አኖረው፤

፲፩፡ ወለአዕዋፍሰ ኢመተሮን ፣

ዋኖስን ርግብን ግን፣ ገዘግዞ ተዋቸው እንጂ አልቈረጣቸውም፤

ወወረዱ አዕዋፍ ላዕለ አብድንት ዘተመትሩ ፣

የታረደውንም ሥጋ እንበላለን ብለው አዕዋፍ መጡ ፤

ወነበረ አብራም ኀቤሆሙ ወሚጦሙ፣

አብራም ከዚያ ተቀምጦ መለሳቸው ፤

፲፪፡ ወሶበ የአርብ ፀሐይ ድንጋጼ መጽአ ለአብራም ፣

ፀሐይ በገባ ጊዜ በአብራም እንቅልፍ (ተደሞ) መጣበት ፤

ወናሁ ግሩም ጽልመት ወዐቢይ መጽአ ላዕሌሁ ፣

ጽኑ ግሩም የሚሆን ጨለማ እነሆ መጣበት ፤

፲፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብራም አእምሮ አእምር ከመ ሀለዎሙ



ለዘርእከ ፈላሴ ይኩኑ ውስተ ምድር እንተ ኢኮነት እንቲአሆሙ ፣

እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው፤ ልጆችህ አገራቸው ባይደለች በግብጽ መጻተኛ ስደተኛ ሆነው ይኖሩ ዘንድ እንዳላቸው ፈጽመህ እወቅ ፤

ወይቀንይዎሙ ወይሣቅይዎሙ ወያጼእርዎሙ አርባዕቱ ምእተ ዓመተ፣

ግብጻውያን አራት መቶ ዘመን መከራ አጽንተው አስጨንቀው እንዲገዙዋቸው እወቅ ፤

፲፬፡ ወካዕበ ለሕዝብ እለ ይሣቅይዎሙ አነ እኴንኖሙ ፣

ዳግመኛም ፣ ሥቃይ በሚያጸኑባቸው በግብጻውያን እኔ እፈርድባቸዋለሁ፤

ወእምድኅረ ዝንቱ ይወፅኡ ዝየ ምስለ ብዙኅ ንዋይ ፣

ከዚህም በኋላ ከብዙ ገንዘብ፣ ከብዙ ጓዝ ጋራ ከግብፅ ወጥተው ወደዚህ ይመጣሉ፤

፲፭፡ ወአንተሰ ተሐውር ወትገብእ ኀበ አበዊከ በርሥዕ ሠናይ ፣

አንተ ግን በሕግ በአምልኮት ኑረህ በበጎ እርግና ሳለህ በሞት ወደ አባቶችህ ትሔዳለህ፣ ወደ መቃብርም ትወርዳለህ ፤ አንድም አእምሮ አእምር ብለህ መልስ፤ የነርሱ ርስታቸው ባይደለች በገሃነም ይኖሩ ዘንድ እንዳላቸው እወቅ፤ (ወይቀንይዎሙ) አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን አጋንንት መከራ ያጸኑባቸዋል፤ (ወካዕበ ለሕዝብ እለ ይሣቅይዎሙ) ዳግመኛም መከራ በሚያጸኑባቸው በአጋንንት እኔ መቻያ አጸናባቸዋለሁ፤ እንዳጸናባቸው እወቅ፤ (ወእምድኅረ ዝንቱ) ከ፭ ሺህ ፭፻ ዘመን በኋላ ከብዙ ጸጋ ክብር ጋራ ከገሃነም ይወጣሉ፤ (ወአንተሰ ተሐውር) አንተም በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀህ፣ አባቶችህ ወደሚገቡባት ወደ ገነት ትመለሳለህ ፤

፲፮፡ ወበራብዕ ትውልድ ይገብኡ ዝየ ፣

በአራተኛውም ትውልድ ከግብጽ ወደ ከነዓን ይመለሳሉ ፤ (ሐተታ) በይሁዳ የቈጠሩ እንደሆነ፣ ፋሬስ፤ ኤስሮም፤ አራም፤ ነአሶን፤ አራት ይሆናል፣ በነአሶን ጊዜ ወጥተዋል፤ በሌዊ የቈጠሩ እንደሆነ፣ ሌዊ፤ ቀዓት፤ እንበረም ፤ ሙሴ አራት ይሆናል ፤ በሙሴ ጊዜ ወጥተዋል ፤

እስመ እስከ ይእዜ ኢተፈጸመ ኃጣውኢሆሙ ለአሞሬዎን ፣

አለመውጣታቸውም እስከ ዛሬ ድረስ የአሞሬዎን ኃጢአታቸው አልተፈጸመምና ስለዚህ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወሶበ ኮነ ጊዜ የዐርብ ፀሐይ፣

ፀሐይ በገባ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤

መጽአ ነድ፣ ወመጽአ እሳት፣ ወመ ጽአ ዕቶን ዘይጠይስ ፣

እሳቱ እየነደደ፣ ምድጃው እየ ጤሰ ሲመጣ አየ ፤

ወኃለፈ እንተ ማዕከሉ ለውእቱ ዘተ መትረ ፣

አርዶ ከሁለት ከሁለት ለይቶ ባኖረውም ሥጋ መካከል እሳቱ እየነደደ ሲመላለስ አየ ፤

፲፰፤ ወበይእቲ ዕለት አቀመ እግዚ አብሔር ለአብራም ኪዳነ ዘአሰፈም፣

በዚያች ቀን እግዚአብሔር ለአ ብራም ተስፋ አድርጎ የነገረውን ቃል ኪዳኑን አጸናለት ፤

ወይቤሎ ለዘርእከ እሁባ ለዛቲ ምድር እምፈለገ ግብጽ እስከ ፈለግ ዐቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ ፣

ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ፣ ከነዓንን ለልጆችህ አወርሳቸዋለሁ ብሎ የነገረውን ቃል ኪዳኑን አጸናለት ፤

፲፱፤ ዘቄኔዎስ ወዘቄኔዝዮስ ወዘቄኔ ሜሌዎስ ፣

ይህችም ምድር የቄኔዎስና የቄ ኔዝዮስ የቄኔሜሌዎስ ናት ፤

፳፤ ወዘኬጤዎን፣ ወዘፌርዜዎን ወዘ ፈራዮን ፣

የኬጤዎን፣ የፌርዜዎን፣ የፈራ ዮን ሀገር ናት ፤

፳፩፤ ወዘአሞሬዎን ወዘከናኔዎን፣ ወዘ ጌርጌሴዎን ወዘኢያቡሴዎን ፣

የአሞሬዎን፣ የከናኔዎን የጌር ጌሴዎን፣ የኢያውቡሴዎን ሀገር ናት፤ የነዚህን ሁሉ ሀገር አወር ስሃለሁ ብሎ ነገረው፤ (ሐተታ) ይህም ምሳሌ ነው ፤ ሦስት ዓመት የሆነውን ላም፣ ሦስት ዓመት የሆነውን ፍየል፣ ሦስት ዓመት የሆነውን በግ አምጣ ማለቱ፣ በሦስተኛው ትውልድ ወደ ግብጽ የመውረዳቸው ምሳሌ ነው ፤ አብርሃም ፣ ይስ ሐቅ፣ ያዕቆብ ሦስት፣ በያዕቆብ ጊዜ ወደ ግብጽ ወርደዋል፤ ላም አምጣ አለው ፤ ላም ከፍየል ይበረታል፤ እስራኤልም በመ ጀመሪያው ፈርዖን በርትተው ተገዝተዋልና ፣ ፍየል አምጣ አለው፤ ፍየል ከላም ይደክማል፣ ከበግ ይበረታል፤ እስራኤልም በሁለተኛው ፈርዖን እጅግም ሳይበረቱ እጅግም ሳይደክሙ ተገዝተዋልና ፤ በግ አምጣ አለው ፤ በግ ከፍየል ይደክ ማል፣ እስራኤልም በሦስተኛው ፈርዖን ፈጽመው ደክመዋልና፤ ከሁለት ስፍራ ማኖሩ ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዘመን በከነዓን፤ ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዘመን በግብጽ የመኖ ራቸው ምሳሌ ነው፤ በየአንጻሩ አኑረው ማለቱም በግብጽ አንድ



ሁነው መከራውን የመቀበላቸው ምሳሌ ነው፤ ኋላ በፋርስ በባቢ ሎን ፣ በጽርዕ በሜዶን ተበት ነው እንደሚቀበሉት አይደለ ምና ፤ ዋኖስ ርግብ የእስራኤል ምሳሌ፤ ዋኖስ ምድረ በዳ ትወ ዳለች ፤ እስራኤልም አርባ ዘመን በምድረ በዳ ኖረዋልና፤ ርግብ መንደር ትወዳለች ፣ እስራኤልም ኋላ ምድረ ርስት ገብተዋልና ፤ አንድም ዋኖስ ርግብ የሙሴ የአሮን ምሳሌ፤ ገዝግዞህ ተዋቸው ማለቱ፣ መከ ራው እንደ እስራኤል በሙሴ በአሮን አልጸናባቸውምና ፤ አን ድም ዋኖስ የሙሴ ፣ ዋኖስ ምድረ በዳ ትወዳለች፤ ሙሴም ከዘመዶቹ ተለይቶ በምድያም አርባ ዘመን ኖሮአልና፤ ርግብ የአሮን፣ ርግብ መንደር ትወዳ ለች ፣ አሮንም ከዘመዶቹ አል ተለየምና ፤ ምሴት የእርግና ፣ እንቅልፍ የሞቱ ፣ አዕዋፍ የአ ሕዛብ ፣ በትር የኪዳኑ አብር ሃም ምሳሌ ነው ፤ አብርሃም በበትር አዕዋፍን መከልከሉ ፣ እስራኤል በኪዳኑ አብርሃም የመጠበቃቸው ምሳሌ ፣ ጨለ ማው፣ እሳቱ፣ ወቅለምቱ የእ ስራኤል የመከራቸው ምሳሌ ነው ፤ አንድም ላም ፣ ፍየል ፣ በግ ፣ ዋኖስ ፣ ርግብ አንድ ወገን ፣ የጌታ የመሥዋዕትነቱ

ምሳሌ ነው ፤ አንድም ላም ፣ የጌታ፣ ፍየል የሐዋርያት፣ በግ የአርድእት፣ ርግብ የእመቤታ ችን፣ ዋኖስ የዮሐንስ ምሳሌ ነው፤ ገዝግዘህ ተዋቸው ማለቱ መከራ በዮሐንስና በእመቤታ ችን እንደ ጌታ ፣ እንደ ሐዋ ርያት አልጸናባቸውምና የዚህ ምሳሌ ነው፤ አንድም ሳዊሮስ ዘእስሙናይን ፣ ሦስት ላም ፣ ሦስት ፍየል፣ ሦስት በግ አምጣ አለው ይላል፤ እነዚህን ከሁለት ከሁለት ሲያደርጋቸው ዐሥራ ስምንት ይሆናሉ፤ ዋኖስና ርግብ ሲጨመሩ ሀያ ይሆናሉ፤ ይህ በተደረገ በሁለት ሺህ ዘመን ጌታ ከቤተ አብርሃም ሰው ሆኖ የመወለዱ ምሳሌ ነው፤ በዚህም ጊዜ የይስሐቅን ልደት ተስፋ ውን ለአብርሃም ነግሮታል ፣ ይህንንም ተስፋውን በሰማ በሀያ አምስት ዘመን ይስሐቅን ወልዶ ታል፤ ይስሐቅ በተወለደ በስድሳ ዘመን ያዕቆብ ተወልድዋል ፣ ያዕቆብ በተወለደ በመቶ ሠላሳ ዘመን ግብጽ ወርደዋል፣ በከ ነዓን የኖሩትም ሁለት መቶ ዐሥራ አምስት ዘመን ይህ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ልጅሽን፣ ቊጥሩ ከብዛቱ የተነሣ የማይቈጠር እስኪሆን ድረስ ፈጽሜ አበዛዋለሁ አላት ፤

፲፩፡ ወይቤላ መልአከ እግዚአብሔር ጽንስት አንቲ ፣

ከእግዚአብሔር የተላከውም መልአክ እንዲህ አላት፣ እነሆ አንቺ ጸንሰሻል ፤

ወትወልዲ ወልደ ፣

ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ፤

ወትሰምዪዮ ስሞ ይስማኤል ፣

ስሙንም ይስማኤል ትዪዋለሽ፤ (ሐተታ) ይስማኤል ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

እስመ ሰምዐ እግዚአብሔር ሥቃየኪ ፣

እግዚአብሔር መከራሽን ሁሉ ሰምቶአልና ፤

፲፪፡ ወይከውን ብእሴ ሐቅል ፣

በምድረ በዳ የሚኖር አርበኛ ይሆናል ፤

እደዊሁ ላዕለ ኲሉ ፣

የሰውንም ሁሉ ገንዘብ ሲቀማ ይኖራል ፤

ወእደወ ኲሉ ላዕሌሁ ፣

ሌሎችም የእርሱን ገንዘብ ሲቀሙት ይኖራሉ፤ አንድም ወይከውን ብእሴ ሐቅል፣ ነጋዴ ይሆናል፤ እደዊሁ ላዕለ ኲሉ፤ እርሱ የሰውን እጅ ሲጸፋ ይኖራል ማለት፣ እርሱ የሌላውን ገንዘብ ይገዛል፣ ወእደወ ኲሉ ላዕሌሁ፣ ሌሎችም የርሱን ገንዘብ ይገዛሉ ፤

ወየኃድር ቅድመ አኃዊሁ ፣

በወንድሞቹ በእስራኤልና በግብፃውያን መካከል ደስ ብሎት ይኖራል ፤

፲፫፡ ወጸውዐት አጋር ስመ እግዚአብሔር ዘተናገራ ፣

አጋር የተናገራትን እግዚአብሔርን አመሰገነች ፤

ወትቤ አንተ እግዚኦ ዘመሐከነ ፣

አቤቱ ጌታዬ ያዘንህልኝ የራራህልኝ አንተ ነህ አለች ፤

እስመ ቅድሜየ ርኢክዎ ለዘአስተርአየኒ ፣

ያነጋገረኝን መልአክ ፣ በፊቴ ተገልጾ አይቼዋለሁና፤ (ሐተታ) ከላይ መልአከ እግዚአብሔር አለ፤ ከዚህ እግዚአብሔር አለ፤ እንደምን ነው ቢሉ፤ በመልአኩ አድሮ የተናገራት እግዚአብሔር ነው ያሉ እንደሆነ ገለጠው፡ ከዚያ የተነጋገራት መልአኩ ነው ያሉ እንደሆነ፣ ከዚህ እግዚአብሔርን ፣ ወጸውዐት ስመ እግዚአብሔር ብሎ በዋዌ አመጣው፤ መልአክ ካለበት እግዚአብሔር ፤ እግዚአብሔር ካለበት መልአክ አይለይምና እንዲህ አለ ፤



፲፬፡ ወበእንተ ዝንቱ ሰመየቶ ስሞ ለውእቱ ዓዘቅት ዘቅድሜየ አስተርአየኒ ፣

ስለዚህም ነገር፣ የምንጬን ስም ለኔ በፊቴ መልአኩ የተገለጠበት ቦታ ነው አለችው ፤

ማዕከለ ቃዴስ፣ ወማዕከለ ጋሬድ፣

ይኸውም ጉድጓድ፣ በቃዴስና በጋሬድ መካከል ያለ ነው ፤

ወገብአት አጋር ፣

ከዚያም በኋላ አጋር ወደ እመቤትዋ ተመለሰች ፤

፲፭፡ ወእምድኅረ ዝንቱ ወለደት ሎቱ አጋር ለአብራም ፣

ከተመለሰችም በኋላ፣ አጋር ለአብራም ወንድ ልጅን ወለደችለት ፤

ወሰመየ ስሞ አብራም ለውእቱ ሕፃን ዘወለደት ሎቱ አጋር ይስማኤል፣

አብራም፣ አጋር የወለደችለትን የልጁን ስም ይስማኤል አለው፤ እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው ፤

፲፮፡ ወ፹ወ፮ቱ ዓመቱ ለአብራም አመ ወለደት ሎቱ አጋር ይስማኤልሃ ፣

አጋር፣ ይስማኤልን በወለደች ጊዜ፣ ለአብራም ሰማንያ አምስት ዘመን ሆኖት ነበር ።

## ምዕራፍ ፲ወ፯

፩፡ ወእምዝ አመ ኮነ ለአብራም ፺ወ፱ቱ ዓመቱ አስተርአዮ እግዚአብሔር ለአብራም ፣

ከዚህም በኋላ ለአብራም ዘጠና ዘጠኝ ዓመት በሆነው ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ታየው ተነጋገረው ፤

ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሪከ ዘሖርኩ በቅድሜከ ፣

በሔድክበት ሁሉ አብሬህ የምሔድ ፈጣሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው ፤

አሥምር ቅድሜየ ፣

ተገዘርልኝ አለው፤

ወኩን ንጹሐ ፣

ንጹሕ ኹን ማለት በግዝረትህም ከአሕዛብ የተለየህ ኹን፤

፪፡ ወእሠይም ኪዳነ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ፣

በእኔና በአንተ መካከል መሐላዬን አጸናለሁ ፤

ወአበዝኃከ ጥቀ ፣

እጅግም አበዛሃለሁ ፤

፫፡ ወወድቀ አብራም በገጹ ፣

አብራም በግንባሩ ወድቆ እጅ ነሣ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፡ ወነሥአ አብርሃም ለይስማኤል ወልዶ።

አብርሃም ልጁን ይስማኤልን አመጣው ፤

ወለኵሉ ልደ ቤቱ ።

ከቤቱ የተወለዱ የባሮቹን ልጆች ሁሉ ፤

ወለኵሉ ተባዕት ዘተሣየጠ በወርቁ።

በወርቁ የገዛውን ወንዱን ባርያ ሁሉ፤

ወለኵሉ ሰብአ ቤቱ ።

ቤተሰቡን ሁሉ አምጥቶ፤

ወገዘሮሙ ከተማ ሥጋ ነፍስቶሙ በከመ ይቤሎ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር እንዳዘዘው የአ ባለ ዘራቸውን ሰንኮፍ ገዘራ ቸው፤

፳፬፡ ወይእቲ አሚረ ተስዓ ወተስዓቱ ዓመት ሎቱ ለአብርሃም አመ ተገ ዘረ ከተማ ነፍስቱ ።

አብርሃም የአባለ ዘሩን ሰንኮፍ በተገዘረ ጊዜ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሁኖት ነበር ፤

፳፭፡ ወለይስማኤል ወልዱ ዐሠርቱ ወሠለስቱ ዓመቱ አመ ተገዝረ ።

ልጁ ይስማኤልም በተገዘረ ጊዜ ዐሥራ ሦስት ዘመን ሁኖት ነበር ፤

፳፮፡ ወበጊዜሃ በይእቲ ዕለት ተገዝረ አብርሃም ።

በጊዜዋ ጊዜ በዚያች ቀን አብ ርሃም ተገዘረ ፤

፳፯፡ ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ተገዝሩ ።

ቤተ ሰቡም ሁሉ ተገዘሩ ::

## ምዕራፍ ፲ወ፰

### ገባኤ

፩፡ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለአ ብርሃም በኀበ ዕፀ መምሬ እንዘ ይነ ብር ኀበ ኆኅተ ሐይመት ቀትረ።

መምሬ ማለት ወይራ ግራር ማለት ነው፤ አብርሃም በቀትር ጊዜ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በወይራ በግ ራር አጠገብ ታየው ተነጋገረው፤ አንድም በድንኳኑ ደጅ በዕን ጨት ወንበር ተቀምጦ ሳለ ታየው ተነጋገረው ፤

፪፡ ወሶበ አልዐለ አዕይንቲሁ ወነ ጸረ ።

አንገቱን ቀና አድርጎ ዓይኑን አራምዶ ባየ ጊዜ ፤

ወናሁ ሠለስቱ ዕደው ይቀውሙ መልዕልቴሁ።

እነሆ ሦስት ሰዎች፣ ከበላዩ ባለ ተራራ ቁመው አያቸው ፤ (ሐተታ) ከድንኳኑ በላይ ተራራ አለ፣ በዚያው በተራራው ሥላሴ



ወደ እርሱ ሲወርዱ አይቶአቸ ዋል ፤

ወርእየ ወሮጸ ለተቀበሎቶሙ እምኆ ኅተ ሐይመት ።

ባያቸውም ጊዜ ከድንኳኑ ደጅ ተነሥቶ ለመቀበል ፈጥኖ ሄደ፤

ወሰገደ ውስተ ምድር ።

ከምድር ወድቆ እጅ ነሣ ፤

፫፡ ወይቤሎ እግዚኦ እመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲከ ኢትኅ ልፍ እምገብርከ ።

አቤቱ በፊትህስ ባለሟልነትን ካገኘሁ አገልጋይህን አትለፈኝ አለው ፤

፬፡ ናምጽእ ለክሙ ማየ ወንሕጽብ እገሪክሙ ።

ውሀ አምጥተን እግራችሁን እን ጠባችሁ ፤ አንድም እግራችሁን እናጥባችሁ ዘንድ ውሀ እናምጣ አለ ፤ (ሐተታ) ቅድመ አዕይን ቲከ ብሎ አንድነትን፣ ናምጽእ ለክሙ ብሎ ሦስትነትን ተናገረ፤

፭፡ ወታጽልሉ ታሕተ ዕፅ ናምጽእ ኅብስተ ወትብልዑ ።

እህልም ትቀምሱ ዘንድ እስክና መጣላችሁ ድረስ ፣ ከዛፉ ጥላ እረፉልን ፤

ወእምዝ ተሐውሩ ኀበ ሐለይክሙ እምከመ ግኀሥክሙ ኀበ ገብርክሙ።

ከእኔ ከባርያችሁ ቤት ከገባችሁ በኋላ፣ ወደ አሰባችሁት ትሄዳ ላችሁ ፤

ወይቤልዎ ግበር ከማሁ በከመ ትቤ።

አሁን እንደ ተናገርኸው ይሁን አድርግ አሉት ፤

፮፡ ወሮጸ አብርሃም ኀበ ሳራ ብእሲቱ ውስተ ሐይመታ ።

አብርሃምም ሚስቱ ሳራ ወዳለ ችበት ድንኳን ፈጥኖ ሄደ ፤

ወይቤላ አፍጥኒ ወአብሕኢ ሠለስተ መሥፈርተ ስንዳሌ ወግበሪ ዳፍንተ።

ልጠ ገርዶ የወጣለት ሦስት መሥፈሪያ ስንዴ ዶቄት ፈጥ ነሽ ለውሰሽ ዳቦ ጋግሪ አላት፤

፯፡ ወሮጸ አብርሃም ኀበ አልሕምት።

አብርሃምም ላሞች ወዳሉበት ፈጥኖ ሔደ ፤

ወነሥአ አሐደ ላሕመ ንዑሰ ወሠናየ ወወሀበ ለቀሩልዔሁ።

የሰባ የወፈረ አንድ ወይፈን አምጥቶ እረደው አወራርደው ብሎ ለብላቴናው ሰጠው ፤

ወአፍጠነ ገቢሮቶ ።

ብላቴናውም ፈጥኖ አርዶ አወ ራርዶ አቀረበለት ፤

፰፡ ወአምጽአ ዕቋነ ወመዓረ ።

የረጋ ወተትና መዓር አመጣ፤

ወውእተ ላሕመ ዘገብረ አቅረበ ሎሙ ወበልዑ ።

ያረደውን ያወራረደውን የወይ ፈኑንም ሥጋ አቀረበላቸው ፤ በሉ ጠጡ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወውእቱሰ ይቀውም ኀበ ዕፅ ወይሜጥዎሙ ፡፡

አብርሃምም ከዛፉ ሥር ፡ አንድም ከድንኳኑ ተራዳ አጠገብ አደግድጎ ቁሞ ያሳልፍ ነበር፡ (ሐተታ) የበሉትስ ምግብ እንደምን ነው ቢሉ፡፡ ሥላሴ በቤተ አብርሃም ፡፡ ሁለቱ መላእክት በሎጥ ቤት፡፡ ሩፋኤል በጦቢት ቤት የበሉት ምግብ፡፡ ግብር አምላካዊ ነው፡ አይመረመርም፡ ይኸውም ምሳሌ ነው ፡ ሦስት መሥፈሪያ ስንዴ፡፡ የሦስትነታቸው፡ አንድ ሆኖ መጋገሩ፡፡ የአንድነታቸው፡ ማር የአራት ምሳሌ ነው ፡ ማር ለጊዜው ሲይዝ የሚለቅ አይመስልም፡፡ ኋላ ግን ቶሎ ይለቃል፡ ኦሪትም ስትሠራ የምታልፍ አትመስልም ነበር ፡ ኋላ ግን አልፋለችና ፡ ዕቋን የወንጌል ምሳሌ ነው፡ ይህ ቅቤ ለጊዜው የሚለቅ ይመስላል፡፡ ኋላ ሲያጥቡት አይለቅም፡ ወንጌልም ለጊዜው ስትሠራ የምታልፍ ትመስል ነበር፡ ኋላ ግን ጸንታ የምትኖር ሆናለችና ፡

፱፡ ወይቤሉ አይቴ ሳራ ብእሲትከ፡፡ እግዚአብሔርም አብርሃምን ሚስትህ ሳራ ወዴት ናት ? አለው ፡ (ሐተታ) ለጌታ ያለችበት ጠፍቶት አይደለም፡ አሁን ትረክብ ሳራ ወልደ የሚለው ነውና ስለዚህ ነው ፡

ወይቤሎ ነያ ውስተ ሐይመት ፡፡

አብርሃምም ያችው በድንኳን ውስጥ አለች አለው ፡

፲፡ ወይቤሎ ሶበ ገባእኩ እመጽእ ኀቤከ አመ ከመ ዮም ትረክብ ሳራ ወልደ፡፡

እንደ ዛሬ ጊዜ ተመልሼ በረድኤት ወደ አንተ በመጣሁ ጊዜ ሳራ ወንድ ልጅን ትወልዳለች አለው፡ (ሐተታ) ዓመት ጸንሳ ወልዳዋለችና፡ እንዲህ አለ? ቢሉ ሐምሌ በገባ በሰባት ቀን ተስፋውን ሰምታለች፡ ጽንሱ በመስከረም፡፡ ልደቱ በሰኔ ነው፡ ዓመት ሊመላ የቀረው ቀኑ ጥቂት ከሆነ ብሎ እንዲህ አለ፡ አንድም ሀውደ ዓመቱ ከተለወጠ ብሎ፡ አንድም እንደ ዛሬ ጊዜ (ከርሞ ይህን ጊዜ) ከሥጋህ ሥጋ፡፡ ከነፍስህ ነፍስ ነሥቼ ሰው ለመሆን በመጣሁ ጊዜ ፡፡ ሳራ ወንጌል ምእመናንን ታስገኛለች አለው፡ ምነው ከአብርሃም እስከ ጌታ ሁለት ሺህ ዘመን አይደለምን ? ቢሉ ፡ በጌታ ዘንድ ጥቂት ከሆነ ብሎ ፡



ወሰምዐት ሳራ እንዘ ትቀውም ኀበ ኆኅት እንዘ ሀለወት ድኅሬሁ ፡፡

ሳራ በድንኳኑ ደጅ ከአብርሃም ኋላ ቆማ ሳለች ፡፡ ጌታ ልጅ ትወልዳለች ሲል ሰማች፡

፲፩፡ ወአብርሃምሰ ወሳራ ልሕቁ ጥቀ ወኃለፈ መዋዕሊሆሙ፡ ወኃደጋ ለሳራ ትክቶ አንስት ፡፡

አብርሃምና ሳራ ግን የጉልማስነታቸው ወራት አልፎባቸው ፈጽመው አርጅተው ነበር ፡ ሳራንም የሴቶች ግዳጅ ትቷት ነበር ፡

፲፪፡ ወሰሐቀት ሳራ በባሕቲታ ፡፡

ሳራም ብቻዋን ሳቀች፡፡ ማለት ተጠራጠረች ፡

እስመ ትቤ በልባ ዓዲየኑ እስከ ይእዜ፡፡

ሲያረጁ አምባር ይዋጁ እንዲሉ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ገና ቆንጆ ነኝን ? ብላ ፡

ወእግዚእየኒ ልሕቀ ፡፡

ጌታዬም አርጅቷል (ቶች) እኔ ገና ነኝን? ብላ፡ አንድም ወእግዚእየኒ ኢልሕቀ ይላል፡ ጌታዬስ አላረጀምን ? ብላ ተጠራጠረች ፡

፲፫፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም፡ ምንት አስሐቃ ለሳራ በባሕቲታ ፡፡

እግዚአብሔርም አብርሃምን ሳራ ብቻዋን ለምን ተጠራጠረች አለው ፡

እንዘ ትብል ዓዲየኑ እስከ ይእዜ፡ ወእግዚእየኒ ልሕቀ ፡፡

ጌታዬ አርጅቷል፡ እኔስ እስከ ዛሬ ገና ነኝን ? ብላ ፡

አማንኑ እወልድ ወናሁ ረሣእኩ አንስ ፡፡

እነሆ እኔ ፈጽሞ አርጅቻለሁ፡፡ በውኑ እንግዲህ እኔ ልጅ እወልዳለሁን ? ብላ ለምን ተጠራጠረች ፡

፲፬፡ ቦኑ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር ፡፡

በውኑ ካረጁ በኋላ እንዲወልዱ ማድረግ ለእግዚአብሔር ይሳነዋልን ?

በዝንቱ ጊዜ ሶበ ገባእኩ ኀቤከ በሳብዕት ትረክብ ሳራ ወልደ ፡፡

ይህን ጊዜ በረድኤት ወደ አንተ በመጣሁ ጊዜ ከግዳጅዋ በነጻች በሰባተኛው ቀን ሳራ ወንድ ልጅን ታገኛለች ፡ (ሐተታ) ምነው አሁን ውነደጋ ትክቶ አንስት ብሎ አልነበረምን ቢሉ፡፡ ኋላ በተአምራት እንደገና ተመልሶላታል ፡ አንድም በፍጹም ሃይማኖትዋ፡፡ በፍጹም ተስፋዋ ወንድ ልጅን ታገኛለች ፡፡ አንድም አስተርአዮ አስተርአዮ ያለው ሰባት ይሆናል ፡ ጌታም ለአብርሃም ሰባት ጊዜ ተገልጾለታል፡፡ በሰባተኛው ወንድ ልጅ

www.ethiopianorthodox.org

ታገኛለች አለው፤ አንድም በሰባተኛው ወር በጥቅምት ወንድ ልጅ ታገኛለች ሲለው ነው፤

፲፭፡ ወክህደት ሳራ እንዘ ትብል ኢሰሐቁ እስመ ፈርሀት ፤

ሳራም ስለ ፈራች እኔስ አልተጠራጠርኹም ብላ አሌ አለች፤

ወይቤላ አላ ሰሐቂ ፤

ጌታም ሳራን ተጠራጥረሻል እንጂ ለምን አልተጠራጠርኹም ትያለሽ አላት ፤

፲፮፡ ወተንሥኡ ክልኤቱ ዕደው እምህየ ወተመይጡ ወሖሩ መንገለ ሰዶም ወገሞራ፤

ሁለቱ ሰዎች ከአብርሃም ቤት ወጥተው ወደ ሰዶም ወደ ገሞራ ሔዱ፤ አብነት አንጻሩ ይላል፤ ወደ ሰዶም አቅንተው ሔዱ ፤

ወሖረ አብርሃም ምስሌሆሙ ያስተፋንዎሙ ፤

አብርሃምም ይሸኛቸው ዘንድ አብሮአቸው ሔደ ፤ (ሐተታ) ሠለስቱ ዕደው ያላቸው ሥላሴ ናቸው፤ የሔዱት ሁለቱ አብ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፤ ከአብርሃም ቤት የቀረው አንዱ ወልድ ነው ፤ ከቤተ አብርሃም ሰው የሆነ እርሱ ነውና፤ ሐይመተ አብርሃም የእመቤታችን ምሳሌ፤ ሥላሴ ከአብርሃም ቤት እንደ ገቡ አብ ለአንጽዖ ፤ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ፤ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን ለመልበስ በእመቤታችን የማደራቸው ምሳሌ፤ አንድም ሠለስቱ ዕደው ያላቸው፤ ሁለቱ መላእክት ናቸው፤ አንዱ ጌታ ነው ፤ የሔዱት ሁለቱ መላእክት ፤ የመልአከ መበሥርዋ የቅዱስ ገብርኤልና የመልአከ ዑቃቢዋ የቅዱስ ሚካኤል ምሳሌ ናቸው ፤

ወተመይጠ አብርሃም ወቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

አብርሃምም ተመልሶ በእግዚአብሔር ፊት ቆመ ፤

፲፯፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ኢየኀብእ እምቍልዔየ አብርሃም ዘእገብር አነ ፤

እግዚአብሔርም የሚሠሩትን ሥራ ከጠላት ይሠውሩታል እንጂ ከወዳጅ ይሠውሩታልን? ብሎ፤ እኔ የምሠራውን ሥራ ከወዳጄ ከአብርሃም አልሠውርም አለ ፤ አንድም በአምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን የማደርገውን ሥጋዌን ከአብርሃም አልሠውርም አለ ፤

፲፰፡ እስመ ሕዝበ ዐቢየ ውብዙኃ ይከውን ፤

ደግ ወገን ብዙ ወገን አደርገዋለሁና ፤



ወይትባረኩ ቦቱ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር፤

አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይከብራሉና፤ አንድም በልጁ በክርስቶስ አሕዛብ ሁሉ ይከብራሉና፤ ኢየኀብእ ብለህ እሠር ፤

፲፱፡ እስመ አአምር ከመ ሀለዎ ለአብርሃም ያአዝዞሙ ለደቂቁ ወለቤቱ፤

አብርሃም ልጆቹንና ቤተሰቦቹን ሕገ እግዚአብሔርን እንዲያስተምራቸው አውቃለሁና ፤

ወያዕቅቦሙ ፍናዊሁ ለእግዚአብሔር፤

ሥርዓቱንም ጠብቁ ብሎ እንዲያስተምራቸው አውቃለሁና ፤

ከመ ይግበሩ ምጽዋተ ወፍትሐ፤

እውነቱን ፍርድ ይፈርዱ ዘንድ፤ ምጽዋቱንም ይመጸውቱ ዘንድ፤

ከመ ይግበር ሎሙ እግዚአብሔር ኵሎ ዘይቤሎ ለአብርሃም፤

እግዚአብሔር ለአብርሃም የነገረውን ሥርዓት ሁሉ ያደርግላቸው ዘንድ ፤

፳፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም፤ ጽራሐሙ ለሰዶም ወለገሞራ በዝኀ (በጽሐ) ወኃጢአቶሙኒ በዝኀት ጥቀ ፤

እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው፤ በሰዶምና በገሞራ ያሉ ባለጸጎች ቅሠፈን፤ ቅሠፈን እያሉ መጮሃቸው በዝቷልና፤ ኃጢአታቸውም ከልክ አልፎአልና፤ (ሐተታ) አሁን ባለጸጎች ቅሠፈን ብለው ጮኸው አይደለም፤ ድሀውን መበደል፤ ቅሠፈን ማለት ነውና ፤ አንድም የባለጸጎች ኃጢአታቸው፤ የድኆች ጩኸታቸው ፈጽሞ ከኔ ዘንድ ደርሷልና ፤

፳፩፡ ረድ እንከሰ ወእርአይ ለእመ በከመ ጽራሐሙ እንተ ትመጽእ ኀቤየ ይፈጽምዋ ወእመ አኮሰ አአምር ፤

ወደ እኔ እንደምትመጣ እንደ ጩኸታቸው መጠን ይህችን ኃጢአታቸውን ይፈጽምዋትም አይፈጽምዋትም እንደ ሆነ ፤ በመዓት ወርጄ መርምሬ አውቃለሁ አለው፤ አንድም ኃጢአታቸውን አብዝተው እንደ መሥራታቸው መጠን መከራውን መታገሥ ይቻላቸው እንደ ሆነ በመዓት ወርጄ እመረምራለሁ፤ ወእመ አኮሰ፤ ያለዚያ ግን ደካማነታቸውን አውቃለሁ አለው ፤

፳፪፡ ወሶበ ተመይጡ እምህየ እልክቱ ዕደው መጽኡ ውስተ ሰዶም፤

እሊያ ሰዎች ተመልሰው ወደ ሰዶም በመጡ ጊዜ ፤

ወአብርሃምሰ ሀሎ ዓዲ ይቀውም ቅድመ እግዚአብሔር ፤

አብርሃም ግን ገና በእግዚአብሔር ፊት ቁሞ ነበር ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፡ ወቀርበ አብርሃም ወይቤ ኢታማስን እግዚኦ ጻድቃነ ምስለ ኃጥአን ፤

አብርሃም ቀርቦ እንዲህ አለ፡ አቤቱ ጌታዬ ጻድቃንን ከኃጥአን ጋራ በአንድነት አታጥፋቸው ፡ አንድም ታጠፋቸው ዘንድ አገባብ አይደለም ፡

ወኢይኩን ጻድቅ ከመ ኃጥእ ፤

ደጉ ሰው በክፉ ሰው በደል አይጥፋ ፡

፳፬፡ ለእመ ሀለዉ ኀምሳ ጻድቃን በውስተ ሀገር ታማስኖሙኑ ፤

ምን ደግ አለና እንዲህ ትላለህ ትለኝ እንደሆነ ፤ በአምስቱ አገር አምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ይቅር አትልምን? ታጠፋለህን?

ወኢታሐዩኑ በእንተ ፶ ጻድቃን ኵሉ ብሔረ ፤

አምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ፤ ስለነሱ ብለህ ሀገሩን ሁሉ ይቅር አትልምን ?

፳፭፡ ሐሰ ለከ እግዚኦ ኢትግበር ዘንተ ነገረ ፤

አቤቱ ይህን ነገር ታደርግ ዘንድ አገባብህ አይደለም ፡

ወኢትቅትል ጻድቃነ ምስለ ኃጥአን፤

ደጋጎችን ሰዎች ከክፉዎች ሰዎች ጋራ አንድነት አታጥፋ ፡

ሐሰ ዘትኬንና ለኵሉ ምድር ኢትግበር ዘንተ ደይነ ፤

ዓለምን ሁሉ የምትገዛ አንተ አቤቱ ይህን ቍርጥ ፍርድ ታደርግ ዘንድ አገባብህ አይደለም ፡

፳፮፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ፤

እግዚአብሔርም አብርሃምን እንዲህ አለው ፡

ለእመ ረከብኩ ውስተ ሀገረ ሰዶም ኀምሳ ጻድቃነ አድኅን ኵሎ ሀገረ በእንቲአሆሙ ፤

ሰዶም በሚባል ሀገር አምሳ ደጋግ ሰዎች ካገኘሁ ስለ እነሱ ብዬ ሀገሩን ሁሉ ከጥፋት አድነዋለሁ አለው ፡ (ሐተታ) ከአምስቱ አገሮች ዐሥር ዐሥር ሰው ቢገኝ ሲል ነው ፡

፳፯፡ ወአውሥአ አብርሃም ወይቤ፤

አብርሃም መልሶ እንዲህ አለ፡

ይእዜ አኀዝኩ እትናገር ምስለ እግዚእየ እግዚአብሔር ፤

እኔ ዛሬ ከጌታዬ ከእግዚአብሔር ጋራ እነጋገር ጀመር ፡

ወአንሰ መሬት ወሐመድ አነ ፤

እኔስ ከፈጣሪ ጋራ ለመነጋገር የማልበቃ አፈር ትቢያ ነኝ ፡



፳፰፡ እመሰኬ ውኅዱ እምእልኩቱ ጻድቃን ኃምስቱ ታማስኖኑ ኵሎ ሀገረ በእንተ ኃምስቱ እለ ውኅዱ፤

ከአምሳው አምስት ሰዎች ቢጐድሉ ፡ አምስት ሰዎች ስለ ጐደሉ ሀገሩን ሁሉ ታጠፋለህን አለው ፡

ወይቤሎ እግዚአብሔር እመ ረከብኩ በህየ አርብዓ ወኃምስተ ኢየማስን በእንቲአሆሙ ፤

እግዚአብሔርም አብርሃምን በዚያ አርባ አምስት ደጋግ ሰዎች ካገኘሁ፤ ስለነርሱ ሀገሩን ሁሉ አላጠፋም አለው ፡ (ሐተታ) አሁን ከአምስቱ አገሮች ዘጠኝ ዘጠኝ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ይቅር እላለሁ ሲል ነው ፡

፳፱፡ ወይቤሎ አብርሃም ለእመኬ ተረክቡ በህየ አርብዓ፤

አብርሃምም በዚያ አርባ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ይቅር አትልምን? አለው፡

ወይቤሎ እግዚአብሔር ኢየማስን በእንተ አርብዓ ፤

እግዚአብሔርም አርባ ደጋግ ሰዎች ካገኘሁ አላጠፋም አለው፡ (ሐተታ) አሁን ከአምስቱ አገሮች ስምንት ስምንት ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ይቅር እላለሁ ሲል ነው ፡

፴፡ ወደገመ ዓዲ ብሂሎቶ አብርሃም ወይቤሎ፤

አብርሃምም ዳግመኛ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡

እመሰኬ በህየ ተረክቡ ሠላሳ፤

በዚያ ሠላሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙሳ ይቅር አትልምን አለው፡

ወይቤሎ ኢየማስን በእንተ ሠላሳ፤

እግዚአብሔርም ሠላሳ ደጋግ ሰዎች ከተገኙስ ይቅር እላለሁ አለው፤ (ሐተታ) ከአምስቱ አገሮች ስድስት ስድስት ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ይቅር እላለሁ ሲል ነው ፡

፴፩፡ ወይቤሎ አብርሃም እስመ ተበቋሕኩ እትናገር ምስለ እግዚእየ እግዚአብሔር ለእመኬ ተረክቡ በህየ ዕሥራ ፤

አብርሃምም ካንተ ከጌታዬ ጋራ ለመነጋገር ፈቅደህልኛልና በዚያ ሀያ ደጋግ ሰዎች ቢገኙሳ ይቅር አትልምን አለው ፡

ወይቤሎ ኢየማስን በእንተ ዕሥራ፤

ሀያ ደጋግ ሰዎች ከተገኙስ አላጠፋም አለው፤ (ሐተታ) አሁን አራት አራት ሲል ነው ፡

፴፪፡ ወይቤሎ አብርሃም አብሐኒ እግዚኦ እንብብ ዓዲ ፤

አብርሃምም አቤቱ ጌታዬ ዳግመኛ እናገር ዘንድ ፍቀድልኝ አለው፡ (ሐተታ) ምነው እስካሁን ሲናገር መጥቶ የለምን ቢሉ

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ አብዝቶበታልና እንዳይ ሰለቸኝ ብሎ ፡

ወለእመኬ ተረክቡ በህየ ዐሠርቱ ፤

በዚያ ዐሥር ደጋግ ሰዎች ቢገኙሳ ይቅር አትልምን? አለው፡

ወይቤሎ ኢየማስን በእንተ ዐሠርቱ፤

ዐሥር ደጋግ ሰዎች ከተገኙ አላጠፋም አለው፡ (ሐተታ) አሁን ሁለት ሁለት ሲል ነው ፡ ከዚህም እመሰኬ ተረክቡ ኃምስቱ ያለበት ነው፡ አብርሃም ጌታን አምስት ደጋግ ሰዎች ቢገኙሳ ይቅር አትልምን ? አለው ፡ ጌታም አምስት ደጋግ ሰዎች ከተገኙስ ይቅር አላለሁ አለው፡

ወሰበ አኅለቀ ተናግሮቶ ለአብርሃም ኀለፈ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋራ ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ ተሠወረው (ረቀቀው)፡

ወአብርሃምኒ ገብአ ኀበ ምንባሪሁ፤

አብርሃምም ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ፤ (ሐተታ) በሰዶም ሎጥ ከነልጆቹ ደጋግ ሰዎች ነበሩና በእንተ ሠለስቱ ይለኛል ብሎ ከዚህ በኋላ ተሠውሮታል።

## ምዕራፍ ፲ወ፱

፩፡ ወበጽሑ ክልኤቱ ፪ኤቱ መላእክት ውስተ ሰዶም ፍና ሠርክ ፤

እኒህ ሁለቱ መላእክት ሰዶም ከሚባል ሀገር ማታ ጊዜ ደረሱ፤

ወሎጥኒ ሀሎ ይነብር ውስተ አንቀጸ ሀገረ ሰዶም ፤

ሎጥም ሰዶም በሚባለው ሀገር ካደባባይ ተቀምጦ ነበር፡ (ሐተታ) መጻተኛ ይኖር በሀገር ፤ ይሰጡት ከድንበር እንዲሉ፤ እንዳላስጠጉት ለማጠየቅ ፤ ይነብር ውስተ አንቀጽ አለ ፡ አንድም ከግብራቸው እንዳልተቀላቀለ ለማጠየቅ ነው ፡

ወሰበ ርእዮሙ ተንሥአ ወተቀበሎሙ ወሰገደ ሎሙ ፤

ባያቸውም ጊዜ ተነሥቶ እጅ ነሥቶ ተቀበላቸው ፤ እጅ ነሣቸው ፡

፪፡ ወይቤሎሙ አጋእዝትየ ትኑሡ ኀበ ቤተ ገብርክሙ ወኅድሩ ወተሐጸቡ እገሪክሙ ፤

ሎጥ ሁለቱን መላእክት እንዲህ አላቸው፡ ጌቶቼ ከኔ ከባሪያችሁ ቤት ገብታችሁ እግራችሁን ታጥባችሁ እደሩ አላቸው፡

ወትገይሡ በነግህ ወተሐውሩ ፍኖተክሙ ፤

ከኔ ቤት አድራችሁ ማለዳ ትሔዳላችሁ ፡

ወይቤልዎ አልቦ አላ ነኀድር ውስተ መርኅብ ፤

ከዚህ ከሚዳው እናድራለን እንጂ ከሰው ቤት አንገባም አሉት፡ (ሐተታ) የሃይማኖቱን



ጽናት የልቡን ትጋት ለማየት እንዲህ አሉት ፡

፫፡ ወሰገደ ሎሙ በገጹ ወአገበሮሙ፤

ከእግራቸው ላይ ወድቆ ግድ ወደቤት ግቡልኝ አላቸው ፡ (ሐተታ) አብርሃም እንግዳ መቀበልን አስለምዶት ነበርና ፡

ወግኅሡ ኀቤሁ ወቦኡ ውስተ ቤቱ፤

እሺ ብለው ወደ ቤቱ ገቡ ፡

ወገብረ ሎሙ ጸፍንተ ናዕተ ፤

ከገቡለትም በኋላ አምባሻ አስጋገረላቸው ፡

ወበልዑ ወሰትዩ ፤

እነሱም በሉ ጠጡ ፡

፬፡ ወእንበለ ይስክቡ ሰብአ ለይእቲ ሀገር ፤

ገና ሳይተኙ የዚያች ሀገር ሰዎች ተሰብስበው መጥተው፡

አገትዋ ለቤቶሙ ኵሉ ሰብአሙ ኀበረ ንዑሰሙ ወዐቢዮሙ ፤

ታናሹም ታላቁም ሁሉ በአንድነት ሂደው የሎጥን ቤት ከበቡት ፡ (ሐተታ) ብዙ ኃጢአት የሚሠራ በጉልማስነት ወራት ነበረ ፡ ከዚህ ግን ሽማግሎችም ኃጢአት ሠሩ ለማለት ንዑሰሙ ወዓቢዮሙ አለ ፡

፭፡ ወጸውዕዎ ለሎጥ ወይቤልዎ ፤

ሎጥንም ጠርተው እንዲህ አሉት ፡

አይቴ እሙንቱ ዕደው እለ ቦኡ ኀቤከ ሌሊተ ፤

በሌሊት ከአንተ ዘንድ የገቡት ሰዎች ወዴት ናቸው ፡

ወአውፅአሙ አፍአ ከመ ንሑሮሙ፤

እንደርስባቸው ዘንድ ወደዚህ አውጣቸው አሉት ፡ (ሐተታ) ኢትሑርን ይዘው ከመ ንሑሮሙ አሉ ፡

፮፡ ወወፅአ ሎጥ ኀቤሆሙ ኀበ ኆኅት ቅድሚሆሙ ወዐፀወ ኆኅተ ድኅሬሁ፤

ሎጥም ደጁን ወደ ኋላው ዘግቶ ሰብአ ሰዶም ወዳሉበት ወደ ደጅ ወጣ፤ (ሐተታ) እንደ ቆሪጣ (ቆሪጣ የቦታ ስም) ቤት በውስጥም በእጻሪያም የሚዘጋ ነው፡

፯፡ ወይቤሎሙ ሐሰ ለክሙ አኃውየ ኢታሕስሙ ላዕለ እሉ ፤

ሎጥም ወንድሞቼ በእነዚህ ሰዎች ላይ የማይገባ ክፉ ሥራ አትሥሩ አላቸው ፡

፰፡ ወናሁ ብየ ክልኤቲ አዋልድ ዘኢያእመራ ብእሴ ፤

ፈቃደ ሥጋ ቢጸናባችሁ ስንኳ፤ ከወንድ ያልደረሱ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉኝ ፡

ወአወፅኦን ለክሙ ወግበርዎን ዘከመ ይኤድመክሙ ፤

አውጥቼ ለእናንተ ልስጣችሁ፤ እናንተ እንደወደዳችሁ አድርጉዋቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወባሕቱ ኀዕለ እሉ ዕደው ኢትግበሩ ምንተኒ እመ፥ እስ በአ ታሕተ ጽላሎተ ቤትየ ፤

ከቤቴ እናድራለን ብለው በገቡ ሰዎች ላይ የማይገባ ሥራ አትሥሩ እንጂ ልጆቼን አውጥቼ እሰጣችኋለሁ አላቸው ፡

፱፡ ወይቤልዎ ሑር ከሀከ ፤

ሎጥን ወግድ ወዲያ አሉት ፡

ቦእከ ከመ ትኅድር ወኢኮ ከመ ትኩንን ፤

በሀገራችን እኛን መስለህ ልትኖር መጣህ እንጂ፣ እኛን ልትሠራ ልትቀጣ መጥተሃልን ? ወግድ ወዲያ ፡

ወይእዜኒ ኪያከ ንግብር ፈድፋደ እም ኔሆሙ ፤

ያለዚያ ግን ከነዚያ ይልቅ በአንተ እንጫወትብሃለን አሉት ፡

ወተኀየልዎ ሎቱ ፈድፋደ ወቀርቡ ከመ ይስብርዋ ለኆኅት ፤

እርሱን ተጋፍተው አልፈው ማንቃውን ለመስበር ወደ ደጃፉ ቀረቡ ፡

፲፡ ወአውዕኡ እደዊሆሙ እልክቱ ዕደው ወሰሐብዎ ለሎጥ ወአብእዎ ኀቤሆሙ ውስተ ቤቱ ፤

እነዚህም ሁለቱ መላእክት እጃቸውን አውጥተው ሎጥን ስበው ወደ ቤቱ አገቡት ፡

ወዐፀዉ ኆኅተ ፤

ማንቃውንም በውስጥ ዘጉት፡

፲፩፡ ወለእልክቱሰ ዕደው እለ ሀለዉ ቅድመ ኆኅቱ ለውእቱ ቤት ፤

በቤቱ ደጃፍ ያሉትን እነዚያን ሰዎች ግን ፡

አያርዎሙ አዕይንቲሆሙ ለንዑሶሙ ወለዐቢዮሙ ፤

ትንሹንም ትልቁንም ሲያዩ እንዳያዩ አደረግዋቸው ፡

ወስርሑ እንዘ የኃሥሥዎ ለውእቱ ኆኅት ወኀጥእዎ ፤

ደጁ ጠፍቶዋቸው በመፈለግ እጅግ ደከሙ ፡

፲፪፡ ወይቤልዎ ለሎጥ እልክቱ መላእክት ቦኑ ዘብከ በዝየ ታእኃ አው ታሕማ ፤

እሊያም መላእክት ሎጥን እንዲህ አሉት ፡ በዚህ ሀገር ወንድም ወይም አማች የለህምን፡

ወእመኒ ደቂቅ ወአዋልድ ፤

ወንዶችና ሴቶች ልጆች የሉህምን ?

ወእመቦ ዘብከ ዐርክ ውስተዝ ሀገር አውፅኦሙ እምዛቲ ሀገር ፤

በዚህ ሀገር ወዳጅ ዘመድ ያለህ እንደ ሆነ ከዚህች ሀገር ይዘሃቸው ውጣ ፡

፲፫፡ እስመ ናማስና ንሕነ ለዛቲ መካን ፤

ይህችን ሀገር እናጠፋታለንና፡



እስመ ዐብየ ገዐሮሙ በቅድመ እግዚአብሔር ወፈነወነ ከመ ንደምስሳ፤

የባለጸጎች ኃጢአታቸው የድሆች ልቅሶአቸው በእግዚአብሔር ፊት ስለ በዛ እናጠፋት ዘንድ ልኮናልና ፡

፲፬፡ ወወፅአ ሎጥ ኀበ ታሕማሁ እለ ይነሥእዎን ለክልኤሆን አዋልዲሁ ወይቤሎሙ ተንሥኡ ወፃኡ እምዝንቱ ሀገር እስመ ይደመስሳ እግዚአብሔር ፤

ሎጥም ሁለቱን ልጆቹን ሊያገቡ ወደ ተጫጩ ወደ አምቻዎቹ ሂዶ እግዚአብሔር ይህን ሀገር ሊያጠፋው ነውና ተነሡ እንውጣ ብሎ ነገራቸው ፡

ወመሰሎሙ ለታሕማሁ ከመ ዘበሥላቅ ይቤሎሙ ፤

አማቾቹም ሎጥ ዋዛ ፈዛዛ ነገርን የነገራቸው መስሏቸው ነበር ፡

፲፭፡ ወሶበ ኮነ አፈ ጽባሕ አኃዙ ያጉጕዕዎ መላእክት ለሎጥ ፤

በነጋ ጊዜ መላእክት ሎጥን ያስቸኩሉት ጀመር ፡

ወይቤልዎ ተንሥእ ወንሣእ ክልኤሆን አዋልዲከ ወብእሲተከ ፤

ልጆችህንና ሚስትህን ይዘህ ተነሣ አሉት ፡

ወፃእ ከመ አንተኒ ኢትሙት በኃጢአቶሙ ለሰብአ ይእቲ ሀገር ፤

በዚህች ሀገር ሰዎች ኃጢአት አንተም አብረህ እንዳትጠፋ ፈጥነህ ውጣ አሉት ፡

፲፮፡ ወአኀዝዎ እዴሁ እልክቱ ዕደው ወእደ ብእሲቱ ፤

ቤት ልቀቁኝ ልቀቁኝ አትል ምና ዳ ቢልባቸው አንዱ መልአክ በአንዱ እጁ ሎጥን ፡ በአንዱ እጁ የሚስቱን እጅ ይዞ ፡

ወክልኤሆን አዋልዲሁ ፤

አንዱም መልአክ የሁለቱን ልጆቹን እጃቸውን ይዞ አወጧቸው፡

እስመ ምሕኮሙ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ራርቶላቸዋልና፡

፲፯፡ ወይቤልዎ ሶበ አውፅእዎ አፍአ አድኅን ነፍሰከ ወኢትነጽር ድኅሬከ፤

ወደ ውጭም ከአወጡት በኋላ ሰውነትህን ከጥፋት አድን ዞሬ ህም ወደ ኋላ አትይ አሉት ፡ ለጊዜው ከጥፋት እንዲድን ነው፡ ፍጻሜው ግን ከመነናችሁ በኋላ ወደ ዓለም አትመለሱ ሲል ነው ፡

ወኢትቁም ውስተ አድያሚሃ ወውስተ ደብራ ለዛቲ ሀገር ፤

በዚህች ሀገር በዳርቻዋም በተራራዋም አትቁም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ኢትርከብከ ለከኒ እኪት ፤

እነዚያን ያገኘ ጥፋት አንተንም እንዳያገኝህ ፤

፲፰፡ ወይቤሎሙ ሎጥ ብቍዑኒ አጋእዝትየ እመ ረከብኩ ምሕረተ በቅድሜክሙ ፤

ሎጥም እንዲህ አላቸው፤ በፊታችሁ ባለምዋልነትን ካገኘሁስ በጅ በሉኝ ፤

፲፱፡ ወአዕበይኩ ለምሕረትከ ምስሌየ ከመ ታሕይዋ ለነፍስየ ፤

ከሁለቱ አንዱን የቀረበውን እንዲህ ይለዋል፤ ሰውነቴን ታድናት ዘንድ ይቅርታህን ለኔ አብዛልኝ ፤

አንሰ ኢይክል አድኅኖ ርእስየ በውስተ ደብር ፤

እኔ ወደ ሩቅ ተራራ ሸሽቼ ራሴን ማዳን አይቻለኝም (ትች)፤

ከመ ኢትርከበኒ እኪት ወኢይሙት፤

በዚህ ምክንያት ይህች መከራ አግኝታኝ እንዳልሞት ፤

፳፡ ወናሁ ዛቲ ሀገር ቅርብት ይእቲ፤

እነሆ ይህች ሀገር ቅርብ ናትና፤

ወንስቲት ፤

መንገድዋ ጥቂት ነውና ፤

ሩጽ ህየ ወአድኅን ርእስየ ፤

ወደዚያ ፈጥኜ ሂጄ ራሴን አድንባት ዘንድ ይህችን በፊቴ ያለች ሀገር አታጥፋብኝ ፤

ወኢኮነት ንስቲተ እምከመ ድኅነት ነፍስየ፤

ሰውነቴም በዚህች ሀገር ከጥፋት ከዳነች ያደረግህልኝ ቸርነት ጥቂት አይደለችም ፤

፳፩፡ ወይቤሎ ናሁ አድኃንክዋ ለገጽከ ፤

እነሆ ላንተ ብዬ በፊትህ ያለችውን ሀገር ከጥፋት አድናታለሁ፤

ወበከመ ትቤ ኢይገፍትዓ ለዛቲ ሀገር እንተ በእንቲአሃ ነበብከኒ ፤

ወደዚያች ሀገር ሔጄ ሰውነቴን ላድን አታጥፋብኝ ብለህ እንደለመንኸኝ አላጠፋትም ፤

፳፪፡ አፍጥን እንከ ወአድኅን ርእሰከ በህየ ፤

እንኪያስ ፈጥነህ ከዚያች ሀገር ተሻግረህ ራስህን አድን ፤

በእንተ ዝንቱ ተሰምየት ይእቲ ሀገር ሴጎር ፤

ስለዚህ ነገር ያች ሀገር ሴጎር ተባለች ፤ (ሐተታ) ሴጎር ማለት ምስጋረ እግር ማለት ነው ፤ ሎጥ ፈጥኖ ገብቶ ስለ ዳነባት ፤

፳፫፡ ወሠረቀ ፀሐይ በዲበ ምድር ወሎጥኒ ቦአ ውስተ ሴጎር ፤

ፀሐይም በምድር ላይ ወጣ ፤ ሎጥም ወደ ሴጎር ገባ ፤



፳፬፡ ወአዝነመ እግዚአብሔር ላዕለ ሰዶም ወገሞራ እሳተ ወተየ እምኀበ እግዚአብሔር እምሰማይ ፤

እግዚአብሔርም ከእሱ ዘንድ ከሰማይ በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳትና ድኝ አዘነመ፤ (ሐተታ) እግዚአብሔር እምኀበ እግዚአብሔር ማለቱ አንድነቱን ሦስትነቱን ሲያይ ነው ፤

፳፭፡ ወገፍትዖን ለእማንቱ አህጉር ወለአድያሚሆን ምስለ ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴቶን ፤

ሰዶምንና ገሞራን አውራጃቻቸውንም ሁሉ በነርሱ ከሚኖሩባቸው ሰዎች ጋራ አጠፋቸው ፤

ወለኵሉ ዘርአ ምድሮሙ ፤

አዝመራቸውን ሁሉ በእሳት አጠፋ ፤

፳፮፡ ወነጸረት ብእሲተ ሎጥ ድኅሬሃ ወኮነት ሐውልተ ፄው ፤

የሎጥም ሚስት ወደ ሀገሬ ሰዶም ብላ ዙራ ብታይ የጨው ደንጊያ ሆነች ፤ (ሐተታ) ስለ ምን የጨው ደንጊያ አደረጋት ቢሉ፤ ጨው አይረባም ጉልቻ ቢያደርጉት ይፈነዳል፤ ከተክል መካከል ቢጥሉት ተክል ያደርቃል፤ እርስዋም እንደዚሁ ሁሉ አትረባም ሲል፤ የጨው ደንጊያ አደረጋት፤ አንድም ኃጢአት ጨው ጨው ይላት ነበርና ፤ አንድም ጨው ልበ ደር ብላ ሔዳ አዕናቍ የመሰሉ ሰዎች መጥተውላችኋል መጥታችሁ ፈቃዳችሁን ፈጽሙ ብላ ተናግራ ነበርና፤ ስለዚህ የጨው ደንጊያ አደርጓታል፤ ይህችንም የሎጥን ሚስት ጌታ በወንጌል የመናንያን ምሳሌ አድርጓታል፤ መላእክት ዙረሽ አትዩ ቢሏት ዙራ አይታ የጨው ደንጊያ እንደሆነች እናንተም ከመነናችሁ በኋላ ወደ ዓለም ብትመለሱ ትጐዳላችሁ ሲል ነው ፤

፳፯፡ ወጌሠ አብርሃም ውስተ ዝኩ መካን ኀበ ቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ፤

አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ወደነበረበት ቦታ ተመልሶ፤

፳፰፡ ወነጸረ ላዕለ ገጸ ሰዶም ወገሞራ ወላዕለ ኵሉ አድያሚሆን ፤

ወደ ሰዶምና ወደ ገሞራ በዙሪያቸው ወዳሉ ሀገሮችም ሁሉ ተመለከተ ፤

ወሶበ ርእየ ናሁ የዐርግ ነድ እምድር ከመ ጢሰ እቶን ፤

በተመለከተም ጊዜ እነሆ የምድጃ ጢስ በዝቶ እንዲወጣ እሳቱ እየተጕረደ ከምድር ሲወጣ አየ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፡ ወኮነ ሶበ ደምሰሶን እግዚአብሔር ለእማንቱ አህጉር ወለኵሉ አድያሚሆን አለ ውስቴቶን የኀድር ሎጥ፤

እግዚአብሔርም ሰዶምንና ገሞራን ሎጥ የሚኖርባቸውንም አውራጃዎች ሁሉ ባጠፋቸው ጊዜ እንዲህ ሆነ ፡

ተዘከሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም፤

ኮነ ያለውን ተዘከሮ ብሎ አመጣው፤ አብርሃምን በረድኤት አሰበው ፡

ወአውፅኦ ለሎጥ እማዕከለ ሙስና ፤

ሎጥን በእሳት ተቃጥሎ ከመሞት አዳነው ፡

፴፡ ወዐርገ ሎጥ እምሴጎር ወኀደረ ውስተ ደብር ፤

ሎጥም ከሴጎር ወጥቶ በተራራ ላይ ተቀመጠ ፡

ወክልኤቲ አዋልዲሁ ምስሌሁ፤

ሁለቱ ሴቶች ልጆችም አብረው ነበሩ ፡

እስመ ፈርሀ ነቢረ ውስተ ሴጎር ፤

በሴጎር መካከል መኖርን ፈርቷልና ፡

ወነበረ ውስተ በዓት ውእቱ ወክልኤሆን አዋልዲሁ ፤

ሁለቱን ልጆቹን ይዞ ከተራራው ጥግ ባለ ዋሻ ተቀመጠ፤

፴፩፡ ወትቤላ እንተ ትልህቅ ለእንተ ትንዕስ፤

ትልቂቱ ትንሺቱን እንዲህ አለቻት ፡

ናሁ አቡነ አረጋዊ ውእቱ ፤

እነሆ አባታችን አርጅቷል ፡

ወአልቦ ሰብእ ዘይበውእ ኀቤነ ፤

እኛን የሚገባን ባል አናገኝም፡

ከመ ይትወለድ ውስተ ኵሉ ምድር፤

በምድር ሁሉ መልቶ የሚኖር ልጅ ይወለድ ዘንድ ፡

፴፪፡ ንዒ ናስትዮ ለአቡነ ወይነ፤

አሁንም አባታችንን ወይን አጠጥተን አስክረን ፡

ወንስክብ ምስሌሁ ወናቅም ዘርአ እምአቡነ ፤

ከአባታችን ጋራ ተገናኝተን በአባታችን እግር የሚቆም ዘር እንተካ አለቻት ፡

፴፫፡ ወአስተያሁ ወይነ ለአቡሆን ፤

አባታቸውን ወይን አጠጥተው አሰከሩት ፡

ወበይእቲ ሌሊት እንተ ትልህቅ ቦአት ወሰከበት ምስለ አቡሃ ፤

በዚያች ሌሊት ትልቂቱ ገብታ ከአባትዋ ተገናኘች ፡

ወኢያእመረ በሰኪቦታ ወበተንሥኦታ ፤

አባትዋ ግን ከእርሱ ጋራ ተገናኝታ ተነሥታ ስትሔድ አላወቀም ነበር ፡ (ሐተታ) አካል ከአካል ሲከፈልስ ሳያውቅ አይቀርም ብሎ የርሱ ልጅ መሆንዋን አላወቀም ነበር ፡



፴፬፤ ወእምዝ ትቤላ እንተ ትልህቅ ለእንተ ትንዕስ ፤

ከዚህ በኋላ ትልቂቱ ትንሺቱን እንዲህ አለቻት ፡

ናሁ ሰከብኩ ትማልም ምስለ አቡነ፤

እነሆ ትናንትና እኔ ከአባታችን ጋራ ተገናኘሁ ፡

ወካዕበ ናስትዮ ወይነ ፤

ዳግመኛ ወይን አጠጥተን እናስክረውና ፡

ስከቢ ምስሌሁ በዛቲ ሌሊት ፤

አንቺም በዚህች ሌሊት ከእርሱ ጋራ ተገናኚ ፡

ወናቅም ዘርአ እምአቡነ ፤

የሚተካ ዘር ከአባታችን እንውለድ አለቻት ፡

፴፭፡ ወአስተያሁ ወይነ በይእቲ ሌሊት ፤

ዳግመኛም በዚያች ሌሊት ወይን አጠጥተው አባታቸውን አሰከሩት ፡

ወቦአት እንተ ትንዕስ ወሰከበት ምስለ አቡሃ ፤

ታናሺቱም ገብታ ከአባትዋ ጋራ ተገናኘች ፡

ወኢያእመረ በሰኪቦታ ወበተንሥኦታ ፤

እርስዋም ተገናኝታ ተነሥታ ስትሔድ አላወቀም ፡ (ሐተታ) ዘርስ ከአካል ሲከፈል ሳያውቅ አይቀርም ብሎ የእርሱ ልጅ መሆንዋን አላወቀም ፡

፴፮፤ ወፀንሳ ክልኤሆን አዋልዲሁ ለሎጥ እምአቡሆን ፤

የሎጥም ሁለቱ ልጆቹ ከአባታቸው ጸነሱ ፡

፴፯፤ ወወለደት እንተ ትልህቅ ወልደ ፤

ትልቂቱ ወንድ ልጅ ወለደች፡

ወሰመየቶ ስሞ ሞአብ ፤

ስሙንም ሳትፈራ ሳታፍር ሞአብ አለችው ፡

ዘእምአቡየ ብሂል ፤

ከአባቴ የወለድሁት ማለት ነው ፡

ወውእቱ አቡሆሙ ለሞአባውያን ፤

ይኸውም የሞአባውያን አባታቸው ነው ፡

፴፰፡ ወወለደት ወልደ እንተ ትንዕሲ ፤

ታናሺቱም ወንድ ልጅ ወለደች፡

ወሰመየቶ ስሞ አሞን ፤

ስሙንም አሞን አለቺው ፡

እንዘ ትብል ወልደ ሕዝብየ ፤

ከዘመዴ የወለድሁት ነው ስትል፤ (ሐተታ) ይህች ትሻል ትልቂቱ ገልጻ ከአባቴ ወለድሁ ብላ ነበርና ፡

ወውእቱ አቡሆሙ ለአሞናውያን እስከ ዮም ፤

ይኸውም እስከ ዛሬ የአሞናውያን አባት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፳

## ጉባኤ

፩፡ ወተንሥአ አብርሃም እምህየ ወሖረ መንገለ ምድረ ዐዜብ ፤

አብርሃም ከዚያ ተነሥቶ በም ሥራቅ አጠገብ ወዳለው ሀገር ሔደ ፤

ወኃደረ ማዕከለ ቃዴስ ወማዕከለ ሱሬ ፤

በቃዴስና በሱሬ መካከል ባለው ቦታ አደረ ፤

ወነበረ ውስተ ጌራራ ፤

ከዚያም ተነሥቶ በጌራራ ተቀ መጠ፤

፪፡ ወይቤሎሙ አብርሃም በእንተ ሳራ ብእሲቱ እኅትየ ይእቲ ፤

አብርሃም የጌራራ ሰዎች በሳራ ምክንያት የሚገድሉት ቢሆን እኅቴ ናት አለ ፤

ወለአከ አቤሜሌክ ንጉሠ ጌራራ ወነሥአ ለሳራ ፤

የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክም ሳራን ልኮ አስወሰዳት ፤

፫፡ ወቦአ እግዚአብሔር ኀበ አቤ ሜሌክ በይእቲ ሌሊት እንዘ ይነ ውም ፤

አቤሜሌክ በዚያች ሌሊት ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር በመዓት መጣበት ፤

ወይቤሎ በሕልም ናሁ ትመውት አንተ በእንተ ዛቲ ብእሲት እንተ ነሣእካ ፤

ቀምተህ በወሰድኻት በሳራ ምክንያት እነሆ ትቀሠፋለህ አለው ፤

እስመ ብእሲተ ብእሲ ይእቲ ፤

የጉልማሳ ሚስት ናትና ፤

፬፡ ወአቤሜሌክሰ ኢለከፋ ፤

አቤሜሌክ ግን ሳራን አልነካ ትም ፤

ወይቤ አቤሜሌክ ሕዝበኑ ዘኢያእ መረ በጽድቅ ትቀትል ፤

አቤሜሌክም ባላወቀ ሰው ትፈ ርዳለህን ? ያላወቀ ወገንን በእ ውነት ታጠፋለህን ባላውቅ ነው እንጂ አለ ፤

፭፡ ለሊሁ ይቤለኒ እኅትየ ይእቲ፤

ብጠይቀው እርሱ እኅቴ ናት አለኝ ፤

ወይእቲ ትቤለኒ እኁቱ አነ ፤

እርስዋንም ብጠይቃት እኁቱ ነኝ አለችኝ ፤

ወበንጹሕ ልብ ወበጽድቀ እደውየ ገበርክዎ ለዝንቱ ፤

በልቤ ተንኰል ፤ በቃሌ መበ ደል፤ በእጄ መግደል ሳይኖር ይህን ነገር አደረግሁት ፤



፮፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር በሕልም አነኒ አእመርኩ ከመ በንጹሕ ልብ ገበርከ ለዝንቱ ፤

እግዚአብሔርም አቤሜሌክን በሕልም እንዲህ አለው፡ እኔም በቃልህ መበደል፤ በእጅህ መግ ደል እንደሌለ አይቼ ፤

ወምሕኩከ ከመ ኢተአብስ ፤

የማይገባ ሥራ እንዳትሠራ ራራ ሁልህ ፤

ወበእንተ ዝንቱ ኢኅደጉከ ትቅረባ፤

ስለዚህ ነገር ከእርስዋ እንዳት ደርስ አደረግሁህ ፤

፯፡ ወይእዜኒ አግብእ ለብእሲ ብእሲቶ ፤

አሁንም ለአብርሃም ሚስቱን መልስለት ፤

እስመ ነቢይ ውእቱ ፤

ደግ ሰው ነውና ይጼሊ ማንሻ፡ አንድም ደግ ሰው ነውና ፤

ወይጼሊ በእንቲአከ ወተሐዩ ፤

ስለአንተ ይለምንልሃል ትድና ለህ፤ (ሐተታ) አቤሜሌክ አባለ ዘሩ መጩጊያ (ትራስ) ያህል አብጦበታል ፤ ያገሩም ሴቶች አፈ ማኅፀናቸው ተዘግቶ የማ ይወልዱ ሁነዋል ፤

ወእመሰ ኢያግባእካ አእምር ከመ ሞተ ትመውት አንተ ወኵሉ ዘዚ አከ ፤

ካልመለስሃት ግን አንተ እንድ ትቀሠፍ ፤ ቤተሰቦችህም ሁሉ እንዲቀሠፉ እወቅ ፤

፰፡ ወተንሥአ አቤሜሌክ በጽባሕ፤

አቤሜሌክም ሲነጋ ተነሥቶ ፤

ወጸውዐ ኵሎ ደቆ ፤

ብላቴኖቹን ሁሉ ጠርቶ ፤

ወነገሮሙ ዘንተ ነገረ ፤

ይህን ጌታ የነገረውን ሁሉ ነገ ራቸው ፤

ወፈርህዎ ለእግዚአብሔር ኵሉ ሰብእ ቤቱ ጥቀ ፤

በነገራቸውም ጊዜ ቤተሰቦቹ ሁሉ እግዚአብሔርን ፈጽመው ፈሩት ፤

፱፡ ወጸውዖ አቤሜሌክ ለአብርሃም፤

አቤሜሌክም አብርሃምን ጠርቶ፤

ወይቤሎ ምንትኑዝ ዘገበርከ ላዕሌየ ወላዕለ መንግሥትየ ኃጢአተ ዐቢየ ዘኢገብሮ መኑሂ ፤

ማንም ማን ያላደረገውን ይህን ሥራ፤ በእኔም በመንግሥቴም የሠራህ ስለምንድር ነው አለው፤ (ሐተታ) ሚስቱን እኅቴ ናት ያለ ከእርሱ በቀር የለምና ዘኢገብሮ መኑሂ አለ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም ምንተ ርእየከ ገበርከሁ ለዝንቱ ነገር፤

አቤሜሌክም አብርሃምን እንዲህ ያለውን ሥራ የሠራህ ምን አይ ተህ ምን ሰምተህ ነው ? አለው ፡

፲፩፡ ወይቤሎ አብርሃም እስመ እቤ ዮጊ አልቦ ፍርሃተ እግዚአብሔር ውስተዝ መካን ፤

አብርሃምም አቤሜሌክን እንዲህ አለው፡ ምናልባት በዚህ ሀገር እግዚአብሔርን የሚፈራ የለምና፡

ወይቀትሉኒ በእንተ ብእሲትየ ፤

በሚስቴ ምክንያት ይገድሉኛል ብዬ ነው አለው ፡

፲፪፡ ወካዕበ አማን እኅትየ ይእቲ እመንገለ አቡየ ወአኮ እመንገለ እምየ ፤

ዳግመኛም በእናቴ ወገን ያይ ደለች በአባቴ ወገን በእውነት እኅቴ ናት ፡

ወኮነተኒ ብእሲተ ፤

ሚስት ሆነችኝ እንጂ ፡

፲፫፡ ወአመ አውፅአኒ እግዚአብሔር እምቤተ አቡየ፤

እግዚአብሔር ከአባቴ ወገኖች ለይቶ ባወጣኝ ጊዜ ፡

እቤላ ዘንተ ጽድቀ ግበሪ ሊተ ውስተ ኵሉ መካን ኀበ ቦእነ ፤

በሔድንበት ሀገር ሁሉ ለእኔ የምታደርጊው ውለታ ፡

በሊ እኁየ ውእቱ ፤

ግበሪ ያለውን በሊ እኁየ ውእቱ ብሎ አመጣው፡ ለጠየቀሽ ሰው ሁሉ ወንድሜ ነው ማለትሽ ነው አልኋት ፡

፲፬፡ ወነሥአ አቤሜሌክ ዐሠርተ ምእተ ጠፋልሐ ብሩር ፤

አቤሜሌክም ሺህ ምዝምዝ ብር አንሥቶ ፡

አግብርተ ወአእማተ አባግዐ ወአልሕምተ ፤

ሴት ባርያ፣ ወንድ ባርያ፣ በጉን፣ ላሙን ጨምሮ፡

ወሀቦ ለአብርሃም ፤

ለአብርሃም ሰጠው ፡

ወአግብአ ሎቱ ብእሲቶ ሳራሃ፤

ሚስቱን ሳራንም መለሰለት ፡

፲፭፡ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም፤

አቤሜሌክ አብርሃምን እንዲህ አለው፡

ናሁ ምድርየ ቅድሜከ ኀበ ፈቀድከ ንበር ፤

በፊትህ የምታየው ሀገር ሁሉ እነሆ የኔ ነው፡ ከወደድኸው ተቀመጥ፡

፲፮፡ ወይቤላ ለሳራሂ፤

ሳራንም እንዲህ አላት ፡



ናሁ ወሀብክዎ ለእኁኪ ዐሠርተ ምእተ ጠፋልሐ ብሩር ፤

እነሆ ለወንድምሽ ለአብርሃም ሺህ ምዝምዝ ብር ሰጠሁት፡

ወዝንቱኒ ይኩንኪ ለኪ ለክብረ ገጽኪ፤

ይኸውም አንድ ጊዜ ፊትሽን ገልጬ ስላየሁሽ ካሳ ይሁንሽ፡ አንድም ለሥልሶ ለውግሮ ይሁንሽ ፡

ወበኵሉ ጽድቀ ተናገሪ ፤

በዚህ ሁሉ እውነት ነገርን ተናገሪት፡

፲፯፡ ወጸለየ አብርሃም ኀበ እግዚአብሔር፤

አብርሃም አቤሜሌክን አድን ልኝ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ ፡

ወፈወሶ እግዚአብሔር ለአቤሜሌክ ወለብእሲቱ ወለአዋልዲሁ ፤

እግዚአብሔርም አቤሜሌክን፣ ሚስቱን ፣ ልጆቹንም አዳና ቸው ፡

ወለአእማቲሁ እለ ውስተ ቤቱ ወወለዳ ፤

በቤቱ ያሉ ቤተሰቦቹን ሁሉ አዳናቸው፣ ልጅም ወለዱ ፡

፲፰፡ እስመ ዐጺወ ዐፀዋ እግዚአብሔር ለማኅፀን እምአፍአ በእንተ ሳራ ብእሲተ አብርሃም ፤

በአብርሃም ሚስት በሳራ ምክንያት አፊ ማኅፀናቸውን እግዚአብሔር ዘግቶባቸው ነበርና፣ አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ቢለምንላቸው ወለዱ ።

## ምዕራፍ ፳ወ፩

፩፡ ወሐወፃ እግዚአብሔር ለሳራ፤

እግዚአብሔር ሳራን በቸርነት በረድኤት ጐበኛት ፡

ወበከመ ይቤ ገብረ ላቲ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ልጅ ትወልጃለሽ ብሎ እንደ ተናገረ አደረገላት፡

፪፡ ወፀንሰት ሳራ ወወለደት ወልደ ለአብርሃም በርስአቲሃ ፤

ሳራም ሙቀት ልምላሜ ከተለያት በኋላ ፀንሳ ለአብርሃም ወንድ ልጅ ወለደችለት ፡

በመዋዕል ዘይቤሎ እግዚአብሔር፤

በሳብዕታ ትረክብ ሳራ ወልደ ባለው ቀን በሰባተኛው ወር በጥቅምት ፀንሳ ወንድ ልጅን ወለደችለት ፡

፫፡ ወሰመዮ አብርሃም ለውእቱ ሕፃን ዘወለደት ሎቱ ሳራ ይስሐቅ ፤

አብርሃምም ሳራ የወለደችለ ትን ልጅ ስሙን ይስሐቅ አለው፣ (ሐተታ) ይስሐቅ ማለት ትፍሥሕት ማለት ነው ፡

፬፡ ወገዘሮ በሳምንት ዕለት ፤

በስምንተኛው ቀን ገዘረው ፡

www.ethiopianorthodox.org

በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔር ግዝረት በስምንት ቀን ይሁን ብሎ እንዳዘዘው፤

፭፡ ወለአብርሃም ምእት ዓመቱ አመ ተወልደ ሎቱ ይስሐቅ ፤

ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ ለአብርሃም መቶ ዘመን ሆኖት ነበር፤

፮፡ ወትቤ ሳራ ሰሐቀ ረሰየኒ እግዚአብሔር ፤

ትፍሥሕተ ረሰየኒ ሲል ነው ፤ ሳራ እግዚአብሔር እኔን ደስታ አደረገኝ አለች ፤ ደስ አሰኘኝ አለች ፤

ወኵሉ ዘይሰምዕ ይትፌሣሕ ሊተ፤

የኔን መውለድ የሰማ ዘመዴ ሁሉም ስለኔ ደስ ይለዋል ፤

፯፡ ወመኑ እምዜነዎ ለአብርሃም ከመ ተሐጽን ሳራ ሕፃነ ዘወለደት በርስአቲሃ ፤

ካረጀች ሙቀት ልምላሜ ከተለያት በኋላ ሳራ የወለደችውን ልጅ እንድታሳድግ ለአብርሃም ማን በነገረው ? አንተ በቸርነትህ ነው እንጂ አለች ፤ አንድም አብርሃም በዚህ ጊዜ አል ነበረም ብሎ ሳራ የወለደችውን ልጅ እንድታሳድግ ለአብርሃም ማን በነገረው አለች ፤

፰፡ ወልህቀ ሕጻን፤ ወአኀደግዎ ጥበ፤

ይስሐቅም ባደገ ጊዜ በሦስት ዓመቱ ጡት አስጣሉት ፤

ወገብረ አብርሃም ማዕደ ዐቢየ በዕለተ አኀደግዎ ጥበ ለይስሐቅ ፤

አብርሃምም ይስሐቅን ጡት ባስጣሉበት ቀን በአዳራሽ ተገኘ፤

፱፡ ወርእየቶ ሳራ ለይስማኤል እንዘ ይትዋነይ ምስለ ይስሐቅ ወልዳ ፤

ሳራ ይስማኤልን ከልጅዋ ከይስሐቅ ጋራ ሲጫወት አይታ፤

፲፡ ወትቤሎ ሳራ ለአብርሃም ፤

ሳራ አብርሃምን እንዲህ አለችው ፤

ስድዳ ለዛቲ አመት ምስለ ወልዳ፤

ይህችን ባርያ ከልጅዋ ጋራ አስወጥተህ ስደዳት አለችው፤

እስመ ኢይወርስ ወልደ አመት ምስለ ወልድየ ይስሐቅ ፤

የባርያ ልጅ ይስማኤል ከልጄ ከይስሐቅ ጋራ ርስት አይወርስምና ፤

፲፩፡ ወዕፁበ ኮኖ ዝንቱ ነገር በቅድሜሁ ለአብርሃም ጥቀ በእንተ ወልዱ ፤

ባሪያዋን ከልጅዋ ጋራ ስደድ ብትለው ስለ ልጁ ይህ ነገር ለአብርሃም እጅግ ጭንቅ ሆነበት ፤

፲፪፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ኢይኩን ዕፁበ በቅድሜከ በእንተ ዝንቱ ሕፃን ፤

እግዚአብሔርም አብርሃምን ስለ ዚህ ሕፃን ይህ ነገር ጭንቅ አይሁንብህ አለው ፤



ወበእንተ ዛቲ አመት ፤

ስለዚህችም ባሪያ ስለ አጋር ጭንቅ አይሁንብህ ፤

ኵሎ ዘትቤለከ ስምዓ ለሳራ ፤

ሳራ ያለችህን ነገር ሁሉ ስምተህ አድርግ አለው ፤

እስመ እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርዕ ፤

ከይስሐቅ ስምህን የሚያስጠራ ደግ ልጅ ያዕቆብ ይወለዳልና፤ አንድም ከይስሐቅ ወገን ክርስቶስ ይወለዳልና ፤

፲፫፡ ወለወልዳኒ ለዛቲ አመት ዐቢየ ሕዝበ እሬስዮ ፤

የዚህችንም ባሪያ ልጅ ይስማኤልን የብዙ ሰዎች አባት አደርገዋለሁ ፤

እስመ ዘርዐ ዚአከ ውእቱ ፤

ልጅህ ነውና ፤

፲፬፡ ወተንሥአ አብርሃም በጽባሕ ወነሥአ ኅብስተ ወሣዕረ ማይ ወወሀባ ለአጋር ፤

አብርሃምም ሲነጋ ፈጥኖ ተነሥቶ ዳቦውን ፤ ውሀ የምትቀዳበትን እርኮቱን (ቆጀውን) አንስቶ ለአጋር ሰጣት ፤ ሣዕረ ማይ ያለው ከነጠጉሩ የለፋ አቅማዳ ነው ፤

ወአንበረ ዲበ መትከፍታ ወሕፃነኒ ወፈነዋ ወሖረት ፤

በትከሻዋ አሸከማት፤ ልጅዋንም አሳዝሎ ሸኝቶ ሰደዳት እርስዋም ሄደች ፤

ወሳኰየት ውስተ ገዳም መንገለ አዘቅተ መሐላ ፤

በተማማሉበት አዘቅት በኩል ባለ ምድረ በዳ በደረሰች ጊዜ ውሀ አጥታ ተቅበዘበዘች ፤

፲፭፡ ወሐልቀ ማይሂ ዘውስተ ሣዕራ፤

በአቅማዳዋ ያለ ውሀም ባለቀ ጊዜ ፤

ወገደፈቶ ለሕፃን ታሕተ አሐቲ ዕፅ ወሖረት ፤

ልጅዋን ከአንድ ዛፍ ሥር ትታው ሄደች በውሀ ጥም ሲሞት አላይም ብላ ፤

፲፮፡ ወነበረት ትኔጽሮ እምርኁቅ ከመ ምንዳፈ ሐፅ ፤

ጉልማሳ ፍላጻ ወርውሮ የሚያደርስበትን ያህል ርቃ ትመለከተው ነበር ፤ አንድም ከመ ነዳፌ ሐፅ ይላል፤ እንደ ቀስተኛ፤ አንድም እንደ ነፍጠኛ ዓይንዋን አጨንቍራ ትመለከተው ነበር ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ትቤ ኢይርአይ ሞቶ ለሕፃንየ ወበከየት፤

የልጇን ሞት አላይም ብላ ርቃ ተቀምጣ እሱን እሱን እያየች አለቀሰች ፤ ይኸውም ምሳሌ ነው ፤ አብርሃም የጌታ ፤ አጋርና ይስማኤል የኦሪት፤ ይስሐቅና ሳራ የወንጌል ፤ አብርሃም አጋርን ከልጅዋ ጋራ ሸኝቶ እንደ ሰደዳት ፤ ጌታ ኦሪትን ከካህናተ ኦሪት ጋራ ለማሳለፉ ምሳሌ ነው ፤ ሳራን ከይስሐቅ ጋራ ማስቀረቱ ወንጌል እስከ ምጽአት ድረስ በሚኖሥ መም ህራን ቃል ስትነገር የመኖርዋ ምሳሌ ነው ፤

፲፯፡ ወሰምዐ እግዚአብሔር አውያቶ ለውእቱ ሕፃን ይስማኤል ፤

ይስማኤል ባለቀሰ ጊዜ ጌታ የእርስዋንም የልጅዋንም ልቅሶ ሰማ ፤

ወጸውዓ መልአከ እግዚአብሔር ለአጋር እምሰማይ ፤

እግዚአብሔር የላከው መልአክ ከሰማይ ሆኖ አጋርን ጠራት ፤ (ሐተታ) ከላይ እግዚአብሔር አለ፤ ከዚህ መልአከ እግዚአብሔር አለ፤ እንደምን ነው አይጣላም ? ቢሉ አዎን አይጣላም፤ ጌታ በመልአኩ አድሮ ተናግሮ ዋታል፤ አንድም እግዚአብሔር ካለበት መልአክ አይለይምና እንዲህ አለ ፤

ወይቤላ ምንተ ኮንኪ አጋር ኢትኅዝኒ ፤

ጌታ አጋርን ምን ሆንሽ አትዘኚ አላት ፤

እስመ ሰምዐ እግዚአብሔር ቃሎ ለሕፃንኪ እምውስተ መካን ኀበ ሀሎ፤

ካለበት ሆኖ ያለቀሰውን የልጅሽን ልቅሶ እግዚአብሔር ሰምቶዋልና ፤

፲፰፡ ተንሥኢ ወንሥኢ ሕፃነ ወአጽንዒዮ በእዴኪ ፤

አሁንም ተነሥተሽ ልጅሽን በእጅሽ ደግፈሽ ያዢው፤ አንድም በቃልሽ አባብዪው፤ ናልኝ ናልኝ ብለሽ በጅሽ አጽኚው ፤

እስመ ሕዝበ ዐቢየ እሬስዮ ፤

የብዙ ሰዎች አባት አደርገዋለሁና ፤

፲፱፡ ወፈትሐ እግዚአብሔር አዕይንቲሃ ለአጋር ፤

እግዚአብሔርም የአጋርን ዓይነ ልቡናዋን ገለጸላት ፤

ወርእየት አዘቅተ ማይ ፤

ተሠውሮአት ነበር ቢሉ ሰዎች የሚቀዱበት ምንጭ ተገለጸላት፤ አንድም ካለችበት ምድረ በዳ ሌላ ውሀ አፍልቆ አሳያት፤



፳፡ ወሖረት ወመልአት ኀዐሪ ማየ ወአስተየቶ ለሕፃን ፤

እርስዋም ሄዳ በእርኰቷ ውሀ መልታ አምጥታ ለብላቴናው አጠጣችው ፤

ወሀሎ እግዚአብሔር ምስለ ውእቱ ሕፃን ፤

እግዚአብሔር ከይስማኤል ጋር በረድኤት ነበረ ፤

ወልሕቀ ውነደረ ውስተ ውእቱ ገዳም፤

አድጎ በዚያው ምድረ በዳ ኖረ፤

ወኮነ ነዳፌ ፤

በበረሀም ስለ አደገ ቀስት የሚስብ ፤ ፍላፃ የሚወረውር አርበኛ ሆነ ፤

፳፩፡ ወእምገዘ ኀደረ ውስተ ሐቅለ ፋራን ፤

ከዚያ በኋላ ተነሥቶ በፋራን አውራጃ ተቀመጠ ፤

ወነሥአት ሎቱ እሙ ብእሲተ እምድረ ግብጽ ፤

እናቱ አጋርም ከግብጽ ሚስት አጭታ አጋባችው ፤

፳፪፡ ወኮነ በውእቱ መዋዕል ፤

በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ ፤

ሐሩ አቤሜሌክ ወአኮዘት መጋቤ መራዕይሁ ወፋኮል መልአከ ሠራዊቱ ኀበ አብርሃም ፤

ኮነ ያለውን ሐሩ ብሎ አመጣው ፤ አቤሜሌክና ላም ራሱ (የመንጋው ሹም) አኮዘት ፤ ቢትወደዱ ፋኮልም ወደ አብርሃም ሄደው ፤

ወይቤልዎ እግዚአብሔር ምስሌከ በኵሉ ዘገበርከ ፤

በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋራ በረድኤት አለ ፤

፳፫፡ ወይቤሎ አቤሜሌክ ይእዜኒ መሐል ሊተ በእግዚአብሔር ፤

አቤሜሌክም እንዲህ አለ፤ አሁንም ስመ እግዚአብሔር ጠርተህ ማልልኝ ፤

ከመ ኢተዐምፀኒ ኢለዘርዕየ ወኢለሥጋየ ወኢለዘምስሌየ ፤

ልጆቼን፤ እኔንም ወገኖቼንም እንዳትበድል ማልልኝ አለው፤

አላ በከመ መጻእከ አንተ ወገበርኩ ለከ ትግበር ሊተ ፤

አንተ ወደኔ በመጣህ ጊዜ እኔ ላንተ በጎ ነገርን እንዳደረግሁልህ አንተም ለእኔ በጎ ነገር አድርግልኝ እንጂ ፤

ወለምድርየኒ እንተ ሀሎከ ውስቴታ፤

ትኖርባት የነበረውንም አገሬን ለሌላ እንዳትሰጥብኝ ማልልኝ፤

፳፬፡ ወይቤ አብርሃም አሆ እምሕል አንስ፤

አብርሃምም እኔስ እምላለሁ እሺ ከዚህ ቀደም አንተ በድለ ኸኛል እንጂ ብሎ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፭፥ ወተዛለፎ አብርሃም ለአቤሜሌክ በእንተ አዘቅተ ማይ ዘሄድዎ ደቁ ።

የአቤሜሌክ ብላቴኖች በቀሙት ውሀ ጉድጓድ ምክንያት አቤሜሌክን ወቀሰው ፤

፳፮፥ ወይቤ አቤሜሌክ ኢያእመርኩ መኑ ገብሮ ለዝንቱ ግብር ።

አቤሜሌክም ይህን ሥራ ፤ የሠራው ማነው? እኔ አላወቅሁም፤

አንተኒ ኢያይዳዕከኒ ወአነኒ ኢሰማዕኩ እንበለ ዮም ።

አንተም አልነገርኸኝ ፣ እኔም አለዛሬ አልሰማሁም አለው ፤

፳፯፥ ወነሥአ አብርሃም አልሕምተ ወአባግዐ ወወሀቦ ለአቤሜሌክ ።

አብርሃምም ላሙን በጉን አምጥቶ ለአቤሜሌክ ሰጠው ፤

ወተማሐሉ በበይናቲሆሙ ።

እርስ በእርሳቸው ተማማሉ ፤

፳፰፥ ወአቀመ አብርሃም ሰብዓ አባግዐ እንተ ባሕቲቶን ።

አብርሃምም ሰባውን በጎች ከብዙ መንጋ ለይቶ ለብቻቸው አቆመ ፤

፳፱፥ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለአብርሃም ።

አቤሜሌክም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤

ምንትኑ እላ ሰብዓ አባግዕ እለ አቀምከን እንተ ባሕቲቶን ።

ለይተህ ለብቻቸው ያቆምኻቸው እኒህ ሰባው በጎች ምንድን ናቸው ? አለው ፤

፴፥ ወይቤሎ አብርሃም ፣ እላንተ ሰብዓ አባግዐ ንሣእ እምእዴየ ።

አብርሃምም አቤሜሌክን እንዲህ አለው ፤ እኒህን ሰባውን በጎች ተቀበለኝ ፤

ከመ ይኩናኒ ስምዐ ከመ ከረይክዋ ለዛቲ አዘቅት ።

ይህችን የውሀ ጉድጓድ እኔ እንደ ቈፈርኋት ምስክር ይሆኑኝ ዘንድ ተቀበለኝ አለው ፤

፴፩፥ ወበእንተዝ ሰመይዎ ስሞ ለውእቱ አዘቅት ቤርሳባዕ ።

በጎቹን ሰጥቶ ስለገዛው ጉድጓዱን ቤርሳባዕ ብሎ ጠራው ፤ በ፸ በግ የተገዛ ማለት ነው፤ አንድም ቤርሳቤሕ ይላል። አዘቅተ መሐላ ማለት ነው ፤

እስመ በህየ ተማሐሉ በበይናቲሆሙ።

አብርሃምና አቤሜሌክ ተማግም ለውበታልና አዘቅተ መሐላ አሉት ፤

፴፪፥ ወተካየዱ ኪዳነ በነበ አዘቅት።

በጉድጓዱም አጠገብ ቁመው መሐላ ተማማሉ ፤



ወተንሥአ አቤሜሌክ ወአኮዘት መጋቤ መራዕይሁ ወፋኮል መልአከ ሠራዊቱ ።

አቤሜሌክም ሳምራሱን (የመንጋውን ሹም) አኮዘትን ቢት ወደዱን ፋኮልን አስከትሎ ከአብርሃም ዘንድ ተነሥቶ ፤

ወተመይጡ ውስተ ምድረ ፍልስጥኤም።

ወደ ፍልስጥኤም አውራጃ ሄዱ፤

፴፫፥ ወተከለ አብርሃም ዕፀ ነበ አዘቅተ መሐላ ።

አብርሃምም በተማማሉበት ጉድጓድ አጠገብ እንጨት ተከለ ፤ (ሐተታ) ለምልክት ፤ አንድም ማረፊያ ጥላ ሊሆን ነው ፤

ወጸውዐ አብርሃም በህየ ስመ እግዚአብሔር ዘለዓለም ።

በዚያም አብርሃም ለዘላለም የሚኖር የእግዚአብሔርን ስም አመሰገነ ፤

፴፬፥ ወነበረ አብርሃም ውስተ ምድረ ፍልስጥኤም ብዙኃ መዋዕለ ።

አብርሃምም በፍልስጥኤም አውራጃ ብዙ ቀን ተቀመጠ ።።

## ምዕራፍ ፳ወ፪

## ገባኤ

፩፥ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ መዋዕል አመከሮ እግዚአብሔር ለአብርሃም።

ከዚያ ወራት በኋላ እንዲህ ሆነ፤ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው ፤

ወይቤሎ አብርሃም አብርሃም ።

አብርሃም አብርሃም ብሎ ጠራው፤ (ሐተታ) በሀገራቸው ደጊመ ቃል ልማድ ነውና ፤

ወይቤ ነየ አነ ።

አብርሃምም ጌታዬ እነሆ አለሁ አለው ፤

፪፥ ወይቤሎ ንሥእ ለወልድከ ዘታፈቅር ይስሐቅሃ ወሑር ውስተ ደብር ላዕላይ ።

የምትወደውን ልጅህን ይስሐቅን ከፍ ወዳለ ተራራ ይዘኸው ሂድ ፤

ወአዕርጎ ህየ ወሡዓዮ ላዕለ አሐዱ ደብር ዘእቤለከ ።

ከዚያም በደረስህ ጊዜ በማሳይህ በአንደኛ ተራራ ላይ አውጥተህ ሠዋው አለው ፤

፫፥ ወተንሥአ አብርሃም በጽባሕ ወረነነ አድጎ ወነሥአ ክልኤተ ደቆ ወይስሐቅሃኒ ወልዶ ።

አብርሃምም ማለዳ ልጁን ይስሐቅን ይዞ፣ ሁለቱን ብላቴኖች

www.ethiopianorthodox.org

አስከትሎ አህያውን ጭኖ ተነሣ ፤

ወሠፀረ ዕፀወ ለመሥዋዕት ወአፆረ ወሖረ ፤

የሚሠዋበትን እንጨቱን ፈልጦ አሸክሞ ሄደ ፤

፬፡ ወበጽሐ ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ይቤሎ እግዚአብሔር በሣልስት ዕለት ፤

እግዚአብሔር ሒድ ብሎ ካዘዘው ቦታ በሦስተኛው ቀን ደረሰ ፤

፭፡ ወይቤሎሙ አብርሃም ለደቀ ንበሩ ዝየ ምስለ አድግ ፤

አብርሃም ብላቴኖቹን በቅሎውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩኝ አላቸው ፤

አነ ወወልድየ ነሐውር እስከ ደብር ወሰጊደነ ንገብእ ኀቤክሙ ዝየ፤

እኔና ልጄ ግን ወደ ተራራ ወጥተን ሰግደን እንመለሳለን አላቸው ፤ (ሐተታ) ደብር የተባለ ውም ቀራንዮ ነው ፤

፮፡ ወነሥአ አብርሃም ዕፀወ ዘመሥዋዕት፤ ወአፆሮ ለይስሐቅ ወልዱ፤

አብርሃም መሥዋዕት የሚሠዋበትን እንጨቱን አንሥቶ ለይስሐቅ አሸከመው ፤

ወነሥአ እሳተኒ ውስተ እዴሁ ወመጥባሕተኒ ወሖሩ ክልኤሆሙ ኅቡረ፤

እሳቱን ወቅለምቱን እርሱ ይዞ ሁለቱም በአንድነት ሄዱ ፤

፯፡ ወይቤሎ ይስሐቅ ለአብርሃም አቡሁ አባ፤

ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ኦባቴ ብሎ ጠራው ፤

ወይቤሎ ምንት ውእቱ ወልድየ፤

አብርሃምም ልጄ ምነው አለው፤

ወይቤሎ ናሁ ዕፅኒ ወእሳትኒ አይቴ ሀሎ በግዑ ለመሥዋዕት ፤

እነሆ እሳቱም እንጨቱም አለ፤ ለመሥዋዕት የሚሆነው በጉ ወዴት አለ ? አለው ፤

፰፡ ወይቤሎ አብርሃም፤ እግዚአብሔር ይሬኢ ሎቱ በግዐ ለመሥዋዕት ወልድየ ፤

ልጄ ለመሥዋዕት የሚሆነውንስ በግ እግዚአብሔር ያውቃል አለው ፤

፱፡ ወሖሩ ኅቡረ ወበጽሑ ውስተ ውእቱ መካን ዘይቤሎ እግዚአብሔር ፤

በአንድነት ሒደው እግዚአብሔር ከአዘዘው ቦታ ቀራንዮ ደረሱ ፤

ወነደቀ አብርሃም ምሥዋዐ በህየ፤

በዚያም አብርሃም መሥዋዕት የሚሠዋበትን ጸፈጸፈ፤ ሠራ፤

ወወደየ ዕፀወ፤

ዕንጨቱንም በምሥዋዑ ላይ ረበረበ ፤



ወአሠሮ ወአዕቀፆ ለይስሐቅ ወልዱ፤

በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ራሱ መሥዋዕት እንደሆነ አውቋል፤ እኔን ልትሠዋኝ ይመስለኛል፤ አባቴ ስወራጭ እጅህን እንዳላስቄር ጥህ እሠረኝ አለው፤ ልጁን ይስሐቅን እጁን እግሩን አሥሮ ሠርጅቶ (ጠልፎ) ጣለው ፤

ወአስከቦ በከብዱ ላዕለ ምሥዋዕ መልዕልተ ዕፀው ፤

የልጅ ዓይኑ ብክን ብክን ሲል ያሳዝናልና ራርቼ ትቼው ከፈጣሪዬ ጋራ እጣላለሁ ብሎ ፤ አንድም ይስሐቅ ዓይኔ ብክን ብክን ሲል አይተህ ፤ ራርተህ ትተወኝና ከፈጣሪህ ጋራ ትጣላለህ ብሎት ዕንጨት በተረበረበበት በምሥዋዑ ላይ በልቡ ደፍቶ አስተኛው ፤

፲፡ ወአልዐለ እዴሁ አብርሃም ከመ ይንሣእ መጥባሕተ ወይኅርዶ ለወልዱ ፤

አብርሃም እጁን ዘርግቶ ወቅለምቱን (ካራውን) መዞ ከአንገቱ ላይ አሳርፋለሁ ሲል ፤

፲፩፡ ወጸውዖ እግዚአብሔር ለአብርሃም፤ ወይቤሎ አብርሃም አብርሃም፤

እግዚአብሔርም አብርሃም አብርሃም ብሎ ጠራው ፤

ወይቤ ነየ አነ ፤

እነሆ ጌታዬ እኔ አለሁ አለ ፤

፲፪፡ ወይቤሎ ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ ወኢትግበር ቦቱ ምንተኒ፤

በልጅህ ላይ እጅህን ጥለህ ምንም ምን አታድርግበት አለው ፤

ይእዜኒ አእመርኩ ከመ አንተ ትፈርሀ ለእግዚአብሔር ፤

እግዚአብሔርን እንድትፈራው እንድታመልከው አሁን ገና አወቅሁ ፤

ወኢመሐከ እምኔየ ለወልድከ ዘታፈቅር ፤

የምትወደውን ልጅህን ከኔ ይልቅ አልወደድከውምና ፤ ኢትደይ እዴከ ብለህ እሠር ፤

፲፫፡ ወሶበ ነጸረ አብርሃም ወርእየ ናሁ አሐደ በግዐ ወእኁዝ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ ፤

አብርሃምም ዞሮ ባየ ጊዜ፤ ዕፀ ሳቤቅ በሚባል ሐረግ ሁለቱን ቀንዶቹን የተያዘ አንድ በግ እነሆ አየ ፤

ወሖረ አብርሃም ወነሥአ ወሦዖ ህየንተ ይስሐቅ ወልዱ ፤

አብርሃምም ይህን ሠዋ ሲለኝ ነው ብሎ ፤ ልጁን ይስሐቅን ትቶ ሒዶ በጉን አምጥቶ ሠዋው፤ (ታሪክ) ይህስ እንደ ምንድን ነው ቢሉ? ጌታ ብየ አርክ አብርሃም ፍቁርየ በዲበ ምድር ብሎ ለመላእክት ነግሮዋቸዋል፤ መላእክትም ይህን ሰምተው፤

www.ethiopianorthodox.org

ብፁዕ አብርሃም አርከ እግዚአብሔር እያሉ አመስግነዋል፤ ተሰምዐ ቃላት በሰማያት ይላል፤ ሰይጣን ይህን ሰምቶ ወዳጅህማ ከሆነ በእርግና ጊዜ የወለደው አንድ ልጅ አለው፣ እርሱን አይሠዋልህምን አለው ፤ ምነው አይሠዋልኝ አለው፤ አሁን ሰይጣን ከእግዚአብሔር ባለምዋልነትን አግኝቶ እንዲህ ብሎ የሚጠይቅ እግዚአብሔርም ለሰይጣን እንዲህ ብሎ የሚመልስ ሆኖ አይደለም፣ የጌታን ምሥጢረ ሞቱን ለአብርሃም፤ የአብርሃምንም ዜና ኂሩቱን ለሰው ለመግለጽ ነው እንጂ ፤ ከዚህ በኋላ ጌታ አብርሃምን ሡዕ ሊተ ይስሐቅሃ ወልደከ ዘታፈቅር አለው ፤ አብርሃምም ይስሐቅን ሁለቱን ብላቴኖቹን ይዞ እስከ ሦስት ቀን ገሥገሠ ፤ ከእግረ ደብር ሲደርስ ብላቴኖቹን ጽንሑ ዝየ አነ ወወልድየ ሰጊደነ ንገብእ ኀቤክሙ ብሎ ወአያሮ ለይስሐቅ ወልዱ ይላል ፤ ዕንጨቱን ለይስሐቅ አሸክሞ እሳቱን ወቅለምቱን እርሱ ይዞ ሲሄዱ ከማዕከለ ደብር ሲደርስ አይቴ በግዑ አባ፤ አባቴ እንጨቱን እሳቱን ወቅለምቱን አያለሁ፤ መሥዋዕት የሚሆነው በጉ ወዴት አለ ? አለው ፤ በግዖሰ የአምር እግዚአብሔር፤ በጉንስ እግዚአብሔር ያውቃል አለው፤ ከርእሰ ደብር ሲደርሱ ደንጊያውን ይጸፈጽፍ እንጨቱን ይረበርብ ጀመረ ፤ አባቴ ደንጊያውን ጸፈጸፍህ ፣ ዕንጨቱን ረበረብህ ፣ በጉ ወዴት አለ ? እኔን ልትሠዋኝ ነው መሰለኝ፣ ስንፈራገጥ እጅህን ፣ እግርህን እንዳላስቈርጥህ፣ እጄን እግሬን እሠረኝ አለው፤ አሠረው፤ ዓይንህ ከዓይኔ ተገናኝቶ ራርተህ ትተኸኝ ከፈጣሪህ እንዳትጣላ ደፍተህ አስተኛኝ አለው፤ ደፍቶ አስተኝቶ ስለቱን ከላዩ አድርጎ እስባለሁ ሲል ፣ ከወደኋላው ኢትደይ እዴከ የሚል ቃል ሰማ ፤ ዞሮ ቢያይ ነጭ በግ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ ፤ ይህን ሠዋ ሲለኝ ነው ብሎ ይስሐቅን ፈትቶ በጉን ሠውቶዋል፤

ይህም ምሳሌ ነው ፣ አብርሃም የእግዚአብሔር አብ ፣ ይስሐቅ የእግዚአብሔር ወልድ፣ አብርሃም ልጁን በሕሊናው እንደ ሠዋው፣ እግዚአብሔር አብም፣ እግዚአብሔር ወልድን በሥጋ ሠውቶታልና፤ አብርሃምን ምሳሌ ሊሆን አስቀድሞታል ፤ እግዚአብሔር አብ ወልድን የሠዋው ልጁ ባይሆን ነው እንዳይሉ ፤ ስንኳንስ ዘልማዱ ኂሩት እግዚአብሔር ፤ አብርሃምስ እንኳ አንድ ልጁን ሠዋ ሲኋቸው



ምላሽ እንዲያጡ ባወቀ ገንዘብ ፤ ሁለቱ ብላቴኖች የፈያታዊ ዘየማንና የፈያታዊ ዘፀጋም፤ አድግ (አድግ) የአድግ ሆሣዕና፣ ዕፅ የመስቀል፣ እሳት የመንፈስ ቅዱስ ፣ ወቅለምት የሥልጣን እግዚአብሔር ምሳሌ ነው ፤ ወቅለምት አጥንትን ከሥጋ እንዲለይ፤ ጌታም አባ አመሐጽን ነፍስየ ውስተ እዴከ ብሎ በገዛ ሥልጣኑ ነፍሱን ከሥጋው ለይቶአልና ፤ ሦስት ቀን ሒዶ እንደ ሠዋው፣ ጌታም ምክረ ሞቱ በተፈጸመ በሦስተኛው ቀን የመሰቀሉ ምሳሌ ነው ፤ ይህስ ይስሐቅ የዳነበት ነው እንጂ የሞተበት አይደለም ብሎ፣ ሕሊና አብርሃም የመቃብር ፣ ይስሐቅ በሕሊና አብርሃም በተሠዋ በሦስተኛው ቀን መዳኑ ፣ ጌታ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው፤ አንድም ምሳሌ ያዛውራሉ፤ በግዕ የጌታ፣ ይስሐቅ የምእመናን ፣ በግዕ ቤዛ ይስሐቅ ሆኖ አል ፣ ጌታም ቤዛ ምእመናን ሆኗልና ፤ በጉ ከሰማይ የወረደ ነው ያሉ እንደሆነ ፣ ጌታ ከሰማየ ሰማያት ለመውረዱ ፤ ከዕፀ ሳቤቅ የተገኘ ነው ያሉ እንደ ሆነ ፣ በኀቱም ድንግልና ከእመቤታችን ለመወለዱ ፤ ከአብርሃም መንጋ የመጣ ነው ያሉ እንደሆነ ከነገደ አብርሃም ለመወለዱ ምሳሌ ነው ፤ አንድም ዕፀ ሳቤቅ የመስቀል ምሳሌ ፣ ዕፀ ሳቤቅ ብሂል ዕፀ ሥርየት መስቀል እንዲል ፤

፲፬፡ ወሰመዮ አብርሃም ለውእቱ መካነ ራእየ እግዚአብሔር ፣

አብርሃምም መሥዋዕት የሠዋበትን ቦታ የእግዚአብሔር መገለጫ አለው ፤

እንዘ ይብል አስተርአዮ አስተርአየኒ እግዚአብሔር በዝ ደብር ፣

በዚህ ተራራ እግዚአብሔር ተገልጾ ተነጋገረኝ ሲል ፤

፲፭፡ ወጸውዖ መልአከ እግዚአብሔር ለአብርሃም ዳግመ እምሰማይ ወይቤሎ ፣

እግዚአብሔር የአዘዘው መልአክም ከሰማይ ሆኖ ዳግመኛ አብርሃምን ጠርቶ እንዲህ አለው፤

፲፮፡ መሐልኩ በርእስየ ይቤ እግዚአብሔር ፣

«አማንየ በርእስየ ሕያው አነ ለዓለም» ብዬ በራሴ ማልሁ አለ እግዚአብሔር ፤

እስመ ገበርከ ለዝንቱ ነገር ወኢመሐከ እምኔየ ለወልድከ ዘታፈቅር ፣

ከእኔ ይልቅ ልጅህን ሳትወድ ይህን ነገር ጨክነህ አድርገኸዋልና ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ከመ ባርኮ እባርከከ ወአብዝኆ አስተባዝኆ ለዘርእከ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ወከመ ኆፃ ዘድንጋገ ባሕር፣

አንተን ፈጽሜ እንዳከብርህ ፣ ልጆችህንም በባሕር ዳር እን ዳለ አሸዋ ፣ በሰማይ እንዳሉ ከዋክብት ፈጽሜ እንዳበዛቸው ማልኹልህ አለህ እግዚአብሔር አለው ፤

ወይወርሱ ዘርእከ አህጉረ ፀር ፣

ልጆችህም የጠላቶቻቸውን አገ ሮች ይወርሳሉ ፤

፲፰፤ ወይትባረኩ በዘርእከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ፣

በልጅህም አሕዛብ ሁሉ ይመ ራረቁበታል፣ ይስሐቅን፤ ያዕቆ ብን ያከበረ አምላክ ያክብርህ እያሉ ፤ አንድም ካንተ የተወ ለዱ ሐዋርያት በትምህርት የአ ሕዛብን አገር ይወርሳሉ ፣ ምእ መናን አሕዛብም በልጅህ በክር ስቶስ ይከብራሉ ፤

እስመ ሰማዕከ ቃልየ ፣

የነገርኹህን ነገር ሰምተህ ፈጽ መሃልና ፤

፲፱፤ ወገብአ አብርሃም ኀበ ደቁ ፣

አብርሃምም ወደ ብላቴኖቹ ተመለሰ ፤

ወተንሥኡ ወሐሩ ኅቡረ ወበጽሑ ኀበ አዘቅተ መሐላ ፣

ባንድነት ተነሥተው ሄደው ወደ ተማማሉበት ምንጭ (ቤርሳቤህ) ደረሱ ፤

፳፤ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር፣

ከዚህ ነገር በኋላ እንዲህ ሆነ፤

ዜነውዎ ለአብርሃም ወይቤልዎ ፣ ወለደት ወልደ ሚልካ ለናኮር እኁከ፣

ኮነ ያለውን ዜነውዎ ብሎ አመ ጣው፣ ሚልካ ለወንድምህ ለና ኮር ወንድ ልጅ ወለደችለት ብለው ነገሩት ፤

፳፩፤ ሆኮስ በኵራ ወመዋክሲን እኁሁ ወቀማኤል አቡሁ ለአራን ፣

መጀመሪያው ሆኮስ ፤ ፪ኛው ወንድሙ መዋክሲን ፤ ፫ኛው የአራን አባት ቀማኤል ፤

፳፪፤ ወአኮዜት፤ ወኤዝራው፣ ወፊሎዛር፣ ወዮሩት ፣

፬ኛው አኮዜት ፤ ፭ኛው ኤዝ ራው፣ ፮ኛው ፊሎዛር፤ ፯ኛው ዮሩት ፤

፳፫፤ ወባቱኤል አቡሃ ለርብቃ ፣

፰ኛው የርብቃ አባት ባቱኤል እነዚህ ናቸው ፤

እሉ እሙንቱ ፰ቱ ደቂቅ ዘወለደቶሙ ሚልካ ለናኮር እኁሁ ለአብርሃም ፣

ሚልካ ለአብርሃም ወንድም ለና ኮር የወለደችለት ልጆች እኒህ ፰ቱ ናቸው ፤



፳፬፡ ወሔማ ዕቅብቱ ወለደቶሙ ለቀዓት፡ ወለቤካ፡ ወለማኮ፡ ወለሚኮ፣

የማኮር ገረድ ሔማም ቀዓትን፣ ቤካን ፣ ማኮን ፣ ሚኮን ወለደ ችለት ።

## ምዕራፍ ፳ወ፫

፩፡ ወኮነ ሕይወታ ለሳራ ምእተ ወዕ ሥራ ወሰብዓተ ዓመተ ፣

ሳራ በሕይወት የኖረችው ዘመን መቶ ሃያ ሰባት ሆነ ፤

፪፡ ወሞተት ሳራ በሀገረ አርባቅ እንተ ውስተ ቈላት፣

ሳራም በቈላ አውራጃ ባለች አርባቅ በምትባል ሀገር ሞተች፤

እንተ ይእቲ ኬብሮን እንተ ውስተ ከነዓን፣

ይህችውም በከነዓን ውስጥ ያለች ኬብሮን ናት ፤

ወቦመ አብርሃም ከመ ይላህዋ ለሳራ ወይብክያ፣

አብርሃም ለሚስቱ ለሳራ ፊጽሞ ያለቅስላት ዘንድ ተነሣ ፤

፫፡ ወተንሥአ አብርሃም እምነበ በድና ወይቤሎሙ ለደቂቀ ኬጢ ፣

አብርሃም ከአስከሬንዋ አጠገብ ተነሥቶ የኬጢን ልጆች እንዲህ አላቸው ፤ (ሐተታ) ኬጢ የሀ ገር ስም ፤ አንድም የሰው ስም ነው ፤

፬፡ ነግድ ወፈላሲ አነ ምስሌክሙ፣

እኔ ከናንተ ጋራ ይህን ያህል ዘመን ስኖር መጻተኛ ነኝ ፤

ሀቡኒ ሊተ ከመ እግየጥ መቃብረ፣

የመቃብር ቦታ እገዛ ዘንድ በዋጋ ሽጡልኝ ፤

ወእቅብር በድንየ ከማክሙ ፣

እንደ እናንተ እናንተን መስዬ ሬሳዬን እቀብር ዘንድ ሽጡልኝ አላቸው ፤

፭፡ ወአውሥእዎ ደቂቀ ኬጢ ለአ ብርሃም ወይቤልዎ አልቦ ፣

የኬጢም ልጆች ለአብርሃም አይ ሆንም ብለው ፣ መለሱለት ፤

፮፡ እግዚኦ ስምዐነ ፣

ጌታችን ሆይ የምንነግርህን ነገር ስማ ፤

እስመ ንጉሥ አንተ ለነ እምነበ እግዚአብሔር ፣

ከእግዚአብሔር ታገዘህ የመጣህ ንጉሣችን አንተ ነህና ፤

በውስተ መቃብሪነ ዘኅረይከ ቅብር በድነከ ፣

እኛ ከምንቀበርበት ከወደድኸው ቦታ ሬሣህን ቅበር ፤

እስመ አልቦ እምኔነ ዘይከልአከ መቃብሪሁ ከመ ትቅብር በድነከ በህየ ፣

በወደድኸው ቦታ ሬሳህን ትቀ ብር ዘንድ ከእኛ ወገን መቃ

ብሩን የሚከለክልህ ሰው የለ ምና ፤

፯፡ ወተንሥአ አብርሃም ወሰገደ ቅድመ ሕዝብ ዘደቂቀ ኬጢ ፤

አብርሃምም ተነሥቶ በኬጢ ልጆች ፊት እጅ ነሣ ፤

፰፡ ወይቤሎሙ እመ ፈቀድክሙ ታቅብሩኒ በድንየ ንግርዎ ለኤፍሮን በእንቲአየ ወልደ ሰዓር ፤

ሬሳዬን ታስቀብሩኝ ዘንድ ከፈቀዳችሁ የኔን ነገር ለሰዓር ልጅ ለኤፍሮን ንገሩት ፤ (ሐተታ) ምነው እርሱ አይነግረውም ነበር ቢሉ፤ ከንጉሥ ፊት ቆሞ ይኸን አድርግልኝ ብሎ የራስን ነገር መናገር ያሳፍራልና ፤

፱፡ የሀበኒ በአተ ካዕበት እንቲአሁ እንተ ሀለወት ውስተ ገራህቱ በወርቅየ በሤጥ በመጠነ ኮነ ወእሣየጥ እምኔሁ ፤

በእርሻው ውስጥ ያለች ገንዘቡ የምትሆን እጥፍነት ያላትን ዋሻ፤ የሆነውን ያህል ዋጋ ሰጥቼ ይሸጥልኝ ዘንድ ፤ ከእርሱም በገንዘቤ እገዛ ዘንድ ንገሩት አላቸው፤ (ሐተታ) በአተ ካዕበት አለ ፤ ውስጥዋ ሁለት ክፍል ናት የዘገየውን ሬሳ ወደ ውስጥ፤ አዲሱን ሬሳ ለመቅበር እንዲመቻቸው በውጭ የሚያደርጉበት ነው፤ አንድም ላይዋ እርሻ የምትሆን ናትና እንዲህ አለው፤

፲፡ ወሀሎ ኤፍሮን ይነብር ማዕከሌሆሙ ለደቂቀ ኬጢ ፤

ኤፍሮንም በኬጢ ልጆች መካከል ተቀምጦ ነበር ፤

ወይቤሎ ኤፍሮን ኬጥያዊ ለአብርሃም እንዘ ይሰምዑ ደቂቀ ኬጢ ፤ ወኵሎሙ እለ ይበውኡ ውስተ ሀገር ፤

የኬጢ ሰው ኤፍሮን ፤ የኬጢ ልጆችና በሀገሩ ያሉትም ሰዎች ሁሉ ሲሰሙ አብርሃምን እንዲህ አለው ፤

፲፩፡ ቅረበኒ እግዚእየ ወስምዐኒ ፤

ጌታዬ አብርሃም የምነግርህን ቀርበህ ስማኝ አለው ፤

ገራህትየኒ ወበአትየኒ ዘውስቴቱ ለከ ወሀብኩከ በቅድመ ኵሉ ሰብአ ሀገርየ ፤

በሀገሬ ሰዎች ፊት በላይ ያለ እርሻውን፤ በውስጥ ያለውንም ዋሻውን ለአንተ ሰጥቼሃለሁ ፤

ወናሁ ወሀብኩከ ፤ ቅብር በድነከ ፤

ወሀብኩከና ወሀብኩከ አንድ ወገን ፤ እነሆ ሰጥቼሃለሁና ሬሳህን ፤ ከወደድከው ቦታ ቅበር አለው ፤

፲፪፡ ወሰገደ አብርሃም ቅድመ ኵሉ ሕዝብ ፤

አብርሃምም ተነሥቶ በሰዎች ሁሉ ፊት እጅ ነሣ ፤



፲፫፡ ወይቤሎ ለኤፍሮን እንዘ ይሰምዑ ኵሎሙ ፤

ሰዎች ሁሉ ሲሰሙ አብርሃም ኤፍሮንን እንዲህ አለው ፤

ስምዐኒ ሤጠ ለገራህትከ ፤

ንግረኒ ሲል ነው ፤ የእርሻህን ዋጋ ንገረኝ አለው፤ ንሣእ እምኔየ ማግኘሻ፤ አንድም ሤጠ ለገራህትከ ንሣእ እምኔየ ብለህ ወደ ታች አውርድ ፤

ንሣእ እምኔየ ወእቅብር በድንየ በህየ፤

የእርሻህን ዋጋ ተቀበለኝና ሬሳዬን ከዚያ ልቅበር ፤

፲፬፡ ወአውሥአ ኤፍሮን ለአብርሃም ወይቤሎ ፤

ኤፍሮንም ለአብርሃም እንዲህ ብሎ መለሰለት ፤

፲፭፡ አልቦ እግዚእየ ስምዐኒ ፤

ጌታዬ ነገሩ እንዲህ አይደለም፤ የምነግርህን ነገር ስማኝ ፤

ምንትኑ ውእቱ ዝንቱ ምድር ፤

ይህ የመቃብር ቦታ ምን ቁም ነገር አለው ፤

ወምንትኑ ውእቱ አርባዕቱ ምእት ጠፋልሕ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ፤

ቢያወጣም አራት መቶ ምዝምዝ ብር ነው፤ በእኔና በአንተ መካከል ምን ቁም ነገር ነው ? አለ ፤

እንከሰ ቅብር በድነከ በህየ ፤

እንግዲህስ ወዲህ ሬሳህን በዚህ ከወደድኸው ቦታ ቅበር አለው፤

፲፮፡ ወሰምዐ አብርሃም ለኤፍሮን ዘይቤሎ በቅድመ ደቂቀ ኬጢ ፤

አብርሃም በኬጢ ልጆች ፊት ኤፍሮን የነገረውን ሰምቶ ፤

ወደለወ ሎቱ አርባዕተ ምእተ ጠፋልሐ ብሩር መፍደ ዘኢኮነ ተምያነ፤

በምሥጢሩ ዋጋውንሲነግረኝ ነው ብሎ ግብዝ ያይደለ የጠራ፤ አንድም ባለዕዳ የሚቀበለው አራት መቶ ምዝምዝ ብር መዝኖ ሰጠው ፤

፲፯፡ ወኮነ ገራህቱ ለኤፍሮን ወበአቱ ወኵሉ ዕፀው እንተ ውስቴታ ኮነ ለአብርሃም ፤

ኮነና ኮነ አንድ ወገን ፤ የኤፍሮን የነበረው እርሻውም ዋሻውም በዚያም ያለው ዕንጨት ሁሉ ለአብርሃም ሆነ ፤

፲፰፡ ወተሣየጣ በቅድመ ኵሎሙ ደቂቀ ኬጢ ፤

አብርሃምም በተናገረው ዋጋ በኬጢ ልጆች ፊት ገዛት ፤

፲፱፡ ወእምዝ ቀበራ ለሳራ ብእሲቱ ውስተ በአተ ካዕበት እንተ ተሣየጣ እምኤፍሮን ፤

ከዚህም በኋላ አብርሃም ሚስቱ ሳራን ከኤፍሮን በገዛት ሁለት ክፍል ባላት ዋሻ ቀበራት ፤

www.ethiopianorthodox.org

(ሐተታ) ይህም ምሳሌ ነው ፤ አብርሃም የጌታ ፣ ገራህት የእመቤታችን ምሳሌ፣ በዓተ ካዕበት መሆንዋ ድንግል በክልኤ የመሆንዋ ምሳሌ፣ ያርማት ይኩ ተኮታት እንደነበረ እመቤታችንም ከፍትወታት ፣ ከኃጣውእ፣ ከእኩያት ንጽሕት ናትና መጠበቁ በመንፈስ ቅዱስ ከልማደ አንስት የመጠበቅዋ ምሳሌ ነው ።

## ምዕራፍ ፳ወ፬

### ገባኤ

፩፡ ወልሕቀ አብርሃም ወነለፈ መዋዕሊሁ ፣

አብርሃም የጉልማስነቱ ወራት አልፎ አረጀ ፤

ወባረከ እግዚአብሔር ለአብርሃም በኵሉ ፣

እግዚአብሔር አብርሃምን በሥራው ሁሉ አክብሮት ነበር ፤

፪፡ ወይቤሎ አብርሃም ለገብሩ ዘይልሕቅ ፣

አብርሃምም ትልቁን ባሪያውን እንዲህ አለው ፤

ዘውእቱ መጋቢሁ ላዕለ ኵሉ ንዋዩ፣

ይኸውም በገንዘቡ ሁሉ ላይ የሾመው ነው ፤

ደይ እዴከ ላዕለ እዴየ ፣

እጄን መትተህ ማል አለው ፤ (ሐተታ) የሰጠኸኝ ገንዘብ አይባረክልኝ በል ሲል ነው ፤ አንድም ላዕለ አብራክየ ይላል፣ ጉልበቴን መትተህ ማል አለው፤ የወለድኋቸው ልጆች አይባረኩልኝ በል ሲል ነው ፤

፫፡ አምሕለከ በአምላከ ሰማይ ወምድር፣ ከመ ኢትንሣእ ብእሲተ ለወልድየ ይስሐቅ እምአዋልደ ከነዓን እለ ምስሌሆሙ አነ አነድር ፣

ለልጄ ለይስሐቅ እኔ አብሬያቸው እኖር ከነበረ ከከነዓን ልጆች ሚስት እንዳታጭለት ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ ፤

፬፡ ዳዕሙ ሖር ውስተ ብሔርየ ውነበሙላድየ፣ ወንሣእ ብእሲተ ለወልድየ ይስሐቅ በህየ ፣

ወደ ተወለድኹበት ወደ አገሬ ሂደህ ለልጄ ለይስሐቅ ከዚያ ሚስት አጭተህ አጋባው እንጂ፤

፭፡ ወይቤሎ ገብሩ ፣

ባሪያውም አብርሃምን እንዲህ አለው ፤

ለእመኬ ኢፈቀደት ይእቲ ብእሲት ትምጻእ ምስሌየ ዘንተ ብሔረ ፣

(ጠንቅቆ ይምላል) ፣ ያች ሴት እኔ ወደምኖርበት ሀገር ከእኔ ጋራ ትመጣ ዘንድ ባትወድሳ ፤



አግብአኑ ለወልድከ ውስተ ውእቱ ምድር እምነበ መጻእከ፣

ልጅህን ይስሐቅን ትተኸው ወደ መጣህበት ሀገር መልሼ ልውሰደውን ? አለው ፤

፮፡ ወይቤሎ አብርሃም ፣

አብርሃምም እንዲህ አለው ፤

ዑቅ ኢታግብእ ለወልድየ ህየ ፣

ልጄ ይስሐቅን መልሰህ ወደ እኔ ሀገር እንዳትወስደው እወቅ ፤

፯፡ እግዚአብሔር አምላከ ሰማይ ወምድር ዘአውፅአኒ እምቤተ አቡየ ወእምድር እንተ ተወለድኩ በውስቴታ ፣

ከተወለድሁባት ሀገር ከዘመዶቼም ወገን ለይቶ ያወጣኝ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ እግዚአብሔር ፤

ወዘመሐለ ሊተ ወይቤለኒ ለከ እሁበከ ዛተ ምድረ ወለዘርእከ ፣

ከነዓንን ዛሬ ላንተ፣ ኋላ ለልጆችህ አወርሳቸዋለሁ ብሎ የማለልኝ እግዚአብሔር ፤

ውእቱ ይፌኑ መልአኮ ቅድሜከ ፣

እርሱ ካንተ በፊት መልአኩን ልኮ ነገርህን ያከናውንልሃል ፤

ወትነሥእ ብእሲተ ለወልድየ እምህየ ፣

አንተም ለልጄ ለይስሐቅ ከአዋልደ ሶርያ ሚስት አጭተህ ታጋባዋለህ ፤

፰፡ ወእመሰ ኢፈቀደት ባሕቲ ይእቲ ብእሲት ትምጻእ ምስሌከ ውስተ ዛቲ ምድር ንጹሕ አንተ እመሐላ ፣

ነገር ግን ያች ሴት ከአንተ ጋራ ወደዚህች ሀገር መምጣት ካልወደደች፣ አንተ ከመሐላ ንጹሕ ነህ ማለት አይደርስብህም ፤

ወዘንተ ዑቅ ከመ ኢታግብእ ለወልድየ ህየ ፣

ልጄ ይስሐቅን ወደዚያ ሀገር መልሰህ እንዳትወስደው እወቅ እንጂ ንጹሕ ነህ አለው ፤

፱፡ ወወደየ እዴሁ ውእቱ ገብር ላዕለ እደ አብርሃም እግዚኡ ፣ ወመሐለ ሎቱ በእንተ ዝንቱ ነገር ፣

ባሪያው ኢያውብርም ስለዚህ ነገር የጌታውን የአብርሃምን እጅ መትቶ ማለለት፣ የሰጠኸኝ ገንዘብ አይባረክልኝ ፤ አንድም ጉልበቱን ጸፍቶ ማለ፣ የወለድሁት ልጅ አይባረክልኝ ሲል፤

፲፡ ወነሥአ ውእቱ ገብር ዐሥርተ አግማለ እምአግማለ እግዚኡ ወኮሎ ሠናየ ዘእግዚኡ ምስሌሁ ፣

ባሪያው ኢያውብርም ከጌታው ግመሎች ዐሥሩን ግመል መርጦ ፤ ከጌታውም ገንዘብ ያማረ ያማረውን ገንዘብ ሁሉ ማጫ ማሥመሪያ ጭኖ ፤

ወተንሥአ ወሖረ ኀበ አፍላገ አራም ሀገረ ናኮር ፣

ተነሥቶ የአራምን ወንዞች ተሻግሮ ወደ ናኮር ሄደ ፤ (ሐተታ)

www.ethiopianorthodox.org

እኒህም ወንዞች ባብና ፋርፋ ይባላሉ ፡

፲፩፡ ወአሰረፈ አግማሊሁ አፍአ እም ሀገር ኀበ አዘቅተ ማይ ፍና ሠርክ ጊዜ ይወፅአ ሐዋርያተ ማይ ከመ ይቅድሓ ፤

ውሀ የሚቀዱ ሴቶች በሚመ ጡበት በሠርክ ጊዜም ከከተማ ውጭ ባለ በውሀ ዳር ግመሎቹን አራግፎ ተቀመጠ ፡

፲፪፡ ወይቤ እግዚእየ አምላኩ ለአብ ርሃም አስተበቍዐከ ሠርህ ሊተ ዮም ወግበር ምሕረተ ምስለ እግዚ እየ አብርሃም ፤

የአብርሃም ፈጣሪ ጌታዬ እለም ንሃለሁ ዛሬ መንገዴን አቅና ልኝ ፤ ለጌታዬ ለአብርሃምም ምሕረትን አድርግ አለ ፡

፲፫፡ ወናሁ ቆምኩ ኀበ አዘቅተ ማይ፤

እነሆ ከዚህ ከውሀው ዳር ተቀ ምጫለሁ ፡

ወአዋልዲሆሙ ለሰብአ ሀገር ይወ ፅኡ ይቅድሓ ማየ ፤

የዚህ ሀገር ሰዎች ሴቶች ልጆች ውሀ ሊቀዱ ይመጣሉ ፡

፲፬፡ ወትኩን ይእቲ ድንግል እንተ እብላ አነ አጽንኒ ቀሡተኪ አስትዩኒ ማየ ፤

ከነዚያ ጋራ የምትመጣ አንዲቱ ድንግል ሆና እኔም እንስራሽን አዘንብለሽ ውሃ አጠጭኝ ብዬት፡

ወትቤለኒ ይእቲ ድንግል ስተይ አንተኒ፡ ወአግማሊከኒ አሰቲ እስከ ይረውዩ ፤

አንተም ጠጣ፤ ግመሎችህንም እስኪጠግቡ ድረስ አጠጣቸዋ ለሁ የምትለኝ ሆና ፡

ኪያሃ አስተዳሎከ ለገብርከ ይስሐቅ እግዚኦ ፤

አቤቱ ጌታዬ ለባሪያህ ለይስሐቅ እርስዋን እንዳዘጋጀህለት አው ቃለሁ ፡

ወበዝንቱ አአምር ከመ ገበርከ ምሕ ረተ ለእግዚእየ አብርሃም ፤

በዚህም፤ ለጌታዬ ለአብርሃም ቸርነትህን እንዳደረግህለት አው ቃለሁ እያለ ሲመኝ ፡

፲፭፡ ወከነ ዘእንበለ የኀልቅ ተናግሮ ከመዝ በልቡ ፤

ይህንን አስቦ ሳይናገረው፡ ተና ግሮ ሳይጨርሰው እንዲህ ሆነ ፡

ወነያ ርብቃ ወፅአት እንተ ተወል ደት ለባቱኤል ወልደ ሚልካ ብእ ሲተ ናኮር እኁሁ ለአብርሃም ወትጸ ውር ቀሡታ ሳዕለ መትከፍታ ፤

ያን ጊዜ ከአብርሃም ወንድም ከናኮር ሚስት ከሚልካ ከተወ ለደ ከባቱኤል የተወለደች ርብቃ ማድጋዋን ነጥቃ ውሀ ልት ቀዳ መጣች ፡

፲፮፡ ወሠናይ ገጻ ጥቀ ለይእቲ ወለት፤

የዚያችም ልጅ መልክዋ እጅግ ያማረ ነበረ ፡



ወድንግል ይእቲ ወኢተአምር ብእሴ፤

ባል ያላገባች ድንግል ነበረች፡

ወወረደት ውስተ አዘቅት ወቀድ ሐት ማየ ፤

ከምንጩ ወርዳ ውሀ ቀዳች ፡

፲፯፡ ወሰበ ዐርገት ሮፀ ውእቱ ብእሲ ወይቤላ አስትዩኒ ሕቀ ማየ እምቀ ሡትኪ ፤

ውሀውን ቀድታ በወጣች ጊዜ፤ ኢያውብር ፈጥኖ ሔዶ ከእን ስራሽ ጥቂት ውሀ አጠጪኝ አላት ፡

፲፰፡ ወትቤሎ ስተይ እግዚእየ ፤

እሺ ጌታዬ ጠጣ አለቺው ፡

ወአውረደት ቀሡታ ፍጡነ እምዲበ መትከፍታ ወአስተየቶ እስከ ይረዊ፤

ከዚህ በኋላ እንስራዋን ከትከ ሻዋ ፈጥና አውርዳ እስኪረካ ድረስ አጠጣቺው ፡

፲፱፡ ወትቤሎ ለአግማሊከኒ እቀድሕ ወይስተዩ ኵሎሙ ፤

ለግመሎችህም ውሀ ልቅዳና ግመሎችህ ሁሉ ይጠጡ ብላ፡

፳፡ ወሦጠት ቀሡታ ፍጡነ ውስተ ምስታይ ወሮፀት ወቀድሐት ለአግ ማሊሁ ኵሎሙ ፤

በእንስራ የቀዳችውን ውሀ ከገ ንዳው ጨምራ ግመሎቹን ሁሉ ለማጠጣት ሁለተኛ ቀዳች ፡

፳፩፡ ወውእቱሰ ብእሲ ይሬእያ ከመ ወየረምም፤

ኢያውብር ግን ዝም ብሎ አተ ኵሮ ያያት ነበር ፡

ከመ ይርአይ እመ ይሴርሖ እግዚ አብሔር ፍኖቶ ወለእመኒ አልቦ ፤

የመጣበትን ነገር እግዚአብሔር ያቀናለትም አያቀናለትም እን ደሆነ ያውቅ ዘንድ ፡

፳፪፡ ወእምዝ ረወዩ አግማሊሁ ነሥአ አዕኑገ ዘወርቅ ዘዘሕልቅ ድልወቱ ፤

ግመሎቹም ከጠጡ በኋላ ፤ ኢያውብር ሚዛኑ አንድ አንድ ወቄት የሚሆን ሁለት ጉትቻ ለጆሮችዋ ፡

ወአውቃፈ ለእደዊሃ ዘዘዐሥሩ ሕልቅ ድልወቱ ፤

ሚዛኑ ዐሥር ዐሥር ወቄት የሚሆን አምባር ለእጅዎችዋ አደረገላት ፡

፳፫፡ ወተስእላ ወይቤላ ወለተ መኑ አንቲ ንግርኒ እስኩ ፤

የሆነስ ሆነና አንቺ የማን ልጅ ነሽ ? እስኪ ንገሪኝ ብሎ ጠየ ቃት፡

ለእመ ቦቱ ማኅደር ውስተ ቤተ አቡኪ ለነ ፤

ከአባትሽ ቤት ለኛ ማደሪያ ይገኝ እንደሆነ ንገሪኝ ? አላት፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ወትቤሎ ወለተ ባቱኤል አነ ወልደ ናኮር፣

እኔ የናኮር ልጅ የሚሆን የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችው ፤

፳፭፡ ወቦ ኀቤነ ማዕርኒ ወሐሰርኒ ወማኅደርኒ ለአግማሊከ ፣

ለግመሎችህም ማደሪያ፤ ማሩም ገፈራውም ገለባውም አለ አለችው ፤

፳፮፡ ወአደሞ ለውእቱ ብእሲ ወሰገደ ለእግዚአብሔር ፣

ኢያውብርም ደስ ብሎት ይህን በጎ ነገር ያሰማኸኝ ሲል ለእግዚአብሔር ሰገደ ፤

፳፯፡ ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለእግዚእየ አብርሃም ዘኢያውዕአ ለጽድቁ ወለርትዑ እምእግዚእየ ፣

ከጌታዬ ቸርነቱን ረድኤቱን ያላራቀ የጌታዬ የአብርሃም ፈጣሪ ይክበር ይመስገን አለ፤

ወሊተኒ ሠርሐኒ ፍኖትየ ውስተ ቤተ እኁሁ ለእግዚእየ አብርሃም ፣

ለኔም ወደ ጌታዬ ወንድም ቤት የመጣሁበትን ነገር ያቀናልኝ እርሱ ይክበር ይመስገን፤

፳፰፡ ወሖረት ይእቲ ወለት ወነገረት ለቤተ እማ ዘንተ ነገረ ፣

ያችም ልጅ ሄዳ ለእናትዋ ወገን ይህን ነገር ተናገረች ፤

፳፱፡ ወባቲ ለርብቃ እኁው ዘስሙ ላባ ፣

ለርብቃም ላባ የሚባል ወንድም ነበራት ፤

ወሮፀ ላባ ኀበ ዝኩ ብእሲ አፍአ ኀበ አዘቅት ፣

ላባም ስሱ ነበርና ይሰጠኛል መስሎት ከቤት ወጥቶ ኢያውብር ወዳለበት ወንዝ ሩጦ ሔደ፤

፴፡ ወሶበ ርእየ አዕኑጊሃ ወአውቃፊሃ ለእኅቱ ፣

ኢያውብር ለእኅቱ የሰጣትን ጉትቻዋን፣ አምባርዋን ባየ ጊዜ ማን ሰጠሽ ብሎ ጠየቃት ፤

ወትቤ ከመዝ ይቤለኒ ውእቱ ብእሲ፣

ያሰው እንዲህ አለኝ አለች ፤ ማለት የማን ልጅ ነሽ አለኝ፣ እኔም የባቱኤል ልጅ ነኝ አልሁት ፤ ከዚያ በኋላ ጉትቻውን ፣ አምባሩን ሰጠኝ አለችው ፤

ወበጽሐ ኀበ ውእቱ ብእሲ እንዘ ይቀውም ኀበ አዘቅት ፣

ኢያውብርም ከውሀ ዳር ተቀምጦ ሳለ ላባ ፈጥኖ ደረሰ ፤

፴፩፡ ወይቤሎ ነዓ ባእ ውስተ ቤት፣

ና ወደ ቤት እንግባ አለው ፤

ይትባረክ እግዚአብሔር ምንት ያቀውመከ አፍአ ፣

እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ምን አጥተን ከዚህ ከእዳሪ ትቀመጣለህ ?



ናሁ አስተዳለውነ ለከ ማኅደረ ፤ ወቤተ ለአግማሊከ ፣

አንተ የምትተኛበትን አልጋውን መከዳውን፤ ግመሎችህ የሚያድሩበትን ቤት አዘጋጅተናልና ተነሥ ወደ ቤት እንግባ አለው፤

፴፪፡ ወቦአ ውእቱ ብእሲ ወአብአ አግማሊሁ ፣

ኢያውብርም ግመሎቹን ይዞ ወደ ቤት ገባ ፤

ወአቅረቡ ሎሙ ሐሰረ ወማዕረ ለአግማሊሁ ፣

ለግመሎቹም ገፈራውን ገለባውን አቀረቡላቸው ፤

ወአምጽኡ ሎቱ ማየ ለእግሩ፤ ወለዕደው እለ ምስሌሁ ፣

ለርሱም፣ ከእርሱም ጋራ ላሉ ሰዎች እግራቸውን የሚታጠቡበት ውሀ አመጡላቸው ፤

፴፫፡ ወአምጽኡ ሎቱ ኅብስተ ዘይበልዕ ፣

የሚበላው ዳቦ ፣ እንጀራ ብላ ብለው አመጡለት ፤

ወይቤሎሙ ኢይበልዕ እስከ እነግር ቃልየ ፣

ኢያውብርም ነገሬን ሳልናገር አልበላም አለ ፤ (ሐተታ) ዛሬ የንጉሥ መልክተኛ የተላከውን ሳይናገር እህል ውሃ እንዳይቀምስ ፤

ወይቤልዎ ንግር ፣

እርሳቸውም ይሁን ነገርህን ተናገር አሉት ፤

፴፬፡ ወይቤሎሙ ገብረ አብርሃም አነ ፣

እርሱም እንዲህ አላቸው፣ እኔ ጥንቱን የአብርሃም ባሪያ ነኝ፤

፴፭፡ ወእግዚአብሔር ባረኮ ለእግዚእየ ጥቀ ወአዕበዮ ፣

እግዚአብሔርም ጌታዬ አብርሃምን እጅግ አከበረው አገነነው ፤

ወወሀቦ አልሕምተ ወአባግዐ ወወርቀ ወብሩረ አግብርተ ወአእማተ አግማለ ወአዕዱገ ፣

ላሙን በጉን ወርቁን ብሩን፣ ወንድ ባሪያውን ሴት ባሪያውን፣ ግመሉን አህያውን ሰጥቶ አከበረው ፤

፴፮፡ ወወለደት ሎቱ ሳራ ብእሲቱ ለእግዚእየ አብርሃም ወልደ በርሥዓን ፣

ሚስቱ ሳራ ሙቀት ልምላሜ ከተለያት በኋላ ለጌታዬ ለአብርሃም አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለት ነበር ፤

ወወሀቦ ኵሎ ዘቦቱ ሎቱ ፣

ያለውን ገንዘቡን ሁሉ ሰጥቶታል ፤

፴፯፡ ወአምሐለኒ እግዚእየ ወይቤለኒ ፣

ጌታዬ እንዲህ ብሎ አማለኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኢትንሣእ ለወልድየ ብእሲተ እምአዋልደ ከነዓን እለ አነድር አነ ምስሌሆሙ ፤

እኔ አብሬያቸው ከምኖር ከከነዓን ልጆች ለልጄ ሚስት አትጭለት ፤

፴፰፡ ዳዕሙ ሑር ውስተ ቤተ አቡየ፣ ወውስተ ነገድየ ወንሣእ ሎቱ ብእሲተ ለወልድየ እምህየ ፤

ወደ አባቴ ወገኖች፣ ወደ ዘመዶቼ ሒደህ ለልጄ ከዚያ ሚስት አጭተህ አጋባው እንጂ ብሎ አምሎኛል አላቸው ፤

፴፱፡ ወእቤሎ ለእግዚእየ የጊ ለእመ ኢፈቀደት ይእቲ ብእሲት መጺአ ምስሌየ ፤

እኔም ያች ሴት ከእኔ ጋራ መምጣትን ምናልባት ያልወደደች እንደሆነ እንዴት ላድርግ አልሁት ፤

፵፡ ወይቤለኒ እግዚእየ ፤

ጌታዬም እንዲህ አለኝ ፤

እግዚአብሔር ዘአሥመርኩ በቅድሜሁ ውእቱ ይፌኑ መልአኮ ቅድሜከ ወያሤኒ ፍኖተከ ፤

በፊቱ ያገለገልሁት እግዚአብሔር መልአኩን ሰዶ ነገርህን ያቀናልሃል ፤

ወትነሥእ ብእሲተ ለወልድየ እምህየ እምነገድየ ወእመ አኮ እምቤተ አቡየ ፤

ከዚያም ሂደህ ከዘመዶቼ፣ ይህም ባይሆን ከአባቴ ወገን ሚስት አጭተህ ታመጣለታለህ አለኝ፡

፵፩፡ ወይእቲ አሚረ ንጹሐ ትከውን እመሐላየ ፤

እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ፣ ያን ጊዜ ከመሐላዬ ንጹሕ ትሆናለህ ፤

ወእመሰ አበዩከ ውሂበ፣ ንጹሕ አንተ እመሐላ ፤

እነዚያ አንሰጥም ቢሉህ ግን የማልሁህ መሐላ አይደርስብህም አለኝ ፤

፵፪፡ ወሶበ በጻሕኩ ዝየ ነበ አዘቅተ እቤ ፤

እኔም ከዚህ ከወንዙ በደረስሁ ጊዜ እንዲህ አልሁ ፤

እግዚኦ አምላከ እግዚእየ አብርሃም ለእመ አንተ አውፃእከኒ ዮም በዛቲ ፍኖትየ እንተ አሐውር አነ ፤

አቤቱ የጌታዬ የአብርሃም ፈጣሪ ዛሬ እኔ በምሔድባት ጎዳና አንተ ወድደህ ካወጣኸኝ ፤

፵፫፡ ናሁ ቆምኩ መልዕልተ አዘቅተ ማይ፣

እነሆ ከወንዙ ዳር ግመሎቼን አራግፌ ተቀምጫለሁ ፤



ወአዋልደ ሰብአ ሀገር ይወፅአ ይቅድሓ ማየ ፤

የሀገሩ ሰዎች ሴቶች ልጆችም ውሀ ይቀዱ ዘንድ ይወጣሉ ፤

ወትኩን ይእቲ ድንግል እንተ አነ እብላ አስትዩኒ ማየ ሕቀ እምቀሱትኪ ፤

ከነዚያም አንዲቱ ከማድጋሽ ጥቂት ውሀ አጠጭኝ የምላት ድንግል ብትሆን ፤

፵፮፡ ወትቤለኒ ስተይ አንተኒ ወለአግማሊከኒ እቅዳሕ ፤

እርስዋም አንተ ጠጣ ግመሎችህንም ቀድቼ አጠጣቸዋለሁ የምትለኝ ድንግል ብትሆን ፤

ይእተ ብእሲተ አስተዳሎከ ለገብርከ ይስሐቅ እግዚኦ፣ ወቦቱ አአምር ከመ ገበርከ ምሕረተ ለእግዚእየ አብርሃም ፤

አቤቱ ለወዳጅህ ለይስሐቅ ይህችን ልጅ እንዳዘጋጀህለት ቸርነትህንም ለጌታዬ ለአብርሃም እንዳደረግህለት በዚህ አውቃለሁ አልሁ ፤

፵፭፡ ወኮነ ዘእንበለ አህልቅ ሐልዮ በልብየ ወበጊዜሃ ወፅአት ርብቃ ወተፀውር ቀሱታ ፤

ይህንን በልቤ ያሰብሁትን ሳልናገረው፣ ተናግሬም ሳልጨርሰው፣ ርብቃ ማድጋዋን ይዛ መጣች ፤

ወወረደት ውስተ አዘቅት ወቀድሐት ማየ ፤

ወደ ወንዝ ወርዳ ውሀውን ቀዳች ፤

ወእቤላ አስትዩኒ ማየ ፤

እኔም ውሃ አጠጭኝ አልኋት ፤

፵፮፡ ወአውረደት ቀሱታ ፍጡነ ወትቤለኒ ስተይ አንተኒ ፤

እርስዋም እንስራዋን ፈጥና አውርዳ ጠጣ አለችኝ ፤

ወሰተይኩ፣ ወአግማልየኒ ሰትዩ ፤

እኔም ጠጣሁ ፣ ግመሎቼም ጠጡ ፤

፵፯፡ ወተስእልክዋ ወእቤላ ወለተ መኑ አንቲ ንግርኒ ፤

እኔም አንቺ የማን ልጅ ነሽ ንገሪኝ ብዬ ጠየቅኋት ፤

ወትቤለኒ ወለተ ባቱኤል አነ፣ ወልደ ናኮር ዘወለደት ሎቱ ሚልካ ፤

እርስዋም እኔ ሚልካ ለናኮር የወለደችለት የባቱኤል ልጅ ነኝ አለችኝ ፤

ወይእተ ጊዜ ሶበ ሰማዕኩ ዘንተ እምአፉሃ አደመተኒ ጥቀ ፤

ያንጊዜ ይህን ነገር ከእርስዋ በሰማሁ ጊዜ እጅግ ደስ አሰኘችኝ ፤

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ፳ወ፭

## ግባኤ

፩፡ ወደገመ አብርሃም አውስቦ ብእሲት እንተ ስማ ኬጡራ ።

አብርሃም ኬጡራ የምትባል ሚስት ዳግመኛ አገባ፤ ደገመ ማለቱ ለሳራ አይደለም ለአጋር ነው እንጂ ፤

፪፡ ወወለደት ወልደ ዘስሙ ዘንበሬ፣ ወዮቃጢንሃ፣ ወሜዶንሃ፣ ወዮብቅሃ፣ ወምድያምሃ፣ ወሴሂሃ ።

ኬጡራም፣ ዘንበሬን፤ ዮቃጢንን፤ ሜዶንን፤ ዮብቅን፤ ምድያምን፤ ሴሂንን ወለደች ፤

፫፡ ወዮቃጢንሂ ወለዶሙ ለሶቤቅ፤ ወለቴማን፤ ወለዱዳን ።

ዮቃጢንም ሶቤቅን፣ ቴማንን፣ ዱዳንን ወለደ ፤

ወዱዳን ወለዶሙ ለራጉኤል ወለእንባብዮ፣ ወለእስራዓም፣ ወለሉዓም፣

ዱዳንም ራጉኤልን ፣ እንባብዮን ፣ እስራዓምን ፣ ሉዓምን ወለደ ፤

፬፡ ወደቂቀ ምድያም ጌፌር ፣ ወኤፋር፣ ወሂኖህ፣ ወአቤሮን፣ ውቴያርሰ፣

የምድያምም ልጆች ጌፌር ፣ ኤፋር፣ ሂኖኅ፣ አቤሮን፣ ቴያርሰ ናቸው ፤

እሉ ኵሎሙ ደቂቀ ኬጡራ ።

እሊህ ሁሉ የኬጡራ ልጆች፣ የልጅ ልጆችዋ ናቸው ፤

፭፡ ወወሀቦ አብርሃም ኵሎ ንዋዮ ለይስሐቅ ወልዱ በሕይወቱ ።

አብርሃምም በሕይወቱ ሳለ ሳይሞት ገንዘቡን ሁሉ ለልጁ ለይስሐቅ ሰጠው ፤

፮፡ ወለደቂቀ ዕቁባቲሁ ወሀቦሙ አብርሃም ሀብተ ።

አብርሃም ከአጋርና ከኬጡራ ለወለዳቸው ልጆቹም እንዳይጣሉ ብሎ ፋንታ ፋንታቸውን ሰጥቶ ፤

ወፈነዎሙ እምገጸ ይስሐቅ ወልዱ ውስተ ምድር ዘመንገለ ምሥራቅ፣

ከልጁ ከይስሐቅ ለይቶ በምሥራቅ በኩል ወዳለው አገር ሰደዳቸው ፤

፯፡ ወዝንቱ ውእቱ ሕይወቱ ለአብርሃም ።

አብርሃም በዚህ ዓለም የኖረው ዘመን ይህ ነው ፤

ወዓመቲሁኒ ምእት ወሰብዓ ወኃምስቱ ።

ሕይወቱ ያለውን ዓመቲሁ ብሎ አመጣው፤ ይኸውም መላ ዘመኑ መቶ ሰባ አምስት ዘመን ነው፤

፰፡ ወረሲያ ጥቀ ሠናየ ርስዓ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ ሞተ አብርሃም፣

አብርሃምም በጎ እርጅና አርጅቶ ማለት የሚበላው የሚ



ጠጣው ሳያጣ ዘመኑን ፈጽሞ ሞተ ፤

ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ።

ከእርሱ አስቀድሞ ወደ ሞቱት ወገኖቹ በሞት ተጨመረ ፤

፱፡ ወቀበርዎ ይስሐቅ ወይስማኤል ደቂቁ ውስተ በአተ ካዕበት ዘገራህተ ኤፍሮን ዘሡዓር ኬጥያዊ ዘአንጻረ ምንባሬ ።

አብርሃም ወምበሩን ዘርግቶ በተቀመጠባት አንጻር ባለች በኬጢ ሰው በሠዓር ልጅ በኤፍሮን እርሻ መካከል ባለች እዕፍነት ባላት ዋሻ ልጆቹ ይስማኤልና ይስሐቅ ቀበሩት ፤

፲፡ ዘተሣየጣ አብርሃም እምደቂቀ ኬጢ ።

ይህችም ቦታ አብርሃም ከኬጢ ልጆች በአራት መቶ ምዝምዝ ብር የገዛት ናት ፤

ወህየ ቀበርዎ ለአብርሃም ወለሳራ ብእሲቱ ።

አብርሃምን ከሚስቱ ከሳራ ጋር ከዚያ ቀበሩት ፤

፲፩፡ ወኮነ እምድኅረ ሞተ አብርሃም ።

አብርሃም ከሞተ በኋላ እንዲህ ሆነ ፤

ባረኮ እግዚአብሔር ለይስሐቅ ወልዱ።

እግዚአብሔር የአብርሃምን ልጅ ይስሐቅን አከበረው ፤

ወኃደረ ይስሐቅ መንገለ አዘቅተ ራእይ ።

ይስሐቅም እግዚአብሔር በታየው በተነጋገረው ቦታ ኖረ ፤

፲፪፡ ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለይስማኤል ወልደ አብርሃም ዘወለደት ሎቱ አጋር አመተ ሳራ ።

የሳራ ባሪያ አጋር ለአብርሃም የወለደችለት የይስማኤል ትውልዱ እንዲህ ነው ፤

፲፫፡ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ይስማኤል በኵሩ ናቡዓት፣

የይስማኤል ልጆችም ስማቸው ይህ ነው የበኸር ልጁ ናቡዓት ይባላል ፤

ወካልኡ ቄዳር፣

ሁለተኛውም ቄዳር ይባላል ፤ ይህ የዘላኖች አባት ነው ፤

፲፬፡ ወናብዳሄል ወመብስን ።

ሦስተኛው ናብዳሄል አራተኛው መብስን ነው ፤

፲፭፡ ወማሴሜ፣ ወዱማ፣ ወማሴን፣ ወኩዳ፣ ወቴማ፣ ወኢያጤር፣ ወናፌስ፣ ወቄዳን ።

አምስተኛው ማሴሜ ፤ ፮ኛው ዱማ ፤ ፯ኛው ማሴን ፤ ፰ኛው ኩዳ ፤ ፱ንኛው ቴማን ፤ ፲ኛው ኢያጤር ፤ ፲፩ኛው ናፌስ ፲፪ኛው ቄዳን ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ይስማኤል፤

እነዚህ ሁሉ የይስማኤል ልጆች ናቸው ፡

ወዝ ውእቱ አስማቲሆሙ በበሀገሮሙ ወበበማኅበሮሙ ፤ ወበበብሔሮሙ ፤ ወበበሕዘቢሆሙ ፤

በየሀገራቸው፤ በየሸንጎአቸው፤ በየመንደራቸው፤ በየወገናቸው የሚጠሩበት ስማቸው ይህ ነው፡

ወዐሠርቱ ወክልኤቱ መሳፍንት ፤

እነዚህም ዐሥራ ሁለት ነገድ ናቸው ፡

፲፯፡ ወኃደረ እምኤውላጥ እስከ ሲይር እንተ ውስተ ግብጽ ፤

ይስማኤል ከልጆቹ ጋራ ከኤውላጥ ጀምሮ በግብጽ ወሰን እስካለች እስከ ሲይር ድረስ ወርሶ ኖረ ፡

ወበጽሐ ውስተ አሶርዮን ወኀደረ ቅድመ ገጸ ኵሉ አኃዊሁ ፤

አሦርዮን እስከሚባል ሀገር ደርሶ በወንድሞቹ በግብጻውያን ፊት ለፊት ኖረ ፡

፲፰፡ ወዝውእቱ ዓመተ ሕይወቱ ለይስማኤል ፤ ምእት ወሠላሳ ወሰብዓቱ ዓመት ፡

ይስማኤል በሕይወት የኖረው ዘመን መቶ ሠላሳ ሰባት ዓመት ነው ፡

ወሞተ ረሲዖ ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ፤

ዕድሜውን ፈጅቶ አርጅቶ ሙቶ ዘመዶቹ በተቀበሩበት መቃብር ተቀበረ ፡

፲፱፡ ወከመዝ ውእቱ ልደቱ ለይስሐቅ ወልደ አብርሃም ፤

የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ልደቱም እንዲህ ነው ፡ (ሐተታ) የይስማኤልን በፊት፤ የይስሐቅን በኋላ ስለምን አደረገው ቢሉ ፡ መጽሐፍ ትቶት የሚሄደውን በፊት፤ ይዞት የሚሄደውን በኋላ ማምጣት ልማዱ ነው፡ አሁንም ይዞት የሚሄደው ይስሐቅን ነውና የይስማኤልን በፊት፤ የይስሐቅን በኋላ አደረገው፡ የቀረው ሐተታ እንዳለፈው ነው ፡

፳፡ ፵ዓ ዓመቱ አመ ነሥአ እማእከለ አፍላግ ዘሶርያ ለርብቃ ወለተ ባቱኤል ሶርያዊ እኅቱ ለላባ ከመ ትኩኖ ብእሲተ ፤

የላባ እኅት የምትሆን በሶርያ ወንዞች መካከል የሚኖር የሶርያውን ሰው የባቱኤልን ልጅ ርብቃን ሚስት ልትሆነው ባገባ ጊዜ ፤ የይስሐቅ ዕድሜ አርባ ዘመን ሁኖ ነበር ፡

፳፩፡ ወሰአለ ይስሐቅ ኀበ እግዚአብሔር በእንተ ርብቃ ብእሲቱ እስመ መካን ይእቲ ፤

ይስሐቅም ሚስቱ ርብቃ መካን ስለሆነች ልጅ ስጣት ብሎ ወደ



እግዚአብሔር ለመነ ፡ ደርሶ ባት መከናለች ማለት አይደለም፤ መካን እንዳትሆን ለመነ፡ ሃያ ዘመን ሳይወልዱ ኑረው፤ ይስሐቅ ስድሳ ዘመን ሲሆነው ባንድ ቀን ፋካቤ ፤ ኤሳውና ያዕቆብ ተወልደዋል፡

ወሰምዖ እግዚአብሔር ወጸንሰት ርብቃ ፤

እግዚአብሔርም ልመናውን ሰምቶ ርብቃን እንድትጸንስ አደረጋት ፡

፳፪፡ ወይትሐወሱ ደቂቃ በውስተ ከርሣ ፤

ኤሳውና ያዕቆብ በእናታቸው ማኅጸን ሳሉ ይጣሉ (ይንቀሳቀሱ) ነበር ፡

ወትቤ እመሰ ሀለወኒ እኩን ከመዝ ለምንት ሊተ ዝንቱ ፤

ርብቃም እየተነዋወጡ ቢያውኳት እንዲህ የምሆን ከሆነ እንዲህ ያለ ነገር ለምኔ ነው አለች ፡

ወሖረት ትሰአል ኀበ እግዚአብሔር፤

የሚጸልዩበት ልዩ ቦታ አላቸውና እግዚአብሔርን ወደምትለምንበት ቦታ ተነሥታ ሄደች፡ አንድም ትስአል ይላል አብነት፤ ቃለ እግዚአብሔር ልትጠይቅ ሄደች ፡

፳፫፡ ወይቤላ እግዚአብሔር ክልኤቱ ሕዝብ ሀለዉ ውስተ ከርሥኪ ፤

እግዚአብሔር በመልአኩም አድሮ ቢሉ በመልከ ጼዴቅም አድሮ ቢሉ እንዲህ አላት ፤ ሁለት ልጆች በማኅጸንሽ አሉ ፡

ወክልኤቱ ሕዝብ ይወፅኡ እምከርሥኪ ፤

ሁለቱም ልጆች ካንቺ ይወለዳሉ ፡

ወሕዝብ እምሕዝብ ይኄይስ ፤

አንዱ ካንዱ ይበልጣል ፡

ወዘየዐቢ ይትቀነይ ለዘይንእስ ፤

ትልቁ ለትንሹ ይገዛል አላት፡ (ሐተታ) እንደዚህም ሁሉ ፡ «ወልድየ ዘበኵርየ» የተባሉ እስራኤል ኢይባእ ሞዓባዊ ወአሞናዊ ለተባሉ ለአሕዛብ ይገዛሉ ሲል ነው ፤ እንከሰ ብኵርና ለነ ወአኮ ለአይሁድ እንዲል ፡

፳፬፡ ወሶበ ተፈጸመ መዋዕለ ወሊዶታ ፤

የምትወልድበት ቀን በደረሰ ጊዜ ፡

ወክልኤቱ ሀለዉ ውስተ ከርሣ ፤

በማኅፀንዋ ሁለት ልጆች ተጸንሰው ነበር፡ (ትችን) የምትወልድበት ቀን በደረሰ ጊዜ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፳፭፡ ወወፅአ ወልዱ ዘበኵሩ፡ ወቀይሕ ኵለንታሁ ከመ ጽጌረዳ ወፀጕር፤

እንደ ጽጌረዳ አበባ ሁለንተናው ቀይ የሆነ፤ ሰውነቱም ሁሉ ፀጕር (ጠጉራም) የሆነ የበኵር ልጅዋ ኤሳው ተወለደ ፡

ወሰመየቶ ስሞ ኤሳው ፤

ስሙንም ኤሳው አለችው ፡ (ሐተታ) ኤሳው ማለት ፈታዊ ፤ ነዓዊ ፤ ሀላዊ ማለት ነው ፡

፳፮፡ ወእምድኅሬሁ ወፅአ እኁሁ ወይእኅዝ በእዴሁ ሰኰና ኤሳው ፤

ከዚህም በኋላ ወንድሙ የኤሳውን ሰኰና እንደያዘ ተወለደ፤

ወበእንተዝ ሰመየቶ ስሞ ያዕቆብ ፤

ስለዚህ ነገር ስሙን ያዕቆብ አለችው፤ አዕቃጺ ማለት ነው ፡

ወ፷ ዓመቱ ለይስሐቅ አመ ወለደቶሙ ርብቃ ለኤሳው ወለያዕቆብ ፤

ርብቃም ኤሳውንና ያዕቆብን በወለደቻቸው ጊዜ ለይስሐቅ ስድሳ ዘመን ሆኖት ነበር ፡

፳፯፡ ወልሕቁ ወኮኑ ወራዙተ ፤

ኤሳውና ያዕቆብም አደጉ ጐለመሱ ፡

ወኮነ ኤሳው ብእሴ ሐቅል ነዓዌ ፤

ኤሳው ከዱር እየሄደ የሚያድን አርበኛ ሆነ ፡

ወያዕቆብሰ ንጹሕ ውእቱ ወይነብር ውስተ ቤት ፤

ያዕቆብ ግን ከቤት የሚውል ድልድል ቅምጥል ነበር ፡

፳፰፡ ወያፈቅሮ ይስሐቅ ለኤሳው እስመ ውእቱ ዘነሀወ ይሴሰይ ፤

ይስሐቅም ኤሳውን ይወደው ነበር፤ ከዱር ዐድኖ ያመጣውን ይመገብ ነበርና ፡

ወርብቃሰ ታፈቅሮ ለያዕቆብ ፤

ርብቃ ግን ከኤሳው ይልቅ ያዕቆብን ትወደው ነበር ፡

፳፱፡ ወአብሰለት ሎቱ ተብሲለ ፤

ምሥር ንፍሮ ቀቀለችለት ፤ አንድም እንደ እንፍርፍር ሽሮ ያለ ሠራችለት ፡

ወመጽአ ኤሳው እምሐቅል እንዘ ይደክም ፤

ኤሳውም ዓደን ውሎ ከዱር መጣ ፡

፴፡ ወይቤሎ ኤሳው ለያዕቆብ አብልዐኒ እምተብሲልከ ፤

ኤሳው ያዕቆብን ከምትበላው ንፍሮ ስጠኝ አለው ፡

እስመ ደከምኩ ጥቀ፤

ርቦኝ እጅግ ደክሜያለሁና ፡

ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስሙ ኤዶም፤

ስለዚህም ስሙ ኤዶም ተባለ፤ ፈታዊ ማለት ነው ፡



፴፩፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለኤሳው አግብእኬ ሊተ ብኵርናከ ፤

ያዕቆብም ኤሳውን እልቅናህን ስጠኝ አለው ፡

፴፪፡ ወይቤሎ ኤሳው ናሁ እመውት ለምንት ሊተ ከዊነ በኵር ፤

ኤሳውም እኔ በረሀብ ስሞት በኵር መሆን ምን ያደርግልኛል? እልቅናው ምን ይረባኛል? ያውልህ ውሰደው አለው ፡

፴፫፡ ወይቤሎ ያዕቆብ መሐልኬ ሊተ ዮም ከመ ታግብእ ሊተ ብኵርናከ፤

ያዕቆብም የነገር መጨረሻ መሐላ ነውና እልቅናህን ልትሰጠኝ አሁን ማልልኝ አለው ፡

ወመሐለ ሎቱ ኤሳው ወአግብአ ሎቱ ከዊነ በኵር ፤

ኤሳውም ምሎ እልቅናውን ለያዕቆብ ሰጠው ፡

፴፬፡ ወወሀቦ ያዕቆብ ለኤሳው ኅብስተ ወተብሲለ ብርስን ፤

ከማለለትም በኋላ ዳቦውን ንፍሮውን ሰጠው፤ አንድም ሽሮውን በእንጀራ አድርጎ ሰጠው ፡

ወበልዐ ወሰትየ ወተንሥአ ወሖረ ፤

ኤሳውም በልቶ ጠጥቶ ተነሥቶ ሔደ፤ (ሐተታ) ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ኤሳው የአይሁድ፤ ያዕቆብ የምእመናን አሕዛብ ምሳሌ ፡ ኤሳው መብሉን ወዶ እልቅናውን እንደ ሸጠ፤ አይሁድም መሥዋዕተ ኦሪትን ወደው ብኵርናቸውን ለምእመናን አሕዛብ አሳልፈው ስጥተዋልና የዚህ ምሳሌ ነው ::

## ምዕራፍ ፳ወ፮

፩፡ ወኮነ ካልዕ ረሀብ ውስተ ብሔር ዘእንበለ ረሀብ ዘኮነ በመዋዕለ አብርሃም ፤

በአብርሃም ዘመን ከተደረገው ረሀብ ሌላ በከነዓን ረሀብ ጸና ፡

ወሖረ ይስሐቅ ኀበ አቤሜሌክ ንጉሠ ፍልስጥኤም ውስተ ጌራራ ፤

ይስሐቅም የፍልስጥኤም ንጉሥ ከሚሆን ከአቤሜሌክ ዘንድ ወደ ጌራራ ሔደ ፡

፪፡ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔር ለይስሐቅ ተገልጾ እንዲህ አለው ፡

ኢትረድ ውስተ ግብጽ ፤

ወደ ግብጽ አትውረድ ፡

ወኅድር ውስተ ምድር እንተ አነ እቤለከ ፤

እኔ በነገርኩህ ሀገር በከነዓን ኑር እንጂ ፡

፫፡ ወንበር ውስተ ይእቲ ምድር ፤

በዚያችም አገር ኑር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአሐውር ምስሌከ ወእባርከከ፣

እኔም ካንተ ጋራ በረድኤት እኖራለሁ ፣ ፈጽሜም አከብር ሃለሁ ፤

እስመ ለከ ወለዘርእከ እሁባ ለዛቲ ምድር ፣

ከነዓንን ላንተም ለልጆችህም አወርሳታለሁና ፤

ወአቀውም ምስሌከ መሐላየ ዘመሐልኩ ለአብርሃም አቡከ ፣

ለአባትህ ለአብርሃም የማልሁለትን መሐላዬን ላንተም አጸና ልሃለሁና ፤

፬፤ ወአበዝኆ ለዘርእከ ከመ ኮከበ ሰማይ ፣

ልጅህን የልጅ ልጅህን እንደ ሰማይ ኮከብ አበዛዋለሁ ፤

ወእሁብ ለዘርእከ ኵሉ ዛተ ምድረ፣

ለልጆችህም ከነዓንን ፈጽሜ አወርሳታለሁ ፤

ወይትባረኩ በዘርእከ ኵሉ አሕዛበ ምድር ፣

አሕዛብ ሁሉ በልጅህ ይመራረቃሉ ፤ (ሐተታ) እስራኤልን ያከበረ አምላክ ያክብርህ እየተባባሉ፤ አንድም ምእመናን አሕዛብ ፣ በልጅህ በክርስቶስ ይከብራሉ ፤

፭፤ እስመ አብርሃም ሰምዐ ቃለ ዚአየ ፤ ወዐቀበ ትእዛዝየ ወኵነኔየ፣ ወሕግየ ፣

አብርሃም የኔን ቃል ሰምቶ በሕገ ልቡና ኢታምልክንና ዘጠኙን ቃላት ሥርዓቴንም ጠብቆ አልና ፤

፮፤ ወነበረ ይስሐቅ ውስተ ጌራራ፣

ይስሐቅም በጌራራ ኖረ ፤

፯፤ ወተስእልዎ ሰብአ ብሔር ለይስሐቅ በእንተ ርብቃ ብእሲቱ ፣

የጌራራም ሰዎች ይስሐቅን ስለ ሚስቱ ስለ ርብቃ ነገር ምንህ ናት ብለው ጠየቁት ፤

ወይቤሎሙ እኅትየ ይእቲ ፣

እርሱም እኅቴ ናት አላቸው ፤

እስመ ፈርሀ አይድዮቶሙ ከመ ብእሲቱ ይእቲ ከመ ኢይቅትልዎ ሰብአ ውእቱ ብሔር በእንተ ርብቃ ብእሲቱ እስመ ሠናይ ገጻ ፣

ሚስቱ ርብቃ መልከ መልካም ስለ ሆነች ፣ በርስዋ ምክንያት የዚያች አገር ሰዎች እንዳይገድሉት ሚስቴ ናት ብሎ መናገርን ፈርቶአልና እኅቴ ናት አለ፤

፰፤ ወነበረ ህየ ብዙኀ መዋዕለ፣

ይስሐቅም በጌራራ ብዙ ዘመን ኖረ ፤



ወሶበ ሐወጸ አቤሜሌክ እንተ መስኮት ርእዮ ለይስሐቅ እንዘ ይትዋነይ ምስለ ርብቃ ብእሲቱ ፣

አቤሜሌክም በመስኮት ሆኖ በተመለከተ ጊዜ፣ ይስሐቅ ከሚስቱ ከርብቃ ጋራ የባልና የሚስት ጨዋታ ሲጫወት አይቶ፤

፱፤ ወጸውዖ አቤሜሌክ ለይስሐቅ ወይቤሎ ናሁ ብእሲትከ ይእቲ ወትቤለኒ እኅትየ ይእቲ ፣

አቤሜሌክ ይስሐቅን ጠርቶ እኅቴ ናት ብለኸኝ አልነበረምን እነሆ ሚስትህ ናትሳ አለው ፤

ወይቤሎ ይስሐቅ እስመ እቤ ይቀትሉኒ በእንቲአሃ ፣

ይስሐቅም በርስዋ ምክንያት ይገድሉኛል ብዬ ነው እንጂ አምን ሚስቴ ናት አለው ፤

፲፤ ወይቤሎ አቤሜሌክ ምንትኑ ዝንቱ ዘረሰይከኒ ፣

አቤሜሌክም ይህ ያደረግህብኝ ነገር ምንድን ነው ? አለው ፤

ሕቀ ክመ ዘእምሰከበ ምስለ ብእሲትከ ብእሲ ዘእምአዝማድየ ፣

ከዘመዶቼ ወገን የሚሆን አንድ ሰው ሚስትህን ሊደርስባት ጥቂት ብቻ ቀርቶት ነበረ አለው፤ (ሐተታ) ራሱን አርቆ ይናገራል ፤ እኔ ሚስትህን ልደርስባት ጥቂት ቀርቶኝ ነበር ሲል ነው ፤

ወአምጻእከ ኃጢአተ ላዕሌየ በኢያእምሮ ፣

አንተም በኔ ላይ ባለማወቅ ጽኑ ኃጢአት ልታመጣብኝ ነበር፣ እንዲህ ያለ ነገር ያደረግኸው ለምንድን ነው? ብሎ ተቈጣው፤

፲፩፤ ወአዘዞሙ ንጉሥ ለኵሎሙ ሕዘቢሁ ወይቤሎሙ ፣

ከዚህም በኋላ ንጉሡ ሠራዊቱን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፤

ኵሉ ዘሰሐጦ ለዝንቱ ብእሲ ሞተ እኩይ ኵነኔሁ ፣

ይህን ሰው የተጣላ ሰው ሁሉ ይሙት በቃ ይፈረድበታል አላቸው ፤

፲፪፤ ወዘርዐ ይስሐቅ ውስተ ይእቲ ምድር ፣

ይስሐቅም በጌራራ ዘር ዘራ ፤

ወኮና ምእተ ምክዕቢተ ፣

መቶ ዕዕፍ ሆነለት ማለት ያለ መጠን በረከተለት ፤

ወባረኮ እግዚአብሔር ፣

እግዚአብሔርም አከበረው ፤

፲፫፤ ወተለዐለ ወዐብየ ጥቀ ፣

እርሱም እጅግ ከበረ ገነነ ፤

፲፬፤ ወአጥረየ አግብርተ ወአዕማተ አባግዐ ወአልሕምተ ብዙኀ ፣

ወንድ ባሪያ፣ ሴት ባሪያ፣ በጉን ላሙን አብዝቶ ገዛ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወቀንዑ ላዕሌሁ ሰብአ ፍልስጥኤም፤

የፍልስጥኤምም ሰዎች በመክ በሩ ቀኑበት ፡

፲፭፡ ወእነኮሰሙ ዐዘቃት ዘከረዩ ደቀ አብርሃም በመዋዕለ አቡሁ ደፈ ንዎሙ ሰብአ ፍልስጥኤም ወመልዕ ዎሙ መሬተ ፤

በአባቱ ዘመን የአብርሃም ብላ ቴዎች የቈፈሩትን ምንጭ ሁሉ፡ የፍልስጥኤም ሰዎች መሬቱን እየመሉ ደፈኑዋቸው ፡

፲፮፡ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለይስሐቅ፣ ሑር እምኔነ እስመ ጸናዕከነ ጥቀ፤

አቤሜሌክም ይስሐቅን እጅግ በርትተህብናልና ከኛ ተለይተህ ወደ ሀገርህ ሂድ አለው ፡

፲፯፡ ወሖረ እምህየ ይስሐቅ ውነደረ ውስተ ቈላተ ጌራራ ወነበረ ህየ ፤

ነደረና ነበረ አንድ ወገን ፡ ይስሐቅም ከዚያ ተነሥቶ ሄዶ ጌራራ በሚባል ቈላ ተቀመጠ፡

፲፰፡ ወካዕበ ከረዮን ይስሐቅ ለዓዘ ቃተ ማይ ዘከረዩ አግብርተ አቡሁ አብርሃም ዘደፈንዎን ሰብአ ፍልስ ጥኤም እምድኅረ ሞተ አብርሃም አቡሁ ፤

ይስሐቅም የአባቱ ባሮች የቈ ፈሩዋቸውን አባቱ አብርሃም ከሞተ በኋላም የፍልስጥኤም ሰዎች የደፈኑዋቸውን ምንጮች እንደገና ቈፈራቸው ፡

ወሰመዮን በበአስማቲሆን በከመ ሰመ ዮን አብርሃም ፤

አብርሃም እንደጠራቸው በየስ ማቸው ቤርሳባዕ ቤርሳቤህ እያለ ጠራቸው ፡

፲፱፡ ወከረዩ አግብርተ ይስሐቅ ዓዘ ቅተ በቈላተ ጌራራ ወረከቡ ነቅዐ ማይ ጥዑመ ፤

የይስሐቅም ባሮች አብርሃም ከቈፈረው ሌላ፣ በጌራራ አው ራጃ ቈፍረው የሚጣፍጥ ውሀ አገኙ ፡ አንድም የጠራ ውሀ አገኙ ፡

፳፡ ወተበዓሱ ኖሎተ ይስሐቅ ወኖ ሎተ ጌራራ ወይቤሉ ዚአነ ውእቱ ማይ ፤

የይስሐቅ እረኞችና የጌራራ ሰዎች እረኞች፣ ይህ ውሀ የኛ ነው፣ የኛ ነው በማለት ተጣሉ፡

ወሰመየ ስማ ለይእቲ ዓዘቅት ዓዘ ቅተ ዐመፃ ፤

የተጣሉባትንም ምንጭ ዓዘቅተ ግፍዕ አላት፣ የተበደልሁባት ማለት ነው ፡

እስመ ዐመፅዎ ፤

የጌራራ ሰዎች በድለውታልና፡

፳፩፡ ወግዕዘ እምህየ ይስሐቅ ወከረየ ካልእተ ዓዘቅተ በህየ ፤

ይስሐቅም ከሰፈረበት ተገፋ ሄዶ በዚያ ሁለተኛ ምንጭ ቈፈረ፡



ወተሳነንዎ በእንቲአሃ ፤

በርስዋም ምክንያት የጌራራ ሰዎች ተጣሉት ፡

ወሰመያ ስማ ዓዘቅተ ጽልእ ፤

ስምዋንም ዓዘቅተ ጽልእ አላት፣ የተጣላሁባት ምንጭ ማለት ነው ፡

፳፪፡ ወግእዘ እምህየ ወከረየ ዓዘቅተ ወኢተበዐስዎ በእንቲአሁ ፤

ከዚያም ተገፋ ምንጭ ቈፈረ፡ በርሱ ምክንያት ግን አልተጣ ሉትም ፡

ወሰመይዎ ስሞ መርኅብ ፤

ስሙን ሰፊ ውሀ አለት ፡ አን ድም ተድላ ደስታ አለት ፡ አንድም ስሙን ዓዘቅተ ፍቅር አለት ፡

እንዘ ይብሉ እስመ አርኀበ ለነ እግዚአብሔር ይእዜ ፤

እግዚአብሔር አገሩን አስፍቶ ሰጥቶናልና፡ አንድም ተድላውን ደስታውን አብዝቶ ሰጥቶናልና፡ አንድም ከጌራራ ሰዎች እንድ ንፋቀር አድርጎናልና ሲሉ ዐዘ ቅተ ፍቅር አለት ፡

ወአብዝኀነ ውስተ ምድር ፤

እኛንም አብዝቶናልና ሲሉ መር ኅበ አለት ፡

፳፫፡ ወግእዘ እምህየ ኀበ ዐዘቅተ መሐላ፤

ከዚያም ተነሥቶ ወደተማማሉ በት ምንጭ ተጓዘ ፡

፳፬፡ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር በይ እቲ ሌሊት ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔርም በዚያች ሌሊት ይስሐቅን ታየው ተነጋገረው ፤ እንዲህም አለው ፡

ነየ አነ ውእቱ አምላኩ ለአብርሃም አቡከ ኢትፍራህ ሀሎኩ ምስሌከ ፤

የአባትህ የአብርሃም ፈጣሪ እኔ እነሆ ካንተ ጋራ በረድኤት አለ ሁና አትፍራ ፡

ወእባርከከ ወአበዝኁ ለዘርእከ በእንተ አብርሃም አቡከ ፤

ስለ አባትህ ስለ አብርሃም ብዬ አከብርሃለሁ ፡ ልጅህን የልጅ ልጅህንም አበዛዋለሁ አለው፡

፳፭፡ ወነደቀ በህየ ምሥዋዐ ለእግዚ አብሔር አምላኩ ፤

በዚያም ለፈጣሪው ለእግዚአብ ሔር መሥዋዕት የሚሠዋበትን ምሥዋዕ ሠራ ፡

ወጸውዐ ስመ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን አመሰገነ ፡ አንድም ቃለ እግዚአብሔርን ጠየቀ ፡

ወተከለ በህየ ዐፀደ ፤

መሠዊያ ከሠራበትም ቦታ ድን ኳን ተከለ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወከረዩ በህየ ደቂቀ ይስሐቅ ዐዘቅተ፤
የይስሐቅ ብላቴኖችም ከዚያ የውሀ ጕድጓድ ቈፈሩ ፤

፳፮፡ ወሖሩ ኀቤሁ እምጌራራ አቤሜሌክ ወአኮዘት ፣ መጋቤ መራዕይሁ ወፋኮል መልአከ ሠርዌሁ ፣
ንጉሡ አቤሜሌክ ፣ ሳም ራሱ (የመንጋው ሹም) አኮዘት፣ ቢት ወደዱ ፋኮል ሆነው ከጌራራ ተነ ሥተው ይስሐቅ ወዳለበት ሄዱ፤

፳፯፡ ወይቤሎሙ ይስሐቅ ለምንት መጻእክሙ ኀቤየ እምድኅረ ጸላእክሙኒ ወአስቈረርክሙኒ ወሰደድክሙኒ እምኀቤክሙ ፣
ይስሐቅም ጠልታችሁ፣ ተመቀኝታችሁ፣ ከናንተ ለይታችሁ ከሰደዳችሁኝ በኋላ ወደኔ ለምን መጣችሁ ? አላቸው ፤

፳፰፡ ወይቤልዎ ኢስመ አኮ ንሕነ ዘአስቈረርናከ ፣
እኛ የጠላንህ የተመቀኘንህ አይደለንም ፤
አላ አንበርናከ ሠናየ ወፈነውናከ በሠናይ ፣
አክብረን አኑረን በተድላ በደስታ ሸኝተን ሰደድንህ እንጂ የተመቀኘንህ፣ የጠላንህ አይደለንም አሉት ፤
ወይእዜኒ ቡሩክ አንተ ለእግዚአብሔር አምላክ ፣
አሁንም ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አንተ ክቡር (ደግ) ፍጥረት ነህ ፤

፳፱፡ ወሶበ ርኢነ ከመ ሀሎ እግዚአብሔር አምላክ ምስሌከ ፣
ፈጣሪህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋራ በረድኤት እንዳለ ባወቅን ጊዜ ፤
ወንቤ ከመ ይኩን ማዕከሌከ ወማዕከሌነ መሐላ ፣
ባንተና በኛ መካከል መሐላ ይደረግ ማለት ፤ አንተና እኛ እንማማል ብለን መጥተናል አሉት ፤
ወንትማሐል ከመ ኢትግበር እኩየ ላዕሌነ ወኢንግበር እኩየ ላዕሌከ ፣
አሁንም አንተ በእኛ ክፉ ነገር እንዳታደርግ፣ እኛም በአንተ ላይ ክፉ ነገር እንዳናደርግ እንማማል አሉት ፤

፴፡ ወገብረ ሎሙ ማዕደ ወበልዑ ወሰትዩ ፣
ማዕድ አቀረበላቸው በሉ ጠጡ፤ (ሐተታ) የፍቅር ምልክት ነው፤

፴፩፡ ወተንሥኡ በጽባሕ ወተማሐሉ በበይናቲሆሙ ፣
ማለዳ ተነሥተው እርስ በርሳቸው ተማማሉ ፤
ወፈነዎሙ ይስሐቅ፣
ይስሐቅም ሒዱ ብሎ ሰደዳቸው፤
ወሖሩ በዳኅና ፣
እነርሱም ወጥተው በደህና ሔዱ፤



፴፪፡ ወኮነ በይእቲ ዕለት ፣
በዚያች ቀን እንዲህ ሆነ፤ በጽሑ አግብርቲሁ ለይስሐቅ፤ ኮነ ያለ ውን በጽሑ ብሎ አመጣ ፤
ወነገርዎ በእንተ ዓዘቅት ዘከረዩ ፤ ወረከቡ ማየ በውስቴታ ፣
በዚያች ዕለት የይስሐቅ ባሮች መጡ፣ ስለ ቆፈሩዋት ጕድጓድ ነገሩት፣ ማለት ውሀ አገኘን አሉት ፤

፴፫፡ ወሰመያ ስማ ቤርሳቤህ ፣
ስሟን መሐላ ብሎ ጠራት ፤
ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየት ይእቲ ሀገር በርሳቤህ እስከ ዮም ፣
ስለዚህ እስከዛሬ የሀገሪቱ ስም ቤርሳቤህ ተባለ ፤

፴፬፡ ወኮኖ ለኤሳው ፵ዓ ዓመተ ፣
ለኤሳው አርባ ዘመን ሲሆነው፤
ወነሥአ ብእሲተ እንተ ስማ ይድን ወለተ ብኤል ኬጥያዊ ፣
ስሟ ይድን የሚባል የኬጢ ሰው የብኤልን ልጅ ሚስት አገባ፤
ወቤሴሞት ወለተ ኤሉን ኤውያዊ፣
የኤውያው ሰው የኤሉንን ልጅ ቤሴሞትንም ሚስት አደረገ፤

፴፭፡ ወይትቀሐዋሆሙ ለይስሐቅ ወለርብቃ ፣
ነገር ግን ርብቃንና ይስሐቅን መጻተኞች እያሉ ይገዳደርዋቸው ነበር ፤ አንድም በቀለብ ይከራከሩዋቸው ነበር ።

## ምዕራፍ ፳ወ፯

፩፡ ወኮነ እምድኅረ ልሕቀ ይስሐቅ ወረስአ ፣
ይስሐቅ ፈጽሞ ካረጀ በኋላ እንዲህ ሆነ ፤
ተሐምጋ አዕይንቲሁ ወኢይሬኢ ፣
ተሐምጋ ብሎ ገለጸው፣ ዓይኖቹ ፈዝዘው አያዩም ነበር ፤

፪፡ ወጸውዖ ይስሐቅ ለኤሳው ወልዱ ዘይልሕቅ ፣
ይስሐቅም ታላቁ ልጁ ኤሳውን ጠርቶ እንዲህ አለው ፤
ወይቤሎ ናሁ ረሳእኩ ወኢየአምር ዕለተ ሞትየ ፣
እነሆ እኔ ፈጽሜ አርጅቻለሁ የምሞትበትን ቀን አላውቅም፤

፫፡ ወይእዜኒ ንሣእ ንዋየ ሐቅልከ ወምጕንጳከ፣ ወቀስተከ ወፃእ ሐቅለ ወነዐው ፣
አሁንም ጋሻ ጦርህን አፎትህን፣ ቀስትህን ይዘህ ወደ በረሐ ውጣና አውሬ አድነህ አምጣልኝ ፤

፬፡ ወግበር ሊተ መብልዐ ዘከመ አፈቅር ወአምጽእ ሊተ እብላዕ ከመ ትባርከ ነፍስየ ዘእንበለ እሙት ፣
(መብሉንም) ምግቡንም እንደ ምወደው አድርገህ አዘጋጅተህ አበላ ዘንድ አምጣልኝና ሳልሞት ሰውነቴ ደስ ብሏት እንድትባርክህ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ ወሰምዓቶ ርብቃ ለይስሐቅ እንዘ ይብሎ ከመዝ ለኤሳው ወልዱ ፤

ርብቃም ይስሐቅ፣ ታላቁ ልጁን ኤሳውን እንዲህ ሲለው ሰማች፡

ወሖረ ኤሳው ሐቅለ ይንሀው ለአቡሁ፣

ኤሳውም ለአባቱ አውሬ አድኖ ሊያመጣ ወደ ምድረ በዳው ሄደ ፤

፮፤ ወትቤሎ ርብቃ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንእስ ፤

ርብቃ ታናሹ ልጇን ያዕቆብን እንዲህ አለችው ፤

ናሁ አነ ሰማዕክዎ ለአቡከ እንዘ ይብሎ ለኤሳው እኁከ ፤

እነሆ አባትህ ወንድምህ ኤሳውን እንዲህ ሲለው ሰማሁ ፤

፯፡ ሑር አምጽእ ሊተ እምዘነዓውከ ወግበር ሊተ መብልዐ ወእባርከ ቅድመ እግዚአብሔር ዘእንበለ እሙት ፤

ካደንከው እንደምወደው አድርገህ አዘጋጅተህ አምጣልኝና በልቼ ሳልሞት በእግዚአብሔር ፊት እንድባርክህ ሲለው ሰምቻለሁ ፤

፰፤ ወይእዜኒ ወልድየ ስምዓኒ ከመ እቤለከ ፤

አሁንም ልጄ ሆይ የምነግርህን ነገር እሺ በለኝ ፤

፱፤ ወሑር ኀበ አባግዒነ ወአምጽእ ሊተ ክልኤተ መሐስዐ ሠናየነ ወእግበሮሙ መብልዐ ለአቡከ ዘከመ ያፈቅር ፤

ወደ በጎቻችን ሂደህ የሰቡ ፤ የወፋፈሩትን ሁለት ጠቦቶች አምጣልኝና እኔም ለአባትህ እንደሚወደው አድርጌ አዘጋጅቼ ሰጥቼህ ፤

፲፤ ወትሰድ ለአቡከ ወይብላዕ ወይባርከ ዘእንበለ ይሙት ፤

አንተም ለአባትህ ወስደህ ሰጥተኸው በልቶ ሳይሞት ይመርቅህ አለችው ፤

፲፩፤ ወይቤላ ያዕቆብ ለርብቃ እሙ ናሁ ኤሳው እኁየ ፀጓር ውእቱ ፤

ያዕቆብም እናቱ ርብቃን እንዲህ አላት ፤ እነሆ ወንድሜ ኤሳው ፀጓር (ፀጉራም) ነው ፤

፲፪፡ ወአንሰ ኢኮንኩ ፀጓረ ፤

እኔ እንደ ወንድሜ እንደ ኤሳው ፀጉራም አይደለሁም ፤

የጊ እመ ገሠሠኒ አቡየ እከውን በቅድሜሁ ከመ ዘአስተኃቅሮ ፤

ምናልባት አባቴ የዳሰሰኝ እንደ ሆነ የዘበትኩበት መስሎት ይረግመኛል ፤

ወአመጽእ ላዕሌየ መርገመ ወአኮ በረከተ ፤

መከፈልት ሲሹ መቅሠፍት እንዲሉ ፤ ምርቃትን ያይደለ መርገምን አመጣ የለምን ?



፲፫፡ ወትቤሎ እሙ ላዕሌየ ይኩን መርገምከ ወልድየ ዳእሙ ስምዓኒ ወሑር ወአምጽእ ሊተ ዘእቤለከ ፤

ልጄ እኔ የነገርኩኽን ሰምተህ ያልኩህን አምጣልኝ እንጂ የሚያገኝህ መርገም በእኔ ይኹን አለቺው ፡

፲፬፡ ወሖረ ወአምጽአ ላቲ ለእሙ፣

ያዕቆብም ሄዶ በጉን አምጥቶ አርዶ አወራርዶ ለእናቱ ሰጣት፡

ወገብረት መብልዐ ዘከመ ያፈቅር አቡሁ ፤

እሷም ምግቡን አባቱ እንደ ሚወደው አድርጋ አዘጋጀች፡

፲፭፡ ወነሥአት ርብቃ አልባሲሁ ለኤሳው ወልዳ ዘይልሕቅ ወዘይሜኒ ዘሀሎ ኀቤሃ ወአልበሰቶ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንእስ ፤

ርብቃም ከሷ ዘንድ ተቀምጦ የነበረውን መልኩ ያማረ የሚሆን የታላቁ ልጁ የኤሳውን ልብስ አምጥታ ለታናሹ ልጁ አለበሰችው ፤

፲፮፡ ወገዘክተኒ አምዕስቲሆሙ ለእልክቱ ክልኤቱ መሐስዕ ወወደየት ላዕለ መታክፍቲሁ ወላዕለ ክሣዱ፣

የሁለቱንም ጠቦቶች ለምዳቸውን አምጥታ በአንገቱ አግብታ ጫንቃውን አለበሰችው፡ አንድም ጠጉሩን እየነጩች በደም አጣበቀችለት ፤

፲፯፤ ወመሀበቶ ዝኩ መብልዐ ወኅብስተኒ ዘገብረት በእደዊሁ ለያዕቆብ ወልዳ ፤

ያዘጋጀችውን ምግቡን ለያዕቆብ በእጁ አስይዛ ሰደደችው ፡

፲፰፤ ወአብአ ለአቡሁ ወይቤሎ አባ፣

እሱም ወደ አባቱ ደጅ ገብቶ አባቴ ብሎ ጠራው ፡

ወይቤሎ አቡሁ ነየ አነ መኑ አንተ ወልድየ ፤

ይስሐቅም እኔስ አለሁ ፤ ልጄ አንተ ማነህ ? አለው ፡

፲፱፡ ወይቤሎ ያዕቆብ አነ ውእቱ ኤሳው ወልድከ ዘበኵርከ ፤

ያዕቆብም እኔ የበኩር ልጅህ ኤሳው ነኝ ፤

ገበርኩ ዘትቤለኒ ተንሥእ ወንበር ወብላዕ እምዘ ነዓውኩ ለከ ከመ ትባርከኒ ነፍስከ ፤

ሰውነትህ ደስ ብሏት ትመርቀኝ ዘንድ ፤ ካደንሁት አዘጋጅቼ አምጥቼልሃለሁና ተነሥተህ ተቀምጠህ (ብላ) ቅመስ አለው ፤

፳፡ ወይቤሎ ይስሐቅ ለወልዱ ምንትኑ ውእቱ ዝንቱ ዘአፍጠንከ ረኪበ ወልድየ ፤

ይስሐቅም ልጁን ልጄ ሆይ እንደምን ፈጥነህ አግኝተህ መጣህ? አለው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ ዘወሀበኒ እግዚአብሔር አም ላክከ ቅድሜየ ፣

ፈጣሪህ እግዚአብሔር ወዲያው ከመንገዴ አጋጥሞኝ ፈጥኜ መጣሁ አለው ፡

፳፩፡ ወይቤሎ ይስሐቅ ቅረበኒ ወል ድየ ወእግሥሥከ ለእመ አንተኑ ውእቱ ኤሳው ወለእመ ኢኮንከ ፣

ይስሐቅም ኤሳው እንደሆን ኸም ፣ እንዳይደለህም ዳስሼ ልይህ ቅረበኝ አለው ፡

፳፪፡ ወቀርበ ያዕቆብ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ ፣

ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስ ሐቅ ቀረበ ፡

ወገሠሦ ወይቤሎ ፣ ቃልሰ ቃለ ያዕ ቆብ ወእደውሰ ዘኤሳው ፣

ይስሐቅም ዳስሶ አይቶ፣ ቃልህ የያዕቆብን ቃል ፣ እጅህ ግን የኤሳውን እጅ ይመስላል አለው፡

፳፫፡ ወኢያእመሮ እስመ እደዊሁ ፀጓራት ከመ እደወ ኤሳው ፣

እጆቹ እንደ ኤሳው እጆች ፀጉ ራሞች ስለሆኑ፣ ያዕቆብ እንደ ሆነ አላወቀም ፡

፳፬፡ ወባረኮ ይስሐቅ ወይቤሎ አንተ ውእቱ ኤሳው ወልድየ ፣

ይስሐቅም ያዕቆብን አንተ ልጄ ኤሳው ነህን ? ብሎ ጠየቀው አዎን አለው ፡

፳፭፡ ወይቤሎ አምጽእ ሊተ እምዘ ነዓውከ ወልድየ ከመ እብላዕ ወት ባርከ ነፍስየ ፣

ልጄ አንተስ ከሆንክ በልቼ ሰውነቴ ትመርቅህ ዘንድ ካደ ንኸው ሥጋ አምጣልኝ አለው፡

ወአቅረበ ሎቱ ወበልዐ፣ ወአምጽአ ሎቱ ወይነ ወሰትየ ፣

ከዚያ በኋላ መብሉን መጠጡን አመጣለት በላ ጠጣ ፡

፳፮፡ ወይቤሎ ይስሐቅ ቅረበኒ ወስዐ መኒ ወልድየ ፣

ይስሐቅም ልጄ ና ቀርበህ ሳመኝ አለው ፡

፳፯፡ ወቀርበ ወስዐሞ ወአጼነዎ ፣

ያዕቆብም ቀርቦ አባቱ ይስሐቅን ሳመው፤ ቃሉ የኤሳው እንዳይ ደለ ተጠራጥሮ ነበርና በመዓ ዛው ለማወቅ አሸተተው ፡

ወዲነዎ ጼና አልባሲሁ ፣ ወይቤ ናሁ ጼናሁ ለወልድየ ከመ ጼና ገዳም ጥቀ ጥንቁቀ ዘባረኮ እግዚአብሔር ፣

በመዓዛው የኤሳው ልብስ እን ደሆነ ዓውቆ ፤ የልጄ መዓዛው እግዚአብሔር እጅግ ፈጽሞ እንዳከበረው በምድረ በዳ እንዳ ለው አበባ ነው፤ አንድም እግዚ አብሔር ፈጽሞ ያከበረው የልጄ መዓዛ በምድረ በዳ እንዳለ አበባ ነው፤ ያ ደስ እንዲያሰኝ ደስ የሚያሰኝ ነው፡ (ሐተታ)



በልብሱ (ጽጌያትን) አበቦችን ይዘግብበት (ይሰበስብበት) ነበ ርና ፡

፳፰፡ ወይቤሎ የሀብከ እግዚአብሔር እምጠለ ሰማይ ወእምጠለ ምድር፣

እግዚአብሔር ከሰማይ በወረደ ጠል፣ ከምድር በተገኘ መስኖ ረድኤት በረከት ሰጥቶ ያክብ ርህ ብሎ መረቀው ፡

ወያብዝኀ ሥርናየከ ወወይነከ ወቅብ ዓከ ፣

ጠለ ሰማይ ያለውን ገለጸው ፡ ስንዴህን ወይንህን ዘይትህን ያብዛልህ ፡

፳፱፡ ወይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ወይስ ግዱ ለከ መላእክት ፣

ሕዝቡም አሕዛቡም ይገዙልህ ፡ አለቆቹም ይስገዱልህ ማለት ይታጠቁልህ ፡

ወኩን እግዚአ ለእኁከ ወይስግዱ ለከ ደቂቀ አቡከ ፣

ለወንድምህ ጌታ ሁነው ማለት ይገዛልህ፤ ያባትህም ልጆች ሁሉ ይገዙልህ ፡

ዘይባርከከ ቡሩከ ለይኩን፤ ወዘይረግ መከ ርጉመ ለይኩን ፣

አንተን የሚያከብርህ የሚመ ርቅህ ሁሉ የተባረከ የተመረቀ ይሁን ፤ አንተን የማያከብርህ የማይመርቅህ ሰው ግን የተዋ ረደ የተረገመ ይሁን ፡

፴፡ ወእምድኅረ አኅለቀ ባርኮቶ ይስ ሐቅ ለያዕቆብ፤ ወዕአ ያዕቆብ እምቅ ድመ ገጸ ይስሐቅ አቡሁ ፣

ይስሐቅም ያዕቆብን መርቆ ከጨ ረሰ በኋላ ፣ ያዕቆብ ከአባቱ ከይስሐቅ ፊት ወጥቶ ሄደ ፡

ወመጽአ ኤሳው እምንዲው ፣

ኤሳውም ሲያድን ከዋለበት መጣ ፡

፴፩፡ ወገብረ ውእቱኒ መብልዐ ወአ ምጽአ ለአቡሁ ፣

አድኖ የመጣውን አዘጋጅቶ ለአባቱ አቀረበ ፡

ወይቤሎ ተንሥእ አባ ወብላዕ እምዘ ነዓውኩ ለከ ወልድከ ከመ ትባርከኒ ነፍስከ ፣

አባቴ ሰውነትህ ትመርቀኝ ዘንድ እኔ ልጅህ ያመጣሁልህን ተነሥ ተህ ቅመስ አለው ፡

፴፪፡ ወይቤሎ ይስሐቅ መኑ አንተ፣

ይስሐቅም አንተ ማነህ? አለው፡

ወይቤሎ አነ ውእቱ ኤሳው ወልድከ ዘበኵርከ ፣

ኤሳውም፣ የበኸር ልጅኸ እኔ ኤሳው ነኝ አለው ፡

፴፫፡ ወደንገጸ ይስሐቅ ዐቢየ ድንጋጼ ጥቀ ፣

ይስሐቅም ጥንቱን ተጠራጥሮ ነበርና እጅግ ፈጽሞ ደነገጠ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ መኑመ ዘአምጽአ ሊተ ዘነ
ዓወ ፣ ወበላዕኩ ወባረክዎ ወቡሩክ
ውእቱ ፣

አድኖ አምጥቶልኝ አሁን በልቼ
የመረቅሁት ማነው ? እሱም
የተመረቀ ነው ፤ (ሐተታ) በም
ርቃት ላይ ምርቃት ይጨምር
ለታል ፤ አንድም እኔ ምን
እዳዬ ሁላችሁም ልጆቼ፣ ጥንቱ
ንም ቡሩክ ነው ፤

፴፬፡ ወኮነ ሰበ ሰምዐ ኤሳው ቃለ
አቡሁ ፣

ኤሳውም የአባቱን ቃል በሰማ
ጊዜ እንዲህ ሆነ ፤

ጸርሐ በዐቢይ ቃል ወአምረረ ጥቀ፣

ኮነ ያለውን ጸርሐ ብሎ አመ
ጣው፤ ቃሉን ከፍ አድርጎ እጅግ
ምርር ብሎ አለቀሰ ፤

ወይቤ ባርከኒ ኪያየኒ አባ ፣

አባቴ እኔንም መርቀኝ አለው፤

፴፭፡ ወይቤሎ ይስሐቅ ለኤሳው
መጽአ እኁከ በጕሕሉት ወነሥአ
በረከተከ ፣

ይስሐቅም ኤሳውን ወንድምህ
በተንኰል መጥቶ ምርቃትህን
ወሰደብህ አለው ፤

፴፮፡ ወይቤ ኤሳው በጽድቅ ተሰምየ
ያዕቆብ እስመ አዕቀጸኒ ፪ተ ጊዜ፣
ቀዳሚ ብኵርናየ ነሥአኒ፣ ወናሁ
ዮም በረከትየኒ ነሥአኒ ፣

ኤሳውም እንዲህ አለ፤ መጀመ
ሪያ ልቅናዬን፣ (አለቅነቴን) አሁ
ንም ምርቃቴን ወሰደ፣ ሁለት
ጊዜ አሰነካከሎኛልና በእውነት
ያዕቆብ ተባለ፤ ያዕቆብ ማለት
አዕቃጺ ማለት ነውና ፤

ወይቤሎ ኤሳው አልቦኑ አባ ዘአት
ረፍከ ሊተ በረከተ ፣

ኤሳውም አባቴ ለኔ ያስቀረኸ
ልኝ ምርቃት የለምን? አለው፤

፴፯፡ ወአውሥአ ይስሐቅ ወይቤሎ
ለኤሳው፣ እግዚእከ ረሰይክዎ ወለኵ
ሎሙ አኀዊሁ፤ አግብርቲሁ ረሰይክ
ዎሙ ፣

ይስሐቅም ኤሳውን እንዲህ
አለው ፤ አንድ ጊዜ ገዢህ አድ
ርጌዋለሁ፣ ወንድሞቹንም ሁሉ
የእሱ ተገዥዎች አድርጌያቸዋ
ለሁ ፤

ወአብዛህኩ ሎቱ ወይነ ወሥርናየ፣
ወትብየ፤ ወለከ ምንተ እሬሲ ወል
ድየ ፣

እንዲህም ሁሉ ወይኑን ስንዴ
ውን፣ ዘይቱን አብዝቼለታለሁ፣
ልጄ ላንተ ምን ላድርግልህ ?
አለው ፤

፴፰፡ ወይቤሎ ኤሳው ለይስሐቅ
አቡሁ አሐቲኑ ክመ በረከትከ ለከሰ
አባ ፣

ኤሳውም አባቱ ይስሐቅን አባቴ
ምርቃትህ አንዲት ብቻ ናትን?
አለው ፤



ወእምዝ ጸርሐ ኤሳው ወበከየ ፣

ከዚህ በኋላ ኤሳው ጮሆ አለ
ቀሰ ፤

፴፱፡ ወይቤ ይስሐቅ ናሁ እምጠለ
ሰማይ እምላዕሉ፣ ወእምጠለ ምድር
ይኩን ሕይወትከ ፣

ይስሐቅም አኗኗርህ (አነዋርህ)
ከሰማይ በወረደ ጠል፣ ከምድር
በተገኘ መስኖ ይሁን ፤

፵፡ ወበመጥባሕትከ ሕየው ወተቀ
ነይ ለእኁከ ፣

ገድለህ ሰልበህ ኑር ፤ ለወንድ
ምህ ተገዛ ፤

ወባሕቱ እመ ትፈቅድ ትግድፍ ያር
እምክሣድከ ተጋነይ ሎቱ ፣

ነገር ግን የወንድምህን አገዛ
ዙን ካንተ ልታርቅ ብትወድ፣
እርሱን ተለማመጠው (ተስማ
ማው) አለው ፤

፵፩፡ ወተበቀሎ ኤሳው ለያዕቆብ በእ
ንተ በረከቱ ዘባረኮ አቡሁ ፣

ኤሳውም ምርቃቱን ከአባቱ
ስለ ወሰደበት በያዕቆብ ቂም
ያዘበት ፤

ወይቤ ኤሳው በልቡ ለትቅረብ መዋ
ዕለ ላሁ ለአቡየ ከመ እቅትሎ ለያዕ
ቆብ ፣

ኤሳውም አባቴ ሙቶ የማለቅ
ስበት ቀን ደርሶ፣ ወንድሜ ያዕ
ቆብን ገድዬው ብሎ ተመኘ ፤

፵፪፡ ወአይድዕዋ ለርብቃ ዘይቤ
ወልዳ ዘይልሕቅ፣

ሰዎችም ታላቁ ልጇ የተናገረ
ውን ለርብቃ ነገሩዋት ፤

ወለአከት ወጸውዐቶ ለያዕቆብ ወልዳ
ዘይንእስ፣ ወትቤሎ፣ ናሁ ኤሳው
እኁከ ይንዕውከ ወይፈቅድ ይቅት
ልከ ፣

ርብቃ ታናሹ ልጇ ያዕቆብን
ልካ አስመጥታ እነሆ ወንድ
ምህ ኤሳው ሊገድልህ ይፈል
ግሃል ፤

፵፫፡ ወይእዜኒ ወልድየ ስምዐኒ
ቃልየ ዘእቤለከ ተንሥእ ወሑር ማእ
ከለ አፍላግ ዘሶርያ ኀበ ላባ እኁየ
ውስተ ካራን ፣

አሁንም ልጄ እኔ የምነግርህን
ነገር ስማኝ፤ ተነሥተህ በሶርያ
ወንዞች መካከል አድርገህ፣ በካ
ራን ወዳለው ወንድሜ ወደ ላባ
ሒድ ፤

፵፬፡ ወንበር ኀቤሁ ኅዳጠ መዋዕለ
እስከ ይቈርር መዓቱ ለእኁከ ፣

የወንድምህ ቁጣ እስኪበርድ
ድረስ ሒደህ ጥቂት ዘመን
ከአጐትህ ከላባ ዘንድ ተቀመጥ፤

፵፭፡ ወይረስእ ዘገበርካሁ ወእልእክ
ወእነሥእከ እምህየ ከመ ኢይኅጉል
ክልኤክሙ በአሐቲ ዕለት ፣

ያደረግኸውን ነገር እስኪዘነጋ
ልህ ድረስ ከዚያ እኔ ልኬ አስ

www.ethiopianorthodox.org

መጣሃለሁ፤ ባንዲት ቀን ሁለታ ችሁንም እንዳላጣ ሂድ አለችው፤

፵፮፡ ወትቤሎ ርብቃ ለይስሐቅ ጸላ እኩ ሕይወትየ እምአዋልደ ከነዓን፣

ርብቃ ይስሐቅን ከከነዓን ልጆች የተነሣ ኑሮዬን ጠላሁ አለችው፤ አንድም ኤሳው ልጄ ያዕቆብን የሚገድለው ከሆነ ከከነዓን ልጆች ጋር መኖሬ ለምኔ ነው ? አን ድም እነዚህ መፃተኞች እያሉ ይሰድቡዋቸው ነበርና ከከነዓን ልጆች ጋር መኖሬ ለምኔ ነው ? አንድም በልብስ፣ በቀለብ ምክ ንያት የኤሳው ሚስቶች ይፈካ ከሩባቸው ነበርና ፤ ከከነዓን ልጆች ጋራ መኖሬን ጠላሁ ፤

ወእመሰ ይነሥእ ያዕቆብ ብእሲተ እምአዋልደ ዝንቱ ብሔር ለምንት እንከ አሐዩ ፣

ያዕቆብ ከከነዓን ልጆች ሚስት የሚያገባ ከሆነ በሕይወት መኖሬ ለምኔ ነው ? አለችው።

## ምዕራፍ ፳ወ፰

### ገባኤ

፩፡ ወጸውዖ ይስሐቅ ለያዕቆብ ወባ ረኮ ወይቤሎ ኢትንሣእ ብእሲተ እም አዋልደ ከነዓን ፣

ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ መረ ቀው ፤ ከከነዓን ልጆች ሚስት እንዳታገባ አለው ፤

፪፡ ተንሥእ ወሑር ማዕከለ አፍላግ ውስተ ቤተ ባቱኤል አቡሃ ለእምከ፡ ወንሣእ ለከ ብእሲተ እምአዋልዲሁ ለላባ እኁሃ ለርብቃ እምከ ፣

በወንዞች መካከል ባለ በሶርያ የእናትህ አባት የባቱኤል ወገን ወዳለበት ተነሥተህ ሒድ፤ የእ ናትህ የርብቃ ወንድም የሚሆን ከላባ ልጆች ሚስት አግባ እንጂ፤

፫፡ ወአምላኪየ ይሑር ምስሌከ ፣

ፈጣሪዬ ከአንተ ጋራ በረድኤት ይኑር አይለይህ ፤

ወያዕቢከ ፣ ወይባርከ ፣ ወያብዝኀከ ወኩን ብዙኃ አሕዛበ ፣

ያክብርህ፣ ያግንንህ ፣ ያብዛህ፣ ብዙ ወገን ሁን ፤

፬፡ ወየሀብከ በረከተ አብርሃም አቡከ ለከ ወለዘርእከ እምድኅሬከ ከመ ትረሳ ለዛቲ ምድር እንተ ወሀበ ለአብርሃም ፣

ለአብርሃም አወርስሃለሁ ያለውን ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ ላንተም ከአንተም በኋላ ለሚ ነሡ ልጆችህ የአብርሃምን በረ ከት ይስጥህ አለው ፤

፭፡ ወፈነዎ ይስሐቅ ለያዕቆብ ወልዱ ማዕከለ አፍላግ ዘሶርያ፣ ኀበ ላባ ወልደ ባቱኤል ሶርያዊ እኁሃ ለርብቃ ፣

ከዚህም በኋላ ይስሐቅ ልጁን ያዕቆብን የርብቃ ወንድም የሶ ርያ ሰው የሚሆን የባቱኤል ልጅ ላባ ወደ አለበት በሶርያ



ወንዞች መካከል ወደ አለው አገር አሰናብቶ ሰደደው ፤

፮፡ ወሶበ ርእየ ኤሳው ከመ ባረኮ አቡሁ ለያዕቆብ ፣

ኤሳውም አባቱ ይስሐቅ ያዕቆ ብን እንደ መረቀው ባየ ጊዜ ፤

ወከመ ሖረ ማዕከለ አፍላግ ዘሶርያ ከመ ይንሣእ ብእሲተ እምህየ ፣

ከዚያም ተነሥቶ ሚስት ያጭ ዘንድ በሶርያ ወንዝ መካከል ወደ አለው አገር እንደ ሔደ ባየ ጊዜ ፤

ከመ ባረኮ ወከመ አዘዞ ወይቤሎ ኢትንሣእ ብእሲተ እምአዋልደ ከነ ዓን ፣

ከከነዓንም ልጆች ሚስት አታ ግባ ብሎ እንዳዘዘውና እንደ መረቀውም ባየ ጊዜ ፤

፯፡ ወሰምዖሙ ያዕቆብ ለአቡሁ ወለ እሙ ወሖረ ፣

ያዕቆብም ያባት የናቱን ቃል ሰምቶ ወደ ሶርያ እንደ ሔደ ባየ ጊዜ ፤

፰፡ ወሶበ ርእየ ኤሳው ከመ እኩ ያት እማንቱ አዋልደ ከነዓን በኀበ አቡሁ ይስሐቅ፣

ሶበን ቢርቀው ደገመው፤ ኤሳ ውም የከነዓን ልጆች ባባቱ በይ ስሐቅ ዘንድ እንዳልተወደዱ ባየ ጊዜ ፤

፱፡ ሖረ ኀበ ይስማኤል ወነሥአ ለቤ ሴሞት ወለተ ይስማኤል ወልደ አብ ርሃም እኁሁ ለናኮር ፣

እሱ ከባለተስፋዎቹ ቢጋባ ፣ እኔስ ከባለተስፋዎች አልጋባ ምን ? ብሎ ወደ ይስማኤል ሂዶ የናኮር ወንድም የአብር ሃም ልጅ የሚሆን የይስማኤልን ልጅ ቤሴሞትን አገባ ፤

ከመ ትኩኖ ብእሲተ ምስለ አንስቲ ያሁ ፣

ቀድሞ ካገባቸው ሚስቶቹ ጋራ ሚስት ትሆነው ዘንድ ፤

፲፡ ወወፅአ ያዕቆብ እምዓዘቅተ መሐላ ወሖረ ኀበ ካራን ፣

ያዕቆብም ከተማማሉበት ቦታ ከወንዙ ተነሥቶ ወደ ካራን ሔደ፤ ወንድሜ ቢከተለኝ ወን በዴ ቢጣላኝ ፣ አውሬ ቢነጣብ ኝሳ ብሎ ፤

፲፩፡ ወረከበ መካነ ወቤተ ህየ እስመ ዐርበት ፀሐይ ፣

ፀሐይ ገብቶ መሽቶ ነበርና ምቹ ቦታ አግኝቶ ከዚያ አደረ ፤

ወነሥአ እምውእቱ ዕብን ዘውስተ ውእቱ ብሔር፤ ወወደየ ውስተ ትር አሲሁ፤ ወሰከበ በውእቱ መካን ፣

በዚያ ቦታ ካለ ደንጊያ አንሥቶ፣ ያንን ትራስ አድርጎ ከዚያ ቦታ ተኝቶ አደረ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፡ ወሐለመ ወይሬኢ ሰዋስወ ዘወርቅ ውስተ ምድር ወርእሱ ይጌድእ ሰማየ ፡፡

ይበጽሕ ሲል ነው፤ በዚያችም ሌሊት በራእይ የወርቅ መሰላል ተተክሎ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሶ አየ ፤

ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ ቦቱ ፡፡

መላእክትም በእርከኑ ይወርዱበት ይወጡበት ነበር ፤

፲፫፡ ወእግዚአብሔር ይቀውም ላዕሌሁ ፡፡

ይነብር ሲል ነው ፤ በበላዩም እግዚአብሔር ተቀምጦበት አየ፤

ወይቤሎ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ አቡከ ኢትፍራህ ፡፡

የአብርሃምና ያባትህ የይስሐቅ ፈጣሪ እኔ ነኝና ወንድሜ ይገድለኛል ብለህ፤ አንድም እንደ ወጣሁ ዕቀራለሁ ብለህ አትፍራ አለው ፤

ወለዛቲኒ ምድር እንተ ላዕሌሃ ትሰክብ ለከ እሁባ ወለዘርእከ ፡፡

ይህችንም የተኛህባትን ምድር ላንተም ለልጆችህም አወርሳታለሁ ፤

፲፬፡ ወይከውን ዘርእከ ከመ ኆፃ ባሕር ወይበዝኅ ፡፡

ልጅህ የልጅ ልጅህም በዝቶ እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል ፤

ወይመልዕ እስከ ባሕር ወውስተ አዜብ ወመስዕ ወውስተ ጽባሕ ፡፡

በአራቱ መዓዝን ሁሉ ይመላል፤

ወይትባረኩ ብከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ወበዘርእከ ፡፡

በምድር ያሉ አሕዛብም ሁሉ ባንተም በልጆችህም ይከብራሉ፤

፲፭፡ ወአነ አሐውር ምስሌከ ፡፡

እኔም ካንተ ጋራ በረድኤት እኖራለሁ ፤

ወአዓቅበከ በኵሉ ፍኖትከ እንተ ተሐውር ወአገብአከ ውስተ ዛንቱ ምድር ፡፡

በሔድክበት አገር ሁሉ በረድኤት ጠብቄ ወደዚህ ወደ ከነዓን እመልስሃለሁ ፤

ወኢየኃድገከ እስከ እገብር ለከ ኵሎ ዘአቤለከ ፡፡

የነገርኩኽን ተስፋ እስክፈጽም ልህ በረድኤት አልለይህም ብሎ ነገረው ፤

፲፮፡ ወነቅሐ ያዕቆብ እምንዋሙ ወይቤ እግዚአብሔር ሀሎ ውስተ ዛቲ ምድር ፡፡

ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቅቶ በእውነት እግዚአብሔር በዚህች አገር በረድኤት አለ ፤

ወአንሰ ኢያእመርኩ ፡፡

እኔ ግን አላወቅሁም ነበር አለ፤



፲፯፡ ወፈርሀ ወይቤ ግሩም ውእቱ ዝንቱ ምድር ፡፡

ካየውም ሕልም የተነሣ ፈርቶ ይህ ዛሬ ያየሁት ቦታ ግሩም ነው አለ ፤

ወይከውን ዝየ ቤተ እግዚአብሔር፡፡

በዚህም ቦታ ቤተ እግዚአብሔር ይሠራል አለ፤ ይኸውም አልቀረ ሀገረ ምስካይ ተሠርቶበታል ፤

ወዛቲ ኆኅት ይእቲ ለሰማይ ፡፡

የሰማይም ደጃፍ ይህች ናት ፡ (ሐተታ) እግዚአብሔር ቁሞባት ፤ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት አይቶአልና የሰማይ ደጃፍ ናት አለ ፤

፲፰፡ ወተንሥአ ያዕቆብ በጽባሕ ወነሥአ ለይእቲ ዕብን እንተ ወደየ ውስተ ትርአሲሁ ወአቀማ ከመ ሐውልት ፡፡

ያዕቆብም ሲነጋ ተነሥቶ ትራስ ያደረጋትን ደንጊያ አንሥቶ እንደ ሐውልት አድርጎ አቆማት ፤

ወሦጠ ቅብዐ ላዕለ ርእሳ ፡፡

በራስዋም ላይ ዘይት አፈሰሰባት ፤ ይኸውም ምሳሌ ነው ፡ ያዕቆብ የጌታ፤ የወርቁ መሰላል የረድኤት፤ እርከኑ ብዙ መሆኑ፤ በብዙ ወገን እረዳሃለሁ ሲል ነው፤ መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ማየቱ ፡፡ እኔ ስረዳህ መላእክትም አብረው ይረዱሃል ሲል ነው ፤ መሰላሉ በደንጊያ ላይ መሆኑ በጽኑ ረድኤት እረዳሃለሁ ሲል ነው፤ አንድም ሰዋስው የእመቤታችን ፡ ወርቅ የንጽሕናዋ የድንግልናዋ ፡፡ እርከኑ ብዙ መሆኑ የሀብትዋ ምሳሌ ፡ መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት ማየቱ ፡ ዓለማቱ ውን ጌታን በፀነሰች ጊዜ መላእክት በማኅፀንዋ ዓለምንት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የማመስገናቸው ፡ ጌታን በስዋስው ላይ ቁሞ ማየቱ፡ እመቤታችን ጌታን በሰውነቱ ስትሸከመው፡ ጌታም በመለኮትነቱ ይሸከማታልና፡ ያርኪዮ እንዘ ውእቱ ይፀውረኪ እንዲል ፡ አንድም ያዕቆብ የሐዋርያት፡ ደንጊያው የአሕዛብ፡ በደንጊያ ላይ መሰላል መሆኑ ፡ አሕዛብ በሐዋርያት ስብከት አምነው በእመቤታችን ፍቅር የመጽናታቸው ምሳሌ፡ አንድም ያዕቆብ የጳጳሳት፡፡ የሊቃነ ጳጳሳት፡፡ ደንጊያው የታቦት፡፡ ዘይቱ የሜሮን፡ በደንጊያው ላይ መሰላል በመሰላሉ ላይ ጌታ መታየቱ የጌታና የእመቤታችን ስም በታቦቱ ላይ የመጻፉ ምሳሌ ፡፡ ዛሬም የጌታና የእመቤታችን ስም ያልተጻፈበት ታቦት፡፡ ሊቀደስበት ሊሰገድበት አይገባም ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፱: ወሰመዮ ስሞ ለውእቱ መካን ቤተ ኤል፤

ሕልሙን ያየበትንም ቦታ ስሙን ቤቴል አለው፤ ቤተ እግዚአብሔር ማለት ነው ፡፡

ወስሙሰ ለውእቱ መካን ትካቲሁ ወለምሕሳ ፤

የዚያ ቦታም ጥንተ ስሙ ወለ ምሕሳ ይባል ነበር ፡፡

፳: ወበጽዓ ያዕቆብ ወይቤ፤

ያዕቆብም እንዲህ ብሎ ተሳለ፤

ለእመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌየ፤

እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ በረ ድኤት ካለ ፡፡

ወዐቀበኒ በዛቲ ፍኖት እንተ አሐ ውር ፤

በዚህች በምሔድባት መንገድም በረድኤት ከጠበቀኝ ፡፡

ወወሀበኒ እክለ ዘእሴሰይ ፤ ወልብሰ ዘእለብስ ፤

የዓመት ልብስ፤ የዕለት ጉርስ ከሰጠኝ ፡፡

፳፩: ወአግብአኒ ቤተ አቡየ በዳህና፤

ወደ አባቴም ወገኖች በተድላ በደስታ ከመለሰኝ ፡፡

ይከውነኒ እግዚአብሔር አምላኪየ፤ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር የሚሰ ጠኝ ይህ ይበቃኛል ፡፡ አንድም ይህን የሰጠኝ እግዚአብሔር አምላኬ ነው ማለት ፡፡ እሱን ብቻ አመልካለሁ ሌላ አላመ ልክም ሲል ነው ፡፡

፳፪: ወዛቲ ዕብን እንተ ዐቀምኩ ትኩነኒ ቤተ እግዚአብሔር ፤

ይህችም ያቆምኳት ደንጊያ ቤተ እግዚአብሔር ትሆንልኛ ለች ማለት፤ ቤተ እግዚአብሔ ርን እሠራባታለሁ ሲል ነው፡፡

ወኵሎ ዘወሀብከኒ ዐሥራተ እዴሁ እዔሥሮ ለከ ፤

ከሰጠኸኝም ገንዘብ ሁሉ ከዐሥር አንድ አውጥቼ እሰጥሃለሁ ብሎ ተሳለ ፡፡

## ምዕራፍ ፳ወ፱

፩: ወተንሥአ ያዕቆብ ወሖረ በጽባሕ ነበ ላባ ወልደ ባቱኤል ሶርያዊ እኁሃ ለርብቃ ፤

ያዕቆብም ሲነጋ ተነሥቶ የር ብቃ ወንድም የሶርያ ሰው ከሚ ሆን ከባቱኤል ልጅ ከላባ ዘንድ ሔደ ፡፡

እሞሙ ለያዕቆብ ወለኤሳው ፤

ርብቃን የያዕቆብና የኤሳው እናት አላት ፡፡ ሐተታ ባለፈው እንደ ቅድሚያቸው በኵሩን ኤሳውን እያስቀደመ፤ ያዕቆብን እያስከተለ ይጠራቸው ነበር፤ አሁን በኵርነቱን እንደ ወሰደ



በት ለማጠየቅ፤ ያዕቆብን አስቀ ድሞ ኤሳውን አስከተለ ፡፡

፪: ወሶበ ይኔጽር ወይሬኢ ናሁ ዓዘ ቅት ውስተ ገዳም ፤

ያዕቆብም አሻግሮ በተመለከተ ጊዜ ፤ በምድረ በዳ ያለውን የውሀውን ጕድጓድ ተመለከተ አየ ፡

ወሀለዋ ህየ ፫ አባግዕ ወይሰክባ ላዕሌሃ፤

በውሀውም ጕድጓድ አጠገብ ሦስት በጎች ተኝተው ነበር ፤ አንድም ጕድጓዱ ደንጊያ ተገ ጥሞ በደንጊያው ላይ ሦስት በጎች ተኝተው ነበር ፡

እስመ እምይእቲ ዐዘቅት ያስትይዎን ለውእቶን አባግዕ ፤

በጎቹን ከዚያች ምንጭ ያጠጡ ዋቸው ነበርና ፡

ወዲበ አፉሃ ለይእቲ ዐዘቅት ዕብን ዐቢይ ፤

ምንጩም በትልቅ ደንጊያ ተገ ጥሞ ነበር ፡

፫: ወይትጋብኡ ህየ ኵሎሙ ኖሎት ወያሴስልዋ ለይእቲ ዕብን እምአፈ ዓዘቅት ወያስትዩ አባግዒሆሙ ፤

እረኞቹ ሁሉ በዚያ በተሰበሰቡ ጊዜ ደንጊያውን ከምንጩ ላይ አንሥተው ጥለው በጎቻቸውን ያጠጡ ነበር ፡

ወያገብእዋ ለይእቲ ዕብን ውስተ አፈ ዐዘቅት ፤

በጎቻቸውንም ካጠጡ በኋላ ደን ጊያዩቱን ከውሀው ላይ መል ሰው ይገጥሙዋት ነበር ፡

፬: ወይቤሎሙ ያዕቆብ አንትሙ አኃውየ እምአይቴ አንትሙ ፤

ያዕቆብም እረኞቹን እናንተ ወን ድሞቼ ከወዴት አገር መጥታ ችኋል ? አላቸው ፡

ወይቤልዎ እምካራን ንሕነ ፤

እነዚያም ከወደ ካራን መጥተ ናል አሉት ፡

፭: ወይቤሎሙ ተአምርዎኑ ለላባ ወልደ ናኮር ፤

ያዕቆብም ወንድሞቼ የናኮር ልጅ ላባን ታውቁታላችሁን ? ብሎ ጠየቃቸው ፡

ወይቤልዎ ነአምሮ ፤

እነሱም አዎን እናውቀዋለን አሉት ፡

፮: ወይቤሎሙ ዳኅንኑ ውእቱ ፤

ጤናውን ደህና ነውን ? አላ ቸው ፡

ወይቤልዎ እወ ዳኅን ወናሁ ራሔል ወለቱ ትመጽእ ምስለ አባግዓ አቡሃ፤

እነሱም አዎን ደህና ነው፤ እነሆ ልጁ ራሔል የአባትዋን በጎች ይዛ ትመጣልሃለች አሉት ፡

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወይቤሎሙ ዓዲ ኢበጽሐ ሰዓት ከመ ይትጋብኡ እንስሳክሙ ወይስተዩ ፤ ወይሑሩ ፤ ወይትረአዩ ፤

ያዕቆብም ከብቶቻችሁ ውሀ ለመጠጣት የሚሰበሰቡበት ፡ ጠጥተውም የሚሰማሩበት ጊዜ አልደረሰምን ? አላቸው ፡

፰፡ ወይቤልዎ ኢንክል ለእመ ኢተጋብኡ ኵሎሙ ኖሎት ወያሴስልዋ ለዛቲ ዕብን እምአፈ ዓዘቅት ፡ ወናስቲ አባግዒነ ፤

እነሱም ጊዜውስ ደርሶ ነበር፤ እረኞች ሁሉ ተሰብስበው ደንጊያውን ከጕድጓዱ ላይ ካላነሡት በጎቻችንን ለማጠጣት የማይቻለን ሆኖ ነው እንጂ አሉት ፡

፱፡ ወእንዘ ዘንተ ይትናገሩ በጽሐት ራሔል ምስለ አባግዓ አቡሃ ፤

ይህን ተነጋግረው ሳይጨርሱ ራሔል የአባትዋን በጎች እየነዳች መጣች ፡

፲፡ ወሶበ ርእየ ያዕቆብ ለራሔል ወለተ ላባ እኁሃ ለእሙ ወለአባግዓ ላባ ወሰዓማ ለራሔል ወጸርሐ በቃሉ ወበከየ፤

ያዕቆብም የናቱ ወንድም የላባ ልጅ የምትሆን ራሔል፤ የላባን በጎች እየነዳች ስትመጣ ባየች ጊዜ ፡ ከብቶቹንም ካጠጣ በኋላ ራሔልን አቅፎ ስሞ ጮሆ አለቀሰ ፡

፲፩፡ ወቀርበ ያዕቆብ ወአሰሰላ ለዕብን እምአፈ ዓዘቅት ወአስተየ አባግዓ ላባ ፤

ያዕቆብም ወደ ጕድጓዱ ቀርቦ ደንጊያዩቱን ከጕድጓዱ አንሥቶ የላባን በጎች አጠጣ ፡

ወአይድዓ ለራሔል ከመ ወልደ ርብቃ ውእቱ እኁሁ ለአቡሃ ፤

ያክስትዋ የርብቃ ልጅ መሆኑንም ለራሔል ነገራት ፡

፲፪፡ ሮፀት ወሖረት ራሔል ወአይድዓቶ ዘንተ ነገረ ለአቡሃ ፤

ራሔልም ፈጥና ሔዳ ለአባትዋ ለላባ በከነዓን የሚኖር የእኅትህ ልጅ መጥቶአል ብላ ነገረችው ፡ ይኸውም ምሳሌ ነው ፤ ያዕቆብ የጌታ፤ አባግዕ የምእመናን፤ ደንጊያው የዓረፍተ ዘመን፤ ኖሎት የነቢያት የካህናት ፤ ውሀው የጥምቀት፤ በጎቹ ውሀው በደንጊያ ተገጥሞ ሳለ ዙሪያውን ከብበው መተኛታቸው ፡ ምእመናን አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ፤ ዓረፍተ ዘመን ገትቶአቸው ተስፋ ጥምቀትን እየሰሙ ደጅ ሲጠኑ የመኖራቸው ምሳሌ፤ ኖሎት ከዚያ አስቀድሞ ተሰብስበው ደንጊያውን አንሥተው በጎቹን ማጠጣታቸው፤ ነቢያት መሥዋዕት ሠውተው፤ ማየ ምንዛሕ ረጭተው አፍአዊ ኃጢአት



የማስተሥረያቸው፤ አንድም እምውኒዝ ስትዩ ማየ በፍኖት እንዲል (መዝ.፻፱) ከ.ያየ ኀደጉኒ ነቅዓ ማየ ሕይወት ወከረዩ ዓዘቅተ ዘኢይትረከብ ማዩ እንዲል (ኤር. ፪፤፲፪) እያሉ የጥምቀትን ነገር ተናግረዋልና፤ ያዕቆብ ብቻውን ደንጊያውን አንሥቶ በጎቹን እንዳጠጣ፤ ጌታም አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ሰው ሁኖ ከምእመናን ፍዳ መርገምን በጥምቀት አጥ ፍቶአልና፤

፲፫፡ ወሶበ ሰምዐ ላባ ስመ ያዕቆብ ወልደ ርብቃ እኁቱ ፤

ላባም የእኅቱ የርብቃ ልጅ ያዕቆብ እንደ መጣ ራሔል ስትናገር በሰማ ጊዜ ፡

ሮፀ ወተቀበሎ ወሐቀፎ ወሰዓሞ ወወሰዶ ቤቶ ፤

ፈጥኖ ሒዶ አንገቱን አቅፎ ስሞ ወደ ቤቱ ይዞት ሔደ ፡

ወነገሮ ለላባ ኵሎ ነገሮ ፤

ያዕቆብም የመጣበትን ነገር ሁሉ ለላባ ነገረው ፡

፲፬፡ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ዐጽምየ ወሥጋየ አንተ ንበር ምስሌየ ፤

ላባ ያዕቆብን አንተ የአጥንቴ ፍላጭ፤ የሥጋዬ ቁራጭ ነህና ከእኔ ጋራ ኑር አለው ፡

ወነበረ ምስሌሁ ፴ መዋዕለ ፤

ያዕቆብም ከላባ ጋራ ሠላሳ ቀን ተቀመጠ ፡

፲፭፡ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ እስመ እኁየ አንተ ኢትትቀነይ ሊተ በከንቱ ንግረኒ ምንት ውእቱ ዐስብከ፤

ላባም ያዕቆብን አንተ ወንድሜ ነህና ደመወዝህ ምን እንደ ሆነ ንገረኝ እንጂ፤ ያለደመወዝ በከንቱ ለእኔ አትገዛ አለው ፡

፲፮፡ ወቦቱ ለላባ ፪አዋልድ ፤

ለላባም ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት ፡

ስማ ለእንተ ትልሕቅ ልያ ፤

የትልቂቱ ልጅ ስምዋ ልያ ነው፡

ወለእንተ ትንዕስ ራሔል ፤

የትንሽቱም ልጅ ስምዋ ራሔል ነው ፡

፲፯፡ ወልያስ ትደዊ አዕይንቲሃ ፤

ልያ ዓይነ ልም ነበረች ፡

ወለራሔልሰ ሠናይ ራእያ ወላህይ ገጻ፤

ራሔል ግን መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች መልካም ቆንጆ ነበረች ፡

፲፰፡ ወአፍቀራ ያዕቆብ ለራሔል ፤

ያዕቆብም ከልያ ራሔልን ወደዳት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ እትቀነይ ለከ ፯ተ ዓመተ በእንተ ራሄል ወለትከ እንተ ትንዕስ ፤

ያዕቆብም ላባን ፣ ስለ ትንሽቱ ልጅህ ስለ ራሔል ሰባት ዓመት እገዛልሃለሁና ፡

ወሀበኒ ኪያሃ ከመ ትኩነኒ ብእሲተ፤

ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እርስዋን ስጠኝ፤ ደመወዜ ይህ ነው አለው፤

፲፱፡ ወይቤሎ ላባ ፣ ይኄይሰኒ ለከ አሀብከ ለማእምርየ ወለሥጋየ እም አሀባ ለካልዕ ብእሲ ነኪር ፤

ላባም ለማላውቀው ሰው ከሰ ጣት ለማውቅህ ላንተ፤ ለባዕድ ከሰጣት ለዘመዴ ላንተ ብሰጣት ይሻለኛ የለምን ፡

ንበር እንከሰ ፤

ፈቃድህስ ከሆነ እኔም ፈቃዴ ነው ፣ ዝም ብለህ ተቀመጥ አለው ፡

፳፡ ወተቀንየ ያዕቆብ በእንተ ራሄል ፯ተ ዓመተ ፤

ያዕቆብም ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ተገዛ ፡

ወኮኖ በቅድሜሁ ከመ ኅዳጥ መዋ ዕል እስመ አፍቀራ ፤

ራሔልን ስለ ወደዳት ሰባቱ ዓመት ለያዕቆብ እንደ ጥቂት ቀን ሁኖ ታየው ፡

፳፩፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ሀበኒ እንከሰ ብእሲትየ ከመ እባእ ኀቤሃ፤

ያዕቆብም ላባን እንግዲህ እገ ናኛት ዘንድ ሚስቴን ስጠኝ አለው ፡

እስመ ፈጸምኩ መዋዕሊሁ ፤

የተቀጠርኹበትን ሰባቱን ዓመት ጨርሻለሁና ፡

፳፪፡ ወአስተጋብአሙ ላባ ለኵሎሙ ሰብአ ብሔሩ ወገብረ ከብካበ ፤

ላባም ያገሩን ሰዎች ሁሉ ሰብ ስቦ ሠርግ አደረገ ፡

፳፫፡ ወሶበ መስየ ነሥአ ላባ ለልያ ወለቱ፤ ወአብአ ኀበ ያዕቆብ ፤

በመሸ ጊዜም ላባ ልጁ ልያን ሸፋፍኖ ለያዕቆብ ሰጠው ፡

፳፬፡ ወወሀባ ላባ ለልያ ወለቱ ዘለ ፋሃ ትኩና አመተ ፤

ላባም ለልጁ ለልያ አገልጋይ ትሆናት ዘንድ ዘለፋን (ትልወት አድርጎ) ሰጣት ፡

፳፭፡ ወሶበ ጸብሐ ነየ ልያ ፤

ሲጨዋወቱ አድረው ሲነጋ ቢያ ያት ልያ ሁና አገኛት ፡

ወይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ለምንት ረሰ ይከኒ ከመዝ ፡ አኮኑ በእንተ ራሄል ተቀነይኩ ለከ ፤

ያዕቆብም ላባን ሰባት ዓመት የተገዛሁልህ ራሔልን ትሰጠኛለህ ብዬ አልነበረምን? ለምን እን ዲህ አደረግኸኝ ፡



ወለምንት አስተሐቀርከኒ ፤

ለምንስ እንደዚህ አድርገህ አታ ለልከኝ አለው ፡

፳፮፡ ወይቤሎ ላባ ኢኮነ ከመዝ ፤

ላባም ያዕቆብን ነገሩ እንዲህ አይደለም አለው ፡

በብሔርነሰ ኢይቀድሙ ውሂበ እንተ ትንዕስ እንዘ ሀለወት እንተ ትል ሕቅ ፤

በአገራችን ታላቂቱ ሳለች አስ ቀድመው ትንሺቱን አይድ ሩም ፡

፳፯፡ ፈጽም ለዛቲኒ ፯ተ ዓመተ ወእሁበከ ኪያሃኒ ፤

ስለዚህችም ሰባት ዓመት አገ ልግልና እርስዋንም ልስጥህ አለው ፡

በእንተ ዘትትቀነይ ሊተ ካልአ ፯ተ ዓመተ ፤

ሁለተኛ ሰባት ዓመት የምትገ ዛልኝ ስለሆነ ፡

፳፰፡ ወገብረ ያዕቆብ ከማሁ ወፈጸመ ላቲኒ ፯ተ ዓመተ ፤

ያዕቆብም እንደ ተዋዋለው አድ ርጎ ስለ ራሔልም ሰባት ዓመት ተገዛለት፡ ይህስ መዋዋል ነው መገዛቱን ኋላ ያመጣዋል ፡

ወወሀቦ ላባ ለያዕቆብ ራሄልሃ ፤

ላባም ለያዕቆብ ራሔልን ሚስት ልትሆነው ሰጠው ፡

፳፱፡ ወወሀባ ላባ ለራሄል ባላሃ ትኩና አመተ ፤

ላባም ለራሔል ታገለግላት ዘንድ ባላን ትልወት አድርጎ ሰጣት፡

፴፡ ወቦአ ያዕቆብ ኀበ ራሄል ወአፍ ቀራ ፈድፋደ እምልያ ፤

ያዕቆብም ራሔልን በተገናኛት ጊዜ ከልያ ይልቅ እጅግ አድ ርጎ ወደዳት ፡

ወተቀንየ ሎቱ ለላባ ካልአ ፯ተ ዓመተ በእንቲአሃ ፤

ፊት እንደ አርእስት አድርጎ ተናግሮት ነበርና አሁን አመ ጣው፡ ያዕቆብም ራሔልን ካገባ በኋላ ዳግመኛ ስለ እርስዋ ሰባት ዓመት አገለገለ ፡

፴፩፡ ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ትጸላዕ ልያ ፈትሐ ማኅፀና ፤

እግዚአብሔርም ልያ በያዕቆብ ዘንድ እንዳልተወደደች ባየ ጊዜ እንድትወልድ አደረጋት ፡

ወራሄልሰ ኮነት መካነ ፤

ራሔል ግን መካን ሆነች ፡

፴፪፡ ወፀንሰት ልያ ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሮቤል ፤

ልያም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለ ደች ስሙንም ሮቤል አለችው፤

እንዘ ትብል እስመ ርእየ እግዚአብ ሔር ትሕትናየ ፤

እግዚአብሔር መጠላቴን መዋ ረዴን ስለ አየ ልጅ ሰጠኝ ስትል

www.ethiopianorthodox.org

ሮቤል አለችው ፤ ሮቤል ማለት ርእየኒ አፍቀረኒ ማለት ነው፤

ወእምይእዜሰ ያፈቅረኒ ምትየ ፤

ከእንግዲስህ ወዲህ ባሊም ይወደኛል ስትል ሮቤል አለችው ፤

፴፫፡ ወዳግመ ፀንሰት ልያ ወወለደት ካልአ ወልደ ለያዕቆብ ፤

ልያም ዳግመኛ ፀንሳ ለያዕቆብ ሁለተኛ ልጅ ወለደችለት ፤

ወትቤ እስመ ሰምዓኒ እግዚአብሔር ስእለትየ ከመ እጸላዕ ወሰከኒ ዘንተ፤ ወሰመየቶ ስሞ ስምዖን ፤

ርእዮ ያለበት ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ተጠላሁ አውቆ ልመናዬን ሰምቶኛልና፤ (ስለ ሰማኝ) ልጅ ጨመረልኝ ስትል ስሙን ስምዖን አለችው ፤ ስምዖን ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

፴፬፡ ወፀንሰት ዓዲ ወወለደት ወልደ፤

አንዱን ሳንዱ ዓዲ እያለው ይሔዳል፤ ሦስተኛ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

ወትቤ እምይእዜሰ ኀቤየ ውእቱ ምትየ እስመ ወለድኩ ሎቱ ፫ተ ደቂቀ ወሰመየቶ ስሞ ሌዊ ፤

ሦስት ልጆች ወልጄለታለሁና እንግዲህስ ወዲህ ባሌ የኔ ገንዘብ ነው ስትል ስሙን ሌዊ አለችው ፤ ሌዊ ማለት ልዑት ማለት ነው፤ ወትከውን ልዑቀ ለእግዚአብሔር እንዲል ፤

፴፭፡ ወፀንሰት ዓዲ ወወለደት ወልደ፤

ዓዲ ለሌዊ ነው፤ አራተኛ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

ወትቤ ይእዜ በእንተዝ አአምኖ ለእግዚአብሔር አምላክ፤ ወበእንተዝ ሰመየቶ ስሞ ይሁዳ ፤

በእንተዝና በእንተዝ አንድ ወገን፤ አራተኛ ልጅ ስለ ሰጠኝ ስለዚህ ነገር ዛሬ ፈጣሪዬ እግዚአብሔርን አምነዋለሁ አመስግነዋለሁ ስትል ስሙን ይሁዳ አለችው ፤ ይሁዳ ማለት ተአማኒ ማለት ነው ፤

ወአቀመት ወሊደ ፤

ከዚህ በኋላ መውለድ ተወች ።

## ምዕራፍ ፴

፩፡ ወሶበ ርእየት ራሔል ከመ ኢወለደት ለያዕቆብ ፤ ቀንአት ላዕለ ልያ እኅታ ፤

ራሔልም ለያዕቆብ ልጅ እንዳል ወለደችለት ባየች ጊዜ በእኅትዋ በልያ ላይ ቀናች ፤

ወትቤሎ ለያዕቆብ ሀበኒ ወልደ ወእመ አኮ እመውት ፤

ያዕቆብን ወንድ ልጅ ትሰጠኝ እንደሆነ ስጠኝ ያለዚያ እሞታለሁ አለችው፤ ትቀማጠልበታለች ፤



፪፡ ወተምዓ ያዕቆብ ለራሔል ወይቤላ ከመ እግዚአብሔርኑ እከውን አነ ዘእከልአኪ ፍሬ ከርሥኪ ፤

ያዕቆብም የማኅፀንሽ ፍሬ የሚሆን ልጅን የምሰጥ የምነሳ እኔ እግዚአብሔር ነኝን? ብሎ ራሔልን ተቈጣት ፤

፫፡ ወትቤሎ ራሔል ነያ አመትየ ባላ ሑር ባእ ኀቤሃ ወትለድ ዲበ አብራክየ ወእትዋለድ አነሂ እምኔሃ ፤

ራሔልም ያዕቆብን እንዲህ አለችው፤ እነሆ ባሪያዬ ባላ አለች ድረስባት፤ በእኔ ተተክታ (ተገብታ) እንድትወልድ ፤ እኔም ከርስዋ በተወለደው ልጅ ከአንተ እንድዛመድ ብላ ፤

፬፡ ወወሀበቶ ባላሃ ትኩና ብእሲተ፤

ሚስት ትሆነው ዘንድ ባላን ሰጠችው ፤

ወቦአ ያዕቆብ ኀቤሃ ወፀንሰት ባላ ወወለደት ወልደ ለያዕቆብ ፤

ያዕቆብ ከባላ ቢደርስባት ባላም ፀንሳ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤

፭፡ ወትቤ ራሔል ፈትሐ ሊተ እግዚአብሔር ወሰምዐኒ ቃልየ ወወሀበኒ ወልደ ፤

ራሔልም፤ እግዚአብሔር ልመናዬን ሰምቶ ፈርዶ ወንድ ልጅ ሰጠኝ አለች ፤

ወበእንተዝ ሰመየቶ ስሞ ዳን ፤

እግዚአብሔር ፈረደልኝ ስትል ስሙን ዳን አለችው፤ ዳን ማለት ፈትሐ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

፮፡ ወፀንሰት ዓዲ ባላ አመተ ራሔል፤ ወወለደት ካልአ ወልደ ለያዕቆብ ፤

የራሔል ገረድ ባላም ዳግመኛ ፀንሳ ለያዕቆብ ሁለተኛ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤

፯፡ ወትቤ መጠቀኒ እግዚአብሔር አዕበየኒ ወአልዐለኒ ወመሰልክዋ ለእኅትየ፤ ወኃየልክዋ፤ ወሰመየቶ ስሞ ንፍታሌም ፤

እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አደረገኝ፤ እኅቴንም ተበራትቼ መሰልኳት ስትል፤ ስሙን ንፍታሌም አለችው፤ ንፍታሌም ማለት ዘንባባ ማለት ነው ፤

፰፡ ወሶበ ርእየት ልያ ከመ ኢወለደት ወኃደገት ወሊደ ፤

ልያም መውለድ ትቶአት ፤ ከመውለድ እንደተገታች ባየች ጊዜ ፤

ነሥአታ ለዘለፋ አመታ፤ ወወሀበቶ ለያዕቆብ ትኩና ብእሲተ ፤

እኔ የባሪያ ጥቂ ነኝ ? ብላ ዘለፋን ሚስት ትሆነው ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወፀንሰት ዘለፋ ለያዕቆብ ወወለ ደት ወልደ ።

ዘለፋም፣ ፀንሳ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

፲፡ ወትቤ ልያ አብፃዕኩ አነኒ፡ ወሰ መየቶ ስሞ ጋድ ።

እኔም ራሴን ንዑድ ክቡር አሰ ኘሁ ስትል ስሙን ጋድ አለችው፤ ጋድ ማለት አክሊል ማለት ነው ፤

፲፩፡ ወፀንሰት ዓዲ ዘለፋ ወወለደት ለያዕቆብ ።

ዳግመኛም ዘለፋ ፀንሳ ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

፲፪፡ ወትቤ ልያ ብፅዕት አነ ወያስተ በፅዓኒ አንስት ወሰመየቶ ስሞ አሴር።

ልያም እንግዲህ ወዲህ እኔም ንዕድ ክብርት ነኝ ፣ ሴቶችም ያከብሩኛል ስትል ስሙን አሴር አለችው ፣ ለጊዜው እኔ አራት ልጆች፣ ባሪያዬ ሁለት ልጆች፣ ከወለድን ችግር አያገኘኝም ስትል ነው፣ ፍጻሜው ግን ባለ ጸጋ የሚሆን ነውና እንደ ትን ቢት አናግሮአታል፣ አሴር ጽጉብ እክል ወውእቱ ይሁብ ሲሳየ ለመላእክት ብሎ እንዲያመ ጣው፤ አሴር ማለት ጽጉብ እክል ማለት ነው ፤

## ጉባኤ

ወሖረ ሮቤል በመዋዕለ ማዕረረ ሥር ናይ፡ ወረከበ ኮለ በሐቅል፣ ወአም ጽአ ላቲ ለእሙ ፣

ሮቤልም የስንዴ አዝመራ በሚ ታጨድበት ወራት ወደ ዱር ቢሄድ በምድረ በዳ እንኮይ አግኝቶ ለናቱ ይዞላት መጣ ፤

፲፫፡ ወትቤላ ራሔል ለልያ ሀብኒ ኮለ ዘወልድኪ ፣

ራሔልም ልያን ልጅሽ ያመጣ ውን እንኮይ ስጭኝ አለቻት፤

፲፬፡ ወትቤላ ልያ ኢአከለኪኑ ዘነሣ እከኒ ምትየ፣ ዓዲ ትፈቅዲ ትንሥ እኒ ኮለሂ ዘወልድየ ፣

ልያም ራሔልን ባሌን የቀማሽኝ አነሰሽና ፤ ደግሞ ልጄ ያመጣ ውን እንኮይ ልትቀሚኝ ትፈል ጊያለሽን ? አለቻት ፤

ወትቤላ ራሔል ለልያ አኮ ከማሁ ፣

ራሔልም ልያን ነገሩ እንዲህ አይደለም አለቻት ፤

ለይቢት የም ኅቤኪ በእንተ ኮል ዘወልድኪ ፣

እንዲያው ስጭኝ አልልሽም ፤ ልጅሽ ያመጣውን እንኮይ ስጭ ኝና ስለዚህ ፈንታ ዛሬ ያዕቆብ ካንቺ ጋራ ይደር አለቻት ፤

ወወሀበታ፣

ልያም ይሁን ብላ እንኮዩን ለራሔል ሰጠቻት ፤



፲፭፡ ወአተወ ያዕቆብ እምሐቅል ፍና ሠርክ ፣

ያዕቆብም ከዱር ወሎ ማታ ገባ ፤

ወተቀበለቶ ልያ ፍና ሠርክ ወት ቤሎ ኅቤየ ትበይት ዮም፣ እስመ ተሣየጥኩከ በኮል ዘወልድየ ፣

ልያም ማታ ጊዜ ሲመጣ ጠብቃ፣ በልጄ ዕንኮይ ገዝቼሃ ለሁና ዛሬ ከኔ ጋራ ታድራለህ አለችው ፤

ወቤተ ኅቤሃ በይእቲ ሌሊት ፣

ያዕቆብም ልያ እንደነገረችው በዚያች ሌሊት ከእርስዋ ጋራ አደረ ፤

፲፮፡ ወሰምዓ እግዚአብሔር ለልያ ወጸንሰት ወወለደት ወልደ ኃምሰ ፣

እግዚአብሔርም የልያን ልመና ዋን ሰምቶ፤ መገፋቷን አይቶ፤ ፀንሳ አምስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች ፤

፲፯፡ ወትቤ ልያ ወሀበኒ እግዚአብ ሔር ዓስብየ እስመ ወሀብክዋ ኮለ ሐቅል ዘወልድየ ፣ ወሰመየቶ ስሞ ይሳኮር ፣

ልያም የልጄን እንኮይ ስለ ሰጠሁዋት ማለት የገዛ ባሌን በገንዘብ ስለ ገዛሁት፣ እግዚአ ብሔር ዋጋዬን ሰጠኝ ስትል ስሙን ይሳኮር አለችው ፤ ዐስብ ብሂል፤ (በእንኮይ የተገዛ ስትል)፣

ይሳኮርም ማለት ዋጋ ማለት ነው ፤

፲፰፡ ወፀንሰት ዓዲ ልያ ወወለደት ወልደ ሳድሰ ለያዕቆብ ፣

ልያም ዳግመኛ ፀንሳ ለያዕቆብ ስድስተኛ ወንድ ልጅ ወለደች ለት ፤

፲፱፡ ወትቤ ልያ ፈትሐ ሊተ እግዚ አብሔር ሠናየ ፍትሐ ፣

ከወለደችም በኋላ ልያ እንዲህ አለች፣ እግዚአብሔር መልካም ፍርድ ፈረደልኝ ፤

እምዮምሰ እንከ ያፈቅረኒ ምትየ እስመ ወለድኩ ሎቱ ፮ተ ደቂቀ ፤ ወሰመየቶ ስሞ ዛብሎን ፣

ስድስት ልጆች ወልጄለታለሁና እንግዴህስ ከዛሬ ጀምሮ ባሌ ይወድደኛል ስትል ስሙን ዛብ ሎን አለችው ፤ ዛብሎን ማለት መስተሳልም ማለት ነው ፤

፳፡ ወእምዝ ወለደት ወለተ ወሰመ የታ ስማ ዲና ፣

ስድስት ወንዶችንም ከወለደች በኋላ ልያ ሴት ልጅ ወለደች ፤ ስምዋንም እግዚአብሔር ፈረ ደልኝ ስትል ዲና አለቻት ፤ ዲና ማለት ፍትሕ ማለት ነው፤ ዳን ማለት ፈትሐ እግዚአብሔር ማለት እንደሆነ፤ አንድም የልጅ መዲና አደረገኝ ስትል ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፡ ወተዘከራ እግዚአብሔር ለራኄል ወፈትሐ ማኅፀና ፤

እግዚአብሔርም ራሔልን በረድኤት አሰባት፤ እንድትወልድም አደረጋት ፡ (ሐተታ) ፈትሐ ማለቱ ፤ መክና ትኖር ነበርና መውለድዋን ሲያይ ነው ፡

፳፪፡ ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ለያዕቆብ ፤

ፀንሳም ለያዕቆብ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፡

ወትቤ አውፅአ እግዚአብሔር እምላዕሌየ ዝንጓጌየ ፤

ከወለደችም በኋላ እግዚአብሔር ስድቤን ከላዬ ላይ አራቀልኝ አስወገደልኝ አለች፤ (ሐተታ) ምን ብለው ይሰድቡዋት ኑረዋል ? ቢሉ ፤ እፀተ ማኅፀን ፤ ይብስተ አጥባት፤ ኀጥአተ በረከት፤ እያሉ ይሰድበዋት ነበር፤

፳፫፡ ወሰመየቶ ስሞ ዮሴፍ ወትቤ ይወስከኒ እግዚአብሔር ወልደ ካልአ፤

እግዚአብሔር ሁለተኛ ልጅ ይጨምርልኛል ስትል ስሙን ዮሴፍ አለችው ፤ ዮሴፍ ማለት ገበገብ ማለት ነው ፤ ገበገባኒ ማለት፤ ዓመት ዓመት ድገመኝ ማለት ነው ፤ ገበገባኒ እንዲል የጋፋት ሰው ፡

፳፬፡ ወሶበ ወለደት ራሔል ዮሴፍሃ ይቤሎ ያዕቆብ ለላባ ፤

ራሔልም ዮሴፍን ከወለደች በኋላ ያዕቆብ ላባን እንዲህ አለው ፡

ፈንወኒ ከመ እሖር ብሔርየ ወውስተ ምድርየ ፤

ወደ አገሬ ወደ ርስቴ እመለስ ዘንድ አሰናብተኝ ፡

፳፭፡ ወሀበኒ ደቂቅየ ወአንስቲያየ ዘበእንቲአሆን ተቀነይኩ ለከ ፤

ስለ እርሳቸው የተገዛሁልህ ሚስቶቼንና ልጆቼንም ስጠኝ ፡

ወለሊከ ተአምር ዘከመ ተቀነይኩ ለከ ፤

ለሚስቶቼና ለልጆቼ ስል እንደ ተገዛሁልህም አንተ ታውቃለህ አለው ፡

፳፮፡ ወይቤሎ ላባ ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ እስመ አእመርኩ ከመ ባረከኒ እግዚአብሔር በእንቲአከ ፤

ላባም ያዕቆብን በፊትህ ባለም ዋልነትንስ ካገኘሁ ማለት፤ ነገሬንስ ወደህ የምትቀበለኝ ከሆነ፤ ባንተ መምጣት እግዚአብሔር እንዳከበረኝ አውቃለሁና ፡

፳፯፡ ፍልጥ ሊተ ዓስበከ ዘእሁበከ፤

የምሰጥህን ደመወዝህን ለይተህ ንገረኝ አለው ፡



፳፰፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ኢተአምርኑ ዘከመ ተቀነይኩ ለከ ፤

ያዕቆብም ደመወዝህን ንገረኝ የምትለኝ የተገዛሁልህን አታውቅምን አለው ፡

ወሚመጠን እማንቱ እንስሳከ ዘኑ ቤየ ፤

ከእኔ ዘንድ ያሉትን በጎች ጠብቅ ብለህ የሰጠኸኝ ጊዜ ምን ያህል ነበሩ ፡

፳፱፡ እስመ ኅዳጣተ ረከብከዎን ፤

ጥቂቶች ነበሩ እኮን፤ ጥቂቶች አልነበሩምን ፡

ወመልዓ ወበዝኃ፤

አሁን ግን ፈጽመው በዝተዋል ፡

ወባረከኮን እግዚአብሔር በእግረ ዚአየ፤

በኔ ትጋት ከለመለመ ሣር ፤ ከጠራ ውሀ እየወሰድኩ ስለ መገብኋቸው፤ እግዚአብሔር ከብቶችህን አበዛቸው ፡ አንድም በእኔ መምጣት እግዚአብሔር በጎችህን አበዛቸው ፡

ወይእዜኒ ማእዜኑመ እገብር አንሰ ቤተ ለርእስየ ፤

እኔስ ለራሴ ቤት ሠርቼ ጎጆ የምወጣ መቼ ነው ? አንድም ጥሪት ቁሪት የማበጅ መቼ ነው ? አለው ፡

፴፡ ወይቤሎ ላባ ምንተኑመ አሁበከ፤

ላባም ያዕቆብን የምሰጥህ ምንድን ነው? ምን ስጠኝ ትላለህ? አለው ፡

ወይቤሎ ያዕቆብ አልቦ ዘትሁበኒ ወኢምንተኒ ፤

ያዕቆብም ላባን አሁን ምንም ምን ስጠኝ የምልህ ነገር የለም፡

ለእመ ገበርከ ሊተ ዘንተ ነገረ ፤ እርኢ ካዕበ አባግዒከ ወአዐቅብ ፤

እርኢና አዐቅብ አንድ ወገን አሁን ወደፊት የምነግርህን ነገር ካደረግህልኝ ዳግመኛ በጎችህን እጠብቃለሁ ፡

፴፩፡ ወይኅልፍ ኵሉን አባግዒከ ዮም ፤

አሁንም በጎችህ ሁሉ በፊትህ ይለፉና ፡

ፍልጥ ሊተ እምውስቴቶን ኵሎ በግዐ ዘፀዓዳ ፀጕሩ ወዘኵሳኵሶ ኅብሩ ይኩኑኒ ዐስብየ ፤

ከበጎችህ ጠጕራቸው ነጫጭ የሆኑትንና መልኩ አይነቱ ዝንጕርጕር የሆነውን ለይተህ ስጠኝ ፤ ይህ ለኔ ደመወዜ ይሁነኝ አለው ፡

፴፪፡ ወኵሉ ዘኢኮነ ኵሳኵሶ ወዘኢኮነ ፀዓዳ ፍጥረቱ ለከ ይኩንከ ውእቱ፤

አይነቱ ዝንጕርጕር ያልሆነውና መልኩ ነጭ ያልሆነው ግን ላንተ ይሁንህ አለው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፴፫፤ ወይቤሎ ላባ ይኩን በከመ ትቤ ፤
ላባም እንዳልክ ይሁን አለው፤

፴፬፤ ወፈለጠ በይእቲ ዕለት አባ ሕኩ አባግዕ ዘኵሳኵስ ወዘፀዓዳ ወዘ ቀይሕ ኀብሩ ፤
በዚያችም ቀን ላባ ነሬጩንም ዝንጕርጕሩንም የበጉን አውራ፤ ነሬጩንም ዝንጕርጕሩንም መልኩ ዳንግሌ የሆነውንም የፍ የሉን አውራ ለይቶ ፤

ወወሀቦሙ ለደቂቁ ፤
ላባ ያዕቆብ እየሰረቀ ያንጠላጥ ላል ይዛችሁ ሒዱ ብሎ ለል ጆቹ ሰጣቸው ፤

፴፭፤ ወርኀቀ ምሕዋረ ሠሉስ መዋ ዕል ማዕከሎሙ ወማዕከለ ያዕቆብ ፤
የላባ ብላቴኖች በነሱና በያዕ ቆብ መካከል ሦስት ቀን የሚ ያስኬድ ጐዳና ርቀው ሔዱ ፤

ወያዕቆብሰ ይርኢ አባግዓ ላባ ዘተ ርፉ ፤
ያዕቆብ ግን ተመርጠው የቀ ሩትን የላባን በጎች ይጠብቅ ነበር ፤

፴፮፤ ወነሥአ ሎቱ ያዕቆብ በትረ ዘልብን ሐመልሚለ ፤ ወዘከርካዕ ዓቢየ ፤
እርጥብ የልምጭ በትርና ታላቅ የሎሚ በትር እንሥቶ ፤

ወለሐፀ ያዕቆብ ወአሰሰለ ቅርፍቶ ፤
ያዕቆብ ቅርፍቱን ልጦ ጣለው፤

ወአስተርአየ ፀዓዳሆን ለእማንቱ አብ ትር እለ ለሐፀ ፤
እነዚህም ያዕቆብ የላጣቸው በት ሮች ነጭ ሁነው ታዩ ፤

፴፯፤ ወወደዮን ለእማንቱ አብትር ውስተ ገብላት ዘምስታየ ማይ ፤
እነዚያንም በትሮች በጎች በሚ ጠጡበት ገንዳ ላይ ጣላቸው፤

ከመ ሶበ መጽአ እማንቱ አባግዕ ይስ ተያ ማየ ይኩና ቅድሚሆን እማንቱ አብትር ፤
በጎቹ ውሀ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ በትሮቹ በፊታቸው ሁነው ይታዩ ዘንድ ፤

፴፰፤ ወሶበ መጽአ እማንቱ አባግዕ ይስተያ ማየ ፀንሳ በአርአያሆን ለእ ማንቱ አብትር ፤
በጎች ውሃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ በትሮችን አስመስለው ፀንሰው፤

ወወለዳ ዐባግዓ ፀዓዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወኵሳኵሰ ፤
ነሬጩን፤ ሐመደ ክቦውን፤ ዝን ጕርጕሩን ወለዱ ፤

፴፱፤ ወቤጸ ያዕቆብ ተባዕተ አባግ ዒሁ ፤
ያዕቆብም ወንድ ወንዶቹን በጎች ለየ ፤

ወፈለጠ ያዕቆብ አባግዓ ወአቀሞን ቅድመ አባሕኵ ዐዓዳ ወዘኅብረ ሐመድ ፀዓዳ ፤
አውራ አውራውንም ከለየ በኋላ ያዕቆብም ዳግመኛ እን



ስት እንስቱን ለይቶ ዝንጕር ጕር ሐመደ ክቦ ነጭ በሚሆኑ አውራዎች ፊት አቆማቸው ፤

ወፈለጠ መራዕየ እንተ ባሕቲቶን፤
መንጋውን ለብቻቸው ለየ እንጂ ፤

ወኢደመሮን ምስለ አባግዓ ላባ ፤
ከላባ በጎች ጋር አላገናኛቸ ውም ፤

፵፤ ወእምዝ እንከ አመ መዋዕል በዘቦቱ ይፀንሳ እማንቱ አባግዕ ይሰ ይሞን ያዕቆብ ለእማንቱ አብትር ቅድመ አባግዕ ውስተ ገብላት ፤
ከዚህም በኋላ በጎቹ በሚፀን ሱበት ወራት ያዕቆብ እሊያን በትሮች በገንዳው ውሥጥ በበ ጎቹ ፊት ለፊት ያኖራቸው ነበር፤

ከመ ይፅንሳ በአርአያሆን ለእማንቱ አብትር ፤
እሊያን በትሮች አስመስለው ይፀንሱ ዘንድ ፤

፵፩፤ ወእምከመ ወለዳ እማንቱ አባ ግዕ ኢይሰይሞን እንከ ፤
በጎቹ ከወለዱ በኋላ ግን እሊ ያን በትሮች በገንዳው ውስጥ አያኖራቸውም ነበር ፤

ወከነ ኰሉ ዘቦቱ ትእምርት ለያዕ ቆብ ፤
ምልክት ያለው ዝንጉርጕር፤ ነጭ ፤ ቀይ የሆነው ሁሉ ለያ ዕቆብ ሆነ ፤

ወዘአልቦ ትእምርት ለላባ ፤
ምልክት የሌለው ግን ለላባ ሆነ ፤ ሦስት በትር አምጥቶ ሁለቱን ጨርሶ ልጧቸዋል ፤ አንዱን ቅጥልጣል አድርጎታል፤ ይህም ምሳሌ ነው ፤ አብትር የሦስቱ አካላት የተላጡት የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቅጥልጣል የሆ ነው የወልድ አምሳል፤ አምላክ ወሰብእ ነውና ፤ አባሕኵ የመ ምህራን፤ አባግዕ የምእመናን፤ ውሀው የጥምቀት ፤ አባግዕ አብ ትርን እየመሰሉ መወለዳቸው፤ ምእመናንም በጥምቀት ምክን ያት ሥላሴን መስለው ይወለዳ ሉና፤ ላባ የዲያብሎስ፤ ያዕቆብ የጌታ ምሳሌ፤ ምልክት ያለው ለያዕቆብ ፤ ምልክት የሌለው ለላባ እንደሆነ ፤ ሀብተ ውል ድና ስመ ክርስትና ያለው ለጌታ፤ ሀብተ ውልድና ስመ ክርስትና የሌለው ለዲያብሎስ ሁኗልና ፤

ወብዕለ ያዕቆብ ጥቀ ፈድፋደ ፤
ያዕቆብም እጅግ ፈጽሞ ከበረ፤

ወአጥረየ አግብርተ ወአዕማተ ፤
ሴቶችንም ወንዶችንም ባሮች ገዛ፤

ወብዙኃ እንስሳ ፤
ብዙም ከብት ፤

አልህምተ ወአባግዐ ፤
ላሞችም በጎችም ፤

www.ethiopianorthodox.org

አግማለ ወአዕዱገ፣

ግመሎችም በቅሎዎችም አግ ኝቶ ነበረ ።

## ምዕራፍ ፴፩

፩፥ ወሰምዐ ያዕቆብ ነገሮሙ ለደቂቀ ላባ ዘይቤሉ ነሥአ ያዕቆብ ኵሎ ንዋየ አቡነ ፣

ያዕቆብም የላባ ልጆች የአባታ ችን የላባን ገንዘብ ሁሉ ጨርሶ ወሰደው ብለው የተናገሩትን ሰማ ፤

ወእምንዋየ አቡነ አጥረዮ ለዝንቱ ኵሉ ክብር ፣

ከአባታችን ገንዘብ የተነሣ ይህን ሁሉ ክብር አገኘ ያሉትንም ሰማ ፤

፪፥ ወርእዮ ያዕቆብ ለላባ ከመ ኢኮነ ከመ ትካት ገጹ ምስሌሁ ፣

ያዕቆብም የላባ ፊቱ እንደቀድ ሞው ከእሱ ጋራ እንዳይደለ፣ እንደተለወጠ በአየ ጊዜ መንገ ዴን አቅናልኝ ብሎ ወደ እግዚ አብሔር አመለከተ ፤

፫፥ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለያዕቆብ፥ ሑር ወግባዕ ብሔረ አቡከ ወአዝማ ዲከ ወአነ እሄሉ ምስሌከ ፣

እግዚአብሔርም ያዕቆብን እኔ በረድኤት ከአንተ ጋራ አለሁና ወደ ዘመዶችህ ወደ አባትህ አገር ተመልሰህ ግባ አለው ፤

፬፥ ወጸውዖን ያዕቆብ ለልያ ወለራሔል ውስተ ሐቅል ኀበ ምርዓዩ ፣

ቤት እንደ ልብ አያናግርምና፣ ያዕቆብ ልያንና ራኄልን በጎቹን ወደሚያሠማራበት ምድረ በዳ ጠራቸው ፤

፭፥ ወይቤሎን ናሁ አነ እሬኢ ገጸ አቡክን ከመ ኢኮነ ምስሌየ ከመ ትካት ፣

እነሆ የአባታችሁ ፊት እንደ ቀድሞው ከእኔ ጋራ እንዳል ሆነ አያለሁ ፤

ወአምላኩ ለአቡየ ሀሎ ምስሌየ ፣

የአባቴ ፈጣሪ ግን ከእኔ ጋራ በረድኤት አለ ፤

፮፥ ተአምራ ከመ በኵሉ ኃይልየ ተቀነይኩ ለአቡክን ፣

በፍጹም ትጋቴ በተቻለኝ ሁሉ ለአባታችሁ እንደ ተገዛሁለት ታውቃላችሁ ፤

፯፥ ወአቡክንሰ አኅዘነኒ ፡ ወወለጠ አስበየ ዐሥርተ ጊዜ ፣

አባታችሁ ግን ዐሥር ጊዜ ደመ ወዜን እየለዋወጠ አሳዘነኝ ፤

ወኢየብሖ እግዚአብሔር ያኅስም ላዕሌየ ፣

ነገር ግን በእኔ ክፉ ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር አላሰናበ ተውም ፤



፰፥ ወለእመ ይቤለኒ ዘኅብር ይኩን አስበከ ይወልዳ ኵሎን አባግዕ ዘኅ ብር ፣

ዝንጕርጕር ዝንጕርጕር ሲወ ለድ ደመወዝህ ይሁን ቢለኝ፣ በጎቹ ሁሉ ዝንጕርጕር ዝንጕ ርጕር ይወልዱ ጀመር ፤

ወለእመ ይቤለኒ ፀዓዳ ይኩን አስበከ ይወልዳ ኵሎን ፀዓዳ ፣

ዳግመኛም ነጫጭ ሲወለድ ደመ ወዝህ ይሁን ቢለኝ በጎቹ ሁሉ ነጫጭ ይወልዳሉ ፤

፱፥ ወነሥአ እግዚአብሔር ኵሎ አባ ግዒሁ ለአቡክን ወወሀበንዮን ሊተ ፣

እንዲህ አድርጎ እግዚአብሔር የአባታችሁን በጎች ሁሉ ለእኔ ሰጠኝ ፤

፲፥ ወእምዝ አመ ይፀንሳ እሬኢ በአ ዕይንትየ በሕልም ፣

ከዚህም በኋላ በሚፀንሱበት ጊዜ በዓይኔ እንደማየው አድርጌ በሕልም ይታየኝ ነበር ፤

ወናሁ አባሕኰ ዘአባግዕ ወዘአጣሊ የዓርጉ ዲበ አባግዕ ወዲበ አጣሊ ፀዓዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወኰሳኵስ፣

እነሆ የበጎቹ አውራዎች ከበ ጎቹ፣ የፍየሎቹም አውራዎች ከፍየሎቹ፣ በነጩም በሐመደ ክቦውም፣ በዝንጕርጕሩም ላይ ሲንጠላጠሉ በሕልሜ አየሁ ፤

፲፩፥ ወይቤለኒ እግዚአብሔር በሕ ልም ያዕቆብ ያዕቆብ ፣

እግዚአብሔርም በሕልም ያዕ ቆብ ያዕቆብ ብሎ ጠራኝ፤ በአ ገራቸው ደጊመ ቃል ልማድ ነውና ፤

ወእቤ ነየ አነ ምንትኑ ፣

አቤቱ እነሆ እኔ አለሁ ምንድ ነው አልኩ ፤

፲፪፥ ወይቤለኒ ነጽር በአዕይንቲከ ወርኢ አባሕኰ ዘአባግዕ ወዘአጣሊ፥ የዓርጉ ዲበ አባግዕ ወዲበ አጣሊ ፀዓዳ ወዘኅብረ ሐመድ ወዘኰሳኵስ ፣

የበጎቹ አውራዎች ከበጎቹ፣ የፍ የሎቹ አውራዎች ከፍየሎቹ፣ በነጩም ፣ በዝንጕርጕሩም ፣ በሐመደ ክቦውም ላይ ሲንጠ ላጠሉ ተመልከት አለኝ ፤

እስመ ርኢኩ ኵሎ ዘይገብር ላዕሌከ ላባ ፣

ላባ በአንተ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ አይቻለሁና ፤

፲፫፥ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላ ክከ ዘአስተርአይኩከ በብሔር በኀበ ቀባዕከ ሊተ ሐውልተ ወበህየ በፃዕከ ሊተ ብፅዓተ ፣

ዘይት ያፈሰስክበትን ደንጊያ ባቆምክበት፤ ለእኔም ስእለት በተሳልክበት ቦታ የታየሁህ ፈጣ ሪህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይእዜኒ ተንሥእ ወሖር ውስተ ብሔር ኀበ ተወለድከ ፤

አሁንም ከዚህ ተነሥተህ ወደ ተወለድክበት አገር ሂድ ።

ወአነ እሄሉ ምስሌከ ፤

እኔም ከአንተ ጋራ በረድኤት አድሬብህ እኖራለሁ አለኝ አላቸው ።

፲፬፡ ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ቦኑ እንከ ዘብነ ርስት ውስተ ቤተ አቡነ፤

ልያና ራሔልም ለያዕቆብ እንዲህ ብለው መለሱለት፤ እንግዲህ ወዲህ በአባታችን ቤት ተቀምጠን የምናገኘው ርስት አለ ይሆን ?

፲፭፡ አኮኑ ከመ ነኪር ንሕነ በኀቤሁ፤

በእሱ ዘንድ እኛ እንደ ባዕድ አይደለንምን ?

ወሤጠነ ወበልዐ ሤጠነ ፤

እኛንስ ሸጦ ዋጋችንን የበላ አይደለምን ?

፲፮፡ ወዝ ኵሉ ክብር ዘነሥአ እግዚአብሔር እምአቡነ ለነ ውእቱ ወለውሉድነ ፤

እግዚአብሔር ከአባታችን ነሥቶ የሰጠህ ይህ ሁሉ ክብር ፤ ጌትነት ለእኛስ ለልጆቻችንስ አይደለምን ?

ወይእዜኒ ግበር ኵሎ ዘይቤለከ እግዚአብሔር ፤

አሁንም እግዚአብሔር ያዘዘህን ሁሉ አድርግ አለት ።

፲፯፡ ወተንሥአ ያዕቆብ ወነሥአ አንስቲያሁ ወደቂቆ ወዐዓኖሙ ዲበ አግማል ፤

ያዕቆብም ሚስቶቹንም ልጆቹንም ይዞ፤ በግመል ጭኖ ተነሣ፤

፲፰፡ ወነሥአ ኵሎ መራዕይሁ ፤ ወቈሳቍሳቲሁኒ ዘአጥረየ በማዕከለ አፍላግ ወኵሎ ዘዚአሁ ፤

በሁለቱ ወንዞች መካከል ባለች በሶርያ የጠራቀመውን መንጋ ውንና ታላላቁን፤ ጥቃቅኑን ገንዘቡን ሁሉ ይዞ ያዕቆብ ጕዞ ጀመረ ።

ወሖረ ኀበ አቡሁ ይስሐቅ ውስተ ምድረ ከነዓን ፤

አባቱ ይስሐቅ ወደ አለበት ወደ ምድረ ከነዓን ሄደ ።

፲፱፡ ወላባሰ ሖረ ኀበ ይቀርዕ አባግዒሁ ፤

ላባ ግን በጎቹን ወደሚሸልት በት ቦታ ሄዶ ነበር ።

ወሰረቀት ራኄል አማልክተ አቡሃ፤

ራኄልም የአባቷን የላባን ጣዖት ሰርቃ ይዛ ሔደች ። ስለምን ቢሉ አመልካቸዋለሁ ብላ ። አንድም የወርቅ ነውና ገንዘብ ይሆነኛል ብላ ።

፳፡ ወያዕቆብሰ ኀብዮ ለላባ ሶርያዊ ወኢያይድዮ ከመ የሐውር ፤

ያዕቆብ ግን ለሦርያው ሰው ለላባ ተሰርቆት ሔደ እንጂ እንዲሔድ አልነገረውም ነበረ ።



፳፩፡ ወሖረ ውእቱ ወኵሉ ዘዚአሁ፤

እሱም ወገኖቹን ሁሉ ይዞ ሔደ እንጂ ።

ወዓደወ ፈለገ ወኀደረ በደብረ ገለዓድ ፤

ወንዙን ተሻግሮ በገለዓድ ተራራ ሰፈረ ።

፳፪፡ ወዜነውዎ ለላባ ሦርያዊ ከመ ሖረ ያዕቆብ ፤

ለሦርያው ሰው ለላባም ያዕቆብ ልጆችህን ይዞ ሔደ ብለው ነገሩት ።

፳፫፡ ወነሥአሙ ላባ ለኵሎሙ አኃዊሁ ፤ ወዴገኖሙ ምሕዋረ ሠሉስ መዋዕል ወረከቦሙ በደብረ ገለዓድ፤

ላባም ወንድሞቹን ሁሉ ይዞ ፤ ያዕቆብ ሦስት ቀን የተጓዘውን መንገድ ተከትሎ በገለዓድ ተራራ አገኛቸው ። ባለፈው ወርኀቁ ምሕዋረ ሠሉስ አለ፤ ላባ ሳለ ሔደ እንዳንል በጎቹን ሊሸልት ላባ ሔዶ ነበር አለ፤ አይጣላም? ቢሉ አይጣላም፤ የላባ መልእክተኛ የተነሣ ዕለት፤ ያዕቆብ አስቀድሞ ተነሣ፤ የላባ መልእክተኛ ገስግሶ ከላባ ዘንድ ገባ፤ ላባም ገስግሶ ያዕቆብ ከተነሣ በት ቦታ ደረሰ፤ ለያዕቆብ ሁለት ቀን ሆነው ። ያዕቆብ ሦስት ቀን የሔደውን ገስግሶ ደረሰ በት ፤ በአራተኛው ቀን ያዕቆብና ላባ ተገናኝተዋል፤ አንድም ምሕዋረ ሰሙን ይላል፤ ያዕቆብ የተነሣ ዕለት የላባ መልእክተኛ ተነሥቶ ሳይርቅ ብሎ ዕለቱን ገስግሦ ለላባ ነግሮታል፤ ላባ መቼም አይመልጠኝም ብሎ ሁለት ቀን አደረ፤ ያዕቆብ ሦስት ቀን ሔደ ። ላባ በአራተኛው ቀን ተነሣ ። ከቤቱ ገባ ።

ያዕቆብ አራት ቀን ሔደ፤ ላባ ከቤቱ ተነሥቶ ያዕቆብ ሰባት ቀን የሔደውን ላባ በሦስት ቀን ደርሷል፤ ተሠፋፍረው አደሩ፤ በስምንተኛው ቀን ተገናኝተዋል፤ ስለዚህ ምሕዋረ ሰሙን አለ፤ አንድም ያዕቆብ የተነሣ ዕለት የላባ መልእክተኛ ተነሣ፤ በሦስት ቀን ከላባ ዘንድ ደረሰ ። ላባ ገስግሦ ከቤቱ በአንድ ቀን ደረሰ፤ ያዕቆብ አራት ቀን ሔደ፤ ላባ ከቤቱ ተነሥቶ ያዕቆብ ሰባት ቀን የሔደውን በሦስት ቀን ደረሰ ፤ ተሠላልፈው አድረው በስምንተኛው ቀን ተገናኝተዋል፤ አንድም ወሶበሂ ነሐውር በእግረ ደቂቅ ነሐውር ይላል፤ ያዕቆብ ጥቂት ጥቂት እያለ ነው የሚሔደው ብሎ፤ ያዕቆብ ሰባት ቀን የሔደውን ላባ ሦስት ቀን ገስግሶ ተሠፋፍረው አድረው በስምንተኛው ቀን ተገናኝተዋል ። ምሕዋረ ሰሙን መዋዕል ያለው ይህ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፡ ወመጽአ እግዚአብሔር ኀበ ላባ ሶርያዊ በሕልም ሌሊተ ፤

እግዚአብሔርም ለሶርያው ሰው ለላባ ሌሊት መጥቶ በራእይ ታይቶ ፡

ወይቤሎ ዑቅ ኢትንብብ ኅሡመ ላዕለ ያዕቆብ ገብርየ ፤

በወዳጄ በያዕቆብ ላይ ክፉ ነገር እንዳትናገር ዕወቅ አለው፤

፳፭፡ ወረከቦ ላባ ለያዕቆብ ፤

ላባም ያዕቆብን አገኘው ፡

ወያዕቆብሰ ይተክል ሐይመቶ ውስተ ደብር ፤

ያዕቆብ ግን ጦር ይዞ እንደ ተከተለው ሳያውቅ ድንኳኑን በተራራ ላይ ተክሎ ሠፍሮ ነበር ፡

ወአቀሞሙ ላባ ለአኃዊሁ ውስተ ደብረ ገለዓድ ፤

ላባም ጦር ያየ እንደሆነ ይደ ነግጥብኛል ብሎ ወንድሞቹን በገለዓድ አውራጃ ባለው ተራራ ደብቆ ትቶዋቸው ሔደ ፡

፳፮፡ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ምንተ ገበርከ ጽሚተ ዘትትኃጥአኒ ፤

በተገናኙም ጊዜ ላባ ያዕቆብን ኰብልለህ ተሠውረኸኝ የመጣህ ምን አደረግሁህ ?

ወትሰርቀኒ አዋልድየ ከመ ዘበኲናት ፄወወ ፤

በፈረስ አንገት፣ በጦር አንደ በት እንደ ማረከ ሰው ልጆ ቼንስ ለምን ሰርቀኸኝ መጣህ? አለው ፡

፳፯፡ ወሶበ ነገርከኒ እምፈነውኩከ በትፍሥሕት ወበሐሤት፣

ተሰናብተኸኝ ቢሆን በፍጹም ደስታ በሸኘሁህ ነበር ፡

ወበማኅሌት ፤

በዘፈን በጨዋታ ፡

ወበመሰንቆ ወበከበሮ ፤

መሰንቆውን ከበሮውን እያስመ ታሁ በሸኘሁህ ነበር ፡

፳፰፡ ወሚመ ኢይደልወኒኑ ከመ እስዓም ደቂቅየ ወአዋልድየ ፤

ወይስ ሴቶቹን ወንዶቹን ልጆ ቹን ስሜ ሸኝቼ ማሰናበት አይገ ባኝም ነበርን ? ለምን ተሰርቀ ኸኝ ትሔዳለህ አለው ፡

ወይእዜሰ ከመ አብድ ገበርከ ፤

አሁንስ አዋቂው አንተ ያለአ ዋቂ ሥራ ሠራህ ፡

፳፱፡ ወይእዜኒ እምክህልኩ ገቢረ እኩይ ላዕሌከ ፤

አሁንም በአንተ ላይ ክፉ ነገር ላደርግ በተቻለኝ ነበር ፡



ወባሕቱ አምላከ አቡከ ይቤለኒ ትማ ልም ዑቅ ርእሰከ ኢትግበር ኅሡመ ላዕለ ያዕቆብ ፤

ነገር ግን ምን ይሆናላ፣ የአባትህ ፈጣሪ በያዕቆብ ላይ ክፉ ሥራ እንዳትሠራ ለራስህ ዕወቅ ብሎ ትናንትና ቢነግረኝ ነው እንጂ፤

፴፡ ወይእዜኒ ሑር እመ ፈተውከ ከመ ትሑር ቤተ አቡከ ፤

አሁንም እኔ ምን ዕዳዬ ወደ አባትህ አገር መሔዱን ከወደ ድክ ሒድ አለው ፡

ወለምንት ትሰርቀኒ አማልክትየ ፤

በዚያውስ ላይ የማመልካቸው አማልክቶቼን ለምን ይዘህብኝ መጣህ ? አለው ፡

፴፩፡ ወአውሥአ ያዕቆብ ወይቤሎ ለላባ እስመ መሰለኒ ዘተሐይደኒ አዋልዲከ ወኵሎ ንዋይየ ፤

ያዕቆብም ገንዘቤን ሁሉ ፣ ልጆ ችህንም የምትቀማኝ ስለ መሰ ለኝ ነው ፣ ብሎ መለሰለት ፡

ወይእዜኒ ርኢ ለእመቦ ዘሀሎ ንዋይከ ኀቤየ ወንሣእ ፤

አሁንም ገንዘብህ ከእኔ ዘንድ ቢኖር (ካለ) አይተህ ውሰድ አለው ፡

ወበኀበ ዘረከብከ አማልክቲከ ኢይሕ የው ፤

ጣዖቶችህ የተገኙበትም ሰው ይሙት እንጂ አይዳን ፡

፴፪፡ ወናሁ አሰምዕ ለከ በቅድመ እሉ አኃዊነ ፤

እነሆ ለእመቦ ዘሀሎ ንዋይከ ኀቤየ ያልኩትን እሊህን ወንድ ሞቻችንን ምስክር አድርጌ እና ገራለሁ ፡

ወኢያእመረ ያዕቆብ ከመ ሰረቀት ራኄል ፤

ያዕቆብም ራኄል ጣዖቶቹን እንደ ሰረቀች አላወቀም ነበርና፣ በኀበ ረከብከ አማልክቲከ ኢይ ሕየው አለ ፡

፴፫፡ ወቦአ ላባ ቤተ ያዕቆብ ወኢረ ከበ ፤

ላባም ከያዕቆብ ቤት ገብቶ ቢበ ረብር ምንም አላገኘም ፡

ወወፅአ ወቦአ ቤተ ልያ ፤

ከያዕቆብ ባያገኝ ወጥቶ ወደ ልያ ድንኳን ገባ ፡

ወፈተነ ወኢረከበ ፤

ወደ ልያም ድንኳን ገብቶ ፈለገ አላገኘም ፡

ወቦአ ቤተ ክልኤሆን ዕቁባቲሁ ወኢ ረከበ ፤

ከዕቁባቶቹ ከባላና ከዘለፋም ድንኳን ገብቶ በረበረ፣ ምንም አላገኘም ፡

ወቦአ ቤተ ራኄል ፤

ራኄል ካለችበትም ድንኳን ገባ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፬፡ ወራኄልሰ ነሥአቶሙ ለአማልክተ አቡሃ ፤

ራኄል ግን የአባቷን ጣዖቶች ሰርቃ አምጥታ ነበርና ፤

ወወደየቶሙ ውስተ ሕንባለ ገመል ወነበረት ላዕሌሁ ፤

በገመል ኮርቻ ውስጥ፤ አንድም በመደላድል ውስጥ አድርጋ በበላዩ ተቀምጣ ነበር ፤

፴፭፡ ወትቤሎ ለአቡሃ ኢይምሰልከ ዘአስተኃቀርኩከ እግዚእየ እስመ ኢይክል ተንሥአ ቅድሜከ እስመ ትክት አነ ፤

ከግዳጄ ስላልጠራሁ በፊትህ መነሣት አይቻለኝምና ነው እንጂ፤ ጌታዬ ተቀምጬ ማየቴ የናቅሁህ የቃለልኩህ አይምሰልህ አለችው ፤

ወፈተነ ላባ ኵሎ ቤታ ለራኄል ወኢረከበ አማልክቲሁ ፤

ላባም የራኄልን ድንኳን ሁሉ በረበረ ጣዖቶቹንም አላገኘም፤

፴፮፡ ወተምዐ ያዕቆብ ወተላኰየ ለላባ ወይቤሎ ፤

ያዕቆብም ተቆጥቶ ላባን እንዲህ ብሎ ተከራከረው ፤

ምንትኑ አበሳየ፤ ወምንትኑ ጌጋይየ ዘዴገንከኒ ወፈተንከኒ ኵሎ ንዋይየ፤

ተከትለህ ገንዘቤን ሁሉ የበረበርክበት ዕዳዬ በደሌ ምንድን ነው ?

፴፯፡ ወምንተ ረከብከ እምነ ቁሳቁሰ ቤትከ ፤

ጓዜን ሁሉ በረበርከው ትልልቁስ ገንዘብህ ይቅርና ከጥቃቅኑ ገንዘብህ ምን አገኘህ ?

ናስተኣኀዝኑ ቅድመ እሉ አኃዊነ፤

በእሊህ በወንድሞቻችን ፊት እንዋቀስና ፤

ወይገልፉ ማዕከሌነ ፤

በእኔና በአንተ መካከል ይፍረዱ ፤

፴፰፡ ፳ወ፩ዱ ዓመት ሊተ እንዘ አሀቅብ አባግዒከ ወአጣሊከ ፤

ኻያ አንድ ዘመን ሙሉ በጎችህን ፍየሎችህን ስጠብቅ ኖርኩ፤

ወኢመሐስአ በግዕ ኢበላዕኩ እምአባግዒከ ፤

ከበጎችህም አንድ ጠቦት ስንኳን አልበላሁም ፤

፴፱፡ ውብላዓ አርዌኒ ኢያምጻእኩ ለከ ፤

አውሬ የነከሰውንም፤ የአውሬ ትራፊ ብዬ አላመጣሁልህም፤

ወእፈድየከ እምነቤየ እመኒቦ ዘተሰርቀ ፤

የተሰረቀ ገንዘብህ ቢኖርብኝ እከፍል ነበር ፤ አንድም የተሰረቀ እንዳለ አሁንም ልክፈልህ አለው ፤



፵፡ እመኒ መዓልተ ወእመኒ ሌሊተ በጠል እበይት ፤

በመዓልትም በሌሊትም በጤዛ ተነክሬ እኖር ነበር ፤

ወነፍዐ ንዋም እምአዕይንትየ ፤

እንቅልፍ ከዓይኔ ጠፍቶ ይኖር ነበር ፤

፵፩፡ ፳ወ፩ዱ ዓመት ሊተ የም ውስተ ቤትከ ዘተቀነይኩ ለከ ፤

እንዲህም ሆኜ በቤትህ ውስጥ የተገዛሁልህ ሃያ አንድ ዘመን ነው ፤

፲ተወ፬ተ ዓመተ ተቀነይኩ ለከ በእንተ ክልኤሆን አዋልዲከ ፤

ስለ ሁለቱ ሴቶች ልጆችህ ዐሥራ አራት ዓመት ተገዛሁልህ ፤

ወ፯ተ ዓመተ በእንተ አባግዒከ ፤

ስለ በጎችህ ሰባት ዓመት ተገዛሁልህ ፤

ወአኅለፍከ ብየ አስበየ ዐሠርተ ጊዜ፤

ደመወዜንም ብዙ ጊዜ አስቀረህብኝ ፤

፵፪፡ ወሶበ አኮ አምላከ አብርሃም አቡየ ዘሀሎ ምስሌየ ፤

የአባቴ የአብርሃም ፈጣሪ ከእኔ ጋራ በረድኤት ያለ ባይሆን ፤

ወሶበ አኮ በፍርሃተ ይስሐቅ ዕራቅየ እምፈነውከኒ ፤

አባቴ ይስሐቅ የሚያመልከው እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ያለ ባይሆን ፤ አንድም አባቴ ይስሐቅ በሚያመልከው አምልኮት ጸንቼ ብኖር እግዚአብሔር የረዳኝ ባይሆን፤ ከገንዘብ፤ ከሚስት፤ ከልጅ ለይተህ ባዶ እጄን በሰደድከኝ ነበር ፤

ወርእየ እግዚአብሔር ፃማሆን ለእደውየ ወገሠጸከ ትማልም ፤

እግዚአብሔር የእጆቼን ድካም አይቶ በወዳጄ በያዕቆብ ምንም ምን ክፉ ነገር እንዳታደርግ ዕወቅ ብሎ ትናንት በሕልም ገሥጾህ እንጂ አንተስ ስንኳን ከብቴን ሰውነቴን ልታጠፋ መጥተህ ነበር ፤

፵፫፡ ወአውሥአ ላባ ለያዕቆብ ወይቤሎ ፤

ላባም ለያዕቆብ እንዲህ ብሎ መለሰለት ፤

ደቂቅከኒ ደቂቅየ፤ ወአዋልዲከኒ አዋልድየ፤ ወእንስሳከኒ እንስሳየ ፤

ወንዶቹም ሴቶቹም ልጆችህ ልጆቼ ፤ ከብቶችህም ከብቶቼ ናቸው ፤

ወገዙኵሉ ዘትሬኢ ዘዚአየ ውእቱ ፤

ይህ የምታየው ገንዘብ ሁሉ ከእኔ ያገኘኸው ነው ፤

ለእላ አዋልድየ ምንተ እንከ እሬስዮን ሎቶን የም ፤

እሊህ ልጆቼን አሁን ምን አደርጋቸዋለሁ ? እገድላቸዋለሁን ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለውሉዶንሂ ዘወለዳ ፤

የወለዷቸውንስ ልጆቻቸውን ምን አደርጋቸዋለሁ፣ ልጆቼ አይደሉምን ፡

፵፬፡ ወይእዜኒ ነዓ ንትመሐል አነ ወአንተ ወይኩን ስላም ማዕከሌየ ወማዕከሌከ፤

አሁንም እኔ በአንተ ፣ አንተም በእኔ ክፉ ነገር እንዳንደራረግ ና ተማምለን እንታረቅ አለው፡

፵፭፡ ወነሥአ ያዕቆብ ዕብነ ወአቀመ ሐውልተ ፤

ያዕቆብም ደንጊያ አንሥቶ ለምስክር አቆመ ፡

፵፮፡ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለአኃዊሁ አልዱ አዕባነ ፡ ወአለዱ ወገብሩ ወግረ ፤

ያዕቆብም ወንድሞቹን ደንጊያ ሰብስቡ ብሏቸው ሰብስበው ኮረብታ የኽል ደንጊያ ከመሩ ፡

ወበልዑ ዲበ ይእቲ ወግር ፤

ሰብስበው በከመሩት ድንጊያ ላይ ተቀምጠው በሉ ፡

ወይቤሎ ላባ ዛቲ ወግር ስምዕ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ዮም፣ ወሰመያ ላባ ወግረ ስምዕ ፤

ላባም ያዕቆብን ይህች ኮረብታ ዛሬ በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ትሁን ብሎ ኮረብታዪቱን ወግረ ስምዕ ብሎ ጠራት፡ ወግረ ስምዕ ባለው ፍሥሐተ ስምዕ ይላል፣ ወግረ ስምዕ ማለት ነው ፡

፵፯፡ ወያዕቆብኒ ሰመያ ከማሁ፤

ያዕቆብም እንደ ላባ ወግረ ስምዕ አላት ፡

፵፰፡ ወይቤሎ ላባ ለያዕቆብ ነያ ዛቲ ወግር እንተ አቀውም ፤ ስምዕ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ፤

ላባም ያዕቆብን ይህች ያቆምኳት ደንጊያ፣ በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ትሁን አለው፡

ወበእንተ ዝንቱ ተሰምየ ስማ ወግረ ስምዕ ፤

ስለዚህ ነገር ስሟ ወግረ ስምዕ ተባለ ፡

፵፱፡ ወይቤሎ ላባ ራእየ ዘአስተር አየኒ እግዚአብሔር ይርአይ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ዮም ፤

ላባም ያዕቆብን ዛሬ በራእይ የታየኝ የተነጋገረኝ እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው ፡ መሐላውንም ባፈረሰው ሰው ላይ ይፍረድ በት ፡

፶፡ እስመ ንትረኃቅ ዕዱ እምካልኡ ከመ ኢትሳቅዮን ለአዋልድየ፣ ወከመ ኢትንሣእ ብእሲተ ላዕሌሆን ፤

እኔ ከአንተ ፣ አንተ ከእኔ ተለየይተን ተራርቀን እንኖራለንና፣ በላያቸው ሚስት አግብተህ ልጆቼን ብታሳዝናቸው በእኔና



በአንተ መካከል እግዚአብሔር ይፍረድ ፡

፶፩፡ ወርኢ ናሁ አልቦ ዘሀሎ ምስሌነ ፤

ከእኛ ጋራ አሁን ሌላ ሰው እንደ ሌለ ዕወቅ ፡

፶፪፡ እመኒ አዶኩ ኀቤከ ዛቲ ወግር፣ ወዛቲ ሐውልት ትትልወኒ በእኪት፣

እኔ መሐላዬን አፍርሼ በተን ኰል ወደ አንተ ብመጣ፣ ምስክር አድርገን ያቆምናት ይህቺ ደንጊያ በክፋት ትከተለኝ ማለት ታስፈርድብኝ ፡

ወአንተኒ ለእመ አዶከ ኀቤየ ፤

አንተም መሐላህን አፍርሰህ በክፋት ወደ እኔ ብትመጣ ፡

፶፫፡ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ናኮር ይፍታሕ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ፤

የአብርሃምና የናኮር ፈጣሪ በእኔና በአንተ መካከል ይፍረድ አለው ፡

ወመሐለ ሎቱ ያዕቆብ በፍርሃተ ይስሐቅ አቡሁ ፤

ያዕቆብም አባቱ ይስሐቅ የሚያመልከውን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ማለለት ፡

፶፬፡ ወሦዓ ያዕቆብ መሥዋዕተ በውስተ ደብር ፤

በተራራውም ላይ ያዕቆብ ፍሪዳ አረደ ፡

ወጸውዖሙ ለአኃዊሁ ወበልዑ ወሰትዩ በቤቱ ፣ ወቤቱ ውስተ ውእቱ ደብር ፤

ወንድሞቹንም ጠርቶ በልተው ጠጥተው በዚያው ተራራ ሰፍረው አደሩ ፡

፶፭፡ ወተንሥአ ላባ በጽባሕ ወሰዓመ አዋልዲሁ ወደቂቆን ወባረኮሙ፡ ወተመይጠ ላባ ብሔሮ ወሖረ ፤

ላባም ማለዳ ተነሥቶ ልጆቹን፣ የልጅ ልጆቹን ስሞ መርቆ ፣ ተመልሶ ወደ ሀገሩ ሔደ ።

## ምዕራፍ ፴ወ፪

፩፡ ወያዕቆብኒ ገብአ ውስተ ፍኖቱ፣

ያዕቆብም ከላባ ከተለየ በኋላ ወደ መንገዱ ተመለሰ ፡

ወነጸረ በአዕይንቲሁ ያዕቆብ ፤

ወደ ኋላውም አቅንቶ በተመለከተ ጊዜ ፡

ወርእየ ተአይነ እግዚአብሔር ኀዱራን ፤

ከእግዚአብሔር የታዘዙ ሠራዊት ሰልፍ ከትመው አየ ፡

ወተራከብዎ መላእክተ እግዚአብሔር ፤

ተዓይን ያለውን መላእክት ብሎ ገለጠው፡ ከእግዚአብሔር የታዘዙ መላእክትም ተገልጠው ተገናኙት ፡

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ወይቤ ያዕቆብ ሶበ ርእየ ተዓይነ እግዚአብሔር ይእቲ ዛቲ ፤

ያዕቆብ ይህን በአየ ጊዜ፣ ይህቺ የእግዚአብሔር ከተማ ናት አለ፡

ወሰመየ ስሞ ለውእቱ ብሔር ተዓይን ፤

የዚያን አገር ስሙን የእግዚአ ብሔር ከተማ አለው፤ ስለምን ድን ነው ስልፍ ሠርተው የታ ዩት ቢሉ፣ ቀድሞ ከላባ እንደ ጠበቅንህ፣ እንግዲህም ከኤሳው እንጠብቅሃለን ፤ የምንጠብቅህ እኛ ነን ሲሉ ፤

ገባኤ

፫፡ ወፈነወ ያዕቆብ ሐዋርያተ ኀበ ኤሳው እኁሁ ብሔረ ሴይር ውስተ ምድረ ኤዶም ፤

ያዕቆብም፣ በኤዶም ውስጥ ወዳ ለች ወደ ሴይር ከወንድሙ ከኤሳው ዘንድ መልእክተኛ ላከ፤

፬፡ ወአዘዞሙ ወይቤሎሙ ከመዝ በልዎ ለኤሳው እግዚእየ ፤

ጌታዬ ኤሳውን እንደዚህ በሉት ብሎ አዘዛቸው ፤ ይፈራዋልና እግዚእየ አለ፤ አንድም፣ ታላቅ ወንድም ነውና ፤

ከመዝ ይቤ ገብርከ ያዕቆብ ኀበ ላባእ ነበርኩእ ወጐንደይኩ እስከ ዮም ፤

ባሪያህ ያዕቆብ እንዲህ ብሏል፣ እስከ ዛሬ ድረስ ከላባ ዘንድ እኖር ነበር ፤

፭፡ ወአጥረይኩ አግብርተ ወአዕማተ አልሕምተ ወአባግዐ፣ አግማለ ወአዕ ዱገ ፤

ሴቶችም ወንዶችም ባሮች፣ ላሞ ችም በጎችም፣ አህዮችም ግመ ሎችም አብዝቼ ሰብስቤአለሁ፡

ወፈነውኩእ ይዜንውዎእ ለእግዚእየ ኤሳውእ ከመ እርከብእ በቅድሜከ ሞገሰእ አነእ ገብርከእ ፤

እኔ ባሪያህ ያዕቆብ በፊትህ ባለ ሟልነትን አገኝ ዘንድ እለምና ለሁ ብላችሁ ለጌታዬ ለኤሳው ንገሩት ብሎ አስቀድሞ ልኮናል በሉት አላቸው ፤

፮፡ ወገብኡ ኀቤሁ ለያዕቆብ እሙንቱ ሐዋርያት እለ ፈነወ ፤

ያዕቆብ የላካቸው መልእክተ ኞችም፣ መልእክታቸውን አድ ርሰው ወደ ያዕቆብ ተመለሱ፡

ወይቢልዎ ሖርነ ኀበ ኤሳው እኁከ፣

ከወንድምህ ከኤሳው ዘንድ እንደ ላክኸን ሔደን ነገርነው ፤

ወናሁ መጽአ ይትቀበልከ፣ ወ፬፻ት ዕደው ምስሌሁ ፤

አሁንም እሱ አራት መቶ ሰው፣ አስከትሎ ሊቀበልህ መጥቷል አሉት ፤

፯፡ ወፈርሃ ጥቀ ያዕቆብ ወኃጥአ ዘይ ገብር ፤

ያዕቆብም አራት መቶ ሰዎች አስከትሎ መጣ ያሉትን ሰምቶ፣ ይህማ ለጦርነት ነው እንጂ ፤



ለመቀበል መች ነው ብሎ ፈርቶ የሚያደርገውን አጣ ተቸገረ ፤

ወነፈቆሙ ለሕዝብ እለ ምስሌሁ ፤

ከእሱም ጋራ ያሉትን ሰዎች ሁለት ወገን አድርጎ ከፈላቸው፤

ወለአባግዕኒ ወለአልሕምትኒ፣ ወለአ ግማልኒ ገብሮሙ ፪ተ ተዓይነ ፤

ላሞቹንም፣ በጎቹንም፣ ገመሎቹ ንም ሁለት ሁለት ወገን አድርጎ ከፈላቸው ፤

፰፡ ወይቤ ያዕቆብ ለእመ መጽአ ኤሳው ውስተ አሐቲ ትዕይንት ፤ ወቀተላ ትድኅን ካልዕት ትዕይንት፣

አንዲቱን ሰፈር ቢያጠፋ፣ አን ዲቱ ሰፈር ትድናለች ብሎ ከሁ ለት ወገን አድርጎ ከፈላቸው ፤

፱፡ ወይቤ ያዕቆብ ውእቱ አምላከ አበውየ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ፣ ዘይቤለኒ ሑር ውስተ ብሔር ኀበ ተወለድከ ወአነ አሤኒ ላዕሌከ ያሤኒ እንከሰ ላዕሌየ ፤

ወደ ተወለድኸበት አገር ተመል ሰህ ሒድ ፤ እኔም ክፉ ነገር አላደርግብህም ያለኝ የአባቶቼ የአብርሃም፤ የይስሐቅ ፈጣሪ፣ እሱ፣ እንግዲህስ በጎ ነገርን ያደርግልኛል (ያድርግልኝ) አለ፤

፲፡ ወበኵሉ ጽድቅ ወርትዕ ዘገበርከ ለገብርከ ረከብኩ ፤

ከዚህ አስቀድሞ ለእኔ ለባሪያህ በአደረግኸው ቸርነት ቅንነት ሁሉ፣ ባለሙዋልነትን አግኝቻ ለሁ ፤

እስመ በበትርየ አደውክዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ፤

ይህን ዮርዳኖስን በበትሬ ማለት በትሬን ይዤ ብቻዬን ተሻግሬ ነበርና ፤

ወይእዜሰ ኮንኩ ፪ኤተ ተዓይነ ፤

ዛሬ ግን፣ ከገንዘቤ ብዛት የተ ነሣ ሁለት ሰፈር ለመሆን በቅ ቻለሁ ፤

፲፩፡ ወአድኅነኒ እግዚኦ እምእዴሁ ለኤሳው እኁየ ፤

አቤቱ አሁንም ከወንድሜ ከኤ ሳው እጅ አድነኝ ፤

እስመ እፈርህ አነ እምኔሁ ላዕለ ርእስየ ከመ ኢይምጻእ ወኢይቅት ለኒ ፤

መጥቶ እንዳያጠፋኝ ከእሱ የተ ነሣ እኔ ለራሴ እፈራለሁና ፤

ወኢይቅትል እመ፡ ምስለ ውሉዳ፣

እናትን ከልጆቿ ጋራ እንዳያ ጠፋ አለ ፤ ልያን ከነልጆቿ ፤ ራኄልን ከነልጆቿ፣ ባላን ከነ ልጆቿ፣ ዘለፋን ከነልጆቿ እንዳ ያጠፋ ማለቱ ነው ፤

፲፪፡ እስመ ትቤለኒ አሤኒ ላዕሌከ፣

በጐ ነገር አደርግልሃለሁ ብለኸ ኛልና ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእሬሲ ዘርአከ ከመ ኆፃ ባሕር ዘኢይትኌለቍ እምብዝኁ ፤

ልጅህን፣ የልጅ ልጅህንም ከብዛቱ የተነሣ እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ አደርገዋለሁ ብለኸኝ ነበርና ከወንድሜ ከኤሳው እጅ አድነኝ ፡

፲፫፡ ወቤተ ህየ በይእቲ ሌሊት ፤

ይህንም ተናግሮ በዚያች ሌሊት ከዚያ አደረ ፡

ወአውዕአ አምኃ ዘይወስድ ለኤሳው እኁሁ ፤

ለወንድሙ ለኤሳው የሚወስደ ውንም እጅ መንሻ አወጣጣ፤

፲፬፡ ፪፻ተ አጣሌ ፤ ወ፳ አባሕኩ አጣሊ ፤

ሁለት መቶ እናት ፍየል፤ ሃያ የፍየል አውራ ፡

ወ፪፻ተ አባግዓ ወ፳ አባሕኩ አባግዕ ፤

ሁለት መቶ እናት በጐች ስሳ የበጎች አውራዎች እየቈጠረ አወጣጣ (ሐተታ) ስለምን የበጉን አብዝቶ የፍየሉን አውራ አሳነሰ ቢሉ፣ የበጉ፣ በፊቲው አይናደድም ኀዳዕ ነውና፣ በጎቹ እንዳያንሱ ብሎ፣ የፍየሉ አውራ በፊቲው ይናደዳል ፤ ጥቂቱ ለብዙ ይበቃል ብሎ ፡

፲፭፡ ፴ ናቃተ ምስለ ዕጐሊሆን ፤

የሚያጠቡ አምሳ ግመሎች ከነ ልጆቻቸው ፡

ወ፵ዓ ዕጐላተ ፤

አርባ ሜል (ሽህር) (መሲና) ፡

ወ፲ተ አስዋረ፤

ዐሥር ገች (በሬ) ፡

ወ፳ አዕዱገ ፤

ሃያ እንስት አህያ ፡

ወ፲ተ ዕዋለ ፤

ዐሥር ወደልጋዝ (ውርንጭላ)፤

፲፮፡ ወወሀበሙ ለደቂቁ መራዕየ እንተ ባሕቲቶሙ ፤

ይህን ሁሉ አውጥቶ፣ ወንድምህ ያዕቆብ እጅ መንሻ ልከልሃል ብላችሁ፣ ለወንድሜ ለኤሳው ስጡት ብሎ ለብላቴኖቹ ለብቻቸው አስረከባቸው ፡

ወይቤሎሙ ሑሩ ቅድመ ወአስተራኀቁ መራዕየ እመራዕይ ፤

መንጋውን ከመንጋ ለይታችሁ እያራራቃችሁ በፊት በፊት ንዱ አላቸው ፡

፲፯፡ ወአዘዞ ለቀዳማዊ ወይቤሎ ፤

በፊት የሚነዳውንም እንዲህ ብሎ አዘዘው ፡



እመ ረከበከ ለኤሳው እኁየ ወተስእለከ ወይቤለከ ዘመኑ ዝንቱ ወአይቴ ተሐውር ፤

ወንድሜ ኤሳውን አግኝተኸው ይህ መንጋ የማነው ? አንተስ ይህን ይዘህ ወዴት ትሔዳለህ?

ወዘመኑ ዝ ዘየሐውር ቅድሜከ ፤

በፊትህስ የሚሔደው ይህ መንጋ የማን ነው ? ብሎ ቢጠይቅህ ፡

፲፰፡ በሎ ዘገብርከ ያዕቆብ አምኃ ዘፈነዎ ለእግዚኡ ኤሳው ፤

ባሪያህ ያዕቆብ ለጌታው ለኤሳው የላከው እጅ መንሻ ነው ፡

ወናሁ ውእቱኒ ይተልወነ ድኅሬነ፤

እሱም አሁን በኋላችን ተከትሎ ናል በለው አለው ፡ (ሐተታ) እጅ መንሻ ሰዶ ፤ መቅረት አለና ይተልወነ አለ ፡

፲፱፡ ወአዘዞ ካዕበ ለካልኡኒ ወለሣልሱኒ፣ ወለኵሎሙ እለ የሐውሩ ቅድሜሁ ወይነድዑ መራዕየ ፤

ዳግመኛ ፡ ሁለተኛ ፤ ሦስተኛ አካች ከእሱ በፊት በፊት መንጋ እየነዱ የሚሄዱትንም ሁሉ እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ፡

ወይቤሎሙ ለእመ ረከብክምዎ ለእኁየ ኤሳው ከመዝ በልዎ ፤

ወንድሜ ኤሳውን ያገኛችሁት እንደሆነ፣ እንዲህ በሉት ፡

ናሁ ገብርከ ያዕቆብ ይበጽሕ ድኅሬነ ፤

ባሪያህ ያዕቆብ በኋላችን ነው አሁን ይመጣል ፡

፳፡ እስመ ይቤ እድኅን እምገጹ በዝንቱ አምኃ ዘይወስዱ ደቅ ቅድሜሁ፤

ይህን እጅ መንሻ አስቀድሞ መላኩ፣ ብላቴኖች ይዘውለት በሔዱት እጅ መንሻ፣ ከወንድሜ ከኤሳው ከፊቱ ቍጣ እድናለሁ ፡

ወእምዝ እሬኢ ገጾ ቅድወ ፤ ወከመ ይትቀበሎ ለገጽየ በጾኅን ፤

ከዚህም በኋላ፣ ፊቱን ደስ ብሎት አየዋለሁ፤ እኔንም በተድላ በደስታ ይቀበለኛል ብሎ፤ በፊት በፊት ሰድዶናል፤ እሱም በኋላ በኋላችን መጥቷል ብላችሁ ንገሩት ብሎ ሰደዳቸው ፡

፳፩፡ ወእምዝ ፈነወ አምኃ ፤

ይህን ሁሉ እጅ መንሻውን ከላከ በኋላ ፡

ወውእቱሰ ቤተ ውስተ ትዕይንት በይእቲ ሌሊት ፤

እሱ ግን በዚያች ሌሊት ከጓዙ ጋራ በሰፈሩ አድሮ ፡

፳፪፡ ወተንሥአ ያዕቆብ፣ ወነሥአን ለክልኤሆን አንስትያሁ ወለክልኤሆን ዕቁባቲሁ ወዐሠርተ ወአሐደ ደቂቆ፤

በነጋው ሁለቱን ሚስቶቹን ፤ ልያንና ራኄልን፣ ሁለቱ ዕቁባ

www.ethiopianorthodox.org

ቶቹን ባላንና ዘለፋን፣ ዐሥራ አንዱን ልጆቹን ይዞ ተነሣ ፤

ወዐደወ ማዕዶተ ያቦቅ ፣

የያቦቅን ወንዝ ተሻገረ ፤

፳፫፣ ወነሥአሙ ወአደወ ውኂዘ ፣

ይዟቸውም ወንዙን ተሻገረ ፤

ወአዕደወ ኵሎ ንዋያቲሁ ፣

ገንዘቡን (ዕቃውን) ሁሉ ይዞ አሻገረ ፤

፳፬፣ ወተርፈ ያዕቆብ ባሕቲቶ ፣

ያዕቆብ ብቻውን ቀረ ፤ ባሕቲቱ ቢል፣ ያዕቆብ ብቻ ቀረ፤

ወተጋደሎ ብእሲ እስከ ጽባሕ ፣

እስኪነጋም ድረስ አንድ ሰው ያዕቆብን ሲታገለው አደረ ፤ (ሐተታ) ብእሲ ያለው ፣ ጌታን ነው ፤ በአምሳለ ብእሲ ታይቶ ታልና ፤

፳፭፣ ወሶበ ርእየ ከመ ኢክህሎ አኀዞ ሥርዎ ኀሩመ እንዘ ይትጋደል ምስሌሁ ፣

ጌታ ያዕቆብን እንዳልቻለውም በአየ ጊዜ፣ ከእሱ ጋራ ሲታገል፣ ዕርዎ የሚሆን ሹልዳውን ያዘው፤

፳፮፣ ወይቤሎ ፈንወኒ እስመ ኀሐ፣ ጽባሕ ፣

ሊነጋ ፣ ኀሕ ቀዷልና ልቀቀኝ አለው ያዕቆብን ፤

ወይቤሎ ኢይፌንወከ ለእመ ኢባረ ከኒ ፣

ያዕቆብም ጌታን ፣ ካልመረቅ ኸኝ፤ አንድም፤ ስም ካላወጣኸ ልኝ አልለቅህም አለው ፤

፳፯፣ ወይቤሎ መኑ ስምከ ፣

ስምህ ማን ይባላል ? አለው ፤

ወይቤሎ ያዕቆብ ስምየ ፣

ስሜስ ያዕቆብ ይባላል አለው ፤

፳፰፣ ወይቤሎ ኢይኩን እንከ ስምከ ያዕቆብ ዳዕሙ ፣ ይኩን ስምከ እስ ራኤል ፣

እንግዲህ ወዲህ፣ ስምህ እስራ ኤል ይባል እንጂ፣ ያዕቆብ አይ ባል አለው ፤

እስመ ክህልከ ምስለ እግዚአብሔር ወምስለ ዕጓለ እመሕያው ፣

ከእግዚአብሔር ጋራ መታገልን፣ ከላባም ጋራ መከራከርን ችለሃ ልና፣ እስራኤል ተባል እንጂ፣ ያዕቆብ አትባል ፤ እስራኤል ማለት ሕዝበ እግዚአብሔር፣ ሕሊና ዘይሬእዮ ለእግዚአብ ሔር ፣ ነጻሬ እግዚአብሔር ፣ ከሃሊ ምስለ እግዚአብሔር ማለት ነው ፤

፳፱፣ ወይቤሎ ያዕቆብ አይድአኒ ስመከ ፣

ያዕቆብ ፤ ጌታን ፣ ስምህን ንገ ረኝ አለው ፤



ወይቤሎ ለምንት ለከ ትሴአል ስምየ፣

ስሜን ለምን ትጠይቀኛለህ ? አለው ፤

እስመ መድምም ውእቱ ፣

ስሜ መድምም (ድንቅ) ነውና፤ ሳታውቀው ለምን ትጠይቃለህ? አንድም ለምን ትጠይቀኛለህ ? ስሜ መድምም ነው ብሎ ስሙን ነገረው ፤

ወባረኮ በህየ ፣

በዚያም ቦታ ጌታ ያዕቆብን መረቀው ባረከው ፤

፴፣ ወሰመዮ ስሞ ያዕቆብ ለውእቱ ብሔር ራእየ እግዚአብሔር ፣

ያዕቆብ፣ የዚያን ቦታ፣ ስሙን፤ የእግዚአብሔር መገለጫ ብሎ ጠራው ፤

እስመ ይቤ ርኢክዎ ለእግዚአብሔር ገጸ በገጽ ፣

እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየ ሁት ሲል ራእየ እግዚአብሔር አለው ፤

ወድኅነት ነፍስየ ወገጽየ ፣

ከዚህም የተነሣ፣ ሰውነቴ ከጥ ፋት፣ ልቡናዬ ከኃዘን ዳነች አለ፤

፴፩፣ ወሠረቀ ዐሐይ ሶበ ኃደጎ ራእየ እግዚአብሔር ፣

ወሶበ ሠረቀ ዐሐይ ኃደጎ ራእየ እግዚአብሔር ሲል ነው፤ ዐሐይ በወጣ ጊዜ ራእየ እግዚአብሔር ተወው ማለት ጌታ ተሠወረው፤

ወሎቱስ ያስየገዞ ሥርወ እግሩ ፣

ሹልዳውን ደንዝዞት ነበር፤ አዎ እግሩም ይላል ሥርወ እግሩ ማለት ነው ፤

፴፪፣ ወበእንተዝ ኢይበልዑ ደቂቀ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት ውእተ ሥርወ ዘአስየዘ ዘሀሎ ውስተ አወ እግሩ ፣

ስለዚህም የእስራኤል ልጆች ፤ በእግሩ ዛላ መካከል ያለ የደነ ዘዘውን ሹልዳውን እስከ ዛሬ ድረስ አይበሉም፣ የደነዘዘ ነው ብለው፤ ሐተታ፣ መታገሉ ስለ ምን ነው ? ቢሉ ፣ በረድኤት እቀርብሃለሁ አልለይህም ሲል ነው፤ ያዕቆብ ጌታን ይዞ መጣሉ እኔን ከያዝክ ጠላትህን ትጥላ ለህ ሲል፤ በውስጥ ሁኖ ጌታ ያዕ ቆብን ማስጨነቁ፣ እኔን ብት ጥል እኔም አንተን አስጨንቅሃ ለሁ ሲል፣ አንድም መታገል እንጂ፣ ደረት ለደረት ገጥሞ ነው ፤ ከሥጋህ ሥጋ ፣ ከነፍስህ ነፍስ ነሥቼ ባሕርይህን ባሕርይ፣ አካልህን አካል አደርጋለሁ ሲል፤

እስመ አኃዞ ሥርዎ ኀሩመ ለያዕቆብ፣

የያዕቆብን ሹልዳውን ጌታ ይዞት ነበርና፤ አንድም አስየዘዘ ይላል፣ ሹልዳውን ደንዝዞት ነበርና ፤

ወውእቱ ሥርው ኀሩም ፣

ይህም ሹልዳ ሊበሉት አይገ ባም ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፴፫

፩፡ ወአንሥአ አዕይንቲሁ ያዕቆብ ወርእየ ፤

ያዕቆብም ዓይኑን ቀና አድርጎ ባየ ጊዜ ፤

ወናሁ ኤሳው እኁሁ መጽአ ወ፬፻ት ዕደው ምስሌሁ ፤

እነሆ ወንድሙ ኤሳው አራት መቶ ሰዎች ይዞ ሲመጣ አየ፤

ወነፈቆሙ ያዕቆብ ለደቂቁ ኀበ ልያ ውኀበ ራኄል፤ ውኀበ ፪ኤሆን ዕቁባቲሁ፤

ልጆቹንም ፤ የልያን ልጆች ከልያ፤ የራኄልን ልጆች ከራኄል፤ የባላን ልጆች ከባላ፤ የዘለፋን ልጆች ከዘለፋ አድርጎ ለይቶ አቆማቸው ፤

፪፡ ወረሰዮን ለዕቁባቲሁ ምስለ ደቂቆን ቅድመ ፤

ዕቁባቶቹን ባላንና ዘለፋን፤ ከልጆቻቸው ጋራ በፊት አደረጋቸው ፤

ወለልያ ወለደቂቃ ድኅሬሆን ፤

ልያን ከነልጆቿ ፤ ከዕቁባቶቹ ቀጥሎ አደረጋቸው ፤

ወለራኄልሰ ወለዮሴፍ ድኅሬሃ ፤

ራሄልንና ዮሴፍን ግን ከሁሉም በኋላ አደረጋቸው ይወዳቸው ነበርና ፤

፫፡ ወውእቱሰ ሖረ ቅድሜሆሙ ፤

እሱ ግን የሁሉንም ሞት አሳ ይም ብሎ በፊት በፊት እየሄደ፤

ወሰገደ ውስተ ምድር ስብዓ እስከ ይበጽሕ ኀበ እኁሁ ኤሳው ፤

ከወንድሙ ከኤሳው እስኪደርስ ድረስ ግንባሩን ምድር እያስነካ፤ አሁንም አሁንም ሰባት ጊዜ ሰገደ፤ እንደ በለው ስግደት ፤

፬፡ ወአቅድመ ረዊጸ ኤሳው፤ ወተቀበሎ ወሐቀፎ ክሣዶ ወሰዓሞ ፤

ኤሳውም ባየው ጊዜ አስቀድሞ ፈጥኖ ሄዶ አንገቱን አቅፎ ሳመው ፤

ወበከዩ ክልኤሆሙ ኅቡረ ፤

ሁለቱም አንገት ላንገት ተያይ ዘው ባንድነት ተላቀሱ ፤

፭፡ ወሶበ ነጸረ ኤሳው ወርእዮን ለአንስት፤ ወለደቂቆን፤ ይቤሎ ምንትከ እሉ ፤

ኤሳው፤ የያዕቆብ ሁለቱ ሚስ ቶቹን ከነልጆቻቸው ቁመው ባያቸው ጊዜ፤ እሊህ ምኖችህ ናቸው አለው ፤

ወይቤሎ ያዕቆብ ደቂቅየ እሙንቱ ዘመሐሮ እግዚአብሔር ለገብርከ ፤

ለኔ ላገልጋይህ እግዚአብሔር የመጸወተኝ ሚስቶቼና ልጆቼ ናቸው አለው ፤



፮፡ ወመጽአ ዕቁባቲሁ ወደቂቆን ምስሌሆን ወሰገዳ ፤

ዕቁባቶቹ ከልጆቻቸው ጋራ መጥተው እጅ ነሡት ፤

፯፡ ወመጽአት ልያ ወደቂቃ ወሰገደት ሎቱ ፤

ልያም ከነልጆችዋ መጥታ እጅ ነሣችው ፤

ወእምዝ መጽአት ራሄል ወሰገደት፤

ከሁሉም በኋላ ራሄል መጥታ እጅ ነሣች ፤

፰፡ ወይቤሎ ኤሳው ለያዕቆብ፤ ምንትከ ውእቱ ዝንቱ ኵሉ ተአይን ዘረከብኩ ፤

ኤሳውም፤ ያዕቆብን ይህ ሁሉ ያገኘሁት ሠራዊት ምንህ ነው? አለው ፤

ወይቤሎ ያዕቆብ ለኤሳው፤ ዘገበርኩ ለከ እግዚኦ ከመ እርከብ ሞገሰ በቅድሜከ ፤

ያዕቆብም ፤ ኤሳውን አቤቱ በፊትህ ባለሟልነትን አገኝ ዘንድ ማለት፤ ደስ ብሎህ ትቀበለኝ ዘንድ ለአንተ ለጌታዬ የላክሁት እጅ መንሻ ነው አለው ፤

፱፡ ወይቤሎ ኤሳው ብየ እንስሳ ብዙኀ እኁየ ወይኩንከ ለከ ዘዚአከ፤

ኤሳውም፤ ወንድሜ ለኔ ብዙ ከብት አለኝ፤ ያንተስ ገንዘብ ላንተ ይሁንህ አለው ፤

፲፡ ወይቤሎ ያዕቆብ አኮ ከመዝ ለእመ ረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ ተመጠው አምኃየ እምእዴየ ፤

ያዕቆብም፤ እንዲህ አይደለም፤ በፊትህስ ባለሟልነትን ካገኘሁ፤ የመጣሁትን እጅ መንሻዬን ደስ እንዲለኝ ተቀበለኝ አለው፤

እስመ በእንተ ዝንቱ እሬኢ ገጸከ ከመ ዘይሬኢ ገጸ እግዚአብሔር ፤

ይህን እጅ መንሻ የተቀበልከኝ እንደሆነ፤ መልአክ ተልእኮውን ቅዳሴውን ፤ ባሕታዊ ትሩፋቱን ጸሎቱን፤ እጅ መንሻ አድርጎ የእግዚአብሔርን ፊት በባለሟ ልነት እንዲያይ ፤ በዚህ ደስ ብሎኝ ፊትህን አያለሁ ፤

፲፩፡ ወእመሰ ታፈቅረኒ ንሣእ አምኃየ ዘአምጻእኩ ለከ ፤

የምትወደኝስ ከሆነ፤ ላንተ ይሁ ንህ ማለትህ ቀርቶ ያመጣሁል ህን እጅ መንሻ ተቀበለኝ አለው፤

እስመ መሐረኒ እግዚአብሔር ወብየ ኵሉ ፤

እግዚአብሔር ሰጥቶኝ ሁሉም መልቶልኛልና ፤

ወአገበሮ ወነሥአ ፤

እንዲህ አድርጎ ግድ ተቀበለኝ ቢለው ተቀበለ ፤

፲፪፡ ወይቤሎ ኤሳው ተንሥእ ንሑር እንተ መንጸር ፤

ኤሳውም ተነሥ በፊታችን ወደ አለች አገር እንሒድ አለው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፡ ወይቤሎ ያዕቆብ ለሊከ ተአምር እግዚእየ ከመ ድኩማን ደቂቅ ወአልሕምት ወአባግዕ ፤

ያዕቆብ፣ ኤሳውን ጌታዬ ልጆቹም፣ ከብቶቹም፣ በጎቹም በመንገድ ደክመው እንዳሉ አንተ ታውቃለህ ፡

ወእጉላትኒ የሐርሳ ላዕሌየ ፤

ላሞቹም በጎቹም እየወለዱ ያጠባሉ ፡ አንድም እርጉዞች ይጨነግፉብኛል ፡

ወለእመሰ መረድኑ ላዕሌሆሙ አሐተ ዕለተ፡ ወእመ አኮ ሰኑየ ይመውቱ ኵሉ እንስሳነ ፤

አንድ ቀን ሁለት ቀን በግሥገሣ አስቸኩለን የነዳናቸው እንደ ሆነ ፣ ከብቶቻችን ሁሉ ያልቃሉ ፡

፲፬፡ ሑር አንተ እግዚእየ ቅድመ ገብርከ ወንሕነሰ በከመ ንክል ነሐውር ፤

ጌታዬ አንተ ቀድመህ ሒድ እኛ ግን እንደ ተቻለን ቀስ ቀስ እያልን እንጓዛለን ፡

ወንውእልሂ ውስተ ፍኖት እንዘ ነሐውር ፤

ስንሔድም ልጆች ከብቶች እየ ደከሙ ስናዘግም በመንገድ እን ውላለን ፡

ወሶበሂ ነሐውር በእግረ ደቂቅ ነሐውር እስከ ንበጽሕ ኀበ እግዚእነ ውስተ ሴይር ፤

በምንሔድበትም ጊዜ ጌታችን አንተ ካለህበት ሴይር እስክን ደርስ ድረስ በሕፃናቱ እርምጃ መጠን ነው የምንሔደው አለው፤ አንድም ፣ በመጠነ ደቂቅ ሲል ነው ፡ በሕፃናቱ መጠን ጥቂት ጥቂት ነው የምንሔደው አለው ፡

፲፭፡ ወይቤሎ ኤሳው እኅድግኑ ለከ እምዝንቱ ሕዝብ ዘምስሌየ ፤

ኤሳውም ፣ ከኔ ጋራ ካሉት ሰዎች ልተውልህን ? አለው ፡

ወይቤሎ ያዕቆብ ለምንትኑ ዝንቱ የአክለኒ ዘምስሌየ ፡

ያዕቆብም ፣ ይህ የምትሰጠኝ ለምንድን ነው? ከኔ ጋር ያለው ሰው፤ አንድም፤ እግዚአብሔር ይበቃኛል ፡

ወዘረከብኩ ሞገሰ በቅድሜከ እግዚእ፣

በፊትህ ያገኘሁት ባለሟልነት ይበቃኛል፣ ማለት፤ ካንተ፤ ሰው አልፈልግም ፍቅርህ ይበቃኛል አለው ፡

፲፮፡ ወገብአ ኤሳው ፍኖቶ በይእቲ ዕለት ውስተ ሴይር ፤

ኤሳውም በዚያች ቀን ፣ ወደ ሴይር መንገድ ተመለሰ ፡



፲፯፡ ወያዕቆብሰ ኃደረ ውስተ ተአይን ፤

ያዕቆብ ግን፣ ከዚያው ከሰፈረ በት ቦታ አደረ ፡

ወገብረ ሎቱ ሐፁረ በህየ ሎቱሂ ወለ እንስሳሁኒ ፤

በዚያም ቦታ፣ ለእርሱም ለከብ ቶቹም ዘለሳ ጣለ ፡

ወበእንተዝ ሰመዮ ለውእቱ ብሔር ማኅደር ፤

ስለዚህ ነገር፣ የሰፈረበትን ቦታ፣ ደስ ብሎኝ አርፌ ያደርኩበት ቦታ ሲል ፡ ስሙን ማኅደር አለው ፡

፲፰፡ ወበጽሐ ያዕቆብ ውስተ ሴሎም ውስተ ሀገረ ሰቂሞን እንተ ሀለወት ውስተ ምድረ ከነዓን እምድኅረ መጽአ እምአፍላግ ዘሶርያ ወበጽሐ አንጻረ ሀገር ፤

የሶርያንም ወንዞች ተሻግሮ ከመጣ በኋላ፣ ያዕቆብ በከነዓን ውስጥ ያለች የሰቂሞን አውራጃ ወደምትሆን ሴሎም ወደምት ባል አገር ደረሰ ፡

፲፱፡ ወተሣየጠ ደወለ ገራህት ወተ ከለ ህየ ማኅደረ ፤

ከከተማውም አጠገብ በደረሰ ጊዜ፣ በገዛው እርሻ ዳር ድን ኳን ተክሎ አደረ ፡

ወገራኅትሰ እንተ ተሣየጠ እምኤሞር፡ አቡሁ ለሲኬም በ፻ት አባግዕ፣

ይኸውም እርሻ፣ ከሲኬም አባት ከኤሞር ፡ በመቶ በግ የገዛው ነው ፡

፳፡ ወአቀመ በህየ ምሥዋዐ ወጸውዖ ለአምላከ እስራኤል ፣

በዚያም ምሥዋዕ ሠርቶ፣ የእ ስራኤልን አምላክ ጠራው ፣ ማለት ፡ እግዚአብሔርን አመ ሰገነው ።

## ምዕራፍ ፴፬

### ጉባኤ

፩፡ ወወፅአት ዲና ወለተ ልያ እንተ ተወልደት ለያዕቆብ ከመ ትርአይ አዋልደ ውእቱ ብሔር ፤

ልያ ከያዕቆብ የወለደቻት ዲናም ፡ የዚያ አገር ሴቶች ልጆች ሲዘፍኑ፣ ሲያጨበጭቡ ለማየት ፡ አንድም ፡ ከመ ትርአይ ግዕዘ ብሔር ይላል ፡ የሀገሩን ልማድ፣ አንድም ሥነ በዓል ለማየት ወጣች፤ (ሐተታ) አሕዛብ በዓል አድርገው አግኝተ ዋቸዋል፤ ዘፈን ዓዋቆች ናቸው ይባላልና እነሱን አያለሁ ብላ ወጥታለች ፡

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ወርእያ ሴኬም ወልደ ኤሞር ኤውያዊ መልአከ ብሔር ፤

የአገር አለቃ የሚሆን የኤውያው ሰው፤ የኤሞር ልጅ ሴኬም ፡ ዲናን ፤ ባየች ጊዜ ፡

ወነሥአ ወሰከበ ምስሌሃ፤ ወአኅሠራ፤

ነጥቆ ወስዶ ደረሰባት አዋረዳት አለ ፡ ከክብር አሳነሳት ፡

፫፤ ወርእየ ነፍስታ ለዲና ወለተ ያዕቆብ፤ ወአፍቀራ ለይእቲ ወለት፤

የያዕቆብን ልጅ ዲናን ፤ የመልኳን ማማር ፤ ባየ ጊዜ ወደዳት ፡

ወተናገረ በእንተ ግዕዛ ፤

የጠባይዋንም ነገር ተናገረ ፡ ማለት ልቧን ደስ በሚያሰኛት ነገር ተናገራት ፡

፬፤ ወይቤሎ ሴኬም ለኤሞር አቡሁ፤ ንሥአ ሊተ ለዛቲ ወለት ትኩነኒ ብእሲተ ፤

ሴኬም፤ አባቱ ኤሞርን፤ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ከዘመዶቿ ተነጋግረህ ይህችን ብላቴና አጋባኝ አለው ፡

፭፤ ወሰምዐ ያዕቆብ ከመ አርኰሳ ለዲና ወለቱ ወልደ ኤሞር፤ ወደቂቁሰ ሐቅለ ሀለዉ ምስለ እንስሳሁ፤ ወአርመመ ያዕቆብ እስከ ይመጽኡ ደቂቁ ፤

ያዕቆብም ፤ የኤሞር ልጅ ሴኬም ነጥቆ ወስዶ ልጁ ዲናን (እንዳዋረዳት) ከክብር እንዳሳነሳት በሰማ ጊዜ፤ ልጆቹ ከብት እየጠበቁ በበረሃ ነበሩና ልጆቹ እስኪመጡ ድረስ ዝም ብሎ ቆየ ፡

፮፤ ወመጽአ ኤሞር አቡሁ ለሴኬም ከመ ይትናገር ፤

የሴኬም አባት ኤሞርም፤ ልጅህን ለልጄ ስጥልኝ ብሎ ሊነጋገረው ወደ ያዕቆብ መጣ ፡

፯፤ ወመጽኡ ደቂቁ እምሐቅል ፤

ልጆቹም ከብት ከሚጠብቁበት ከበረሐ መጡ ፡

ወሶበ ሰምዑ ዘከመ ሰከበ ሴኬም ምስለ ወለተ ያዕቆብ ደንገጹ ጥቀ ወተከዙ ፤

እኅታቸው ዲናንም የኤሞር ልጅ ሴኬም እንደ ደረሰባት፤ ከክብርም እንዳሳነሳት በሰሙ ጊዜ፤ እጅግ ደንግጠው አዘኑ፤

እስመ ኃፍረተ ገብረ ላዕለ እስራኤል፤

በእስራኤል ላይ የሚያሳፍር ሥራ ሠርቷልና ፡

ወኢኮነ ከማሁ ሕጉ ፤

ሥርዓቱም እንዲህ አይደለምና ማለት፤ ግዙራን እስራኤል ከቈላፋን አሕዛብ፤ መምለክያነ እግዚአብሔር እስራኤል፤ ከመምለክያነ ጣዖት አሕዛብ ጋራ አይጋቡም ነበርና፤ ልጆቹ እጅግ ደንግጠው አዘኑ ፡



፰፤ ወተናገሮሙ ወይቤሎሙ ኤሞር፤ ሴኬም ወልድየ አፍቀራ ለወለትክሙ ሁቡዎ ትኩኖ ብእሲተ ፤

ኤሞርም ልጄ ሴኬም፤ ልጃችሁን ወዷታልና ሚስት ትሆነው ዘንድ ስጡት ብሎ ለመናቸው ፡

፱፤ ወትትሐመዉነ ሀቡነ አዋልዲክሙ ፤ ወአዋልዲነኒ ንሥኡ ለደቂቅክሙ ወንበሩ ምስሌነ ፤

በጋቢም ከእኛ ጋራ ትዛመዱ ዘንድ ፤ ሴቶች ልጆቻችሁን ለእኛ ስጡን፤ የእኛንም ሴቶቻችንን ለወንዶች ልጆቻችሁ አጋቡ፤ እንዲህ ሁናችሁ ከእኛ ጋራ በአንድነት ኑሩ ፤

፲፤ ወምድርነሂ ናሁ ረኃብ በቅድሜክሙ ኅድሩ ውስቴታ ወተገበሩ፤

ይህችም የምታይዋት ሀገራችን እነሆ ሰፊ ናት ፤ እሷን እያረሳችሁ እየቆፈራችሁ ፤ እናንተ ግምጃ፤ እኛ አውራጃ ሁነን እንኑር አላቸው ፡

፲፩፤ ወይቤሎሙ ሴኬም ለአቡሃ ወለአኃዊሃ ረስዩ ሊተ ዛተ ፍትሐ በቅድሜክሙ ፤ ወኵሎ ዘትብሉኒ እሁብ ፤

ሴኬምም ለአባቷና ለወንድሞቿ ፤ ይህን የላክሁባችሁን ነገር ወድዳችሁ ፈርዳችሁ አድርጉልኝ ፤ በጅ በሉኝ ፡

፲፪፤ ወመጠነ አብዛኅክሙ ጥቀ ሕዜሃ እሁበክሙ ሀቡኒያ ለዛቲ ወለት ትኩነኒ ብእሲተ ፤

ሚስት ልትሆነኝ ይህችን ብላቴና ስጡኝ፤ ማጫዋን ያላችሁኝን ያህል እጅግ አብዝቼ እሰጣችኋለሁ አላቸው ፡

፲፫፤ ወአውሥእዎሙ ደቂቀ ያዕቆብ ስምዖን ወሌዊ ፡ ለሴኬም ወለኤሞር አቡሁ ፤ በጕህሉት ፤

የያዕቆብ ልጆች ስምዖንና ሌዊም ፤ ለሴኬምና ለአባቱ ለኤሞር ፤ የተንኰል ምላሽ መለሱላቸው ፡

እስመ አርኰስዋ ለዲና እኅቶሙ ፤

እኅታቸው ዲናን ስላዋረዱዋት፤ ከክብር ስለ አሳነሱዋት፤ ተናድደው ነበርና ፡

፲፬፤ ወይቤልዎሙ ፤

እንዲህ አሏቸው ፡

ኢንክል ገቢሮቶ ለዝንቱ ነገር ከመ ነሀብ እኅተነ ለብእሲ ዘኢኮነ ግዙረ፤

ሳልተገረዘ ቈላፍ ለሆነ ሰው እኅታችንን እንሰጥ ዘንድ፤ ይኸን ነገር ልናደርገው አንችልም፤ ማለት፤ እኅታችንን ልንሰጥ አይገባንም አሉት ፤

እስመ ጽእለት ውእቱ ለነ፤

ለኛ፤ ይኸ ነቀፋችን ስድባችን ነውና ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ወባሕቱ፣ በዝንቱ ትከውኑ ከማነ ወንነብር ምስሌክሙ፤ ለእመ ገዘርክሙ ኵሎ ተባዕተክሙ ፣

ነገር ግን፣ ወንድ ወንዱን ሁሉ ብትገዝሩ፣ በዚህ እኛን ትመስላላችሁ፤ እኛም እናንተን መስለን እንኖራለን ፤

፲፮፤ ወንሁበክሙ አዋልዲነ ወንነሥእ አዋልዲክሙ ለነ አንስትየ ፣

ለወንዶች ልጆቻችሁ፣ ሴቶች ልጆቻችንን ለእናንተ እንሰጣችኋለን፣ እኛም የእናንተን ሴቶች ልጆች እናገባለን ፤

ወንነብር ምስሌክሙ ፣ ወንከውን አሐደ ዘመደ ፣

በግቢ አንድ ወገን ሆነን ተዛምደን፣ ተዋልደን እንኖራለን፤ አንድ ዘመድ፣ አንድ ወገን እን ሆናለን ፤

፲፯፤ ወለእመሰ ኢሰማዕክሙነ ንነሥእ ወለተነ ወነሐውር ፣

የነገርናችሁን ይኸን ካልሰማችሁን ግን፣ ልጃችንን ይዘን ወደ ሌላ አገር እንሔዳለን ፤

፲፰፤ ወአደሞሙ ለኤሞር ወለሴኬም ዝንቱ ነገር ፣

ለኤሞርና ለሴኬም ይህ ነገር፣ ደስ አሰኛቸው ፤

፲፱፤ ወኢያጐንደየ ገቢሮቶ ውእቱ ወልድ ለዝንቱ ነገር፣ እስመ ያፈቅራ ለወለተ ያዕቆብ ፣

ያም ልጅ ፣ የያዕቆብን ልጅ ዲናን ስለ ወደዳት፣ ይህን ነገር ከመሥራት ወደ ኋላ አላለም፣ አለ ፤ ፈጥኖ አደረገው እሺ በጄ አለ ፤

ወውእቱ ይከብር እምኵሉ ቤተ አቡሁ ፣

ካባቱ ወገኖች ሁሉ ይልቅ እሱ ይከብር ነበርና፤ (ሐተታ) አሁን ያገሩን ሰው ይዞ ተገዘረ የሚል ነውና ይከብር እምኵሉ አለ፤

፳፤ ወሖሩ ኤሞር ወሴኬም ወበጽሑ ውስተ አንቀጸ ሀገሮሙ ወነገሩ ለኵሉ ዕደወ ሀገሮሙ ፣

ኤሞርና ሴኬምም ሒደው ከሀገራቸው አደባባይ በደረሱ ጊዜ፣ በሀገራቸው ላሉ ሰዎች ሁሉ ይህን ነገር ነገሯቸው ፤

፳፩፤ ወይቤልዎሙ እሉ ዕደው ስንዕ እሙንቱ ምስሌነ ወይንበሩ ውስተ ምድርነ ወይትገበርዋ ፣

እሊህ ሰዎች ከኛ ጋራ ስምምናቸው፣ ምድራችንን እያረሱ እየቈፈሩ በሀገራችን ይኑሩ ፤

እስመ ረሐብ ይእቲ ምድር ቅድሜሆሙ ፣

ይጠበናልም እንዳይሉ፣ ሰፍረውባት ያለች አገር ሰፊ ናትና እሷ ትበቃቸዋለች ፤

ወአዋልዲሆሙ ንነሥእ ለነ አንስትየ፤ ወአዋልዲነኒ ንሁቦሙ ፣

እንዲህ የሆነ እንደሆነ ፣ እኛ የነሱን ሴቶች ልጆች አግብተን፤ እነሱም የኛን ሴቶች ልጆች አግብተው፣ እነሱ ግምጃ፤ እኛ አውራጃ ሁነን እንኖራለን ፤



፳፪፤ ወበዝ ባሕቲቱ ንትመሰሎሙ ከመ እሙንቱኒ ይኩኑ ከማነ፣ ወንኩን አሐደ ዘመደ ፣

እነሱም እኛን መስለው አንድ ወገን ሁነን እንኖር ዘንድ በዚህ ብቻ እንምሰላቸው ፤

ወንግዝር ኵሎ ተባዕተነ በከመ እሙንቱ ይገዝሩ ፣

እነሱ ወንድ ወንዱን ሁሉ እን ዲገዝሩ፣ እኛም ወንድ ወንዱን ሁሉ እንግዘር ፤

፳፫፤ ወመራዕይሆሙኒ ወእንስሳሆሙኒ ወንዋዮሙኒ አኮኑ ለነ ውእቱ፣

እንዲህ የሆነ እንደሆነ፣ መንጋ ቸውም፣ ገንዘባቸውም ከብታ ቸውም የኛ አይደለምን ፤

ወባሕቱ በዝንቱ ከመ ንኩን ከማሆሙ ወይንበሩ ምስሌነ ፣

ነገር ግን፣ እነሱ ከኛ ጋራ ይኖሩ ዘንድ በዚህ ብቻ እንምሰላቸው፤

፳፬፤ ወይቤልዎሙ ለኤሞር ወለሴ ኬም ወልዱ ኵሎሙ እለ ይበውኡ ውስተ አንቀጸ ሀገር አሆ ፣

ባደባባይ የሚወጡ የሚገቡ ሰዎች ሁሉ ለኤሞርና ለልጁ ለሴኬም እሺ እንገዘራለን ብለው መለሱላቸው ፤

ወተገዝሩ ከተማ ሥጋ ነፍስቶሙ ኵሉ ተባዕቶሙ ፣

ወንድ ወንዶቹ ሁሉ ፣ የብልት የብልታቸውን ስንኩፍ ተገዘሩ፤ (ሐተታ) መጀመሪያ ኤሞርና ሴኬም ተገዝረዋል፤ ያገር ቀንድ ናቸውና፣ ሁሉም እነሱን አይቶ አንድ ቀን ተገዝሮ ውሏል ፤

፳፭፤ ወእምዝ አመ ሣልስት ዕለት እንዘ ሀለዉ ውስተ ሕማም ወዕለ ዋን እሙንቱ ፣

ከዚህ በኋላ፣ በሦስተኛው ቀን በቍስል ታመው ደክመው ሳለ፤ (ሐተታ) የግዝረት ቍስል ፣ ከዕለቱ በማግስቱ፣ ከማግስቱ በሣልስቱ ይጸናልና ፤

ነሥኡ ፪ኤሆሙ ደቂቀ ያዕቆብ ስም ዖን ወሌዊ አኀዊሃ ለዲና፤ መጣብሒ ሆሙ ዘዘዚአሆሙ ፣

የዲና ወንድሞች ፣ የያዕቆብ ልጆች፣ ስምዖንና ሌዊ ሁለቱ፣ እየራስ እየራሳቸው አፋ፣ አፋ ቸውን ታጥቀው ተንሥተው ሔዱ ፤

ወቦኡ ውስተ ሀገር ተታቢያሙ ወቀ ተሉ ኵሎ ተባዕቶሙ ፣

አይዞህ አይዞህ ተባብለው እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ መንደር ገብተው ወንድ ወንዱን ሁሉ ፈጁት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፡ ለኤሞርሂ ወለሴኬም ቀተል ዎሙ ፣

ኤሞርንና ሴኬምንም ገድለው፡

ወነሥእዋ ለዲና እኅቶሙ፣ ወአውፅ እዋ እምቤተ ሴኬም ፣

እንዲህ አድርገው እኅታቸው ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥተው ወሰዱዋት ፡

፳፯፡ ወቦኡ ደቂቀ ያዕቆብ ኀበ ቅቱ ላን፣ ወበርበርዋ ለይእቲ ሀገር እንተ ውስቴታ አርኰስዋ ለዲና እኅቶሙ፣

የያዕቆብ ልጆች ስምዖንና ሌዊም ፣ ወደ ሞቱት ሰዎች መንደር ገብተው፣ እኅታቸው ዲናን ከክብር ያሳነሱዋትን ሰዎች ያሉባትን አገር ፣ በረበሩዋት ዘረፉዋት ፡

፳፰፡ ወነሥእዎሙ አባግዒሆሙ ፣ ወአልሕምቲሆሙኒ፣ ወአዕዱጊሆሙኒ ወኵሎ ዘሀሎ ውስተ ሐቅል ወው ስተ ሀገር ፣

በጎቻቸውንም ላሞቻቸውንም፣ አህዮቻቸውንም በዱር በመን ደር ያለውን ሁሉ ፡

፳፱፡ ወነባሪሆሙኒ ወአንስቲያሆሙኒ ወኵሎ ቄሳቍሰሙ ጼወዉ ፣

ቤተሰቦቻቸውን ፣ ሚስቶቻቸ ውን፣ ጥቃቅኑን የቤት እቃ ሁሉ ፡

ወበርበሩ ኵሎ ዘውስተ ሀገር ወዘ ውስተ አብያት ፣

በቤትም በሀገርም ያገኙትን ሁሉ ዘረፉአቸው ፡

፴፡ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለስምዖን ወለሌዊ እኩየ ረሰይክሙኒ ወአጽላእ ክሙኒ በኀበ ኵሉ ምድር፣ በኀበ ከናኔዎን ወፌርዜዎን ፣

ያዕቆብም ስምዖንና ሌዊን ፣ ክፉ አደረጋችሁብኝ፣ በከናኔ ዎን፣ በፌርዜዎንም ሁሉ አው ራጃ በሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ዘንድ አስጠላችሁኝ ፡

ወአንሰ ውሁድ አነ በኍልቍየ ፣

እኔ በቍጥር ከአሕዛብ ሁሉ የማንስ እጅግ ጥቂት ነኝ ፡

ወይትጋብኡ ላዕሌየ ወይቀትሉኒ ፣

አንድ ሁነው በጠላትነት ይነ ሡብኛል ፡

ወእትቀጠቀጥ አነ ወቤትየ ፣

እኔም ወገኖቼም አንድ ሁነን እንጠፋለን አላቸው ፡

፴፩፡ ወይቤልዎ ለምንትኑ ከመ ዘማ ረሰይዋ ለእኅትነ ወአኅሥርዋ፣

ስምዖንና ሌዊም፣ እኅታችንን እንደ ዘማ አድርገው ለምን አዋ ረዷት? ከክብር ለምን አሳነሷት? አሉት ፡፡



## ምዕራፍ ፴ወ፭

፩፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለያዕቆብ፣

እግዚአብሔር ፣ ያዕቆብን እን ዲህ አለው ፡

ተንሥእ ወሑር ውስተ ቤቴል ወን በር ህየ ፣

ተነሥተህ ወደ ቤቴል ሒደህ በዚያ ኑር ፡

ወግበር መሥዋዕተ ሊተ ዘአስተርአ ይኩከ አመ ጉየይከ እምገጸ ኤሳው እኁከ ፣

ከወንድምህ ከኤሳው ፊት ሸሽ ተህ በሔድክ ጊዜ፣ ለታየሁህ፣ ለተነጋገርኩህ ለኔ መሥዋዕት ሠዋልኝ አለው ፡

፪፡ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ለሰብአ ቤቱ ወለኵሎሙ እለ ምስሌሁ ፣

ያዕቆብም ቤተሰቦቹን ከሱ ጋራ ያሉትንም ሰዎች ሁሉ እንዲህ አላቸው ፡

አሰስሉ እምኔክሙ አማልክተ ነኪር ወአውፅኡ እማዕከሌክሙ ፣

ከናንተ ዘንድ ያሉ (የሆኑ) ጣዖታ ትን ከመካከላችሁ አውጥታችሁ አርቁ ፡

ወንጽሑ ወሕጽቡ አልባሲክሙ ወተ ንሥኡ ንዕርግ ውስተ ቤቴል ፣

ልብሳችሁን አጥባችሁ ንጹሐን ሁናችሁ ተነሡ ወደ ቤቴል እንውጣ ፡

፫፡ ወንግበር በህየ ምሥዋዓ ለእግዚ አብሔር ዘሰምዐኒ በዕለተ ምንዳቤየ፣ ወዘሀሎ ምስሌየ፣ ወአድኃነኒ በፍኖ ትየ ወአዕደወኒ ፣

በመከራዬ ጊዜ የለመንኩትን ለሰማኝ፣ ዛሬም በረድኤት ከኔ ጋራ ላለ ፣ በሔድኩበትም ሁሉ ከመከራ አድኖ ወደዚህ ላሻገ ረኝ ለእግዚአብሔር በዚያ መሥ ዋዕት እንሠዋ አላቸው ፡

፬፡ ወወሀብዎ ለያዕቆብ ኵሎ አማል ክተ ነኪር ወኵሎ ዘሀሎ ኀቤሆሙ፣

ቤተሰቦቹም ለያዕቆብ ልዩ የሆኑ ጣዖታትን ከነሱ ዘንድ ያለው ንም ሁሉ ፡

ወአዕኑገኒ ዘውስተ ዕዘኒሆሙ ፣

በጆሮአቸው ያለ ጉትቻ፣ መንደ ልቶ ሁሉ አውጥተው ሰጡት፡

ወኃብኦ ያዕቆብ ውስተ ዕፅ ዘስቂሞን፣

ያዕቆብም፣ በሰቂሞን ባለችው ዕንጨት ሥር ቀበረው ፡

ወአሕጐሎሙ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ፣

ሲጽፍ እስከ ዮም አለ ፣ እስከ ዛሬ ድረስ ቀብሮአቸው ጠፍ ተው ይኖራሉ ፡

፭፡ ወግዕዘ እስራኤል እምሴቂም፣ ወኮነ ፍርሃተ እግዚአብሔር ላዕለ እማ ንቱ አህጉር እለ ዓውዶሙ ወኢተለ

www.ethiopianorthodox.org

ውዎሙ ድኅሬሆሙ ለደቂቀ እስራ ኤል ።

ያዕቆብም ከሴቄም ተነሥቶ በተ ጓዘ ጊዜ ፣ በዙሪያቸው ባሉ በአ ኒያ አገሮች ላይ ፣ ከእግዚአ ብሔር ታላቅ ፍርሃት አድሮባ ቸው የእስራኤልን ልጆች ከወደ ኋላቸው አልተከተሉአቸውም፤

፮፤ ወበጽሐ ያዕቆብ ኀበ ሎዛ እንተ ውስተ ምድረ ከነዓን፣ እንተ ይእቲ ቤቴል ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስ ሌሁ ።

ያዕቆብም፣ አብረዉት ከአሉት ጋር በከነዓን አውራጃ ወዳለች ወደሎዛ፣ እርሷም ቤቴል ናት፣ በደረሰ ጊዜ ፤

፯፤ ወነደቀ በህየ ምሥዋዓ ለእግዚአ ብሔር ።

በዚያ ቦታ ለእግዚአብሔር ምሥ ዋዕ ሠራ ፤

ወሰመዮ ስሞ ለውእቱ መካን ቤቴል፣

የዚያንም ቦታ ስሙን ቤቴል አለው ፤

እስመ በህየ አስተርአዮ እግዚአብ ሔር አመ-ተነጥአ እምገጸ ኤሳው እኁሁ ።

ከወንድሙ ከኤሳው ሸሽቶ በሔደ ጊዜ ከዚያ ቦታ ጌታ ታይቶት ተነጋግሮት ነበርና ቤቴል አለው ቤተ እግዚአብ ሔር ሲል ፤

፰፤ ወሞተት ዲቦራ ኃፂኒታ ለርብቃ፣

የርብቃ ሞግዚት የነበረች ዲቦ ራም ያንጊዜ ሞተች ፤

ወተቀብረት እምታሕተ ለቤቴል ኀበ ዕፀ ባላን ።

በቤቴል በታች ባለ በወይራ በግራር ሥር ተቀበረች ፤

ወሰመይዎ ያመ ላህ ።

ዛፉንም፣ የዲቦራ ልቅሶ የተለ ቀሰበት ዛፍ አሉት ፤

፱፤ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለያ ዕቆብ፣ አመ ወፅአ እማዕከለ አፍላግ ዘሶርያ ።

ከሶርያ ወንዝ መካከል በወጣ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ያዕቆብን ታየው ተነጋገረው ፤

፲፤ ወባረኮ እግዚአብሔር ወይቤሎ ኢይሰመይ ስምከ ያዕቆብ ዳዕሙ እስራኤል ።

ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ብሎ፤ እግዚአ ብሔር ያዕቆብን መረቀው ፤

፲፩፤ ወይቤሎ አነ ውእቱ አምላክከ ብዛኅ ወተባዛኅ ።

የማከብርህ ፈጣሪህ እኔ ነኝ ፣ ብዙ ፣ የብዙ ብዙ ሁን ፤

ወይኩን እምኔከ ሕዝብ ወማኅበረ አሕዛብ ወነገሥት ይፃኡ እምኔከ ።

ሕዝብም አሕዛብም ነገሥታ ትም ካንተ ይወለዱ ፤ ይኸንማ



ቀድሞ ነግሮት አልነበረምን ? ስለምን ደገመው ቢሉ ፤ ለማጽ ናት ሁለተኛ ነግሮታል ፤ አን ድም ከኤሳው ሲሸሽ ሰዋሰወ ወርቅን ባየ ጊዜ ኢይሰመይ ብሎ በራዕይ ነግሮት ነበርና፣ ከላባ ዘንድ ሲመለስ በራዕይ ከታየበት ቦታ ሎዛ ደረሰ ፤

፲፪፤ ወለዛቲ ምድር እንተ ወሀብኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ለከ እሁባ ወለዘርእከ እምድኅሬከ ።

ለአብርሃም ለይስሐቅ የሰጠኋ ትን ይህችን ምድር ላንተም ካንተም በኋላ ለሚነሡ ለልጆ ችህ አወርሳችኋለሁ አለው ፤

፲፫፤ ወዓርገ እግዚአብሔር እምኔቤሁ እምውእቱ ብሔር ኀበ ተናገሮ ።

እግዚአብሔርም በዚያ አገር ያዕቆብን ከተነጋገረው በኋላ ተሠወረው ፤

፲፬፤ ወአቀመ ያዕቆብ ሐውልተ ውስተ ውእቱ ብሔር ኀበ ተናገሮ ።

ያዕቆብም፣ እግዚአብሔር ከሱ ጋራ በተነጋገረበት በሎዛ ምል ክት ደንጊያ አቆመ ፤

ወአውጽሐ ሞጻሕተ ላዕሌሃ ወከዓወ ላዕሌሃ ቅብዓ ።

በደንጊያውም ላይ ወይንና ዘይት አፈሰሰበት ፤ (ሐተታ) ቀድሞ ዘይት አፍስሶበት ነበረ ሲመለስ ወይን አፈሰሰበት ፤

፲፭፤ ወሰመዮ ስሞ ያዕቆብ ለውእቱ መካን ቤቴል ።

ያዕቆብ ፣ ያንን ቦታ ስሙን ቤቴል አለው ፤ ቤተ እግዚአብ ሔር ማለት ነው ፤

፲፮፤ ወግዕዘ እምነ ቤቴል፣ ወተከለ ማኅደረ ኀበ ማኅፈድ ዘጋዴር፣

ያዕቆብም ከቤቴል ተጓዞ ሔዶ በጋዴር ባለ ግምብ አጠገብ ድን ኳን ተክሎ ሰፈረ ፤

ወእምዝ ሶበ በጽሐ ውስተ ምድረ ኤፍራታ ወለደት ራሔል ወአጸበት በወሊድ ።

ከዚህ በኋላ፣ ኤፍራታ ከምት ባል ቦታ በደረሰ ጊዜ፣ ራሔል፣ በምጥ ተጨንቃ ወለደች ፤

፲፯፤ ወእምዝ እንዘ ሀለወት ውስተ ሕማመ ወሊድ ትቤላ መወልዲት ኢትፍርሂ እስመ ዝኒ ይከውነኪ ወልደ ።

ዝኒ ፤ ዋዌው ለዮሴፍ ነው ፤ በምጥ ተይዛ ሳለች ሞግዚቲቱ ራሔልን ይህም እንደ ዮሴፍ የሚጠቅም ልጅ ይሆንልሻልና አይዞሽ አትዘኝ አለቻት ፤

፲፰፤ ወእምዝ አልጸቀት ከመ ትፃእ ነፍሳ እስመ ቦቱ ከነ መዊታ ።

ሞቷ በሱ ምክንያት ነውና ያን ጊዜም ነፍሷ ከሥጋዋ ልትለይ ደረሰች ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሰመየቶ ስሞ ወልደ ፃዕርየ ፣

ስሙንም በጭንቅ የወለድኩት ልጄ አለችው ።

ወአቡሁሰ ሰመዮ ብንያም ፣

አባቱ ግን ብንያም አለው ። ወልደ ኃይል ወልደ የማን ማለት ነው ። አንድም አንበሳ ማለት ነው ። አንድም ናዚ ማለት ነው ።

፲፱፡ ወሞተት ራሔል ወተቀብረት ውስተ ፍኖት ዘኤፍራታ እንተ ይእቲ ቤተልሔም ፣

ራሔልም በሞተች ጊዜ፣ በኤፍራታ መንገድ ዳር ተቀበረች፤ ይህችውም ቤተልሔም ናት ።

፳፡ ወዓቀመ ያዕቆብ ሐውልተ ላዕለ መቃብራ ፣

ያዕቆብም በራሔል መቃብር ላይ ለምልክት ሐውልት አቆመ፤

ወይእቲ ተሰምየት ሐውልተ መቃብረ ራሔል እስከ ዮም ፣

ሲጽፍ እስከ ዮም አለ ። ያቺም ደንጊያ እስከ ዛሬ በራሔል መቃብር ላይ ለምልክት የተተከለች ሐውልት ትባላለች ።

፳፩፡ ወእምዝ እንዘ ሀሎ እስራኤል፤ ውስተ ይእቲ ምድር፤ ሖረ ሮቤል፣ ወሰከበ ምስለ ዕቅብተ ያዕቆብ አቡሁ፣ ምስለ ባላ ፣

ምስለና ምስለ አንድ ወገን ፣ ከዚህ በኋላ፣ እስራኤል የተባለ ያዕቆብ፣ በቤተልሔም አውራጃ ሰፍሮ ሳለ ፣ ሮቤል ሂዶ ካባቱ ከያዕቆብ ዕቅብት ከባላ ደረሰ፤

ወሰምዓ እስራኤል ወኮነ እኩየ በቅድሜሁ ፣

ያዕቆብም ይህን በሰማ ጊዜ በፊቱ ክፉ ነገር ሆነ፣ ማለት፤ ከፋው አዘነ ። (ሐተታ) ማን ነግሮታል ቢሉ ። ባላ ከተክል ቦታ ገብታ እርቃኗን ጥላ ስትታጠብ ሮቤል አይቶ በሐዐ ዝሙት ተነደፈ፤ ሌሊት ከተኛችበት ሔዶ ሳታውቀው ደረሰባት ፣ ከዚያ በኋላ ልሒድ አላት ያዕቆብ መስሏት፣ ከመጣህማ ወዲያ አታድርምን ? አለችው፤ አላወቅሽኝምን? እኔ እንጂ ሮቤል ነኝ አላት ፣ ደንግጣ ስታለቅስ አድራለች፣ በሌላ ቀን ያዕቆብ ሂዶ ልድረስብሽ አላት ፣ ሮቤል ልጅህ አርክሶኛል አለችው ትቷት ሔዷል ።

፳፪፡ ወዐሠርቱ ወክልኤቱ እሙንቱ ደቂቀ ያዕቆብ ፣

የያዕቆብም ልጆች ዐሥራ ሁለት ናቸው ።

፳፫፡ ደቂቀ ልያ ሮቤል በኲሩ ፣

እነዚሁም፣ የልያ ልጆች በኵሩ ሮቤል ።

ወስምዖን ፣

ሁለተኛው ስምዖን ።



ወሌዊ ፣

ሦስተኛው ሌዊ ።

ወይሁዳ ፣

አራተኛው ይሁዳ ።

ወይሳኮር፣

አምስተኛው ይሳኮር ።

ወዛብሎን ፣

ስድስተኛ ዛብሎን ናቸው ።

፳፬፡ ወደቂቀ ራሔል ዮሴፍ ወብንያም ፣

የራሔል ልጆችም፣ መጀመሪያው ዮሴፍ፣ ሁለተኛው ብንያም ናቸው ።

፳፭፡ ወደቂቀ ባላ አመተ ራሔል፣ ዳን፣ ወንፍታሌም ፣

የራሔል ገረድ፣ የባላ ልጆችም፤ መጀመሪያው፣ ዳን፣ ሁለተኛው ንፍታሌም ናቸው ።

፳፮፡ ወደቂቀ ዘለፋ፣ አመተ ልያ፣ ጋድ፣ ወአሴር ፣

የልያ ገረድ፣ የዘለፋ ልጆችም፤ መጀመሪያው፣ ጋድ፤ ሁለተኛው አሴር ናቸው ።

፳፯፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ያዕቆብ እለ ተወልዱ ሎቱ ማዕከለ አፍላግ ዘሶርያ ፣

በሶርያ ወንዞች መካከል ባለች በካራን ሳለ፣ የወለዳቸው ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች እሊህ ናቸው ። ሐተታ ምነው ፲ቱ ወ፪ቱ እለ ተወልዱ ማዕከለ አፍላግ ዘሶርያ አለ፣ ብንያም የተወለደ በቤተልሔም አይደለምን ? ቢሉ፣ ለመጽሐፍ የፊቱን ወደ ኋላ፤ የኋላውን ወደ ፊት፤ አድርጎ መናገር ልማዱ ነውና ከጀመረ አንድ አድርጎ ተናገረው ።

ወበጽሐ ያዕቆብ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ ውስተ ሀገረ ምንባሬ እንተ ውስተ ሐቅል ፣

ያዕቆብም፣ በምድረ በዳ አቅራቢያ ባለች ፣ አብርሃም ይቀመጥባት በነበረ አገር ከአባቱ ከይስሐቅ ዘንድ ደረሰ ።

እንተ ይእቲ ኬብሮን በምድረ ከናዓን ኀበ ነበሩ አብርሃም ወይስሐቅ ፣

ይህችውም፣ አብርሃምና ይስሐቅ በኖሩባት በከነዓን ያለች ኬብሮን ናት፤ አንድም ምንባሬ ባለው፣ መምሬ ይላል፤ አባቱ ይስሐቅ፣ አብርሃም ይቀመጥባት በነበረ በወይራ በግራር ሥር ተቀምጦ ሳለ ፣ ያዕቆብ ከአባቱ ከይስሐቅ ዘንድ ደረሰ ።

፳፰፡ ወኮነ መዋዕሊሁ ለይስሐቅ ፻ት ወ፹ ዓመት ፣

ያንጊዜም ፣ የይስሐቅ ዘመኑ መቶ ሰማንያ ነበር ። ሐተታ የአብርሃም ዘመን መቶ ሰባዓ አምስት ነው ። ለይስሐቅ ስለ

www.ethiopianorthodox.org

ንጽሕናው አምስት ዘመን ተጨ ምሮለታል ፡

ወልሕቀ ይስሐቅ ፣

ይስሐቅም አረጀ ፡

፳፱፡ ወረሚአ፣ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ ሞተ ፣

የተሰጠውን ዘመን ጨርሶ ፣ አርጅቶ ሞተ ፡

ወተወሰከ ኀበ ሕዝቡ ፣

በሞት፣ ከአባቶቹ ተደረበ ፡

ወቀበርዎ ኤሳው ወያዕቆብ ደቂቁ፣

ልጆቹ ኤሳውና ያዕቆብ እያለ ቀሱ ቀበሩት ።

## ምዕራፍ ፴ወ፮

### ግባኤ

፩፡ ወከመዝ ይእቲ ልደቱ ለኤሳው፣ ወውእቱ ለሊሁ ኤዶም ውእቱ ፣

የኤሳውም የልደቱ ቍጥር እን ዲህ ናት፡ (ነች) ከመዝ ያለውን ያምጣው ፣ ውእቱና ለሊሁ አንድ ወገን ነው፡ ይኸውም፣ ኤሳው ፈታዊ ነው አለ፣ ያልተ ሰጠውን የሚሻ ነው፡ አንድም፣ ወውእቱ ኤዶም ይላል አብነት፡ እንደዚሁ ያስተረጕማል ፡

፪፡ ወነሥአ ሎቱ አንስትየ እምአዋ ልደ ከነዓን ሐዳሰ ወለተ ኤሎን ኬጥ ያዊ ፡ ወኤሌማ ወለተ ሐና ወልደ ሴቤሶ ኤውያዊ፡ ወቤሴሞት ወለተ ይስማኤል እኅቱ ለናቡዓት ፣

ኤሳውም ከከነዓን ልጆች መራ ርጦ ለራሱ አገባ ፣ እለዚህም (አገባቸው ያልሁት ሴቶች) ያገ ባቸው ሴቶች፣ አንዲቱ የኬጥ ያው ሰው የኤሎን ልጅ ሐዳሶ ናት ፡ ሁለተኛዪቱም ፣ የኤው ያው ሰው ሴቤሶ፣ የሴቤሶ ልጅ ሐና፣ የሐና ልጅ ኤሌማ ናት (ሦስተኛዪቱም) ወለት እኅት ብሎ ለአንዲቱ ቀጽሎላታል ፡ ሦስተኛዪቱንም ፣ የናቡዓት እኅት፣ የይስማኤል ልጅ ቤሴ ሞት ናት ፡ አንድም ወልደ ናቡዓት ይላል፣ አብነት ሦስተ ኛዪቱም የበኵር ልጁ ናቡዓት የሚሆን የይስማኤል ልጅ ቤሴ ሞት ናት ፡

፫፡ ወወለደቶ ሐዳሰ ለኤልፋዝ፡ ወቤ ሴሞት ወለደቶ ለራጉኤል ፣

ሐዳሶም ኤልፋዝን ወለደችው፡ ቤሴሞትም ራጉኤልን ወለደ ችው ፡

፬፡ ወኤሌማ ወለደቶሙ ለዮሔል ወለይጉሚል ወለቆሬ ፣

ኤሌማም ዮሔልን ይጉሚልን፡ ቆሬን፣ እለዚህን ሦስቱን ወለ ደቻቸው ፡



፭፡ እሉ እሙንቱ ደቂቁ ለኤሳው እለ ተወልዱ ሎቱ በምድረ ከነዓን፣

በከነዓን አገር የተወለዱለት የኤ ሳው ልጆች እኒህ ፭ቱ ናቸው፡ ምነዋ ከላይ ሲቈጥር ኤሌማን አስቀድሞ ቤሴሞትን ወደኋላ አድርጓት ነበር፣ አሁን ከዚህ ቤሴሞትን አስቀድሞ ኤሌማን ስለምን ወደ ኋላ አደረጋት ? ቢሉ ፣ እንዳገኘ ቈጥሮ ነው ፡ አንድም በማግባት ጊዜ ኤሌማ ቀድማታለች፣ በመውለድ ጊዜ ግን፣ ቤሴሞት ቀድማታለችና ስለዚህ ቤሴሞትን አስቀደመ ኤሌማን ወደ ኋላ አደረገ ፡

፮፡ ወነሥአ ኤሳው አንስትያሁ ወደ ቂቆ ወአዋልዲሁ ወኵሎ ነባሬ ቤቱ ወኵሎ እንስሳሁ ወኵሎ ንዋየ ዘአጥ ረየ በምድረ ከነዓን ወሖረ እምድረ ከነዓን እምገጸ ያዕቆብ እኁሁ ፣

ኤሳውም ሚስቶቹን፣ ወንዶቹ ንም ሴቶቹንም ልጆቹን ቤተሰ ቦቹንም ከብቶቹን ሁሉ በከነ ዓን አገር ያጠራቀመውን ገንዘ ቡንም ሁሉ ይዞ ምንስ ቢሆን ብኵርናውን ለቅቄለት የለምን? ብሎ ከወንድሙ ከያዕቆብ ተለ ይቶ ከከነዓን አገር ተነሥቶ ሔደ፡

፯፡ እስመ ብዙኀ ንዋዮሙ ወኢክህሉ ነቢረ ኅቡረ በእንተ ብዝኃ ንዋዮሙ፣

ገንዘባቸው ብዙ ነውና ብዙ ስለ ሆነ፣ ወንድማማቾች ያዕቆብና ኤሳው በአንድነት መኖር አል ተቻላቸውምና፣ ስለ አልተቻላ ቸው፡ ነሥአ ወሖረ ብለህ እሥር፣ ኢክህሉ ነቢረ ማንሻ ፡ አንድም ብዙኀ ንዋዮሙና ብዝኃ ንዋዮሙ አንድ ወገን ፣ ገንዘባቸው ብዙ ነውና ፣ ብዙ ስለሆነ ወንድማ ማቾቹ ያዕቆብና ኤሳው በአን ድነት መኖር አለተቻላቸውም ፡

፰፡ ወኃደረ ኤሳው ውስተ ደብረ ሴይር ወለሊሁ ኤሳው ኤዶም ውእቱ፣

ኤሳውም ከከነዓን ሒዶ ሴይር በሚባል ተራራ አደረ (ኖረ) ፣ ይኸውም ኤሳው ፈታዊ ነው አለ፣ ያልተሰጠውን የሚሻ ነው፡

፱፡ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለኤሳው አቡሆሙ ለኤዶም በደብረ ሴይር፣

በሴይር ተራራ ያሉ የኤዶም ያስ ሰዎች አባታቸው ኤሳውም፣ ግብሩ እንዲህ ነው አለ፣ ያልተ ሰጠውን መሻት ነው ፡

፲፡ ወዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ ኤሳው፣ ኤልፋዝ ወልደ ሐዳሶ፣ ብእ ሲተ ኤሳው፣ ወራጉኤል ወልደ ቤሴ ሞት ብእሲተ ኤሳው ፣

የኤሳው ወንዶች ልጆች ስማ ቸው ይህ ነው ፡ አስማቲሆሙ ያለውን ወደ ፊት ያመጣል ፣ አንዱ የኤሳው ሚስት የምት ሆን የሐዳሶ ልጅ ኤልፋዝ ነው፡ ሁለተኛውም፣ የኤሳው ሚስት የምትሆን የቤሴሞት ልጅ ራጉ ኤል ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወኮኑ ደቂቀ ኤልፋዝ ወልደ ኤሳው ቴማን፣ ወኤሞር፣ ወሳፍር፣ ወጎቶን፣ ወቄኔዝ ፣

ኮነ ያለውን ወደፊት ያመጣዋል ፤ የኤሳው ልጅ ኤልፋዝ የወለዳቸው ልጆቹ ፣ ቴማን ፣ ኤሞር፣ ሳፍር፣ ጎቶን፣ ቄኔዝ፣ ናቸው ፤ ኮነ ያለውን አመጣ ፤ አንድም ኮነ ያለውን ወደፊት ያመጣል ፤

፲፪፡ ወተምናኅ ዕቅብቱ ለኤልፋዝ ወልደ ኤሳው፣ ወለደት ሎቱ አማሌቅሃ ፣

የኤሳው ልጅ የኤልፋዝ ዕቅብቱ የምትሆን ተምናኅም አማሌቅ የሚባል ልጅ ወለደችለት፤ እለ ኮነ ያለውን አመጣ ፤ ኮነ ያለውን ወደፊት ያመጣል ያለው ይህ ነው ፤

እሉ እሙንቱ ደቂቀ ሐዳሰ ብእሲተ ኤሳው ፣

የኤሳው ሚስት፣ የሐዳሰ ልጆች እሊህ ናቸው አለ ፣ ልጇንም የልጅ ልጆቿንም ቈጥሮ እሉ እሙንቱ አላቸው ፤

፲፫፡ ወደቂቀ ራጉኤል ወልደ ኤሳው፣ ናሆት፣ ወዛራ፣ ወሲን፣ ወሞዛኅ ፣

የኤሳው ልጅ ራጉኤል የወለዳቸው ልጆቹ ፤ ናሆትና ዛራ፣ ሲንና ሞዛኅ ናቸው ፤

እሉ እሙንቱ ደቂቀ ቤሴሞት ብእሲተ ኤሳው ፣

የኤሳው ሚስት ቤሴሞት የወለደቻቸው ልጆች እሊህ ናቸው አለ፣ እንዳለፈው ልጇንም የልጅ ልጆቿንም ቈጥሮ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ቤሴሞት አላቸው ፤

፲፬፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሌማ ወለተ ሐና ብእሲተ ኤሳው ዘወለደት ለኤሳው ዮሔል፣ ወይጉሚል ወቆሬ፣

ለኤሳው የወለደችለት የኤሳው ሚስት የሐና ልጅ ኤሌማ፣ የወለደቻቸው ልጆች ፣ እሉ እሙንቱ፣ እሊህ ናቸው አለ፣ ዮሔል፣ ይጉሚል ፣ ቆሬ ናቸው ፤ እሉ እሙንቱ ያለውን አመጣ ፤

፲፭፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቁ ለኤሳው መሳፍንት ፣

መስፍንነት የተሾሙ ኤሳው የወለዳቸው ልጆቹ እኒህ ናቸው አለ ፣ ይህ የወል ነው ፤ እሉ እሙንቱ መሳፍንት ያለውን ወደፊት እየተረተረ ያመጣዋል፤

፲፮፡ ደቂቀ ኤልፋዝ በኵሩ ለኤሳው ቴማን መስፍን፤ ወኤሞር መስፍን፤ ወሳፍር መስፍን፤ ወቄኔዝ መስፍን፣

መስፍንነት የተሾሙ የኤሳው የበኵር ልጁ ኤልፋዝ የወለዳቸው ሹማምንቱ እሊህ ናቸው፣ አንዱ መስፍንነት የተሾመ ቴማን ነው፤ ሁለተኛው ኤሞር ነው፤ ሦስተኛው መስፍን (ሹም)



ሳፍር ነው፡ አራተኛው መስፍን ቄኔዝ ነው ፤

፲፯፡ ወቆሬ መስፍን፡ ወጎቶ መስፍን፡ ወአማሌቅ መስፍን ፣

ቆሬም መስፍን ነው ፤ ጎቶም መስፍን ነው አለ፣ እኒህ የኤልፋዝ የልጅ ልጆቹ ናቸው፤ አምስተኛው መስፍን አማሌቅ ነው አለ ፤ አማሌቅ ግን ልጁ ነው ፤

እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ኤልፋዝ በምድረ ኤዶም እለ ተወልዱ እምነ ሐዳሰ ፣

እለ ተወልዱ በምድረ ኤዶም መሳፍንት፣ በምድረ ኤዶም ብለው ይገጥሙታል፤ በኤዶምያስ አገር፣ ከሐዳሰ የተወለዱ፣ ኤልፋዝ ፣ መሳፍንት አድርጎ የሾማቸው እኒህ ናቸው ፤ አንድም ከሐዳሰ የተወለዱ ኤልፋዝ በኤዶምያስ አገር መሳፍንት አድርጎ የሾማቸው እሊህ ናቸው፤ በሀገሩ ከእናት ከአባቱ ተወልዶ በሀገሩ መሾም እጅግ የሚያስደንቅ ሀብተ እግዚአብሔር ነውና ይህን ሲያይ እለ ተወልዱ በኤዶም መሳፍንት በኤዶም ብሎ ተናገረው ፤

፲፰፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ራጉኤል ወልደ ኤሳው መሳፍንት ፣

የኤሳው ልጅ ራጉኤል የወለዳቸው መስፍንነት የተሾሙ ሰዎች እኒህ ናቸው ፤ አንድም መስፍንነት የተሾሙ የኤሳው ልጅ ራጉኤል የወለዳቸው ልጆች እኒህ ናቸው ፤ መሳፍንት ያለውን ይተረትራል ፤

ናሆት መስፍን ወዛራ መስፍን፡ ወሲን (ወሲም) መስፍን፣ ወሞዛኅ መስፍን፣

መሳፍንትም ያላቸው መጀመሪያ መስፍንነት የተሾመ አንዱ ናሖት ነው፣ ሁለተኛው መስፍን ዛራ ነው፣ ሦስተኛው መስፍን ሲን፣ አራተኛው መስፍን ሞዛኅ ነው ፤

እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ራጉኤል በምድረ ኤዶም እለ ተወልዱ እምነ ቤሴሞት ብእሲተ ኤሳው ፣

እለ ተወልዱ በምድረ ኤዶም መሳፍንት ፣ በምድረ ኤዶም ብለው ይገጥሙታል ፣ ትርጓሜው እንደዚያው ነው፣ ሐተታውም እንዳለፈው ነው ፤

፲፱፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሌማ ብእሲተ ኤሳው መሳፍንት ፣

መስፍንነት የተሾሙ የኤሳው ሚስት ኤሌማ የወለደቻቸው ልጆች እኒህ ናቸው ፤ አንድም የኤሳው ሚስት ኤሌማ የወለደቻቸው መስፍንነት የተሾሙ ሰዎች እኒህ ናቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ዮሔል መስፍን፣ ወይጉሚል መስፍን፡ ወቆሬ መስፍን ፤

መሳፍንትም ያላቸው አንዱ መስፍን ዮሔል ነው ፤ ሁለተኛው መስፍን ይጉሚል፣ ሦስተኛው መስፍን ቆሬ ነው ፡

፳፡ እሉ እሙንቱ ደቂቀ ኤሳው መሳፍንተ ኤዶም ፤

በኤዶምያስ መስፍንነት የተሾሙ የኤሳው ልጆች እሊህ ናቸው ፡ አንድም እነሀ የኤሳው ልጆች በኤዶምያስ መስፍንነት የተሾሙ ናቸው ፡

፳፩፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሲን ሂርያዊ (ደቂቀ ሴይር ሆርያዊ) እለ ይነብሩ ዲበ ምድር ፤

በኤዶምያስ አገር የሚኖሩ የሆርያ ወገን የሚሆን የሲን ልጆች እነሀ ናቸው፡ አንድም ደቂቀ ሴይር ሆርያዊ ይላል አብነት፣ በኤዶምያስ አገር የሚኖሩ በሆርያ አጠገብ ያለ የሴይር ልጆች እሊህ ናቸው አለ ፤ ሴይርም ሆርያም፣ ስመ ሀገር ነው፡ በተወለዱበት አገራቸው ደቂቀ ሴይር ብሏቸዋል፡ ልጅ የአማራ፣ ልጅ የጎጃም እንዲሉ ፤ በሀገር ለመጠራት፡ አንድም ስመ ሰብእ ነው ፤ በኤዶምያስ የሚኖሩ የሆርያ ወገን የሚሆን የሴይር ልጆች እሊህ ናቸው ፤ ይህ ሴይር የሲን ሁለተኛ ስሙ ነው፡

አንድም የራጉኤል የልጅ ልጁ ነው ፡

፳፪፡ ሎጣን ወሶባን ወሳባት ወአናም (ወእናን) ወዲሶን ወኤሶር ወዲሳን፣

ደቂቅ ያለውን ይተረትራል ፤ እሊህም የሴይር ልጆች ናቸው ያላቸው፣ ሎጣን፣ ሶባን፣ ሳባት፣ አናም ፤ ዲሶን ፤ ኤሶር ፤ ዲሳን ናቸው፡ እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ደቂቀ ሴይር ሆርያዊ (ወደቂቀ ሲን ሂርያዊ) ከሔሪ የተወለዱ የሲን (የሴይር) ልጆች መሳፍንት እሊህ ናቸው ፡

፳፫፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሎጣን ሔሪ ወሐማን ፤

የሎጣን ልጆች እነሀ ናቸው ፤ እነሀም ሐማንና ሔሪ ናቸው፡

ወእኅተ ሎጣን ትምናእ ፤

የሎጣንም እኅት ትምናእ ናት አለ፣ በሀገራቸው ወንድና ሴት ቀላቅለው አይቆጥሩም ነበር ስለምን ይቺን ሴት ከወንዶች ጋር ቀላቅሎ ቈጠራት ቢሉ፣ ደግ ሴት ነበረችና ስለ ደግነቷ አብሮ ቀላቅሎ ቈጥሯታል ፡

፳፬፡ ወደቂቀ ሶባን አልዋን ወማኔሐት ወአቤል ወሳፋን ወአውናም ፤

የሶባንም ልጆች አልዋን፣ ማኔሐት፣ አቤል፣ ሳፋን፣ አውናም ናቸው ፡



፳፭፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ሳባቅ፣ ኢአ ወአናን ፤

የሳባቅም ልጆች እሊህ ናቸው፣ እሉ እሙንቱ ያለውን ወደፊት ያመጣል ፤ እለዚህም አናንና ኢአ ናቸው ፡

ወውእቱ አናን ዘረከበ ለየሚን በገዳም ወቀተሎ ለአንበሳ እንዘ ይርኢ አዕዱገ ሳባቅ አቡሁ ፤

ይኸውም አናን በምድረ በዳ ትኩስ (ፍል) ወሀ ፡ አንድም አንበሳ ያገኘ እሱ ነው ፤ አንበሳውንም ፤ የአባቱ የሳባቅን አህዮች ሲጠብቅ ገደለው ፡

፳፮፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ አናን ዴሳን ወኤሊሚ ወለተ ሐናን ፤

የአናን ልጆች እነሀ ናቸው ፤ እለዚህም የአናን ልጅ የምትሆን ኤሊሚን፣ ዲሳን ናቸው፡

፳፯፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ዲሳን ሕምዳን፣ ወአስባን፣ ወቢያር፣ ወይትራን፣ ወክራን ፤

የዲሳንም ልጆች እሊህ ናቸው፡ እሊህም ፤ ሕምዳን ፤ አስባን ፤ ቢያር፣ ይትራን፣ ክራን ናቸው፡

፳፰፡ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ኢሶር ብልሐን ወዛአን ወአቃን ፤

የኢሶርም ልጆች እሊህ ናቸው እለዚህም ብልሐን ፤ ዛአን ፤ አቃን ናቸው ፡

፳፱፡ ወእሉ እሙንቱ እንከ ደቂቀ ዲሳን ዑሳ ወአራን ፤

የዲሳንም ልጆች እሊህ ናቸው፣ እሊህም ዑሳ፣ አራን ናቸው ፡

፴፡ ወእሉ እሙንቱ መሳፍንተ ሄሪ፣ (ሖሪ) ሎጣን መስፍን ወሶባን መስፍን ወዲሶን መስፍን፣ ወኢሶር መስፍን፣ ወአናን መስፍን ፤

ሄሪ ስመ ሰብእ ነው፣ አባታቸው ሄሪ መስፍንነት የሾማቸው ፡ አንድም ሄሪ ስመ ሀገር ነው፣ በሖሪ መስፍንነት የተሾሙ እነሀ ናቸው፣ እሊህም አንዱ መስፍን ሎጣን ነው፣ ሁለተኛው መስፍን ሶባን ነው፣ ሦስተኛው መስፍን ሳባቅ ነው፣ አራተኛው መስፍን ዲሶን ነው፣ አምስተኛው መስፍን ኢሶር ነው፣ ስድስተኛው መስፍን አናን ነው ፡

፴፩፡ እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ሔሪ በበመሳፍንቲሆሙ ውስተ ምድረ ሴይር ፤

ሔሪ አባታቸው በሴይር አገር በየሹመት በየሹመታቸው ፡ መስፍን አድርጎ የሾማቸው ፤ አንድም መሳፍንተ ሖሪ ውስተ ምድረ ሴይር ብለህ ግጠም ፡ በሴይር አገር ውስጥ ባለች ሆሪ በምትባል አገር በየሹመት በየሹመታቸው መስፍን ሁነው ተሹመው የሚገዙ እነሀ ናቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፡ ወእሉ እሙንቱ ነገሥት እለ ነግሡ በኤዶም ዘእንበለ ይንግሥ ንጉሥ ለእስራኤል ።

ለእስራኤል ንጉሥ ሳይነግሥላቸው፣ ለኤዶምያስ የነገሡ ነገሥታት፡ እንድም፣ በእስራኤል ንጉሥ ሳይነግሥባቸው በኤዶምያስ የነገሡ ነገሥታት እሊህ ናቸው ።

፴፫፡ ወነግሠ በኤዶም ባላቅ ወልደ ቤዖር ወስመ ሀገሩ ዲናባ ።

የቤዖር ልጅ ባላቅም መጀመሪያ በኤዶም ነገሠ ። የተወለደበት የሀገሩም ስም፡ እንድም ነግሦ ከተማ ያደረገበት የሀገሩ ስም ዲናባ ይባላል ።

፴፬፡ ወሞተ ባላቅ፣ ወነግሠ ህየንቴሁ ኢዮባብ ወልደ ዛራ ዘእምነ ባሱራስ፣

ባሱራስ (ባሶራ) ይላል ፣ ከዚያ በኋላ ባላቅ ሞተ፣ ባሱራስ ስመ ሀገር ነው ፣ ከባሱራስ አገር የተወለደ፡ እንድም ስመ ሰብእ ነው፡ ከባሱራስ የተወለደ፣ የዛራ ልጅ ኢዮባብ ፡ እንድም ከባሱራስ የተጋባ የዛራ ልጅ ኢዮባብ በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ፡

፴፭፡ ወሞተ ኢዮባብ፣ ወነግሠ ህየንቴሁ ሑሳም፣ ዘእምነ ምድረ ቴማኒ፣

ከዚያ በኋላ ኢዮባብ ሞተ ፣ ቴማኒ ስመ ሀገር ነው፣ ከቴማኒ አገር የተወለደ ሑሳም፡ እንድም ስመ ሰብእ ነው፣ ከቴማኒ የተወለደ ፡ እንድም ከቴማኒ አገር የተጋባ ሑሳም በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ ፡

፴፮፡ ወሞተ ሑሳም ወነግሠ ህየንቴሁ አዳድ ወልደ በዳድ ፣ ዘቀተሎሙ ለምድያም በሐቅለ ሞዓብ ወስመ ሀገሩ አዊት ፣

በዚያ ወራት ሑሳም ሞተ ፣ ወልደ በዳድ ዘቀተሎሙ ብሎ ሁለት ቅጥል ለአዳድ ቀጠለ፣ በሞዓብ አውራጃ የምድያምን ሰዎች የወጋቸው የበዳድ ልጅ አዳድም በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ ፡ እንድም እየራሱ ለማውጣት ዘቀተሎሙ ለምድያም ብሎ ለበዳድ ይቀጽላል፣ ወልደ በዳድ ብሎ ለአዳድ ቀጸለ ፣ በሞዓብ አውራጃ የምድያምን ሰዎች የገደለ (የወጋ) የበዳድ ልጅ፣ አዳድም በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ፣ የተወለደበት፡ እንድም ነግሦ ከተማ ያደረገበት የገሩም ስም አዊት ይባላል ፡

፴፯፡ ወሞተ አዳድ ወነግሠ ህየንቴሁ ሰምላ ዘእምነ መስርቃ ፣

አዳድም በዚያ ወራት ሞተ ፣ መስርቃ ፣ ስመ ሀገር ነው ፡ መስርቃ ከሚባል አገር የተወለደ ሰምላም፣ በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ፡ እንድም መስርቃ ስመ ሰብእ ነው፡ መስርቃ



ከሚባል ሰው የተወለደ ፡ እንድም መስርቃ ከሚባል ሰው ጋር የተጋባ ፡ እንድም እምንታማሣ ነው፣ መስርቃ ሚስቱ የሆነች ሰምላም በእሱ ተተክቶ ነገሠ ፡

፴፰፡ ወሞተ ሰምላ ወነግሠ ህየንቴሁ ሳኦል ዘእምነ ሮአቦት እንተ ፈለግ፣

ከዚህ በኋላ ሰምላ ሞተ፣ ሮአቦት ስመ ሀገር ነው፣ በታላቅ ወንዝ አጠገብ ያለ ሮአቦት ከሚባል አገር የተወለደ ሳኦልም በእሱ ተተክቶ ነገሠ፡ እንድም ስመ ሰብእ ነው፣ በታላቅ ወንዝ አጠገብ ከሚኖር ሮአቦት ከሚባል ሰው የተወለደ ፡ እንድም በታላቅ ወንዝ ዳር ከሚኖር ሮአቦት ከሚባል ሰው ጋር የተጋባ፡ እንድም በታላቅ ወንዝ ዳር ካለች ሮአቦት በምትባል አገር ከተማ አድርጎ የሚኖር ሳኦልም፣ በእሱ ፈንታ ተተክቶ ነገሠ ፡

፴፱፡ ወሞተ ሳኦል ወነግሠ ህየንቴሁ በአለናን ወልደ አክቦር ፣

ከዚህ በኋላ፣ ሳኦል ሞተ የአክቦር ልጅ በአለናንም በእሱ ተተክቶ ነገሠ ፡

፵፡ ወሞተ በአለናን ወልደ አክቦር ወነግሠ ህየንቴሁ አዳር ፣ ወስመ ሀገሩ ፍጉ ወስመ ብእሲቱ ምኤጠብኤል ወለተ ምጥሬድ (መጥሬድ) ወለተ ሜዛአብ ፣

የአክቦር ልጅ በአለናንም ከዚያ በኋላ ሞተ ፣ አዳርም በእሱ ተተክቶ ነገሠ፡ የተወለደበት አገርም ፍጉ ይባላል፡ እንድም ነግሦ ከተማ ያደረገበት አገርም ፍጉ ይባላል ፡ (የሀገሩም ስም ፍጉ ይባላል) የሚስቱም ስም፣ የመጥሬድ የሜዛአብ ልጅ ምኤጠብኤል ነው፣ መጥሬድ አባቷ ነው ፣ ሜዛአብ አያቷ ነው ፣ ስለዚህ ሁለት ቅጽል ቀጸለላት፣ ወለተ መጥሬድ ፡ ወለተ ሜዛአብ ብሎ፡ እንድም መጥሬድ እናቷ ናት፡ ሜዛአብ አያቷ ነው፣ የሚስቱም ስም ፣ የሜዛአብ ልጅ፣ መጥሬድ፣ የመጥሬድ ልጅ ምኤጠብኤል ነው ፡

፵፩፡ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆሙ ለመሳፍንቲ ኤሳው በበነገዶሙ ወበበሐሮሙ ወበበአስማቲሆሙ ፣

በየነገዳቸው፣ በየሀገራቸው፣ በየስማቸው ከኤሳው ተወልደው መስፍንነት የተሾሙ ሰዎች ስማቸው ይህ ነው አለ፣ አስማቲሆሙ ያለውን ይተረትራል ፡

፵፪፡ ትምናእ መስፍን፣ ዐልዋ መስፍን፣ ኢቴት መስፍን፡ ኤሌማ መስፍን፣ ኢላ መስፍን፣ ፊኖን መስፍን ቄኔዝ መስፍን ፣ ቴማን መስፍን ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሚብሳር መስፍን፡ መግዲኤል መስ ፍን፣ ኢራም መስፍን ፣

አንዱ መስፍን ትምናዕ ነው፡ ሁለተኛው መስፍን ዓልዋ ነው፡ ሦስተኛው መስፍን ኢቴት ነው፡ አራተኛው መስፍን ኤሌማ ነው፡ አምስተኛው መስፍን ኢላ ነው፡ ስድስተኛው መስፍን ፊኖን ነው፡ ሰባተኛው መስፍን ቄኔዝ ነው፡ ስምንተኛው መስፍን ቴማን ነው፡ ዘጠኘኛው መስፍን ሚብ ሳር ነው፡ ዐሥረኛው መስፍን መግዲኤል ነው ፡ አሥራ አን ደኛው መስፍን ኢራም ነው ፡ አንድም መሳፍንተ ኤሳው ያለ ውን ይተረትራል ፡ አንዱ ትም ናዕ መስፍን ነው ፣ ሁለተኛው አልዋ መስፍን ነው ፡ ሦስተ ኛው ኢቴት መስፍን ነው ፡ አራተኛው ኤሌማ መስፍን ነው፡ አምስተኛው ኢላ መስፍን ነው፡ ስድስተኛው ፊኖን መስ ፍን ነው ፡ ሰባተኛው ቄኔዝ መስፍን ነው ፡ ስምንተኛው ቴማን መስፍን ነው ፡ ዘጠኝ ኛው ሚብሳር መስፍን ነው ፡ ዐሥረኛው መግዲኤል መስፍን ነው፡ አሥራ አንደኛው ኢራም መስፍን ነው ፡

፵፫፡ እሉ እሙንቱ መሳፍንተ ኤዶም በበማኅደሮሙ ዘበምድሮሙ ፣

በሀገራቸው በየማደሪያቸው የኤዶምያስ መሳፍንት እኒህ ናቸው ፡ አንድም በበማኅደ ሮሙ፣ ወበበምድሮሙ ይላል፣ በየሀገራቸው በየማደሪያቸው ሁነው በኤዶምያስ መስፍንነት የተሾሙ ሰዎች እኒህ ናቸው ፡

፵፬፡ ወለሊሁ ኤሳው አቡሆሙ ውእቱ ለኤዶም ፣

የኤዶምያስ ሰዎች አባታቸው ኤሳው ነው፡ አንድም፣ ኤዶም ማለት ፊታዊ ማለት ነው ፣ ኤሳውም ማለት ፊታዊ ማለት ነው ፡ ያልተሰጣቸውን የሚሹ ሰዎች አባታቸው ያልተሰጠ ውን የሚሻ ኤሳው ነው ፡ አን ድም ያልተሰጣቸውን ለሚሹ ሰዎች ያልተሰጠውን የሚሻ አባታቸው ኤሳው ነው ።

## ምዕራፍ ፴ወ፯

፩፡ ወነበረ ያዕቆብ ውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ነበረ አቡሁ ውስተ ምድረ ከነዓን ፣

በዚያ ወራት ያዕቆብ በከነዓን ውስጥ አባቱ ይስሐቅ ይኖርባት በነበረች አገር ኖረ ፡ አንድም ወነበረ ያዕቆብ ውስተ ምድር እንተ ውስቴታ ነበረ አቡሁ ይላል ፣ ያዕቆብ በዚያ ወራት ፣ አባቱ ይስሐቅ ይኖርባት በነበ ረች አገር ኖረ፣ እንተ ውስቴታ ነበረ አቡሁ ያለውን ገና ወደ ፊት ያመጣል ፣ ውስተ ምድረ ከነዓን ፣ ይህችውም አባቱ ይስ ሐቅ ይኖርባት ነበር ያልኋት አገር በከነዓን ውስጥ ያለች መንደር ናት ፡



፪፡ ወከመዝ ውእቱ ፍጥረቱ ለያዕ ቆብ ፣

የያዕቆብ ግብሩ ይህ ነው ፣ አንድም የያዕቆብ የትውልዱ ቍጥር ይህ ነው ፡

ወከኖ ለዮሴፍ ፲ተወ፯ተ ዓመተ ወይ ርዒ ምስለ አኃዊሁ አባግዓ አቡሁ ወወሬዛ ውእቱ ምስለ ደቂቀ ባላ ወምስለ ደቂቀ ዘለፋ አንስትያ አቡሁ ፣

ያን ጊዜ ለዮሴፍ አሥራ ሰባት ዘመን ሆኖት ነበር ፣ ከወንድ ሞቹ ጋራ እንደ ወንድሞቹም የአባቱን የያዕቆብን በጎች ይጠ ብቅ ነበር፣ እንደ አባቱ እንደ ያዕቆብ ሚስቶች እንደ ዘለፋ ልጆችና እንደ ባላ ልጆችም ሕፃን ነበር ፡ አንድም ወከኖ ለዮሴፍ ፲ተወ፯ተ ዓመተ ወወ ሬዛ ውእቱ ወይርዒ ምስለ አኀዊሁ አባግዓ አቡሁ ይላል አብነት፣ በዚያ ወራት ለዮሴፍ አሥራ ሰባት ዘመን ሆኖት ነበር ፣ እሱም ያሥራ ሰባት ዘመን ወጣት (ሕፃን) ነበር ፡ ምንም ሕፃን ቢሆን ከአባቱ ከያዕቆብ ሚስቶች ከዘለፋ ልጆ ችና ከባላ ልጆች ጋር የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር ፡

ወአምጽኡ ላዕለ ዮሴፍ ውጼተ እኪተ ኀበ አቡሆሙ እስራኤል ፣

በዚያ ወራት ወንድሞቹ በዮሴፍ ላይ ፣ በአባታቸው በያዕቆብ ዘንድ ጽኑ ነገር ሥራ አመጡ በት አለ ፣ ነገር ሠርተን እና ጣላው አሉ ፡

፫፡ ወያዕቆብሰ ያፈቅሮ ለዮሴፍ እምኵሎሙ ደቂቁ እስመ በርስዓኑ ወለዶ ፣

ያዕቆብ ግን ፣ በእርግናው ወል ዶታልና ፣ በእርግናው ስለ ወለ ደው ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ዮሴፍን ይወደው ነበር ፡ አን ድም ፣ ራሔልን ይወዳት ነበርና የራሔል ሺታ እያለ ዮሴፍን ይወ ደው ነበርና ፡

ወገብረ ሎቱ ክዳነ ዘኅብረ ዓስቅ ፣

ከመውደዱም የተነሣ አራት ኅብር ግምጃ አሠርቶ አልብሶት ይኖር ነበር ፡

፬፡ ወሶበ ርእዩ አኀዊሁ ከመ ኪያሁ ያፈቅር አቡሆሙ እምኵሎሙ አኀ ዊሁ ጸልእዎ ወኢክህሉ ተናግሮቶ ሠናየ ቃለ ፣

አባታቸው ያዕቆብም ከሁላቸው ይልቅ እሱን ብቻ ለይቶ እንደ ወደደው ባዩ ጊዜ ፣ ወንድሞቹ ዮሴፍን ጠሉት፣ በጎ ቃል ሊና ገሩትም አልተቻላቸውም ፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወሐለመ ዮሴፍ ሕልመ ወነገሮሙ ለአኃዊሁ ፤

በዚያ ወራት ዮሴፍ ሕልም አለመ ፤ ሕልሙንም ለወንድሞቹ ገልጦ ነገራቸው ፤

፮፡ ወይቤሎሙ ስምዕዎ ለዝንቱ ሕልም ዘሐለምኩ ፤

ለወንድሞቹም ይኸንን ያለምኹትን ሕልም ስሙት አላቸው፤

፯፡ እሬኢ ከላስስቲክሙ ዘዘኢአክሙ ማዕከለ ገዳም ወተንሥአ ክልስስት ዘኢአየ ወቆመ ወተመይጡ ከላስስቲክሙ ወሰገዱ ለዘኢአየ ክልስስት ፤

በምድረ በዳው መካከል ዓሥራ ሁለት ነዶዎችና ሁለት ክምሮች አያለሁ፤ ከአሥራ ሁለቱ ነዶዎች፤ አንዱ ነዶ በእኔ በኩል ነው፤ ዓሥራ አንዱ ነዶዎችና ሁለቱ ክምሮች በእናንተ በኩል ናቸው፤ ያንጊዜ፤ በእኔ በኩል ያለው አንዱ ነዶ ተነሥቶ ሲቆም በናንተ በኩል ያሉት አስራ አንዱ ነዶዎችና ሁለቱ ክምሮች ተመልሰው መጥተው በእኔ በኩል ላለው ላንዱ ነዶ ሲሰግዱለት አየሁ አላቸው ፤ (ሐተታ) ያንጊዜ አባቱ ያዕቆብ ይህንን ሰምቶ ሲተረጉምለት፤ ሁለቱ ክምሮች እኔና እናትህ ነን ፤ እናቱማ ሙታ የለም ? ቢሉ፤ ብትኖር የምትሰግድለት ስለ ሆነ፤ አንድም ሞግዚቲቱን ቈጥሮ ነው ፤ አሥራ አንዱ ነዶዎች፤ አሥራ አንዱ ወንድሞችህ ናቸው ፤ በአንተ በኩል ላለው ለአንዱ ነዶ ሲሰግዱለት ማየትህ፤ እኔና እናትህ ወንድሞችህም በዚህ ዓለም፤ ለአንተ እንገዛልህ ይሆናል ብሎ ተረጐመለት፤ ልጄ እንግዴህ ወዲያ አለምኹ አለምኹ አትበል ብሎ ነግሮታል ፤

፰፡ ወይቤልዎ ነጊሥኑ ትነግሥ ላዕሌነ ወሚመ እግዚአኑ ትከውነነ ፤ ወአፈድፈዱ ዓዲ ጸሊዖቶ በእንተ ሕልሙ ወበእንተ ነገሩ ፤

እንዲህ ብሎ ቢነግራቸው ከእኛ በላይ ንጉሥ ሁነኸ ትነግሥብን ይሆን? ይህም ባይሆን ከንጉሥ በታች መስፍን ሁነህ ትገዛን ይሆን ? ብለው ቀድሞ ሕልም ስለማየቱ ፤ ኋላም ደፍሮ ስለ መናገሩ ዳግመኛ አጽንተው ጠሉት ፤

፱፡ ወደገመ ዓዲ ወርእየ ሕልመ ወነገሮ ለአቡሁ ወይቤሎ ናሁ ሐለምኩ ካልዓ ሕልመ፤ ወከመዝ ሕልሙ፤ ፀሐይ ወወርኅ ወ፲ቱ ወ፩ዱ ከዋክብት ይሰግዱ ሊተ ፤

ዳግመኛ ዮሴፍ ሕልም አየ (አለመ)፤ አንድም ዳግመ ዓዲ ይላል፤ ዳግመኛ ሁለተኛ ዮሴፍ ሕልም አየ ፤ ሕልሙንም ለአባቱ ለያዕቆብ ነገረው፤ እንዲህ ብሎ ፤ ሁለተኛ ሕልም አየሁ ፤



አንድም ካልዓ ሌላ ሕልም አየሁ ፤ አንድም ይቤሎ ካልዓ ናሁ ሐለምኩ ሕልመ ይላል ፤ በሌላ ጊዜ እነሆ ሕልም አለምኩ፤ ሕልሙም እንዲህ ነው፤ በፀሐይና በጨረቃ መካከል አሥራ ሁለት ከዋክብት አያለሁ፤ ከአሥራ ሁለቱ ከዋክብት አሥራ አንዱ ኮከቦች በአንተና በእናቴ በወንድሞቼ አጠገብ ናቸው፤ አንዱ ኮከብ በእኔ በኩል ነው፤ ያን ጊዜ አሥራ አንዱ ኮከቦች ፀሐይና ጨረቃ አንድ ሁነው ተመልሰው መጥተው በእኔ በኩል ላለው ለአንዱ ኮከብ ሲሰግዱ አየሁ አለው ፤

፲፡ ወገሠፆ አቡሁ ወይቤሎ ምንትኑ ውእቱ ዝንቱ ሕልምከ ዘሐለምከ ሶበሰ አሐዝብ ንመጽእ አነ ወእምከ ወአኃዊከ ወንሰግድ ለከ ዲበ ምድር፤

ይህንንም ሰምቶ አባቱ ይህ ያለምኸው ሕልምህ ምንድን ነው? አንድም አንተ ያለምኸው ሕልምኽ ይህ ምንድነው? ልጄ ምነው አለምኹ አለምኹ አትበል ብዬህ አልነበረምን ? ብሎ ተቈጣው፤ አንድም ወገሠፆ፤ ለጊዜው ይህን ሰምቶ ተቈጣው፤ ወይቤሎ ምንትኑ ዝንቱ ሕልምከ ይላል ፤ ይህ ሕልምህ ደጋገሙኝ ምን ይሆን ? ብሎ አደነቀ ፤ ይወደዋልና ይተረጕምለታል ፀሐይና ጨረቃ እኔና እናትህ ነን ፤ ምነዋ እናቱማ ሙታ የለም ? ቢሉ፤ ሐተታ እንዳለፈው ነው፤ አሥራ አንዱ ከዋክብት፤ አሥራ አንዱ ወንድሞችህ ናቸው ፤ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንዱ ከዋክብት አንድ ሁነው በአንተ በኩል ላለው ለአንዱ ኮከብ ሲሰግዱለት ማየትህ እኔስ እንዳሰብኹት ፤ እኔና እናትህ አሥራ አንዱ ወንድሞችህ አንድ ሁነን በዚህ ዓለም ለአንተ እንገዛልህ ይሆናል ብሎ ተረጐመለት ፤

፲፩፡ ወቀንኡ ላዕሌሁ አኃዊሁ፤ ወአቡሁሰ ዐቀቦ ለዝንቱ ነገር በልቡ ፤

አሥራ አንዱ ወንድሞቹም ይኸን ሰምተው ቀድሞ ሕልም በማየቱ ፤ ኋላም ደፍሮ በመናገሩ በዮሴፍ ቀኑበት ፤ አባቱ ያዕቆብ ግን ይህነን ነገር በልቡናው አኑሮ አስተዋለው ፤ ተመለከተው ፤

፲፪፡ ወሖሩ አኃዊሁ ይርአዩ አባግዐ አቡሆሙ ውስተ ሴኬም ፤

ከዚያ በኋላ ወንድሞቹ የአባታቸውን የያዕቆብን በጎች ይዘው ወደ ሴኬም ኀደና ሔዱ ፤

፲፫፡ ወይቤሎ እስራኤል ለዮሴፍ አኮኑ አኃዊከ ውስተ ሴኬም ነዓ እልአከ ኀቤሆሙ፤ ወይቤሎ እሆ ነየ፤

በዚያ ወራት እስራኤል የተባለ ያዕቆብ፤ ዮሴፍን፤ ወንድሞችህ

www.ethiopianorthodox.org

በሴኬም በጎች አንድነው ያሉ አይደለምን፤ አንድም ወንድሞችህ በጎች አንድነው በሴኬም አሉና ወደ እነሱ ና ልላክህ ፤ አንድም ና ወደ እነሱ ልላክህ አለው ፤ ዮሴፍም እነሆ አለሁ ላከኝ ፤ አንድም ላከኝ እነሆ አለሁ አለው ፤

፲፬፤ ወይቤሎ ሑር ርኢ እመ ዳኅኑ አኃዊከ ወአባግዒሆሙኒ ወዜንወኒ ወፈነዎ እምቈላተ ኬብሮን ወበጽሐ ውስተ ሴኬም ፤

ወንድሞችህ በጎቻቸውም ደኅና እንደሆኑ ሒደህ አይተህ ንገረኝ ፤ አንድም ወንድሞችህ ፤ ወአባግዕየኒ ፤ በጎቼም ደኅና እንደሆኑ አይተህ ንገረኝ ፤ ሒድ ብሎ የስንቅ አቅማዳውን አስይዞ ከኬብሮን ቈላ ላከው፤ ዮሴፍም ከኬብሮን ቈላ ተነሥቶ ሒዶ ወንድሞቹ ከአሉበት ሴኬም ደረሰ ፤

፲፭፤ ወረከቦ አሐዱ ብእሲ እንዘ የዓይል ወይሳኰ ውስተ ገዳም ወተስእሎ ወይቤሎ መኑ ተሐሥሥ ፤

ዮሴፍም ወደ ወንድሞቹ የሚሔድበት ጎዳና ጠፍቶት ሲዞር ሲባክን በምድረ በዳው ሲቅበዘበዝ አንድ ሰው አገኘው፤ አንድም ወረከበ አሐደ ብእሴ እንዘ የዐይል ይላል ፤ ዮሴፍ ጐዳና ጠፍቶት ሲዞር ሲባክን በምድረ በዳው ሲቅበዘበዝ አንድ ሰው አገኘ፤ አሐዱ ብእሲ ያለው ያልታወቀ ሰው ነው ፤ አንድም መልአክ በአምሳለ ብእሲ ታይቶታል ፤ ተነጋግሮታል (ወተሰእሎ ዮሴፍ) የራሱን ጎዳና ለመጠየቅ ወንድሞቹንም ለመጠየቅ ፤ ወንድሜ ፤ ማንን ትፈልጋለህ? ብሎ ጠየቀው፤ አንድም፤ ያ ሰው ፤ አንድም መልአኩ ዮሴፍን ወንድሜ ማንን ትፈልጋለህ ? ብሎ ጠየቀው ፤

፲፮፤ ወይቤሎ ዮሴፍ አይድዐኒ አይቴ ይርእዩ አኃውየ ፤

ዮሴፍም፤ ያን ጊዜ ወንድሞቼ በጎች አሰማርተው የሚጠብቁበት ቦታ የት ነው ? ወንድሜ እስኪ ንገረኝ? አለው፤ አንድም ዮሴፍ ወንድሜ እስኪ ንገረኝ? ወአይቴ ፤ ወንድሞቼ በጎች አንድነው የሚጠብቁበት ቦታ ወየት ነው ? አለው ፤

፲፯፤ ወይቤሎ ውእቱ ብእሲ ግዕዙ እምዝየሰ ወሰማዕክዎሙ ፤ ይብሉ ነሐውር ዶታዮን ፤ ወሖረ ዮሴፍ ወተለዎሙ ለአኃዊሁ ወረከቦሙ በዶታዮን ፤

ያ ያልታወቀ ሰው ፤ አንድም መልአኩ ዮሴፍን፤ ወንድሞችህስ የሉም ፤ ከዚህ ተጉዘው ሒደዋል እኔም «እንዘ ይብሉ» ሲል ነው፤ ወደ ዶታዮን እንሔዳለን ሲሉ ሰማኋቸው አለው ፤ ከዚያ በኋላ፤ ዮሴፍ ወንድሞቹ



በጎች አሰማርተው ወዳሉበት ቦታ ተከትሎ ሔዶ በዶታይን አገኛቸው፤ አብነት፤ ዶታዮን፤ ዶታዎን፤ ዶታዮን፤ ዶታይን ይላል፤ አንድ ወገን ነው፤ ገደፊ አያሰኝም እንደዚሁ ያስተረጉማል ፤

፲፰፤ ወቀደሙ ርእዮቶ እምርኁቅ ዘእንበለ ይቅረብ ኀቤሆሙ ወመከሩ ለቀቲሎቱ ፤

ወንድሞቹም ገና ወደ እነሱ ሳይቀርብ ከሩቅ ሁነው ወንድማቸው ዮሴፍን ወደነሱ ሲመጣ አዩት፤ አንድም ወንድማቸው ዮሴፍ፤ ገና ወደነሱ ሳይቀርብ ከሩቅ ሁኖ ወንድሞቹ አስቀድመው አዩት፤ መከሩ ለቀቲሎቱ ያለውን ገና ወደፊት ያመጣል፤

፲፱፤ ወተበሃሉ አሐዱ ምስለ ካልኡ ነዋ ዝንቱ ሐላሚ ፤

ተበሃሉ ካለ ፩ዱ ወካልኡ፤ አሐዱ ምስለ ካልዑም ካለ ተበሃለ ባለ በቀና ነበር ፤ ልማደ መጽሐፍ ነው፤ አንዱ ካንዱ ጋራ ሁነው ያ ወንድማችን መጣ ተባባሉ ፤ አንድም ያ አለምኹ አለምኹ የሚል ወንድማችን ይህ ነው ፤

፳፤ ንዑ ንቅትሎ ወንግድፎ ውስተ አሐዱ ግብ ወንበል አርዌ እኩይ በልዖ ወንርአይ ምንት እማንቱ ሕልሚሁ ፤

አሁንም ኑ እንግደለው፤ አንድም እንግደለው ኑ ገድለንም ባንዱ ቀበሮ ጕድጓድ እንጣለው ፤ አንድም ከቀበሮ ጕድጓድ ባንዱ እንጣለው ገድለን ከቀበሮ ጕድጓድም ባንዱ ጥለን ቀበሮ በላው እንበል ፤ ያ አለምሁ አለምሁ የሚለው ሕልሙ የሚያደርግለት ምን እንደ ሆነ እስኪ እንይ ፤ አንድም እስኪ እንይ ያ አለምሁ አለምሁ የሚለው ሕልሙ የሚያደርግለት ምንድ ነው ? ተባባሉ ፤

፳፩፤ ወሰሚዖ ሮቤል አድኀኖ እምእዴሆሙ ወይቤሎሙ ኢትቅትሉ ነፍሶ፤ ወኢትክዓው ደሞ፤ ደይዎ ኀበ ዝንቱ አዘቅት ዘውስተ ገዳም ወባሕቱ እዴክሙ ኢታውርዱ ላዕሌሁ ፤

ሮቤልም ፤ እንዲህ ሲባባሉ በሰማ ጊዜ ፤ ርእዮን ሰማ ሲል ነው ፤ አንድም ሮቤል ገና ሲመጣ ዮሲፍን በሩቁ ባየው ጊዜ ፤ አንድም ዮሴፍ ሲመጣ ሮቤል በሩቁ ሁኖ ባየው ጊዜ፤ ከእጃቸው (ከቃላቸው) ተከራክሮ አዳነው፤ ወንድሞቼ ከወንድማችን ደም ምን አለን ? ተዉ አትግደሉት፤ ደሙንም በግፍዕ አታፍስሱት፤ በምድረ በዳ ካለው ከቀበሮ ጕድጓድ ባንዱ ጥላችሁት ከዚያው ተጣጥሮ ይሙት፤ እናንተ ግን አትግደሉት፡ አንድም ደይዎ ፤ በምድረ በዳ ካለው ከቀበሮ ጕድጓድ ባንዱ

www.ethiopianorthodox.org

ጥላችሁት በዚያው ተጣጥሮ ይሙት እንጂ፣ እናንተስ አት ግደሉት አላቸው ፡

፳፪፥ ወከመዝ ይቤ ሮቤል ከመ ያድኅኖ እምእዴሆሙ ወያግብኦ ኀበ አቡሁ ፣

ሮቤልም እንዲህ ማለቱ ለጊ ዜው ታላቅ ወንድም እንደ አባት ያለ ነውና ፣ ሳይመክር ፣ ሳያስ ተምር ቀረ ይሉኛል ብሎ ነው፡ አንድም ሮቤል ከአባቱ ከያ ዕቆብ ዕቅብት ከባላ ደርሶ ነበ ርና ተከራክሬ (ከቃላቸው) ከእ ጃቸው አድኜ ሰርቄ ወስጄ ከአ ባቴ ከያዕቆብ ጋር መታረቂያ ይሆነኛል ብሎ ነው ፣

፳፫፥ ወእምዝ ሶበ በጽሐ ዮሴፍ ኀቤሆሙ ሰለብዎ ክዳኖ ዘአስቆ ዘይ ለብስ ፣

ከዚያ በኋላ (ከዚያ ቀጥሎ) ወን ድማቸው ዮሴፍ፣ (ናፍቀውኛል) የናፈቁት መስሎት ገስግሶ ወን ድሞቹ ወዳሉበት በደረሰ ጊዜ፣ ሰለብዎ ብለህ እሰር፡ አንድም እነሱ ተሯሩጠው ወደሱ ሒደው ይዘው የለበሰውን አራት ኅብር ግምጃ ገፍፈው ፣ ከበው ይዘው ደበደቡት ፡

፳፬፥ ወነሥእዎ ወወረውዎ ውስተ አዘቅት፣ ወአዘቅቷኒ ሐዳስ ወአል ባቲ ማይ ፣

ልብሱንም ገፍፈው ራቁቱን አድ ርገው አንሥተው ወደ ቀበሮ ጒድጓድ ወርውረው ጣሉት፣ ጒድጓዲቱም አዲስ ነበረች ፣ ውሀም የላትም ነበር ፡ አንድም ጒድጓዲቱ አዲስ ናት ስንኳን ውሀ ርጥበት የላትም ነበር፣ በሀ ገራቸው ዋዕዩ ጽኑዕ ነውና ራቁ ቱን ሁኖ ሲወድቅ ርጥበቱ ያቀ ዘቅዘው ነበርና እንዲህ አለ ፡

፳፭፥ ወነበሩ ይበልዑ እክለ ፣

ያንጊዜ እሱን ራቁቱን አድር ገው፣ በቀበሮ ጒድጓድ ጥለው፣ የጒድጓዱን አፍ በደንጊያ ገጥ መው፣ እነሱ በዚያ ላይ ሁነው፣ የመጣላቸውን ይበሉ ይጠጡ ጀመር ፣ ያንድ ቤት ሰዎች ናቸውና፣ ይኸውም ምሳሌ ነው፡ ዮሴፍ የወልደ እግዚአብሔር፣ ወንድሞቹ የአይሁድ ፣ ምግባ ቸውን ይዞላቸው ቢሔድ ከበው እንደ ደበደቡት፡ ጌታም፣ እንሰ እ.ብለከሙ እንሰ እ.ብለከሙ እያለ ምግበ ነፍሳቸውን ቢያስ ተምራቸው ፡ አይሁድ ጠል ተው ተመቅኝተው የመግደላ ቸው (የመስቀላቸው) ምሳሌ ነው፡ ከዚህ በኋላ ሮቤል ለጉዳዩ ሔዶ ሳለ ፡ አንድም ከብት የሚ መልሱት በተራ ነውና (ነበርና) ከብት ሊመልስ ሔዶ ሳለ ፡

ወሶበ አልዐሉ አዕይንቲሆሙ ወርእዩ ናሁ ነጋድያን ይመጽኡ እምገለዓድ፣ ወይስማኤላውያን እሙንቱ፣ ወዕፁናን አግማሊሆሙ አፈዋተ ወርጢነ ወማየ ልብን፣ ወየሐውሩ ያውርዱ ብሔረ ግብፅ ፣

ዓይናቸውን አቅንተው ቢያዩ፣ ነጋድያን ሽቱ በግመል ጭነው ወደ ግብፅ ሊወርዱ ከገለዓድ ሲመጡ አዩ ፡

፳፮፥ ወይቤሎሙ ይሁዳ ለአኃዊሁ ምንት ይበቍዓነ ለእመ ቀተልናሁ ለእኁነ ወኀባዕነ ደሞ ፣

ያንጊዜ ፣ የይሁዳ ፈታውራሪ ይሁዳ ፣ ወንድማችንን ገድለን ደሙን ብንሠውረው ለኛ ምን ይረባናል ? ምን ይጠቅመናል ?

፳፯፥ ንዑ ንሢጦ ኀበ እሉ ይስማኤላውያን ወእዴነሰ ኢናውርድ ላዕሌሁ እስመ እኁነ ውእቱ ወሥጋነ ወሰምዕዎ አኃዊሁ ዘይቤሎሙ ፣

ለእስማኤላውያን ነጋድያን ኑ እንሸጠው፣ ምንም ቢሆን ወን ድማችን ዮሴፍ የሥጋችን ቁራጭ፣ የአጥንታችን ፍላጭ፣ ወንድማችን ነውና፣ እኛ ግን፣ አንግደለው አላቸው ፡ ይሁዳ ወንድማቸው የነገራቸውን ነገር ወንድሞቹ ሰምተው ፡

፳፰፥ ወእንዘ የኃልፉ እሙንቱ ይስማ ኤላውያን፣ ሰሐብዎ አኃዊሁ ወአው ፅእዎ እምአዘቅት ወሤጥዎ ለዮሴፍ ለይስማኤላውያን በ፳ ዲናር፣ ወወ ሰድዎ ለዮሴፍ ብሔረ ግብፅ ፣

ከይስማኤል የመጡ ነጋዶች ሽቱ ጭነው ሲሔዱ አይተው ዮሴፍን ከጣሉበት ከቀበሮ ጒድ ጓድ ስበው ጎትተው አውጥተው ለይስማኤላውያን ነጋድያን ዮሴ ፍን ፡ በኻያ ወቄት (ብር) ሸጡት ፣ እስማኤላውያን ሽቱ ጭነው ወደ ግብፅ ሲሔዱ ፡ እናንተ ሰዎች ባሪያ አትገዙም ? አሏቸው ፣ ካገኘንማ ምነው አን ገዛ ? አሏቸው ፡ እንኪያስ ደኅና ባሪያ አለላችሁ ግዙ አሏቸው ፣ እስኪ አሳዩን አሏቸው ፣ አው ጥተው ቢአሳዩዋቸው፣ መልከ መልካም ነውሳ አሏቸው ፣ ስምዮን እድግ (ታዳጊ) ባሪያ ቢሆን ነው ይልቅስ እንዳያመል ጣችሁ ብሎ በሰይፍ ጥፊ መትቶ ሸጦታል፡ ይኸውም ሊታወቅ፣ ወትሮ ባሪያ ሲሸጥ፣ በጫማ ጥፊ መትቶ ነውና (ይመታል) ከዚህ በኻያ ወቄት አለ፣ ከዚያ በሠ ላሳ ወቄት ይላል፣ አይጣላም? ቢሉ ፣ አይጣላም ፣ ኻያው በከ ተማ አዋቂ (ሚዛን) ፴ ይሆ ናል ፣ አንድም በከተማ ሚዛን ኻያው ወቄት በሌላው አዋቂ (ሚዛን) ፴ ይሆናል ፡ አንድም ለ፴ ወቄት ሸጠውታል ፡ ዐሥ ሩን ለቀረጥ ፣ ለስንቅ ይሁና ችሁ ብለው ቀንሰውላቸዋል ፡ አንድም ነጋዴ ከረከሰበት ገዝቶ ከተወደደበት አገር ማትረፍ ልማድ ነውና ፣ በኻያ ወቄት ገዝተው ወስደው ፣ ለ፴ ብር ሸጠውታል፡ እስማኤላውያንም፣



www.ethiopianorthodox.org

ዮሴፍን በኻያ ብር ገዝተው ወደ ግብፅ አገር ወሰዱት ፡፡

፳፱፡ ወገብአ ሮቤል ኀበ አዘቅት ወሶበ ኢረከቦ ለዮሴፍ ሰጠጠ አልባሲሁ ፤

ሮቤል ለጉዳዩ ከሔደበት ተመ ልሶ፤ አንድም ከብት ሊመልስ (ለመመለስ) ከሔደበት ተመ ልሶ ፤ ዮሴፍ ወደ ወደቀበት ወደ ጉድጓዱ ሔደ ፡ ሒዶም ዮሴፍን ከጉድጓዱ ባጣው ጊዜ ልብሱን አሰለበ (ቀደደ) ፡፡

፴፡ ወሖረ ሮቤል ኀበ አኃዊሁ ወይቤሎሙ፤ ኢሀሎ ወልድ ውስተ አዘቅት፤ ወአይቴ አሐውር እንከ አነ ፤

ሮቤልም ልብሱን (አስልቦ) ቀዶ ከዚህ በኋላ ወንድሞቹ ወዳሉበት ቦታ ሒዶ ያ ብላቴና ከጣልንበት ጉድጓድ የለም እኔ እንግዲህ ወዴያ ወዴት ልሒድ ? አንድም እንግዲህ እኔ ወዴት እሔዳ ለሁ ? አላቸው ፡፡

፴፩፡ ወነሥኡ ክዳኖ ዘአሥቅ ወሐ ረዱ ላዕሌሁ መሐስዓ ጠሊ ወመልዕዎ ደመ ለክዳኑ ፤

ከዚያ በኋላ፤ አራት ኅብር ያለ ውን ልብሱን ወሰዱ፤ አንድ የፍ የል ጠቦት አርደው ልብሱን ደም ቀቡት ፡፡

፴፪፡ ወወሰዱ ኀበ አቡሆሙ ወይቤ ልዎ ዘንተ ልብሰ ረከብነ ወርኢ ለእመ ውእቱ ክዳኑ ለወልድከ ወለእመ ኢኮነ ፤

ደም የተቀባ ልብሱንም፤ ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ ወስደው፡ ያን ብላቴና ወደኛ ሰደኸው ነበርን ? ይኸንን ልብሱን ከቀ በሮ ጉድጓድ አገኘነው፤ ከእኛ አንተ በምር ታውቀዋለህና ይኸ ንን ልብስ የልጅህ ልብስም እንደሆነ፤ አይደለምም እንደሆነ፤ ከእኛ በምር አንተ ታውቀዋለ ህና ብለን ወደ አንተ ሰድደን ልሃል አሉት ፡፡

፴፫፡ ወአእመረ ወይቤ ክዳኑ ለወል ድየ ውእቱ ፡ ወአርዌ እኩይ በልዖ ወመሠጠ ለዮሴፍ ፤

ያንጊዜ ያዕቆብ አገላብጦ አይቶ የልጄ የዮሴፍ ልብስ እንደ ሆነ አወቀ፡ እውነት ነው የልጄ ልብስ ነው አለ፡ አንድም አእሚሮ ይቤ ይላል ፤ የልጄ ልብስ እንደሆነ አውቆ፤ እውነት ነው ይህ የልጄ ልብስ ነው ፤ ዮሴፍ ልጄንም ቀበሮ በልቶት ነው አለ ፡፡

፴፬፡ ወሠጠጠ አልባሲሁ ያዕቆብ ወለብሰ ሠቀ ወቀነተ ውስተ ሐቌሁ ወለሀዎ ለወልዱ ብዙኃ መዋዕለ ፤

ያዕቆብም ፤ ልብሱን (አስልቦ) ቀድዶ ማቅ ምንጣፍ ለበሰ፤ ማቅ ምንጣፉንም በወገቡ ታጠቀ ፤ ከዚያ በኋላ ማቅ ምንጣፍ ታጥቆ ለልጁ፤ ብዙ ዘመን አለቀሰለት፡



፴፭፡ ወተጋብኡ ደቂቁ ወአዋልዲሁ ወመጽኡ ወአስተብቍዕዎ ለአቡሆሙ ከመ ያንግፍዎ ላሀ፤ ወአበዮሙ ነጊፈ ላህ ወይቤሎሙ ፤ ዳዕሙ እወርድ ውስተ መቃብር ኀበ ወልድየ እንዘ እላህዎ ወበከዮ አቡሁ ፤

ከዚያ በኋላ፤ ወንዶቹና ሴቶቹ ልጆቹ ተሰብስበው መጥተው፤ ኀዘኑን፤ ልቅሶውን ተው ይበቃ ሃል ብለው አባታቸው ያዕቆብን ማለዱት ፤ አባታቸው ግን ፤ ለልጄ ሳለቅስ ሳዝን (እያለቀስኩ እያዘንኹ) ወደ መቃብር እወር ዳለሁ እንጂ አይሆንም ልቅሶ ዬን ኃዘኔን አልተውም አላቸው፤ ያዕቆብም ለልጁ ለዮሴፍ ሲያ ለቅስ (እያለቀሰ) ዓይኑ ጠፋ ፡ (ጠፍቷል) ፡፡

፴፮፡ ወእልክቱሰ እስማኤላውያን ሤጥዎ ለዮሴፍ ብሔረ ግብፅ ለጲጥ ፋራ ሊቀ መበስላኒሁ ለፈርዖን ፤

እስማኤላውያን ግን፤ ዮሴፍን ወደ ግብፅ አገር ወስደው ለፈ ርዖን አዛዥ ቢትወደድ ፡ አን ድም ራቅ ማሰሪያ ስሙ ጲጥፋራ ለሚባል ሰው በ፴ ብር ሸጡት፤ ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ዮሴፍ የወልደ እግዚአብሔር፤ ወንድ ሞቹ የአይሁድ ፤ ይሁዳ የይ ሁዳ፤ እንሸጥን ያነቃ እሱ ነው፤ ይሁዳም ክርስቶስን የሸጠ እሱ ነውና ፤ ስምዖን የጸሐፍት ፈሪ ሳውያን ፤ በሰይፍ ጥፊ መትቶ እንደ ሸጠው፤ ጸሐፍት ፈሪሳው ያንም፤ ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ጸፍአከ ፤ ተነበይ ለነ ክርስቶስ መኑ ኰርዓከ ፤ ብለው (እያሉ) ደብድበውታልና፤ ዮሴፍ ሕያው በግብፅ፡ ምውት በከነዓን ነው፤ ጌታም ሕያው በመለኮቱ ፤ ምውት በትስብእቱ ነውና፡ አን ድም ምሳሌ ይለውጣሉ፡ ዮሴፍ የመለኮት፤ ልብስ የትስብእት፤ ደም የመከራ ምሳሌ ነው ፡ ደሙ ልብሱን እንጂ ዮሴፍን እንዳላገኘው፤ መከራውም ትስ ብእትን ነው እንጂ መለኮትን አላገኘውምና ፡ እንዲህ ስላልነ ግን ፤ ዮሴፍ ከልብሱ እንደ ተለየ፤ መለኮትም ከትስብእት ተለየ ማለት አይደለም፤ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ነው፡ ወሶበ ንሜስል ዘንተ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ኢይምስል ክሙ ዘንፈልጠ ለመለኮት እምትስብእት፡ በከመ ተፈልጠ ዮሴፍ እምልብሱ ከማሁ ኢተፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ እንዲል፡፡

## ምዕራፍ ፴ወ፰

## ገባኤ

፩፡ ወእምዝ ወረደ ይሁዳ በእማንቱ መዋዕል እምኀበ አኃዊሁ ወኃደረ ኀበ አሐዱ አዶላማዊ ዘስሙ ኤራስ ፤

ከዚህ በኋላ ፤ (ከዚህ ቀጥሎ) ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ በዚያ

www.ethiopianorthodox.org

ወራት ወደ ከነዓን ወረደ ፣ ወርዶም (ሒዶም) ስሙ ኤራስ ወደሚባል ከአዶሎሙ ሰው ቤት አደረ ፤

፪፡ ወርእየ አሐተ ወለተ ፩ዱ ብእሲ ከነናዊ፣ ወስማ ሴዋ፣ ወነሥአ ወአውሰባ ፣

ይሁዳም፣ የአንድ የከነዓን ሰው አንዲት ልጅ አይቶ ስሟም ሴዋ ይባላል ብለህ ቸልታ ተርጉም፤ አንድም ወ ያለው ዘ ነው፤ ስሟ ሴዋ የሚባል የአንድ የከነዓን ሰው አንዲት ሴት ልጅ አይቶ ወስዶ አገባት ፤

፫፡ ወፀንሰት ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ኤር ፣

እሷም ከይሁዳ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ስሙንም ኤር አለችው ፣ ፀሐይ ማለት ነው ፤

፬፡ ወፀንሰት ዳግመ ወወለደት ወልደ፣ ወሰመየቶ ስሞ አውናን ፣

ዳግመኛም ፀንሳ ከይሁዳ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ስሙንም አውናን አለችው ፣ ወይን ማለት ነው ፣ አውያን ማለት ነው ፣ መጽሐፍ ፣ ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቀቅምና ፤ አንድም በአገራቸው አውያን ማለት፣ የአንድ ሰው ስም ነው፣ በሀገራችን ፣ አንዱን ሰው ብዙነህ እንድንለው ፤

፭፡ ወዓዲ ደገመት ወወለደት ወልደ ወሰመየቶ ስሞ ሴሎም ፣

አንዱን ለአንዱ ዓዲ ይለዋል፣ ዳግመኛ ፀንሳ ከይሁዳ ወንድ ልጅ ወለደች፣ አንድም ወዓዲ ዳግመ ወለደት ወልደ ይላል፣ ዳግመኛ ሁለተኛ ፀንሳ ከይሁዳ ወንድ ልጅ ወለደች ፣ ለመጀመሪያው ሁለተኛውን ፤ አንድም ለሁለተኛው ሦስተኛውን ዓዲ ዳግመ አለው፣ ስሙንም ሴሎም አለችው ፍቅር ስትል ፤

ወአመ ወለደቶሙ ሀለወት ፣ በውስተ ብሔር ዘስሙ ኬሴቤ፣

እነዚህንም ሦስቱን ወንዶች ልጆች በወለደቻቸው ጊዜ ፣ ስሙ ኬሴቤ በሚባል አገር ትኖር ነበረች ፤

፮፡ ወነሥአ ይሁዳ ብእሲተ እንተ ስማ ትዕማር ለኤር በኵሩ፣

ይሁዳም ለበኵር ልጁ ለኤር ስሟ ትዕማር የሚባል ሚስት አጭቶ አጋባው ፤

፯፡ ወኮነ ኤር በኵሩ ለይሁዳ እኩየ በቅድመ እግዚአብሔር ወቀተሎ እግዚአብሔር፣

የይሁዳ የበኵር ልጁ ኤርም እግዚአብሔር ባወቀው ፤ አንድም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሰው ሆነ አለ፣ ክፉ ሥራ ሠራ፣ አባቴ ፈቃዱ ባይሆን ነው እንጂ፣ ፈቃዱማ ቢሆን ተስፋ ካላቸው



ከአብርሃም ፣ ከይስሐቅ ፣ ከያዕቆብ፣ ከወገኖቼ ያጋባኝ ነበር እንጂ፣ ተስፋ ከሌላቸው ከአሕዛብ ያጋባኝ ነበር ? ብሎ የማ ይደርስባት ሆነ ፤ ፀሩስ ለእግዚአብሔር ትዕቢት ውእቱ እንዲል፤ እግዚአብሔርም ትዕቢቱን አይቶ ቀሠፈው ፤

፰፡ ወይቤሎ ይሁዳ ለአውናን ባዕነበ ብእሲተ እኁከ ወተሐመዎ ወአቅም ዘርአ ለእኁከ ፣

ይሁዳም ፣ አውናን የሚባል ልጁን ወደ ወንድምህ ወደ ኤር ሚስት ግባ፣ ሚስቱንም አግብተህ ለወንድምህ ለኤር ልጅ ወልደህ ተካለት አለው ፤

፱፡ ወሶበ አእመረ አውናን ከመ ኢኮነ ሎቱ ዘርእ ሶበ ቦአ ኀበ ብእሲተ እኁሁ ይክዑ ዘርአ ዲበ ምድር ከመ ኢየሀብ ዘርአ ለእኁሁ ፣

አውናንም የወንድሙ የኤርን ሚስት አግብቶ ያ የወለደው ልጁ የሱ ልጅ ነው እንደማይባል አውቆ ለወንድሙ ልጅ ወልዶ እንዳይተካለት ከእሷ ሥራውን ሠርቶ ከዓዌ ዘርዕ አፍአ እማኅፀን ሆነ ፤

፲፡ ወኮነ እኩየ ውእቱኒ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ከመዝ ገብረ ወቀተሎ ሎቱኒ ፣

አሁንም ፣ እንደ ተናገርሁት ከዓዌ ዘርዕ አፍአ እማኅፀን ሁኗልና እሱ ባወቀው በእግዚአብሔር ፊት የሠራው ሥራ ክፉ ሆነ ፣ አንድም ውእቱኒ ቅድመ እግዚአብሔር እስመ ከመዝ ገብረ ኮነ እኩየ፣ እሱ ባወቀው በእግዚአብሔር ፊት አሁን እንደ ተናገርኩት ከዓዌ ዘርዕ አፍአ እማኅፀን ሁኗልና ይህ የሠራው ሥራ ክፉ ነገር ሆነ ፤ በዚህም ሥራው እግዚአብሔር እሱን ቀሠፈው፤ ቀተሎ ማንሻ ነው፤ አንድም አሁን እንደተናገርኩት ከዓዌ ዘርዕ አፍአ እማኅፀን ሁኗልና እሱንም እንደ ወንድሙ እንደ ኤር እግዚአብሔር ቀሠፈው ፤

፲፩፡ ወይቤላ ይሁዳ ለትእማር መርዓቱ፣ ንበሪ መበለተኪ ውስተ ቤተ አቡኪ እስከ ይልሕቅ ሴሎም ወልድየ፣ እስመ ይቤ የጊ ይመውተኒ ዝኒ ከመ አኃዊሁ ወሖረት ትእማር ወነበረት ቤተ አቡሃ ፣

ይሁዳም ምራቱ ትእማርን ፤ አንድም መርዓቶሙ ይላል ፣ መርዓቶሙ፤ የአባትና የልጆች ነው፤ የአባትና የልጆች ምራታቸው ትእማርን፤ ይህም እንደ ወንድሞቹ እንደ ኤርና እንደ አውናን ይሞትብኝ ይሆን ? ብሎ ፤ አንድም እንደ ወንድሞቹ እንደ ኤርና እንደ አውናን ይህም ይሞትብኛል ብሏልና አድጎ ሳለ እንዳላደገ፣ ደርሶ

www.ethiopianorthodox.org

ሳለ፤ እንዳልደረሰ አድርጎ ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ሒደሽ በአባትሽ ቤት ጋለሞታ ሁነሽ ተቀመጭ አላት፤ ይኸንም ባላት ጊዜ ትእማር ሒዳ በአባቷ ቤት ጋለሞታ ሁና ኖረች ፤

፲፪፡ ወሶበ ተፈጸመ መዋዕሊሃ ሞተት ሴዋ ብእሲተ ይሁዳ፤ ወነጊፎ ላሃ፤ ይሁዳ ዐርገ ኀበ ይቀርፅ አባግዒሁ ውእቱ ወኤራስ ኖላዊሁ አዶላማዊ ውስተ ቴምናታ ፤

ከእግዚአብሔር ዘንድ በተፈጥሮ የተሰጣት ዘመኗም በተፈጸመ ጊዜ የይሁዳ ሚስት ሴዋ በዚያ ወራት ሞተች፤ ይሁዳም መዋዕለ ላሁን ጨርሶ፤ አንድም መዋዕለ ላሁን ከጨረሰ በኋላ፤ የኤዶላማው ሰው በግ መልከኛው ኤራስና እሱ በጎቹን ወደሚያሸልትበት ወደ ቴምናታ ዐርጎ ያለበት ነው፤ ወጡ ፤ አንድም መዋዕለ ላሁን ጨርሶ (መዋዕለ ላሁን ከጨረሰ በኋላ) ከኤዶላማው ሰው ከበግ መልከኛው ከኤራስ ጋራ ሁኖ ፤ ዐርገ ኀበ ይቀርፅ አባግዒሁ ውስተ ቴምናታ ይላል ፤ በጎቹን ወደሚያሸልትበት ወደ ቴምና ወጣ ፤ አንድም ወነጊፎ ላሃ ፤ ይሁዳ ኀበ ይቀርፅ አባግዒሁ ውስተ ቴምናታ ዐርገ ውእቱ ወኤራስ ኖላዊሁ አዶላማዊ ይላል ፤ ይሁዳ መዋዕለ ላሁን ከጨረሰ በኋላ በጎቹን ወደሚያሸልትበት ወደ ቴምናታ ከኤዶላማው ሰው ከበግ መልከኛው ከኤራስ ጋራ ወደ ቴምና ወጣ ፤

፲፫፡ ወአይድዕዋ ለትዕማር መርዓቱ ወይቤልዋ ናሁ ሐሙኪ የዐርግ ውስተ ቴምና (ቴምናታ) ይቅርፅ አባግዒሁ፤

ሰዎች አይተው ሰምተው ለምራቱ ለትእማር ነገሯት፤ ምራቱ አላት፤ ቀድሞ የልጆቹ ሚስት ናትና ፤ አንድም ፤ እንዳለም ይሆናል፤ ምንም ቀድሞ የልጆቹ ሚስት ብትሆን ኋላ እሱ ደርሶባታልና ፤ አንድም ፤ መርዓቶሙ ይላል፤ አባትና ልጆች ደርሰውባታልና፤ አንድም መርዓቶሙ የሁሉም ምራት ናትና እነሆ አማትሽ ይሁዳ በጎቹን ሊያሸልት ወደ ቴምናታ ወጣ ብለው ነገሯት ፤

፲፬፡ ወኅደገት አልባሲሃ ዘበመበለታ ወለብሰት ሞጣሕታ ወተከድነት ወነበረት ውስተ አንቀጸ ዘፍኖተ ቴምና እስመ ርእየት ከመ ልሕቀ ሴሎም ወውእቱሰ ኢፈቀደ የሀባ ኪያሃ ትኩኖ ብእሲተ ፤

አላደገም ያላት ልጁ ሴሎም እንደ አደገ፤ አልደረሰም ያላት ልጁ ሴሎም እንደ ደረሰ አይታ ለችና ውእቱሂ ሲል ነው ፤ እሱም እሷን ሚስት እንድትሆነው ለሴሎም ሊሰጠው እንዳል ወደደ አውቃለችና ፤ አንድም



ኪያሁ ይኩና ብእሲሃ ይላል ፤ እሱን ለእሷ ባል ሊሆናት፤ የሀባ ሊሰጣት እንዳልወደደ አውቃለችና፤ የድህነት ልብሷን አውልቃ (ትታ)፤ ልብሰ ዘማ ለብሳ፤ ስርሜዶዋን ተጐናጽፋ ተከናንባ ተቀብታ አጊጣ ፤ እሱ እንዳታለለኝ ላታልለው ፤ እሱ እንዳሞኘኝ ላሞኘው ብላ ሒዳ በቴምናታ አጠገብ ባለ ፤ በተመሳቀለ ጎዳና ድንኳን አስተክላ ተቀመጠች ፤

፲፭፡ ወሶበ ርእያ ይሁዳ አምሰላ ዘማ እስመ ተገልበበት ገጻ ወኢያእመራ፤

ይሁዳም አጊጣ ተሸልማ ስርሜዶዋን ተጐናጽፋ ባየት ጊዜ (በስርሜዶዋ ተጐናጽፋለችና) እሱም ምራቱ ትእማር እንደ ሆነች አላወቃትምና አሁን እንደ ተናገርኩት አጊጣ ተሸልማ ባየት ጊዜ ዘማን አስመሰላት አለ፤ ዘማ ናት አለ ፤

፲፮፡ ወተግኅሠ ኀቤሃ እምውስተ ፍኖት ወይቤላ አብእኒ ኀቤኪ፤ ወትቤሎ ምንተ ትሁበኒ እመ ቦእከ ኀቤየ፤

ያን ጊዜ ይሁዳ ከጐዳና ወጥቶ እሷ ወዳለችበት ሔዶ በጄ በዩኝ ወደ አንቺ ልግባ አላት፤ እሷም በጄ ብዬህ ወደኔ ብትገባ የዘማነቴን ዋጋ ምን ትሰጠኛለህ ? አለችው ፤

፲፯፡ ወይቤላ እፌኑ ለኪ መሐስዐ ጠሊ እምአባግዕየ ፤

እሱም ነገ ይኸን ጊዜ ከበጎቼ ለይቼ አንድ የበግ (የፍየል) ጠቦት እልክልሻለሁ አላት ፤

ወትቤሎ ሀበኒ አኀዘ እስከ ትፌኑ ሊተ ፤

እሷም እንኪያስ ነገ አንድ የበግ (የፍየል) ጠቦት እስክትልክልኝ ድረስ ዛሬ መያዣ ስጠኝ አለችው ፤ አንድም ነገ አንድ የበግ (የፍየል) ጠቦት እስክትልክልኝ ድረስ ዛሬ እንኪያስ መያዣ ስጠኝ አለችው ፤

፲፰፡ ወይቤላ ምንተ እሁበኪ አኀዘ፤

የመያዣ ወገን ስልቱ ብዙ ነውና ፤ ከመያዣ ወገን ምን መያዣ ልስጥሽ ? አላት ፤

ወትቤሎ ሕልቀተከ ወቆብዓከ ወበትረከ ዘውስተ እዴከ ወወሀባ ወቦአ ኀቤሃ ወፀንሰት ፤

ቀለበትህን፤ ኮፌትህን፤ በእጅህ የተያዘ በትርህን፤ ስጠኝ አለችው ይኸንንስ እንቼ ብሎ መያዣ ሰጥቶ ወደ እሷ ገብቶ ደረሰባት ፀነሰች ፤

፲፱፡ ወተንሥአት ወሖረት ወአንበረት ውእተ አልባሲሃ ወለብሰት አልባሰ መበለታ ፤

እሷም ከዚያ በኋላ፤ ከዚያ ቦታ ተነሥታ ሒዳ፤ በዘማነት የለበሰችው ልብሷን አውልቃ አኑራ፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም የዘማነት ልብሷን አውልቃ አኑራ የድህነት ልብሷን ለበሰች ፡

፳፡ ወፈነወ ላቲ ይሁዳ ውእተ መሐስዐ ጠሊ ምስለ ኖላዊሁ አዶላማዊ ከመ ይንሣእ አኀሠ እምኀበ ይእቲ ብእሲት ወኢረከባ ፤

የበግ (የፍየል) ጠቦቱን ሰጥቶ ከትዕማር መያዣውን ተቀብሎ ሊመለስ ለኤዶላማው ሰው ለበግ መልከኛው፤ ይሁዳ የበግ (የፍየል) ጠቦቱን ለትእማር ሰደደላት ፤ የበግ መልከኛው የኤዶላማው ሰውም፤ በዘማነት ቦታዋ አላገኛትም፤ ይህስ አይደለም ብሎ በምትኖርበት አገር ፈልጎ አላገኛትም ፡

፳፩፡ ወተስእለ ሰብአ ውእቱ ብሔር፤ ወይቤ አይቴ ይእቲ ዘማ እንተ ነበረት ውስተ ፍኖት፤ ወይቤልዎ ኢሀለወት ዝየሰ ዘማ ፤

የኢዶላማው ሰው የበግ መልከኛው ኤራስም ሒዶ ትላንት በተመሳቀለ ጐዳና ድንኳን ተክላ የነበረች ዘማ የት ናት ? ብሎ ያገሮቹን ሰዎች ጠየቀ፤ እነሱም በዚህስ ቦታ ዘማ የለችብንም አሉት፤ ከዚያ ቀድሞ አያውቋትም ነበርና ፡

፳፪፡ ወገብአ ኀበ ይሁዳ ወይቤሎ ኢረከብክዋ ወሰብአ ውእቱኒ ብሔር ይቤሉኒ ኢሀለወት ዝየሰ ዘማ ፤

የኤዶላማው ሰው የበግ መልከኛው ኤራስም ወደ ጌታው ወደ ይሁዳ ተመልሶ ሒዶ እኔስ ያቺን ሴት በዘማነት ቦታዋ ተቀምጣ፡ አንድም ባለችበት አገርም ብፈልጋ ብፈልጋ አላገኘኋትም፤ ያገሮቹንም ሰዎች ብጠይቃቸው እኛስ በዚህ ቦታ ዘማ የለችብንም አሉኝ ብሎ ነገረው ፡

፳፫፡ ወይቤ ይሁዳ ኅድግዋ ላቲ ከመ ኢይስሐቁ ላዕሌነ ፈነውኩ አንስ መሐስዐ ወሰበ ኢረከብካሃ ኮነ ሊተ ፤

ይሁዳም ጠቦት ወደ መያዣ አድርጎ የሰጠውን ገንዘብ፤ እንደ ተወው ቀረ ፤ ብለው ሰዎች እንዳይዘብቱብን ተዋት አለ ንጉሣዊ አነጋገር ፡ አንድም ኅድጋ ላቲ ከመ ኢይስሐቁ ላዕሌየ ይላል ፤ የበግ (የፍየል) ጠቦት ወደ መያዣ አድርጎ የሰጠውን ቀለበቱን፤ ኩፌቱን፤ በትሩን እንደ ሰጣት ቀረ፤ ብለው ሰዎች እንዳ ይዘብቱብኝ፤ ኅድጋ ላቲ፤ ካጣሃትማ ተዋት፡ እኔስ የተናገርኩትን ቃል አላስቀርም ብዬ የበጉን ጠቦት ላክሁላት፤ ብትፈለግ ብትፈለግ ካለችበት አገር ካላገኘሃትስ ይህ ጠቦት ለኔ ገንዘብ ነው ለኔ ይሆናል አለው፡



፳፬፡ ወእምዝ እምድኅረ ፫ቱ አውራኅ ዜነውዎ ለይሁዳ ወይቤልዎ ዘመወት ትዕማር መርዓትከ ወናሁ ፀንሰት በዝሙት ወይቤ ይሁዳ ያውፅእዋ ወያውዕይዋ በእሳት ፤

እምዝና እምድኅረ አንድ ወገን ነው ፤ ከሦስት ወር ቀጥሎ ፡ አንድም ከሦስት ወር በኋላ ፤ ትእማር ምራትህ ከሌላ ወንድ ሰስና በዝሙት ፀነሰች ብለው ሰዎች ሒደው ነገሩት፤ በዚያ ወራት ሠልጥኖባቸው ነበርና ይሁዳም ከከተማ በአፍአ አውጥታችሁ በድንጊያ ወግራችሁ፤ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት ብሎ አዘዘ ፡

፳፭፡ ወእንዘ ይወስድዋ ለአከት ኀበ ሐሙሃ ወትቤሎ ዝንቱአ ዘመኑአ ወዘአይኑአ ብእሲአ ዝንቱአ ጽንስአ ወትቤሎ ርኢአ ዘንተአ ቆብዓአ ወዘንተ በትረአ ፤

ወዘንተ ኀልቀተአ ያለበት ነው፤ መካነ ምቅታል አለ፤ ከከተማ በአፍአ አውጥተው ሊደበድቡ ይዘዋት (ሲወስዱዋት) ሲሔዱ ወደ አማቷ ወደ ይሁዳ ላከች፤ መያዣ አድርገህ የሰጠኸኝ ይህ ኩፌት፤ ይህ በትር፤ ይህ ቀለበት የማነው ? የማን ይመስልሃል ? ይህስ ዕንስ የማን ነው ? የማን ሰው ይመስልሃል ? ብላ ላከችበት፤ ሆዱ እያወቀ ይህንንስ አላምንም ቢል፤ እንኪያስ መያዣ አድርገህ የሰጠኸኝ ይኸንን ቀለበት ፤ በትር ፤ ኩፌት እይ ተመልከት አለችው ፡ አንድም ወትቤሎአ፤ ዝንቱአ ዘመኑአ፤ ይህ ዕንስ፤ ይህ ኩፌት፤ ይህ በትር ፤ ይህ ቀለበት ፤ የማን ነው ? የማን ይመስልሃል ? ብላ ላከችበት ይህ የወል ነው ፤ ይህ ዕንስ ብሎ አንድ አርእስት ፤ ይህ ኩፌት ፤ ይህ ቀለበት፤ ይህ በትር ብሎ ሁለት አርእስት ተናገረ ፤ ለሁለቱም ወደፊት ያመጣለታል ፤ ትቤሎና ትቤሎ አንድ ወገን ነው፤ ይህ ዕንስ የማን ይመስልሃል? አለችው ፤ ዕንስ ላለው ነው ፤ ይህ ኩፌት፤ ይህ በትር፤ ይህ ቀለበት የማነው ? የማን ይመስልሃል? አለችው፤ ዘንተ ቆብዓ ወዘንተ በትረ ፤ ወዘንተ ሕልቀተ ላለው ይስማል ፡

፳፮፡ ወርእየ ይሁዳ ወይቤ ጸድቀት ትእማር እምኔየ እስመ ኢወሁብክዋ ሴሎምሃ ወልድየ ወኃደገ ቀቲሎታ እንከ ፤

እምኔየ ያለው ኪያየ ሲል ነው፤ አማቷ ይሁዳም የሰደደችለትን ምልክት ኩፌቱን ፤ ቀለበቱን ፤ በትሩን አይቶ ፤ ልጄ ሴሎምን አድጎ ሳለ እንዳላደገ፤ ደርሶ ሳለ እንዳልደረሰ አድርጌ አልሰጠኋትምና ዛሬ ትእማር እኔን ረታችኝ አለ ፡ አንድም ይሁዳ የሰደደችለትን ምልክት አይቶ

www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ ትዕማር እኔን ረታችኝ ይህንንም ያደረገች ልጄ ሴሎ ምን አድጎ ሳለ እንዳላደገ፣ ደርሶ ሳለ እንዳልደረሰ አድርጌ አልሰጠኋትምና ስለዚህ ነው አለ፤ አንድም እምኔየ እንዳለም ይሆናል፣ ትዕማር ከእኔ ይልቅ በለጠች ተሻለች፣ ይህን ያደረገች፣ እመ ኢወሀብክዋ ይላል ልጄ ሴሎምን አድጎ ሳለ እንዳላደገ፣ ደርሶ ሳለ እንዳልደረሰ አድርጌ ባልሰጣት ነው፤ አንድም ተስፋ ካላቸው ከአብርሃም ከይስሐቅ ከያዕቆብ ተጋብቼ ልጅ ሳልወልድ ቀረሁ ብላ ነው አለ ፣ ከዚህ በኋላ ተዋት አትግደሉዋት አለ ፤ አንድም ይህን ከተናገረ በኋላ ወኃደግዋ እንከ ቀቲሎታ ይላል፣ ይህንን ሰምተው ሊገድሉዋት የሔዱቱ ሰዎች ከመግደል ተዋት ፤

፳፯፡ ወኢደገመ ይሁዳ ቀሪቦታ ፣ ወሶበ ቀርበ ወሊዶታ ናሁ ሀለዉ መንታ በውስተ ከርሣ ፣

ከዚያ በኋላ ፣ ይሁዳ አምጧት ብሎ አልደረሰባትም የምትወልድበትም ጊዜው በደረሰ ጊዜ በማኅፀኗ ሁለት መንታ ልጆች ነበሩ ፤

፳፰፡ ወእምዝ እንዘ ትወልድ፣ አውፅአ እዴሁ አሐዱ፣ ወነሥአት መወልዲት ፣ ፈትለ ቀይሐ ወአሠረት ውስተ እዴሁ፣ ወትቤ ዝንቱ ይቀድም ወፂአ ፣

ከዚህ በኋላ (ከዚህ ቀጥሎ) ምጥ ተይዛ መንታ ልጅ ስትወልድ፣ ከመንታ ልጆች አንዱ አስቀድሞ እጁን አወጣ፣ ያን ጊዜ አዋላጆቱ ቀይ ሐር አምጥታ ባውራ ጣቱ አሠረችለት፣ ይህንንም ማድረጓ፣ ይህ ከወንድሙ አስቀድሞ ይወለዳል ብላ ነው፤

፳፱፡ ወሶበ አሰሰለት እዴሃ ወናሁ ወፅአ እኁሁ ወትቤ ዕፁብ ውእቱ ወሰመዮ ስሞ ፋሬስ ፣

መወልዲቱ ከእሱ እጁን ካነሣች በኋላ፣ ባነሣችለት ጊዜ ወንድሙ ተወለደ፣ እሷም ይህ ነገር ድንቅ ነው ስትል ስሙን ፋሬስ አለችው፣ ፋሬስ ማለት ጣሽ ጠምሳሽ ዕፁብ፣ ያየነው ቀርቶ ያላየነው ማለት ነው ፤

፴፡ ወእምድኅሬሁ ወፅአ እኁሁኒ ዘተአሥረ እዴሁ ፣ ወሰመዮ ስሞ ዛራ ፣

ከእሱ በኋላ (ከእሱ ቀጥሎ) አውራ ጣቱን በቀይ ሐር የታሠረ ወንድሙ ተወለደ ስሙንም ዛራ አለችው፣ ፈትል ቀይሕ ወለት ድክምት ቅድመ ዘርኢ ናሁ ማለት ነው፣ ይኸም ምሳሌ ነው ፤ ይሁዳ የእግዚአብሔር አብ፣ ኤራስ አዳላማዊ የቅዱስ ገብርኤል፣ በግዕ የእግዚአብሔር ወልድ፣ ሕልቀት የሃይማኖት፣



ኩፌት፣ የአክሊለ ሦክ፣ በትር፣ የመስቀል፣ ትእማር የቤተ አይሁድ፣ ትዕማር መያገር ይዛ ቀረች እንጂ ዋጋዋን እንዳላገኘች ፣ ቤተ አይሁድም ትንቢቱን ተስፋውን ሰምተው ቀሩ እንጂ በክርስቶስ አላመኑምና ፤ አንድም የምሳሌ ምሳሌ ፣ ትዕማር የም ኵራብ ፣ ምኵራብ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት ፤ ትዕማር ልጆቿን ከአባታቸው ከይሁዳ አገኘች እንጂ ከልጆች እንዳላገኘች ቤተ ክርስቲያንም ፣ ምእመናንን ከእግዚአ ነቢያት፣ ከእግዚአ ካህናት ከክርስቶስ አገኘች እንጂ ፤ ከነቢያት ፣ ከካህናት አላገኘችምና፤ አንድም፤ ትዕማር የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ፣ ትዕማር ከአባትም ከልጆችም ዘር ስትቀበል እንዳልተጸየፈች ፣ ቤተ ክርስቲያንም ፣ ከሕዝቡ ከአሕዛቡ፣ ከሐቃል፣ ከሀገሪት፣ ከግዙር፣ ከቈላፍ ያመኑትን ሁሉ ትቀበላለች አትጸየፍምና፣ ለዘ መጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወፅአ አፍአ እንዳለ ፤ ፋሬስ የኦሪት፣ ዛራ የወንጌል ምሳሌ፣ ዛራ አስቀድሞ እጁን እንዳወጣ፣ ወንጌልም፣ በመልከጼዴቅ ጊዜ ታይታ ቀርታለችና፣ ፋሬስ እሱን ወደኋላ ስቦ እንደተወለደ በመካከል ኦሪት ተሠርታለች፣ ዛራ በኋላ እንደ ተወለደ ከኦሪት በኋላ ወንጌል ተሠርታለችና፣ እደ ዛራ የቀሳውስት ፣ ፈትለ ለይ የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው ፤ ይኸንስ ለምን ይሻዋል ቢሉ፣ ትዕማር በሃይማኖት እንደ ከበረች፣ አሕዛብም በሃይማኖት እንዲከብሩ ለማጠየቅ፣ በእስራኤል ዘለፋ፣ ለአሕዛብ ተስፋ ለመሆን፤ በልደተ ሥጋ ይመካሉና፣ ለእኛስ ክርስቶስ ከትዕማር ተወልዶልን የለምን ለማለት፣ በዐቂበ ሕግ ይመካሉና እናንተስ የሕግ አፍራሽ ልጆች አይደላችሁምን ? ለማለት፤ አንድም፣ ክርስቶስ፣ በዳዊት ከበረ ይላሉና ፤ ዳዊት በክርስቶስ ከበረ እንጂ እሱማ የትዕማር ልጅ አይደለም ? ለማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፴ወ፱

### ገባኤ

፩፡ ወዮሴፍሰ ወረደ ብሔረ ግብጽ ወተሣየጦ ጲጥፋራ ሐዕዉ ለፈርዖን ሊቀ መበስላኒሁ ፣ ውእቱ ብእሲ ግብፃዊ እምእደ ይስማኤላውያን እለ አውረድዎ ህየ ፣

ዮሴፍ ግን፣ በዚያ ወራት ተሸጦ ወደ ግብፅ አገር ወረደ፣ ሔጥዎ ለዮሴፍ ብሔረ ግብፅ ብሎ ነበርና ወደ ጥንተ ነገሩ ተመለሰ፣ አዛኘ ቢትወደዱ ራቅ ማሠሪያው የፈርዖን ባለሟሉ ጲጥፋራ

www.ethiopianorthodox.org

ከእስማኤላውያን እጅ ገዛው፣ ይኸውም የገዛው ጲጥፋራ ከወንድሞቹ ገዝተው ወደ ግብፅ አገር ካወረዱት ከይስማኤላውያን እጅ ነው ፤

፪፡ ወሀሎ እግዚአብሔር ምስለ ዮሴፍ ወኮነ ብእሴ ብፁዐ ወተሠይመ ላዕለ ቤተ እግዚኡ ፣

በዮሴፍም፣ እግዚአብሔር በረድኤት አድሮበት ይኖር ነበር፣ ዮሴፍም፣ በሰው በእግዚአብሔር ዘንድ የተመሰገነ ደግ ሰው ሆነ፣ በጌታውም ቤት ፣ ባለ ገንዘቡ ሁሉ ተሾመ፣ አለ ጌታው ብል ህነቱን አይቶ ባለ በገንዘቡ ሁሉ ሾሞታል ፤

፫፡፬፡ ወሶበ ርእየ እግዚኡ ከመ ሀሎ እግዚአብሔር ምስሌሁ ፣ ወኵሎ ዘገብረ ይሜርሖ እግዚአብሔር በእዴሁ ፣ ሤሞ ላዕለ ኵሉ ቤቱ ወአወፈዮ ኵሎ ዘቦ ለዮሴፍ ወረከበ ዮሴፍ ሞገሰ በቅድመ እግዚኡ እስመ ያሠምሮ ፣

ጌታውም፣ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር በረድኤት አድሮ እንዳለ በእጁ፣ በቃሉ፣ የሠራውንም ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያከናውንለት ባየ ጊዜ ፣ ከቤተሰቦቹ በላይ አድርጎ ሾመው ፣ ከሽበት እስከ ኩተት ያጠራቀመውንም ገንዘብ ሁሉ ፣ ንግ አንተ ባወቅህ አስተዳድርልኝ ብሎ ለዮሴፍ ሰጠው፣ ዮሴፍም ጌታውን በእጁ ፣ በቃሉ ፣ በሠራው ሥራ ሁሉ ደስ አሰኝቶታልና በጌታው ዘንድ ክብር ባለሟልነትን አገኘ ፤

፭፡ ወእምዝ እምድኅረ ተሠይመ ላዕለ ኵሉ ቤቱ ፣ ባረኮ እግዚአብሔር ለውእቱ ግብጻዊ፣ በእንተ ዮሴፍ ወኮነ በረከተ እግዚአብሔር ላዕሌሁ፣

እምዝና እምድኅረ አንድ ወገን፣ ዮሴፍ ባለገንዘቡ በቤተሰቡ ሁሉ ከተሾመ በኋላ በዮሴፍ ምክንያት ያን የግብጽ ሰው እግዚአብሔር አከበረው፣ የእግዚአብሔርም በረከት በዚያ በግብጹ ሰው በጲጥፋራ ላይ አደረበት፤

፮፡ ወኵሎ ንዋዮ ዘሐቅል ወዘሀገር አግብአ ኵሎ ዘቦ ውስተ እዴሁ ለዮሴፍ ፣

«ዘሐቅል» ከከተማ በአፍአ ያለውን «ወዘሀገር» በከተማ ውስጥ ያለውን ገንዘቡን ፤ አንድም ዘሐቅል፣ እንደ ቀሐ፣ እንደ አንገረብ ያለውን ፤ ወዘሀገር፣ እንደ ጐንደር ውስጥ ያለውን ፤ አንድም ዘሐቅል እንደ አሪንጎ፣ እንደይባባ ያለውን ፣ ወዘሀገር እንደ ቀሐ ፣ እንደ አንገረብ ፣ እንደ ጎንደር ያለውን በነገሥታቱ ከተማ ሁሉ የመኳንንቱም የወይዛዝሩም አላቸውና፣ ነሣሣለትና ያለውን ሁሉ ገንዘቡን አንተ ባወቅህ አስተዳድርልኝ ብሎ ለዮሴፍ ሰጠው ፤



ወአልቦ ዘየአምር ውእቱ ዘሀሎ ንዋዮ ዘእንበለ እክል ዘይበልዕ ፣

ከሚበላው እህል በቀር ያለ ገንዘቡን ሁሉ ይኖር አይኖር ይህ ሰው (ያሰው) አያውቅም ነበር፤ አንድም ስንኳን ሌላ ገንዘቡን የሚበላውን እህል ሳይቀር አያውቅም ነበር አለ፣ ሲሰጡት ይበላ ነበር እንጂ አለቀ ደቀቀ አይልም ነበር ፤

ወሠናይ ውእቱ ዮሴፍ ወላህዩ ርእየቱ ገጹ ጥቀ ፣

ዮሴፍ መልኩ ያማረ የተወደደ ነበር ፣ ይልቁንም መልክ አቀናን ከደም ግባት፣ ደም ግባት ከመልክ አቀናን የተፈጸመለት ነበር፤ ሰው፣ ደም ግባት ቢኖረው፣ መልክ አቀናን የለውም፤ መልክ አቀናን ቢኖረው፣ ደም ግባት የለውም ፤ እሱ ግን ፣ መልክ አቀናን ከደም ግባት፣ ደም ግባት ከመልክ አቀናን የተፈጸመለት ውብ ጉልማሳ ነበር ፤

፯፡ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር ወደየት አዕይንቲሃ ላዕለ ዮሴፍ ብእሲተ እግዚኡ፣ ወትቤሎ ስክብ ምስሌየ፣

ኮነ ያለውን ወደፊት ያመጣል፣ ከዚህ በኋላ (ከዚህ ቀጥሎ) መልክ አቀናን ከደም ግባት የተፈጸመለት ነበርና የጌታው ሚስት እመቤቱ፣ በዮሴፍ ላይ ዓይኗን ጣለችበት ሲገባ ደረቱን፣ ሲወጣ ባቱን እያየች ና ድረስብኝ አለችው ፤

፰፡ ወአበየ ወይቤላ እግዚእየ አግብአ ሊተ ኵሎ ዘቦ ውስተ እዴየ ፣

ጌታዬ ባለ ገንዘቡ ሁሉ አሠልጥኖኛል፤ አንድም ጌታዬ በቤቱ ያለውን ሁሉ በእጄ ጭብጥ ፣ በእግሬ እርግጥ አድርጎ አስገዝቶኛል፣ በዚህ ሁሉ ሲያሰለጥነኝ ፣ (ባለ ገንዘቡ ሁሉ ሲያሰለጥነኝ) ባንቺ ግን አላሠለጠነኝም፣ ይኸንም ማድረግ ጠልቶኝ ነፍጎኝ አይደለም፣ ሚስቱ ብትሆኚበት በሚገባው ነው ፣ ተዪ አይሆንም ብሎ እምቢ አላት ፤

፱፡ ወአልቦ ዘየአምር ዘውስተ ቤቱ ወኢምንተኒ ወአልቦ ዘሀሎ ውስተ ቤት ዘኢኮነ ብውሑ ሊተ ዘእንበሌኪ እስመ ብእሲቱ አንቲ ወእፎ እንከ እገብሮ ለዝንቱ ነገር እኩይ ፣

ይኸውም ሊታወቅ፣ በቤቱ ካለ ገንዘቡ ሁሉ ያለ እኔ እሱ ፣ ምንም ምን የሚያውቀው የለም፤ ሚስቱ ነሽና ሚስቱ ስለሆንሽ በት ያለ አንቺ በቀር በዚህ ቤት ባለ ገንዘቡ ባለ ቤተሰቡ እኔ ያልሠለጠንህበት ገንዘብ፣ እኔ ያልሠለጠንህበት ቤተሰብ የለም፤ እንዲህ አድርጎ በሁሉ ሲያሠለጥነኝ፣ ይህን ክፉ ነገር

www.ethiopianorthodox.org

እንደምን ደፍሬ አደርገዋለሁ ይላታል ፤

፲፡ ወትትናገሮ ከመዝ እንተ ጸብሐት ለዮሴፍ ወአበየ ሰኪበ ምስሌሃ ወተራክቦታ ፤

አሁን እንደ ተናገርኩት ነዓ ስክብ ምስሌየ እያለች ጧት ማታ ትነጋገረው ነበር (ነበረች)፤ አንድም፣ ትትናገሮ ክመ ይላል፣ ጧት ማታ ሳታፍር ሳትፈር ነዓ ስክብ ምስሌየ እያለች ፊጽማ ትነጋገረው ነበር፣ እሱም አል ደርስብሽም ተዪ አይሆንም ብሎ እምቢ አላት ፤ ስንኳንስ ልደር ስብሽ አንቺ ወዳለሽበት አልወ ጣም አልገባም አላት ፤

፲፩፡ ወኮነ በአሐቲ ዕለት ቦአ ዮሴፍ ውስተ ቤት ይግበር ግብሮ ወአልቦ ዘሀሎ ስብእ ውስተ ውሣጤ ቤት ወአኀዘት ልብሶ ፤

ኮነ ያለውን ወደፊት ያመጣ ዋል፣ ከዕለታት በአንድ ዕለት ዮሴፍ ፤ ተክል ለመኰብኘት ወደ ተክል ቦታ ገብቶ ሳለ ፤ አንድም ብሌዩን ከሐዲስ ፤ ሐዲሱን ከብሌዩ ለማናፈስ ወደ ቤተ መዛግብት ገብቶ ሳለ ፤ በዚያ በቤተ መዛግብቱ ያን ጊዜ አንድ ሰው ስኳን አልነበረም፣ ሰው አለመኖሩን አይታ ሳታ ፍር ሳትፈራ፣ አንተ ባሪያ ዛሬስ አለቀቅሁህም ብላ ተራምዳ

ልብሱን ያዘችው፤ ኮነ ያለውን አመጣ ፤

፲፪፡ ወትቤሎ ነዓ ስክብ ምስሌየ ወኃደገ አልባሲሁ በእዴሃ ወጐየ ወወፅአ ፤

አንተ ባሪያ ዛሬስ አልለቀቅሁ ህም ና ድረስብኝ አለችው ፤ እርሱም፤ ቊርጥ ነገሯን አይቶ፤ አነዘት ልብሶ ብሎ ነበርና የለ በሰውን ልብስ በእጇ ጥሎላት ሸሽቶ ወጥቶ ሔደ ፤ አንድም ወጥቶ ሸሸ ፤

፲፫፡፲፬፡ ወሶበ ርእየት ከመ ወፅአ ውነደገ አልባሲሁ በእዴሃ ጸውዐቶሙ ለእለ ሀለዉ ውስተ ቤት ካልእ ወትቤሎሙ ምንተ አምጻእክሙ ላዕሌየ፣ ርእዩ ዘገብረ ላዕሌየ ዝንቱ ገብር ዕብራዊ ከመ ይሣለቅ ላዕሌየ ቦአ ኀቤየ ወይቤለኒ ስክቢ ምስሌየ ወጸራኅኩ በዐቢይ ቃል ፤

እሷም ፤ ዮሴፍ የያዘችበትን ልብሱን በእጇ ጥሎላት ወጥቶ እንደ ሔደ ባየች ጊዜ በሌላ ቤት ያሉትን ሰዎች በጩኸት ጠራቻቸው፤ አንድም እሷ ቢነ ድዳት ቢቆጫት ልብሷን ከወደ ኋላዋ ቀድዳ፣ አንድም ከወደ ፊቷ ልብሷን ቀድዳ ፤ አመድ ትቢያ፣ በራሷ ነስንሳ፣ እጇን በራስዋ ላይ አድርጋ ጮኸች፣ በጎረቤት ያሉ ሰዎች መጡ ፤ አንድም ፀውዐቶሙ ውስተ ቤት ለእለ ሀለዉ ካልዓን ይላል፣ በእ



ዳሪ ያሉትን ሰዎች፣ እሷ ወዳለ ችበት ቤት ጠራቻቸው ፤ አን ድም ፀውዐቶሙ ለእለ ሀለዉ ውስተ ቤት ካልዕ ካልዓን ይላል፣ በሌላ ቤት ያሉትን ሌሎችን ሰዎች በጩኸት ጠራቻቸው ፤ ዛሬ በእኔ ላይ ምን ክፉ ነገር አመጣችሁብኝ ፤ ይህ ዕብራዊ ባሪያ በእኔ ያደረገውን እዩ ተመልከቱ ዘገብረ ያለውን ያምጣው፣ በጌታዬ ሚስት በእ መቤቴ ደረስኩባት ብሎ ሊዘብ ትብኝ እኔ ወዳለሁበት ደፍሮ ገባ፣ ገብቶም ነዪ ልድረስብሽ አለኝ፤ እኔም ደካማ ሴት ነኝና አልችልም ይደፍረኛል ስል ወደ እናንተ ጮህኩ ፤

፲፭፡ ወሶበ ሰምዐ ከመ አልዐልኩ ቃልየ ወጸራኅኩ ፤ ኀደገ አልባሲሁ ወጐየ አፍአ ፤

አልዐልኩና ጸራኅኩ አንድ ወገን፣ አሰምቼ ወደ እናንተ እንደ ጮኹ ባየ በሰማ ጊዜ ልብሱን ጥሎልኝ ሸሽቶ ወጣ፤ አንድም ወጥቶ ሸሸ ፤ ባሪያ ሲገዙ ራሰ ቆርዳዳ ፤ ፊተ ጨምዳዳ ፤ አፍ ንጫ ጎራዳ ፤ ምላሰ ድዳ ፤ ይገ ዟል እንጂ ፤ ከእሱ የበለጠ ዓይንና ጥርሱ የሚያጣቅስ ባሪያ ገዝቶ በጌታዬ ሚስት በእመ ቤቴ ዘበትኩባት ሊለኝ እንዲህ አደረገኝ፣ እዩ ተመልከቱ አለቻ ቸው ፤ የዮሴፍን ደግነት ሁሉ

ያውቀዋልና ፤ ዮሴፍን ያህል ሰው ይህን ነገር ደፍሮ ያደርገው አይመስለንም ፤ ነገር ግን ፤ ሎሌና ጌታ ተማግቶ ፤ ቅልና ደንጊያ ተማትቶ (ተጋጭቶ) አይ ሆንምና ታሥሮ ይቆይ ብለው አሥረው አቆይተውታል፤ ይኸ ውም ምሳሌ ነው ፤ ብእሲተ ጲጥፋራ የኃጢአት ፤ ዮሴፍ የንጽሕና፣ ወረሰየ አምሳለ ለን ጽሕ እንዲል፤ አንድም ብእሲተ ጲጥፋራ የዚህ ዓለም ፤ ዮሴፍ የመናንያን አምሳል ነው፣ ብእ ሲተ ጲጥፋራ እይዝነ እይዝነ ስትለው ዮሴፍ ነጥቋት ጥሏት ወጥቶ እንደ ሔደ ፤ ይህችም ዓለም በክብት ፤ በንብረት ፤ በሹመት፣ በሽልማት፣ በልጅ፣ በቤት፣ በሚስት፣ ሳታባብላቸው መናንያን ጥለዋት የመሔዳ ቸው ምሳሌ ፤

፲፮፡ ወአንበረት እስከ ይመጽእ እግዚኡ ውስተ ቤት ፤

እሷም ሐሰተኛ ነገሯ እውነት እንዲመስልላት የዮሴፍን ልብስ፣ ጌታው ወደ ቤቱ እስኪመጣ ድረስ አኑራ አቆየችው ፤

፲፯፡ ወነገረቶ ዘንተ ነገረ ለምታ፣ ወትቤሎ ገብርከ ዕብራዊ ዘአምጻእከ ቦአ ኀቤየ ይሣለቅ ላዕሌየ ፤

ጌታውም ፤ ከዋለበት በመጣ ጊዜ ፤ ይኸንን ነገር ለባሏ አሳ

www.ethiopianorthodox.org

ክሳ (አጋንና) አስመስላ ነገረ ችው፡ ይህ ገዝተህ ያመጣኸው ዕብራዊ ባሪያህ በጌታዩ ሚስት በእመቤቴ ዘበትኩባት ሊለኝ እኔ ወደ አለሁበት ደፍሮ ገባ፡

ወይቤለኒ እስክብ ምስሌከ ፣

ገብቶም ልድረስብሽ አለኝ ፡

፲፰፡ ወሶበ ሰምዐ ከመ አልዐልኩ ቃልየ ወጸራኅኩ ኃደገ አልባሲሁ ወጕየ አፍአ ፣

አልዐልኩና ጸራኹ አንድ ወገን፣ እኔም ቃሌን አሰምቼ እንደ ጮሁብት ባየ በሰማ ጊዜ ይህች ሴት ልታሲዘኝ ነው ብሎ ልብ ሱን ጥሎልኝ ሸሸ፣ አሁንስ ባሪያ ሲገዙ ራስ (ፀጉረ) ቆርጾዳ፣ ፊት ጨምዳዳ ፣ አፍንጫ ጎራዳ ፣ ምላሰ ድዳ፣ ባሪያ ይገዟል እንጂ፣ ከአንተ የበለጠ፣ ዓይንና ጥርሱ የሚያጣቅስ ባሪያ ገዝተህ እን ዲህ አድርገህ አዘበትኩብኝ አለችው ፡

፲፱፡ ወሶበ ሰምዐ እግዚኡ ነገረ ብእሲቱ ዘትቤሎ ከመዝ ረሰየኒ ገብርከ ዕብራዊ ተምዐ መዓተ ዐቢየ ፣

ሚስቱ ፣ ይህ ዕብራዊ ባሪያህ እንዲህ አደረገኝ ብላ የነገረች ውን ነገር ጌታው በሰማ ጊዜ፣ ያደርጋል አሠልጥኘዋለሁ ብሎ ተቈጣበት ፡ አንድም ወሶበ ሰምዐ እግዚኡ ነገረ ብእሲቱ ዘትቤሎ ብሎ ያካፍላል፣ ሚስቱ የነገረችውን ነገር ጌታው በሰማ ጊዜ ፣ ከመዝኑ ረሰየኒ ገብር ዕብራዊ፣ ይህ ዕብራዊ ባሪያዩ ለካን እንዲህን አድርጎኛል ? አንድም ለካ እንዲህን አድርጎ ኛል ብሎ ፣ ሴት የላከው ጅብ አይፈራም እንዲሉ ያደርጋል፣ በሁሉም አሠልጥኘዋለሁ ብሎ ተቆጣበት፡ ያንጊዜ «ወሐማ እገ ሪሁ በመዋቅሕት» ወአምሠጠት ነፍሱ እምሐዊን ይላል ፡ አም ሠጠት ነፍሱ እምሐዊንን ያስ ቀድማል ፡ አምሠጠት ነፍሱ እምሐዊን ያደርጋል አሠልጥኘ ዋለሁ ብሎ፣ ጦር ቃጥቶበታል፣ ሰይፍ መዝዞበታል፣ ወሐማ እገ ሪሁ በመዋቅሕት ፣ ከፈርዖን እሥረኞች ጋር አሳስሮታል (አሥ ሮታል)፡ አንድም እንዳለ ይሆ ናል፡ ወሐማ እገሪሁ በመዋቅ ሕት፣ ከፈርዖን እሥረኞች ጋር አሳሥሮታል ፡ ወአምሠጠት ነፍሱ እምሐዊን ፣ ሊቀ ዓቀ ብተ ሞቅሕ ብልህነቱን አይቶ ፊትቶ እሥረኞች በአንተ ይውጡ፣ ይግቡ፣ ፀሐይ ይሙቁ፣ ብሎ ሾሞታል ፡

፳፡ ወነሥኦ ለዮሴፍ ወአንበሮ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ኀበ ይነብሩ እለ ሞቅሐሙ ንጉሥ ውስተ ሙዓል ፣

ያን ጊዜ ጲጥፋራ ዮሴፍን ወስዶ፣ ፈርዖን አስቀድሞ አሥሮ፣ ካና



ራቸው እሥረኞች ጋር በግ ዞት ቤት አኖረው ፡

፳፩፡ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ ዮሴፍ፣ ወከዐወ ላዕሌሁ ምሕረቶ ወወሀቦ ሞገሰ በኀበ ሊቀ ዐቀብተ ሞቅሕ፣

እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር በረድኤት ነበርና ቸርነቱን አብ ዝቶ አደረገለት ፣ በእሥር ጠባ ቆች አለቃ ዘንድም ባለሟልነ ትን ሰጠው ፡

፳፪፡ ወአወፈዮ ለዮሴፍ ኵሎ ቤተ ሞቅሕ ፣

ሊቀ ዓቀብተ ሞቅሕም በእሥ ረኞች ቤት የሚደረገውን ሥራ ሁሉ ለዮሴፍ ሰጠው አለ ፣ እሥረኞች በአንተ ፈቃድ በአ ንተ ትእዛዝ ይውጡ ይግቡ ፀሐይ ይሙቁ ብሎ ከእሥራቱ ፈትቶ በእሥረኞች ላይ ሾመው ወሀቦ ሞገሰ ያለውን አመጣ ፡

፳፫፡ ወአልቦ ዘየአምር ኵሎ ዘይት ገበር በቤተ ሞቅሕ ሊቀ ዐቀብተ ሞቅሕ ወኢምንተኒ እስመ ኀደገ ሎቱ ኵሎ ለዮሴፍ እስመ እግዚአ ብሔር ሀሎ ምስሌሁ ወበኵሉ ዘገ ብረ ይሤርሕ እግዚአብሔር በእዴሁ፣

እግዚአብሔር በረድኤት ከእሱ ጋር አድሮበት ስለ ኖረ በእጁም በቃሉም የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር የሚያከና ውንለት ስለሆነ፣ የእሥር ቤት ሹማምት አለቃ ሁሉን ነገር አንተ ባወቅህ አድርግ ብሎ ትቶለታልና በእሥር ቤት ሹማ ምት የተሾመው አለቃው በእ ሥር ቤት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ምንም ምን አያውቅም ነበር ፡ አንድም ለዮሴፍ ሁሉን አንተ አድርግ ብሎ ትቶለታ ልና ፣ ሁሉን አንተ አድርግ ብሎ ስለ ተወለት ፣ በእሥረ ኞች ቤት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ፣ ምንም ምን አያውቅም ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ከዮሴፍ ጋር በረድኤት አድሮበት ይኖር ነበርና (አድሮበት የሚኖር ስለ ሆነ) በእጁ በቃሉ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ያከ ናውንለት ነበር ።

## ምዕራፍ ፵

### ገባኤ

፩፡ ወኮነ እምድኅረ ዝንቱ ነገር አበሱ ክልኤቱ ሕፅዋኒሁ ለንጉሥ ሊቀ ቀዳ ሕያን ፣ ወሊቀ ሐባዝያኑ ለንጉሠ ግብጽ ለእግዚኦሙ ፣

ኮነ ያለውን አበሱ ብሎ ያመጣ ዋል፤ ከዚህ በኋላ (ከዚህ ቀጥሎ) የንጉሥ ሁለቱ ባለሟሎች በደሉ በደላቸው አልታወቀም ለና ለ የተደራረበ ቀለም ነው፣ ለአብ ለዘይኄንን እንዲል ፪ቱ ሕፅዋ ኒሁ ያለውን አመጣ ፡ አንዱ የጠጅ አዛዥ የጠጅ አሳሳፊ ነው፣

www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛው የግብጹ ንጉሥ የእንጀራ አዛዥ (እንጀራ አበዛ) ነው፤ አንድም ፤ ሊቀ ቀዳሕያን ፤ ወሊቀ ሐባዝያን አበሱ ለንጉሥ እግዚአሙ ይላል ፤ የእንጀራ አዛገፍና የጠጅ አዛገፍ እነዚህ ሁለቱ ሁነው የግብጽ ንጉሥ ጌታቸውን በደሉ ፤

፪፤ ወተምዐ ንጉሥ ላዕለ ክልኤሆሙ ሕፅዋኒሁ ፤

ንጉሡም ፤ የበደሉትን በደል ሰምቶ በሁለቱ ባለሟሎቹ ተቆጣባቸው ፤

ወአንበሮሙ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ውስተ መካን ኀበ ሀሎ ዮሴፍ ፤

ንጉሡም ተቆጥቶ አልቀረ አሥሮ አግዞ ዮሴፍ በታሠረበት ቦታ አኖራቸው ፤

፬፤ ወሊቀ ዓቀብተ ሞቅሕ አንበሮሙ ውስተ ሞቅሕ ምስለ ዮሴፍ ወውእቱሰ ይትቀነዮሙ ፤ ወነበሩ ውስተ ቤተ ሞቅሕ አሐተ ዓመተ ፤

የእሥር ቤት አለቃውም የግዞት እሥረኞቹን በእሥር ቤት ከዮሴፍ ጋር አሠራቸው፤ ዮሴፍ ግን ፤ ያገለግላቸው ነበር ፤ በእስር ቤትም አንድ ዓመት ኖሩ፤

፭፤ ወሐለሙ ሕልመ ክልኤሆሙ በአሐቲ ሌሊት ፩ዱ ፩ዱ እምኔሆሙ ርእዩ ሕልሞሙ ሊቀ ቀዳሕያን ወሊቀ ሐባዝያኑ ለንጉሥ ግብጽ እለ ሀለዉ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ፤

ክልኤሆሙ ሊቀ ቀዳሕያኑ ወሊቀ ሐባዝያኑ ብሎ ይገጥማል፤ በእሥር ቤት ታሥረው ተግዘው ያሉ የግብጹ ንጉሥ እንጀራ አዛገፍና ጠጅ አሳላፊው ሁለቱም በአንዲት ሌሊት አንዱም አንዱም እየራሳቸው ሕልም አዩ፤ አንድም በበአሐቲ ሌሊት ፩ዱ ፩ዱ እምኔሆሙ ርእዩ ሕልሞሙ ይላል ፤ በእሥር ቤት ታሥረው ተግዘው ያሉ፤ የግብጹ ንጉሥ እንጀራ አዛገፍና ጠጅ አሳላፊው እነዚህ ሁለቱ በያንዳንዲቱ ሌሊት ፤ አንዱም አንዱ እየራሳቸው ሕልም አዩ ፤

፮፡፯፤ ወቦአ ዮሴፍ ኀቤሆሙ ወርእየሙ ትኩዛኒሆሙ ፤ ወተስእሎሙ ዮሴፍ ወይቤሎሙ ምንትኑ ኀዙናን ገጽክሙ ዮም ፤

በሀገራቸው ፤ ሕልም ተርጉመው ፤ ፍጺማ ሰፍተው ፤ ለራሳቸው በቅተው ለሰው ይተርፉበታልና የዮሴፍን ሕልም መተርጉም ሰምተው፤ አስጠርተውት ወደ እነሱ ገባ፤ አንድም ለሌላ ጉዳዩ እሱው በፈቃዱ እነሱ ወዳሉበት ገባ፤ ቢገባ ልቡናቸው አዝኖ፤ ፊታቸው ጠቍሮ አያቸው ፤ ለታሠረ ሰው ማዘን መቈርቈር ልማዱ ነው ፤ ይል



ቁንም እናንት ፊታችሁ ጠቍሯል፤ ልቡናችሁ አዝኗል ምን ሁናችኋል ? ብሎ ጠየቃቸው ፤

፯፤ ወይቤልዎ ሐለምነ ሕልመ ወኃጣእነ ዘይፌክር ለነ ፤

ሕልም አይተን የሚተረጉምልን አጥተን አለት ፤

፰፤ ወይቤሎሙ ዮሴፍ አኮኑ እግዚአብሔር ዘወሀቦ ይፌክር ሕልመ ፤

ዮሴፍም፤ ሕልምን እንጂ የሚተረጉም እግዚአብሔር የገለጠለት ነው ፤ አንድም ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር የገለጠለት አይደለም ? ሕልምስ የሚተረጉም እግዚአብሔር የገለጠለት ነው፤ ብሎ መምለኪያን ጣዖት ናቸውና አምላኩተ እግዚአብሔርን ይሰብክላቸዋል ፤

ወይእዜኒ ንግሩኒ ምንትኑ ሕልም ክሙ ፤

አሁንም ሕልማችሁን ንገሩኝ ልተርጉምላችሁ አላቸው ፤

፱፤ ወነገሮ ሊቀ ቀዳሕያን ሕልሞ ለዮሴፍ ወይቤሎ እሬኢ በሕልምየ ሐረገ ወይን በቅድሜየ ፤

ጠጅ አሳላፊውም ፤ ያን ጊዜ ሕልሙን ለዮሴፍ ነገረው ፤ በፊቴ አንዲት የወይን ሐረግ በቅላ አያለሁ ፤ (በፊቴ አንድ የወይን ሐረግ በቅሎ አያለሁ)፤

፲፤ ወውስተ ውእቱ ሐረግ ሠረፁ ሠለስቱ አዕፁቅ ወአውፅኡ ሠለስተ አስካለ ፤

በዚያ ባንዱ በወይን ሐረግ ሦስት አዕቆች ሲወጡ፤ ደግሞ ሦስቱ አጽቆች ሦስት ዘለላ ወይን ሲያፈሩ ፤

ወጽዋዑ ለፈርዖን ውስተ እዴየ ፤

ጌታዬ ፈርዖን የሚጠጣበት ጽዋ ፤ እንደ ቀድሞው በእጄ ተይዞ ፤

፲፩፤ ወነሣእክዎሙ ለአልክቱ አስካል ፤ ወአጸርክዎሙ ውስተ ጽዋዑ ለፈርዖን ወመጠውክዎ ፤

እነዚያንም ሦስት ዘለላዎች ቈርጬ አምጥቼ፤ ጌታዬ ፈርዖን በሚጠጣበት ወርቅ ጽዋ ላይ ጠመቅኋቸው፤ እንደ ቀድሞው ለጌታዬ ለፈርዖን በዚያ ጽዋ ስሰጠው አየሁ ብሎ ነገረው ፤

፲፪፤ ወይቤሎ ዮሴፍ ዝንቱ ውእቱ ፍካሬሁ ለሕልምከ ፤

ዮሴፍም የሕልምህ ትርጓሜው ይህ ነው ፤ አንድም ከመዝ ውእቱ ፍካሬሁ ለሕልምከ ይላል፤ የሕልምህ ትርጓሜው እንደዚህ ነው አለው ፤

እሉ ሠለስቱ አስካል ሠላስ መዋዕል እማንቱ ፤

እኒህ ሦስቱ ዘለላዎች ሦስት ቀኖች ናቸው፤ ከመዝ ያለውን አመጣ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወእስከ ሠላስ መዋዕል ይዜክር ፈርዖን ሢመተከ ወያገብአከ ውስተ ሊቀ ቀዳሕያን ወትሜጥዎ ጽዋዖ ለፈርዖን በእዴከ ከመ ቀዲሙ ሢመትከ አመ ውስተ ሊቀ ቀዳሕያን አንተ፡

እስከ ሦስት ቀን ድረስ ጌታህ ፈርዖን የቀደመ ሹመትህን አስቦ ወደ ቀድሞ ሊቀ ቀዳሕያንነትህ ይመልስሃል፡ አንተ ሊቀ ቀዳሕያንነት በተሾምኸበት ወራት እያሳለፍክ ትሰጠው እንደነበረ ዛሬም እንደ ቀድሞው ተሹመህ በወርቅ ጽዋ የወይን ጠጁን ለጌታህ ለፈርዖን ትሰጠዋለህ ፤ አንድም እንዲህ ብሎ ተረጐመለት ፤

፲፬፡፲፭፤ ወተዘከረኒ አመ አሠነየ ለከ ወግበር ምሕረተ ላዕሌየ ወአዘክሮ ለፈርዖን በእንቲአየ፡ ወአውፅአኒ እምዝንቱ ቤተ ሞቅሕ፡ እስመ ሰረቅት ሰረቁኒ ጽሚተ እምብሔረ ዕብራውያን፡ ወበገዝየኒ በዘአልቦ ዘገበርኩ ወኢምንተኒ አንበሩኒ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ፡

እስማኤላውያን ከዕብራውያን አገር ሰርቀው ገዝተው ወደ ግብጽ አምጥተውኛልና፡ ይኸስ አይደለም፡ በወርቃቸው ቢገዙ ሰረቅት አያሰኛቸውም ብሎ ወንድሞቼ ዕብራውያን፡ ከእስራኤል ሀገር ሰርቀው ሸጠው ወደ ግብጽ እንድመጣ አድርገውኛልና፡ በዚህም አገር የሥራሁት ክፉ ሥራ ምንም ምን ሳይኖርብኝ አስረው አግዘው በእስራት ቤት ጥለውኛልና፡ ለአንተ በጎ ነገር ባደረገልህ ጊዜ እኔንም በቸርነት አስበኝ፡ ለእኔም በጎ ነገር አድርግልኝ ፡ የእኔንም ነገር ለጌታህ ለፈርዖን አሳስብልኝ ፤ አሳስበህም ከዚህ ከእሥራት፡ ከግዞት ቤት እንድወጣ አድርግልኝ አለው፤

፲፮፤ ወሶበ ርእየ ሊቀ ሐባዝያን ከመ ሠናየ ፈከረ ሎቱ ይቤሎ ለዮሴፍ አነሂ ርኢኩ ከመዝ በሕልምየ ፫ቱ አክፋር ላዕለ ርእስየ ፡

እንጀራ አዛገፑም፤ ለጠጅ (አበዛው) አሳላፊው ሕልሙን በጎ አድርጎ እንደ ተረጐመለት በአየ ጊዜ፤ ዮሴፍን፡ እንዲህ አለው፤ እኔም እንዲህ አየሁ ፤ አንድም እኔም እንደሱ በሕልሜ እንደ ዚህ ያለ ሕልም አየሁ፡ ሦስት እንቅብ (ቅርጫት) ተሸክሜ ፤ አንድም ሦስት እንቅብ ፡ አንድም ሦስት መሶብ፤ በራሴ ላይ ተሸክሜ ፤

፲፯፤ ወውስተ ሠለስቱ አክፋር ሀሎ ላዕሌሁ ኵሉ ዘመደ መብልዕ ዘይበልዕ ፈርዖን ንጉሠ ግብፅ፡ ወበልዕ ዖፍ አዕዋፍ በውስተ ከፈር ዘላዕለ ርእስየ ፡

በዚያም በሦስቱ እንቅብ ላይ የግብጹ ንጉሥ ፈርዖን የሚበላው የመብሉ አይነት ሁሉ አለበት፤ ያነን ተሸክሜ ስሔድ፡



አዕዋፍ መጥተው በራሴ ላይ ካለው እንቅብ፡ እየተነጣጠቁ ወስደው፡ ሲበሉት አየሁ አለው፤

፲፰፤ ወአውሥአ ዮሴፍ ወይቤሎ ዝንቱ ውእቱ ፍካሬሁ ለሕልምከ እልክቱ ሠለስቱ አክፋር ሠላስ መዋዕል እማንቱ ፡

ዮሴፍም መለሰለት፡ እንዲህም አለ፤ የሕልምህ ትርጓሜ ይህ ነው ፤ አንድም ከመዝ ይላል፡ የሕልምህ ትርጓሜ እንዲህ ነው፤ በራስህ ላይ የተሸከምኻቸው እኒህ ሦስት እንቅቦች ሦስት ቀኖች ናቸው ፤

፲፱፤ ወእስከ ሠላስ መዋዕል ይመትር ፈርዖን ርእሰከ እምኔከ ወይሰቅለከ ላዕለ ዕፅ ወይበልዑ አዕዋፈ ሰማይ ሥጋከ ፡

እስከ ሦስት ቀን ድረስ ፈርዖን ራስህን ከቸብቸቦህ ይቈርጠዋል ፤ አንድም ፡ ቸብቸቦህን ከራስህ ይቈርጠዋል፡ እንዲህም አድርጎ በእንጨት ላይ ይሰቅልሃል ፤ አንድም ያካፍላል ፡ ይመትር ፈርዖን ርእሰከ ወኪያከ ይሰቅለከ ላዕለ ዕፅ ይላል፡ ቸብቸቦህን ካንተ ይቆርጠዋል፡ እንዲህም አድርጎ አንተን በዕንጨት ላይ ይሰቅልሃል፤ ከዚያ በኋላ፡ ንጉሥ የሰቀለውን አንበሳ የሰበረውን የሚነካ የለምና ተሰቅለህ ሙተህ የሚቀብርህ አጥተህ ቀን አዕዋፍ ፡ ሌሊት አራዊት ሥጋህን ይነጣጠቁታል ብሎ ለዚያም ተረጐመለት ፡ በሱም ተረጐመበት ፤

፳፤ ወኮነ በሣልስት ዕለት ዘአመ ዕለተ ተወልደ ፈርዖን ገብረ ማዕደ ሀቢየ ለሰብኡ ፡

ይህን በተረጐመበት በሦስተኛው ቀን ፤ ፈርዖን በተወለደበት ቀን ፡ ለሠራዊቱ ታላቅ ማዕድ (ግብር) አደረገ አለ ፤ አዳራሽ ተገኘ ሲል ነው ፡ ከነ ያለውን ገብረ ብሎ አመጣው፤ አሕዛብ፡ የተወለዱበትን ቀን ያከብራሉና፡ ዘአመ ዕለተ ተወልደ አለ፤

ወተዘከረ ሢመቶ ለሊቀ ቀዳሕያን ወሢመቶ ለሊቀ ሐባዝያን በማዕከለ ሰብእ፡

ያንጊዜ ፈርዖን በሠራዊቱ መካከል፡ የእንጀራ አዛገፑን ሹመትና የጠጅ አዛገፑን ሹመት አሰበ አለ፡ ተበልቶ ሲጠጣ፡ ዛሬ የአዳራሻችን ነገር እንደ ምን ሁኖ ዋለ ? ብሎ ጠየቀ ፤ አዳራሹስ ድንቅ ሁኖ ነበር ፡ በጠጅ አሳላፊው ተተክቶ የተሾመው አጥፍቶ አከፍቶ ዋለ እንጂ አሉት ፡ ያነን ሽሮ ፤

፳፩፤ ወአግብኦ ለሊቀ ቀዳሕያን ውስተ ሢመቱ ወመጠዎ ጽዋዖ ለፈርዖን ውስተ እዴሁ ፡

ይኸነን የቀድሞውን የጠጅ አሳላፊውን ወደ ጥንቱ ሹመቱ መል

www.ethiopianorthodox.org

ሶ:ታል ፣ ለፈርዖን ለጌታውም በወርቅ ጽዋ እንደ ጥንቱ የወይን ጠጅ ሰጥቶታል ፤

፳፪፤ ወለሊቀ ሐባዝያንስ ሰቀሎ ዲበ ዕፅ በከመ ፈከረ ሎቱ ዮሴፍ ፣

በእንጀራ አዛገፎ ቦታ የተሾመ ውሳ ብሎ ጠየቀ ፤ በእንጀራ አዛገፎስ ቦታ የተሾመው አሳምሮ ደስ አሰኝቶ ውሏል ፣ ያ የቀድሞው ግን ያሳማህ ፣ ያስጠላህ ነበር አሉት፣ (ብለው ነገሩት) ለካ የሰጠነው ሳያንሰው ያ ሹማችን አሳምቶን አስጠልቶን ይኖር ኑሯልን ብሎ ፣ ዮሴፍ እንደተረጐመበት ቸብቸበውን ቈርጦ ሰቅሎታል ፤

፳፫፤ ወኢተዘከሮ ሊቀ ቀዳሕያን ለዮሴፍ አላ ረስዖ ፣

ጠጅ አሳላፊውም በዚያ ወራት ዮሴፍን ዘነጋው እንጂ አላሰበውም፤ ምን አዘነጋው ቢሉ ዘመናይነት ነው አዘንግቶታል ፤ አንድም ፣ ዮሴፍ ትውክልቱን በሰው አድርጎ ነበርና፣ ስለዚህ እንዲዘነጋው አደረገው (አድርጎታል)፤ አንድም ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ እንዲል፣ እስከ ጊዜው ድረስ አቆይቶታል ።

# ምዕራፍ ፵ወ፩

፩፤ ወኮነ እምድኅረ ፪ቱ ዓመት ርእየ ፈርዖን ሕልመ ከመ ዘይቀውም መልዕልተ ፈለግ ፣

ይህ ከሆነ በኋላ በሁለተኛው ዓመት አለ ይኸን ከተረጐመላቸው በኋላ ፤ አንድም ለተወለደባት ቀን በዓል ካደረገ በኋላ በሁለተኛው ዓመት፣ ይኸ ከመ፣ በባለቤት የገባ ከመ ነው፤ በወንዝ ዳር ቁሞ ሌሊት ሕልም አየ፤ አንድም ሌሊት በሕልሙ ከወንዝ ዳር ቁሞ አየ ፤

፪፤ ወናሁ ከመ እምፈለግ የዐርጉ ሰብዓቱ አልህምት ሠናይ ራዕዮሙ ወስቡሕ ሥጋሆሙ ወይትረዓዩ ውስተ ማዕዶት ፣

ይህ ከመ፣ እንደዚያው በባለቤት የገባ ከመ ነው፤ ከወንዙ ሰባት ላሞች ወጡ ፤ አንድም ከመን እንዘ ሲል ነው ፣ ወትሬኢ ከመ ይሜረዉ ኃጥአን እንዲል ከመን እንዘ ሲል ፣ እነሆ ሰባት ላሞች ከወንዙ ሲወጡ እነዚሁም መልካቸው ያማረ የተወደደ ነው ፣ ሥጋቸውም የወፈረ የሰባ ነው ፣ ከወንዙ ወጥተውም ወደ ማዶ ተሻግረው ሔዱ፤

፫፤ ወዐርጉ ካልአን ሰብዓቱ አልህምት እምድኅሬሆሙ እምውስተ ፈለግ ወእኩይ ራዕዮሙ ወድግዱግ ሥጋሆሙ



ወይትረዓዩ ኀበ እልክቱ አልህምት ውስተ ማዕዶተ ፈለግ ፣

ከእነሱ ቀጥሎ (ከእነሱ በኋላ) ሌሎች ሰባት ላሞች ከወንዙ ሲወጡ፣ እነዚሁም መልካቸው እጅግ የከፋ፣ ሥጋቸውም እጅግ የከሳ ነው ፣ እነዚኸም ወንዙን ተሻግረው ወደ ሔዱ ወደ ሰባቱ ወፍራሞች ላሞች ተከትለው ሔዱ፤ አንድም እነዚህ የከሱት የደረቁት ሰባት ላሞች፣ ወደ ወፈሩት ሰባት ላሞች ወንዙን ተሻግረው ተከትለዋቸው ሲሔዱ አየ ፤

፬፤ ወውሕጥዎሙ እልክቱ ሰብዓቱ አልሕምት እለ እኩይ ራዕዮሙ ወድግዱግ ሥጋሆሙ ለእሙንቱ አልሕምት እለ ስቡሕ ሥጋሆሙ ወሠናይ ራዕዮሙ ወነቅሐ ፈርዖን ፣

እኒህም መልካቸው የከፋ ፣ ሥጋቸው የከሳ የደረቀ ፣ የቀጠነ ሰባቱ ላሞች፣ መልካቸው ያማረ ፣ የተወደደ ሥጋቸው የሰባ የወፈረ ሰባቱን ላሞች ውጠዋቸው ከክሳታቸው ሳይመለሱ አይቶ ፣ ፈርዖን ከእንቅልፉ ነቃ ፤

፭፤ ወኖመ ወደገመ ሐሊመ ወናሁ ሰብዓቱ ሰዊት የዓርጉ እምአሐዱ ሥርው ኅሩያን ወሠናያን ፣

ተመልሶ ተኛ፣ ዳግመኛ ሕልም አየ ካንድ ሥር ካንድ ዘለላ ያማሩ የተወደዱ የተመረጡ ፍሬያማዎች ሰባት ወፍራሞች ገብሶች ሲወጡ ፤

፮፤ ወናሁ ሰብዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ወዕኡ እምድኅሬሆሙ ፣

ደግሞ ከእነሱ ቀጥለው (ከእነሱ በኋላ) የሰለቱ የደረቁ ሰባት ገብሶች ሲወጡ ፤

፯፤ ወውሕጥዎሙ እልክቱ ሰብዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ለእልክቱ ሰብዓቱ ሰዊት ኅሩያን ወምሉዓን ፣

ሰባቱ የደረቁ የሰለቱ ገብሶች ከእነሱ በኋላ ከእነሱ ቀጥለው ወጥተው ሔደው፣ ያማሩ የተወደዱ ፍሬያማዎች የሚሆኑ ሰባቱን ወፍራሞች ገብሶች ውጠዋቸው ከክሳታቸው ሳይመለሱ አየ ፤

ወተንሥአ ፈርዖን ወአእመረ ከመ ሕልም ውእቱ ፣

ፈርዖንም ፣ ከመኝታው ተነሥቶ ፣ ሕልም እንደሆነ አወቀው አለ ፣ ታይቶ የሚደረግ የማይቀር ቀዋሚ ሕልም እንደሆነ አወቀው ፤

፰፤ ወኮነ ሶበ ጸብሐ ተሐውከት ነፍሱ ለፈርዖን ፣

ይኸነን ሕልም ሌሊት አይቶ በነጋ ጊዜ፣ የፈርዖን ልቡናው ታወከችበት ፤

ወለአከ ይፀውዕዎሙ ለኵሎሙ መፈክራነ ግብጽ ወለኵሉ ጠቢባኒሆሙ

www.ethiopianorthodox.org

ወመጽኡ ወነገሮሙ ፈርዖን ሕልሞ ወስእኑ ፈክሮ ሎቱ ለፈርዖን ፤

ያንጊዜ፣ ከበላው አብልቶ ከጠጣው አጠጥቶ፣ የሚያኖራቸው ጠበብት አሉት (ነበሩት) መፈክራነ ግብጽ ሕልም እንተረጕ ማለን የሚሉ ናቸው ወለኰሎሙ ጠቢባኒሆሙ ፤ ፈላስፎች ናቸው ፤ እነዚህን ሁሉ ጥሩልኝ ብሎ አስጠራቸው ፤ ተጠርተው ተሰብስበው መጡ ፈርዖንም ያየውን ሕልሙን ነገራቸው፣ እነሱ ግን፣ ሕልሙን ተርጕመው ለፈርዖን መንገር ተሳናቸው ፤

፱፡ ወይቤሎ ሊቀ ቀዳሕያን ለፈርዖን ኃጢአትየ እዜከር ዮም ፤

ያንጊዜ ጠጅ አሳላፊው ቢገባ፣ ፈርዖንን አዝኖ ተክዞ አየው ፤ ምነው ንጉሥ ሆይ አዝነሃል ተክዘሃል አለው ፤ እኔ አላዝን ማን ይዘንልኝ ሕልም አይቼ የሚተረጕምልኝ አጥቼ አለው፤ ጠጅ አሳላፊውም አንሰ እዜክራ ለኃጢአትየ አለ፤ ለዝንጋዔየ ሲል ነው፣ ዕዳዬን በደሌን፣ የተዘነጋኝን ዝንጋዔየን አስባለሁ ፤ አንድም ለኃጢአትየ እንዳለም ይሆናል ፤ አትርሱኝ ያሉትን መዘንጋት ኃጢአት ነውና ፤

፲፡ ፈርዖን ንጉሥ ተምዕዖሙ ለአግብርቲሁ ወአንበረነ ውስተ ቤተ ሞቅሕ ፤ ኪያየ ወሊቀ ሐባዝያን ፤

አንተን በድለን ፤ አንተ ንጉሣችን ተቈጥተህ በእሥራት ቤት እንጀራ አሳላፊውንና እኔን ጠጅ አሳላፊውን አሥረህ አግዘኸን ሳለ ፤

፲፩፡ ወሐለምነ ሕልመ ክልኤነ አነ ወውእቱ ዘዚአነ ሐለምነ ፤

ሁለታችንም በእሥራት በግዞት ቤት ሳለን እሱና እኔ እየራስ እየራሳችን ሕልም አየን ፤ አንድም፣ ሁለታችንም በእሥራት በግዞት ቤት ታሥረን ሳለን ፤ እሱና እኔ ዘዚአነ፣ የራስ የራሳችንን ሕልም አየን ፤ አንድም በእሥራት በግዞት ቤት ሳለን እየራስ እየራሳችን ሁለታችንም ሕልም አየን ፤

፲፪፡ ወሀሎ ምስሌነ ወልድ ዕብራዊ ወሬዛ ዘሊቀ መበስላን ፤ ወነገርናሁ ወፈከረ ለነ ፤

ሊቀ መበስላን አዛዥ ቢትወደድ ራቅ ማሰሪያ ነው ፤ የጲጥፋራ አገልጋይ የሚሆን አንድ ዕብራዊ ሰው ከእኛ ጋር ታሥሮ ነበር፤ ሁለታችንም ሕልም አይተን ነገር ነው፤ ለእኔ ተረጕመልኝ፤ በእስ ተረጕመበት ፤



፲፫፡ ወኮነነ በከመ ፈከረ ለነ ፤

ይኸውም ነገር ፤ እሱ እንደተረጐመልኝ ተደረገልኝ፤ እሱም እንደ ተረጐመበት ሆነ አለ ፤ ሁለት አርእስት ተናግሯል ፤ ለሁለቱም ያመጣል ፤

ወከማሁ ረከብነ አነሂ ገባዕኩ ውስተ ሢመትየ ፤ ወለዝክቱኒ ሰቀልዎ ፤

አሁን እንደ ተናገርኹት ፤ አንድም እሱ እንደተረጐመው ፤ እኔም የተረጐመልኝን፣ እሱም የተረጐመበትን አገኘን አለ ፤ ያምጣው ወገባዕኩ ውስተ ሢመትየ፣ እኔም ወደ ሹመቴ ተመለስኩ አለ፤ እንደ ተረጐመልኝ ላለው ፤ ወለዝክቱኒ ሰቀልዎ ያነንም ሰቀሉት አለ፣ እንደ ተረጐመበት ላለው ፤ አሁንም እሱን አስጠርተህ አምጥተህ እሱ ይተርጕምልህ እንጂ ይህንስ ነገር ሌላ የሚተረጕምልህ የለም አለው ፤

፲፬፡ ወለአከ ፈርዖን ወፀውዕዎ ለዮሴፍ ወአውፅእዎ እምቤተ ሞቅሕ ወላፀይዎ ርእሶ ፤ ወወለጡ አልባሲሁ ፤ ወአምጽእዎ ኀበ ፈርዖን ፤

ያንጊዜ ፈርዖን ይህነን ሰምቶ ሒዱ አምጡት ብሎ ላከ ፤ ከሒደው ዮሴፍን ጠሩት ፤ ከእሥራት ከግዞት ቤትም አወጡት፣ ራሱን (ጠጕሩን) ላጩት ልብሱንም ለወጡለት ፤ ልብሱንም ለውጠው ሌላ ልብስ አልብሰው ወደ ፈርዖን አመጡት፣ ምነዋ ዮሴፍን አልታሠረም አላልንም ? ቢሉ ፤ ታሥሯል ያሉ እንደሁ የተመቸ፣ አልታሠረም ያሉ እንደሁ ዮሴፍ የእሥረኛ ግብር አድርጓል ፤ እሥረኛ ራሱን አይላጭ ፤ ገላውን አይታጠብ ፤ ጥፍሩን አይቆርጥ ፤ አዲስ አይለብስ፣ የላመ የጣመ አይቀምስምና ፤ ሒዱ ራሱን ላጭታችሁ ፤ ጥፍሩን ቈርጣችሁ፣ ገላውን አጥባችሁ፣ አዲስ ልብስ አልብሳችሁ አምጡልኝ ብሎ ላከ ፤ ሒደው ራሱን ላጭተው ፤ ጥፍሩን ቈርጠው ፤ ገላውን አጥበው ፤ አዲስ ልብስ አልብሰው ፤ ወደ ፈርዖን አመጡት ፤

፲፭፡ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ፤ ሕልመ ሐለምኩ፣ ወዘይፌክር ሊተ ኀጣዕኩ፣ ወሰማዕኩ በእንቲአከ ከመ ሰማዕከ ሕልመ ወፈከርከ ፤

ፈርዖንም ዮሴፍን ፤ አሁንስ ያስጠራሁህ ሕልም አይቼ የሚተረጕምልኝ አጥቼ ሳለሁ ያንተን ነገር ሰማሁ ፤ ሁለቱም ባለሟሎቼ ሕልም አይተው እንደ ተረጐምክላቸው ሰማሁ ፤ አንድም ይኸ ከመ ፤ ቅጽል ነው ፤ የሁለቱን ባለሟሎቼን ሕልም ሰምተህ የተረጐምኸላቸውን ነገር ሰማሁ ፤ ይህነን

www.ethiopianorthodox.org

ሰምቼ ስለዚህ አስጠራሁህ አለው ፤

፲፭፡ ወአውሥአ ዮሴፍ ለፈርዖን ወይቤሎ ዘእንበለ እግዚአብሔር ዘወሀቦ ኢይክል ፈክሮ ፤

ዮሴፍም ለፈርዖን መለሰለት፤ እንዲህም አለው መምለኬ ጣዖት ነውና ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ይሰብክለታል ፤ ሕልምን እንጂ እግዚአብሔር የገለጸለት ይተረጕማል ፤ በል ንገረኝ ልተርጕምልህ አለው ፤

፲፮፡ ወነገሮ ፈርዖን ለዮሴፍ ወይቤሎ እሬኢ በሕልምየ ከመ ዘእቀውም በማዕዶተ ፈለግ ፤

ፈርዖንም ለዮሴፍ ሕልሙን ነገረው፤ ነገሮ ለዮሴፍ ያለውን ያምጣው ፤ አጸፋውን ይነግረዋል፤ ይህ ከመ በባለቤት የገባ ነው ፤ በውህ ዳር ቁሜ ሕልም አየሁ ፤ እሬኢ በሕልምየ ያለውን ያምጣው ፤

፲፯፡ እምውስተ ፈለግ የዐርጉ ሰብዓቱ አልሕምት እማዕዶተ ፈለግ ስቡሓን ሥጋሆሙ ወሠናያን ራዕዮሙ ወይትረዐዩ ውስተ ማዕዶት ፤

መልካቸው ያማረ የተወደደ ፤ ሥጋቸው የሰባ የወፈረ ፤ ሰባት ወፍራሞች ላሞች፤ ከወንዝ ወጥተው ወንዙን ተሻግረው ሔዱ ፤

፲፰፡ ወናሁ ካልአን ሰብዓቱ አልሕምት የዐርጉ እምድኅሬሆሙ እምውስተ ፈለግ እኩያን ወሕሱም ራዕዮሙ ወድግዱግ ሥጋሆሙ ፤

እነሆ መልካቸው እጅግ የከፋ፤ ሥጋቸው የቀጠነ የከሳ፤ ሌሎች ሰባት ላሞች ፤ ከእነሱ በኋላ ፤ ከእነሱ ቀጥለው ከወንዙ ወጥተው ወንዙን ተሻግረው እነሱን ተከትለዋቸው ሔዱ ፤ አንድም ሌሎች ሰባት ላሞች ከእነሱ ቀጥለው ከእነሱ በኋላ ከወንዙ ወጥተው ወንዙን ተሻግረው እነሱን ተከትለው ሲሔዱ አየሁ፤ እለዚህም መልካቸው እጅግ የከፋ ፤ ሥጋቸውም እጅግ የቀጠነ የከሳ ነው ፤

ወኢርኢኩ ዘከማሆሙ ሕሡመ በኵሉ ምድረ ግብጽ ፤

እኔም በግብጽ አገር ሁሉ እንደ እነሱ የከፋ አላየሁም ፤

፳፡ ወውሕጥዎሙ እልክቱ ድግዱጋን ፤ ለእልክቱ ሰብዓቱ አልሕምት ስቡሓን ወሠናያን ወቦኡ ውስተ ከርሦሙ ፤

እኒህ በኋላ የወጡት ፤ ሥጋቸው የከሳ፤ መልካቸው የከፋ፤ ሰባቱ ሌሎች ላሞች ፤ ፊት የወጡ መልካቸው ያማረ የተወደደ ፤ ሥጋቸው የሰባ የወፈረ፤ ሰባቱን ላሞች ሲውጧቸው ፤



፳፩፡ ወኮነ ከመ አልቦ ዘቦአ ውስተ ከርሦሙ ወገጸሙኒ ሕሡም ፤ ከመ ቀዳሚ ወነቃሕኩ ፤

እነዚያን ውጠዋቸው ከክሳታቸው ሳይመለሱ ይኸነን በሕልሜ አይቼ ነቃሁ ፤

፳፪፡ ወሰከብኩ ካዕበ ወርኢኩ በሕልምየ ከመዝ ሰብዓቱ ሰዊት ይወፅኡ እምአሐዱ ሥርው ምሉዓን ወሠናያን ፤

ዳግመኛም ተመልሼ ተኝቼ በሕልሜ እንዲህ አየሁ አለ፤ እንደ ላሞቹ ሕልም የገብሶቹ ንም ሕልም ከመዝ አለ ፤ አንድም እንደዚህ ያለ ሕልም አየሁ አለ ፤ ከመዝ ያለውን ወደፊት ያምጣው ፤ ሰባት ያማሩ የተወደዱ ወፍራሞች ፍሬያማዎች ገብሶች ከአንድ ሥር ከአንድ ዘለላ ሲወጡ ፤

፳፫፡ ወካልአን ሰብዓቱ ሰዊት ቀጢናን ወይቡሳን ወፅኡ እምድኅሬሆሙ፤

የሰለቱ የደረቁ ሌሎችም ሰባት ገብሶች ከእነሱ በኋላ ከእነሱ ቀጥለው ከአንድ ሥር ከአንድ ዘለላ ወጡ ፤ ሲወጡ ፤

፳፬፡ ወውኅጥዎሙ እልክቱ ቀጢናን ወይቡሳን ለእልክቱ ሰብዓቱ ሰዊት ምሉዓን ወሠናያን ወነገርክዎሙ ለመፈክራን ወአልቦ ዘፈከሩ ሊተ ፤

ከአንድ ሥር ከአንድ ዘለላ በኋላ የወጡ የደረቁ፤ የሰለቱ ሰባት ገብሶች ፊት የወጡ ያማሩ፤ የተወደዱ ወፍራሞች ፍሬያማዎች ሰባቱን ገብሶች ሲውጧቸው ፤ ውጠዋቸውም ከክሳታቸው ሳይመለሱ አየሁ ብዬ ሕልም ለሚተረጕሙልኝ ሰዎች ነገርኳቸው፤ ከእነዚያ አንዱም አንዱስ ስንኳ የተረጐመልኝ የለም አለው ፤

፳፭፡ ወይቤሎ ዮሴፍ ለፈርዖን ሕልሙ ለፈርዖን አሐዱ ውእቱ ዘይገብር እግዚአብሔር አርአዮ ለፈርዖን ፤

ያንጊዜ ዮሴፍ ፈርዖንን ሕልምህ አንድ ወገን ነው፤ እግዚአብሔርም በኋላ ዘመን የሚደረገውን ነገር ለአንተ ገልጦልሃል አለው ፤

፳፮፡ እልክቱ ሰብዓቱ አልሕምት ሠናያን ፯ቱ ዓመት እሙንቱ፤ ወእልክቱ ፯ቱ ሰዊት ሠናያን ፯ቱ ዓመት እሙንቱ፤ ሕልሙ ለፈርዖን አሐዱ ውእቱ ፤

ይህ አንድ ወገን ነው፤ ሰባት ዓመት ጥጋብ አለ ፤

፳፯፡ ወእልክቱ ሰብዓቱ አልሕምት ድግዱጋን እለ ዓርጉ እምድኅሬሆሙ ፯ቱ ዓመት እሙንቱ ፤ ወእልክቱ ፯ቱ ሰዊት ቀጢናን ወዕቡራን ፯ቱ ዓመት እሙንቱ ፤ ወይከውን ፯ቱ ዓመት ዘረኃብ ፤

ይህም አንድ ወገን ነው፤ ሰባት ዓመት ረኃብ አለ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፰፡ ወዝንቱ ቃል ዘእቤሎ ለፈርዖን ዘይገብር እግዚአብሔር አርአዮ ለፈርዖን ፤

ላንተም የነገርኩህ ቃል ይህ ነው ፤ ወዘይገብር ፤ እግዚአብሔርም በኋላ ዘመን የሚያደርገውን ነገር ፤ ለአንተ ገልጦ አሳየህ ፤ አንድም ለአንተ የነገርኩህ ይህ ቃል ፤ እግዚአብሔር በኋላ ዘመን የሚያደርገውን ነገር ለአንተ የገለጸልህ ነገር ነው ፤

፳፱፡ ናሁ ይመጽእ ፯ቱ ዓመት ዘብዙኅ ጽጋብ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፤

መልካቸው ያማረ የተወደደ ፤ ሥጋቸው የወፈረ የሰባ ሰባት ላሞች ፤ ያማሩ የተወደዱ ወፍራሞች ፍሬያማዎች ሰባቱም ገብሶች ፤ ይህ አንድ ወገን ነው፤ ሰባት ዓመት ብዙ ጥጋብ ይመጣል ፤

፴፡ ወይመጽእ ፯ቱ ዓመት ዘረኃብ እምድኅሬሁ ወይረስዕዎ ለጽጋብ በኵሉ ምድረ ግብጽ ፤

መልካቸው የከፋ፤ ሥጋቸው የቀጠነ የከሳ ሰባት ላሞች፤ የሰለቱ የደረቁ ሰባቱም ገብሶች ይህ አንድ ወገን ነው ፤ ከሰባቱ ዓመት ጽጋብ በኋላ ፤ ከሰባቱ ዓመት ጽጋብ ቀጥሎ ፤ ሰባት ዓመት ረኃብ ይመጣል ፤ በግብጽ አገር ያሉ ሰዎች ፤ አንድም በግብጽ አገር ያሉ ሰዎች ሁሉ የሰባቱን ዓመት ጽጋብ ይዘነጉታል ፤

፴፩፡ ወየሐልቅ በረኃብ ኵሉ ሰብእ እምውእቱ ረኃብ ዘይመጽእ እምድኅሬሁ እስመ ዐቢይ ውእቱ ጥቀ ፤

ይህ የሚመጣው ሰባቱ ዓመት ረኃብ ጽኑ ክፉ ነውና ፤ ጽኑ ክፉ ስለሆነ ከጥጋቡ በኋላ ፤ ከጥጋቡ ቀጥሎ ከሚመጣው ረኃብ የተነሣ ሰው ሁሉ በረኃብ ያልቃል ፤

፴፪፡ ወዘደገመ ፈርዖን ሐሊሞቶ እስመ እሙን ውእቱ ነገሩ እምኀበ እግዚአብሔር ወፍጡነ ይገብሮ እግዚአብሔር ለዝንቱ ፤

ለአንተ መላልሶ ማሳየቱ ግን ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታገዞ የሚደረግ እውነተኛ ነገር ነውና ስለ ጽና ነገር ነው ፤ ከአንድ ባሕር ፤ ከአንድ ሥር ሲወጣ ማየትህ ግን ፤ ይህ ሁሉ የሚደረግ በአንተ ዘመን ነው ፤ ይህ ነንም ነገር እግዚአብሔር ፈጥኖ ያደርገዋል አለው ፤ ፈርዖንም ለዚህሳ ነገር ምን ይሻለኛል ምን ላድርግ ? አለው ፤ ይኸን ቢለው ዮሴፍም፤ እግዚአብሔር ድንቅ አድርጎ ከሰባት ዓመት ረኃብ ሰባቱን ዓመት ጥጋብ አስቀድሞታል ፤



፴፫፡ ወይእዜኒ ኅሥሥ ለከ ብእሴ ጠቢበ ወልብወ ወሚሞ ላዕለ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፤

አሁንም ለዚህ ነገር ብልህ ዓዋቂ ሰው ፈልገህ በግብጽ አገር ሁሉ ሹመው ፤

፴፬፡ ወይግበር ፈርዖን መዛግብተ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ፤ ወይድፍንዎ ለእክለ ግብጽ ዘሰባቱ ዓመት ፤

አንተም በየሀገሩ ሁሉ ሪቅ ፤ ጎተራ አሠሩ ፤ ሰው በጥጋብ ዘመን ወርቅ አምጣ ከሚሉት ፤ እህል አምጣ ሲሉት ይቀልለዋል፤ እህሉን እየተቀበለ፤ የሚነቅዘውን እያስፈጨ ፤ ጡብ እያስጣለ ፤ የማይነቅዘውን በሪቅ በጎተራ ለሰባት ዓመት ረኃብ የሚያኖር ብልህ ሹም ሹም ፤

፴፭፡ ወያስተጋብዕዎ ለኵሉ እክል ዘ፯ቱ ዓመት ዘጽጋብ ፤

የግብጽ ሰዎችም እንዲህ አድርገው አንተ ከሾምኸው ከብልህ ሹም ጋራ ሁነው የሰባቱን ዓመት የጥጋቡን ዘመን እህል በሪቅ በጎተራ ይሰብስቡት፤ ይህ በየሀገሩ የሚደረገው ነው ፤

ወያስተጋብእ ፈርዖን ሥርናዮ ወእክሎ ውስተ ኵሉ አህጉር ፤

ይልቁንም አንተ ንጉሥ ለሁሉ ልብስ ፤ ጉርስ ነውና በየሀገሩ ስንዴውን ሌላውንም እህል ሁሉ በሪቅ በጉተራ ሰብስብ ፤

ወይትዐቀብ ፤

ይኸውም የተጠራቀመው ለሰባት ዓመት ረኃብ ይጠበቅ ፤

፴፮፡ ወይኩን ውእቱ እክል ዘየዐቅቡ ሲሳየ ለኵሉ ብሔር ለአመ ረኃብ ዘይመጽእ ውስተ ብሔረ ግብጽ ወኢይመውት ሰብእ በረኃብ ፤

ለአገሩ ሁሉ ምግብ ሊሆን የሚጠበቀው እህሉ ሁሉ፤ ይኸውን ለአመ ረኃብ ፤ በግብጽ አገር ለሚመጡ ለሰባት ዓመት ረኃብ ጊዜ ይሆናል ፤ ሰውም ያን ጊዜ በረኃብ ምክንያት አይሞትም ፤ አንድም እንዲለ ይሆናል ፤ በግብጽ አገር ምግብ ሊሆን የሚጠበቀውም እህል ሁሉ ፤ ይኩን ለአመ ረኃብ ፤ በግብጽ አገር ለሚመጣው ለረኃብ ጊዜ ይሁን ፤ ወኢይመውት ሰብእ በረኃብ ፤ ሰው ሁሉ በረኃብ አይሙት፤ በጥጋቡ ዘመን ያገኛችሁትን እህል አታባክኑ ሲል ነው ፤ አሁንም እንደ ነገርኩህ አድርጎ የሚያዘጋጅ ብልህ ሹም መሾም ነው አለው ፤ ያን ጊዜ ዮሴፍ ሹመት የተካሰሰ ይመስላል ፤

፴፯፡ ወአደሞ ለፈርዖን ዝንቱ ነገር ወለኵሉ ሰብኡ ፤

ያንጊዜ ዮሴፍ አስመስሎ አሳክሎ አስረድቶ በነገረው ጊዜ ፈርዖን ደስ አለው ፤ መኳንን

www.ethiopianorthodox.org

ቱንም ሠራዊቱንም ደስ አሳ ቸው ፤ አንድም ዝንቱ ነገር፣ ይህ ነገር ፈርዖንን ደስ አሰኘው፣ መኳንንቱንም ሠራዊቱንም ደስ አሰኛቸው ፤

፴፰፤ ወይቤሎሙ ፈርዖን ለኵሉ ሰብኡ ቦኑ እንከ ዘተረክበ ከመ ዝንቱ ብእሲ ዘመንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ፣

ያንጊዜ ፈርዖን ሠራዊቱንም መኳንንቱንም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤቱ ያደረበት እን ዲህ ያለ ሰው በውኑ ተገኝቶ ያውቃልን አላቸው ፤

፴፱፡፵ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ እስመ ለከ አርአየከ እግዚአብሔር ዘንተ ኵሉ ወአልቦ ብእሲ ዘይጠበበከ ወዘይሌቡ እምኔከ አንተ ኩን ላዕለ ኵሉ ቤትየ ወለቃለ ዚአከ ይት አዘዝ ኵሉ ሕዝብ ፣

ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህ አለው ይህንን ሁሉ ነገር እግዚአብሔር ለአንተ ገልጸልሃልና ፣ ከአንተ በቀር ብልህ የሚሆን ዓዋቂ ሰው የለም ፣ አንተ ኩን ማንሻ ፤ አንድም ይኸን ሁሉ ነገር ፈጣሪህ እግዚአብሔር ለአንተ ገልጸልሃልና፣ ከአንተም የሚበ ልጥ ብልህ ዓዋቂ ሰው የለምና፣ በቤቴ ሁሉ አንተ ተሾም፣ ሠራ ዊቴም ሁሉ ለአንተ ቃል ይታ ዘዝ አለው ፤

ወዘእንበለ መንበር አልቦ ዘእፈደፍ ደከ አነ ፣

ከምትኖርበት ዙፋን ፣ ከምቀመ ጥበት ወንበር በቀር ከአንተ የምበልጥበት ነገር የለኝም አለው ፤

፵፩፤ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ ናሁ ሜምኩከ አነ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፣

ፈርዖን ዮሴፍን እንዲህስ ከሆነ በግብጽ አገር ሁሉ አንተን እሾምሃለሁ ፤ አንድም እንጻለ ይሆናል፣ እንዲህ ከሆነ በግ ብጽ አገር ሁሉ አንተን ሾም ኹህ አለው ፤

፵፪፤ ወአውፅአ ፈርዖን ሕልቀቶ እም እዴሁ ወወደየ በእዴሁ ለዮሴፍ ፣

ይህንም ብሎ አልቀረ ፈርዖን የእጅ ጣቱን ቀለበት አውጥቶ በዮሴፍ እጅ ጣት አደረገለት ፤

ወአልበሶ ልብሰ ሜላት ወአዕነቆ ባዝ ግና ወርቅ ላዕለ ክሳዱ ፣

ነጭ ሐር አለበሰው ፣ በአንገ ቱም የወርቅ ዝርግፍ አሠረለት፤

፵፫፤ ወአፅዐኖ ዲበ ፈረስ ዘዚአሁ ወአያደ አዋዴ ቅድሜሁ ወሤሞ ላዕለ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፣

እሱው ራሱ በሚቀመጥበት ፈረስ አስቀመጠው ፣ አዋጅ ነጋሪም በፊቱ ቆሞ አዋጅ ነገረ ቅድሜሁ ለፈርዖን ነው ፤ አን ድም ለዮሴፍ ነው ፤ እንዘ



ይብል ያለበት ነው ፤ ፈርዖን ዮሴፍን በግብጽ አገር ሁሉ ሾመው ብሎ ዓዋጅ ነገረለት፤ አንድም በፊቱ ቆሞ ዓዋጅ ነጋሪ ነገረለት፣ ወሤሞ ዓዋጅ ከነገረለትም በኋላ በግብጽ አገር ሁሉ ሾመው ፤ ይኸንማ ከላይ ሜምኩከ አለ፣ ከዚህ ሜሞ አለ፣ አይጣላም ? ቢሉ አይጣላም ፣ ያነኑ ገልጦ መናገር ነው ፤ አንድም ከላይ በእልፍኝ ለብ ቻው ከባለሟሎች ጋር ሳለ ሜም ኩከ ብሎታል ፣ ከእዚህ ግን በነጋሪት፣ በአዋጅ፣ በሠራዊት ያደረገለትን ሲያይ ሜሞ አለ፤ አንድም ከላይ እሱ ሜምኩከ ብሎ የተናገረውን ከዚህ መተ ርጉም ሜሞ ብሎ ጻፈው ፤

፵፬፤ ወይቤሎ ፈርዖን ለዮሴፍ አነ ለልየ ፈርዖን ዘእንበሌከ አልቦ ዘእገ ብር ወኢምንተኒ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፣

ፈርዖንም ዮሴፍን ስንኳንስ ሌላው እኔ ራሴ ቅሉ በግብጽ አገር ሁሉ ያለ አንተ ፈቃድ ፣ ያለ አንተ ምክር የማደርገው ነገር የለኝም አለው ፤

፵፭፤ ወሰመዮ ፈርዖን ስሞ ለዮሴፍ እስፍንቶፎኔሕ ፣

ስሙንም እስፍንቶፎኔሕ አለው አለ፣ መዝገበ ኅቡአት፣ ሊቀ ማእምራን ማለት ነው ፤

ወወሀቦ አስኔትሃ ወለተ ጴጥሬፌራ ማሪ ዘሀገረ ሄልዮቱ ትኩኖ ብእሲተ፣

ዘሀገረ ሄልዮቱ፣ ዘሀገረ ፀሐይ ሲል ነው ፤ ፀሐይነት ያላት አገር ፣ ካህነ ጣዖት የሚሆን የጴጥፋራ ልጅ አስኔትን ሚስት ልትሆነው አጋባው፤ ጴጥፋራ የዮሴፍ ጌታው ነው ፣ የጌታ ውን ልጅ አጋብቶታል፣ ማሪ አለው ፣ በአንድ ወገኑ ቢት ወደድ ቢሆን ፣ በአንድ ወገኑ ካህንነት አለውና ፤ አንድም ሌላ ጴጥፋራ ፣ ሌላ ማሪ ነው ፤ የእሱን ልጅ አጋባው ፤ አን ድም ጴጥፋራማሪ ይላል ጥቅል ስም ዘሀገረ ሄልዮቱ ብሎ ቀጸ ለለት የእሱን ልጅ ሚስት ልትሆነው አጋባው ፤

፵፮፤ ወሠላሳ ዓመቱ ለቱ ለዮሴፍ አመ ይቀውም ቅድመ ፈርዖን ንጉሠ ግብጽ ፣ ወሖረ ወፅአ ዮሴፍ እምቅ ድመ ገጹ ለፈርዖን አንሶሰወ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብፅ ፣

ዮሴፍም ሲሾም በፈርዖን ፊት በቆመ ጊዜ ፴ ዘመን ሆኖት ነበር ፣ ዮሴፍም ተሹሞ በፈር ዖን ፊት በወጣ ጊዜ ፤ አንድም ተሹሞ በፈርዖን ፊት ከወጣ በኋላ ፣ በግብጽ አገር ሁሉ ተመላለሰ አለ ፣ ሊያይ ሊመራ ነው፣ ሠላሳ ዘመንም ያለውን ከዚህ ይቈጥሩታል ፣ በእናት በአባቱ ቤት ዐሥራ ሰባት

www.ethiopianorthodox.org

ዓመት ፤ በጺጥፋራ ቤት ዐሥር ዓመት፤ በእሥር ቤት ሁለት ዓመት ፤ ሃያ ዘጠኝ ይሆናል ፣ አንዱን ዓመት ጅምር ጭርስ አድርጐ ሠላሳ አለ ፣ አንድም ከሩሌ የእሥራት ቤቱን ሦስት ዓመት ይላልና ብሎ፣ ፴ ያለው ይህ ነው ፤ ይኸውም ምሳሌ ነው ፣ ዮሴፍ ለሹመት በሠላሳ ዘመኑ ከፈርዖን ፊት እንደቆመ፤ ጌታም በጲላጦስ ፊት የቆመው በሠላሳ ዘመኑ ነውና ፤

፵፯፡ ወኮሎ እክለ ዘአውዕአት ምድር ዘብሔረ ግብጽ እስከ ፯ቱ ዓመት ዘጽጋብ ከላስስቲሁ ወኮሎ እክለ አስተጋብአ ፣

በሰባቱ ዓመት በጥጋቡ ዘመን የግብጽ አገር ያስገኘችውን እህል ሁሉ ነዶውን እያስከመረ፣ የሚነቅዘውን እያስፈጨ ጡብ እያስጣለ ፣ የማይነቅዘውን በሪቅ በጎተራ ሰብስቦ አኖረ ፤

፵፰፡ ወዘገበ እክለ ውስተ ኮሉ አህጉር ወአድያመ ብሔር ከመ ይኩን ሲሳየ ፣

በሀገሩ በአውራጃው ሁሉ የተገኘውን እህል ለሰባት ዓመት ረኃብ ምግብ ይሆን ዘንድ እንደዚህ አድርጎ ሰበሰበ ፤

፵፱፡ ወዘገበ ዮሴፍ ሥርናየ ከመ ኆፃ ባሕር ብዙኃ ጥቀ እስከ ስዕኑ ኈልቈቶ ወዘእንበለ ኈልቍ ኮነ ፣

የግብጽ ሰዎች መስፈር መቁጠር እስኪሳናቸው ድረስ፣ ዮሴፍም እህሉን እንደ ባሕር አሸዋ ብዙ አድርጎ ሰበሰበ፤ አንድም ከመ ኆፃ ባሕር ብዙኅ ጥቀ ይላል ፤ ብዙኅን ለኆፃ ይቀጥሏል፤ ዮሴፍ እህሉን እንደበዛ፣ እንደ ባሕር አሸዋ አድርጎ ሰበሰበው ፤ አንድም ዮሴፍ ያደለበው የእህሉ ድልብ እንደ ባሕር አሸዋ ብዙ ነው ፤ ይኸውም ከብዛቱ የተነሣ ያለ ስፍር ያለ ቍጥር ሆነ አለ ፣ በዝቶ ሳይቈጠር ሳይሰፈር ቀረ ፤ አንድም ተሰፍሮ ተቈጥሮ ከብዛቱ የተነሣ ተሳስቶ ያለ ቍጥር ቀረ፤

፶፡ ወተወልዱ ለዮሴፍ ፪ቱ ደቂቅ ዘእንበለ ይምጻእ መዋዕለ ረኃብ ዘወለደት ሎቱ አስኔት ፣

ወተወልዱ ለዮሴፍ ፪ቱ ደቂቅ ዘወለደት ሎቱ አስኔት ዘእንበለ ይምጻእ መዋዕለ ረኃብ ብለህ አቅና ፣ የረኃቡ ዘመን ገና ሳይመጣ አስኔት የወለደቻቸው ሁለት ልጆች ለዮሴፍ ተወለዱለት ፤

፶፩፡ ወሰመዮ ስሞ ለበኵሩ ምናሴ እንዘ ይብል እስመ ገብረ ሊተ እግዚአብሔር ከመ እርሳዕ ኵሎ ሕማምየ ወኵሎ ዘቤተ አቡየ ፣

መከራዬን ሁሉ፣ የአባቶቼንም ወገን መከራ ሁሉ እዘነጋው ዘንድ እግዚአብሔር እንድዘነጋው አደረገልኝ ሲል ፤ አንድም መከራዬን ሁሉ፣ የአባቶ



ቼንም ወገን መከራ ሁሉ እንድዘነጋው እግዚአብሔር አድርጎልኛልና ብሎ የበኵር ልጁን ስም ምናሴ አለው ፤ ምናሴ ማለት መርስዔ ኀዘን ማለት ነውና ፤ አንድም እስመ ያለው ቀሪ ነው፣ መከራዬን ሁሉ፣ የአባቶቼንም ወገን መከራ ሁሉ ፣ እግዚአብሔር እንድዘነጋው አደረገልኝ ብሎ የበኵር ልጁን ስም ምናሴ አለው ፤

፶፪፡ ወሰመዮ ስሞ ለካልኡ ኤፍሬም፣ እንዘ ይብል እስመ አዕበየኒ እግዚአብሔር በብሔረ ሥቃይ ፣

እስመ ያለው ቀሪ ነው፣ መከራ በታዘዘበት አገር እግዚአብሔር አከበረኝ ፣ አበዛኝ ፤ አንድም እንዳለም ይሆናል ፤ እግዚአብሔር መከራ በታዘዘበት አገር አክብሮኛል አብዝቶኛል ሲል፤ አንድም ይኸ እስመ ከመ ነው ፤ እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ እንዲል፤ መከራ በታዘዘበት አገር እግዚአብሔር እንድከብር እንድበዛ አደረገኝ ሲል፣ የሁለተኛውን ልጁን ስም ኤፍሬም አለው ፤ ኤፍሬም ማለት ዕበይ ፍሬ ማለት ነውና ፤

፶፫፡ ወሐሊፎ ፯ቱ ዓመት ዘጽጋብ እንዘ ይምጻእ ፯ቱ ዓመት ዘረኃብ በከመ ይቤ ዮሴፍ ፣

የጥጋቡ ዘመን ሰባት ዓመት አልፎ ፣ የረኃቡ ዘመን ሰባት ዓመት ይመጣል ብሎ ዮሴፍ እንደተናገረ ፣ የጥጋቡ ዘመን ሰባት ዓመት አልፎ ፤ የረኃቡ ዘመን ሰባት ዓመት ይመጣ ጀመረ ፤

፶፬፤ ወኮነ ረኃብ ውስተ ኵሉ ምድረ ግብጽ ፣

በግብጽ አገርም ሁሉ ረኃቡ ታዘዘ ፤

ወጸርሐ ኵሉ ሕዝብ ኀበ ፈርዖን በእንተ እክል ፣

ሰውም ሁሉ ተሰብስቦ ሒዶ ፈርዖንን ፣ እህል ስጠን ፤ ወይ እህል ፣ ወይ እህል አለው ፤

፶፭፤ ወይቤሎሙ ሑሩ ኀበ ዮሴፍ ወዘይቤለክሙ ውእቱ ፣ ግበሩ ፣

ፈርዖንም ወደ ዮሴፍ ሒዱ ችሁ ዮሴፍ የነገራችሁን ነገር አድርጉ አላቸው ፤

፶፮፡ ወረኃብሰ በጽሐ ውስተ ኵሉ ገጸ ምድር ወርእዮ ዮሴፍ አርኃወ መዛግብተ እክል ፣ ወሤጠ ለኵሉ ሰብአ ግብጽ ፣

ረኃቡ ግን በግብጽ አገር ሁሉ ታዘዘ ፣ ያን ጊዜ ዮሴፍ ይኸንን ነገር አይቶ ፣ ሪቅ ፣ ጐተራውን ከፍቶ ለግብጽ ሰዎች ሁሉ እየሰፈረ እየሰፈረ ፤ እህሉን ሸጠላቸው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፶፯፤ ወመጽኡ ኵሉ በሐውርት ውስተ ግብጽ ከመ ይሣየጡ እክለ እምነበ ዮሴፍ በእንተ ረኃብ እስመ ዐቢይ ረኃብ ኮነ ውስተ ኵሉ ብሔር ፤

በሀገሩ ሁሉ ጽኑ ረኃብ ሁኗልና ፤ ጽኑ ረኃብ ስለሆነ ስለ ረኃቡ ጽናት ፤ የግብጽ አገር ሰዎች ሁሉ እህል ሊሸምቱ ዮሴፍ ወዳለበት መጡ ።

## ምዕራፍ ፵ወ፪

### ገባኤ

፩፤ ወሰምዐ ያዕቆብ ከመቦ እክል ዘይሠይጡ በብሔረ ግብፅ ፤

ያዕቆብም በግብጽ የሚሸመት እህል እንዳለ ሰማ ፤ (ሐተታ) ማን ነግሮታል ? ቢሉ ፤ ሸማግሌ ከመንገድ ዳር ፤ ከድንበር መቀመጥ ልማድ ነውና ከዚያ ተቀምጦ ሳለ ፤ ነጋድያን ሸምተው ሲመጡ በግብፅ እህል ተርፏል ሲሉ ሰምቷል ፤ አንድም መልአኩ በግብጽ እህል ተርፏል አሸምተህ ብላ ብሎ ነግሮታል ፤

፪፤ ወይቤሎሙ ለደቂቁ ለምንት ትቴክዙ ፤

ልጆቹንም ከውጭ ሲገባ አንገታቸውን ደፍተው አገኛቸው ፤ ምን ያሳዝናችኋል ፤

ናሁ ሰማዕኩ አነ ከመቦ እክል በብሔረ ግብጽ ፤

እነሆ በግብፅ አገር እህል እንዳለ እኔ አሁን ሰምቻለሁ ፤

ሑሩ እንከ ወተሣየጡ ለነ ከመ ንሕየው ወኢንሙት በረኃብ ፤

እንግዲህስ በረኃብ ከመሞት እንድን ዘንድ ሒዳችሁ እህል ሸምታችሁ አምጡ አላቸው ፤

፫፤ ወወረዱ ፲ቱ አኀዊሁ ለዮሴፍ ከመ ይሣየጡ እክለ እምብሔረ ግብፅ ፤

የዮሴፍም ዐሥሩ ወንድሞቹ ከግብፅ አገር እህል ይሸምቱ ዘንድ ወደ ግብፅ ወረዱ ፤

፬፤ ወለብንያምሰ እኁሁ ለዮሴፍ ኢፈነዎ አቡሁ ምስለ አኃዊሁ እስመ ይቤ ኢይድወየኒ ውእቱሂ ፤

ዋዌው ለዮሴፍ ነው ፤ አባቱ ያዕቆብ የዮሴፍ ወንድም ብንያምን ግን ታሞ እሱም እንደ ዮሴፍ በመንገድ ይሞትብኛል ብሎ ከወንድሞቹ ጋር ወደ ግብፅ አልላከውም ፤

፭፤ ወበጽሑ ደቂቀ እስራኤል ኀበ ዮሴፍ እስመ ዐቢይ ረኃብ ኮነ ውስተ ምድረ ከነዓን ፤

የእስራኤልም ልጆች በከነዓን አውራጃ ረኃብ ጽንቶ ነበርና፤ ነግ ሠልስት ሳይሉ ወዲያው ተነሥተው ሒደው ከዮሴፍ



ዘንድ ደረሱ ፤ (ሐተታ) በሌላው አገር ውሎ ራት መብላት ነበረ፤ በከነዓን ግን ጦም ውሎ ጦም ማደር ሆኖ ነበርና፤ ዐቢይ ረኃብ ኮነ በከነዓን አለ ፤

፮፤ ወዮሴፍሰ መልአክ ውእቱ ለብሔረ ግብጽ ወውእቱ ይሠይጥ እክለ ለኵሉ አሕዛበ ምድር ፤

ዮሴፍ ግን በግብጽ አገር አዛዥ ቢትወደድነት ተሹሞ በግብጽ አውራጃ ላሉ ለአሕዛብ ሁሉ እህል ያሸምት ነበረ ፤

ወሶበ በጽሑ አኀዊሁ ሰገዱ ሎቱ በገጾሙ ውስተ ምድር ፤

የዮሴፍም ወንድሞች ከዮሴፍ ዘንድ በደረሱ ጊዜ በግንባራቸው ከምድር ላይ ወድቀው ሰገዱለት ፤

፯፤ ወሶበ ርእዮሙ ዮሴፍ ለአኀዊሁ አእመሮሙ ወተናገሮሙ እኪተ፤

ዮሴፍም ባያቸው ጊዜ ወንድሞቹ እንደ ሆኑ ዓውቆ ክፉ ቃል ተናገራቸው፤ እኪተ ባለው አጸብጺበ ይላል፤ ጽኑዓ ነገረ፤ እኩየ ነገረ ማለት ነው ፤

ወይቤሎሙ እምአይቴ መጻእክሙ፤

እሊህ የአገሩን መውጫ መግቢያ ሊያዩ የመጡ ጉበኞች ናቸው፤ ያዙዋቸው ብሎ አስይዞ ከወዴት መጥታችኋል ? ብሎ ጠየቃቸው ፤

ወይቤልዎ እምብሔረ ከነዓን ንሣየጥ እክለ ፤

እህል እንሸምት ዘንድ ከከነዓን መጥተናል አሉት ፤

፰፤ ወዮሴፍሰ አእመሮሙ ለአኀዊሁ፤ ወእሙንቱሰ ኢያእመርዎ ፤

ዮሴፍ ወንድሞቹን ዓወቃቸው እንጂ እነሱ አላወቁትም ፤

፱፤ ወተዘከረ ዮሴፍ ሕልሞ ዘሐለመ ፤

ያንጊዜም ያለመውን ሕልም አሰበ ፤

ወይቤሎሙ ሰብአ አይን አንትሙ ወመጻእክሙ ትርአዩ ግዕዘ ብሔር፤

የአገሩን አኳኋን ማለት መውጫውን፤ መግቢያውን የቅጽሩን መጥበቁን፤ መላላቱን፤ የሠራዊቱን ማነሱን ፤ መብዛቱን ፤

ሊታዩ የመጣችሁ ናችሁ አላቸው ፤

፲፤ ወይቤልዎ አልቦ እግዚኦ አግብርቲከሰ መጽኡ ይሣየጡ እክለ ፤

አቤቱ እንዲህ አይደለም ፤ ባሮችህስ እህል ልንሸምት መጥተናል እንጂ ፤

፲፩፤ ወኵልነ ደቂቀ አሐዱ ብእሲ ንሕነ ፤ ወኢኮነ ሰብአ አይን አግብርቲከሰ ፤

አቤቱ እንዲህ አይደለም፤ ባሮችህስ እህል ልንሸምት እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

ሰላዮችም አይደለንም ፤ በዚያ ውም ላይ ሁላችንም የአንድ ሽማግሌ ልጆች ነን ፤ (ሐተታ) ሰላይ ከአንድ አገር አንድ ሰው፣ ከአንድ አገር አንድ ሰው ተወ ጣጥቶ ነው እንጂ የሚመጣ ፣ የአንድ ሽማግሌ ልጆች አንድ ሁነን እንለቅ ብለን እንዲህ ሁነን እንመጣለን ? አሉት ፤

፲፪፡ ወይቤሎሙ አልቦ አላ ሰብአ አይን አንትሙ፣ ወመጻእክሙ ታእ ምሩ ግዕዘ ብሔር ፣

የአገሩን አኳኋን ልታዩ የመ ጣችሁ ሰላዮች ናችሁ እንጂ እህል ልትሸምቱ የመጣችሁ አይ ደላችሁም፤ በዚያውስ ላይ አንድ ሰው እንዲህ አስተካክሎ እያን ዳንዱን ዐሥር ልጅ ያደርሳል? አላቸው ፤

፲፫፡ ወይቤልዎ ፲ቱ ወ፪ቱ ንሕነ አግብርቲከ ወአኃው ንሕነ በብሔረ ከነዓን ፣

እኛ ባሮችህስ እንዲያውም በከነዓን ምድር ከአንድ አባት የተወለድን ዐሥራ ሁለት ወን ድማማቾች ነበርን ፤

ወሀሎ አሐዱ ኀበ አቡነ ዘይንዕስ ፣

አንዱ ትንሹ ወንድማችን ከአ ባታችን ዘንድ ቀርቷል ፤

ወካልዑሰ ሞተ ፣

አንዱ ታላቁ ግን ሞቷል አሉት፤

፲፬፡ ወይቤሎሙ በእንተዝ እብለክሙ ሰብአ አይን አንትሙ ፣

ጉበኞች ናችሁ ያልኳችሁ ስለ ዚህ ነገራችሁ ነው ፣ ቀድሞ ዐሥር ፤ አሁን አሥራ ሁለት ነን አላችሁ ፤

፲፭፡ ወበእንተዝ ትትዓወቁ ፣

በዚህ ነገራችሁ ጉበኞች መሆ ናችሁ ትታወቃላችሁ ፤

ሕይወተ ፈርዖን ከመ ኢትወፅኡ እም ዝየ ለእመ ኢየምጻእክምዎ ለእኁ ክሙ ዘይንዕስ ፣

ከአባቱ ዘንድ አለ ያላችሁትን ትንሹን ወንድማችሁን ካላመጣ ችሁት ከዚህ እንዳትወጡ የፈ ርዖን በረከት አይደርብኝ ፤

፲፮፡ ፈንዉ አሐደ እምኔክሙ ወያም ጽኦ ለእኁክሙ ፣

አሁንም ከናንተ አንዱን ልካ ችሁ ወንድማችሁን ያምጣው፤

ወአንትሙሰ ንበሩ እስከ ይትዓወቅ ነገርክሙ ለእመ አማነ ትብሉ፣ ወለ እመ አልቦ ፣

እናንተስ ነገራችሁ እውነትም እንደሆነ ፣ ሐሰትም እንደሆነ እስኪታወቅ ድረስ ከዚህ ተቀ መጡ ፤

ወእመ አኮሰ ሕይወተ ፈርዖን ከመ ሰብአ ዓይን አንትሙ ፣

ይህ ካልሆነ ግን ጉበኞች መሆ ናችሁ ነውና ከዚህ እንዳትወጡ



የፈርዖን በረከት አይደርብኝ አለ ፤

፲፯፡ ወአንበሮሙ ውስተ ቤተ ሞቅሕ እስከ ሠሉስ መዋዕል ፣

ይህን ብሎ እስከ ሦስት ቀን ድረስ በግዞት ቤት አስነበታ ቸው ፤

፲፰፡ ወእምዝ ይቤሎሙ ከመዝ ግበሩ ወተሐይዉ ፣ እስመ አንሰ እፈርሆ ለእግዚአብሔር ፣

ከሦስት ቀን በኋላ እንዲህ አላቸው ፣ እኔ እግዚአብሔርን እፈራዋለሁና ከዚህ ከግዞት ቤት እንዳትሞቱ እንዲህ አድርጉ ፤

፲፱፡ ወእመሰ ስንእ አንትሙ ይንበር ፩ዱ እምኔክሙ ውስተ ሞቅሕ ፣

ስምም ከሆናችሁ ማለት ፣ ሰላዮች ካልሆናችሁ ፣ እህል ልትሸምቱ የመጣችሁ የአንድ ሽማግሌ ልጆች ከሆናችሁ ፣ ከእናንተ አንዱ መያዣ ሁኖ ከግዞት ቤት ይቆይ ፤

ወአንትሙሰ ሑሩ ወሰዱ እክለክሙ ዘተሣየጥክሙ ፣

የቀራችሁት ግን የሸመታችሁ ትን እህል ይዛችሁ ሒዱችሁ ፤

፳፡ ወአምጽኡ ኀቤየ እኅዋክሙ ዘይ ንዕስ ፣

ያንን ታናሽ ወንድማችሁን ወደኔ ይዛችሁት ኑ ፤

ወነአምነክሙ ቃለክሙ ፣

ያንን ታናሽ ወንድማችሁን ያመ ጣችሁት እንደሆነ ነገራችሁን እንቀበላችኋለን ፤

ወእመ አኮሰ ትመውቱ ፣

ይህን ካላደረጋችሁ ግን ትሞ ታላችሁ ፤

ወገበሩ ከማሁ ፣

አሁን እንደ ነገርኳችሁ አድርጉ አላቸው ፤

፳፩፡ ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ አማን በኃጢአትነ ረከበነ ፣

እርስ በርሳቸው እንዲህ ተባ ባሉ ፣ በእውነት በሠራነው ኃጢአት ይህ ሁሉ መከራ አገ ኘን ፤

እስመ ተዓወርነ ሥቃዮ ለእኁነ እንዘ ያስተምህረነ፣ ወኢሰማዕናሁ አሚሁ፣

እስኪ ምን ባደረግሁ ትሸጡ ኛላችሁ ? ትደበድቡኛላችሁ ? እያለ እያለቀሰ ሲነግረን ፣ ወንድማችንን ያን ጊዜ አንሰ ማው ብለን ሳያሳዝነን ቸል ብለ ነዋልና ፤

ወበእንተ ዝንቱ መጽአ ላዕሌነ ዝንቱ ሥቃይ ፣

ስለዚህ ነገር በወንድማችን ግፍ ይህ ሁሉ መከራ መጣብን ተባ ባሉ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፤ ወአውሥአሙ ሮቤል ወይቤሎሙ ኢይቤለክሙኑ ኢተአምጹ ሕፃነ ወኢሰማዕክሙኒ ፤

ሮቤልም አልሰማ አላችሁኝ እንጂ እኔማ ይህን ብላቴና አትበድሉ ብያችሁ አልነበረ ምን ፤

ናሁ ዮም ደሞ ይትኃሠሠክሙ፤

እነሆ ዛሬ ደሙ ሊያጠፋችሁ ይመራመራችኋል አላቸው ፤

፳፫፤ ወእሙንቱሰ ኢያእመሩ ከመ ይሰምዖሙ ዮሴፍ እስመ መተርጕም ሀሎ ማዕከሎሙ ፤

የዕብራይስጥና የግብፅ ቋንቋ የሚያውቅ መተርጕም በመካከላቸው ነበረና ያንጊዜ ግን የለም ነበረና ፤ ዮሴፍ እንዲሰማቸው አላወቁም ነበር ፤ አንድም መተርጕም ዮሴፍ ፤ በመካከላቸው ሳለ ዮሴፍ እንዲሰማቸው አላወቁም ፤

፳፬፤ ወተግኅሠ ዮሴፍ እምኀቤሆሙ ወበከየ ፤

ዮሴፍም እንባ ቢፈላበት ከነሱ ተለይቶ ሒዶ አለቀሰ ፤

ወእምዝ ገብዓ ኀቤሆሙ ወተናገሮሙ፤

ከዚህ በኋላ እንባውን በውሀ ታጥቦ ተመልሶ ወንድሞቹን ተነጋገራቸው ፤ (ሐተታ) ምን ብሎ ተነጋግሯቸዋል ቢሉ ከናንተ አንዱ ይቅርና የቀራችሁት ሒዱ ብሏቸዋል ፤

ወነሥአ ለስምዖን ወአሠሮ በቅድሜሆሙ ፤

ስምዖንን እያዩት በፊታቸው ይዞ አሠረው፤ (ሐተታ) አላሠረውም ብለው ቸል እንዳይሉ፤ ፈጥነው እንዲመጡ ብሎ እያዩት አሠረው፤ ስምዖንን አሥሮ ማስቀረቱ ስለምን ነው ? ቢሉ ፤ አልመከሩብኝም መስሎት ፤ ዮሴፍ ፤ ካንዱም ካንዱም ተጠግቷል ፤ ከስምዖን ቢጠጋ በሰይፍ ጥፊ መትቶት ነበርና ፤ መከራን ይቅመሰው ብሎ፤ ዮሴፍንስ ያህል ሰው እንዲህ ያለ በቀል አያደርግም፤ አፍቅሮ ጸላእት እንዲሆንለት፤ ከእሾህ ከእንቅፋቱ አርፎ ሲበላ ሲጠጣ ይሰንብት ብሎ ነው ፤

፳፭፤ ወአዘዘ ዮሴፍ ያምጽኡ እኅዋሆሙ ፤ ወይደዩ ሎሙ እክለ ፤

ዮሴፍም ዳውላቸውን አቁማዳቸውን አምጥታችሁ እህሉን ቋጥሩላቸው ፤

ወወርቆሙኒ ለለ፩ዱ ይደዩ ውስተ አኅባሊሆሙ ፤

ሊሸምቱበት ያመጡትን ወርቃቸውንም ለእያንዳንዱ በአቁማዳቸው መልሳችሁ እያገባችሁ ቋጥሩላቸው ብሎ ሹሙን አዘዘ ፤

ወከማሁ ገብሩ ፤

እንዳዘዛቸውም አደረጉ ፤



፳፮፤ ወፀዓኑ እክሎሙ ዲበ አዕዱጊሆሙ ፤ ወኃለፉ እምህየ ፤

የሸመቱትን እህላቸውን በወደል ጋዛቸው ላይ ጭነው ከግብፅ ወጥተው ሔዱ ፤

፳፯፤ ወፈትሐ አሐዱ ኃሥሎ በኀበ ኃደሩ ከመ ያውዕእ እክለ ለአዕዱጊሆሙ፤ ወረከበ ዕቁረ ወርቆ ውስተ አፈ ኃሥሉ ፤

ከነዚያ አንዱ ካደሩበት ቦታ ለአህዮቻቸው ገፈራ ለመስጠት አቁማዳውን ቢፈታ፤ ከአቁማዳው አፍ ወርቁን ተቋጥሮ አገኘው ፤

፳፰፤ ወይቤሎሙ ገብዓኒ ሊተሰ ወርቅየ ወናሁ ውስተ አፈ ኃሥልየ ረከብክዎ ፤

እኔስ የሸመትሁበት ወርቅ ተመለሰልኝ፤ እነሆ በአቁማዳዬ አፍ ተቋጥሮ አገኘሁት አላቸው ፤

ወደንገፆሙ ልቦሙ ፤ ወተሐውኩ በበይናቲሆሙ ፤

ልቡናቸው ደንግጦባቸው እርስ በእርሳቸው ታወኩ ፤

ወይቤሉ ምንተ ረሰየነ እግዚአብሔር ወምንትኑዝ ከመዝ ፤

ይህ ነገር ምንድን ነው ? እግዚአብሔር ለምን እንዲህ አደረገን እያሉ እርስ በርሳቸው ታወኩ ፤

፳፱፤ ወበጽሑ ኀበ ያዕቆብ አቡሆሙ ውስተ ምድረ ከነዓን ፤

ከግብፅ ወደ ከነዓን ተመልሰው ከአባታቸው ከያዕቆብ ዘንድ በደረሱ ጊዜ ፤

ወነገርዎ ኵሎ ዘረከቦሙ ፤

በግብፅ ያገኛቸውን ነገር ሁሉ ነገሩት ፤

፴፤ ወይቤልዎ እኪተ ተናገረነ ብእሲ በአለ ብሔር ወወደየነ ውስተ ቤተ ሞቅሕ፤ ወይቤለነ ከመ ሰብአ ዓይን ንሕነ ለብሔር ፤

አገረ ገዢው ክፉ ነገር ተናገረን፤ ማለት ሰላዮች ናችሁ ብሎ አሥሮ ወደ ግዞት ቤት አገባን፤

፴፩፤ ወንቤሎ ስንዕ ንሕነ ወኢኮነ ሰብአ ዓይን ፤

እኛስ ተስማምተን እህል ልንሸምት መጥተናል እንጂ ሰላዮች አይደለንም ፤

፴፪፤ ወ፲ቱወ፪ቱ አኃው ንሕነ ደቂቀ ፩ዱ ብእሲ ፤

በዚያውም ላይ ዐሥራ ሁለታችንም ከአንድ አባት የተወለድን ወንድማማቾች ነን ፤

ወአሐዱ እምኔነ ሞተ ፤

ከእኛ አንዱ ሞቷል ፤

ወዘይንዕስ ሀሎ ኀበ አቡሁ ውስተ ምድረ ከነዓን ፤

ትንሹም ወንድማችን በአገራችን በከነዓን ከአባቱ ዘንድ ቀርቷል አልነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

፴፫፤ ወይቤለነ ውእቱ ብእሲ በአለ ብሔር ፤

አገረ ገዢውም እንዲህ አለን ፤

በዝንቱ ትትዓወቁ ከመ ስንዕ አን ትሙ፤ አሐደ እምኔክሙ ኅድጉ ዝየ ኀቤየ ፤

ከናንተ አንዱን ከኔ ዘንድ ትታ ችሁ ሒዳችሁ ያንን ወንድማ ችሁን ያመጣችሁ እንደሆነ ከአንድ አባት የተወለዳችሁ ወንድማማች መሆናችሁ በዚህ ይታወቃል፤ ከእናንተ አንዱን ከኔ ዘንድ ተዉት ፤

ወእክለክሙሰ ዘተሣየጥክሙ ንሥኡ ወሑሩ ፤

የሸመታችሁትን እህል ግን ይዛ ችሁ ሒዱ ፤

፴፬፤ ወአምጽእዎ ለእኁክሙ ንኡስ፤

ወንድማችሁንም ይዛችሁ ወደኔ አምጡት ፤

ወአአምር ከመ ስንዕ አንትሙ ወኢ ኮንክሙ ሰብአ ዓይን ፤

እንደዚህ የሆነ እንደሆነ ገብኛ እንዳይደላችሁ በፍቅር የመጣ ችሁ የአንድ ሰው ልጆችም እንደ ሆናችሁ አውቃለሁ ፤

ወአገብኦ እንከ ለክሙ ለእኁክሙኒ፤

ከዚያ በኋላ ወንድማችሁንም እመልስላችኋለሁ ፤

ወትትጌበሩ ውስተ ብሔርነ ፤

ወደ አገራችን እየመጣችሁ ትነ ግዳላችሁ አለን ብለው ነገሩት፤

፴፭፤ ወእምዝ ሶበ ሃጡ አኅሳሊ ሆሙ ረከቡ ኮሎሙ ዕቁረ ወርቆሙ ውስተ አኅሳሊሆሙ ፤

ከዚህ በኋላ አቁማዳቸውን በገ ለበጡ ጊዜ ፤ በአቁማዳቸው ውስጥ የተቋጠረ ወርቃቸውን ሁሉም አገኙ ፤ (ሐተታ) ነጋዴ የሆነ እንደሆን በመንገድ ጭነ ቱም ስንቁም እየራሱ ነው ፤ እሊህ ግን የአንድ ልጆች ናቸ ውና ያንዱን እየበሉ ገፈራ እያ ፈሰሱ ሒደው ከቤታቸው ሲደ ርሱ ፈትተው ቢያዩ ሁሉም ወርቃቸውን አግኝተዋል ፤

ወሶበ ርእዩ ወርቆሙ ፈርሁ እሙ ንቱሂ ወአቡሆሙኒ ፤

ወርቃቸውንም ባዩ ጊዜ በእሳ ቸውም በአባታቸውም ፍርሃት አደረባቸው ፤ (ሐተታ) የስም ያን ዋጋ አድርጎ ሰጥቶን ይሆን ብለው ፤ ያዕቆብም ይሆናል እንጂ ብሎ በሁሉም ፍርሃት አደረባቸው ፤

፴፮፤ ወይቤሎሙ ያዕቆብ ሊተ ዳዕሙ አኅጣእክሙኒ ውሉደ ፤

ያዕቆብም እኔን ብቻ ልጅ አሳ ጣችሁኝ አላቸው ፤



ዮሴፍኒ ኢሀሎ፤ ወስምዖንሂ ኢሀሎ፤ ብንያምሃኒ ትነሥኡኒ ፤

ዮሴፍ ከኔ ጋራ የለ ፤ ስምዖንም የለ ፤ ደግሞ ብንያምን ትወስ ዱብኝ ነውን ?

ላዕሌየ ዳዕሙ ኮነ ኮሉ ዝንቱ ነገር ፤

ይህ ሁሉ መከራ የተደረገ በእኔ ብቻ ነውን ? ወይስ በሌ ላም አለ ? ብሎ አዘነ ፤

፴፯፤ ወይቤሎ ሮቤል ለአቡሁ ክል ኤሆሙ ደቂቅየ ቅትል ለእመ ኢያ ግባዕክዎ ኀቤከ ፤ ወአወፍየንዮ ሊተ ውስተ እዴየ ለወልድከ ወአነ አገ ብኦ ለከ ፤

ሮቤልም አባቱን ልጅህን ለኔ በእጄ ስጠኝ ፤ እኔም መልሼ አመጣልሃለሁ ፤ ባልመልሰው ግን ሁለቱን ልጆቼን ግደላ ቸው አለው ፤ (ሐተታ) ያለ አላዋቂ አነጋገር ስለሆነ እን ዲህ አለ እንጂ ፤ ያዕቆብ የልጅ ልጆቹን የሚገድል ሁኖ አይደለም ፤

፴፰፤ ወይቤሎሙ ኢይወርድ ወል ድየ ምስሌክሙ ፤

ያዕቆብም ምንም ቢሆን ልጄ ብንያም ከናንተ ጋራ ወደ ግብጽ አይወርድም ፤

እስመ እኁሁኒ ሞተ፤ ወውእቱ ባሕ ቲቱ ተርፈ ፤

ወንድሙ ዮሴፍ ሞቶ እሱ ብቻ ቀርቷልና ፤

ለእመቦ ከመ ደወየ ወሞተ በፍኖት እንዘ ተሐውሩ ፤

ስትሔዱ በጐዳና ታሞ ቢሞት፤

ወታወርድዎ ለሲበትየ ውስተ መቃ ብር ፤

በኀዘን ያረጀ ሰውነቴን በኀዘን ላይ ኀዘን ጨምራችሁ ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ አይ ሆንም አላቸው ።

## ምዕራፍ ፵ወ፫

፩፤ ወእምዝ ጸንዓ ረኃብ ውስተ ብሔር ፤

ከዚህ በኋላ በከነዓን አገር ረኃብ ጸና ፤

፪፤ ወሶበ አኅለቁ ተሴስዮ እክል ዘአ ምጽኡ እምብሔረ ግብጽ ፤

ከግብጽ ያመጡትን እህል በል ተው በጨረሱ ጊዜ ፤ (ሐተታ) ተሸምቶ ባቁማዳ ጆሮ የመጣ እህል አይበረክትምና ፤

ወይቤሎሙ አቡሆሙ ሑሩ ካዕበ አምጽኡ ለነ እክለ ተሣይጠክሙ ኅዳጠ ፤

አባታቸው ዳግመኛ ሒዳችሁ ጥቂት እኽል ሸምታችሁ አም ጡልን አላቸው ፤

፫፤ ወይቤሎ ይሁዳ በሰማዕት አስ ምዐ ለነ ውእቱ ብእሲ በዓለ ብሔር፤ ወይቤለነ ኢትሬእዩ እንከ ገጽየ

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወርእዩ እለ ይነብሩ ውስተ ምድረ ከነዓን ውእተ ላሀ በነበ ዓውደ እክል ዘአጣታ ወይቤሉ ከመዝኑ ላሀ ዘግብጽ ዐቢይ ፤

በከነዓን የሚኖሩ ሰዎች በአጣታ እህል አውድማ አጠገብ ይህን ልቅሶ አይተው የግብጽ ልቅሶ እንዲህ ጽኑዕ ነውን ? አሉ ፡፡

ወበእንተዝ ሰመይዎ ስሞ ላሀ ግብጽ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

ስለዚህም ነገር የቦታውን ስም የግብጽ ልቅሶ የተለቀሰበት ቦታ ብለው ጠሩት ፡፡ ይኸውም በዮርዳኖስ ማዶ ያለ ቦታ ነው ፡፡

፲፪፡ ወከመዝ ገብሩ ሎቱ ደቂቁ ፤

ልጆቹ እንዲህ አደረጉለት ፡፡

፲፫፡ ወአግብእዎ ውስተ ምድረ ከነዓን ወቀበርዎ ውስተ በዓት እንተ ተሣየጣ አብርሃም ለመቃብር እም ኤፍሮን ኬጥያዊ እንተ አንፃረ ምንባሬ ፤

ከግብጽ ወደ ከነዓን አውጥተው አብርሃም ይቀመጥበት በነበረ አንፃር ለመቃብር ሊኾን አብርሃም ከኬጥያ ሰው ከኤፍሮን በገዛት ዋሻ ቀበሩት ፡፡

፲፬፡ ወገብዓ ዮሴፍ ውስተ ግብጽ ውእቱ ወኵሎሙ እለ ዓርጉ ምስሌሁ ኅቡረ ይቅብርዎ ለአቡሆሙ ፤

ዮሴፍም አባታቸውን ይቀብሩ ዘንድ ከእሱ ጋራ በአንድነት የወጡትን ሁሉ አስከትሎ ወደ ግብጽ ተመለሰ ፡፡

ወአኃዊሁኒ ፤

ወንድሞቹም ተመለሱ ፡፡

፲፭፡ ወእምዝ ሶበ ርእዩ አኃዊሁ ከመ ሞተ አቡሆሙ ይቤሉ ዮጊ ይዜክር ብነ ዮሴፍ እኪተ እንተ ገበርነ ላዕሌሁ ወያገብእ ለነ ፍዳሃ ለኵላ እኪት እንተ አርአይናሁ ፤

ከዚህ በኋላ ወንድሞቹ አባታቸው እንደ ሞተ በአዩ ጊዜ ፡፡ ወይም እንጂ ዮሴፍ በእሱ ላይ ያደረግነውን መከራ አስቦ ያሳየነውን የመከራ ሁሉ ብድራት በእኛ ይመልስብን ይሆናል ብለው ፡፡

፲፮፡ ወመጽኡ ኀበ ዮሴፍ እንዊሁ ወይቤልዎ ፤ አቡከ አምሐለ አምሐለነ ዘእንበለ ይሙት ፤

ወንድሞቹ ከዮሴፍ ዘንድ መጥተው እንዲህ አሉት ፡፡ አባትህ ሳይሞት መሐላን አምሎናል ፡፡

፲፯፡ ወይቤ ከመዝ በልዎ ለዮሴፍ ኅድግ ሎሙ ፤ አበሳሆሙ ወጌጋዮሙ እስመ እኪተ አርአዩከ ፤

መከራ አጽንተውብሃልና፣ በደላቸውን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ብሎሃል ብላችሁ ለዮሴፍ ንገሩት ብሎናል ፡፡



ወይእዜኒ ሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ ለአግብርቲከ በአምላኮሙ ለአበዊከ ፤

አሁንም በአባቶችህ ፈጣሪ የባሮችህን ኃጢአታችንን ይቅር በለን ብለው ነገሩት ፡፡

ወበከየ ዮሴፍ እንዘ ይትናገርዎ ፤

ይህንንም ሲናገሩት ዮሴፍ አለቀሰ ፡፡ እንዲህ ማለታቸው ጠርጥረውኝ ነው ? ብሎ ፡፡

፲፰፡ ወመጽኡ ኀቤሁ ወይቤልዎ ናሁ ንሕነ ኮነ አግብርተ ለከ ፤

ወንድሞቹም ወደ እሱ ቀርበው እነሆ እኛ የአንተ ተገዥች ኾነናል አሉት ፡፡

፲፱፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ኢትፍርሁ፣ እስመ እምእግዚአብሔር ኮነ ፤

ዮሴፍም በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ ነውና አይዟችሁ አትፍሩ አላቸው ፡፡

፳፡ አንትሙሰ መከርክሙ እኪተ ላዕሌየ ፤ ወእግዚአብሔር ባሕቱ መከረ ሠናይተ ላዕሌየ ከመ ይኩን ዮም በዘይሴሰይ ሕዝብ ብዙኅ ፤

እናንተስ በእኔ ላይ ክፉ ምክር መክራችሁ ነበረ፣ እግዚአብሔር ግን ብዙ ወገን በሚመገብ ገንዘብ ዛሬ ይደረግ ዘንድ ለእኔ በጎ ነገርን መከረ እንጂ ፡፡

፳፩፡ ወይቤሎሙ ኢትፍርሁ አነ እሴስየክሙ ወለቤትክሙኒ ፤

አሁንም አይዟችሁ እናንተንም ወገኖቻችሁንም እመግባችኋለሁ አትፍሩ አላቸው ፡፡

ወጸውዖሙ ወተናገሮሙ ዘይበውዕ ውስተ ልቦሙ ፤

ጠርቶ ከልባቸው ጥልቅ ብሎ የሚገባ ነገርን ነገራቸው ፡፡

፳፪፡ ወነበረ ዮሴፍ ውስተ ግብጽ ውእቱ ወአኃዊሁ ወኵሉ ቤተ አቡሁ፣

ዮሴፍም ከወንድሞቹ ጋራ ፤ ከአባቱ ቤተሰቦችም ሁሉ ጋራ በግብጽ ኖረ ፡፡

ወሐይወ ዮሴፍ ፻ተ ወ፲ተ ዓመተ፣

ዮሴፍም መቶ ዐሥር ዘመን ኖረ ፡፡

፳፫፡ ወርእየ ዮሴፍ ደቂቀ ኤፍሬም እስከ ሣልስ ትውልድ ፤

ዮሴፍም የኤፍሬምን ልጆች እስከ ሦስት ትውልድ ድረስ አየ ፡፡

ወደቂቀ ማኪር ወልደ ምናሴ እለ ተወልዱ ላዕለ ሕፅኑ ለዮሴፍ ፤

በዮሴፍ ጉልበት ያደጉ የምናሴ ልጅ ፤ የማኪርን ልጆች አየ ፡፡

፳፬፡ ወይቤሎሙ ዮሴፍ ለአኃዊሁ ፤

ዮሴፍም ወንድሞቹን እንዲህ አላቸው ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

አንሰ እመውት ወእግዚአብሔር ይሔ ውጽክሙ ፤

እኔ እሞታለሁ እግዚአብሔር እናንተን በረድኤት ይጎበኛች ኋል ፤

ወያወፅአክሙ እምዛቲ ምድር ወያበ ውአክሙ ውስተ ምድር ዘመሐለ ለአ በዊነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ፤

ከዚህች አገር አውጥቶ ለአባቶ ቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደማለላቸው አገር ያገባችኋል አላቸው ፤

፳፭፤ ወአምሐሎሙ ዮሴፍ ለደቂቀ እስራኤል ፤ ወይቤሎሙ አመ ይሔ ውጽክሙ እግዚአብሔር አውፅኡ አዕፅምትየ እምዝየ ምስሌክሙ ፤

ዮሴፍም የእስራኤልን ልጆች እግዚአብሔር በረድኤት በጎበ ኛችሁ ጊዜ አጥንቴን ይዛ ችሁ ውጡ እንጂ ከዚህ አት ተዉ ብሎ አማላቸው ፤ አን ድም ለጊዜው ፀአት እንዳላ ቸው ለማጠየቅ ነው ፤ ፍጻሜው ግን ግብጽ የመቃብር ፤ ከነ ዓን የትንሣኤ ፤ ግብጽ የገሃነም፤ ከነዓን የመንግሥተ ሰማይ አም ሳል ናትና፤ (ሐተታ) ያዕቆብም እንዲህ አለ ዮሴፍም እንዲህ አለ፤ ስለምነው ቢሉ፤ አባቶቻ ችን እንዲህ ማለታቸው መው ጣታችንን ቢያውቁ ነው ብለው እንዲነቁ ፤ እንዲተጉ ፤ አን ድም ለማስጸየፍ ፤ አባቶቻችን አጥንታችን ስንኳ ከዚህ አይ ቅር ብለዋል ብለው እንውጣ እንዲሉ ፤

፳፮፤ ወሞተ ዮሴፍ በ፻ት ወ፲ቱ ዓመት ፤

ዮሴፍም በመቶ ዐሥር ዘመኑ ሞተ ፤

ወአምዓዝዎ ወሤምዎ በነፍቅ ውስተ ብሔረ ግብጽ ፤

ሽቱ ቀብተው በሣጥን አድረ ገው በግብጽ አኖሩት ፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘልደት በሰላመ እግ ዚአብሔር ፈጣሬ ኵሉ ፍጥረታት ፤

ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት በፈ ጠረ በእግዚአብሔር አጋዥ ነት ፤ የሥነ ፍጥረትን ነገር የሚናገር ኦሪት ዘልደት ደረሰ ተፈጸመ፤ ወስብሐት ለእግዚአ ብሔር ፤

አነሣሥቶ ለአስጀመረን፤ አተ ጋግቶ ለአስፈጸመን፤ ለእግዚአ ብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፤

## አሜን



## መ ቅ ድ ም

ኦሪት ዘፀአት ዜና ዘፀአት ሲል ነው፤ እስራኤል ከግብፅ መውጣታቸውን የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው፤ መውረዳ ቸውን ተናግሮ ነበርና መው ጣታቸውን ተናገረ፤ ምነው ይህንማ ተናግሮት አልነበረም ስለምን ደገመው ቢሉ፤ ከቆመ በት አያይዞ ተናገረ፤ አንድም በመካከል ነገር እንዳልቀረው ሲያጠይቅ፤ አንድም ለአብር ሃም የነገረው ተስፋ እንዳልቀረ ሲያጠይቅ፤ ዘፍ፤ ፲፭፤ ፲፫-፲፬፤ አንድም ከመ ወጽአ ሲል ነው፤ ሰባ ሆነው ወርደው ይህን ያህል ሁነው ወጡ ለማለት፤ ይህ አርእስት ነው፤ ፫ቱ ፶ት ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፤ እርሱ ግን ነገሩን ዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ብሎ ያመጣዋል።

## ምዕራፍ ፩

የኦሪት ዘፀአት አንደኛው ምዕ ራፍ ይህ ነው፤ አንድም ምዕራፊ አሐዱ ይላል፤ ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት የአንደኛው የኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ ይህ ነው፤ ለሁሉም ምዕራፍ ምዕራፍ አላቸውና አንድም ምዕራፊ አሐዱ አሐዱ ይላል፤ ከስምንቱ ብሔረ ኦሪት የአንዱ የኦሪት ዘፀአት አንደኛው ምዕራፍ ይህ ነው፤ አንድም ምዕራፊ ክልኤቱ አሐዱ ይላል፤ ለኦሪት ዘልደት ሁለተኛ የሚሆን የኦሪት ዘፀአት አንደኛ ምዕራፍ ይህ ነው፤

፩፤ ዝውእቱ አስማቲሆሙ ለደቂቀ እስራኤል እለ ቦኡ ብሔረ ግብጽ ምስለ ያዕቆብ አቡሆሙ ብእሲ ብእሲ ወቤቱ፤

አንዱም አንዱ ወገኑና፤ አንዱም አንዱ ሰው ከአባታቸው ከያዕቆብ ጋራ ወደ ግብጽ አገር የገቡ የእስራኤል ልጆች ስማቸው ይህ ነው፤ ብእሲ ብእሲ ብሎ አንድ አርእስት፤ ወቤቱ ብሎ ሁለት አርእስት ተናገረ፤ ወቤቱ ያለው ደቂቀ እስራኤል ሳለው ነው፤ ብእሲ ብእሲ ያለውን ወደፊት ያመጣል፤

፪፤ ቦኡ ሮቤል ወስምዖን ሌዊ ወይሁዳ፤

ሮቤል ስምዖን ሌዊና ይሁዳ፤

፫፤ ይሳኮር ወዛብሎን ዳን፤

ይሳኮር፤ ዛብሎንና ዳን፤

፬፤ ወንፍታሌም ጋድ ወአሴር ወብንያም፤

ንፍታሌም፤ ጋድ፤ አሴርና ብንያም ናቸው፤

www.ethiopianorthodox.org